# ከምድራዊነታችን ባሻገር

## አራተኛ መጽሐፍ

## መንፈሳዊ ጉዞ - ማስታወሻና ማስተዋያ

# ከምድራዊነታችን ባሻገር

## አራተኛ መጽሐፍ

## መንፈሳዊ ጉዞ - ማስታወሻና ማስተዋያ

መ. ኃ. መስቀል (ዶ/ር)

# ጸሎት

አቤቱ ፈጣሪአችን አምላካችን ቸሩ እግዚአብሔር ሆይ!

የእውር ሰውን ልቦና ባለ አይን ከሚያየው የበለጠ እንዲያይ

ማድረግ የምትችል አንተ ነህና፤

ይህ መጽሐፍ ለአንባብያን የሚጠቅም ሆኖ ይጨረስ ዘንድ፥

ስለአንተ ፈቃድ እለምናለሁ።

አሜን።

Copyright © 2019 by M.H. Meskale (PHD)

መልሶ የማሳተም መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው።

የሽፋን ሥዕል - ውጪ የሚመስል ሰማይ ቤታችን፤ ውስጥ የሚመስል ምድር ውጪአችን (ከቤታችን ወጥተናልና፥ ወደቤታችን እንመለሳለን)።

ከዚህ መጽሐፍ ሽያጭ የሚገኝ ገቢ ሁሉ ለመንፈሳዊ እና ለበጎ አድራጊ ድርጅቶች የሚሰጥ፥ ለድኩማንም መርጃ የሚውል ይሁን።

# መታሰቢያ

ለባለቤቴ እና ለልጆቼ

# ምስጋና

ከሁሉ አስቀድሜ እዚህ ያደረሰኝን ፈጣሪ አምላኬን በከፍተኛ ደረጃ አመሰግነዋለሁ። በእውነት ፍጹምና ኃያል፥ ስሙ ክቡር፥ ለዘለአለምም የተመሰገነ ፈጣሪ አምላካችን የጨለመውን የሚያበራ፥ ቀናውንም መንገድ የሚያሳይ፥ እኔ በእውቀት ሳይሆን፥ በብዙ ዓመታት ጥረትና በጸሎት የተጋሁበትን ሥራ አይቶ እርሱ እንደረዳኝ አምኛለሁ፤ የተማመንኩበት አምላኬ አላሳፈረኝም።

በአካላዊነት የማትታየው ባለቤቴን እና በኑሮዬ ደስ እንዲለኝ የሚያደርጉኝ ልጆቼን በጣም አመሰግናለሁ። ለደገፉኝ ለኔ ዘመዶችና ለባለቤቴ ዘመዶች ከፍተኛ ምስጋና አቀርባለሁ።

በቅርብም ሆነ በሩቅ ሆናችሁ በመንፈስ ላልተለያችሁኝ ወገኖቼ ሁሉ ሙሉ ምስጋናዬን ከመንፈሳዊ ፍቅር ጋር አስተላልፋለሁ።

በከፊልም ሆነ በብዛት መንፈሳዊ ትምህርትን ላስተማሩኝ (ለሰበኩኝ) ኦርቶዶክሶች፥ ካቶሊኮችና ፕሮቴስታንቶች ከፍተኛ ምስጋና አቀርባለሁ። የሁላችንም ሕይወት በምድር ላይ እክል እንዳይበዛበት መንፈሳዊነትን የሚያስተምሩ፥ የሚያጽናኑ፥ የሚመክሩ ሁሉ የተመሰገኑ ናቸው።

በእርማትም ሆነ አስተያየት በመስጠት ለተባበሩኝ ሁሉ፥ በተለይም ለወንድሜ ለአዲስ አለሙ እና ለጓደኛዬ ለተስፋየሱስ መንግሥቱ ከፍተኛ ምስጋና አቀርባለሁ።

በጽሑፎቼ ሁሉ አዎንታዊ አስተያየቶችን የሰጡኝን በሙሉ አመሰግናለሁ። ወደ መጨረሻ ሕትመትም እንዳመራ ያደፋፈረችኝን እና የደገፈችኝን ወይዘሮ ፋናዬ ድጋፌ ማመጫን በጣሙን አመሰግናለሁ።

# የአጻጻፍ መመሪያዎች

ይህ መጽሐፍ ለምሁራኑ እንዲሁም ለሠፊው ሕዝብ ቀላል ምንባብ እንዲሆን የሚከተሉትን የአጻጻፍ መመሪያዎች ተከትሏል፡-

- በተቻለ መጠን አረፍተ ነገሮችን በማሳጠር፥ በቀላል አማርኛ ተዘጋጅቷል።
- ከተጠቀሱት ዋቢ መጻሕፍት ሌላ፥ የድረ ገጽ ምንጮችና ተጨማሪ ማብራሪያዎችን ከግርጌ ማስታወሻዎች (foot notes) ይመለከቷል።
- አንዳንድ ቃላት በትእምርተ ጥቅስ (quotation mark) የታጠሩት፥ አረፍተነገሩ ከሚያመለክተው ውጪ ሌላም ትርጉም ሊሰጠው እንደሚችል በአጽንኦት ለማመልከት ነው። ለምሳሌ፡- በሥጋም በመንፈስም "አንድ" ነን ሲል፥ "አንድ" የሚለው ቃል አንጻራዊ ስለሆነ ለአረፍተነገሩ የተለያየ ፍቺ ይሰጠዋል - ሰውን ሁሉ አንድ ያስመስለዋል - ሳይሆን። የመጽሐፉ ስሜት እንዲጠበቅ ሲባል ነው ትእምርተ ጥቅስ ያስፈለገው።
- አንዳንድ ቃላት በመጥበቅም ሆነ በመላላት ሲነገሩ የተለያየ (አሻሚ) ፍቺ እየሰጡ እንዳያደናግሩ፡- አልፎ አልፎ (እንደየአስፈላጊነቱ፥ አሻሚ ፍቺ እንዳይኖር) አንዳንድ ሆሄዎች ላይ በመጥበቅ መነገር ሲኖርባቸው ከሥራቸው ተሰርዞባቸዋል። ለምሳሌ፥ አ<u>ል</u>ለይህም (ሰረዙ አንድ ሆሄ ላይ ብቻ ነው)፤ አ<u>ይገባ</u>ም (ሰረዙ ሦስት ሆሄዎች ላይ ነው)። ይህ የተደረገው፥ በተለይ አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው ሆኖ፥ ወይንም በውጭ አገር ብዙ ስለቆዩ፥ ወይንም ከዛ ስለተወለዱ፥ የአማርኛን ስነጽሐ#ፍ ምንባብ ላልተለማመዱ አንባቢያን እንዲቀላቸው ለማድረግ ነው እንጂ፥ በዚህ ረገድ የአማርኛን ስነጽሑፍ ለማሻሻል ታስቦ አይደለም።
- ከመደበኛው የአጻጻፍ ዘዴ ወጣ ቢልም፥ ልክ እንደ ንግግር ሆኖ ቀለል ይል ዘንድ፥ ነጠላ ሰርዞች በዛ ብለውበት ይሆናል።
- ብዙሓኑ ሲያነቡት፡- የማውቀውን ቀስቅስ እንጂ አትንገረኝ እንዳይሉ፥ በተቻለ መጠን ጎኃድ የሆኑ ሃሳቦች መጠቀሳቸው ለአንዳንድ የአስተሳሰብ ዘገባዎች የግድ አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር፥ ተወግደዋል።

- የወንድ  ጾታ ብቻ አልፎ አልፎ ቢጠቀስ፥ የሴትን ጾታም በውስጠ ታዋቂነት አብሮ በማጠቃለል ነው።
- በመጽሐፉ ውስጥ የተካተቱ ሃይማኖት ነክ ጉዳዮች፥ ከመንፈሳዊ ይዘታቸው አልፈው፥ የማንንም ሃይማኖት አይመለከቱም።
- የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተጠቀሱት፥ አንዳንድ ሃሳቦችን ለማብራራት ነው እንጂ፥ መጽሐፍ ቅዱስ ከሚያመለክተው መንፈሳዊ ትርጉም ጋር ለማመሳሰል አይደለም፤
- አንዳንድ ፖለቲካዊ  ወይንም ሃይማኖታዊ አመለካከቶች ሲብራሩ፥ የሚያነበው ሁሉ ከራሱ ሃሳብ ርቆ የሚሄድ ባለ አንድ አቅጣጫ አክራሪ ሃሳብ እንዳይጎላበትና እንዳይሰናከል ጥንቃቄ ተደርጓል። ምናልባት በግላጭ ወይንም በድብቅ ወገናዊነት ቢታይባቸው፥ የአንባቢ ይቅርታ ይጠየቃል።
- ይህ መጽሐፍ፥ አንዳንድ እስከ ዛሬ ያልተደረሰባቸውን ፍሬ ሃሳቦች ስለሚያካትት፥ ለወደፊት ትኩረት እንዲሰጣቸው በማሰብ፥ እጅግ በተቃለለ መንገድም ቢሆን፥ ደራሲው የራሱን ነፃ አስተያየት ከመሰንዘር አልተቆጠበም።

# መቅድም

ይህ መጽሐፍ የፍልስፍና ወይንም የሳይንስ መጽሐፍ አይደለም፤ የሃይማኖት ወይንም የልብ ወለድ መጽሐፍም አይደለም። በመንፈሳዊ ቅንዓት የተቀሰቀሰ፥ ከሚታየውና ከሚጨበጠው ወደማይታየውና ወደማይጨበጠው በሃሳብ እየነጠቀ የሚሄድ፥ ከግል ችግሮች በመነሳት፥ አጠቃላይ ምድራዊ ችግሮችንም የሚዳስስ ሁለገብ ነው።

ቀደም ሲል "ከምድራዊነታችን ባሻገር" በሚል አቢይ ርዕስ ሥር የተጻፉትን ሦስት መጽሐፍት በመከተል፥ በተለይም በሦስተኛው መጽሐፍ የተካተቱትን ሳይንሳዊና መንፈሳዊ ሃተታዎች በማጉላት፥ ከሰው ልጅ ምድራዊ ማንነት ጋር፥ ሰማያዊ ማንነቱን፥ በተለያዩ መንገዶች ለመግለጽ የሚሞክርም ነው ይህ መጽሐፍ።

በሦስተኛው መጽሐፍ ውስጥ ሳይንስ ለመንፈሳዊነት (ለማንኛውም ሃይማኖትም ቢሆን) ድጋፍ ቢሆን እንጂ ጠላቱ ሊሆን እንደማይችል ለመግለጽ ሞከርኩ። አሁን ደግሞ፥ በሃይማኖት ውስጥም ሆነ ከሃይማኖት ውጪ፥ ለሁላችንም እውነት የሚሆን እውነት ከሰው ዘንድ ይደበቃል እንጂ አይጠፋም በማለት፥ "መንፈሳዊ ጉዞ" በሚል ርዕስ መጻፍ ጀመርኩ። መቼም ሰው ሲያዝን ወደ መንፈሳዊነት የሚጠጋ መሆኑን አንባቢ እንዲያስተውለውና እንዲማርበት፥ የራሴንም ታሪክ ጣልቃ አስገብቻለሁ - እጅግ እየመጠንኩ።

ከግለሰብ እስከ ህብረተሰብ ድረስ የሥጋን እና የመንፈስን ነገር ከውስጤ ወደ ጽሑፌ ለማምጣት ስታገል አስራ ስምንት ዓመታት ቆጠርኩ። ይሁን። እስከ እርጅና ድረስም ቢሆን - በግርድፉም ቢሆን በደቃቁ - ከማውቀው እኔም ቢሆን ከማላውቀው እኔ - ይኸው ነው እኔ ለአንባቢ የማበረክተው ብዬ እንዳልደፍር፥ እንደ ማንኛውም ሰው ሙሉ በሙሉ በዚች ምድር ለመኖር የሚያበቃ እውቀት እንኳን አጥቼ የተቸገርኩበት ወቅት መኖሩንም ለአንባቢ ግልጽ ማድረግ አስፈልጎኛል። ደካማ መሆኔ ሳያንስ፥ ከድክመቴ የተማርኩበትንም ማሳወቁ፥ ይህንን ጽሑፍ ለየት ሊያደርገው ይችላል።

የመጻሕፍትን የመጻፍ ሥራ ከመጀሬ በፊት፥ "ለመሆኑ እኔስ ማነኝና? ምንስ አውቄ? እንዴትስ ብደፍር?.. እስቲ እራሴን በቅድሚያ ልመርምር...." በማለት

የምድራዊነቴን እና የነፍሴን (የመንፈሴን) ጉዳይ ሳሰላስል፥ "ውስጣዊ ስሜታዊ ውይይት" በሚል ርዕስ ከአንደኛው መጽሐፍ መጨረሺያ እንደ አባሪ አቅርቤዋለሁ።

በዚያ በቀደመው (አንደኛ መጽሐፍ ውስጥ - በአባሪው)፥ እኔ የሥጋ ሰው (ቶማስ) የመንፈስ ሰው የሆነውን እኔን (ዮሐንስን) ሥፈራ ስቸር፥ "ተለይተኸኝ አትሂድ.." ስለው ነበር። እርሱም፡- "አንተ ግን በራስህ የምትንቀሳቀስ ነፍስ ያለህ ቤት ሆነህ፥ እኔም በውስጥህ ብኖር፥ ይህ ለጊዜው መሆኑን አስታውሳለሁ። አንተን ትቼ "እውነተኛው እኔን(?)" ብጠብቅ ምን እንደሚሆን አላወቅሁም።" እያለ፥ ከእኔ ከቶማስ ተለይቶ ለመሄድ ያስፈራራኝ ነበር እኔ ዮሐንስ።

እኔም ቶማስ "...ተስፋ ቆርጬ፥ ጎዶሎነቴ ሲሰማኝ፥ መንፈስ አይራቀኝ፥ መንፈስ አይራቀኝ እያልኩ ስማጸንህ ተገነጥዬ እሄዳለሁ እያልክ ታስፈራራኛለህ፤ ጨኸቴን ስትቀማኝ የኔን ላንተ አደረግህ" እያልኩ ከኔ ተገንጥሎ እንዳይሄድ ስማጸነው ነበር እኔን ዮሐንስን። ተገንጥሎኝ ሊሄድ ፈልጎ ሳለ፥ ግን አልሆነለትምና፤ ይኸው እስከዛሬ ድረስ አብረን ቆየን።

አሁንም በድጋሜ - በዚህ መጽሐፍ ወደ መጨረሻ ላይ፥ ዮሐንስን (እንደ አንድ የመንፈስ ሰው) እና ቶማስን (እንደ አንድ ምድራዊ ሰው) ያሳተፍኳቸው፥ ያንን ከቀድሞውም የተቀሰቀስኩበትን ላለመደበቅ ብዬ ነው። እና፥ በቶማስና በዮሐንስ በኩል የተደረገውን የሃሳቦች ልውውጥ አንባቢያን ከሁለት አቅጣጫ ከሚሰነዘሩ ሃሳቦች መካከል የትኛውን እንከተል ሳትሉ፥ ለራሳችሁ የሚጠቅመውን ብቻ እያሰባችሁ በቀላሉ አንብቡት።

ይህ ነው ሕይወቴ መንፈሳዊነት የሌለበት የሚል ማነው? ለመሆኑ፥ እንቅልፍ ሲወስደንና በሕልም አለም ውስጥ እልም ብለን ስንጠፋ፥ ወደተለየ ሥፍራም ገብተን አካላዊ ትርጉም የማንስጠውንም ስናይ፥ ምንድነው ሙሉ በሙሉ በአንጎላችን ውስጥ የተከናወነውን ነገር የሚገልጸው? የኢሌክትሮ ኬሚካሎች አካላዊ ክንውን ብቻ ነው? ምድራዊም ሰማያዊም ሆነን የተፈጠርን እኛ ተፈጥሮአዊ የመንፈሳዊነታችንን ጣዕም ከሕይወታችን ውስጥ አውጥተን የምንጥል ከሆነ፥ ራሳችንን ከደናል ማለት ነው።

"እኛ ካለ ምንም መንፈሳዊ እውቀት፥ በምድራዊ እይታዎቻችን ብቻ እንኳን ቢሆን፥ በጥልቀቱ ካሰብንበት ሕይወታችን ወደ መንፈሳዊነት ማምራቱ አይቀርም" በማለት፥ አንዳንድ መሠረታዊ ሃይማኖታዊ ጉዳዮችን በመዳሰስ፥ አንዳንድ ፍሬ ሃሳቦችን ለማካፈል የሚቃጣው ነው ይህ መጽሐፍ።

በተለይ በሳይንሳዊ ስነ አመክኖአዊ አመለካከት እያሳበቡ፥ ወይንም በሃይማኖታዊ ግንዛቤ እጥረት ምክንያት፥ የሰዎችን መንፈሳዊ ጠባይ ለምድራዊነት የለወጡ፥ የእግዚአብሔርንም ፈጣሪነት የሚጠራጠሩ፥ በአንዳንድ ሃሳቦች ላይ በጥልቀት እንዲያስቡበት የሚቀሰቅስ ነው ይህ መጽሐፍ።

አዋቂና አላዋቂ በተጻፈና በተነገረ ላይ እና ሊታወቁ በሚችሉ ጉዳዮች ላይ ይመዘናሉ፤ ባልተጻፈና ባልተነገረው እና ሊታወቁ በማይችሉ ጉዳዮች ላይስ፥ ማን ከማን የበለጠ ያውቃል? ለምሳሌ፥ ስለ "ገሃነመ እሳት" ጉዳይ የማን እውቀት ከማን እውቀት ይበልጣል?

የሰው አይምሮ ውሱን እንደመሆኑ መጠን፥ ምድራዊ እውቀትም ውሱን ነው የሚሆን - አካል በሆነ ሁሉ ላይ ውሱንነት አንዱ ጠባዩ ነውና። መንፈሳዊ እውቀት ግን - የሚመነጨው ከሰው አይምሮ ውስጥ - እንዲሁም "ከውጪ" ከሆነ (ከታመነበት) - በአካላዊ ጠባዩ ውስጥ አካላዊ ያልሆነ ጠባይ ስለሚኖረው፥ ውሱንነት የለውምና፤ በአይምሮና "ከአይምሮ ውጪ" በመንፈስ አርቅቀው ለተመለከቱ "ብዙ ነገር" ግልጥልጥ ሊል ይችላል (በምድራዊነታችን ከምናስበው በላይ)።

ስለዚህ፥ በእውነት "ከምድራዊነታችን ባሻገር" የሚታሰበንን (ወርቁን) - መንፈሳዊነታችንን በአጽንኦት እንድናስበው ነው የዚህ መጽሐፍ ዋና አላማ። ይህ መጽሐፍ ምድራዊና ሰማያዊ ከሆነ ውጥንቅጥ ነገር ውስጥ ጥልቅ እያለ - የመንፈሳዊነታችንን ጉዳይ እንድንመራመርበት ወደሚመራን ስነ አመክንዮ ነው የሚሸጋገረው።

እውቀትና ፍልስፍና ጊዜ የሚፈጅ ነው፤ ሲቀርቡት እየራቀ። እስቲ ማን አለ እውቀትን ችሎ የጨበጠ። ከእውቀት ይልቅ ምናባዊነት - ሃሳባዊነት እና ስሜታዊነት የሚበዛበት፥ ቢሆንም፥ ከምታስቡት ሁሉ ጋር፥ ስለ ማንበባችሁ ምስጋና ይግባችሁና፥ ይህንን መጽሐፍ በጥሞና ተመልከቱት፤ ኢትዮጵያችንንም በተመለከተ፥ በአንደኛው መጽሐፍ በምዕራፍ አንድ ለተጠቀሰው የሚከተለው ጥያቄ ከምድራዊነታችን መልሱን ባናገኝ ከመንፈሳዊነታችን ለማግኘት ይቻለን እንደሆነ፥ እያነበባችሁም አስቡበት።

"የረከሰው የሰው ልጅ ጠባይ በገሃድ እየታየ፥ ውሸታምና ከዳተኛ በዝቶ፥ ሰው እርስ በርሱ ሲባላ፥ የማይጠግበውን የሥጋ ከርሱን ሲሞላ፥ ሞራላዊነቱን (መንፈሳዊነቱን) ረስቶ፥ እንስሳዊነቱን ሲያጎላ - ውሸታምነት፥ ራስን ወዳድነት፥ የሥልጣን ጥም፥ ክፋት፥ ውዳሴ ከንቱ፥ ስግብግብነት፥ ትምክህተኛነት፥ እብሪተኛነት፥ አክራሪነትና ጀብደኛነት..፥ ይህ ሁሉ ሕዝቦችን ለመምራት የማይሆን መጥፎ ጠባይ

ከሁሉ ቦታ እየታየ፤ የሰው ልጅ ይህን ሁሉ አስከፊ ጠባያት ተሸክሞ፥ ሠፊውን ሕዝብ በቅንነት የሚያስተዳድር መንግሥት እንዴትና ከወዴት ይገኛል? ዘረኛነት እና አክራሪነት ሳይጠፉ እንዴት ነው ተደማምጦና በጥሞና ተወያይቶ አብሮ መሥራት የሚቻል?”

አንድ ሰው (ማንኛውም ሰው - አዋቂም ሆነ አላዋቂ)፥ ከመሞቱ በፊት፥ ሊሞት ሲል፥ ወይንም ሲሞት፥ አንድ “ትንሽ” እውነት ብልጭ ማለቱ አይቀርም። ምናልባት ይህ የሚያመላክተው፥ ይህ ምድራዊነታችን አንቆ ይዞን ነው እንጂ፥ ፍጹም እውነትን በውስጣችን ይዘናት ነው የምንኖረው። እና፥ በኢትዮጵያችንም ጥሩ የአንድነት አየር ሽው የሚልበት ጊዜ ይመጣል።

ምንም ብንቸገር በአፈጣጠራችን መንፈሳዊነታችንም ስላለ፥ መጽናናትን እና ብርታትን እንደምናገኝ፥ እንደ ምስክር፥ እንደ ማስታወሻና እንደ ማስተዋያም ቢሆንም፥ ይህንን መጽሐፍ እስከ መጨረሻው ድረስ አንብቡት። የእውነትና የፍቅር ምንጭ - የጥሩ ነገር ሁሉ ምንጭ አንድ፥ እርሱም እግዚአብሔር ብቻ ነውና፤ የበለጠውን የሚያሳውቅ፥ አሳውቆም የሚያስደስት መንፈስ ቅዱስን እርሱ እንደሚሰድላችሁ እተማመናለሁ። ሁላችንም ማወቅ የሚገባንን እንድናውቅ የሚያደርግ የእግዚአብሔር መንፈስ ከሁላችን ጋር ይሁን።

<u>የአንደኛው መጽሐፍ ይዘት - ከግለሰብ እስከ አገር - ማስታወሻና ማስተዋያ፡</u>

አባቶች/እናቶች በበኩላችን የሄድንበትን ጎዳና፥ ያሳለፍነውን ክፉውንም ደጉንም ጊዜ ለልጆቻችን እንድናሳውቅ፤ ለሁላችንም ቢሆን እንደ ማስታወሻ፥ እንደ ማስተዋያም እንዲሆን በማሰብ ተዘጋጀ።

ይህ መጽሐፍ በወታደራዊው አገዛዝ (ደርግ) ዘመን፥ ደራሲው በኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) ውስጥ የነበረውን ወቅታዊ አብዮታዊ ተሳትፎ፥ በዚያውም ስለ አገሪቱ የፖለቲካ ሁኔታ እና በኢሕአፓ ውስጥም ስለተፈጠረው ውስጣዊ የፖለቲካዊ ውዝግብ ያወሳል። በመጨረሻም፥ ኢትዮጵያችን ካሁን ቀደም የገጠሟት ችግሮች እንዳይደጋገሙባት በመምከር፥ በነፃነትና በእኩልነት አንድነታችንን እንድንገነባ ያሳስባል።

**<u>የሁለተኛው መጽሐፍ ይዘት - ሁሉም ለአንድነት - ማስታወሻና ማስተዋያ ግጥሞች፡</u>**

"ከምድራዊነታችን ባሻገር" በሚል አቢይ ርዕስ ሥር ከተዘጋጁት ሌሎች መጻሕፍት የተጠቀሱ አንዳንድ "ጠቃሚ" ሃሳቦችን በስእሎችና በግጥሞች ያጠናክራል። ግጥሞቹ የተዘጋጁት በስሜቶች ብቻ የሚገባን ከሚመስለን ጋር መቆየታችንን ለማስታወሻ፥ መሠረታዊ ጥያቄዎቻችንንም ለማሰላሰል እንዲረዳን ሲሆን፥ በአጠቃላይ የግጥሞቹ ይዘት በኢትዮጵያችንም ሆነ በተቀረው አለማችን ውስጥ ግለሰብአዊ፥ ቤተሰብአዊና ሕብረተሰብአዊ ኑሮአችንን ይመለከታል፤ ትኩርት በምድራዊ ኑሮ ብቻ እንዳይሆንም የሰውን መንፈሳዊ ጠባይ አጉልቶ ለማሳየት ይሞክራል።

**<u>የሦስተኛው መጽሐፍ ይዘት - ሳይንስ፥ እምነት፥ ሥልጣኔ፥ ማስታወሻና ማስተዋያ፡</u>**

ምድራችን ከመፈጠሯ በፊትና በኋላ እንዴት እንደነበር ግምታዊ - ሳይንሳዊ ማብራሪያ ያቀርባል። በጂኦሎጂ (ሥነ ምድር) ምርምር ከተገኙ መረጃዎች በመነሳት፥ በምድራችን የተከናወኑትን ተፈጥሮአዊ ክስተቶች - ተፈጥሮአዊ እድገት በአካላዊነቱ ከፍጥረትና ከዝግመተ ለውጥ (evolution) እንዴት ተለይቶ እንደሚታይ ያብራራል። ለአንዳንድ መሠረታዊ ሳይንሳዊ ጥያቄዎችም ጥንቃቄ በተመላበት መንገድ፥ ሃይማኖታዊ (መንፈሳዊ) አስተያየት ያቀርባል። ቀጥሎም ስለ ሰው ዘር አመጣጥ፥ ስለ ስደቶቻችን እና ስለ ቀደሙ ሥልጣኔዎች በማውሳት፥ ስለ መንፈሳዊ አንድነታችን ጉዳይ ያሳስባል። የሁሉም አቅጣጫ ሳይንስ ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርብ እንጂ የሚያርቅ አለመሆኑን ለማስረገጥ ነው።

**<u>ሁሉም ለአንድነት - ድረገጽ፡</u>**

ቀደም ሲል፥ ሁሉም ለአንድነት በሚል መርሆ፥ የሚከተለው ድረገጽ ተዘጋጅቶ አያሌ ግለሰቦች በአለም ዙሪያ ተመልክተውታል። ጽሑፎቹ ሁሉ፥ ከስዕሎቹም ጋር ሆነው "ከምድራዊነታችን ባሻገር" የተሰኘውን አቢይ አርእስት ባይመጥኑት ይቅርታ።

https://www.amharicbooksforunity.org/

መጻሕፍቱን ገዝተው ለማንበብ ያልቻሉ፥ ለግል ጥቅም ብቻ እስከሆነ ድረስ፥ ጽሑፎቹን ብቻ፥ ከዚሁ ድረ ገጽ እያተሙም ቢሆን፥ መጠቀም ይችላሉ።

# ማውጫ


| | | ገጽ |
|---|---|---|
| ምስጋና፡ | | i |
| የአጻጻፍ መመሪያዎች፡ | | ii |
| መቅድም፡ | | iv |
| ማውጫ፡ | | ix |
| መግቢያ፡ | | 1 |
| ምዕራፍ አንድ፡ | መንፈሳዊ ማንነታችን - እንደ መንደርደሪያ፡ | 3 |
| ምዕራፍ ሁለት፡ | የፍቅር በረከት፡ | 15 |
| ምዕራፍ ሦስት፡ | ግፊት - ወደ ሃይማኖት፡ | 35 |
| ምዕራፍ አራት፡ | የሃይማኖት ተክል - በኢትዮጵያ፡ | 43 |
| ምዕራፍ አምስት፡ | ሃይማኖቶች - የመንፈስ መስተዋቶች፡ | 61 |
| ምዕራፍ ስድስት፡ | በአንድ አለም ሁለት አለም፡ | 137 |
| ምዕራፍ ሰባት፡ | እውቀት ወይንስ ጥበብ፡ | 171 |
| ምዕራፍ ስምንት፡ | ፍቅር መንፈሳዊነትን ይቀሰቅስ፡ | 211 |
| ምዕራፍ ዘጠኝ፡ | የማንነት ግንዛቤ - ከቶማስና ከዮሐንስ ፡ | 217 |
| ምዕራፍ አስር፡ | ሰማያዊ ተስፋ - ከጥፋትና ከኃጢአት ባሻገር፡ | 241 |
| ምዕራፍ አስራ አንድ፡ | አንድነት - የሥጋና የመንፈስ ውህደት፡ | 261 |
| አባሪዎች፡ | | 271 |
| አባሪዎች - ደብዳቤ፥ መንፈሳዊ መዝሙሮች፥ ጸሎታት፡ | | |
| ዋቢ መጻሕፍት (ለአራቱም መጻሕፍት)፡ | | 287 |

# መግቢያ

በምድራዊ ሥልጣኔ ብቻ ላይ የሙጥኝ ማለታችን፥ ማንነታችንን እየከደነብን ወዳልተፈለገው አቅጣጫ እየመራን መሆኑን ተገንዝበን፥ ምድራዊ እውቀቶቻችንን ሁሉ በመንፈሳዊ እውቀት መከለሱ ይበጀናል፤ ያ ነውና ለፍቅር፥ ለሰላምና ለደስታ የሚሆን፥ መጨረሻ የሌለው መንፈሳዊ ሥልጣኔ ማለት።

የዘመኑ ምድራዊ ሥልጣኔም እኛን ፍጹም ሰው በማድረግ ፋንታ፥ ወደ ፍጹም አውሬነት እየመራን ያለ ይመስላል - እስከ ዛሬ ያካበትነው ምድራዊ ሥልጣኔ ከሁሉ በላይ ጭካኔን - እርስ በርሳችን መጨራረስን ነው ያሳወቀን። ይልቁንስ፥ መንፈሳዊ ሥልጣኔ ከዘመናችን ምድራዊ ሥልጣኔ እጅጉን የረቀቀ መሆኑን መገንዘብ ግድ ይላል፤ ሁላችንንም የሚያስተሳስረን - ፍቅር፥ ስላም እና አንድነትንም የሚያስገኝልን እርሱ ነውና።

ይህ መጽሐፍ - ከምድራዊ ሥልጣኔ ጎንም ቢሆን፥ መንፈሳዊ ስልጣኔን ብንሻ፥ የማንደርስበት ሥፍራ፥ ፈልገን የማናገኘው ነገር እንደማይኖር በማመን፥ ውስጣዊ ማንነታችንን እየመረመርን (ምድራዊ እይታችንን በመንፈሳዊ እይታ እየቀየርን ወይንም እያከልንበትም ቢሆን)፥ መንፈሳዊ ሥልጣኔን እናሳድግ የሚል ነው።

በምድራችን ውስጥ ያሉ ችግሮች ሰውን የሚያጠቁት በግል (በተናጠል) ብቻ ሳይሆን በጋራም ስለሆነ፥ የጋራ ችግሮቻችን በጋራ (በሕብረት እና በአንድነት) ተመልክተን በጋራ መንፈሶቻችን ብርታት የማንወጣው ችግር አይኖርም። ስለዚህ፥ ወደድንም ጠላንም፥ ለሰላማዊ ኑሮ፥ ለጋራ ጥቅምና ብልጽግና አብረን በምናስበው ላይ መንፈሳዊነታችን ታላቅ ተጽንኦ ይኖረዋል። እና፥ ለምድራችን ልማት፥ ለሕዝቦች ደህንነት - ለመጻኢ እድል ፈንታችንም የተሻለ ስለሚሆን፥ የመንፈሳዊነታችንን ተፈጥሮአዊ ጠባይ በትምህርት፥ በአስተሳሰብ፥ በምርምር እና በጸሎት ብዛት እንድናጎላው የሚያደፋፍር ነው ይህ መጽሐፍ።

የጋራ እውቀትን በማዳበር ሳቢያ - ያቺን እውነት በግልጽ ለማየትና ለማሳየት ስንሞክር ሃይማኖትን ፈጠርን፤ የሁላችንንም እውነት ባንድላይ ለማምጣትና በጋራ እውነት አብሮ ለመራመድ ስለፈለግን ደግሞ - በተለያዩ ማህረሰቦች ውስጥ ተጠቃለን፥ እያንዳንዳችን በየማህበረሰባችን ውስጥ የተለያዩ ሃይማኖቶችን መሠረትን። ሁለንተናዊ እውነት ሊገለጽ በማይችልበት በምድራችን ውስጥ ማድረግ የምንችለውን ሁሉ

ማድረጋችን ደግ ነው፤ በሃይማኖት ጉዳይ መከራከር ግን ሞኝነት ነው - ሃይማኖት የጋራ (የሕብረተሰብ) ነውና። እምነት ግን የግል ነው፤ ሰዎች (ሳይንቲስቶች፥ ፈስፎች፥ ቄሶች፥ ወዘተ.) ከአንድ ወይንም ከተለያዩ ሃይማኖቶች ለየግላቸው እውነት የሚመስላቸውን እየመረጡ፥ ለራሳቸው እምነት ያደርጉታልና።

እኛ ሰዎች ሥጋውያን ብንሆንም፥ በአፈጣጠራችን መንፈሳዊነታችንም ከውስጣችን ስለሚኖር፥ አስተሳሰባችን ወደ ሥጋዊነት ቢያደላም፥ መንፈሳዊው ውስጣዊ ተፈጥሮአችን ከውስጣችን እየቀሰቀሰን፥ ከምድራዊነታችን ውጪ ብዙ ነገር እየታየን፥ ያወቅን እየመሰለንም ቢሆን፥ ብዙ አውርተናል፤ ብዙም ጽፈናል። ካሁን ቀደም አያሌ ሊቃውንት - ፈላስፎችና ሳይንቲስቶች፥ ይህንን አውቀናል ብለው ብዙ አውርተዋል ብዙም ጽፈዋል በከፍታ፤ ከዛ ውስጥ ግን የሰውን ውስጣዊ እውነቱን መረዳት ነው ከባድ የሆነው። ሆኖም፥ የሰውን ውስጣዊ እውነቱን እንጂ የሰውን ሃይማኖታዊ እውቀቱን ለማይከተሉ ሰዎች፥ በሃይማኖቶች ሁሉ ውስጥ የሚገኘውን እውነት ማግኘት አይከብዳቸውም።

እግዚአብሔር የርሱን እውነት ይግለጽልን። አሜን።

መልካም ምንባብ።

# ምዕራፍ አንድ

## መንፈሳዊ ማንነታችን - እንደ መንደርደሪያ

ምድራዊና ሰማያዊ ሂደቶችም የራሳቸው ምክንያቶች ይኖራቸዋል። በእነዚህ ሂደቶች ውስጥ፥ የእኛ ተሳትፎ ምንድነው? ለምንድነው በምድራችን ተደላድለን መኖር ያቃተን? ምንድነው የምድራዊ መንፈሶች ተጽንኦ በኑሮአችን ላይ? የሰው ልጅ ክፉ የሚሆነው፥ ምድራዊ መንፈስ አንቆ ስለሚይዘውና ክፉ ስለሚያሠራው ነው?

እኛ ሁላችንም ምድራዊያን ብቻ ብንሆን ኖሮ፥ ምንም ሳናጉረመርም፥ ጥሩና መጥፎውንም ሳንለይ፥ ተደላድለን እንኖር ነበር። ግን በተፈጥሮአችን የጥሩነት መንፈስ ስላለብን፥ መጥፎውን አይተን በቸልተኝነት ማለፍ አቅቶናል።

በዚህ አለም ላይ ብዙ ክፉና ደግ ነገር እንደሚሠራ፥ የግለሰብም ሕይወት በዚህ አለም ላይ ከሚሠራው ሥራ ሁሉ ጋር እንደሚያያዝ ዝነኛው ኢትዮጵያዊ ሰዓሊ አቶ ገብረ ክርስቶስ ደስታ በአንድ ስዕል ገልጸውታል።

ስዕሉን ከሩቅ ሲመለከቱት የቀለማት ሕብረት በክብ በክብ ሆነው የተቀመጡ ነው የሚመስለው። ቀረብ ብለው ሲመለከቱት ደግሞ፥ በክቦቹ ውስጥ ሰዎች በምድራችን ላይ (በከተማዎች፥ በመንደሮችም) የሚያከናውኑት ክንውን (ከፍቅር እስከ ግድያ) በግልጽ ይታያል።

በስዕሉ ዙሪያ ባለው አውታር (ፍሬም) ላይ አንድ የኢሌክትሪክ ማጥፊያና ማብሪያ ተጣብቆበታል። ጊዜ ከምድራዊ ክንውን ውጪ ሆኖ እንደሚታዘበን ለመግለጽ፥ ነው አውታሩ (ፍሬሙ) ላይ ማጥፊያና ማብሪያ የተጣበቀ።

ማብሪያና ማጥፊያውን ሲነኩት፥ ከአንድ ሴኮንድ ባነሰ ጊዜ ውስጥ መብራት ይበራል፤ ከአንድ ሴኮንድ ባነሰ ጊዜ ውስጥ መብራት ይጠፋል። በዛች ጠባብ ጊዜ ውስጥ በስዕሉ የሚታየው አይነት ጉድ ሁሉ በአለም ዙሪያ ይፈጸማል፤ መብራት እንደሚበራና እንደሚጠፋ ሁሉ፥ ጥሩና መጥፎውም እንዲሁ ይፈራረቃል ማለት ነው።

በምድር የሚሠራው ከጠፈር ጋር ሁሉ ይያያዛል። እግዚአብሔር ሰው የሚሠራውን ሥራ ሁሉ ለረጅም ጊዜ እያየ፥ ከትእግስቱ በላይ ሲሆንበትም እያጠፋን ከዚህ ደረስን።

አንድ ግለሰብ በራሱና ለራሱ (ለሥጋውና ለነፍሱ) የሚበጀውን ሁሉ ቢያደርግ፥ ግን ከራሱ አልፎ ከጎኑ ላለ ሰው እንግዳ ሆኖ ብቻውን ቢቀመጥ፥ ይህ ምን ትርጉም አለው? የመንፈሳዊነት ግቡ ምንድነው? ጥቅሙ ለራስ ብቻ ከሆነ፥ ለሕብረተሰብ፥ ለአገር ለወገንም ካልጠቀመ። ግለሰብ ለራሱ የሚያደርጋቸው ሁሉ አብረውት ይሞታሉ፤ ለሌላው የሚያደርጋቸው ግን ዘለአለማውያን ናቸው።

ስለ ምድራዊ ሕይወታችን በደንብ የሚገባን ልንሞት ስንል ነው? የሰው ልጅ እስከ መጨረሻው እስትንፋሱ ድረስ ለምን ጥሩ ሰው እንዲሆን ይሰበካል? ስለማይገባው ነው? ከሥጋ ሞት በኋላ በሰማያዊ ሕይወቱ እንዲጠቀምበት ነው? እስከ ጊዜ ሞቱ ድረስ ትምህርት ያስፈለገው።

በዚህ በውስብስብ አለም ውስጥ ለአንድ አካሉ ከሚያዝን ይልቅ ለሰብአዊነት የሚያዝን ይበልጣል። ከግላዊነታችን ወደ ህብረተሰባችን (አገራችን - ኢትዮጵያችን - አለማችን) መለስ ማለት እንደሚሻል ከዕዝራ መማር ይቻላል። የዚያን ጊዜም - በዚያ ሥፍራ እንዲህ ሆነ (መጽሐፈ ዕዝራ)፡-

ዕዝራ በምድረ በዳ ገብቶ የእንጨት ፍሬዎችን እየበላ በሚኖርበት ወቅት አንድ የምታለቅስ ሴት በድንገት ብቅ ብላ ታየችው። ይህችም ሴት ልብሷን ቀዳ፥ በራሷም ላይ አመድ ነስንሳ፥ ምርር ብላ ታለቅሳለች። ዕዝራ ወደዚህች ሴትዮ በመጠጋት ለምን እንደምታለቅስ ጠየቃት። ይህችም ሴት - "ጌታዬ፥ በራሴ ላይ በመጣብኝ መከራ አለቅስ ዘንድ አትከልክለኝ። በደረሰብኝ መከራ በልቤ ሃዘን ገብቶኛልና በመከራዬ ልዘንበት ተወኝ...." አለችው።

ዕዝራም "ምን ሆነሻል? እባክሽ ንገሪኝ..." አላት። እርሷም - "እኔ ባርያህ ለሠላሳ ዓመታት ያህል በትዳር ላይ ሳለሁ ልጅ አልወለድኩም ነበር። በመካንነት ስኖር እግዚአብሔር ልጅ እንዲሰጠኝ አጥብቄ ለመንኩት። እርሱም ጸሎቴን ሰምቶና ድካሜን አይቶ ወንድ ልጅ ሰጠኝ፤ በዚህም እኔና ባለቤቴ እጅግ ደስ አለን። ሰው ሁሉ በኛ ደስ ብሎት እግዚአብሔርን እያመሰገን ኖርን። ልጄም ለአቅመ አዳም በደረሰ ጊዜ ሚስት ያገባ ዘንድ ትልቅ ሠርግ ደገስን። ወደ ጫጉላውም በገባ ጊዜ ወድቆ ሞተ። ለፍቼ ያሳደግሁት ልጄ በድንገት ስለሞተብኝ ነው ያዘንኩት።

በልጄ ሞት ሰው ሁሉ በጣም አዘነ፤ እኔም ልቅሶዬን መግታት አልቻልኩም። ሌሊትም በሆነ ጊዜ እኔን ለማረጋጋት ሰዎች አቃታቸው። እኔም ከመላከላቸው ጠፍቼ ወደዚህ ወደ ምድረ በዳ መጥቻለሁ። ከእንግዲህ ወደአገሬ ላልመለስ ቆርጫለሁ። ቀሪ ሕይወቴን በጾም በጸሎት ለማድከም፥ እህል ላልበላ፥ ውሃም ላልጠጣ፥ እስከሞት ድረስ እያለቀስሁ ለመኖር ወስኛለሁ..." አለችው።

ዕዝራም በድንጋጤና በሃዘን ስሜት - “አንቺ ሴት - አንቺ ስለ አንድ ልጅሽ ታለቅሺያለሽ፤ እስቲ እኛን ሁላችንም ተመልከቺን። ያለቁብንን ልጆቻችንን ሁሉ እየቆጠርን፥ የደረሰብንን መከራ ሁሉ ተሸከምን። እስቲ ምድርን ተመልከቻት። እርሷም እንዳንቺ ያፈራቻቸው ልጆቿ ናቸው በያለበት የረገፉት። እስቲ የኢየሩሳሌምን መከራ፥ የቤተ መቅደሳችንንም መፍረስ፥ የዘውዳችንን መውደቅ፥ የታቦተ ጽዮንን መማረክ፥ ይህን ሁሉ አስቢ። ይልቅስ ስለ አንድ እራስሽ ብቻ ብለሽ ምርር ማለቱ ይቅርብሽ።

በእርግጥ፥ የልጅ ሃዘን ከባድ ነው፤ ግን ሰው የማይሞትበት የለምና ተረጋጊ። አሁንም ከዚህ ምድረ በዳ መጥቶ ማዘኑ ይቅርብሽ፤ ወደ አገርሽና ወገኖችሽ ተመለሽ። ከባለቤትሽም ተለይተሽ አትቅሪ። እባክሽ ሂጂ - ተመለሺ - ከቤትሽ ግቢ...” እያለ ይመክራት ጀመር።

ዕዝራ እንዲህ እያለ ለማጽናናት ሲለፈልፍ፥ ለካስ ሴቲተ የእውነት ሴት አልነበረችም! ለካስ ሴቲቱ ምናባዊ ነበረች። ሰቲቱ ተለውጣ በሴት የተመሰለች አገር ሆና ታየችው።

ውጣ ውረድ፥ ሃዘንና ደስታ በሁሉም ያለ ነው። በእርግጥ የግለሰብ ሃዘንም በጊዜ ውስጥ እየተደራረበ ሰውን ከህብረተሰቡ ሊያስወጣው ይችላል። ግለሰብ ከገዛ ህብረተሰቡ ከወጣ እንደ እብድ ይቆጠራል። ነገር ግን አንድ ሃዘንተኛ ለጋራ ችግር የሚያዝን ቢሆን፥ ያ ሰው እንደ ዕዝራ ወደ መንፈስ በመቅረብ ስለጠቅላላ የሕዝቦች ችግር የሚያዝን፥ የሚያስብና የሚጸልይ ይሆናል እንጂ፥ ከህብረተሰቡ ተለይቶ የብቸኛ ሃዘንተኛ ሆኖ አይቀርም። ስለ ሌላው ችግር የሚያስብ፥ የራሱ ችግር ይቃለልለታል።

ከምድራችን ምንጊዜም ጥሩ ውጤት እንደማይገኝ የእግዚአብሔር መልአክ ለዕዝራ ገልጾለታል። መልአኩ - “ለምን ሃዘን ታበዛለህ? ለምንስ ትኩረትህ በምድር ላይ ብቻ ይሆናል? ለምን ሌላኛውን አለም አሻግረህ አታይም ብሎ ዕዝራን መክሮታል። ከምድራዊነታችን ባሻገር ያለውን መመልከት - ከምድር ያጣነውን ከሰማይ የምናገኝበት ተስፋችን መሆኑን ገልጾለታል።

በምድራዊ ሃዘን መዋጥ ራስን ይጎዳል እንጂ አይጠቅምም። ይልቅስ፥ አዎንታዊ ሆኖ ለአገሬና ለዚህች አለም ምን እየሠራሁ ልኑር ማለት ነው የሚሻለው። በአንድ ሰው ሕይወት ውስጥ አያሌ አደጋዎች የሚከሰቱትም በምድራዊነት ላይ ብቻ የሙጥኝ ከማለት ሊሆን ይችላልና፤ ከራስ ወጣ እያሉ ህብረተሰቡን መመልከት ይጠቅማል።

እያንዳንዱ ሰው ከግላዊነቱ እየወጣ፥ ችግሩን፥ ደስታና ሃዘኑን ሕብረተሰብአዊ ቢያደርገው ለሁላችንም የጋራ ቅፍትሔ ለማግኘት ይረዳል።

የሰዎች ስሜት መንፈሳዊ ሲሆን፥ በጋርዮሽም ሲተሳሰር ደስታም ሆነ ሃዘን የጋራ ይሆናል። ሃዘኑም ቢሆን ተስፋና ደስታ አዘል ይሆናል እንጂ፥ ፍጹማዊ ሃዘን አይሆንም።

በማንኛውም ጊዜ (ለክፉም ሆነ ለደግ)፥ ሰዎች እርስ በርስ ሃሳብ ለሃሳብ ሲለዋወጡ፥ ትንሽ - ትንሽ አንዱ ሌላውን ይመስላል። በዚህን ጊዜ ክፋቶችና ደግነቶች ሁሉ ካንዱ ወደ ሌላው ይዛመቱና ሁለት አቢይት ማዕበሎች ይፈጠራሉ።

የክፋት ማዕበሎች ሲደማመሩ ሰው እርስ በርሱ ይጨራረሳል። የደግነትም ማዕበሎች ሲደማመሩ ማሕበራዊ ግንባታ ይሆናል፤ ሁለቱ ተቃራኒ ማዕበሎች ሲደነቃቀፉ ደግሞ፥ ምንም ሳይሠራ እድሜ መፍጀት ብቻ ይሆናል።

ለጊዜው ነው እንጂ ሥጋ አይጠቅምም፤ ምድራዊ ኑሮ ሲያስመርር ብንመለከት እንጂ፥ መንፈሳዊ ኑሮ ጸጸት ሲሆን አላየንም። ከምድራዊነታችን ባሻገር ሰማያዊ እና ዘለአለማዊ አለም ውስጥ የሚከተን፥ ቀድሞ ከእግዚአብሔር የመጣ በኋላም ወደ እርሱው የሚመለሰው ጥሩው መንፈሳችን በምድርም በሰማይም ሕያው ሆኖ ይኖራል።

ታዲያ፥ እስከዛው ድረስ፥ ከመመላለሺያ አለማችን፥ መኖሪያ አገራችን፥ መሰናበቺያ ጊዜአችን፥ ሁሉንም በአይነ ሕሊና እየተመለከትን እናውራ በደስታ። በዚህ አለም የሚሠራው ሥራ ሁሉ (ይህን እና ያን የሚመስለውም ሁሉ) ከግለሰብ እስከ ሕብረተሰብ የሰውን ሕይወት ሲያተራምስ፥ እንዲሁ ዝም ተብሎ የሚታለፍ አይደለም፤ በደምሳሳውም ቢሆን፥ ውስጠ ጠባዩንና ሂደቱን መመልከት ያስፈልጋል።

ቋንቋ የሚያስለጥን - አንደበት የሚከፍት፥

የሚያሳውቅ - የሚያዝናና የሚያጫውት፥

የሚያቀራርብ - የሚያፋቅር፥

ደስታን ከቤት ወደ ቤት - ከአድማስ ወደ አድማስ የሚያዛምት፥

በአለማችን የሚታየው ሁሉ - የሰው ጥሩነቱ ሲከፈት፤

ያምራል ሲገልጡት።

የደስታን ስሜት ለመስረጽ ብልሃቱ ምንድነው?

ምንድነው ሰው ለሰው የሚሰጠው?

የተደበቀው የተፈጥሮ ጸጋ ከማንም ዘንድ ያለው፥

የእግዚአብሔርን ሰላምታ በፈቃዱ የሚለግሰው፥

ቀንም፥ ማታም፥ ፈገግታ የማይለየው፥

ጥሩውን መንፈሱን ከውስጡ የሚያወጣው፥

ትህትናውን በንግግር - በወሬ የሚገልጸው፥
ጣፋጭ የሚሆንለት ቋንቋው - የፈለገውን መግለጽ የሚቻለው፥
ይህቺን አለም ጥሩ መኖሪያ ሥፍራ የሚያደርገው፥
የት ነው ያለው የጥንቱና የወደፊቱ ቀና ሰው።

ከአካላዊ ህልውና - ከምድራዊነት ሌላ - የተለየ - መንፈስ መኖሩን ለመገመት የሚያስችል አይምሮ ተሰጥቶናል። ግን ይኸው አይምሮአችን፡- መንፈስ የሚባል ነገር የለም ብሎ ቢነግረን፥ ያለን ምርጫ ከአይምሮአችን ወጣ ብለን የተቀረውን - ከአይምሮ ጋር የሚነካካውን ኃይል በእምነት፥ በጸሎት እና አርቅቆ በመሄድ (በእውቀትና በፍልስፍና ሳይሆን) ማዳመጥ ነው።

“የጥንቱ የኢትዮጵያ ሥርዓተ ትምህርት (በብዛት) በንባብና በቃል ትምህርት ላይ ያተኮረ - የተቀባይነት እንጂ የመመራመርና የማወቅ ዓላማ ያልነበረው በመሆኑ የመንፈሳዊነታችንን እድገት ሊያፋጥነው ያልቻለ እንደሆነ…” የሚያትቱ ብዙዎች ናቸው[1]። ይህንን ሙሉ በሙሉ ሁላችንም እንቀበለው ዘንድ ያስቸግራል። ሆኖም፥ የኢትዮጵያ ተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታዮች (በብዛትም ባይሆን በከፊል) እምነትን እንጂ ምርምርና እውቀትን ዓላማቸው ስለማያደርጉ በሌሎች ሃይማኖቶች እየተማረኩ እንደሚሄዱ ተመልክተናል።

ከኢትዮጵያውያን ፈላስፎች አንዱ ዘርዓ ያዕቆብ (1592 – 16685) እጅግ ሲፈላሰፍ፥ ከክርስትና እምነት ተገንጥሎ ፈላስፋ ብቻ ሆኖ ቀርቷል።

ዘርዓ ያዕቆብ ጥልቅ በሆነው መንፈሳዊ እውቀቱ፥ ሲያስተምር እና ሲተረጉም “ካቶሊኮች እንዲህ እንዲህ ይላሉ፥ ኦርቶዶክሶች እንዲህ እንዲህ ይላሉ” እያለ “እኛ ጥሩዎች ስንሆን ሁሉም ጥሩ ይሆናል” ማለቱ ከዚህ መጽሐፍ ጋር ይስማማል። ግን እርሱ ከእምነቱ ይልቅ (አይ! ከሃይማኖቱ ይልቅ ማለት ሳይሻል አይቀርም) ምርምርና እውቀትን አስበልጧል።

አያሌ የሃይማኖት መጻሕፍትን አንብበን ለመመራመር ጊዜ የማይኖረን እኛ (ሳይንቲስቶች፥ ሐኪሞች፥ መሃንዲሶች፥ ገበሬዎች፥ አስተማሪዎች፥ ነጋዴዎች….ወ.ዘ.ተ…) በቅድሚያ ስናምን ነው እንጂ ብዙ እውቀት የሚገለጥልን፥ እውቀትን እና ፍልስፍናን እናስቀድም ብንልስ፥ በዚሁ በምድራዊነታችን ተውጠን

[1] “የኢትዮጵያ ፍልስፍና” በሚል ርዕስ - ስለ ዘርዓያዕቆብና ወልደ ሕይወት ሐተታዎች ትንታኔ፥ በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ የፍልስፍና መምህር ከሆኑት ከአቶ ብሩህ ዓለምነህ (2010) ከተጻፈው መጽሐፍ።

እንቀራለን - ለማመንስ አስቀድመን እንወቅ ብንል አንችልም፤ ብዙውን ጊዜአችንን በሳይንስና በመሳሰለው ፈጅተነዋልና (አይደለም እንዴ?)።

ዘርዓ ያዕቆብ የተጻፈን ሁሉ እውነት ወይንም ውሸት መሆኑን ሳትመረምሩ አትቀበሉ ይላል። መልካም ብሏል። ነገር ግን እርሱ በመጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈውን በራሱ እየመረመረ፥ "እግዚአብሐር እንደዚህ ሊያስብ አይችልም - ይህ ከእግዚአብሔር የመጣ ስላልሆነ ውሸት መሆን አለበት" ይላል።

አብዛኛው የዘርዓ ያዕቆብ ስነ አመክንዮ ቀጥተኛ ቢሆንም፥ ደፍሮ "ውሸት ነው - ይህስ ከእግዚአብሔር የመጣ ሊሆን አይችልም.." ከማለቱ አስቀድሞ፥ ያ እርሱ ውሸት ነው ከሚለው ውስጥም ትንሽ እውነት እንደምትኖርና ያቺን እውነት በማጉላት፥ ለሰዎች የሚጠቅመውንና የሚጎዳውን ሰዎች ራሳቸው ለይተው እንዲያውቁ መንገድ ቢከፍት አይሻልም ነበር?

ለምሳሌ - "ከእኔ ይልቅ ወንድ ልጁንና ሴት ልጁን የሚወድድ ለእኔ ሊሆን አይገባውም.." የሚለውን የወንጌሉን ቃል ሲተች፥ ከእኔ (ከእውነት ይለቅ) የሚለውን ለቀቅ አድርጎ፥ ወንድ ልጁንና ሴት ልጁን የሚወድድ በሚለው ላይ በማተኮር፥ "ልጅን ለጽድቅ ብሎ መተው ከዱር አራዊት የከፋ ነው" ይላል። አይ! ከፈላስፋውስ ዘርከፈላስፋው ዘርዓ ያዕቆብ ንጉሡ አፄ ዘርዓ ያዕቆብ ይቀርባል ለዚህ መጽሐፍ።

ከፈላስፋው ዘርዓ ያዕቆብ 200 ዓመታት በፊት የኢትዮጵያ ንጉሥ አፄ ዘርዓ ያዕቆብ ለትክክለኛ ፍርድ እና ለእውነት በመቆም፥ ወንጀለኛው ልጁን በሞት እንዲፈረድበት አድርጓል። ይኸውም እንዲህ ነው -

የንጉሡ አፄ ዘርዓ ያዕቆብ ባለቤት ቅዱስ ቁርባን ስትቀበል፥ ከጸጉሮቿ መካከል አንዷ ጽዋው ውስጥ ጥልቅ ስትል ዲያቆኑ "የጌታዬን ደም!..."ብሎ እጅግ በመሳቀቅ፥ ቶሎ ጸጉሯን አውጥቶ ደሙን ባፉ መጠጠው፥ ጸጉሯንም በጥርሱ እኝክ አድርጎ ዋጠው። ይህንን ያስተውል የነበረ የንጉሡ ልጅ በድርጊቱ እጅግ ተናደደ፤ እርሱም "እንዴት የናቴን ጸጉር!..." ብሎ ዲያቆኑን ገደለው።

የንጉሡ ልጅ ለፍርድ ቀረበ። በሕጉ መሠረት የገደለ መገደል አለበት። ነገር ግን ዳኞኙ በንጉሣቸው ልጅ ላይ ለመፍረድ ስለፈሩ - "በል አንተው ፍረድ..." ብለው ዳኝነቱን ለንጉሡ አስተላለፉለት። ንጉሡም "በሕጉ መሠረት ይፈጸም.." በማለት በገዛ ልጁ ላይ ፈረደበት። የንጉሡ አፄ ዘርዓ ያዕቆብ ልጅ በሞት ትቀጥቶ ሞተ።

ንጉሡ አፄ ዘርዓ ያዕቆብ ይህንን በማድረጉ - ከገዛ ልጁ ይልቅ እውነትን (ትክክለኛ ፍርድን) ማስቀደሙ እርሱንም ትክክለኛ ሰው መሆኑን ያረጋግጣል እንጂ፥ እንደ ዱር አራዊት አያስቆጥረውም። ታዲያ፥ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "ከእኔ ይልቅ ወንድ ልጁንና ሴት ልጁን የሚወድድ ለእኔ ሊሆን አይገባውም.." ማለቱ፥

ከእውነት የሚበልጥ ምንም ነገር እንደሌለ ማስተማሩ 'ማይደል። ይህ የገባው ከፈላስፋው ዘርዓ ያዕቆብ ይልቅ ንጉሡ አፄ ዘርዓ ያዕቆብ ይመስለኛል።

ንጉሡ አፄ ዘርዓ ያዕቆብ ለኢትዮጵያችን ልክ እንደ ቆስጠንጢኖስ የሃይማኖት መሪዎችን በየጊዜው እየተገናኙ እንዲወያዩ ያደረገ፥ የተለያዩ የሃማኖት መጻሕፍትን ከያሉበት በማሰባሰብ፥ ቤተ መጻሕፍትን ያቋቋመ፥ ፍትሃ ነገሥትን እና ተአምረ ማርያምን ከአረብኛ ቋንቋ ያስተረጎመ፥ ግማደ መስቀሉን በግሸን ማርያም ያስቀመጠ፥ ...ባጠቃላይ አፄ ዘርዓ ያዕቆብ ለክርስትና ሃይማኖት በኢትዮጵያችን መስፋፋት ታላቅ አስተዋጽኦ ያደረገ ታላቅ ንጉሥ ነው።

የፈላስፋው የዘርዓ ያዕቆብ ፍልስፍና ግን፥ በብዛት ለምድራዊ ኑሮአችን የሚያመቻች እንጂ፥ ለጥልቅ መንፈሳዊ ኑሮ (ለክርስቲያንነትም ሆነ ለሌላ ሃይማኖት) የሚበጅ አይመስልም። የዘርዓ ያዕቆብ ፍልስፍና - ፍልስፍና በአንድ አቅጣጫ ብቻ ሲረቅና፥ ክርስቲያናዊ እውነቶችን እያደበዘዘ፥ ምድራዊ እውነቶችን የሚያጎላ ይመስላል። ሆኖም ይህ መጽሐፍ "የተጻፈን ሁሉ እውነት ወይንም ውሸት መሆኑን ሳትመረምሩ አትቀበሉ" የሚለውን የፈላስፋውን የዘርዓ ያዕቆብ አባባል የሚደገፍ ነው። እኛም የተነሳሳነው ነገሮችን በቁንጽሉ ሳንመለከት - ሁሉንም በእርጋታ እየመረመርን፥ በአዎንታዊነት ከብዙ ውሸቶች መካከልም ቢሆን ጥቂቷን እውነት ለይተን በማውጣት መንፈሳዊነታችንን እንድናሳድግ ነው እንጂ፥ የምድራዊ ኑሮአችንን ለማበልጸግ አይደለም (ያ በራሱ - በጥሩነታችን የሚመጣ ነውና - ስለ ምድራዊነታችንስ ጉዳይ የዘመኑ ሰው አውቆበታልና ወደዛ አንገባም)።

"በሬ ከአራጁ ጋር ይውላል እንዲሉ"፥ እኛም ስንኖር በጠፈር ሁሉ ከነበረ የመጠፋፋት ክስተት ጋር ነው። መጠፋፋት የነበረና ያለ ስለሆነ፥ ምንጊዜም ከመጠፋፋት እንድንተርፍ - የመቆያ ዘዴዎቻችንን አይምሮአችን ይነግረናል። አጥፊው እንዳይበረታብን መከላከያ ዘዴውንም ከሃይማኖት እንማራለን።

እነሆ! የሰማይ፥ የየብስና የባሕር ሕዋሳት ተፈጥረው ሲበዙና ሲባዙ፥ እኛ ሰዎች ገና አልተፈጠርንም ነበር፤ እኛ በኋላ ተፈጥረን፥ ገና በጨቅላነታችን ግራና ቀኝ ተመልክተን ከተፈጥሮ ብዙ ብዙ ነገር ተማርን።

በመጀመሪያ ከተናካሽ አውሬዎች እየሸሸን ነበር ኑሮአችን፤ ቀስ በቀስ ምድራዊ እውቀታችን ኃይለኞች፥ ጥበበኞችም አደረገንና ከፍጥረታት ሁሉ የበላይ ሆን፤ ግን በምድራዊ ጠባዮቻችን ተለያይተን፥ እርስ በርስ በመፈቃቀር ፋንታ፥ ጠበኞች ሆንና እንጨራረሳለን።

ዳርዊን- "ይህ የሰለጠነው የሰው ዘር ኋላ ቀሩን ከምድር ገጽ አጥፍቶ በራሱ ዘር እንደሚተካው አያጠራጥርም…" ብሎ ነበረ (ከምድራዊነታችን ባሻገር - ከሦስተኛው መጽሐፍ የተዘገበ)። የኔ ዘር ይኑር፤ ሌላው ይጥፋ የሚል የምድራዊነትን ጠባይ ምን አጠፋው?

ይህ የሰለጠነው የሰው ዘር ያልሠለጠነውን - ኋላ ቀሩን - እስካሁን ድረስ ከምድር ገጽ ሳያጠፋ የመቆየቱ ምክንያት፡-

ጥሩ ሆኖ በሰማይ የተፈጠረ፥

ከምድር ሲገባ በጠባዩ ተቀየረ፤

ምድራዊነት - ይህ ሰማያዊ ጠባይን የሚቀይር ነገር፥

ከምድራችን እሳት፥ ውሃ፥ አየርና አፈር ባሻገር፥

ሰይጣናዊ ልባምነት - ሌላው ይሙት፥ እኔ ብቻ ልኑር ማለት፥

ሲተካ አይተነዋል በመንፈሳዊነት - አብሮ በመኖር - በፍቅር በአንድነት።

ምድራዊ ክፋት በአጭሩ ተቀጭቷል፤

ከሰማይ የመጣ ትምህርት አይሎበታል፤

ተመስገን፤ እስካሁን ሳንጠፋ ሰንብተናል።

ይህ የሰለጠነው የሰው ዘር ኋላ ቀሩን ከምድር ገጽ ለማጥፋት ቢያስብም፥ ካሁን በኋላ አይችልም። ካሁን በኋላ ላጥፋ ብሎ ቢነሳ እንዳይሆንለት የሚያደርጉ ብዙ ሁኔታዎች ተዘርግተዋል። እነሆ! በምድራዊነት የማይበገረው የመንፈሳዊነት ጠባይ በውስጣችን ስላለ እና ጠባቂም ስላለን ሳንጠፋፋ ቀረን።

በምድራዊነታችን እርስ በርስ ብንለያይም፥ የሁላችንም መንፈስ ምንጩ አንድ ነውና፤ ማሕበራዊ ኑሮአችን በሃይማኖቶች ውስጥ በሚገኙ እውነቶች (በእምነት) የጸና ሆነልን። ለወደፊት ልዩነቶቻችንን በማጥበብ፥ በስምምነትና በሰላም አብረን እንድንኖር የሚያደርገን ሁኔታ ይፈጠራል የሚል አስተሳሰብ ከአይምሮአችን ቢቀረጽ፥ ይህ አስተሳሰብ በሳይንስ ወይም በሃይማኖት ብቻ የሚመጣ አይደለም፤ በሰው ዘር ያለ የመንፈስ ሥራ (ሕገ ልቦና) ነው እንጂ።

ሳይንስ በሰላምና በፍቅር ተስማምተን እንድንኖር አላስተማረንም። ይህንን የተማርነው ከሃይማኖት ነው። የሰው ልጅ እየተቀራረበ ነው የመጣው። ይህ መቀራረብ ነው የወደፊቱ የሰው ልጅ ዕድል - የመንፈሳዊነታችን ተስፋ - ደግነት - የመቆያ ምሥጢር።

ዛፍና ሳር ከማይበቅልበት ጭው ካለ በረሃ ትንሽ ንፋስ ሽው ቢል፥ አሸዋ ለአሸዋ ይጋፋና፥ ከፍተኛ ድምጽ ይፈጠራል፤ ግን በከተማ ጨኸት የደነዘዘ ጆሮ አይሰማውም። አንድ ሰው ለብቻው ከበረሃ የሚኖር ቢሆን፥ ዝቅተኛ የሆኑ የድምጾችን ሞገዶች ማዳመጥ ከገዛ ኑሮው ጋር ስለሚያዛምደው፥ ጆሮዎቹም ለከተማ ሰው የማይሰሙትን ሁሉ የሚሰሙ ይሆናሉ። ልክ እንደማንነታችን፥ በእኛ የነፃ ፈቃድ የምናርቃቸው ወይንም የምናቀርባቸው ተጻራሪ መንፈሶች አሉብን (አሉልን)።

በጠፈር ውስጥ የሁላችንንም ግንዛቤ የሚያቅፍ ሁለንተናዊ ሃሳብ ቢኖርና፥ አንድ ሰው አንዴ ወደፊት አንዴ ወደኋላ እያለ በሃሳብ ምጥቀት ብዙ ቢመላለስ፥ ከገዛ አይምሮው የሚመነጩ ሃሳቦቹ ከጠፈራዊ ሁለንተናዊ ሃሳብ ጋር አንድ አይነት ግንኙነት ያደርጉ ይሆናል። የዛን ጊዜ ሰው (ግለሰብ) የሚሰማው ስሜት ወደ ጥሩም ሆነ ወደ መጥፎ ቢወስደውም፥ መንፈሳዊ ጆሮዎቹ ከሩቅ የሚያዳምጡ ይሆናሉ - ልክ እንደማንነታችን።

ሰላም፥ ፍቅር እና አንድነትን የምንሻ ብዙዎቻችን በዚህ ውጥንቅጥ አለም ውስጥ በማንኛውም ድርጊቶቻችን የበኩላችንን እየፈጸምን ወደፊት ስንጓዝ፥ ለችሎታችን መገታት እንዳለበት ማወቃችንም ወደ መንፈሳዊነት ይመራናል።

በእውን በሃሳባችን፥ በሕልም እንዲሁም በራዕይ፥ በጠፈር ያለ ሁሉ በአካልም በመንፈስም የሚያያዝ መሆኑን ከተረዳን፥ ሰውም አካላዊ ሆኖ፥ በመንፈሱ ሊበር - በመንፈሱ ሊራመድ - ወደ ሰማይ፥ ወደ ጠፈር ሊገባ ከጠፈር ህያዋን (ሚሻክላውያን) ጋርም ሊቀላቀል ይችላል (ይሆን?)።

"ለትርጉም እንዲያመች" አካላዊ አለም ውስጥ እንደገባንና በመሬት ስበት ከተወስኑ ሥጋውያን ጋር ተጣብቀን እንደቀረን፤ ይህንንም አለም ከነርሱው ጋር ሆነን፥ "ጥርት" ባለ መንገድ (በብርሃን ሞገድ አማካኝነት) እንደተመለከትን፤ መኖራችን ከዚህ አደረሰን። ተመስገን።

በቀጥታም ሆነ በተለየ መንገድ ስለ እግዚአብሔር መኖርና ኃያልነት ለእውነት ስንል እንደመሰከርን ሁሉ፥ ምድራዊ ኑሮአችን በሰማያዊ ተስፋ እየታደሰ፥ ሰላማችንን አግኝተናል። በምድራዊነታችን የጎደለብንን ሁሉ አሟልተን ወደ ፍጹማዊነት የምንጠጋው በግለሰብ ደረጃ ብቻ ሳይሆን፥ በሰብአዊነት (በሕብረተሰብ ታሪክ) ደረጃም እንደሆነ ሁሉ፥ ለሁላችንም አንቀሳቃሽ መንፈስ አለን።

በሳይንስ የተጣበበ አይምሮ፥ አንድ ቀን፥ በስተእርጅናም ቢሆን - "ምድራዊነት የወጣለት እውቀት - መልካም ጥበብ ከወዴት ይገኛል?" ማለቱ አይቀርም። በእርግጥ የሰው ልጅ እድገቱ መታየት ያለበት ከምድራዊነቱ አንጻር ብቻ መሆን የለበትም። ለምሳሌ በብራዚል የአማዞን ጫካ፥ እንዲሁም በሌሎች በአንዳንድ

ሞቃት ሥፍራዎች የሚኖሩ ሰዎች- “ልብስ ምን ይሠራል? ቶሎ ያድፋል፤ ቶሎም ያልቃል፤ እግዚአብሔር የሰጠን ገላችን ይሻለናል” ይላሉ። የእነኚህ ሰዎች መንፈሳዊ እድገት አሁን “በሠለጠነው አለም” በታላላቅ ከተማዎች ውስጥ ከሚኖሩ ሰዎች ጋር ሲወዳደር እጅግ የላቀ ነው። እነርሱ በጋርዮሽ ሲኖሩ ካለ ምንም ቁስ አካላዊ ግን'ኙነት ነው፤ በመንፈሳቸው አንድነትን መሥርተዋል። አዎ! የሰው ልጅ በምድራዊነት እድገቱ ሁሉን ማድረግ ቢችል፥ በመንፈሳዊነቱም የደረሰንበትን እድገት መመርመር ይገባዋል።

ሰው ቢሞት የማይሞተው (የማይሸነፈው) መንፈሱ ስለሚቀር፥ ለዚህ መንፈስ ማደሪያነት የሚያገለግል ምድራዊ አካል ካልኖረለት የግድ ሰማያዊ አካል (ፍጽምተ አካል) መኖር አለበት። የሕያው መንፈስ ዘለአለማዊ የመኖሪያ ሥፍራ አካላዊ አለም ካልሆነ፥ የግድ ሰማያዊ አለም መሆን አለበት።

መንፈሳውያንም ይህንን አካላዊ አለም እርግፍ አድርገው በየቀኑ በሚኖሩት ሕይወት፥ በእጅ የማይዳሰሱ መላእክትን ልክ እንደሚነኩና እንደሚዳሰሱ አድርገው በድርሳናቸው የሚደግሙት ለነርሱ ሰማያዊ አለም “እውን” ስለሆነ ይሆናል፤ ወይንም ሲኒማ ቤት ከመግባት - ትያትር ከማየት - ልብ ወለድ መጻሕፍትን ከማንበብ ይሻለናል ብለውም ይሆናል።

በብርሃነ ሕሊና መጓዝ፤ እራስን በማይታይ አለም ውስጥ መከተት፤ ከመላእክት፥ ከጻድቃንና ከቅዱሳን ጋር ፈጣሪ አምላክን እያመሰገኑ በሰማያዊ አለም መኖርን ከዚሁ ከምድር ሆኖ መለማመድ ይቻላል በማለት፥ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ተከታዮች እንዲህ ያለውን መንፈሳዊ አመለካከት በህብረተሰብአዊ ኑሮአቸው ውስጥ በማካተት ደመቅ ያለ ኑሮ ይኖራሉ።

በምድርም ሆነ በሰማይ ሲመላለሱ የማናያቸው ህያዋን አይጠፉም። እግዚአብሔር ብቻውን አይኖርም፤ እርሱን እንደማናየው ሁሉ፥ ሌሎቹንም መናፍስት አናያቸውም።

ሰው ወደ እግዚአብሔር ሲቀርብ የሚጠጋው ጥሩ መንፈስ አይታጣም። በጻድቃን ትይዩ ኃጢአተኞች፥ አስማተኞችና ጠንቋዮች እንደሚኖሩ ሁሉ፥ ሰው ከእግዚአብሔር ሲርቅም የሚጠጋው መጥፎ መንፈስ ይኖራል፤ ለዚህም ነው በሁለት አለም መካከል ንኪኪ የሚኖር። ታዲያ በሁለቱ መካከል አጣብቂኝ ውስጥ ወድቆ ከመንፈራገጥ ያሚያድነውን የመንፈሳዊነታችንን ነገር እንገንዘብ።

ይህ የሚታየው ሁሉ ይጠፋል፤ የማይታየው ነው ዘለአለማዊው። ታዲያ፥ ከዚሁ ከምናየው ከአካላዊው የተለየ ሌላ አካላዊ ያልሆነ አለም የለም ማለት እግዚአብሔር የለም እንደማለት ይቆጠራል። እግዚአብሔር የለም ስንል ደግሞ ብዙ

ጽንሰ ሃሳቦች ይደመሰሳሉ (ፍልስፍና - እውቀት - ጥበብ - ባለ አንድ አቅጣጫ ይሆኑና ሰይጣናዊ - ክፉዎች ይሆናሉ)።

አንዳንድ ቁልፍ ሃሳቦችን እየሰነዘርን የምንነጋገርባቸው፥ አንዱ ካለ ሌላውም ይኖራል ከሚል ቀጥተኛ ስነአመክኖአዊ አመለካከት በመነሳት ነው። በዚህ ስነአመክኖአዊ አመለካከታችን፥ እስካሁን ድረስ (ከምድራዊነታችን ባሻገር - ከሦስተኛው መጽሐፍ የተዘገበ) ከሳይንስ ድጋፍ እንጂ ቅዋሜ አላጋጠመንም።

በዚህ አለም ላይ (በጠፈርም ቢሆን) ሁሉ ነገር ሊሆንም ላይሆንም እንደሚችል፤ ምንጊዜም የያንዳንዳችን አስተሳሰብ (የኛ ኃይል) በጠፈር ሁሉ እንደሚሳተፍ ሁሉ፤ አንድን ነገር እንዲሆን ወይንም እንዳይሆን የምናደርገው እኛው ራሳችንም ልንሆን እንደምንችልም እናስበው። የእኛ ህልውና የተጠበቀ የሚሆነው ከምድራችን፥ በጠፈር ውስጥም ከሚገኙት ጋር ሁሉ በስምምነት ስንኖር መሆኑን እናስበው ከማይታዩ መላእክት ጋር ለው ያለነው።

በሳይንስ ባዶ የምንለው ጭራሽ ባዶ አለመሆኑን ከተረዳን፥ የመንፈስን ነገር ሳናስበው ማለፍ አይሆንልንም። ስለዚህ - “ሁለት አለማት መኖር አለባቸው፤ አለዚያማ እንዴት ይሆናል?” ብለን ስንጠይቅ ነው ምረምር ውስጥ የምንገባ።

ሰዎች እርስ በርስ ይግባቡ ዘንድ ቋንቋ እንደተሰጣቸው ሁሉ፥ መንፈስ የተባለውም ቃል ሁለት አለማት እንዲተዋወቁ (እንዲገናኙ) የሚያደርግ ሆኖልናል። እስካሁን ድረስ (ለወደፊትም) በአካል የማይገለጸው ሁሉ መኖሩን የሚናገር መንፈስ በሰዎች ሕሊና እየገባ ሃይማኖታችንን እውን አድርጎልናል። ሃይማኖታችንን እውን ስላደረገልን፥ ምድራዊ ኑሮአችን ሰማያዊም እንዲመስል የሚያደርገውም ባህል በውስጡ ተወልዶ አደገ (በተለይ በተዋህዶ ኦርቶዶክስ)።

ይህች ምድር ካለ አንዳች የተወሰነ ምድራዊ የአኗኗር ዘዴ እንድንኖር አትተወንምና፤ ምድራዊ ኑሮን እንድናውቅበት፥ ከዛም አልፈን፥ ከምድራዊነታችን ባሻገር ስለሚወስደን ስለ መንፈሳዊነታችን ጉዳይ መማር እንደሚያስፈልገን ውስጣዊው እኛነታችን ይነግረናል።

በዚች ምድር እውነትን ስንሻ፥ የተለያዩ ችግሮች ያጋጥሙናል። ሰው ሁሉ በሰላም እንዳይኖር የሚያበጣብጥ መንፈስም በምድራዊ አለማችን ሊኖር ስለሚችል፥ ያንንም ለማየት እንሞክር - ወደ ቀድሞው መንፈሳዊ ሥልጣኔ ተመልሰን መንፈሳዊ ጉዞአችንን እንመርምር፤ አገር አመራርና አስተዳደርም በመንፈሳዊነት ሲሆን ጥሩ ውጤት እንደሚያመጣ፥ ከኢትዮጵያችን የእስከዛሬ ታሪክ ማገናዘብ ይቻላል።

ጊዜና አካል የተያያዙ ስለሆኑና ጊዜም የሚጓዘው አካልን ተከትሎ ወደፊት ብቻ ስለሆነ፥ ከአካላዊ ክንውን የወደፊቱን ማወቅ አይቻልም። እንግዲያስ፥

በህልማችንም ቢሆን፥ የነገውን ማወቅ የምንችል እኛ አካላዊ ብቻ አይደለንም። እንግዲያስ፥ የወደፊቱን የተነበዩ ነቢያት አካላዊ ብቻ አልነበሩም።

የብዙ ሰው ትኩረቱ በምድራዊ እውቀቱ ብቻ ላይ ሆነና፥ "ከውጪ" ሆኖ የተፈጥሮን ሂደት መመልከትና ሰውን ከጥፋት ማዳን አልተቻለም። የእሳተ ገሞራ መፈንዳትን፥ የመሬት መንቀጥቀጥን፥ ወዘተ... እየተነበየ የሰውን ልጅ ከእልቂት ያዳነ ምድራዊ አመለካከት (ሳይንስም) የለም።

አይምሮአችን የመንፈስን ነገር ሁሉን አሳውቆ፥ "ይህ ነው ትክክለኛው ሃይማኖትህ፤ እምነትህም ይኸው መሆን አለበት" አይለውም። ግን አይምሮአችን አርፎ ስለማይተኛ፥ ለአንዲት ቅጽበት እንኳን ከፉ ከማሰብ ለመቆጠብ በምንሞክርበት ወቅት፥ ባጠገባችን ብዙ- ብዙ መጥፎ ሥራዎች ሲከናወኑ እናያለን። አለምን በጥሩ ለማየት ስንሻ (አንዳንዶቻችንም ስንታገል)፥ አመለካከታችን መንፈሳዊ ከመሆን ይልቅ በምድራዊነት ላይ ብቻ በማተኮሩ ምክንያት ይደክመናል፥ ያቅተናልም። ደግሞም ከአንዳንድ ሥፍራ ሃይማኖት ለምድራዊነት (ለገንዘብ፥ ለሃብት) ይሰበካል። የሃይማኖት እድገት ከምድራዊነት ወደ መንፈሳዊነት መሆኑ ቀርቶ - ተመልሶ ወደ ምድራዊነት ከሆነ፥ ሰማያዊ ዓላማው ይስታል። አዎ! ከሥጋ የለም ፍጹም እውነት፤ ከምድር ሊገኝ የሚችል አይመስልም ፍጹም ሃይማኖት - መመጻደቂያ እውቀት ያልሆነው ትክክሉ እምነት። አዎ! ዘመን አለፈና፥ ሃይማኖት ከምድራዊነት ጋር ተዳቀለና፤ በዘመናችን ሃይማኖት ካፒታሊስትም እየመሰለ መጥቷል። ታዲያ ምድራዊም ሰማያዊም በሆነ የሰው ሕይወት ላይ የመንፈሳዊነትን ጣዕም ቢያክሉበት፥ ለምድራችን ልማት፥ ለሕዝቦችም ደህንነት - ለመጻኢ እድል ፈንታችንም የተሻለ ሳይሆን አይቀርም። እና፥ ስለ መንፈሳዊነታችን ጉዳይ በጥሞና መነጋገር፥ ማሰብ እና መጻፍ አይቀሬ ስለሆነ፥ ከወዲሁ እንጀምረው በማለት የተጀመረ ይህ ሃተታ ዘርፈ ብዙ ሆነ።

እኔስ፥ "ውስጣዊ ተፈጥሮአዊ ማንነቴ ይምራኝ እንጂ፥ በምድራዊ ማንነቴ በተሸፋፈንኩት እኔ ውሸትን አልሰብክም። መንፈሳዊነትን ለመስበክ በቂ መንፈሳዊ ትምህርት (እውቀት) ባይኖረኝም፥ "እኔስ ብዙ ብዙ ነገር እየታየኝ ዝምታን አልመርጥም" ብዬ በአንድ ልገልጸው በማልችለው የግፊት ኃይል ተነሳስቻለሁ። ያ የግፊት ኃይል ውስጣዊ ማንነት ሊሆን ይችላል፤ ውስጣዊ ማንነት ደግሞ ምድራዊ ካልሆነ፥ መንፈሳዊ (ሰማያዊ) ነው ሊሆን የሚችል። ታዲያ፥ የሰው ልጅ ውስጣዊ ማንነቱ መንፈሳዊ ከሆነ፥ ያንን መንፈሳዊ ማንነት ምን ደበቀው? የሰው ልጅ ከፍጥረቱ ሰማያዊ (መልአካዊ) ሆኖ ሳለ፥ የውጫዊ ማንነቱ እስረኛ ሆኖ በዚች ምድር ይመላለሳል፤ ደስታንም ሲሻ አያገኛትም። አይ ሰው! ለካስ ሰው ማንነቱን ሳያውቅ እንዲሁ ይኖራል።

# ምዕራፍ ሁለት

## የፍቅር በረከት

በኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)[2] በኩል ኮከቤ ከምትባል ቆንጆ ሴት ጋር በፓርቲው ሥራ ተገናኝተን አብረን ስንሠራ ቆይተን፤ ሁለታችንም ታስረን ነበር፤ በኋላም ተፈተን ከፖለቲካ ውጪ የሆነ ኑሮአችንን መግፋት ጀምረናል።

ከእለታት አንድ ቀን፥ ከሥራ ወደ ቤቴ ስሄድ ኮከቤን ከሩቅ አየኋት። እርሷም እንደኔ ከመገደል ተርፋ፥ "ኢሕአፓ ከተመታ፥ ብቻዬን ለአገሬ የማበረክተው ከሌለኝ፥ ምድራዊ ሕይወቴን የተሟላ የሚያደርገው ምንድነው?" እያለች ስታሰላስል ቆይታለች።

አለባበሷ ተለውጧል። እርሷ ብቻ አይደለችም፤ ከአብዮት መልስ የብዙ ወጣቶች አለባበስ ተለውጧል። አብዮቱን የተው መሆናቸው እስኪያስታውቅ ድረስ ጥሩ-ጥሩ ይለብሳሉ (መስሎ ማደር - የመቆያ ምሥጢር)። አብዮቱ የተፋቸው ሆነው ሳለ፥ እነርሱ ግን አብዮቱን ትተው ሌላ ልዩ አለም ውስጥ የገቡ ለማስመሰል የሚጥሩ ይመስላል።-

ከኮከቤ ጋር በኢሕአፓ በኩል በየቀኑ እንገናኝ ነበር። እርሷም ጓዴ - እህቴ ስለነበረች፥ ብወዳትም በጓዳዊነት መንፈስ ብቻ ነበር። ግን ጊዜ ሲለዋወጥ የምንተነፍሰውም አየር እንዲሁ ተለውጦ፥ "ይህች ናትና ሚስትህ ተከተላት..." ብሎ የሚነግረኝን ውስጣዊ ስሜቴን ልገታው አልቻልኩም።

ገና ሳትቀርበኝ ኮከቤ ብዬ ከሩቅ ጠራኋት። ከትግል ጓደኞቼ መካከል የቀረችልኝን እርሷን ለማየት በመቻሌ እጅግ በጣም ደስ አለኝ። ወደርሷም ተጠጋሁና፥ "አንቺ ተረፈ ኢሕአፓ፥ በይ አናግሪኝ፤ ከበላይ አካል የተላለፈ መልእክት.....የሚለውን አይነት የአነጋገር ፈሊጥ ትተሽ..." አልኳት።

ከኮከቤ ጋር ከቀድሞ ለየት ያለ ግንኙነት ጀመርን። ስናገር ታዳምጠኛለች፤ የምናገረውም ቶሎ - ቶሎ ይገባታል። እኔም ስናገር የሚገባውና የምግባባው ሰው በማግኘቴ የደስ ደስ ይሰማኝ ጀመር።

---

[2] ከምድራዊነታችን ባሻገር በአንደኛው መጽሐፍ እንደተጻፈው።

አንድ ሰው ቀለል ያለ ሃሳቡን ሲገልጽ በጥሞና የሚያዳምጠው ካላገኘ በስተቀር፥ ጠለቅ ወዳለው ሃሳቡ ተሻግሮ መናገር ይሳነዋል፥ ግን ሰው በአዎንታዊነት እያዳመጠ፥ አጋር ሃሳቦችንም ሲሰነዝር፥ ጥልቅ በሆኑ ሃሳቦች ላይ በጋራ እያሰቡ መቆየት ይቻላል።

ኮከቤ አስተሳሰቧ ካለ እድሜዋ የረቀቀ፥ አስተዋይ ሴት ናትና፤ ምንጊዜም ሃሳብ ለሃሳብ እንግባባለን። ከአይምሮዬ ያለውን እንጂ ካፌ የሚወጣውን የቃላት መቀነባበር የማትጠብቅ ናት። እኔም ይህን ስለማውቅ፥ ከርሷ ጋር ሳወራ ስነ አይምሮዬ ይዝናናል፤ ንግግሬም ከሃሳቤ ጋር ይሰምርልኛል። ስለዚህም ይመስለኛል፥ ከርሷ ጋር ሳወራ ሥጋዬና መንፈሴ በመዋሃድ አንደበቴ ይከፈትና፥ ካለ ምንም እገታ ጥልቅ ሃሳቦቼን ስገልጽ፥ ንግግሬም ይጣፍጥልኛል።

ኮከቤ የመኖርን ተስፋ፥ የሕይወትን ጣዕም አስረዳችኝ። ኢሕአፓም ባይኖር (ቢያከትም)፥ "ከተቀረው ተንቀሳቃሽ ፍጡር" ጋር እየተተራመሱ መኖር የሚቻለን መሆኑን አስረዳችኝ። በሃሳብ መ<u>በ</u>ተን (በመሸነፍ ስሜት) ምክንያት ያጣሁትን የህልውና ጽንአት ቀስ በቀስ ሳገኘው ይታወቀኝ ጀመር። የኮከቤ ጓደኝነት፥ እኔም እንደ ማንኛውም ሰው፥ በምድር ላይ የመኖር መብቴን የሚያረጋግጥልኝ እየሆነ፥ ካለ ፍርኃትና ስጋት መጠነኛ ሕይወት ሊኖረኝ እንደሚችል ተረዳሁ።

ሕይወት መቀጠል ስላለበት፥ ከብዙ የሃሳቦች መተረማመስ በስተጀርባ፥ ተስፋ የሚሰጠው ልቦናችን ኑሮን ወደፊት እንድንገፋበት አዲስ ምዕራፍ ይከፍትልናል። ግራ ተጋብቶ መዝለቅ አይቻልምና፤ አይምሮ ጠቃሚ ጠቃሚውን ከመምከር አያቋርጥም።

አንድ ግለሰብ በገዛ ሰውነቱ፥
ለድርብ ሕይወት ድፍረቱ፥
"ባጣ ይቆየኝ" ምክንያቱ፥
ራሱን በራሱ ሲሸነግል፥ ብቸኝነትን በመጥላቱ፤
በስሜት አረቄ እንጉርጉሮ ቤቱ፥
ፍዝዝ ያለ ደስታ - ኀምዘዝ ያለ ኑሮ፥ ጭንቀትም ባናቱ።
 ግን፥ ምንድነው ይህ - እንዲህ ያ<u>ለ</u> ሰቀቀን፥
 ለያይቶ ማስቀመጥ ያስቸገረ - አገርና ግለሰብን።
 ባልተረጋጋ ጊዜ፥ በተረበሸ ሕዝብ፥
 ፖለቲካ፥ ሃይማኖት፥ ባህል፥ ልምድ - ሁሉም ድብዝዝ፥

ሶሻሊስት በሚሉት ባይተዋር፥
አገሬን ኢትዮጵያን በማይመጥን፥
ለአገርም ለራስም የማይሆን።
ያለመሞት እድሌ ጭብጥ አድርጎ ያዘኝ፤
እናት ሞልቃቃ ልጇን እንደምታባብል ሲያባብለኝ፥
ሲያጽናናኝ - ሲመክረኝም በብዛት ምድራዊነትን እየጋተኝ....፥
እህ! ....የመኖርን ተስፋ በግድ እንካ ሲለኝ፥
"ብቀል ልጄ፥ ተንቀሳቀስ እንጂ - አትተኛ" እያለ ወተወተኝ።

አንድ ሰው መጥፎነቱ ቢጋነንበት፥ በውስጡም ምንም ጥሩነት እንደሌለው መስሎ ቢሰማው፥ ያ ሰው ሞቱን ያስመኝዋል። እኔም፥ የራሴን መጥፎነት (ደካማነት) ብቻ እያሰብኩ ስኖር፥ ጥሩነቴ ለራሴ ሊታወቀኝ ስለማይችል፥ በዚህ አለም ስለመኖሬ በቂ ምክንያት አጣበት ነበር። አሁን ኮከቤ እኔም በውስጤ ጥሩነት እንዳለኝ ነገረችኝ። ስለራሴ ጥሩነት እንጂ መጥፎነት እንዳይሰማኝ አደረገችኝ። ይህ ነው ጓደኛ ማለት፤ ሰው በራሱ ማንነት እንዳይከፋ የሚያደርግ፤ ጥሩነቱን የሚያጎላለት፥ የበለጠ ጥሩም እንዲሆን የሚያደፋፍር።

"እንዴ! እንዴ! እንዲህ ያለ ቆንጆ ሰው በራሴ ውስጥ አለ ለካስ?..." እያልኩ፥ ቀስ በቀስ "ሰው" የሚሉት አይነት "ሰው" እየሆንኩ መጣሁ። አዳዲስ ሸሚዞችና ሱፍ ኮቶች፥ ጫማዎችም እየገዛዛሁ እራሴን ማሰማመር ጀመርኩ። ለራሴ መድኃኒት የሚሆነኝን - እኔን፥ ጓደኛዬ ከራሴ ውስጥ አውጥታ ሰጠችኝ።

ከኮከቤ ጋር በየቀኑ እየተገናኘን ስናወራ፥ ሰው ለሰው የግድ አስፈላጊ መሆኑ በደንብ ገባኝ። ኮከቤ፥ የሰውን ውስጡን የምታነብ ናትና፤ ውስጤን ወደደችው። እኔም ይህን የመወደድ ጸጋ ሳገኝ ዳግመኛ የተፈጠርኩ መሰለኝና፤ በእጆቼም በልቤም አቀፍኳት።

ዓመታት አለፉ - ስለ ትዳር እያሰብኩ ቆየሁ። በደርግ መንግሥት - ከውጪ "የቀድሞ ኢሕአፓ" ተብሎ፥ በውስጥ በኢሕአፓነት መንፈስ ተጠምዶ፥ በዚህ ባልተረጋጋ ሕብረተሰብ ውስጥ ትዳር ይዞ መኖር ማለት ራስን ወዳድነት - ከዳተኝነት መስሎ ታየኝ፤ ያም ባይሆን፥ የተረጋጋ የትዳር ኑሮ መመሥረት የሚሳካ መስሎ አልታይ አለኝ። ገንዘቡም ተጠራቅሞ ትዳር ሞቅ የሚያደርግ - ቤት የሚገነባ አይመስልም። በሁሉም አቅጣጫ ኑሮ ከባድ መስሎ ይታያል።

ከእስር ተፈቶ ነጻ ለሆነ ሰውም፥ አዲስ ኑሮን መመሥረት የሚቻል መሆኑ ቢገባኝም (ከትንሽ ትንሽ አድር ባይነት ጋር)፥ በስነአይምሮ ተረጋግቶ በነፃነት ለመኖር

ከኢትዮጵያ መውጣት የሚሻል መሰለኝ። ስለዚህ ጉዳይ ኮከቤን ሳማክራት፥ እርሷም እንዲሁ ካገር መውጣት የምትፈልግ መሆኑን ነገረችኝ። የቦታ ርቀት ወይም የጊዜ መርዘም የማያግደው ፍቅር እኔና ኮከቤን ያገናኘናል በማለት ወደ ፈረንጅ አገር ለመሄድ ቆረጥኩ፤ እንዲህም ብዬ ጸለይኩ፡-

"የፈጠርከኝ አምላኬ ሆይ! በማላውቀው ገብቼ አንተን አስቀይሜሃለሁና፤ ይቅር በለኝ። የመኖር እድል የሰጠኸኝ አንተው መሆንክን አሁን ገብቶኛል። እባክህ ከዚች ከኢትዮጵያ ምድር አውጣኝ።

አምላኬ ሆይ! አንተው እራስህ የምትፈልገውና የምትወደውን - የሰው ልጆች በሰላም፥ በፍቅር እና በእኩልነት አብረው የሚኖሩበትን አለም በኔ (በግብረ አበሮቼም) ትግል ማስገኘት አልቻልኩምና፤ ከእንግዲህ በሙሉ ልቤ የፖለቲካ ተሳታፊ አልሆንም።

አምላኬ ሆይ! የሰውን ልጅ ክፋቱ እንጂ ጥሩነቱ ሲገዛው አልታይህ ብሎኛል። እኔ ግን በበኩሌ ጠባዬን አርማለሁ፤ አንተ ከሌለህበት የብቻኛ ትግል ውጤቱ እንደማያምር ተረድቻለሁ። በአስተሳሰቤም - በተለይ ለኢትዮጵያችን - ሰው ብቻውን እንደማይበቃ ገብቶኛል። አገራችንን ኢትዮጵያን አንተ ጠብቃት።

አ! ፈጣሪዬ - አምላኬ፥ ፈቃድህ ከሆነ ሌላ አገር ወስደህ ጣለኝ፤ ከዛም እንድኖር አድርገኝ። ኮከቤንም እባክህ እርዳት፤ ፍላጎቷንም አሟላላት። የተቀረውን ሁሉ አንተው አስተላክለው...።" ብዬ እግዚአብሔርን ብዙ ለመንኩት። እግዚአብሔር ሰማኝ፤ ጸሎቴ ሠመረና ፈረንጅ አገር መጣሁ።

አገሩን ለቆ መሰደድን ማን መረጠው?
እጣ ክፍላችን ይኸው ሆኖ ነው እንጂ፥
በደረስንበት ሁሉ እንግዳ ሰው (stranger) የተባልነው።
የመሬቱን፥ ያፈሩን፥ የድንጋዩን፥ የሳር የቅጠሉን፥
የጫካውን፥ የሸለቆውን፥ የሜዳውን የጋራውን፥
የመንደሩን የከተማውን፥ ከዳር እስከዳር ሁሉን፤
ለምንጊዜም ትዝታዋ የማይለየን የአገራችን፥
ምንጊዜም አይረሳም - በሥጋም በመንፈስም የተወለድንበት ሥፍራችን።

አዬ! እንጃ! ወደንም ሆነ ተገደን! በትውስታ እየተጠመድን፥
እህ! ለገዛ ኑሮአችን ብለን ይሆን?
ኢትዮጵያ ተረጋግታ እንድትቀመጥ ያደረግናት በአይምሮአችን።

ሃሳባውያን ብቻ ሆነን እንደቀረን፥ በይስሙላ በተሸፋፈነ የፈረንጅ አገር ሕይወታችን - ኢትዮጵያን መናፈቅ፥ ያን የመረረ ትግል (ፖለቲካውንና የመሳሰለውን የሰው ልጅ ጭቅጭቅ) ያስታውሳልና፤ አልፎ አልፎ ትዝ ቢልም ወዲያው እንዲረሳ ይደረጋል። ከሰው ለተፈጠረ የማይገባ፥ ብዙ ድርጊት የተፈጸመባት አገር ውስጥ ያደግን እኔና ጓዶቼ (ያሉትም የሄዱትም) - ሳንረሳት የረሳናት መሰልን እንጂ (በዚህ በፈረንጅ አገር ኑሮ!) - ኢትዮጵያ ባጭር ጊዜ ውስጥ እንደምትታይ አይነት ሳይሆን፥ ከዘመን ዘመን ተሻግራ፥ ልዩ ሆና በክብር ከአይምሮአችን ተቀምጣለችና፤ ሳንከዳት የከዳናት መሰልን እንጂ (በዚህ በፈረንጅ አገር ኑሮ!) ኢትዮጵያን (ኤርትራን ጨምሮ) አላጠፋናትም።

ሚስት አግብቶ ለመኖር በቂ ምድራዊ እውቀት ያስፈልጋል። ለኮከብዬ የወደፊቱን እኔን አሰማምሬ ልጠብቃት በማለት፥ በሙያዬ ከፍተኛውን ትምህርት ተምሬ አገባደድኩ። በአውሮፓ ትምህርቴን እንደጨረስሁ ስደተኞች ተረጋግተው ወደሚኖሩበት ወደ አሜሪካ ወይም ወደ ካናዳ ለመምጣት ስል ከጣልያን አገር በስደተኝነት ተመዘገብኩ።

የሰው እድሉ በራሱ ትግል ብቻ ሊመጣ እንደማይችል የተረዳሁት ለተወሰነ ጊዜ በዚሁ በጣሊያን አገር፥ ከአንድ የካቶሊኮች ገዳም ለመኖር የሚያስገድደኝ ሁኔታ በተፈጠረ ጊዜ ነበር። ይህ አገር የማርያም ሃውልትና ስዕል በብዛት የሚታይበት አገር ነው። የእግር መንገደኞች የማርያም ሃውልት ካለበት ሥፍራ ሲደርሱ ያማትባሉ፤ አንዳንዶችም ለጥቂት ደቂቃዎች ቆም እያሉ ትንሽ ጸሎት ያደርሳሉ። ሲበሳጩም፥ “..ምነው እመቤቴ? ምነው!...” ማለት ይቀናቸዋል።

ባትታይም እመቤታችን ማርያምን ልክ አብራቸው እንደምትኖር ደግ እናት እየቆጠሩ፥ በርሷ ይጽናናሉ፥ ደስም ይላቸዋል፥ ተስፋም ያገኛሉ። እየጮሁ ስለሚያወሩ፥ ከውጪ ሲያዩአቸው ቁጡዎች ይመስላሉ። ግን ውስጣቸው በማርያም የርህራሄ መንፈስ የተገራ ስለሆነ፥ ደጎች ናቸው። በዚህ አገር በሴት ልጅ ላይ እጁን የሚሰነዝር ልክ እንደ እንስሳ ይቆጠራል፤ ሴትን የሚማታም ቅጣቱ ከፍተኛ ነው።

በየቀኑ ከማፊያ ጋር የሚጋጩ የዚህ አገር ፖሊሶች ኃይለኞች ናቸው፤ ግን ኢትዮጵያዊ (ኤርትራዊ) ሲያዩ ለሰለስ ይላሉ። ኢትዮጵያኖች ሰብሰብ ብለው ሲያዩ መታወቂያ ወረቀት - ፓስፖርት ይጠይቃሉ። ሕጋዊ የመኖሪያ ፈቃድ የሌላቸውን ወዲያው ከመኪናቸው ያስገቡና ወደ ፖሊስ ጽሕፈት ቤት ይወስዷቸዋል። ከዚያም የቆይታቸውን ምክንያት ይጠይቁአቸውና፥ ስደተኞች መሆናቸውን ካረጋገጡ በኋላ፥ እያንዳንዳቸውን ፎተግራፍ አንስተው፥ የእጆቻቸውንም አሻራ ወስደው፥ የመኖሪያ ፈቃድ (ሴጀርኖ) ከሰጧቸው በኋላ ሰላምታ ሰጥተው ያሰናብቷቸዋል።

የዚህ አገር ሰዎች ወሬ ሲያወሩ እያዳነቁ ነው። ፓፓውን (ያለፈውን ፖፕ ፖልን) በጣም ይወዱታል። ፓፓው እንዳጋጣሚ አንድ የመንደር ቤተ ክርስቲያን ገብቶ የቀደሰ እንደሆነ፥ ያ መንደር ለአንድ ዓመት የሚያወራው ወሬ አገኘ ማለት ነው።

በአገራችን በጣም ትልቅ ክብር የሚሰጣቸው የጦር ክፍሉ አባሎች ናቸው፤ ሁሉም እንደ ማዕረጋቸው። እዚህ ደግሞ ክብር የሚሰጣቸው መንፈሳውያን ናቸው፤ ሁሉም እንደ ማዕረጋቸው። በገዳሙ ውስጥም ልክ እንደ ወታደር ብዙ ስነስርዓት አለ። ለበላይ አለመታዘዝን ለእግዚአብሔር እንዳለመታዘዝ ስለሚቆጥሩት፥ ሁሉም በየምድቡ ተሰማርቶ እንደ ንብ ሲሠራ ይታያል። ለያንዳንዱ ስነ ምግባር የተወሰነ ሰዓት ተሰጥቶታል፤ በጸሎት ሰዓት በጸሎት መትጋት፥ በሥራም ሰዓት ሥራን ማገባደድ የውዴታ ግዴታ ነው።

በመንፈሱ የተወደደ፥ የተፈራና የተከበረ የገዳም አስተዳዳሪ ቢሞት፥ በሕይወቱ ሳለ የሠራው ሥራ ሁሉ ይጻፍለታል። ቅዱስ ተብሎ መጠራት እንደኛ አገር ከባድ ስላልሆነ፥ ቅዱስ ተብሎ እንዲጠራ የገዳማቱ አባላት ሁሉ ብዙ ጥረት ያደርጋሉ።

ይገርማል! ሲያዩአቸው በቁጥር ከሃምሳ አይበልጡም፤ ግን ለተመለከታቸው ኑሮአቸውን ከአንድ ሺህ ጻድቃን እና ቅዱሳን ጋር የመሠረቱ ነው የሚመስለው። በአገራችን የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን አባሎችም ህብረተሰባዊ ኑሮ እንደዚሁ ነው። አዎ! የእኛንም ኑሮአችንን ከጻድቃን - ሙታን ጋር የተቆራኘ የሚያስመስለው፥ እንደ ዝክር፥ ፍትሃት፥ ስም ማስጠራት፥ .. ብዙ ነገር አለ። ጠባቂያችን አንድ እግዚአብሔር ነውና፤ ሁላችንም (እኛ የምንታየውም - እኛ የማንታየውም) በአንድ በተወሰነ መንገድ እንገናኛለን።

አንድ የገዳም አባል በጠና ከታመመ፥ የዘጠኝ ቀን ሱባኤ (እንደኛ ሰባት ቀን መሆኑ ነው) ይገባለታል (በር ተዘግቶ ይጸለያል)።

ከጭንቅላቷ ውስጥ ቱመር አድጎ ከሆስፒታል የገባች አንዲት ማድሬ ፖሎምቦ የተባለች ማድሬ (እናት)፥ ከአንድ ወር በላይ እድሜ የላትም ስለተባለች፥ ጠቅላላ የገዳሙ አባላት የዘጠኝ ቀን ጸሎት አደረጉላት። እርሷም) ከጥቂት ቀናት የሆስፒታል ቆይታ በኋላ ሙሉ ጤንነቷ ተመልሶ (ቱመሩም ጠፍቶ) ፈጽሞ ዳነች። ጸሎት መድኃኒት ሆኖ ፈውስ ሲያመጣ ለማየት በቃን።

ወደ ቀድሞው ነገራችን እንመለስና - መቼም ሰው ካገሩ ሲወጣ ነፍስና ሥጋው እንደሚለይ አይነት ይሆናል። ቅሪት ሃሳቦች ወደ ፍቅር ካልተለወጡ ሰውን ይጎዳሉ። ብዙ የማይታወቁ ሃሳቦች ወደ አይምሮዬ ቢሰርጉም፥ ከመንፈሳዊነት

በስተቀር መልስ የማይገኝላቸው መሆኑን በመገንዘብ፥ በሌሎችም ባልታወቁ ምክንያቶች፥ እኔ ሁሉን ነገር እርግፍ አድርጌ ተውኩና (ከልቤ አንድ ቀን እንኳን ኮከቤን ሳላጠፋ) መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ ጀመርኩ። በዚህን ጊዜ፥ መንፈሳዊው እኔነቴ ከቤተ ክርስቲያን ሥፍራ ይመራኝ ጀመር። የማነበው መጽሐፍ ቅዱስ ከዛ የባይተዋር ትምህርት - ከምድራዊ ፖለቲካ ሁሉ የበለጠ ይጥመኝ ጀመር።

የገዳሙ አባላት “ሰው በማክበርና በትሁት መንፈሳዊ ጠባያችሁ እናንተ ከሌሎች ለየት ብላችሁ ትታዩናላችሁ። ምናልባት እናንተን በተለይ ጥሩዎች ያደረጋችሁ የእናንተ ሃይማኖት ከአኗኗራችሁ ጋር ስለተዋሃደ ሳይሆን አይቀርም። ሃይማኖታችሁን አጥብቅችሁ ያዙ፤ ወደ ምዕራቡ አለም ስትሄዱ ይህን መልካሙን ጠባያችሁን እንዳትለውጡት አደራ - አደራ” እያሉ በየጊዜው ይመክሩናል። አልፎ አልፎም መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምሩናል።

“የኢትዮጵያኖች ሃይማኖት እንደኛው ነው...” ሲሉ አላመንኳቸውም ነበር። በኋላ ግን የኛኑ ጸሎተ ሃይማኖትን ሲደግሙ አመንኳቸው። እነርሱም የአትናቴዎስ እንጂ የአርዮስ ወገኖች እንዳልሁኑ ገባኝ።

በወጣትነት ዘመኔ ከኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሄጄ ስለማላውቅ፥ ክርስቲያን ተብዬ የተጠራሁበት ምክንያቱ እንዴትና ለምን እንደሆነ አልገባኝም ነበር። አሁን ያለኝ ምርጫ፥ ክርስቲያን የተባልኩበትን ምክንያት መርምሮ መረዳት ነው ብዬ፥ ወደ አንድ የምወደው የገዳም ሰው (ወንድም) ተጠጋሁ። እርሱም የገዛ ሃይማኖቴን በደንብ እንዳውቀው እንጂ፥ ችላ ብዬ እንዳላልፈው ይመክረኝ ነበር። ይህ ሰው እኔን እና ሌሎች አምስት ሰዎች እያሰባሰበ በሳምንት አንድ ቀን ለብዙ ሰዓታት ያስተምረን ነበር።

ኮከቤም ከኢትዮጵያ የመውጣትን እድል አግኝታ ናይሮቢ (ኬንያ) ገባች። በደብዳቤ መገናኘቱን አላቋረጥንም ነበርና፤ እኔ ካለሁበት ለመምጣት ወሰነች።

በዚህ ግርግርና ውካታ በሞላበት አለም፥ አካላውያን እርስ በርስ ይጠፋፋሉ (ይረሳሳሉ)፤ ልክ እቃ ጠፍቶ እንደሚቀር ነው። ሆኖም በሰዎች መካከል ያሉ መንፈሳዊ ስሜቶች እንደ አካል ፈጽሞ ጥፍት አይሉም። ጫካና ተራራ፥ ወንዝና ባህር የማይለያየው፤ በአካል የተራራቁትን የሚያቀራርብ - እሩቁን ቅርብ የሚያደርግ መንፈስ አለ - የእውነት ፍቅር ልጆች ይመጣሉ ከሩቅ - ይመጣሉ ከሩቅ። ኮከቤ መጣች። ይህ የኮከቤን እና የእኔን ዕድል የሚመራ የመንፈስ ሥራ ነው ብዬ ቀድሞ የገመትኩት ነገር ነበር። ግን አሁን የማምንበት ሆነ።

መንፈሳዊ የሆነውን የሰው ልጅ ተፈጥሮ፥ በብልጭልጭ አለም የማትለውጥ ያችው ኮከቤ ናት። ተለያይተን ብንቆይም፥ ለብዙ ዓመታት ተጋብተው ከቆዩ በኋላ፥

ተነፋፍቀው እንደተገናኙ ባልና ሚስት መሰልን። በጊዜና በቦታ ተራርቀን ብንቆይም፥ ኮከቤ ያው እርሷ ናት፤ አልተለወጠችም። ኮከቤን ቶሎ ላገባት ከጀልኩ።

ለሰዎች የማይታይ ሞቃት ብርሃን የምታበሪ፥

በምድራዊ ሰማያዊ ፍቅር ሰውን የምታስሪ፥

በሃሳቤ የምትከተዪኝ፥ በዞርኩበት የምትዞሪ፥

ለኔ የንጋት ኮከቤ ነሽ፥ ምንጊዜም ከልቤ ውስጥ የምትኖሪ።

ሰው በፍጥረቱ ብቻውን መሆን ያቅተዋል። ለሰው ምድራዊነት ብቻ አይበቃም፤ ሰማያዊነትም በቀላሉ አይገኝም። ሰው ጎዶሎነት ሲሰማው፥ “የት ልሂድና ማንነቴን ላግኝ? ማነው ማንነቴን የሚያስረዳኝ” ብሎ ይጠይቃል። አዎ! በቶሎ ሚስት ማግባት ይሻላል።[3]

እጅግ የረቀቀ ነው፥ ራስን መፈለግና ሚስት ማግባት፤

ሁለት ሰዎችን አንድ የሚያደርግ ፍቅር ሲሆን እውነት፥

ጠባቂ መንፈስ ከመሃል - ሰው ራሱን እንዳይከፍል ለሁለት።

ባገራችን ውስጥ ጋብቻ ትልቅ ክብር ስላለው፥ የሚጋቡትን ግለሰቦች እነርሱ (ተጋቢዎቹ) ከሚጠብቁት በላይ ህብረተሰቡ ሲያከብራቸው፥ እነሆ በዛች የጋብቻ ሰርግ ዕለት የዘመድ አዝማድ፥ የሰው ሁሉ ደስታና ፍንጠዛ፥ መልካም ምኞት፥ ጸሎትና ምርቃት ሁሉ የሰርገኞቹን የተናጠል ጎዶሎነት ወደ ሙሉነታቸው የሚያሸጋገር ይመስላል (ይሆናል)።

ፍቅር ፍጹማዊ የሆነ ሰማያዊ ጠባዩ በምድር ላይ ሲገለጥ፥ የሰማዩን ደስታ በምድር እንዲያንጸባርቅ፥ በከፍተኛ ጥንቃቄ ሰርግ ተሰርጎ፥ እጅግ ተከብሮና ድምቅ ብሎ ነው። ይገርመኛል፤ መልካም ምድራዊ ስሜት ክቡር ሰማያዊ መሆኑ ነው።[4]

ሰማያዊ ደስታ በሰዎች አካላዊነት ተተርጉሞ ከትውልድ ትውልድ ቢሸጋገር፥ ጋብቻም እንደ አንዱ ሰማያዊ ደስታ ይቆጠር ይሆን?

ሰርገኞቹም እስከ ጋብቻቸው ቀን ድረስ አንድ እራሳቸውን ሆነው ከኖሩበት አለም ወጥተው፥ በሁለትነትና አንድነት የሚሸጋገሩበት አለም ውስጥ ሲገቡ፥ ከፍ - ከፍ ብለው፥ ከጋብቻ በፊት ከነበራቸው ኑሮ የተሻለ ልዩ፥ እውነተኛና ጣፋጭ አለም

---

[3] ዘፍ. 2፡24፤ ማር.10፡7 .......ወ.ዘ.ተ.

[4] ቃና ዘገሊላን በማስመልከት፡ ዮሐ. 2፡1-11

ይሆንላቸው ዘንድ፥ እነሆ በዛች ዕለት በሰውነታቸው የሚሰርግ ታላቅ ተስፋ፥ ደስ የሚል ትዝታ ሆኖ የጋብቻ ሕይወታቸውን ያድስላቸዋል።

ሰው ራሱን በመስተዋት አይቶ የገዛ ሰውነቱን እንዲለይ ሁሉ፥ ሚስትም ለባሏ መስተዋት ሆና - ባልም ለሚስቱ መስተዋት ሆኖ፥ ሁለቱ ባንድነት እራሳቸውን እያመሳከሩ (reality check) "በሰብእነታቸው" ደስ እያላቸው ይኖራሉ፤ የሰው "ሰብእነቱ" በግለሰብነቱ ብቻ አይረጋምና።

እርግጥ ሰው አገባም አላገባም፥ ካለ እግዚአብሔር መንፈስ መቆየቱ ነው ጎዶሎ የሚያደርገው። ማንም ሰው በውስጡ የእግዚአብሔር መንፈስ ከተዋሐደው ሙሉ ሰው ነው። ሰውም ሆነ መልአክ ከእግዚአብሔር መንፈስ ጋር ራሱን ሳያዛምድ እራሱን ማወቅና እራሱን መሆን አይችልም።

ሰው በራሱ ሙሉ ለመሆን ቢያቅተው፥ ሙሉነቱ የተናጋበት ምክንያት፥ ትዳል ባለመያዙ ብቻ ሳይሆን፥ የራሱን መንፈሳዊነቱን ባለማግኘቱ ይሆናል። በዚህ አለም ላይ ሙሉነታችንን የሚያጎድሉብን በርካታ ምክንያቶች ይኖራሉ።

ኮከቤና እኔ በልባችን የተመኘነውን እግዚአብሔር አሳካልን። በተሟላ የቤተ ክርስቲያን ስነ ስርዓት፥ ከዛው ከገዳሙ ሰርጋችን በተሳካ ሁኔታ ተፈጸመ። ለገዳሙ ከፍተኛ ምሥጋና ይድረሰው።

"ሚስት ያገኘ፥ በረከት አገኘ፤ ከእግዚአብሔርም ሞገስን ይቀበላል።" ምሳሌ 18:22

"ስለዚህ ሰው አባትና እናቱን ይተዋል፤ ከሚስቱም ጋር ይተባበራል፤ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ።" ኤፌ. 5፡31

በታላቅ ደስታ ተውጬ ውስጠዊ ደስታ አሰከረኝ፤ ከእንግዲህስ ኑሮዬ የተሟላ ሊሆን ነው ብዬ የሕይወት እስትንፋስ ተነፈስኩ። ከእንግዲህ ሌላው ሰው ሁሉ እንደሚኖር እኖር ዘንድ የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆነ አልኩ።

የሚዋደዱ ባልና ሚስት አይፋቱም፤ ሞት እንኳን ቢመጣ አይለያዩም፤ አንድ ላይ ይሆናሉ ምንጊዜም - ምንጊዜም። ኮከቤና እኔን እንድንገናኝ ያደረገ አምላክ ሁለታችንንም ይመለከተናል። ይህች ጠባየ ሸጋ ሚስቴ እኔነቴን የማይባት ሕይወቴ ናትና፤ እንደ አይኔ ብሌን እሳሳላታለሁ። እናቴ፥ እህቴ፥ እመቤቴ፥ ባለቤቴም፥ ጓደኛዬም ናት። ተመስገን፤ ከእንግዲህ ሚስቴ ለሕይወቴ ብሩህ ተስፋ ትሰጠዋለች። ሁለታችንም ባንድነት የምንመሠርተውን ትዳር እግዚአብሔር ይባርከዋል።

ተጋብተን ጥቂት ከቆየን በኋላ፥ የወደፊት የትዳር ኑሮአችንን እንድንኖርበት ከአንድ በረዶ እና ውሃ ከበዛበት፥ ጫካና ደን፥ ማእድት፥ የዱር አራዊትም ከሞሉበት - እድላችን ገግፍቶ ወደ ካናዳ አመጣን።

የመጣነው ጉልበተኞቹ እንግሊዞችና ፈረንሳዮች ነባሮቹን አስለቅቀው፥ እነርሱ የሰፈሩበት ሥፍራ ነው። ነባሮቹ ለመኖሪያ አመቺ የሆነውን መሬት ስለተነጠቁ፥ ሰው ከማይደርስበት ከወደ በራዱ የሰሜን ዋልታ ተሸጋሽገዋል። ከጥቂት ዓመታት ወዲህ፥ በተቀረው መሬት የአለም ሕዝብ ሰፍሮበታል።

በዚህ አገር ሁሉም እንደየአመጣጡ ቋንቋውን፥ ሃይማኖቱንና ባህሉን እያስከበረና እያዳበረ፤ በውህደት (assimilation) ሳይሆን በመቀላቀል (integration) እንዲኖር የሚያደፋፍር መንግሥታዊ ስርዓት (ተቋም) አለ። ከነልዩነት ተከባብሮ መኖር በሚቻልበት በዚህ አገር የአለም ቁንጅና በአካልና በመንፈስ ጎልቶ ይታያል።

የካናዳ መንግሥት የፖለቲካ ተቋም - የሰው ልጅ ሠርቶ በሰላም የሚያድርበት ምቹ ሥፍራ ካገኘ፥ ሰላም ፈላጊ እንጂ ጠበኛ እንደማያደርገው ስለሚያንጸባርቅ፥ በሰላም ወዳድነት በዓለም የታወቀ ሆኗል። በዚህ አገር ልጆቻችን እና የልጅ ልጆቻችን እናት አገራቸውን ሳይረሱ፥ እስከ አለም ፍጻሜ ድረስ ቢኖሩበት ቅር አያሰኝም።

ወደዚህ አገር ከአንድ ታላቅ ከተማ ገብተን የትዳር ኑሮ ጀመርን። ሁለት ቆንጆ - ቆንጆ ልጆች (ሴትና ወንድ) በማከታተል ወለድን።

ባልና ሚስት ልጆች ሲወልዱ ኩራት ይሰማቸዋል። ከልጆቻቸው ጋር ሲኖሩም ለልጆቻቸው የሚያስተላልፉትን ደስታ መልሰው ያገኙታል። ሁሉን አስተላክሎ የሚሰጥ እግዚአብሔር ደስተኞች ስላደረገን እናመሰግነዋለን።

<u>እውነተኛ ገጠመኝ - መጥፎ አጋጣሚ</u>

ያልተረጋገጠ ነገር "እውነት ነው - እውነተኛ ገጠመኝ ነው" ብሎ ማውራትን እንደ ኃጢአት ነው የምቆጥረው። ግን የሰው ልጅ በምድር ላይ ተደላድሎ እንዳይኖር፥ ልክ እንደ አውሎ ነፋስ ከቦታ ቦታ እየለዋወጠ፥ በተለይ አንዳንድ ግለሰቦችን "የሚያጠቃ ነገር" መኖር አለበት (ይመስለኛል)። አወሎ ነፋስ የሚነሳበትና የሚደርስበት ምክንያት እንደሚኖረው ሁሉ፥ ምድራዊ ግፊቶችም (ምናባዊ - ሃሳባዊ ቢሆኑም) የሚነሱበትና የሚደርሱበት ምክንያት ይኖራቸዋል። ይህንን ምክንያት መረዳት ነው ቀላል የማይሆነው።

ከእለታት አንድ ቀን፥ በማያቋርጥ ሃሳብ ተጠምጄ፥ ሌሊቱን በሙሉ እንቅልፍ ሳይወስደኝ አደርኩ። ለሥራ ጉዳይ ራቅ ያለ ሥፍራ መሄድ ስለነበረብኝ፥ ሲነጋጋ መኪናዬን አስነስቼ በትልቁ አውራ ጎዳና ማብረር ጀመርኩ። መኪናዬን እየነዳሁ፥ በድንገት አንድ እንደ ራአይ አይነት ነገር (እውነታ - ጥቅልል የሃሳብ ጉም ልበል?) ተገለጠልኝ። በዚህም እየተገረምኩና እየተደሰትኩ ሳለሁ፥ የደስታው ብዛት አላስችል አለኝና፥ መኪና መንዳቴን አቁሜ ትንሽ አረፍ ማለትና ማሰላሰል እንዳለብኝ አሰብኩ። ወደ አንድ የቤንዚን ማደያ ስደርስም፥ ባዶ የመኪና ማቆሚያ ወዳለበት ዳርቻ ሥፍራ መኪናዬን አቆምኩ፤ በዚሁም ራእይ መሰል ነገር ተጠምጄ በሃሳብ ደነዘዝኩ።

ከዛ መቼና እንዴት መኪናዋን አስነስቼ ጉዞ እንደጀመርኩ አላስታውስም። ግን ከአይምሮዬ የተቀረጸ መንፈሳዊ ሃሳብ ተያይዞና ተሳስሮ አንድ ቀጥተኛ የሆነ ሃይማኖታዊ ፍልስፍና ውስጥ ስለከተተኝ፥ መኪና መንዳቴን እስከመርሳት አደረሰኝ። መኪናዋ ከድልድይ ጋር ተላትማ፥ እኔም ከመሪውና ከበሩ ጋር ተጣብቄ፥ የትራፊክ ፖሊስ ሲያላቅቀኝና ሲያወጣኝ ልክ ከእንቅልፉ እንደተቀሰቀሰ ሰው ሆንኩ።

ከዚህ ከባድ አደጋ ተርፌ፥ በሰውነቴ ላይ ጉዳት ባለመድረሱና ባለመሞቴ ደስ አሰኝቶኝ መንገዴን ቀጠልኩ። አሁንም ለኔ በደረሰብኝ ግጭት ከመጎዳቴ የበለጠ ያሳሰበኝ - ያ እንደ ራአይ አይነት ነገር (እውነታ - ጥቅልል የሃሳብ ጉም?) ነበር። ግን ከዛን የመኪና አደጋ በኋላ፥ በጭንቅላቴ የነበረው ሃሳብና ራእይ መሳይ ነገር ሁሉም አንድ ሳይቀር ድምስስ ብሎ ጠፍቷል። ግን ትንሽ ትንሽ፥ የሆነ ቦታ ደርሼ የመጣሁ ይመስለኛል። ግን ሁለት አለም አይተዋወቅ....፤ ለአካላዊ ሰው - በምድር - በዛ ጭንቅላት ምን ይሰረግ? ለአካላዊ ሰው - በምድር በዛ ጭንቅላት ምን ይቀመጥ (የሚታወስ)። ባይገባኝ አይገርመኝም፤ ግን ላይገባኝ እንደሚችል ከተረዳሁ ይበቃኛል።

ከተጠቀሰው የመኪና አደጋ በኋላ፥ በየቀኑ ረጅም ጉዞን ለመቀነስ ስንል እና በሌሎችም ምክንያቶች፥ ከኮከቤና ከልጆቼ ጋር ያን ታላቅ ከተማ ለቀን ከዛው ከምሠራበት አንድ ትንሽ ከተማ ገብተን መኖር ጀመርን።

ከእለታት አንድ ቀን፥ ከምሽቱ ስምንት ሰዓት ላይ ከኮከቤ ጋር ብቻ ሆኜ (ልጆቻችንን ለአክስቶቻቸው ትተን)፥ እኔ መኪና እየነዳሁ፥ ጭልም ያለ መንገድ ውስጥ ገባን። ባለቤቴ አንድ የባለ አንድ አይን መኪና ወይም የሞተር ቢስኪሌት መብራት የመሰለ ብርሃን ከኋላ ሲከተለን ታስተውላለች።

“ምንድነው ይህ ከኋላ ኋላ የሚከተለን ብርሃን? የመኪናም የሞተር ቢስኪሌትም አይመስልም!” ትለኛለች ፍርኃት በተሞላበት ስሜት። እኔም “እባክሽ

ዝም በይ፥ ታዲያ ሌላ ምን ይሆናል? ባለ አንድ አይና የመኪና መብራት ይሆናል ወይንም የሞተር ቢስኪሌት መብራት። ሌላ ምን ሊሆን ይችላል ብለሽ ነው?" አልኩ ቆጣ በማለት። እርሷ ግን፥ ይህን ብርሃን በተደጋጋሚ እያየች ስትነግረኝ ችላ ብያት መቆየቴ አሳሰባትና ተጨነቀች።

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ፥ አንድ ባለ አንድ አይና መኪና ከጎናችን ሲያልፍ፥ "ይኸው አካልኩሽም!" አልኩና የተናገረችውን ውድቅ አደረግሁባት። ትንሽ ቆይቶ፥ "ተመልከት! ተመልከት! ተመልከት! .." አለችኝ በፍርኃት።

ከሩቅ አንድ ብርሃን በታላቅ ፍጥነት እየገሰገሰ ይመጣና ልክ አጠገባችን ሲደርስ ጥፍት ይላል። አሁንም ትንሽ ቆይቶ እንደዚሁ ሆነ። ባጠገባችን የሚያልፍ ሌላ ባለ አንድ አይን መኪና ጠፋ። ይህንኑ ጉዳይ ለማጣራት ብዬ የመኪናዬን ፍጥነት በመጨመርም በመቀነስም ሞካከርኩ። ይህ ብርሃን ከኋላችን በመንገዱ ትይዩ ዝቅ ብሎ ይጀምርና፥ ቀስ በቀስ ከፍ እያለ ወደ ላይ ይመጣና ልክ ወደኛ መኪና ሲዳረስ ከመኪናዊ ጣሪያ በላይ ይወጣና ይሰወራል። ይህን በተደጋጋሚ ሁለታችንም ስላየነው፥ ሌላ ባለ አንድ አይና መኪና ወይንም ሞተር ቢስኪሌት ሊሆን እንደማይችል እርግጠኞች ሆን (በዛን ወቅት)።

ይህ ብርሃን እኛን የሚከታተለን መሆኑ አስፈራን። ስናስበው አይመጣም፤ ሳናስበው ይከተለናል። ከአስተሳሰባችን ጋር ምን ግንኙነት እንዳለው አልገባንም። የብርሃኑም ፍጥነት ከፍተኛ ስለሆነ ከሩቅ ይነሳና ባንድ ጊዜ ካጠገባችን ሲደርስ ይሰወራል፤ ይህ ለአምስት ጊዜ ተደጋገመ።

በሚቀጥለው መገንጠያ ላይ ይለቀናል ብለን አሰብን። "አሁን ከተገነጠልን በኋላም የሚከተለን ከሆነ፥ በእውነትም እኛን የሚከታተል መሆን አለበት" አልን። ተገንጥለን ትንሽ እንደተጓዝን አሁንም ተከተለን። በዚህን ጊዜ ሁለታችንም ፍርኃት ያዘንና ሳናቋርጥ -"በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ፥ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ፥ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ...." እያልን ወደ አንድ ቤንዚን ማደያ ስንደርስ መኪናችንን አቆምን። እኔም በድፍረት ከመኪና ወጥቼ መንገዱን ማስተዋል ጀመርኩ - ድንገት የሚያልፍ መኪና ወይንም ሞተር ቢስኪሌት ቢኖር ብዬ። ምንም አላየሁም፤ ያ ሲከተለን የነበረ ብርሃን ጠፋ። እኛም ከአፋችን በወጣው "በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ.." እየተጽናናን፥ በልባችንም ይህንኑ እያልን መንገዳችንን ቀጥለን፥ በሰላም ከቤታችን ደረስን።

ወደድንም ጠላንም፥ ይህ የማይታበል ክስተት ከመንፈሳዊነታችን ጋር (ከሃሳባችንም ጋር ቢሆን) ያለው ግንኙነት አልገባኝም። የሁኔታው መፈጸም የሚከታተለን ኃይል አለብን ብለን እንድናስብ አድርጎናል። ለማንኛውም እኛ

ባቅማችን ማድረግ የምንችለው፥ በእናትና አባታችን ሃይማኖት - በእምነታችን ጠንክረን መገኘት ነው። “በእምነታችን ጠንካሮች ከሆንን፥ የሚመጣውን ሁሉ በእግዚአብሔር ኃይል እንቋቋማዋለን...” በማለት እራሳችን አጽናንተናል።

የዘመኑ አዋቂዎች ነን ባዮች፥ እነርሱ በሕይወታቸው መጽሐፍ አንብበው፥ ተምረው፥ ከሰው ሰምተው፥ ወይንም በገጠመኞቻቸው ሊያውቁ የቻሉትን ትንሿን ነገር እጅግ አሳብጠው፥ እነርሱ ከሚያውቁት ውጪ ሌላ ማንም ሰው የብቻው የሆነ የተለየ ነገር ሊያጋጥመው እንደማይችል አድርገው ያዩታል። ሌሎች አታላዮች ደግሞ፥ ውሸቶችን እየፈጣጠሩ እውነት በማስመሰል ይነግዱበታል - ይከብሩበታል - ይገኑበታልም።

በምድራዊ መንፈሶች (ወይም እኛ ከምድራዊነታችን በወረስነው ጠባያችን) ተጽንኦ፥ በዚህ አለም ኑሮአችን አስከፊ ሲሆን፥ የሰው የመንፈሱ ጥሩነት ለዚህ አለም እንግዳነቱን ሲያሳውቀው፤ የት ላይ ነው የምድራዊ ሕይወታችን ተስፋ ያለው?

በዚህ አለም እውነተኛ ታሪክ እየተበረዘ ውሸት የበዛው - ትንሿን እውነት በትንሽነቷ የሚያስቀምጣት ስለጠፋም ይሆናል።

<u>የራሄላውያን ተንኮል?</u>

በአለም ውስጥ (ከግለሰብ፥ እስከ ሕብረተሰብ እና አለም አቀፍ ደረጃ ድረስ) ብዙ አስከፊ ነገሮች ይሠራሉ። ሁሉንም ከምድራዊ መንፈሶች (ከምድራዊነታችን) ተጽንኦ አንጻር መመልከት ይቻላል። ምድራዊ መንፈስ አንቆ የያዘው ሰው ክፉ ይሆናልና፤ ስነ አመክንዮ አስተሳሰባችንም አድሎአዊ ከመሆን አያመልጥም።

አንዳንድ ወሬ ፈጣሪዎችም ትንሽ እውነት ያገኙ እንደሆን፥ ያቺን ያባዙና፥ ያራቡና፥ እያጣፈጡ በማጋነን ያወራሉ፤ ይጽፉሉም። እነርሱ ሳያስቡት ያቺ ትንሽ እውነት ጥልቅ ውሸት ትሆናለች። በዚህም አይነት ሳይሆን አይቀርም፥ አንድ ራሄል የተባለ ጆርናሊስት - ታላቅ ወሬኛ ስለ ጠፈር ሰዎች በማጋነን የጻፈውና፤ በኋላም እምነት ሆኖ የቀረው።[5]

---

[5] https://en.wikipedia.org/wiki/Ra%C3%ABlism

*ራሄሊዝም በክላውድ ቮሪልሆን የተጀመረ ሃይማኖታዊ ንቅናቄ ነው።*

The Raëlian Movement teaches that life on Earth was scientifically created by a species of humanoid extraterrestrials, which they call the Elohim.

ባሁኑ ዘመን ጸረ ሃይማኖተኞች (በእግዚአብሔር የማያምኑ) ብዙ የተንኮል ሥራዎችን ይሠራሉ። "በጠፈር ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች አሉ.." ብለው የሚያምኑ ብዙዎች ናቸው፤ ግን ሁሉም በእግዚአብሔር የማያምኑ አይደሉም። ራሄላውያን የተባሉ - ራሱን ራሄል ብሎ የሰየመው የፈረንሳይ አገር የስፖርት ጋዜጠኛ የነበረው የክላውድ ቮሪልሆን ተከታዮች ናቸው። እነርሱ በእግዚአብሔር የሚያምኑ ቢሆኑም፥ በምድር ላይ ሕይወት የተጀመረው፥ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ፥ ጠፈር ውስጥ በሚኖሩ - ኤሎሂም በተባሉ ፍጥረታት ነው ብለው ያምናሉ።

አንዳንድ ሰዎች በውስጣቸው ካለው እውነት ይልቅ የጠባያቸው ትምክህተኛነትና ግትረኛነት ይገንባቸዋል። ስለዚህም መሳሳታቸውን እያወቁም እንኳን ቢሆን፥ አንዴ የተናገሩት በሌላ እውነት እንዳይቀለበስባቸው ሲሉ የሚቻላቸውን ሁሉ ያደርጋሉ።

ያ ቀደም ሲል የገለጽኩት ክስተት (ሲከተለን የነበረው ብርሃን) በተፈጸመበት ወቅት፥ በአካባቢው ራሄላውያን ያየሉበት ወቅት ስለነበረ፥ እነርሱው የፈጸሙት ትንኮል ሳይሆን አይቀርም (ላይሆንም ይችላል)።

ወሬ ፈጣሪዎች ትንሽ እውነት ያገኙ እንደሆን፥ ያቺን ያባዙና፥ ያራቡና፥ እያጣፈጡ በማጋነን ያወራሉ፤ ይጽፋሉም። ታዲያ ያቺ ትንሽ እውነት ትልቅ ውሸት ትሆንና ብዙዎችን ታሳስታለች።

አቶ ክላውድ ቮሪልሆን (ራሄል) የተባለውም ጋዜጠኛ "በጠፈር ላይ በሚኖሩ ሰዎች ተወስጄ፥ ከነርሱ ጋር ኖሬአለሁ...፤" እያለ ይሰብካል። እርሱም መጽሐፍ ቅዱስን (በተለይ ትንቢተ ሕዝቅኤልን) እየጠቀሰ፥ ሌላ አለም እንዳለ፥ በዚያም አለም ያሉ ሰዎች እጅግ የሠለጠኑና ብዙ ሺህ ዓመታት የሚኖሩ መሆናቸውን በብዛት ይተርካል። ስለዚህም ከሰዎች የተደበቀ አለም በማብራራት አንድ መጽሐፍ ጽፏል። በዚህም መጽሐፉ ውስጥ እግዚአብሔርን፥ ክርስቶስን፥ አብርሃምን...አየሁአቸው ይላል። እራሱን ከክርስቶስ ጋር ያመሳስላል። ክርስቶስ በሰይጣን እንደተፈተነ እኔም እንዲሁ ተፈትኛለሁ ይላል።

"ማንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ። ብዙዎች እኔ ክርስቶስ ነኝ እያሉ በስሜ ይመጣሉና፤ ብዙዎችንም ያስታሉ።" ማቴ. 24፥4 - 5 በማለት ክርስቶስ የተናገረው በተለይ እንደራሄል ያሉትን ቀባጣሪዎች ስለሆነ፥ አንዳንድ እውነት የሚመስሉ የዘመኑ ትረካዎችን በሚመለከት ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል።

ባሁኑ ወቅት በሰዎች ጭንቅላት የሚጉላሉ ብዙ - ብዙ ጥያቄዎች አሉ። እነኚህም ጥያቄዎች የሚመነጩት አንዳንድ ሰዎች አካላዊ የሆነ (ወይንም የመሰለ) ከሰማይ ላይ የሚያንዣብብ ነገር (UFO – unidentified Flying Object) ተመልክተናል ከሚል፥ እውነት ይሁን ውሸት ከማይታወቅ ወሬ በመነሳት ነው።

የጠፈር መንኮራኩር አለ ቢባል፥ ወይንም ሌላ የማይታይ ረቂቅ የመንቀሳቀሻ መንገድ አለ ቢባል፥ ይህንን በሳይንሳዊ መንገድ ማረጋገጥ ያስቸግራል።

የምድር ሰው በአህያና በበቅሎ እየተጠቀመ ከቦታ ቦታ በሚዘዋወርበት ወቅት፥ "የሰማይ ፍጡራን" ከምድር አይሮፕላንና ሌሎችም የምድር መንኮራኩሮች በበለጡ መንኮራኩሮች ይጠቀሙ ነበር ለማለት የሚያበቃ ጥቅስ በትንቢተ ሕዝቅኤል ይነበባል።

"....በምድር ላይ አንድ መንኮራኩር አየሁ፤ የመንኮራኩሩም መልክ እንደ ቢሪሌ ነበር፤..." ሕዝ. 1፡15 - 16

ነገር ግን፥ መንኮራኩር የተባለው አካላዊ ቢመስለንም፥ የመንኩራኩሩ ተጠቃሚ (መሪ) መንፈስ እንደሆነ እንደሚከተለው ተገልጿል።

"..በእነዚያ መንኮራኩሮች ውስጥ የሕይወት መንፈስ አለና፤ ከምድር በተነሱ ጊዜ፥ መንኮራኩሮቹ ከእነርሱ ጋር ይነሳሉ።" ሕዝ. 1፡21

እንዲሁም "እንስሶቹም እንደ መብረቅ ምስያ ይሮጡና ይመለሱ ነበር።" ሕዝ. 1፡14 ሲል፥ እንስሶቹም፥ መንኮራኩሮቹም አካላዊ አለመሆናቸውን፤ ሰማያዊ አካላት ቢሆኑም፥ የመንፈስን ህልውና በተለያየ መንገድ የሚገልጹ መሆናቸውን ይጠቁማል።

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከመቃብር ተነስቶ ወደ ሰማይ ባረገበት ጊዜ፥ ያ የሰዎችና የመላእክቶች ሁሉ ጌታ መንኮራኩር ቀርቦለት አይደለም ወደ ሰማይ ያረገው፤ እንዲሁ በራሱ ከፍ - ከፍ ብሎ ወደ ሰማይ ወጣ እንጂ።

ክርስቶስ ባረገበት ወቅት መንኮራኩር እንዳልቀረበለት ሁሉ፥ ካለ አካላዊ ኃይልም እንዳረገ ሁሉ፥ ወደ አካላዊ ያልሆነ ሰማይ ውስጥ እንጂ፥ እንደገና ወደ ሌላ አካላዊ አለም እንዳልሄደ "እንገነዘባለን"።

ስለ ሰማያዊ አካል ሐዋርያው ጳውሎስ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

"....ደግሞ ሰማያዊ አካል አለ፤ ምድራዊም አካል አለ፤ ነገር ግን የሰማያዊ አካል ክብር ልዩ ነው፤ የምድራዊውም አካል ክብር ልዩ ነው።" 1ኛ ቆሮ. 15፡40 - 41

ሐዋርያው ጳውሎስ ሰማያዊ አካል የሚለው "ነገር" ቁስ አካል (matter) አይደለም። የሰማያዊ አካል ክብር ልዩ ነው፤ የምድራዊውም አካል ክብር ልዩ ነው ሲል ደግሞ፥ ሁለቱ የተለያየ ሕግጋት ያላቸው መሆናቸውን ይጠቁማል።

እኛ የምናውቀው ምድራዊ አካል (ከፕሮሮቶን፥ ኒውትሮን፥ ኢሌክትሮን..ወዘተ) የተገነባ ሲሆን፤ ይህም ዋነኛ ጠባዩ በስባሽነት ነው (የሰው፥ የእንስሳትና የእጽዋት በስባሽነት)። ከዚህ በስባሽ ከሆነው አካል ሌላ የማይበሰብስ ሰማያዊ አካል ብቅ ይላል በማለት በሰፊው ተብራርቷል። 1ኛ ቆሮ. 15፥41 - 58

ታዲያ እኛም የሐዋርያው ጳውሎስን ትንተና በመከተል የሰማያዊ አካል አጠቃላይ ጠባይ የማይበሰብስ ነው ብንል፥ ያ የማይበሰብሰው "የሰማይ ሰው" የመሬት ሰውን የመሰለም ቢሆን አካላዊ አለመሆኑን (የተለየ ክብር እንዳለው)፤ የሰውነቱም ቅርጽ (በምድራዊ ቋንቋ) ሰማያዊ "ሥራዎችን" ለመሥራት እንደሚሆንም እናገናዝባለን።

ሰውም ሆነ እንስሳ ምድራዊ በመሆን ከመሬት (አፈር፥ ውሃ፥ እሳትና ነፋስ) በመገንባት አካላዊ ወይም ሥጋዊ ደማዊ ሲሆን፥ በምድር ለመኖር የሚያስችል የአካል ቅርጽ ይኖረዋል፤ የምድር ሥራን እንዲሠራ ተፈጥሯልና። በሰማይ ግን ሥራው ሁሉ ሰማያዊ ስለሆነ፥ ክብሩ (ፍጥረቱ) የተለየ ነው። መላእክት ግን በዚሁ በምድር ቋንቋ ከእሳትና ነፋስ ተፈጥረዋል።

"ስለ መላእክቱም "መላእክቱን ነፋሳት፥ የሚላኩትንም የእሳት ነበልባል የሚያደርጋቸው እርሱ ነው" አለ።" ወደ ዕብ. 1፥7

የጋዜጠኛው የክላውድ ቮሪልሆን (ራኤል) የመጀመሪያ መጽሐፉ[6] የጠፈር "ሰዎችና መኖሪያቸው?" ይህንኑ ምድራችን የመሰለ፥ ፍጹም አካላዊ አለም እንደሆነ አድርጎ ነው የገለጸው። ቢሆንም (ወይንም ቢመስል) አያስገርምም (የሄኖክ መጽሐፍም እንደዚሁ ሰማያዊውን አለም ምድራዊ የሚያስመስል ሃተታ አለበት)።

የራኤል ሁለተኛው መጽሐፉ በተለይ የወጣቶችን ስሜት ለመማረክ የታቀደ ይመስላል። ይኸውም መጽሐፉ አይምሮን በሃሳብ አስክሮ፥ ለምድራዊ አስረሽ ምቺው የሚያዘጋጅ ነው። የሶዶምና ጎሞራን ግብር የሚከተል በመሆኑም፥ ብዙ ወጣቶች ለዚሁ ሲሉ ከራኤል ማህበር ይገባሉ። እርሱም አስመስሎ በማውራት ችሎታው ብዙ ተከታዮች አፍርቷል። ከነኚህ ተከታዮቹ፥ በፍትወተ ሥጋ ፍላጎት ያልተጠመደ፥ እድሜውም ሽማግሌ የሆነ፥ ለእውነት የቆመ አይገኝም - ሁሉም በምድራዊነታቸው ደስ እያላቸው መኖርን ብቻ የሚሹ፥ ከምድራችን ደስታን አሳዳጆች - ወዳዶች (pleasure mongers) ናቸው።

የመጽሐፉን ይዘት የተመለከትነው እንደሆነ፥ ይህ ሰው ለራሱ የሚመኘውን ሁሉ ከሰማይ ቤት እንደሚገኝ ያስመስለዋል። በጭንቅላቱ ካለው የስፖርት ፍቅር

[6] Vorilhon Claude, 1983

ባለመላቀቁ፥ በሰማይ ቤት ያሉ ሰዎች አብዛኛውን ጊዜአቸውን የሚያጠፉት በእስፖርት ላይ ነው ይላል። በሴቶች ላይ ለመደሰት ካለው ፍቅር ባለመላቀቁም፥ በሰማይ ቤት ያሉ ወንዶች ቆንጆ - ቆንጆ ሴቶችን በሰው መፍጠሪያ መሳሪያ እየፈጠሩ እንደሚደሰቱባቸው ይገልጻል። "በሰማይ ቤት ሳለሁ አስር ሴቶች ከበው አስደሰቱኝ.." እያለ የሚቀባጥረው ሁሉ ስነ አይምሮአዊ ማንነቱን የሚገልጽ ነው እንጂ፥ ቅንጣት እውነተኛነት ቢኖረው ኖሮ፥ ጭራሽ የማይመስል ትረካ ውስጥ ባልገባ ነበር።

ይህ ሰው ከፍተኛ የማሳመን ችሎታ አለው (እጅግ አዋቂ የሚባልም ሊሆን ይችላል)። ከአስርት ዓመታት ጀምሮ እንዲሁ ካለማቋረጥ ባደረገው ሰበካ፥ ቀስ በቀስ ብዙ ተከታዮችን አፍርቷል። በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ የማሠራበት ገንዘብ እርዱ እያለ በመሰበክ ገንዘብ አጠራቅሟል። አላማውም በኢየሩሳሌም ላይ ንጉሥ ተብሎ አለምን ለመግዛት ነበር። ይህ እንደማይሳካለት ሲገነዘብ ጊዜ፥ ባጠራቀመው ገንዘብ ሳይንቲስቶችን በመግዛት፥ ሰውን ሰው ሊፈጥረው ይችላል የሚል ፍልስፍና ማስፋፋት ጀመረ። ለጥቅም የተገዙ ሳይንቲስቶችም ለገንዘብ ሲሉ የርሱን ምኞት ለማሳካት ቆርጠው ተነስተዋል። ከእንግዲህ የሰውን ጥሩ የአካል ባህሬ ያለውን እየመረጥን ሰውን መልሰን እንፈጠረዋለን (clone እናደርገዋለን) ባዮች ናቸው።

ራሄል በዝግመተ ለውጥ አያምንም፤ ሰው በምድር የተፈጠረው የዛሬ 22 ሺህ ዓመት ነው ይላል። እንግዲህ የትኛው ነው ሳይንቲስቶቹ እውነት የሚመስላቸው። ሰው ሁሉ የሚታለለው ከእውቀት ማነስ (ወይንም ከእውነት መጉደል) ብቻ አለመሆኑን የራሄል ተከታዮች ከሆኑ ሳይንቲስቶች መረዳት ይቻላል፤ እነርሱ ለገንዘብ ሲሉ እያወቁ "አዎን፥ አዎን፥ ልክ ነህ!..." አሉት እንጂ፥ ለአንድ እውነተኛ ሳይንቲስት "ሰው በምድር የተፈጠረው የዛሬ 22 ሺህ ዓመት ነው" ቢባል፥ ውሸት መሆኑን በቀላሉ ማስረዳት አያቅትም[7]።

የሰውን ልጅ ክፋቱንና ደግነቱን ከአካላዊ ህዋሱ - የሰውን ምድራዊ ጠባይ የሚወስነውን ኬሚካል ከመንፈሳዊ ባህሬው ለይቶ ማውጣት የሚቻለው ማነው? ሳይንቲስቶች በአካል ጤነኛ ሰው ቢፈጥሩ፥ "ያ ሰው በመንፈሱ ምን አይነት ይሆናል..?" ብሎ ማሰብ ያስፈልጋል።

የሰውን የአካሉን ውስጠ ባህሬ በደንብ ቢያውቁ እንኳን፥ አካላዊ ያልሆነውን የመንፈሱን ነገር ካላወቁት፥ "ጥሩ የአካል ባህሬ ያለውን እየመረጥን ሰውን መልሰን እንፈጠረዋለን - ክሎን እናደርገዋለን" ሲሉ፥ ያ የነርሱ የመጨረሺያው የሥራ ውጤት

[7] "ከምድራዊነታችን ባሻገር" በሦስተኛው መጽሐፍ የተገለጸውን ይመለከቷል።

ስኬታማ ቢሆንም እንኳን፥ እንደ ሰይጣን ያለ አውሬ መሳይ ነገር እንዳያስገኝ ብሎ ማሰብ ያባት ነው።

አይ ፍዳችን!.. ከሰይጣን - በጠፈር ሁሉ መንገሥን፥ ከዳርዊን - በድንገት መገኘትን፥ ከኮሙኒስቶች - ከሃዲነትን፥ ከራሄላውያን - ቅጥፈትን፥ ... ። እንግዲህ ይህንን ሁሉ መደናበር ማየታችን የሰው ልጅ እውነተኛ ፈጣሪውን እንዳያውቅ፥ ....ምድራዊ ክፋቶች አስተሳሰባችን ሁሉ ከምድራዊነታችን እንዳይላቀቅና እውነትን እንዳናገኝት አደረጉት። አንድ ያልገባን ነገር አለ (ይመስለኛል)፡- ይኸውም - በሳይንስም በሃይማኖትም ቢሆን ያልደረስንበት ሊኖር መቻሉን መገመት (ማሰብ) እንደማንችል። ከምድራችን እድሜ አንጻር (4.5 ቢሊዎን ዓመት)፥ የሰው ልጅ ከተፈጠረ አምስት ደቂቃ እንኳን አልሞላውም፤ ታዲያ በዚህ ጨቅላ እድሜአችን አንጻር፥ ገና ያልደረስንበት መኖሩን ለምን አላሰብነውም?

ለወደፊት እግዚአብሔር ከፈለገ አዲስ ሰው ይፈጥር ይሆናል። ግን ስለ ፍጥረት ጉዳይ ስንመራመር፥ ለማንኛውም ነገር መፈጠር ቅድመ ዝግቶች እንደሚኖሩ ነው የተረዳነው[8]። ብዙ ዓመታት ከሚፈጅ፥ ሥጋዊና መንፈሳዊ ለውጦች በኋላ፥ የተለያዩ የሰው ዘሮች በአንድነት ተሰባስበው (ተዳቅለው) አንድ የሰው ዘር ከመሰሉ በኋላ ይሆናል እግዚአብሔር አዲስ ሰው የሚፈጠረው።

የተጠቀሰው አስገራሚ ትእይንት አመጣጥ ከየት እንደሆነ ለማወቅ ባለመቻላችን እኔን እና ባለቤቴን ኮከቤን እጅግ ያሳሰበን ነበር (ለማን እንደምንነግር እና ከማን ዘንድ እውነቱን ማግኘት እንደምንችል ሳይገባን ቆይቷል)። ሆኖም ከምድራዊነታችን ባሻገር ብዙ አለም ይኖራል፤ ብዙም ነገር ይሠራ ይሆናል። ለማንኛውም እምነታችን ሁሉን በማወቃችን ላይ አልተመሠረቱምና፤ በሃይማኖታችን ጸንተን እንቆይ በማለት ተጽናንተናል።

አንዳንድ ሰዎች “ይህ አስገራሚ ትእይንት አለ ከተባለ፥ አካል ካልሆነ ሌላ ምንድነው ሊሆን የሚችለው?” በማለት ጥያቄ ያበዛሉ። ሌሎችም አፋቸውን ከፍተው፥ “ይህ ያየኸው ውሸት መሆን አለበት..” በማለት የግለሰቡ የራሱ የሆነውን እውነት ይደፍኑበታል።

የእሳተ ገሞራን መፈንዳትና ማቃጠልን ሁላችንም ስለምናየው ለሁላችንም እውነት ነው። ለሰው ሁሉ እውነት የሆነ ብቻ ነው ወይ እውነት? ለሰው ሁሉ እውነት ያልሆነ እውነት የለም ወይ? የእግዚአብሔር ለሰዎች ሁሉ አለመታየት እውነት ነው።

[8] ይህንን ጉዳይ ከምድራዊነታችን ባሻገር ሦስተኛው መጽሐፍ በሰፊው ያብራራል።

እንግዲያውስ ሁላችንም እግዚአብሔርን አለማየታችን ለሁላችንም እውነት ከሆነ፥ እግዚአብሔር የለም ማለት ነው?

አንዳንድ አወቅን ባይ ተመጻዳቂዎች፥ በስነ አይምሮ የሚቀረጹ ሃሳቦች እንደ እውነት እየመሰሉ ሰውን ያታልላሉ እንጂ ጭራሽ ሊሆን አይችልም ብለው፥ ራሳቸው ከራሳቸው በሚቀረጽ ሃሳባቸው ተነሳስተው፥ ወይንም በተማሩት የእውቀት መመዘኛ ፍልስፍናቸው[9]፥ ለራሳቸው እውነታቸው የሆነውን እውቀታቸውን ብቻ በማጉላት፥ በሌላው ላይ የአስተሳሰብ ተጽንኦ እያደረጉ፥ የባሰ ያስጨንቃሉ። ማንም ሰው የሚያጋጥመቅውን እና የሚያየውን ከግለሰቡ በስተቀር የሚያውቅ ሊኖር አይችልም። እና ማን ይሆን፥ ከዚህ መለስ እውነት የሆነ እውቀት ከዚህ መለስ ውሸት የሆነ ድንቁርና ብሎ የሚለይ?

ኔይል ቦህር የተባለው ሳይንቲስት ሊቅ - "..physics is not about nature, it is about what we can say about nature"[10]. በማለት፥ ስለሚታወቀው ተፈጥሮ የሚታወቀውን ስላወቅን ብቻ ያለውን ሁሉ (ተፈጥሮን) እናውቃለን ማለት እንዳልሆነ፥ የፊዚክስ እውቀት አላማም ይህ እንዳልሆነ ባጭሩ አስረድቷል። አዎ! ስለ ተፈጥሮ የምናውቀውን ያህል መናገራችን ስለተፈጥሮ ማወቃችንን አይገልጽም፤ ብናውቅ - ያቺ የምናውቃት እጅግ ትንሽ ናትና።

ያ ያየነው ብርሃን ከማናውቀው አለም የመጣ ሊሆን ይችላል ብሎ ማሰብ ይቻላል። ወይንም የተጠቀሰውን ታሪክ እውነተኛነት ለማረጋገጥ ቀኑን፥ ሰዓቱንና ሥፍራውን በማገናዘብ፥ ከዚያ ሥፍራ በዚያን ሰዓት ምን እንደታየ፥ ወሬዎችን ከሌሎች ሰዎችና ከጋዜጣዎች ማጠናቀር ይቻል ነበር (ያስፈልግ ነበር)። ግን የዚህ መጽሐፍ አላማ "ይህንን ተአምር አየን..." እያልን ከመሠረቱ (ምክንያቱ) ያልተረጋገጠ ወሬን ለማሰራጨት አይደለም። እውነት የጋራ ሆኖ በሰው ሁሉ እውነትነቱ ሊታወቅ የሚችል ካልሆነ በስተቀር ውሸት መሆን አለበት ለማይል ሰው - የግለሰብን እውነት ማዳፈን ተገቢ አለመሆኑን ለመጠቆም፥ እንዲሁም አንዳንድ መልእክቶችን ለማስተላለፍ የሚጠቅም ይሆናል ተብሎ ስለታሰበም ነው የተጠቀሰው።

ከአካላዊ አለም ውጪ ለምክንያት የሚመጣ ክስተት እንዴት እንደሚከናወን ማወቅ አይቻለንም፤ ልክ የሚመስሉ ነገሮች በርከት ማለታቸው፥ ፍጹም እውነት ተራ

[9] epistemology – እውቀትን እውቀት በሚያሰኘው በተለያዩ መንገዶች ፈትኖ፥ የሚታመንና የሚታወቅ የሆነውን ብቻ እንደ እውቀት መቁጠር።

[10] John Brockman (editor), 2010, pp. 288

ሆኖ በቀላሉ የማይገኝ መሆኑን ያሳያል። ይህም ባይሆን፥ የገዛ አይምሮአችን አንዳንድ አስገራሚ ትርዕይቶችን እያጣመመ በመተርጎም ይሆናል የሚነግረን።

አይምሮአችን ምንጊዜም ፍጹማዊውን እውነት ቁልጭ እያደረገ ማቅረብ ስለሚያቅተው፥ እኛን - በመምሰል ባህር ውስጥ እየከተተን - ቀባጣሪዎች ያስመስለናል። በዚህም ምክንያት አንዳንድ አወቅን ባዮች (ሳይንቲስቶችም)፥ "ይህ ሰው እውነትን በትክክሉ መመልከት አይችልም፤ (delusion ውስጥ ገብቷል...)፥ ይህ ሰው ቀውሷል እያሉም፥ በነርሱ የሰው አይምሮ መመዘኛ እየመዘኑ ኢቃቂር ያወጣሉ። የሌላው ሰው አይምሮ የሚሠራውን ሥራ እየመዘኑ ትክክል የሆነውን እና ያልሆነውን እየለዩ የሚያስቀምጡ የነኚህ የ"አዋቂዎች" አይምሮ ምንኛ የረቂቅ ይሆን?

አይደለም (ላይሆን ይችላል)፤ የነኚህ የ"አዋቂዎች" አይምሮ ከሌላው አይምሮ ተለይቶ የሚታይ አይደለም። የነርሱ እውቀት ከብዙ መጻሕፍት በተጻፉ፥ እውነት መሳይ ነገሮች ተጨናንቋል፤ ካነበቧቸው መጻሕፍት ውጪ ማሰብን ቢጀምሩ፥ ወደ ሃይማኖታዊ ፍልስፍና ውስጥ ገብተው ቢፈላሰፉ፥ የሚገለጥላቸው ነገር ይኖራል (ምናልባት)።

ሰብአዊ ስነ አይምሮ በመንፈሳዊነት ከፍ ከፍ እያለ ሲራቀቅ - በሥጋዊነትና በመንፈሳዊነትም መካከል ልዩነት እየቀነሰ ሲሄድ - ምናልባት የዛን ጊዜ ይሆናል አሁን የማይገቡን ነገሮች የሚገቡን። እኛ ግን ቸኮልን፤ በጣም ቸኮልን - ከጠፈራዊ አካላዊ ክስተቶች የተለየ መኖሩን ብናውቅም - ባናውቅም ለ"ሊሆን ይችል ይሆናል - እኛ አናውቅም" የሚል አስተሳሰብ ጥቂት ክፍተት መስጠት ሰውን አይጎዳም።

የሰው ልጅ አብዛኛውን በመሬት እየኖረ፥ ትንሽ - ትንሽ በሌላው አለም (በሰማይ) ሳያስበው እንደሚኖር - ምድራዊ ኑሮአችን ስንሞት ከምንሄድበት ሥፍራ ጋር እኛ በማናውቀው መንገድ እንደሚነካካ እያሰብን፥ ወደ መንፈሳዊነት መዝለቃችን ለራሳችን ደስታን ይሰጠናል እንጂ አያሰናክለንም።

እንግዲህ! ወደ ዋናው ቁም ነገር ዞር ብለን እንመልከት፡- በዚህ አለም ላይ ብዙ ነገር ከእውነታው የሚመስለው (በአይምሮ መስሎ የሚቀረጸው) በርካታ ይሆናል። ግን ሁሉም (የሚመስለውም፥ የማይመስለውም - የሆነውም፥ ያልሆነውም) ተያይዞ ሰብአዊነትን ወደ አንድ ተፈላጊ አቅጣጫ ይመራዋል። ወዴት? ይህንን ለማወቅ (ባናውቅም ለማመን) የሚረዳን ሃይማኖት እንጂ እኮ ነው።

# ምዕራፍ ሦስት

## ግፊት - ወደ ሃይማኖት

የሰው መንፈሱ እንቅልፋም ስላልሆነ በቀንም በማታም፥ በእውንም በሕልምም ንቁ ነው (ይጓዛል - ይመጥቃል)። ስለዚህ፥ አንዳንድ ያልታወቁ አስገራሚ ትርእይቶች ቢፈጸሙ፥ ምድራዊ ሕይወታችንን እንዳያውኩት መጠንቀቅ ይገባል።

በምድራችን ውስጥ ያሉ ችግሮች ሰውን የሚያጠቁት በግል (በተናጠል) ብቻ ሳይሆን በጋራም ስለሆነ፥ ከችግሮቻችን ለመላቀቅ የጋራ ችግሮቻችንን በጋራ (በሕብረት እና በአንድነት) እንመልከታቸው። ምድራዊ ሁኔታዎች ጥሩዎችም መጥፎዎችም እየሆኑ ሰውን ያስደስቱታል ወይንም ያስከፉታል። በአንድ አለም ውስጥ ሁለት አለም እንዳለ እናውቃለን። የሁለት አለም ሚዛን እምኑ ላይ እንደሆነ ማወቁ ነው ያስቸገረው።

የሰው አይምሮ ውሱን እንደመሆኑ መጠን፥ ምድራዊ እውቀትም ውሱን ነው። መንፈሳዊ እውቀት ግን የሚመነጨው ከሰው አይምሮ ውጪ ከሆነ (ከታመነበት) ወሰን የለውም። በአይምሮና "ከአይምሮ ውጪ" በመንፈስ አርቅቀው ሲመለከቱት "ብዙ ነገር" ግልጥልጥ ይላል።

እንዳንድ ጊዜ ምድራዊ ሁኔታዎች ሰውን ወደ ውስጣዊ ማንነቱ - ወደ መንፈሳዊ ተፈጥሮው (ሕገ ልቦናው) ይገፋፋዋል። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ፥ ሃይማኖታዊ እውቀት ሰውን ወደ መንፈሳዊ ተፈጥሮ ይመራል።

ወደ ቀድሞ ነገራችን እንመለስና፡- በዛ ቀድሞ በነበርንበት ከተማ ውስጥ ስንኖር፥ ልጆቻችን ያቆረብንበት አንድ የግብጾች ቤተ ክርስቲያን አልፎ - አልፎ እንሄድ ነበርና፤ ከእለታት አንድ ቀን የቤተ ክርስቲያኑ ካህን እኔን ቀረብ ብለው - "ሰላም ላንተ ይሁን፤ አንተና ጥቂት ኢትዮጵያኖችን ከዚህ እየመጣችሁ ስታመልኩ ስመለከት ደስ ይለኛል። በሌላም በኩል ለምን የራሳቸውን ቤተክርስቲያን መሥርተው በራሳቸው ቋንቋ አይቀድሱም እላለሁ። ግን ይህንን ለማድረግ ቁጥራችሁ የበዛ ላይሆን ይችላል ብዬ አስባለሁ። የሆነው ሆኖ፥ ይህንኑ የኛን ቤተክርስቲያን ተካፍለን እናንተም በቋንቋችሁ

እኛም በቋንቋችን ብንቀድስ ይበቃናልና፤ እስቲ እናንተ ተሰባሰቡ እንጂ፥ ቤተ ክርስቲያን እኔ እሰጣችኋለሁ አሉ።"

እኔም ነገሩን ችላ ብዬ ከልቤ አላቆየሁትም። በሌላ ጊዜም ከቤተ ክርስቲያን ስንሄድ ይህንኑ ይናገሩኝ ስለነበረ - " እኚህ ቄስ ከኔ ምን አላቸው? ባያስጨንቁኝ ምናለበት?" እያልኩ አጉረመርም ነበር።

ልጃችን ድንገት ታመመችብንና ምን እንደመራኝ ሳላውቅ ቀጥታ ከካህኑ ቤት ሄድኩ (የካህኑ ቤትና ቤተ ክርስቲያኑ የተያያዙ ናቸው)። ካህኑም ሲያዩኝ፥ ልክ እንደ ዘመዳቸው ሞቅ ባለ ሰላምታ ከተቀበሉኝ በኋላ፥ ከቤታቸው አስገብተው "ቁጭ በል ልጄ" አሉና፥ ሻይ እንዲፈላልኝ አዘዙ።

እኚህ ካህን (ሽኑዳ) ባፋቸው ከመናገራቸው እያስቀደሙ በመንፈስ ለማናገር የሚሹ መሆናቸው ከሁኔታቸው ይታያል። ቀስ ብለው- "ዛሬ ምን ሆነህ መጣህ? " አሉኝ በቀስታ። እኔም ስለ ልጄ መታመም ነገርኳቸውና፥ እንዲጸልዩልኝ ብዬ ነው አልኳቸው። "ሃኪም ቤት ወስደሃታል ወይ?" አሉኝ። እኔም - "አዎን ወስጃታለሁ፤ መድኃኒትም እየወሰደች ነው፤ እንዳው ቶሎ አልድን ስላለች፥ ፈጥና ትድን ዘንድ እንዲጸልዩልኝ ብዬ ነው" አልኳቸው።

አንገታቸውን ዘንበል፥ ቀለስ ማድረግ ልማዳቸው የሆነ፥ እኚህ ካህን ትንሽ ዝም አሉና - "ልጄ፥ ካሁን በፊት ከዚህ ቤተ ክርስቲያን ትመጣጣ ነበር፤ አሁን ግን ጥፍት ብለሃል። አንድ ምዕመን ከቤተ ክርስቲያን ጥፍት ሲል ችግር ይደርስበታል። በበኩሌ የምመክርህ፥ ባለቤትህን እና ልጆችህን ይዘህ እንደ ወትሮህ እንድትመጣጣ ነው፤ ሌላ ምንም አልልህ። ለልጅህ እጸልይላታለሁ፤ ምንም አትሆን፤ አይዞህ..." ብለው አደግፈሩኝ።

ከዛም ብስኩትና ሻይ ቀረበልኝ። ብስኩተን እየበላሁ፥ ሻዩንም እየጠጣሁ፥ ከሳቸው ጋር ስለ ሌላ ሌላ ነገር ማውራት ጀመርን። ቀደም ሲል እናትና አባቴን አስተዋውቄአቸው ስለነበር፥ ጨዋታው ሁሉ በነርሱ ላይ አተኮረ። አባቴም እንደርሳቸው ካህን ስለሆነ፥ ሁለቱ ከንግግራቸው ይልቅ በመንፈስ ተቀራርበው፥ ስሜት ለስሜት ሲለዋወጡ፥ ገና አፍ ያልፈቱ ሁለት ሕጻናት ሲገናኙ እንደሚሆኑት ነበር የሚመስሉት - አተኩሮ ለተመለከታቸው በመንፈስ የሚያሸበሽቡ።

በመጨረሻም ተሰናብቻቸው ልሄድ ስል - "እንካ ይህንን ውሰድ፤ እኚህ የመንፈስ አባትህ ስለሆኑ፥ በደንብ እወቃቸው..." ብለው እጅግ ብዙ (ትላልቅ እና ትናንሽ) የአባታችን የቅዱስ አቡነ ተከለ ሃይማኖትን ስእሎች ሰጡኝ። እኔም ይህንኑ

ተቀብዬ ተሰናበትኳቸውና ወደ ቤቴ ተመለስኩ። እነኛን ስእሎች በደንብ አላየኋቸውም። ባለ ስድስት ክንፎች መሆናቸውን እያስታወስኩ፥ ከመጻሕፍት ገጾች መካከል ሻጥ ሻጥ አደረግኋቸው።

ከጥቂት ቀናት በኋላ ልጃችን ድና እንደወትሮዋ መጫወት ጀመረች። መቼም ችግር ሲደርስበት ብቻ የሚቀሰቀስ አይምሮ፥ የእለት እለት ፍላጎቱ ከተሟላለት ማስተዋል የሚገባውን ሁሉ ይስታልና፤ እኔም የተሰጠኝን ስእል እና ካህኑን ረሳኋቸው። አልፎ - አልፎ ከቤተ ክርስቲያን ብንሄድም፥ ካህኑ እንዳያዩኝ ስል ቀደም እያልኩ እወጣለሁ።

መጽሐፍ ቅዱስን አነባለሁ፤ ስለ ሃይማኖት ጉዳይ እከታተላለሁ፤ ነገር ግን እኔ በእምነቴ ማድረግ ያለብኝን ማንም ሰው አይነግረኝም (አያስተምረኝም) ባይ ነኝ። እውነት ነው፤ በግዴታም ሆነ በውዴታ፥ እኔን ጊዜ እንጂ ሰው አስተምሮኝ አያውቅም። ግትር ሰው ነኝ። አመጣጡና አቅጣጫው ሳይገባኝ፥ ይህንኑ የግተረኝነት ጠባዬን ይዤ ቀርቻለሁ።

የምንኖርበትን ከተማ ከለወጥን በኋላ፥ አልፎ - አልፎም ቢሆን የምንሄድበት የግብጾች ቤተ ክርስቲያን ራቅ ያለ ስለነበረ፥ ለቤታችን ቅርብ የሆነ ሌላ ቤተ ክርስቲያን ማማረጥ ጀመርን። "ቤተ ክርስቲያን ይሁን እንጂ የፕሮቴስታንትም ቢሆን ምናለበት..." እያልን፥ ወደአቅራቢያችን ወደሚገኝ ቤተ ክርስቲያን መሄድ ጀመርን።

በዚህ የባላገር ከተማ ሁሉም እርስ በርሱ የሚተዋወቅ ስለሆነ፥ አዲስ ሰው ሲያገኙ ቶሎ ብለው ወደራሳቸው ሃይማኖት ለመቀየር ነው የሚጥሩት። ይህም ሁኔታ ደስ ስላላለን፥ ለሃይማኖታችን የቀረበ የካቶሊክ ሃይማኖት ስለሆነ፥ ራቅ ያለም ቢሆን፥ ወደዛው መሄድ ይሻለናል ብለን መሄድ ጀመርን።

ይህም ድሮ በልጅነታችን ስንሰማ የነበረውን የቅዳሴአችንን ዜማ የማያስታውሰን ስለሆነ፥ መንፈሳውነታችንን የሚያረካ በማጣታችን፥ ከጊዜ ወደ ጊዜ የጎደለንን ለሟሟላት የምንችልበትን ወቅት ናፋቂዎች ሆነን ቀረን። "ከቤታችን ወጥተን ሌላ - ከውጪው አለም የሚሰውረን (ከምድራዊነታችን ወጣ የሚያደርገን)፥ ወደ እውነተኛው የሰማይ ቤት እስከንገባ ድረስ መጠለያ የሚሆን፤ የብዙ ሰዎችን መንፈሳዊ ሞቅታ የምናገኝበት ቤተ ክርሰቲያን የት ይሆን?" እያልን ስናስብ፥ እነኛ ኢትዮጵያኖች በራሳቸው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሆነው፥ ቄሱ ሲቀድስ ተሰጥኦውን የሚቀበሉ ወንዶችም ሴቶችም በአይምሮአችን ይቀረጻሉ።

አይ ! ለእኔና ቤተሰቤ ያች ትንሽ ከተማ በተለያየ መንገድ አልተስማማችንምና፤ ለከፉውም ለደጉም አበሾች የሚኖሩበት የኢትዮጵያ ተዋህዶ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ወደሚገኝበት ሥፍራ እንሂድ ብለን ከአንድ መለስተኛ - ተለቅ ያለ ከተማ ገባን፤ ከዚያም መኖር ጀመርን።

በዚህ ከተማ ቀደም ሲል ኢትዮጵያኖች ተሰባስበው፥ አንድ ቤተክርስቲያን ከፈረንጆች ተውሰው በሳምንት አንድ ጊዜ ብቻ (ያውም ከሰዓት በኋላ) የእግዚአብሔርን ቃል ይሰማሉ፤ ይጸልያሉ፤ ይዘምራሉም። ከመካከላችን፥ ያልተካኑ፥ ግን ጠለቅ ያለ መንፈሳዊ እውቀት ያላቸው ስለነበሩ፥ እነርሱ ያስተምሩን ነበር። እኛም በዕለተ እሁድ ብቻ ለሦስት ሰዓታት ያህል ብቻ በትምህርታቸው (ስብከታቸው) እየረካን፥ ጥዑመ ዝማሬዎችንም ከዘማሪዎቻችን እየሰማን መንፈሳዊ ጥማታችንን እናረካ ነበር።

እንዲህ ከባለቤቴ ጋር ኢትዮጵያኖች ወደሚሰባሰቡበት ወደ ቤተ ክርስቲያን እየሄድን፥ መንፈሳዊነታችንን በጋራ ለማጠናከር አብረን ስናነብና አብረን ስንጸልይ ቆይተናል። ብዙውን ጊዜ ኮከቤ የሰማይ ቤት ቅዳሴ ይሰማኛል ትላለች። እኔም እጅግ ደስ የሚሉ ዜማዎች በሕልሜ እሰማለሁ። እንደ እኛ የሚሰማቸው ሰዎች ብዙዎች ባይሆኑ ኖሮ፥ እኛን እንደተለዩ ሰዎች መቁጠር ይቻል ነበር። የሰው ልጅ ሁለት ስለሆነ፤ ባንድ ጎኑ ፍጽሙንና ንጹሁን፥ በሌላው ጎኑ ደግሞ፥ ከምድር የተዋሐደውን (ወይም የተደባለቀውን) ያያል - ይሰማልም።

ቅዳሴ አልባ ትምህርት (ስብከት) ከማንነታችን ጋር መጠነኛ አለመስማማት እየፈጠረ፥ የተዋሕዶ ልጆችን ሁሉ ያንጫጫቸው ጀመር። “እንተ ሰብሳቢያችን ሁንልን” ብለው መረጡኝ። ለማንነታችንም መታወቂያም ይሆን ዘንድ መጀመሪያ ለቤተ ክርስቲያናችን ስም እናውጣ ብለን ዕጣ ጣልን። እንድ ትንሽ ልጅ እጣውን አወጣ - የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ስም ብቅ አለ።

በዚህን ጊዜ፥ የግብጹ ካህን የሰጡኝ ስዕሎች የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ስዕሎች መሆናቸውን በማስታወስ፥ እንደምንም ፈልጌ ከመጻሕፍት መካከል አገኘኋቸው። ቀጥሎም፡- መንፈሳውያን የሆኑ ሰዎችን ዘርና አገር ድንበር የማይወስናቸው ቢሆንም፥ የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ውለታ በተለይ ለኛ ስለሆነ፥ ስዕላቸው ከግብጾች ቤተ ክርስቲያን ሲገኝ ለምን ከኛስ ዘንድ አይኖርም ብዬ አሰብኩ። እነኚህ ስዕሎች ከኔ ዘንድ ከሚቀመጡ ይልቅ ለቤተ ክርስቲያን ቢሰጡ ይሻላል አልኩና፥ ለአንዲት የቤተ ክርስቲያናችን ዘማሪ ሰጠኋት። ሌላ ከቤት የቀረ እንደነበር አላስታወስኩም። ነገር ግን በተለያየ ወቅት

ከምገልጣቸው መጻሕፍት ሁሉ ስዕላቸውን በማገኝበት ወቅት፥ “እንዴ! ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ?” እያልኩ መጠየቄ አልቀረም።

እኔም ያንን ቅዳሴ ለማምጣት ላይ ታች ስል ቆየሁ። እውነተኛ ነገር ይቀጥላል፤ ያድጋል፤ ይስፋፋል፤ ይጠናከራል። ሌላ በፈለግንበት ሰዓት የምንገለገልበት ከፍ ያለ የቤ ተክርስቲያን አዳራሽ ከካቶሊኮች ለማግኘት በቃን። ካህናትም ዲያቆናትም አገኘን፤ በእግዚአብሔር ቸርነት ያንን የተመኘነውን ቅዳሴ ለመስማት በቃን።

ከቤተሰቤ ጋር ቤተ ክርስቲያን በመሄድ መንፈሳዊነታችን ስናጠናክር፥ በቅዳሴውም በሚመጣ ደስታ ራሳችን ስናድስ ሰነበትን፤ “ብሩክ ስሙ ለእግዚአብሔር ወብሩክ ዘይመጽእ በስመ እግዚአብሔር/ በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ ብሩክ ነው....።” እያልን - ተሰጥኦውን እየተቀበልን። እንዲህ የመንፈስ ደስታ እያገኘን ስንኖር ብዙ ጊዜ አለፈ።

ወደ ሰዎች ሃይማኖት ስንገባ ሁለት አይነት መልክ ይታይበታል። አንደኛው መልኩ ግራ የማያጋባ፥ ቀጥ ያለ፥ ሰዎች ሁሉ በቀላሉ ሊከተሉት የሚቻላቸው፥ በሥራ ላይ ሲውል ግለሰቡን ደስ አሰኝቶ ለሕዝቦች ሁሉ (ለሕብረተሰብም) የሚጠቅም ነው። ሌላው መልኩ (ያው አንዱ ሃይማኖት) በሁለተኛው መልኩ ግራ የሚያጋባ ነው (ምድራዊ ስነ አመክኖአዊ አስተሳሰብ ሲታከልበት?)።

በአንዳንድ ነጥቦች ላይ ከባለቤቴ ጋር ስንወያይ እንዲህ አልኳት - “ስሚኝ ኮከቤ፥ እኔ የኦርቶዶክስ ሃይማኖትን አየሁ እንጂ አልተማርኩትም። ከቤቴ ቁጭ ብዬ ከአባቴ ነው ይህን ሃይማኖት ያየሁት። አባቴ መምሬ የተባለ፥ የተማረና ሃይማኖቱን ጠንቅቆ የሚያውቅ፥ ከቤተ ክርስቲያን እየሄደ ማህሌት የሚቆም፥ የሚቀድስ፤ ከቤትም ሲመጣ የሚቀድስ ነው። ባለቤቴ ሆይ! እውነቱን ስነገርሽ አድምጪኝ። አባቴ እስላሞችና ሚሲዮኖችን ወደ ታች ዝቅ አድርጎ የራሱን ሃይማኖት ከፍ ሲያደርግ አንድ ቀን እንኳን አላየሁትም - አልሰማሁትም። እኔም ይህ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት በሰዎች መንፈሳዊነት ውስጥ ምንም መበላለጥ የማያደርግ፥ እጅግ ትሁትና ታጋሽ መሆኑን ከአባቴ የተማርኩ ይመስለኛል። አንዳንድ የምሰማቸው ነገሮች ስለከነከኑኝ ነው የማዋይሽ።

ሰው የራሱን ሃይማኖት የሚያመሳስልበት ካላገኘ እንዴት ይሆናል? እኔስ የአባቴን ሃይማኖት በመከተል ወደ ተግባር ለመሸጋገር ስነሳ፥ የተለያየ አመለካከት መንፈሳዊ ማህበራችን ሲጎዳው፥ ግለሰቦችም እንደ ውስጣዊ ፍላጎታቸው ሆነው፥ ካለ እንቅፋት ወደፊት መራመድ ሲያስቸግራቸው ተመለከትኩ።”

ባለቤቴም እንዲህ አለች - "ባጠቃላይ፥ የመንፈሳዊነታችን ታሪክ፥ በትምህርት ቤት እንደምንማረው ሳይንስ፥ ታሪክና ጂኦግራፊ፥ ቀጥ ያለ፥ ስነ አመክኖአዊ (logical) ሂደት ስላለው ነው በአለም ላይ የሃይማኖትም ትምህርት የተስፋፋው። ይህ ባይሆን ኖሮ ዘልቆ ከዚህ አይደርስም ነበረ። ነገርግን በሃይማኖታችን ውስጥ ምድራዊ ጥቅሞችን ተከትሎ የሚመጣ፥ ለመንፈሳዊነት ባይተዋር የሆነ አስተሳሰብ እንደሚኖር አትዘንጋ። ጥሩ ጥሩውን እያሰብን ብንቀጥል አይሻልም?.."አለች።

እኔም "አዎ! በአዎንታዊነታችን እራሳችን የጋርዮሽ አደረግን እንጂ፤ የብቸኝነታችን ብቸኝነት፥ እንኳን ከሌላ ሰው ይቅርና ከራሳችንም ሊገነጥለን ይችላል። ለዚህ ነው የአዎንታዊነታችን ነጸብራቅ የሆነውን ሃይማኖትን በጋራ የመንፈሳዊነታችን ህልውና አድርገን የተቀበልን። ይህ ሃይማኖታችን የመግባቢያ ቋንቋችን ነው፤ መሰባሰቢያችን - ማህበራችን ነው። በእያንዳንዱ ሃይማኖት ውስጥ ሰዎች በጋርዮሽ በሚገባቸው ቋንቋ መሠረታዊ እምነቶች ተገልጸው ይገኛሉ። ሆኖም፥ አንዳንድ ጊዜ፥ የአንዳንድ ሰዎችን ኑሮ የሚቀይሱ ወሳኝና መሪ ሃሳቦች ድንገት ይቀሰቀሳሉ፤ ግን መነሻቸውና መድረሻቸው አይታወቅም። መንፈሳዊና አካላዊ ሕይወታችን ወደ አይምሮአችን በሚገቡ ሃሳቦች ይተራመሳልና ለዚህ ነው ግራ የተጋባሁት.." አልኩ።

ኮከቤም "ታዲያ'ኮ የኛ ተግባር በራሳችን ሃይማኖት ጸንቶ መቆየት ነው እንጂ፥ በሃይማኖቱ ውስጥ ሊሰገሰጉ በሚችሉ ምድራዊ ጉዳዮች ላይ ማተኮር፥ ለነፍስም ለሥጋም አአይጠቅምም.." አለች።

እኔም መልሼ እንዲህ አልኩ፡ "እውነት ብለሻል፥ ግን፥ የሰው ሃይማኖቱና እምነቱ - በረዶ በውሃነቱ ጥርት እንደሚል ካልሆነ፥ በረዶ ካፈር ጋር ሲነካካ እንደሚቆሽሽ አይነት ከሆነ ደስ አይልም። የትኛው ሃይማኖት ነው ጥርት ያለው? በሰዎች ተነካክቶ ያልቆሸሸው። የትኛው ሃይማኖት ነው ሰማያዊው? በአከራሪዎች ተቀይሶ ፈር ያልለቀቀው። የትኛው ሃይማኖት ነው ? ከአብ ከወልድና ከመንፈስ ቅዱስ ከሰማይ እንደወረደ መሬት ላይ ቁጭ ያለው።

ሌላውን የሚነቅፍ፥ የራሱን የሚያቆላምጥ፥ በእውቀቱ የሚቅጻደቅ ነው። በእውቀቱ የሚመጻደቅ፥ ለራሱ ክብርን የሚፈልግ ነው፤ ለራሱ ክብርን የሚፈልግ፥ በሰዎች ላይ የበላይነት የሚሰማው ነው፤ የበላይነት የሚሰማው የሥልጣን ጥም ያለበት ነው። የሥልጣን ጥም የሰዎች ልጆች አንዱ የምድራዊነት መለያ ጠባያቸው ነው፤ ይህም በሰይጣን በኩል ከሰማይ የወረደ ኃጢአት ነው።

ሰውን የሚነዳ፥ እግዚአብሔርን ይነዳል። የሰውን ሃይማኖት የነቀፈ፥ ሰውን ይነቅፋል፤ ሰውን የነቀፈ እግዚአብሔርንም እንደነቀፈ ይቆጠራል። የሰውን ሃይማኖት ያላከበረ፥ ሰውን አያከብርም፤ ሰውንም ያላከበረ እግዚአብሔርን አያከብርም።

በተለያዩ አቅጣጫዎች ያስብ ዘንድ የተገደደ አይምሮ ሃይማኖቱም እንደሃሳቡ ብዛት ቢበራከትበት አያስደንቅም። ግን በተለያዩ ሃይማኖቶች መካከል የሚታዩትን ልዩነቶች አንዳንድ ሰባኪዎች ነገርን (ልዩነቶችን) እያከረሩ ሰውን ከሰው መከፋፈላቸው ያሳዝናል።" በማለት የውስጤን ቅሬታ ተናገርኩ።

ኮከቤም ስለዚህ ጉዳይ በጥሞና ካዳመጠችኝ በኋላ - " የአለም ሕዝብ እንዲህ በተለያዩ ሃይማኖቶች የተከፋፈለው በፈጣሪ አምላካችን ፈቃድ ከሆነ፥ አሁንም በፈጣሪ አምላካችን ፈቃድ  አንድ ያደርገናል" ብላ ዝም አለች።

አዎ! የሰው አይምሮ የሚጸንሰው ሃሳብም እንዲሁ እጅግ የተበራከተ ሆነና፤ የሃይማኖት አይነቱ እጅግ በዛ። ለምሳሌ፥ በማንኛውም ሃይማኖት ውስጥ የሰማዩን ትታችሁ የምድሩን አስቡ የሚል የለበትም። ነገር ግን የሰማዩ ስለማይታወቅ በዚሁ በምድር ላይ ሆነንም ኑሮአችን በሰማይ እንደሚሆን አድርገን ብንወስደው ይሻላል የሚል ሃሳብ በብዙ ሰዎች አይምሮ እንዲታሰብ ሆኗል። እንዲሁም በአንጻሩ - በማንኛውም ሃይማኖት ውስጥ የምድሩን ትታችሁ የሰማዩን አስቡ የሚል የለበትም። ነገር ግን እርግጠኛው ኑሮ የሰማዩ ስለሆነ፥ የምድሩን ችላ እያልን የሰማዩን እያሰብን እንኑር የሚል ሃሳብ በብዙዎች አይምሮ እንዲታሰብ ሆኗል።

ሁሉ ነገር ግልጥልጥ ብሎ ካልታወቀ፥ የማይታወቅ ሊሆንም ይችላል። ሰው ሁሉ አውቆና ተፈላስፎ አይደለም  ወደ እምነት ሰተት ብሎ የሚገባው። ለምሳሌ አረመኔው ሞተለሚ የመንፈስ አባታችን በሆኑት በአቡነ ተክለ ሃይማኖት በኩል የተደረገውን ተአምር አይቶ አመነ፤ ተጠመቀ።

በየትም፥ በየትም፥ አምልኮተ እግዚአብሔር በሰፈነው፥
በአይሁድ፥ በእስላም፥ በክርስቲያን፥ እንዲሁም በሌላው፥
ሰው ዘራሽ ልዩነት የማይመክተው፥
የእግዚአብሔር ፍቅር እንደሆነ አቸናፊው፥
ይህን ሃቅ የሸፈነው ማነው?
እያጨበጨበ ድንቁርናን የሚጣራው።
በመስቀል ላይ በተሰቀለው፥ ምህረትን በዘራው፥

የክርስቲያናዊነት ፍቅር መሠረቱ - የፍቅር ወሰኑ የት ድረስ ነው?
የአለምን ሃይማኖት ካላቀፈው፥
የሰውን ልጅ ወንድማማችነት ካልተረዳው።
የየትኛው ሃይማኖት ነው ከእግዚአብሔር ፈቃድ የወጣው?
አንዱን ሃይማኖት ከእግዚአብሔር ገንጥሎ ለሰይጣን የሰጠው፤
ውስጥ ውስጡን በምሥጢር ሰይጣን የሚመራው።
ክርስቲያናዊነት ምኑን እውነት ሆነ፥
የፍቅርን ጥልቀቱን ከወሰነ፤
ሌላውን ከነቀፈ፥ ከተሳደበ፥ ከፈረደ።
ክርስቲያናዊነት ምኑን እውነት ሆነ?
የፍቅር ችሎታውን ከመጠነ።
ምድር የእግዚአብሔር ልጆች ማረፊያ ጊዜያዊ ቤት፥
ሁሉም ሃይማኖት ነው የሚያለሳልሳት፥
ምድራዊ ክፋቶችን የሚጋፈጥላት፥
ምሬቷን የሚያጠፋላት።

ሃይማኖትን ሰፋ አድርገው ካልተመለከቱት ይጠባል፤ ከጠበበም መግቻ የሌለው መጥበብ ሊሆን ይችላል። ሰፋ ያለ አመለካከት ያለው ጠባብ አመለካከት ያለውን ያቅፈዋል፤ ጠባብ አመለካከት ያለው ሰፋ ያለ አመለካከት ያለውን ያርቀዋል። ሰዎች በጠባቡ ሲያስቡ፥ እግዚአብሔርን ደስ የሚለው ምንድነው ብለው በመጠየቅ ፋንታ የራሳቸውን ጠባብ ስሜት በማርካት ብቻ ይወሰናሉ።

"እኔ ስለ ሃይማኖቶች ጉዳይ አስቤ - አስቤ መጨረሺያውን የማልደርስበት ስለሆንኩ፥ ለኔ የሚታወቀኝና እግዚአብሔር የገለጸልኝ እምነቴ እስከዚህ ድረስ ነው" ብሎ በራሱ እምነት የሚረጋ፥ የገዛ እምነቱንም በሥራ ለመተርጎም የሚተጋ፥ ልቡ ንጹህ የሆነ ጥሩ ሰው ነው። የሌላውን የሚነቅፍ ግን ትምክህተኛ ነው።

በሃይማኖታችን ውስጥ ስለ አንዳንድ መንፈሳዊ ጉዳዮች የምንጠራጠር ከሆነ፥ ለጥያቄዎቻችን ሁሉ በቂ የሚሆኑ መልሶች እንደሚኖሩ፤ በተለይ የመንፈስን ነገር ለመመርመር እና የበለጠ በማወቅ የገዛ እምነትን ለማጠናከር፥ በእርኩስ መንፈስ ኃይል አለመሸነፍንም ከቅዱሳን አባቶቻችን ታሪክ ልንማር እንደምንችል አንዘንጋ።

# ምዕራፍ አራት

## የሃይማኖት ተክል - በኢትዮጵያ

የአለም ሕዝቦች በያሉበት - የሰው ልጅ በሥጋውም በመንፈሱም ተፈጥሮ - አድጎና ጎልምሶ መንፈሳዊ መልክ እንደወጣላቸው እነርሱ ምስክሮች ናቸው። በኢትዮጵያችንም ይህንን (በመንፈሳዊነት የተገራ ምድራዊ አኗኗር) ማየት ቀላል ነው።

በተለይ፥ በአለም ዙሪያ፥ ከሕዝቦች መካከል የአንዳንድ ቅዱሳን አባቶች መንፈሳዊ ታሪክ እጅግ ጎልቶ ይታያል። ከነኚህም ቅዱሳን አባቶች መካከል የኢትዮጵያዊው የጻዲቁ የቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት መንፈሳዊ ተጋድሎ ለልጆቻቸው መንፈሳዊ ብርታትን እየሰጠ እስከ ዘመናችን ድረስ ስማቸውን ስንጠራ ቆይተናል (ተክልዬ እያልን - ለኢትዮጵያችን ያበረከቱትን የሃይማኖት ተክል እያስታወስን)።

"የአቡነ ተክለ ሃይማኖትን ታላቅነትና መንፈሳዊነት ከሚያስረዱት ከብዙዎቹ ነገሮች ውስጥ አንባቢ ሊረዳላቸው የሚገባው በጳጳስነት ሲገዙ ኖረው፥ በዚያው በዘበናቸው ጳጳስ እንዲመጣ መፍቀዳቸው፥ ከመጣ በኋላም፥ ለሥልጣኑ ሳይጓጉ፥ ሳይቀኑም፥ ጠብና ጦርነትም ሳያስነሱ በሰላም አስረክበው፥ እርሳቸው ወደገዳማቸው መግባታቸው ነው።" ተክለ ጻድቅ መኩሪያ 1951 (የኢትዮጵያ ታሪክ 2ኛ መጽሐፍ፥ ገጽ 19)።

ተክልዬ በእርግጥ እንደ ጴጥሮስና እንደ ጳውሎስ የኢትዮጵያ ሐዋርያ የነበሩ ናቸው (የቅዱስ ሚካኤል ጓደኛ - የሰይጣን ጠላት)። ግን፥ "እርሳቸው በእርግጥ ምን ተጨባጭ መንፈሳዊ ሁኔታን አቆዩላት ለኢትዮጵያችን?" ብለው ለሚጠይቁ፥ ገድላቸው ከተጻፈው (የጥንት ሊቃውንት እንደጻፉትና እንደተረጎሙት - 1946) በማውጣጣት ይህንን ጽሑፍ አዘጋጀን - በዚህ መጽሐፍ ለሚንሸራሸሩ ሃሳቦች ሁሉ ድጋፍ እንደሚሆንም በመመን (ካለፈውም ምዕራፍ በመቀጠል - ለማንነታችን - ለመንፈሳዊነታችን - ለሃይማኖታችን አንድ ማረጋገጫ እንደሚሆን በማሰብ)።

የማይታየውን - የሰማዩን (ከምድራዊነታችን ባሻገር ያለውን) በአይነ ሕሊና ማየትም እንደሚቻል ያልተገነዘበ፥ ትኩረቱ ከምድር በሚሰበሰብ ሃብትና ንብረት ላይ እንደሆነ ሁሉ፥ ለሰፊው አይምሮ (ግለሰብ ሊያውቅ ከሚችለው በላይ - ለጋርዮሽ

አይምሮ - ጠፈራዊ ንቃተ ሕሊና) እድል ሳይሰጡ፥ በገዛ አይምሮ ብቻ መተማመን ስለማይበቃ፥ ሰው ከምድራዊነቱ ወጣ እያለ፥ ራሱን እየተራመደ (እየዘለለ) ቢሄድ የት ሊደርስ እንሚችል ለማመልከት በፍርኃት ተጻፈ፤ ለሁላችንም መንፈሳዊ አርአያ ስለሚሆን ስለ አንድ ኢትዮጵያዊ ሐዋርያ ማስታወሺያ።

ከምድራዊነታችን ባሻገር ያለውን ለመግለጽ ከምንጠቀምባቸው መንገዶች መካከል አንዱ ምስባክ ነው። በዘመናችን ስብከት ከገንዘብ ጋር የተያያዘ ሆኗል። ከብዙ ነገረ ሃሳቦች መካከል የሰዎች ሕሊና የሚቀሰቀስበት መንገድ በመብዛቱ፥ ተለይቶም ባለመታወቁ ምክንያት፥ አንድ እውነት ሲነገር በሺህ መንገድ ይተረጎማል። ስለዚህ ሕዝቦችን አስተምሮ - ሰብኮ በአንድ አቅጣጫ መምራት አስቸጋሪ ሆኗል።

እውነት ተቀባይነት የሚኖረው ተቀባዩ በሚገባውና በሚፈልገው አይነት መንገድ ሲቀርብለት ብቻ ይሆናል። ግን ይህን ማድረግ የሚችል ማነው? በምሳሌ እያደረገ ያስተማረ ክርስቶስ ተመልሶ ቢመጣና ቢያስተምር ለዚህ ትውልድ በምን አይነት መንገድ ነው እንዲገባው የሚያደርግ?

የግለሰብ (ወይም የቤተሰብ) ሕይወት ከምድራዊነት ይልቅ ወደ ሰማያዊነት እየተጠጋ እንደሚሄድ ሁሉ፥ ሰው ሁሉ በራሱ የሕሊና ነፃነቱ ሰላምና ጸጥታውን እንዲያስከብር የመጨረሺያ - ዝቅተኛ ከሆነው ተከባብሮ አብሮ የመኖር ግንዛቤአዊነት በመነሳት፥ በሕዝቦች መካከል ምን ጊዜም ምክንያታዊ ልዩነቶች መኖራቸውን ማወቅ (መገንዘብ)፥ ማመን፥ መፍቀድና፥ ማክበር፤ ቀጥሎም ከነልዩነቶች አብሮ ለመኖር የሚያበቃ ፍቅር እንዲኖር የሚያበቃ ትምህርት (ስብከት) መስጠት አስፈላጊ ይሆናል።

በኢትዮጵያችን - በደርግ ጊዜ - ክህደት ተስፋፍቶ ስለነበር፥ ኢትዮጵያ ታመመች። የታመመችውን ያህል ጤንነቷ ተመልሶ ደህና ልትሆንልን ስትል፥ በዚህ የቀና ሰይጣን እየበረታብን እርስ በርሳችን ተስማምተን እንዳንኖር በመካከላችን ሥራውን እየሠራ ይገኛል። በተክልዬና በመሳሰሉ ጻድቃን ጸሎት መንፈሳዊነቷ ያለመለመ ይህች አገር እንደገና መንፈሳዊ ድርቀት ውስጥ እንዳትገባ መከላከል የሁላችንም ኃላፊነት ነው።

ተክልዬ በኢትዮጵያ ያከናወኑትን መንፈሳዊ ተግባራት ኢትዮጵያውያን ቢያውቁት፥ ምናልባት የርሳቸው መልካም መንፈስ የበለጠ ያፋቅረን ይሆናል። የተክልዬን ታሪክ ማወቅ አስፈላጊነቱ፥ ለኢትዮጵያ ገዳማትና ቤተ ክርስቲያናት ብቻ አይደለም - ለመላው የአለም ሕዝብ ጭምር ነው እንጂ።

በጣልያን አገርና በአለም ዙሪያ ታዋቂ የሆነው የቅዱስ ፍራንቼስኮን (Francis of Assisi) ምሳሌነት - የሮማ ካቶሊክ ሃይማኖት ቢከተል ኖሮ፥ ይህች

አለም እንዴት ያማረባት ትሆን ነበር እየተባለ ይነገራል።[11] ሰዎች እንደ ቅዱስ ፍራንቼስኮ እና ሌሎችም ጻድቃን - ቅዱሳን አባቶች በመንፈሳቸው ጠንካሮች ሲሆኑ፥ በአለማችን ፍጹም ሰላም እንዳይመሠረት የሚከላከሉ እርኩስ መናፍስትን ያጠፏቸዋል።

የጻዲቁ እና የቅዱሱ የአቡነ ተክለ ሃይማኖትን ታሪክ (ገድል) ጸጳሳት፥ ቀሳውስትና ዲያቆናት እንዲሁም ምዕመን ተመልክተው - "ከእኖስ የጎደለው ምንድነው?" ብለው ቢጠይቁ፥ ሃይማኖትን በተግባር ለመግለጽ እንደ እርምጃ ሄዱ።

በታሪካቸው ብዙ ተመሳሳይነት ያላቸው ሁለት ቅዱሳን (ቅዱስ ፍራንቼስኮና ቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት) በአንድ ዘመን አካባቢ ነበር የኖሩት።[12] ሁለቱም ሃብት ንብረታቸውን ለድሆች አከፋፍለው ነበር የምንኩስናን ኑሮ የጀመሩት። ሁለቱም እንስሳትን ያዙና ይገስጹ ነበር።[13] ሁለቱም በጸሎታቸው ይታወቃሉ፤ ሁለቱም የሥጋቸው መጎዳት የማይሰማቸው በመንፈሳቸው ኃይል የሚንቀሳቀሱ - የመንፈስ ጸሐዮች ስለነበሩ፥ ሁለቱም በጣም ብዙ የመንፈስ ልጆች አፍርተዋል።

በጣልያን የካናሪያና ያካባቢው ሰዎች በፍራንቼስኮ ሰበካና ትምህርት እየተሳቡ፥ ሥራቸውን እየተው ፍራንቼስኮን ተከተሉት። በፍራንቼስኮ ትምህርት እጅግ በመመሰጥ የተጋቡ ባልና ሚስት "እየተፋታን እንመንን" እያሉ ፍራንቼስኮን ይጠይቁት ነበር። እርሱ ግን - በትዳር ላይም ሆኖ እግዚአብሔርን ማገልገል እንደሚቻል አስተማራቸው።

የወንድም ፍራንቼስኮ ገዳማት፥ በርሱም የተሠሩ ሆስፒታሎች እስከዛሬ ግልጋሎት እየሰጡ ነው። በቅዱስ ፍራንቼስኮ ዘመን አንድ ጳጳስ ባለማዕረግ የሆነውን ቀሚሳቸውን አውልቀው የቅዱስ ፍራንቼስኮን ባለ ወይን ጠጅ ቀሚስ ለበሱና እንዲህ ብለው ተናገሩ - "ይህንን ቀሚስ በመልበሴ ማዕረግ አገኘሁ፤ ከጽጽስና ማዕረጌ ላይ አንድ ወይን ጠጅ አከልኩበት፤ ግን ይህን ማድረጌ ምናልባት የማይገባኝን ክብር ለራሴ መስጠት ይሆንብኛል በማለት እፈራለሁ....።"[14] ይህን የወይን ጠጅ ቀሚስ (ምሳሌነቱ

[11] ስለ ፍራንቼስኮና ሥራዎቹን ከሚገልጹ ጽሁፎች።

[12] ቅዱስ ፍራንቼስኮ (1181 -1226) ቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ( 1160 – 1259 ዓ.ም. አካባቢ)።

[13] ተኩላዎች የገበሬዎች ለማዳ እንስሳትን እየበሉ፥ ሕጻናትንም እስከ ማሳደድ በደረሱበት ወቅት፥ ቅዱስ ፍራንቼስኮ ገስጿቸዋል (እንዳይተናኮሉ አዟቸዋል)። ተክልዬም ዝንጀሮዎች ሰብል እያበላሹ፥ እመበለቶችን እየተደባደቡ ባስቸገሩበት ወቅት ገዝተዋቸዋል (ከመሞታቸው በፊር ግዝቱን ፈተዋል)።

[14] ከፍራንቼስኮ ድረ ገጽ።

የክርስቶስ ደም)፥ እየለበሱ፥ ምድራዊ ክብራቸውን ሁሉ ጥለው የመነኑ ብዙዎች ነበሩ። የገዳማቱም ቁጥር፥ አባላቱም ተበራከቱ።

"የወንድም ፍራንቼስኮ መቀነት እንኳን እኔን፥ የንጉሡንም ቤተሰብ ቢሆን ያስራል" እያሉ፥ ፍራንቼስኮን በመከተል ወደ እግዚአብሔር የተጠጉ እጅግ ብዙዎች ነበሩ። ይህን ቁጥርጥር መቀነት የፈረንሳይ ንጉሥ፥ የሃንጋሪ መግሥት ታጥቀውታል[15]።

የሮማ ቤተ ክርስቲያን የፍራንቼስኮን ቅዱስነት እንደተቀበለ ሁሉ፥ የአቡነ ተክለ ሃይማኖትንም ቅዱስነት በመቀበል፥ በቅዱሳኑ መንፈሳዊ መዝገብ (ስንክሳር) ላይ በክብር አሥፍሯል።[16]

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታዮች ካጠገባቸው ምሳሌ የሚሆንላቸው ሰው ቢያጡ፥ የጻዲቁን የአቡነ ተክለ ሃይማኖትን ሃይማኖታዊ ተግባራት ተመልክተው፥ እነርሱ ከሚያውቁት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እምነት ጋር ያመሳስሉበታል። የሌሎች ሃይማኖት ተከታዮችም (እስላም ቢሆንም ፕሮቴስታንት) ሕዝቦችን በጋራ የሚያስተሳስር የእግዚአብሔር ፍቅር ብቻ መሆኑን እንደሚገነዘቡ ሁሉ፥ ይህም የእግዚአብሔር ፍቅር በኢትዮጵያ እንደነበረ፥ አሁንም መኖሩን፤ ይልቁንም፥ ማንኛውም ሰው በእምነቱ ከጸና፥ በመንፈሱም ከበረታ - ልክ እንደ ተክልዬ - ከዚያም በላይ ቢሆን፥ እርኩስ መንፈስን እያሳደደ ከሰዎች ማባረር እንደሚችል ያስተውላሉ።

እግዚአብሔር የሚቀርበውንና የሚያገለግለውን ሰው እርሱም የሚያፈቅረው መሆኑን፤ ይህንንም ፍቅር ሰዎች እንዲያውቁት - እንዲያወሩት እንዲጽፉትም ይፈልጋል።

ከጥንት ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ፥ በአገራችንም ሆነ በውጪ አገር አያሌ ህመምተኞች በእርኩስ መንፈስ ላይ ሥልጣን ወደተሰጣቸው ጻድቃን - ቅዱሳን ዘንድ እየሄዱ ፈውስን እንዳገኙ አስተውለናል። አቡነ ተክለ ሃይማኖትም ከረዳታቸው ከቅዱስ ሚካኤል ጋር እየሆኑ ሰይጣንን በተደጋጋሚ አቸንፈውታል። ታዲያ፥ እንዲህ ያለው ታሪክ ለዘመኑ ሰው (አዋቂዎች ነን ባዮች፥ ፈላስፎችና ሳይንቲስቶችም) የማይጥም ነው ብሎ ከማለፍ ይልቅ፥ በውስጡ ምን ጥሩ ነገር ይገኝበታል ብሎ መመራመር ነው የሚሻለው።

---

[15] ከፍራንቼስኮ ድረ ገጽ።

[16] ተክለ ጻድቅ መኩሪያ 1951 (የኢትዮጵያ ታሪክ 2ኛ መጽሐፍ)

ከአይምሮ በሚፈልቀው ርዕዮት (ወይም ስነ አመክንዮ) ብቻ ተወስኖ የሚሄድ ሃይማኖታዊ ትንተና መልሶ ወደ ምድራዊነት ይከታል፤ የተክልዬን ታሪክ (ገድል) መመልከቱ ግን፥ ከሚታየው አካላዊ አለም ሌላ በአካል የማይታይ መኖሩን ይናገራል።

ጻዲቁ አባታችን ቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት፡- 1) ቤተ ክርስቲያን አሠርተው፥ 2) ቀድሰው፥ 3) አስተምረው፥ 4) አጥምቀው፥ 5) አቁርበው ሐዋርያዊ ግዳጃቸውን ተወጥተዋል። እነኚህን ተግባራት እንዳያከናውኑ ተከላካይ ነበረባቸው። ግን ከእግዚአብሔር በተሰጣቸው የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ሰይጣንን በማቸነፍ፥ ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን ደስ አሰኝተዋል።

አቡነ ተክለ ሃይማኖት ያለፈውን ሁሉ እየረሱ፥ የጌታን መስቀል በመመልከት፥ በተስፋ ወደፊት ብቻ መሄድና ክርስትናን ማስፋፋት የአንድ ክርስቲያን ተግባሩ መሆኑን ያስተማሩን አባት ናቸው። ገድላቸው ሲነበብ ያስደንቃል፥ ያስለቅሳልም። ይህንን ድንቅ ታሪካቸውን በደንብ በታሪካዊ ማስረጃዎች ተደግፎ በታሪክ መጽሐፍ ታትሞ ለተማሪዎች አለመቅረቡ በጣም ያሳዝናል።

ከዚህ ከዘመኑ ሰው መካከል አንድ መልካም ተአምራታዊ ሥራ የሠራ ሰው ቢኖር - ያ ሰው በሚኖርበት አካባቢ፥ ከተቻለም በአለም ዙሪያ የሠራው ሥራ እንዲነገርለት፥ እንዲታወቅለትና እንዲከበርበት፥ አድናቆትን አትርፎ - ከሰው ሁሉ በላይ ሆኖ መታየትን ይመኛል። ነገር ግን ተአምር የሚሠራ እግዚአብሔር ነው እንጂ ሰው አይደለምና፤ እግዚአብሔር በሰዎች መከበር ሲገባው፥ ሰዎች የእግዚአብሔርን ክብር ነጥቀው፥ እነርሱ ሊከበሩበት አይገባም። እንዲሁም፥ በእግዚአብሔር ፈቃድ በአቡነ ተክለ ሃይማኖት በኩል የተሠራ ተአምር ከአንድ አካባቢ ተወርቶ በሰዎች ዘንድ ሰብአዊ ክብር ወደ አባታችን ሲመጣ፥ እርሳቸው ታላቅ ሃዘን እየተሰማቸው፥ ሊኖሩበት የፈቀዱትን ሥፍራ እየለቀቁ ወደ ሌላ ሥፍራ ይሄዱ ነበር። ታዲያ ስለርሳቸው ታሪክ እና በርሳቸው በኩል ስለተሠራ ተአምር ሁሉ እንዴት በግልጽ ይታወቃል?

ኤሌይን መሬይ እስቶን የተባለች የውጪ አገር ዜጋ ስለ አባታችን ታሪክ ስዕላዊ መጽሐፍ አዘጋጅታ ለውጪ አገር ልጆች መማሪያ ሆኗል። የሴቲቱ አላማ - አንድ መንፈስ ጠንካራ መነኩሴ በእግዚአብሔር እርዳታ ምን ያህል ታላቅ ወንጌላዊ ሥራን መሥራት እንደሚችል ለማስረዳት ነው።

ተክላ (Tekla) ብላ የምትጠራው (ተክልዬ) ወጣ ገብ፥ ገደል፥ ተራራና ሸለቆ የሚበዛበትን የኢትዮጵያ አውራጃዎች በስብከቱ ያዳረሰው በአንድ የእግዚአብሔር ተአምር መሆን አለበት በማለት የተረከችው ይህንኑ ያረጋግጣል።

የተክልዬ ታሪክ በስንክሳር፥ በተአምረ ማርያም፥ በሌሎችም መጻሕፍትም ባጭሩ ተመዝግቦ ይገኛል፤ በአረብኛ፥ በእንግሊዝኛም ተጽፏል።

ለሁላችንም መንፈሳዊ አርአያ የሚሆን የአባታችን ታሪክ - እየተባዛ ለሰው ሁሉ ቢዳረስ መልካም ነው። ኢትዮጵያም እንዲህ ጻድቅ የሆነ ሐዋርያ ነበራት ብለን በርሳቸው እንድንኩራራባቸው አይደለም፤ እርሳቸው ውዳሴ ከንቱን የማይወዱ ትሁት አባት ናቸውና። ከእርሳቸው ታሪክ ትምህርት አግኝተን ብንጠቀምበት፥ እግዚአብሔርም ደስ ይለዋል፤ ለአምላካችን ክብር ምስጋና ይድረሰው።

በአለም ዙሪያ መንፈሳዊ ሥራዎች በሕያውነት ሲንቀሳቀሱ እናያለን። ግን የቅዱሳን ገድል፥ ብዙውን ጊዜ (ወይም አንዳንዴ) ከብዙዎቻችን (ወይም ከአዳንዶች) አይምሮ ዘልቆ አይገባም (አይታመንም)። እንዲሁም፥ በገድላቸው የተመዘገበውን የአቡነ ተክለ ሃይማኖትን ታሪክ የዘመኑ ሰው በቀላሉ አይቀበለውም ብሎ ከማለፍ (ከመተው) ይልቅ፥ ታሪክ መዝጋቢዎች አለማዊ ታሪኮችን በማስረጃ እያስደገፉ ለመጻፍ ከሚያደርጉት ጥረት በጥቂቱ ለመንፈሳዊ ታሪኮቻችንም ቢያደርጉ (ቅዱሳት መጻሕፍት እንዳሉ ሆነው)፥ የዘመኑ ሰው የጎደለውን እንዲያሟላ ይረዳው ይሆናል።

*ኦ! እግዚአብሔር የፈጠርከኝ አምላኬ - ያንተን ሥራ በተዘዋዋሪ ለመግለጽ እስከሆነ ድረስ፥ እባክህ የአባታችን የቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖትን ገድል ስለ ገድላቸው ከተጻፈው ውስጥ ዋና ዋናውን - ለሰዎች ትምህርት ሊሆን የሚችለውን በመጥቀስ እንዳዘጋጅ ፍቀድልኝ።*

በኢትዮጵያ ውስጥ በሸዋ ክፍለ አገር ዞረሬ ከምትባል አውራጃ እግዚአብሔርን በመውደድና ትእዛዙን በመፈጸም፥ ድሆችን በመርዳት፥ ጥሩ ሥራዎችም በመሥራት የተሰማሩ ጸጋ ዛፍ እና እግዚእ ሐረያ የተባሉ ደጋግ ባልና ሚስት ይኖሩ ነበር። እነኚህ ፍቅረኞች እግዚአብሔር ልጅ ይሰጣቸው ዘንድ የዘወትር ጸሎታቸው ነበር።

በዚሁ በሸዋና ዳሞት አውራጃ ውስጥ፥ ቤተ ክርስቲያን በማቃጠል፥ የሰው ሚስት በመቀማትና ልዩ ልዩ አስጸያፊ ሥራዎችን በመሥራት የታወቀ፥ ለጣኦት የሰገደ፥ ሞተለሚ የተባለ አረመኔ ንጉሥ ነበር።

ከእለታት አንድ ቀን፥ ይህ ሞተለሚ የተባለ አረመኔ ከወታደሮቹ ጋር በመሆን፥ ዞረሬን በመከበብ፥ የተለመደ ዘረፋውን ፈጸመ። ወታደሮቹም ጸጋ ዛፍን ለመግደል ሲያሳድዱት፥ ቅዱስ ሚካኤል ደረሰለትና ዞረሬ ከሚገኘው ቤተ ክርስቲያን አስገባው።

የሞተለሚ ወታደሮች የጸጋ ዛፍን ባለቤት - እግዚእ ሐረያን ባዩአት ጊዜ - ይህች እጅግ የተዋበች ሴት ለንጉሣችን ትገባለች በማለት ማርከው ለንጉሡ አመጡላት። ንጉሡም ባያት ጊዜ እጅግ ደስ አለውና "ይህችንስ ቤተ መንግሥቴ በተመለስኩ ጊዜ በወግ በማእረግ ነው የማገባት..." በማለት፥ እስከዛው ድረስ በነግሥታቶች ማእረግ ለብሳና አጊጣ፥ ካጠገቡ ሳትርቅ እንድትቀመጥ አደረገ።

በቁጥር አስር ለሚሆኑ ሚስቶቹ እና ለሕዝቡ፥ በአንድ ሳምንት ውስጥ እጅግ ትልቅ ድግስ ከቤተ መንግሥቱ እንዲዘጋጅ ትእዛዝ አስተላለፈ። በትእዛዙም መሠረት ድግሱ ተዘጋጀ። እግዚእ ሐረያ ግን በሃዘንና በጭንቀት ማቀቀች። “አቤቱ ፈጣሪዬ፥ የባለቤቴን (የወዳጄን) መሃላ አስበህ ከዚህ ሰይጣን አላቀኝ፤ እባክህ! እባክህ!...” በማለት ምርር ብላ እያለቀሰች፥ እግዚአብሔርን ከዚህ ጉድ እንዲያወጣት ለመነችው።

የሰርጉ ስነ ስርዓት የሚፈጸምበት ቀን ደረሰ። የሞተለሚ ቤተ መንግሥት በሚገኝበት ማልደረቢ ከተባለ ሥፍራ እግዚአ ሐረያን አመጧት፤ ከቤተ ጣኦትም አስገቧት። የጋብቻው ስነ ስርዓት ሊጀመር ሆነ። ብዙ ሕዝብ በተሰበሰበበት፥ ከዚህ ጣኦት ካለበት ሥፍራ፥ በቅድሚያ ለጣኦታት እንድትሰግድ ታዘዘች።

እርሷም - “አምላኬ፥ አምላኬ፥ አባክህ - እባክህ ከዚህ አረመኔ አድነኝ...” እያለች በሆዷ ከመጸለይ አላቋረጠችምና፤ በድንገት ቅዱስ ሚካኤል ደርሶ፥ ከተሰበሰበው ሕዝብ መካከል መንጥቆ፥ ወደ አንዲት መንደር - ባለቤቷ ከሚገኝበት ከቤተ ክርስቲያን አደረሳት።

ከዚያም መንደር ሁለቱ ፍቅረኞች ተደብቀው ቆዩ። ልጅም ተጸነሰና፥ ታህሳስ 24 ቀን ህጻን ከጸጋ ዛፍና ከእግዚእ ሐረያ ተወለደ። ይህም ህጻን በአርባ ቀኑ ተጠመቀ። ስሙም ፍስሐ ጽዮን ተባለ። ትርጓሜውም የጽዮን ደስታዋ ማለት ነው።

ፍስሐ ጽዮን ገና ህጻን ሳለ፥ በሸዋ አውራጃ በተለይም በዞረሬ ጽኑ ረሃብ ገባ። እናትና አባቱም የሚካኤልን በዓል ለማክበር፥ መደገሻ የሚሆን በማጣታቸው፥ እጅግ አዝነው ሲጸልዩ፥ ፍስሐ ጽዮን ተመለከተ። ወዲያውም በእንቅብ በሚገኘው የእህል ዱቄት ውስጥ እጁን ሲያስገባ እንቅቡ እየሞላ ይፈስ ጀመር። ይህን በመመልከት እናቱ ከቤት ውስጥ ያለውን ባዶ እንቅብ ሁሉ አቀረበችለት። ሁሉንም በዱቄት ሞላው። ዳግመኛም ቅቤ ያለበትን ማሰሮ አቀረበችለትና እጁን እንደ መስቀል አማትባ ከማሰሮው ከተተችው። ማሰሮውም በቅቤ ተሞላ። ከዛም በኋላ፥ የሚካኤልን በዓል መጋቢት 12 ቀን ለተቸቸገሩ እና ላገሬው ሰው በመደገስ ታላቅ ግብዣ አደረጉ። የረሃቡም ዘመን እስኪፈጸም ድረስ የተቸገሩትን እያበሉ ኖሩ።

ተስፋ ጽዮን በሰባት ዓመቱ ዳዊትን ተማረ። የብሉይና አዲስ መጻሕፍትን አጠና። በአስራ ስድስት ዓመቱ አቡነ ጌርሎስ ከተባለ ጳጳስ ድቁናን ተቀበለ። ከጥቂት ዓመታት በኋላ ካህን በመሆን ተሾመ። ከዛም በሸዋ አውራጃ ሁሉ የሊቀ ካህናትን ማእረግ ከአቡነ ጌርሎስ ተቀበለ።

የፍስሐ ጽዮን እናትና አባት፥ በአንድ ሳምንት ውስጥ በመከታተል ከዚህ አለም ተለዩ። እርሱም ካለ እህትና ካለ ወንድም በመፈጠሩና ብቻውን በመቅረቱ እጅግ ሃዘን

ገብቶት ሳለ፥ እግዚአብሔር አጸናው። የክህነቱንም ሥራ በትጋት እየፈጸመ፥ በእናትና አባቱ ቤት ለሰባት ዓመታት ተቀመጠ።

ከእለታት አንድ ቀን መንፈስ ቅዱስ አናገረው፤ እንዲህም አለው። “ለካህናት ተገቢ የሆነው ሥራ፥ ሃይማኖትን ማስተማርና ሕዝቡን መምከር ነውና፤ ከእንግዲህ ሰውን ወደ እግዚአብሔር ለመመለስ እንድትታገል ይሁን። ይህንንም በምታደርግበት ወቅት ልዩ የመንፈስ ኃይል እግዚአብሔር ሰጥቶሃል። ከእንግዲህ ስምህ ፍስሐ ጽዮን በመባል ፈንታ ተክለ ሃይማኖት ይባል።” ብሎት ተለየው።

ወዲያውም ፍስሐ ጽዮን ገንዘብ ንብረቱን ሁሉ አንድ ሳይቀር ሰብስቦ፥ ለድሃ አከፋፈለ፤ ለቤተ ክርስቲያንም ሰጠ። ተክለ ሃይማኖት እየተባለ በመጠራት፥ በክርስቶስ ስም በሰማዕትነት ለመሞት የተዘጋጀ ሆነ። የሐዋርያትን ሥራ፥ ወንጌልን ለማስተማር ከቤቱ ወጥቶ ሄደ፤ የሚቀድመውና የሚከተለው ሳይኖር፥ ወደ ሰልፍ እንደሚገባ አርበኛ፥ አንደ ትጉህ ገበሬ ሆኖ፥ “ለሰው አለምን ሁሉ ቢገዛ፥ ነፍሱን ግን እንዲጎዳ ከሆነ፥ ምን ይጠቅመዋል፥ ምን ይረባዋል” እያለ። “.....ነፍሱንም ስለኔ የሚያጠፋ ያገኛታል።” (ማቴ.10፡39) የሚለውን ጥቅስ - ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረውን ሁሉ እያሰበ። የሐዋርያትን ፈለግ በመከተል፥ ወንጌልን ለማስተማር ሲል፥ ዳግመኛ ወደ ቤቱና ንብረቱ ሳይዞር ወደፊቱ ገሰገሰ - ከክርስቶስ ደቀ መዝሙሮች (ከሐዋርያት) ተግባር ጋር ተመሳሳይ የሆነ እውነተኛ ክርስቲያናዊ ተግባሩን ለመጀመር ሲል፥ ቤቱ እንደተከፈተ ትቶ ሄደ።

አባታችን አቡነ ተክለ ሃይማኖት ጣኦታትን የሚያመልኩ ሰዎች መኖራቸውን ከሰሙ ወደዛው ይገሰግሳሉ[17]። ከዛም ቶሎ ለሚገባቸውና ለሚቀበሏቸው ሰዎች የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ትምህርት በማስተማር፤ ቶሎ ለማይገባቸው ደግሞ፥ ልዩ ልዩ ተአምራትን በማሳየት ወደ ክርስትና እምነት ይመልሳሉ።

በከተታ አውራጃ እያስተማሩና እያጠመቁ፥ ኢጋንትን እያወጡና ድውያንን እየፈወሱ ለሦስት ዓመታት ኖሩ። ከዚህ አውራጃ ከወጡ በኋላ ግን፥ በተአምር ካልሆነ በስተቀር በእግር ተሄዶ ማዳረስ የማይቻል አያሌ ሥፍራዎችን በማዳረስ አስተምረዋል። በገድላቸው ላይ እንደተጻፈው ሁሉ፥ በብርሃን ሰረገላ ሆነው ነበር የሚጓዙት።

ዊፋት ከምትባል ተራራ ኢጋንትን ካጠፉ በኋላ ሕዝቡን አስተማሩ፤ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጠመቋቸው። ሕዝቡንም ቤተ ክርስቲያን እንዲሠሩ አድርገው የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብረ ሥጋ ወደሙን አቀበሏቸው።

[17] ካሁን በኋላ አንቱ እንበላቸው።

በአናርእት አውራጃ ጣኦታትን አጠፉ፤ ቀጥሎም አስተማሩ። በጉራጌ አገር ቢለት ከምትባል ሥፍራ ጣኦታትን ለማጥፋት ባደረጉት ትግል አጋንት በድንጋይ በመቀጥቀጥ ሊገድሏቸው ሲሉ፥ ጓደኛቸው የሆነው ቅዱስ ሚካኤል ደርሶ አዳናቸው። ሚካኤልም - "አጋንት ሲመጡብህ ለምን በመስቀል አማትበህ አታባርራቸውም?" ቢላቸው፥ "ሥጋን የሚገድሉትን ነፍስን ግን መግደል የማይቻላቸውን አትፍሩ፤ ይልቅስ ነፍስንም ሥጋንም በገኃነም ሊያጠፋ የሚቻለውን ፍሩ።" (ማቴ. 10፡28) የሚለውን ጥቅስ - ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረውን በማስታወስ - "ሥጋዬን ቢገድሉ ነፍሴን የት ያገኛታል?" በማለት ካለ ፍርኃት መለሱለት።

በመጨረሻም አባታችን አቡነ ተክለ ሃይማኖት ለአጋንት የሚሰዋበትን ሥፍራ በማፈራረስ፥ ተአምራቶችን ሁሉ በማሳየትና በማስተማር፥ የአካባቢው ሰው ወደ እግዚአብሔር እንዲመለስ አድርገዋል።

በዳሞት አውራጃ ዝባፈተን ከሚባል ተራራ ጣኦታትን በማፈራረስ፥ ሕዝቡን ማስተማር ጀመሩ። በዚያን ጊዜ ሽማግሌዎችና መኳንቶች ተናደዱ፤ አባታችንንም ይዘው ለአገረ ገዢው (ለክፍለ አገር አስተዳዳሪው) አስረከቡ። "ይህንን ሰው ከንጉሡ እስክናደርሰው ድረስ ጠብቅ..." ብለው፥ አገረ ገዢውን (በኋላ አባታችን ስላጠመቁት ገብረ ዋህድ የተባለውን) አስጠነቀቁት።

ገብረ ዋህድ ግን፥ ልጁን ከሚጥል በሽታ አባታችን አድነውለት ስለነበር፥ ከቤቱ አስቀመጣቸው። እርሳቸውም በዳሞት አካባቢ የታመሙትን እየፈወሱ፥ የክርስትና ሃይማኖትን እያስተማሩ ለሦስት ወራት ያህል ተቀመጡ።

በዚህን ጊዜ፥ ያገር ሽማግሌዎችና መኳንንቶች እንደገና ተናደዱ። ከገብረ ዋህድ ቤትም በመምጣት - "ጠብቅ ያልንህን ሰው ከንጉሡ ስለምናቀርበው አሁን አምጣ.." ብለው ጠየቁት።

ገበረ ዋህድም - "እኔም አብሬ ከርሳቸው ከአባቴ ጋር እሞታለሁ እንጂ አልሰጣችሁም.." አላቸው። ያገር ሽማግሌዎችና መኳንንቶች እጅግ ተቆጡ። ይህንም ጉዳይ ፈጥነው ለንጉሡ ነገሩት። ንጉሡም - "ሁለቱንም አስራችሁ አምጡልኝ.." ብሎ አዘዘ። ሁለቱም ታስረው ወደ ንጉሡ በሚሄዱበት ወቅት፥ ገብረ ዋህድ ለአባታችን ስለ ንጉሡ ታሪክ እንዲህ እያለ ያጫውታቸው ጀመር።

"ይህ ሞተለሚ የተባለ ንጉሥ፥ ከሃያ አምስት ዓመታት በፊት አንዲት የተዋበች ሴት ወዶ ነበር። እርሷንም ለማግባት የሰርግ ስነ ስርዓት በማከናወን ላይ እንዳለ፥ ድንገት ባልታወቀ ኃይል ካጠገቡ ጠፋችበት። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አእምሮውን አጣ። ምናልባት እርስዎ ከዚህ በሽታው ቢያላቅቁት በነጻ ይለቀን ይሆናል። አለበለዚያ ግን ሁለታችንም እንደሚገድለን አልጠራጠርም....።"

ተክልዬና ገበረ ዋህድ እንዲህ እያወሩ፥ ከቤተ መንግሥት ደረሱ። ንጉሡም ባያቸው ጊዜ በንዴት አስር ሰዎች መረጠና - “በሉ እነኚህን ሁለት ባለጌዎች ፈጥናችሁ ከሁለት ቀፎ ክተቱና፥ ቀፎውን በደንብ ዘግታችሁ በእርጥብ ቁርበት ጠቅልላችሁ፥ ጦመ ግራር ከተባለው ገደል ወርውራችሁ ጣሉልኝ...” ብሎ አዘዘ።

በትእዛዙም መሠረት ተፈጸመ። ዳሩ ግን አባታችንና ገብረ ዋህድ ከጣሉአቸው ሰዎች አስቀድመው፥ ከንጉሡ ፊት ለፊት ቆመው ተገኙ። የጣሉአቸው ሰዎች ሲመለሱ ባዩአቸው ጊዜ ለጊዜው ተደናገጡና - “እኛ ከእንግዲህ ወዲያ በነኚህ ሰዎች አምላክ ለማመን ወስነናል..” አሉ።

ንጉሡም ሳይጥሉ ጥለናል ብለው የዋሹት መስሎት በንዴት - ጣሉ ከተባሉት ጭምር፥ አስራ ሁለት ቀፎ ተዘጋጅቶ፥ ሁሉንም፥ ብዙ ሰው በምስክርነት በሚገኝበት፥ ወደ ገደል እንዲከቷቸው ትእዛዝ አስተላለፈ።

በትእዛዙም መሠረት ተፈጸመ። ነገር ግን ከጣሉአቸው ሰዎች አስቀድመው፥ አስራ ሁለቱም ሰዎች ከንጉሡ ፊት ለፊት ቆመው ተገኙ። በዚህን ጊዜ ሞተለሚ እጅግ ከመናደዱ የተነሳ፥ በያዘው ጦር አባታችንን ለመውጋት ሲወረውር፥ ጦሩ ከእጁ ላይ እንደ ሰም ተጣብቆ ቀረ።

ሞተለሚ ተክልዬን ለማስገደልና ለመግደል ያደረገው ጥረት ሁሉ ከሸፈበት። እሱው ራሱ ከጦሩ ጋር ተጣብቆ፥ በሽተኛ ሆኖ ተሰቃየ። በዚህን ጊዜ፥ ገብረ ዋህድ የሚከተለውን አስታራቂ ሃሳብ አቀረበ፡-

“ንጉሡ የሚያምንባቸው አዋቂዎችና ጠንቋዮች (ማርያኖች) ሁሉም ይምጡና ንጉሡን ለማዳን የሚቻላቸውን ያድርጉ። ከተክለ ሃይማኖትና ከማርያኖች ንጉሡን ለማዳን የተቻለው እንዳይሞት፥ ለማዳን ያልተቻለው እንዲሞት ይሁን።”

ንጉሡ በገብረ ዋህድ ሃሳብ ስለተስማማ ማርያኖች ተጠርተው እንዲመጡ አደረገ። ንጉሡን የማዳን ሙከራ በማርያኖች ተጀመረ። ማርያኖች የተቻላቸውን ሁሉ አደረጉ፤ ግን ንጉሡን ማዳን አቃታቸው። ቀጥሎም አባታችን ተጠሩ። እርሳቸውም- “በጌታዬ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ከደዌህ ዳን...” ብለው የሞተለሚን እጅ መዳሰስ ሲጀምሩ፥ ወዲያው ጦሩ ከጁ እየተላቀቀ፥ የሰለለ ክንዱም እየዳነ፤ አይምሮውም እየተስተላከለ መጣና፥ ፈጽሞ ጤነኛ ለመሆን በቃ። (ድንቅ ነው የእግዚአብሔር ሥራ)።

ሞተለሚ አይምሮው ሲመለስለት፥ ካሁን በፊት የነበረበትን ሁኔታ እያገናዘበ፥ ስለ አባታችንም በማጠያየቅ ማንነታቸውንም ከተረዳ በኋላ፤ አባታችንን እንዲህ ሲል ጠየቃቸው - “እባክህ እናትና አባትህ ያወጡልህን ተስፋ ጽዮን የተሰኘውን ስምህን ለኔ ስጠኝ፤ እኔ ደግሞ በምትኩ ሺህ ወርቅ ልስጥህ....” ብሎ ጠየቃቸው። እርሳቸውም -

“የመንግሥትህን እኩሌታ ብትሰጠኝ እንኳን የቀድሞ ስሜን በፈቃዴ አልሰጥህም። ነገር ግን በፈጣሪዬ ስም አምነህ ብትጠመቅ ካለ ዋጋ እሰጥሃለሁ...” ብለው መለሱለት።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ማርያኖች ውሸታሞች፥ አባታችን ግን እውነተኛ እንደሆኑ የሚገልጹ አያሌ ተአምራቶች ተፈጽመዋል። ይህን ሁሉ በማየት ሞተለሚ ከልቡ በእግዚአብሔር ለማመን ውሳኔ አደረገ። አዋጅ አስነግሮም ለጣኦት የሰገደ ሁሉ የሚቀጣ መሆኑን፤ ሕዝቡም በተክለ ሃይማኖት ፈጣሪ እንዲያምን እንጂ፥ ማርያኖችን እንዳይከተል በትእዛዝ መልክ አስጠነቀቀ።

ከዚህ በኋላ ሞተለሚ ጭፍሮቹንና ሠራዊቱን ይዞ፥ አባታችን እንዲያጠምቁት ጠየቃቸው። እርሳቸውም ውሃውን ባርከው በአብ፥ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም አጠመቁት (የአንድ ሐዋርያዊ ሥራ)[18]። እስከ ነገ ጧት ምንም እንዳትቀምስ ብለው አስጠነቀቁት።

ቅዱስ ቁርባን አድርገውም ለሞተለሚ እና ለሠራዊቱ ሥጋ ወደሙ አቀበሏቸው። ይህን በሚያደርጉበት ወቅት ቅዱስ ሚካኤል እና የመላእክት አለቆች አብረዋቸው በመሆን ይራዱቸው ነበር። ሞተለሚ ከዚህም ቀን ጀምሮ ሞተለሚ መባሉ ቀርቶ ፍቦሥሐ ጽዮን ተባለ።

እንዲህ ሁኔታዎች ተቀያይረው፥ ፍሥሐ ጽዮን (የቀድሞው ሞተለሚ) ልዩ አለም ውስጥ ገባ። ከደስታው የተነሳ፥ ለአባታችን ብዙ ወርቅና ገንዘብ ሰጣቸው። አባታችንም ይህን ገንዘብ ተቀብለው ለድሆችና ለችግረኞች አከፋፈሉ። ከዚህ በኋላ በአባታችን ትእዛዝ ፍሥሐ ጽዮን በመንግሥቱ ሁሉ ቤተ ክርስቲያን አሠራ። በተለይ በዳሞት አውራጃ ብዙ ቤተ ክርስቲያን ተሠራ። ጣኦት ማምለክ፤ ዛርና ጠንቋይ መጠየቅም ቀረ።

አባታችን ወዲያ ወዲህ የማያወላውሉ፥ እውነትን ብቻ የሚያስተውሉ፥ ይህንም እውነት በተግባር ለመፈጸም ቀጥ ብለው ወደፊት ብቻ የሚጓዙ ስለነበሩ፥ ያንን አረመኔ ሞተለሚ ክርስቲያን አድርገው ማቁረባቸው፥ ክፉውን በበጎ ለመለወጥ ያላቸውን ችሎታ ያሳያል። ቅዱስ ቁርባን ለማንም ሰው መዳኛ ይሆን ዘንድ የተሰጠ መድኃኒት መሆኑን በተግባር አሳውቀውናል (ለአንድ የተዋህዶ ኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታይ እርሳቸውን በአርአያነት መከተል ከመጠራጠር እና ከስህተት ያድናል)።

ተክልዬ ሞተለሚን ክርስቲያን ስላደረጉት ከአረመኔነት ተለውጦ ጣኦት በማምለክ፥ ዛርና ጠንቋይ በመጠየቅ ፋንታ ቤተ ክርስቲያን በማሠራት ይተባበራቸው ጀመር። ክፉውን በደግ የሚቀይር ይህ የጻዲቁ አባታችን መንፈስ ሕያው ሆኖ

[18] ማቴ 28፡ 19

በኢትዮጵያችን (እንዲሁም በምድራችን) ይኑርልን፤ እኛም እንደእርሳቸው ከፉውን በደግ ለመመለስ ያብቃን።

አንዳንድ አድርባይ ቄሶች በሞተለሚ ግፌት ቅስናቸውን አፍርሰው ለጣኦታት ሰግደው ነበረ። መጥፎውን ወደ ጥሩ በመመለስ ችሎታቸው፥ አባታችን ቄሶቹን እንደገና አስተምረውና መክረው ወደ ቀድሞው ክርስቲያናዊ ተግባራቸው እንዲመለሱ አደረጉ። በጊዜያዊ ጥቅም ተታለው ከሃዲ የሆኑትን ቄሶች ዳግመኛ ቅስና ሰጧቸው፤ ለዲያቆናቱም እንዲሁ አደረጉ (ማውገዝ እና ማግለል ሲችሉ)።

ተክልዬ ቄሶች ቅስናቸውን ለሥጋዊ ኑሮአቸው መጠቀሚያ ብቻ እንዳያደርጉት፤ የፈተና ጊዜ ሲመጣም ጸንተው እንዲቆዩ አስተማሩ እንጂ፥ እነርሱን ኮንነው አላባረሯቸውም (አልገዘቷቸውም)። ሰው ሆኖ በሰው ላይ መፍረድ የማይገባ ስላልሆነ፥ ቄሶቹን እና ያካባቢውን ሁኔታ በግንዛቤአዊነት ተመልክተው፥ ጻዲቁ አባታችን ለቄሶቹ ራሩላቸው፤ የቅስና ማዕረጋቸውን መልሰውላቸው፥ አብረዋቸው እንዲቀድሱ ስለ ፈቃዳዊ ነፃነታቸው ተማጸኑ እንጂ፥ እነሱን አገልለው ለብቻቸው አልቀሩም። እንዲህ አብሮ ለመሥራት የሚያስችል ሁኔታን የሚያስተካክል የጻዲቁ አባታችን መንፈስ ሕያው ሆኖ በኢትዮጵያችን (እንዲሁም በምድራችን) ይኑርልን፤ እኛም እንደርሳቸው ከነልዩነቶቻችን በግንዛቤአዊነት አብሮ ለመሥራት ያብቃን።

አባታችን በዳሞት አውራጃ 12 ዓመታት ከኖሩ በኋላ፥ በምትካቸው ገብረ ዋህድ እና ካህናቱ ሕዝቡን እንዲያስተምሩና እንዲንከባከቡ በሃላፊነት አስረክበው ተለዩአቸው።

መንገዳቸውን ወደ ሰሜን አቀኑ። እግረ መንገዳቸውንም ብዙ በሽተኞችን ከፈወሱ በኋላ፥ ወደ አንድ ገዳም ደረሱ። የዚህም ገዳም አበ ምኔት አባ በጸሎተ ሚካኤል ይባላሉ። አባታችን እዚህ ገዳም ውስጥ ለስድስት ዓመታት በመኖር፥ እራሳቸውን ዝቅ አድርገው በወፍጮ ሥራና በሌላም ሥራ ያገለግሉ ጀመር፤ “የሰው ልጅ ሊያገለግል፥ ነፍሱንም ሊሰጥ እንጂ፥ እንዲያገለግሉት አልመጣም።” (ማቴ. 20፡28) የሚለውን ጥቅስ - ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረውን በማስታወስ።

ተክልዬ ከገዳም በሚኖሩበት ወቅት፥ በውስጣቸው ያለው የመንፈስ ኃይል፥ ባካባቢያቸው የሚገኙትን በሽተኞች ሳይረዱ እንዳይቀመጡ አደረጋቸው። በዚህም ምክንያት ብዙ በሽተኞችን አዳኑ። በዚህም ሥራቸው በመደነቅና በመከበር በአማራው አውራጃ ሁሉ ታወቁ። አበ ምኔቱም የአባታችንን የተደበቀ ታሪካቸውን በመስማታቸው በልዩ ክብር ይንከባከቧቸው ጀመር።

የሰው ልጅ በመልካም ሥራው ቢመሰገን መልካም ነው፤ ግን የመንፈስን ወሮታ ለሥጋ ለውጦ ለራስ ክብርን መቀዳጀት - ውዳሴ ከንቱ ስለሆነ፥ የሚጠላ እንጂ

የሚወደድ አይደለም። ስለዚህ፥ አባታችን ይህን ውዳሴ ከንተ በመሸሽ፥ በወሎ ክፍለ አገር ሐይቅ ወደምትባል ሥፍራ ለመሄድ ቆረጡ። ከመሄዳቸውም በፊት አበምኔቱና መነኮሳቱ - የምንድንበትን ነገር ምከረን ብለው አባታችንን በጠየቁ ጊዜ እንዲህ አሏቸው። "ትእግስትን፤ ትህትናን እና እግዚአብሔርን መፍራትን ገንዘብ አድርጉ፤ ቅናት፥ ትእቢትና ትምክህት እንዳያጠምዷችሁ ደግሞ ተጠበቁ..." ብለው መከሯቸው። "አትኩሩ፥ አትታበዩ፤ በጸብም፥ በውዳሴ ከንቱም አትጠመዱ። ነገር ግን በልብ ትህትና ከላንት እያንዳንዱ ባልንጀራውን ከራሱ አብልጦ ያክብር፤ ያም ለራሱ ብቻ አያስብ፥ ለባልንጀራውም እንጂ፤ ሁላችሁም ይህን አስቡ።" (ፊል. 2፡ 3-4)

ተክልዬ ሐይቅ እንደደረሱ፥ በደሴቲተ ከሚገኘው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከገዳሙ አበምኔት ከአባ ኢየሱስ ሞአ ጋር ተገናኙ። ከዚህም ሥፍራ ሆነው በጸሎት ሰውነታቸውን አደከሙ። አባታችን በሐይቅ ገዳም በነበሩበት ወቅት፥ ከዚህ የሚከተለውን እጅግ አስገራሚና አስደናቂ ሕልም አዩ፡-

በእግዚአብሔር ትእዛዝ፥ ቅዱስ ሚካኤል ከፀሐይ የበለጠ ወደምታበራ አገር አባታችንን ወሰዳቸው። የተለያዩ ቀለማት ባሏቸው ምሶሶዎች በቆመ፥ እጅግ ሰፊ የሆነ ቤት አስገባቸው። ያንዱ ምሶሶ ቅርጽ በሌላው ውስጥ ይታያል። መሬቱም እንደ ብርሌና እንደጠራ እንቁ ያማረ ነው። በቤቱም ውስጥ ዙፋኖች አሉ። የእሳት ወጋጋን በያለበት አለ፤ ግን ደስ የሚያሰኝ እንጂ የሚያቃጥል አይደለም።

አባታችን ይህን ድንቅ ቤት በማድነቅ የማን እንደሆነ ቅዱስ ሚካኤልን ጠየቁት። እርሱም ሁሉንም አስጎብኝቶ ከጨረሰ በኋላ፥ ይህ ቤት ያንተ ነው። የመካከለኛውም ዙፋን ያንተ ነው። እንዲሁም በዙፋኖች ግራና ቀኝ ያሉ በሺህ እልፍ የሚቆጠሩ አዕማድ፥ ካንተ በኋላ ለሚመጡ በመንፈስ የወለድካቸው ልጆችህ ነው ብሎ ለአባታችን ነገራቸው። ከዚያም በኋላ ወደ ሌላ ሥፍራ ወሰዳቸውና፤ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንዲቀርቡና በረከትን እንዲቀበሉ አደረገ። (የህልሙ መጨረሻ)።

ተክልዬ በሐይቅ ገዳም ለአስር ዓመታት ከተቀመጡ በኋላ ወደ ትግራይ ምድር በማምራት፤ አቡነ አረጋዊ የመሠረቱት ደብረ ዳሞ የምትባል ገዳም በትግራይ (አዲግራት አጠገብ) ደረሱ። ይህም የደብረ ዳሞ ገዳም ከላይ ሜዳ ሆኖ፥ ዙሪያውን ትልቅ ገደል ነው። ሰዎች ወደላይና ወደ ታች የሚመላለሱት ወገባቸውን በጠፍር (ወይም በገመድ) እየታሠሩና እየተሳቡ ነው። የዚህም ገዳም አበ ምኔት አባ ዮሃኒ ይባላሉ። አባታችንም ከአባ ዮሃኒ አስኬማና ቆብ ከተቀበሉ በኋላ፤ በምግባራቸውና መንፈሳዊ ፍቅራቸው፥ መነኮሳቱን ሁሉ እያስደሰቱ ለአስራ ሁለት ዓመታት ተቀመጡ።

ከዚህ በኋላ፥ የትግራይን ገዳማት እንዲጎበኙ፥ ከእግዚአብሔር በደረሳቸው ትእዛዝ መሠረት፥ አባ ዮሃኒን ተሰናብተው ለመሄድ ተነሱ። ወገባቸውን በገመድ

ታስረው፥ ከገዳሙ አፋፍ በመውረድ ላይ እንዳሉ፥ ገመዱ ተበጠሰ። ወዲያውም ነፍሳቸውን የሚያድኑበት ስድስት ክንፎች እግዚአብሔር ለአባታችን ሰጣቸው። (የጸጋ ክንፎች ናቸው፤ እንደ ማንኛውም አካል በሰው ሁሉ የሚታዩ አካላዊ አይደሉም፤ እንደ ሰማያዊ ፍጽምተ አካላት ድንገት ለተወሰኑ ጻድቃን የታዩ ናቸው እንጂ)።

“..ገመዱ ከካስማው ሥር ተቆረጠና ክቡር አባታችንን ተከትለው ስድስት ክንፎችም ተሰጡት፤ ክንፎቹንም እያማታ በረረ፤ የደብሩም መነኮሳት ሁሉ እያዩት ሦስት ዘንግ ወርውሮ የሚያርፍበት ያህል ሄደ፤ ..” (ገድለ ተክለ ሃይማኖት ገጽ 128)

መነኮሳቱም በዚህ ተአምር የአባታችን ነፍስ በመትረፉ በመደሰት እግዚአብሔርን አመሰገኑ። አባታችን የትግራይን ገዳማት ሁሉ እየተዘዋወሩ ከጎበኙ በኋላ፥ መንገዳቸውን ወደ ኤርትራ አቀኑ። ከዛም ባህሩን ተሻግረው ከኢየሩሳሌም ደረሱ። እግረ መንገዳቸውን አንድ ሰው በውሃ ጥም ሞቶ ሳለ አድነውታል። ይህም ሰው በኋላ ተከታያቸው በመሆን አልተለያቸውም። ከአባታችንም ምንኩስናን በመቀበል፥ ስሙ አርአየነ ጸጋሁ ተባለ።

በኢየሩሳሌም ገዳማት ተዘዋውረው ከጎበኙ በኋላ፥ እዛው ለመቅረት ፍላጎት አደረባቸው። ነገር ግን ቅዱስ ሚካኤል ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለሱ ነገራቸው። ወደ ኢትዮጵያ ከተመለሱም በኋላ፥ በትግራይ ውስጥ ከቦታ ቦታ በመዘዋወር፥ ሴቶችንና ወንዶችን ለምንኩስና የሚያበቃ ትምህርት እያስተማሩ፥ ብዙዎችን አመንኩሰዋል። አባታችን በትግራይ ክፍለ አገር በጣም የተወደዱ ከመሆናቸው አተነሳ፥ እስካሁን ድረስ ብዙዎች በስማቸው ይጠራሉ።

ተክልዬ - አባታችን ዳግመኛ ወደ ኢየሩሳሌም ሄደው ተመለሱ። እንደገና ለሦተስተኛ ጊዜ ደርሰው ሲመለሱ፥ የትግራይን አውራጃዎች ሁሉ እየዞሩ በማስተማር አዳረሱ። ከዚያ በኋላ፥ ወደ ደብረ ዳሞ ገዳም ወጡ። ከዚያም እንደደረሱ አንዳንድ መነኮሳት - “ያ እግዚአብሔር ስድስት ክንፎች ሰጥቶት ከሞት ያዳነው ሰው ተመልሷል...” እያሉ እጅግ ከፍ ከፍ አደረጓቸው። እርሳቸው ግን በደብረ ዳሞ ያለውን የገዳሙን ኑሮ ቢወዱትም፥ በሰዎች ዘንድ መወደስ አላስደሰታቸውም። ከዚህም ውዳሴ ከንቱ ለመራቅ ብለው ወደ ሌላ ቦታ ለመሄድ ወሰኑ።

አባ ዮሃኒን በመሰናበት ወደ ቀንጦራር ተራራ ወጡ። ከዚያም ወደ ሐይቅ ተመለሱ። ነገር ግን፥ ቀደም ሲል ያፈሯቸውን ክርስቲያኖች በመንፈስ እንዲመግቡ ስለታዘዙ፥ ከዚህም ሥፍራ ተነስተው፥ ለተከታያቸው አርአየነ ጸጋሁ በትርና የእጃቸውን መስቀል ሰጥተው፥ እርሳቸው ወደ ሸዋ ተመለሱ።

በሸዋ ክፍለ አገር ውስጥ በሙገር፥ በገፄማ እና በሌሎችም ሥፍራዎች በመዘዋወር፥ እያስተማሩና እያጠመቁ ከቆዩ በኋላ፥ አሰቦ ከሚባል ዋሻ ደረሱ። ከዚህም

ሥፍራ ከአስራ አምስት ደቀ መዛሙርቶቸው ጋር ተቀመጡ። ከዚህም ዋሻ በመነሳት ባካባቢውና በሸዋ አውራጃዎች ሁሉ እየተዘዋወሩ ያስተምሩ ነበር። ከትምህርታቸውና ከታምራታቸው ብዛት እጅግ የተወደዱ ሆኑ። በውስጣቸው ከነበረው የመንፈስ ኃይል የተነሳ ሰይጣን ካጠገባቸው ራቀ። ሰይጣነ ዝሙትም ልጆቻቸውን (መነኮሳቱን) ፈጽሞ እንዳይተናኮልባቸው አድርገው ስለነበረ፤ ወንዱ የሴቲቱን፥ ሴተቱም የወንዱን ልብሰ በመልበስ በወንድና ሴት መካከል ልዩነት መኖሩ የተረሳበት ወቅትም ነበር።

ባካባቢው ያሉ ዝንጀሮዎች እህል እያወደሙ አስቸገሩ። ከእለታት አንድ ቀን ግመር ዝንጀሮ ካንዲት እመበለት ምግብ ከቀማ በኋላ፥ እመበለቷን ደበደባት። አባታቸንም ከዛን ጊዜ ጀምሮ የአራዊትን አፍ ሁሉ በተመሳሳይ ተግባር ሰዎችን እንዳያጠቁ አሰሯቸው (ገዘቷቸው)።

አንድ የአይምሮ በሽታ ሲያስታምሙ የቀረበለትን ጠላ ሰው ካልቀመሰው አልጠጣም ቢል፥ ደቀ መዝሙሩን "ቅመስለት!" አሉት። እርሱም - በጾም ቀን እንዴት እቀምሳለሁ ቢል፥ "ከጾምማ ፍቅር የሚበልጥ አይደለምን ልጄ ሆይ!..." ብለው እንዲቀምስ አደረጉት። እርሳቸው ተከታዮቻቸውን ሁሉ በትክክሉ የሚመሩ መንፈሳዊ አባት ስለነበሩ፥ ከጾምስ የሚበልጠው መልካም ምግባር መሆኑን አስተማሩን።[19]

አባታችን አቡነ ተክለ ሃይማኖት ወንጌልን እየዞሩ በማስተማር ሰውነታቸው በደከመ ጊዜ፥ ኑሮአቸውን በአንድ ሥፍራ (በአሰቦ ዋሻ) መቆምና መጸለይ አደረጉት። በአሰቦ ውሻ ውስጥ ግራና ቀኝ እጃቸውን ለመዘርጋትና ለመቆም የሚያበቃቸውን ያህል ብቻ ፍርኩታ ሠርተው፥ በግራና በቀኝ በሚጠጉበት ወቅት፥ የሚወጋቸው ስለታም ጦር በማድረግ፥ አዲስ ገድል ጀመሩ።[20]።

አባታችን ሥጋቸው ከዚህ አለም የሚሰናበትበት ወቅት በደረሰ ጊዜ፥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አነጋገራቸው። "ወዳጄ ተክለ ሃይማኖት ሆይ! ገድልህን ጨርሰሃልና፥ ከእንግዲህ ከድካምና ከሃዘን ወደ ዘለአለም እረፍትና ድሎት ትሄዳለህ። የመቃብርህም ሥፍራ እስከ አምሳ ሰባት ዓመት ድረስ ከዚሁ ሥፍራ ይሆናል። ከዚያም በኋላ ልጆችህ አስከሬንህን አፍልሰው፥ ላንተ አጽም ማረፊያ በተመደበልህ ሥፍራ ያኖራሉ። ከዚህም

---

[19] ጾም ለግለሰብ እንደ ችሎታውና እንደፈቃዱ የመንፈስ ጥንካሬን ማስገኘያ እንጂ፥ በራሱ ማጽደቂያ ሆኖ መታየት የለበትም። "ከእግዚአብሔር የሚያደርስ ጾምስ የልብ ንጽሕና ነው..." ፍትሐ ነገሥት ገጽ 156 ጾምና መልካም ምግባር አብሮ መሄድ አለበት። (ኢሳ. 58)

[20] ከቅዱሳን ታሪክ - የአንድ ሰው መንፈሳዊ ጥንካሬ ምድራዊ ትርጉም የማይገኝለት፥ ተአምራታዊ ሥራን ሊሠራ እንደሚችል፤ ሥጋዊ ፍላጎቶችን ሁሉ ለመቆጣጠር ከመቻሉም በላይ፥ ሥጋና ነፍስ እስኪላቀቅ ድረስ ያለውን የሥጋ ህመም ሁሉ መቋቋም እንደሚችል እንማራለን። "ለደካማ ኃይልን ይሰጣል፥ ጉልበት ለሌለው ብርታትን ይጨምራል፥.." ኢሳ. 40፡29

ሥፍራ (የደብረ ሊባኖስ ገዳም) ከመንፈስ ቅዱስ የሚወለዱ ልጆችህ ብዙሓን ይሆናሉ...።"

አባታችን የመሞቻቸው ሰዓት መቃረቡን ስለተረዱ፥ የመንፈስ ልጆቻቸውን ሰብስበው ብዙ ብዙ መከሯቸው - "የሙሽርነቱንም የሠርግ ልብስ እንደ ለበሰ እንደ አንድ ሰው፥ ከእግዚአብሔር ክብር እንደ ራቀው አትሁኑ፤ በበጎ ሥራ ያልተሸለመ ሰው ወደ ሰማያዊው ሙሽራ ሠርግ አይገባምና።" ማቴ. 22፡11- 14 የሚለውን ጥቅስ - ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረውን በማስታወስ።

አንዲት እመበለት በርሳቸው የታሰሩ (የተገዘቱ) እንስሳት መኖራቸውን አሳሰበች። እርሳቸውም - "ከሰው እስከ እንስሳ የታሰሩ ካሉ የተፈተ ይሁኑ.." አሉ። እንስሳትም አፋቸው በታሰረ በአስራ ስምንት ዓመት ተፈታ።

የመንፈስ ልጆቻቸውን ብዙ ብዙ ምክር ከመከሯቸው በኋላ- "በእውቀት ወይም ካለ እውቀት የሠራችሁትን በደላችሁን ሁሉ እግዚአብሔር ይቅር ይበላችሁ..." በማለት ተሰናበቷቸው፤ በተወለዱ በዘጠና ዘጠኝ ዓመታቸው ነሐሴ 24 ቀን ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ።

አባታችን አቡነ ተክለ ሃይማኖት ባረፉ በሃምሳ ሰባተኛው ዓመት፥ ክቡር አባ ሕዝቅያስ ከየካቲት 19 ቀን ጀምሮ አስከ ግንቦት 12 ቀን ድረስ ተበታትነው የነበሩትን የአባታችን ልጆች አሰባሰቡ። ግንቦት 12 ቀን የአባታችንን አጽም ከተቀበሩበት ዋሻ አውጥተው በሳጥን አስቀመጡት። የተገነዙበትን ጨርቅ በትንሽ በትንሹ አድርገው በመቅደድ ተከፋፈሉት። የተቀበሩበትን አፈር እንኳን ዘግኖ ለመውሰድ ታላቅ ትንንቅ ነበር። የአባታችን አጽም ወደ ታላቁ የደብረ ሊባኖስ ቤተ ክርስቲያን ግንቦት 12 ቀን በማፍለስና በማስገባት፥ መምህራን በተገኙበት ታላቅ በዓል ተደረገ። በዚያን ጊዜ የታየ ተአምር ነበር፤ ከዚያም በኋላ እስከ ዛሬ ድረስ፥ በደብረ ሊባኖስ ልዩ ልዩ ተአምራት እየተፈጸመ ነው።[21]

ይህ ነው የጻዲቁ አባታችን የቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ታሪክ ባጭሩ። የጻድቃን - ቅዱሳን ታሪክ "የመንፈሳዊነታችንን ታሪካዊ ሂደት" ስለሚያንጸባርቅ፥ እንዲህ ደስ የሚለውን (የሚጣፍጠውን) የሰውን የመንፈሳዊነቱን ታሪክ በመከታተል፥ እጅግ ጠቃሚ መንፈሳዊ ትምህርት ማግኘት ይቻላል። "የእግዚአብሔርን ቃል የተናገሩአችሁን ዋኖቻችሁን (መሪዎቻችሁን) አስቡ፤ የኑሮአቸውንም ፍሬ

---

[21] ተአምራት እየተፈጸሙ አልተፈጸሙም ብሎ መከራከር ይቻላል። ነገር ግን፥ የሰው ልጅ አይምሮ የሆነውን እንዳልሆነ፥ ያልሆነውንም እንደሆነ ማድረግ ስለሚችል፥ ይህንን ችሎታ የሰው ልጅ እንዳሻው ይጠቀምበታል፤ ትላንት፥ ዛሬና ለወደፊት ከምድር ላይ በሚሠሩ ተአምራቶች ሳቢያ - ሰዎች በነፍስ ወከፍ በተለያዩ አመለካከቶቻቸው ውስጥ የሚሰርጹ ሃሳቦች ይኖሩ ዘንድ ግዴታ ነውና።

እየተመለከታችሁ በእምነታቸው **ምሰሉአቸው**። ኢየሱስ ክርስቶስ ትላንትና፥ ዛሬ፥ እስከ ዘለአለምም ያው ነው....።” ወደ እብራ.13፡7 -8

የአቡነ ተክለ ሃይማኖትም ታሪክ - በጎ መንፈስ ከስነ ምግባር ጋር ሲዋሐድ ምን ያህል ታላቅ ኃይል ሊሆን እንደሚችል የሚያሳይ ነውና፤ ካቶሎክ፥ ፕሮቴስታንት ወይም እስላም ሳይባል ለሰው ሁሉ መንፈሳዊ አርአያነት ያገለግላል። “በእውነት የሚሰግዱ ለአብ በመንፈስና በእውነት የሚሰግዱበት ጊዜ ይመጣል፤ አሁንም ሆኗል፤ አብ ሊሰግዱለት እንደነዚህ ያሉትን ይሻልና፤ እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል....።” ዮሐ. 4፡23 - 26

መንፈሳዊ ገጽታዋ የኢትዮጵያችን፥
በጻድቃን መንፈሳዊ አርአያነት መመሳሰላችን፥
ሕብረታችን፥ አንድነታችን እና ጽናታችን፥
የተክልዬ መንፈስ መስተዋቱ - መተያያችን።
ከቦታ ቦታ እየተዘዋወሩ ማስተማር - ወንጌላዊነት፥
ረግቶ መቆየት - በሃይማኖት ጽናት፥
በሰው አለመፍረድ፥ ይቅር ማለት፥
ለውዳሴ ከንቱ - ለሥጋዊ ክብር - ለሥልጣን አለመጓጓት፥
በመልካም ምግባር ወደ ጥሩው ለመጠጋት ጥረት፥
ይህ ነው ከተክልዬ የተማርነው - የምንከተለውም በአረያነት።
የተክልዬ መንፈስ - የሚያቃጥል፥ ሰይጣናትን - ኢጋንትን፥
ጥንት የነበረ ስጦታችን፥ አሁንም አለ በኢትዮጵያችን።
ታሪክ መዝጋቢዎች ተጠንቅቃችሁ በጽሑፍ አስፍሩት፤
የምታዩትን፥ በቪዲዎ የቀረጻችሁትን፥ ችላ ሳትሉ ተከታተሉት፤
ለሳይንቲስቱም እንዲገባው ማስረጃውን አቅርቡለት፤
መጪው ትውልድ ይማርበት፤
የጌታ ትምህርት በሥራ ላይ ሲውል ይታይበት።

ሰይጣን ምንጊዜም ሰዎችን ለማሳሳትና ወደ እርሱ አለም ውስጥ ለማስገባት ካለማቋረጥ ይሠራል። እኛም በየጊዜው እንፈተናለን። ምንጊዜም በሰይጣን እንዳንሸነፍ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። ማንም ከቅዱስ መንፈስ ጋር

የሚተባበር ሰው እርኩስ መንፈስን ሊያቸንፈው ይችላል፤ ሳናቸንፍ ቀኑ መሽቶ አይንጋ። ለወደፊት ሰዎች ሁሉ እንደ ተክልዬ በመንፈሳቸው ጠንካሮች ሲሆኑ፥ በአለማችን ፍጹም ሰላም ይመሠረት ዘንድ ተከላካይ እርኩስ መናፍስትን ያጠፏቸዋል፤ አሁንም እያጠፏቸው ነው።

መጨረሺያው የት ነው? የሰው ልጅ ብርታት፤
ገትሮ ሲያሙቅው ሥጋን እንደ እንጨት፤
ውስጠ መንፈስ ብርቱ ተክለ ሃይማኖት።
እንደ ተተከለ አምድ፥ በመቆም ለጸሎት፤
ሥጋዎን በድለው፥ ምንም ሳይሳሱለት፤
ቀኑ መሽቶ ነጋ እንቅልፍ ሳይወስድዎት።

የአባ አባታችን - የጻድቅ ሰው ሞት፥
በእግዚአብሔር ቤት ክብር፥ ለኛም ትሩፋት፤
እንግዲህ ያስቡን እኛን ልጆችዎን፥
ኢትዮጵያን አስታውሱ፥ በጸሎት አይርሱን።

ከክርስቶስ ቀጥሎ በሐዋርያት፥ በያለበት ሲነግሥ ክርስቶሳዊነት፥
ለእግዚአብሔር የሚሰግዱለት ሲበዙለት፥
ምድር አቧራዋን ዮሐንሶች - ኤልያሶች ሲጠርጉላት፥
መልካም ዜና ሲያበስሩላት፥
በሕዝቦች መንፈሳዊ እድገት - መንፈሳዊ ንቃት።

እኛም እንምሰላቸው ጻድቃኖቹን፥
ጊዜ አናጥፋ በጭቅጭቅ፥ እናሰማምር ቤታችንን፤
እንቅረብ ወደ እግዚአብሔር አምላካችን፤
በትህትና እራሳችንን ዝቅ አድርገን።
እንስገድለት ለክብሩ፥ ለፈጣሪነቱ፥
ለኃይሉ፥ ለመለኮታዊነቱ።
በእግዚአብሔር እምነታችን፥ በመልካም ምግባር ባህላችን፥
በፍቅር እንተሳሰር - ሰላም ይሁን ለሁላችን።

# ምዕራፍ አምስት

## ሃይማኖቶች - የመንፈስ መስተዋቶች

ለዘለአለም የሚቆይ እውነት ሲሰበክ ብዙ ሺህ ዓመታት አልፈዋል፤ እውነት በምድራዊነት እየተደባበሰ ቆይቷል። በዚሁ ምክንያት ሃይማኖቶች በዝተዋል።

በመጥፎ አድራጊዎች ያልተጠለፈ ሃይማኖት የሰውን ልጅ ምድራዊ ኑሮም ሊያሻሽለው የሚችል ከሆነ (በሰላምና በፍቅር እንዲኖር የሚረዳ ከሆነ)፥ ይህንኑ ለሰው ሁሉ ማዳረስ፥ ለልጆቻችንም ማስተማር ይገባል። ወደድንም ጠላንም ሃይማኖቶቻችን የመንፈሳዊ ህልውናችን ማረጋገጫ መስተዋቶቻችን ናቸው።

ምንም እንኳን፥ አንዳንድ ሰዎች ሃይማኖትን ከሕይወታቸው ውጪ ሊያደርጉት ቢሹም፥ እውነትን ሲፈልጉ - ሁለ ገብ ወደ ሆነው ወደ ሃይማኖት ይጠጋሉ - “ጥሩነት እንዴት ይገኛል? ጽድቅስ እንዴት ይመጣል? በእርግጥ፥ ከየት ነው ያለችው እውነት?...”ሲሉ።

ሃይማኖት ለሰው ልጅ የማይጠቅም ስለሆነ፥ ከሰው ልጅ አይምሮ ይጥፋ (ይደምሰስ) የማንል ከሆነ፥ በአንዳንድ ሃይማኖታዊ ጽንሰ ሃሳቦች ላይ ቆየት እያልን እንመራመር።

በተለያዩ ጽንሰ ሃሳቦችና ፍልስፍናዎች ላይ የጋራ ትርጉም በመስጠት የሰዎችን ብቸኛ አይምሮ እርስ በርሱ በማገናኘት እርስ በርስ ልንግባባ ችለናል። ሃይማኖትም አለን። ሆኖም፥ የእጅ አሻራ የተለያየ እንደሚሆን ሁሉ፥ የሰውም አስተሳሰቡ እንዲሁ የተለያየ ነው የሚሆን።

የሰው አይምሮ ቁስ አካላዊ መሳሪያ የማያነበውን፥ ከቁስአካላዊ ሞገድ “ሌላ” - ከተለያዩ ኃይላት (መንፈሳዊ) የሚመጣውን የሚያነብ ቢሆን፥ ይህንን ከግለሰቡ በስተቀር ማንም ሊያውቅ አይችልም። እያንዳንዳችን በተለያየ መንገድ ነው መንፈሳዊ ግንዛቤ የሚኖረን።

ከማንኛውም እውቀት ጋር ሁለት አይነት አመለካከት (ቅዱስ እና እርኩስ) እንደሚኖር ሁሉ፥ በአይምሮአችን የምናስበው፥ በአፋችን የምንናገረውና በየቀኑ የምንሠራው ሁሉ ተጠራቅሞ እድል ፈንታችንን እንደሚቀይስ ሁሉ፥ ለማይታወቀው

ሁሉ ክፍተት በመስጠት - ሃይማኖቶችን ከመናቅ ቆጠብ ማለትን ብንለማመድ፥ እግዚአብሔርንም በመፍራት ከከፉ ነገር ብንርቅ፥ የመጥፎ እድል ተጠቂዎች አንሆንም።

እግዚአብሔርን የማይፈራ ጠቢብ አይደለም፤ ጠቢብ ስላልሆነም፥ አለማወቁን መዝኖ ሳያውቅ ለዘለፋና ለነቀፋ ይሮጣል። ብዙ የሚያውቁ ሰዎች ባንድ በኩል የእውቀታቸውን ጸጋ ለሰዎች ሁሉ ሲያካፈሉ፥ በሌላ በኩል ደግሞ ከማወቃቸው ጋር አለማወቅ እንደሌለበት እየሳቱ እጅግ ሲመጻደቁ፥ ሌላውን ይዘልፋሉ፥ ያሳንሳሉ፥ ይፈርዳሉም።

እስከ ዛሬ በታሪክ እንደታየው ሁሉ - የሰው ልጅ የሚሠራው መጥፎ ሥራ ሁሉ ችግርና መከራን ሲያተርፍለት፤ ግን ከጥፋቱ ሲታረምና ራሱን ሲያሻሽል ኑሮ ሲመቻችለት፣ አለዚያም በመጥፎ ሥራው ከቀጠለ፥ እንዲማር የተሰጠውንም ጊዜ ካልተጠቀመበት፥ ኑሮ ይበላሽበታል። በዚህ አንጻር እንኳን ብናየው፥ እኛ ስለ አካላዊ የተፈጥሮ ክስተቶች እንቀሳቃሽ ኃይሎች እንዲሁም ስለ ሰው አካላዊ ጠባይ ተወያይተን ለመግባባት እንችል ዘንድ ያለን ምርጫ፥ በአካል ትይዩ መንፈስ መኖሩንም በማሰላሰል መሆን ይኖርበታል።

መጥፎ ሰው ለራሱና ላካባቢው መጥፎ እንዳይሆን ሃይማኖት አስፈልጎታል። ካለ ምንም ሃይማኖትና መንፈሳዊ ትምህርት የሚኖሩ ደጋግ ሰዎች ጥሩነታቸው እንዲሁ በተፈጥሮ የተገኘ ስለሆነ - “በተቻለ መጠን ከማንም ሰው ጋር ተስማምቶ መኖር ነው ደጉ፥” በሚል የኑሮ ፍልስፍና ብቻ ረክተው፥ ከክፋት ርቀው ይኖራሉ። “ኑሮን ላወቀበት ትመቻለች፤ ላላወቀበትም ትመራለች፤ ደግነትና ጥሩነት ለራስ ይበጃል፤ በክፋትና በተንኮል የተሰማሩ ሰዎች እራሳቸውን ጉዳት ላይ ይጥላሉ፤” በሚል ማራኪ ፍልስፍና ይመራሉ። በተፈጥሮአቸው ጥሩዎች ስለሆኑ፥ ደግ መሥራት ይቀላቸዋል። በልባቸው ክፋት ስለሌለ፥ መጥፎውን በመጥፎ መተካት ይከብዳቸዋል፤ መጥፎውን ወደ ጥሩ መቀየር፥ መሳቅና መጫወት ይቀናቸዋል። ከክፋት የራቁ ናቸውና፥ በዚሁ አዎንታዊ ጠባያቸው አለም ቀና ስለምትሆንላቸው፥ የራሳቸውን ኑሮ፥ አካባቢያቸውንም በደስታ የተመላ ለማድረግ ይጥራሉ።

ነገር ግን በምድር ለመኖር የሚያበቃ ፍልስፍና በውስጡ መንፈሳዊነትም ከሌለው በስተቀር፥ ከአንድ ሥፍራ ላይ ሲደርስ (ምድራዊ ችግር ሲመጣ) ይሰበራል። ደጉ ሰው ድንገት ሳይታሰብ ቅይር ብሎ መጥፎ ሲሆን ተመልክተናል። ለዚህ ነው፥ ምን ጊዜም ተስፋ እንደማይቆርጡ ሐዋርያት፥ ከምድራዊ ሥቃይ ባሻገር፥ ደስ የሚል ሰላማዊ ኑሮ መኖሩን የሚያበስር ሃይማኖት ያስፈለገ፤ እሳት በውሃ እንደሚጠፋ ምድራዊ ክፋቶችም በሃይማኖት ይጠፋሉና።

በስነ አይምሮ የተራቀቁ ሊቃውንት፥ ፈላስፎች እና ሳይንቲስቶች እንዲህ ይላሉ - "ሰዎች በምድራዊ ኑሮአቸው ፍርኃት፥ ጥርጣሬና ጭንቀት ውስጥ በሚገቡበት ጊዜ አንድ ነገር እንደጎደላቸው ይሆናሉ (ባዶነት ይሰማቸዋል)። ስለዚህ፥ ይህንን ባዶነት (ስነ አይምሮአዊ ክፍተት) ለማሟላት በሃይማኖት ላይ የሙጥኝ ይላሉ።"

አዎ! ምድራዊነት ብቻውን የስነ አይምሮ ክፍተት ያመጣል፤ አንዳንድ ጊዜም፥ ለዚህ የስነ አይምሮ ክፍተት ቶሎ መፍትሔ ካልተገኘለት ከጉዳት ላይ ሊጥል ይችላል። ሰው ሳይርበው እንደማይበላ ሁሉ፥ የአንድ ሰው ሃይማኖተኛ መሆን ከተጠቀሰው ስነአይምሮአዊ ክፍተት ጋር የተገናኘ ቢሆን አያስደንቅም። ስለዚህ፥ የተጠቀሰውን ባዶነት (ስነ አይምሮአዊ ክፍተት) ለማሟላትም ቢሆን ሃይማኖት ለሰው ልጅ አስፈላጊ ሆነ።

እምነት ባለ ብዙ ዘርፍ ሲሆን - ሲበጅለት ክፍተት፥
በእርግጥ፥ ከየት ነው ያለችው እውነት?
የለም አይደለም፥ ከሥጋ የለም ፍጹም እውነት፤
ከምድር ሊገኝ የሚችል አይመስልም ፍጹም ሃይማኖት።
ሃይማኖትስ ምኑን ሃይማኖት ሆነ? ካልጋበዘ ገለልተኛውን፥
ካልጠራ የራቀውን፥ ካላቀፈ የቀረበውን።
ሃይማኖት በምን ተግባሩ ተከበረ?
ሰውን ከሰው ካላቀራረበ፥ ገለልተኛም ሆኖ ከቀረ።

ምንድነው የሃይማኖት ሥራው፥
የመጨረሻ ግቡና አላማው?
የትኛውን እንከተል - የትኛው ነው እውነት?
ሃይማኖት ምኑን ሃይማኖት ሆነ? ካልመሰለ ሰማያዊ ኮሙኒስት፥
አብሮ ለመኖር፥ ለመተሳሰብ፥ ለፍቅር፥ ለህብረት እና ለአንድነት።

ግን ከጥንት ጀምሮ እኛ ያስተዋልነው፥
ግጭት ሲካሄድ የጥሩውና የመጥፎው፤
ጥሩው ሲያቸንፍ መጥፎው ሲሸነፍ ነው።

ስንቱን ምልክት እናመልከት፥ እግዚአብሔር መሬት የወረደበትን፤
እንደ ሰው ሆኖ ያስተማረበትን።
ስንቱን ቅዱሳን እንቁጠር ለሃይማኖት መልክ ያወጡለትን?

ሰዎች ሆነው ከሰው በላይ የታዩትን።
እግዚአብሔር ሲፈጥረን እንድናመልከው፥
እኛ ስናፈነግጥ፥ ስንሸሸው፥
እርሱ ሲያስተምረን - ሲመልሰን በየጊዜው፥
ይህንን ነው ከታሪክ የተማርነው።

በእስላም፥ በክርስቲያን፥ በሲክ፥ በቡድሃ፥ በሺንቶም ቢሆን በሞርሞን፥
በአለም ዙሪያ አዳዲስ ሃይማኖቶች ቢበዙልን፥
ሁላችንም እንደየእምነታችን፥
አምልኮተ እግዚአብሔር እንዲጸናልን።
የሰውም ልጅ ችላ ብሎ ግላዊነቱን፥
በምንምነት ተክቶ ራሱን፥
ግን አውቆ አንድ እውቀትን፥
ራሱን እንዲያሻሽል - እንዲመስል ፈጣሪውን።

ፈጣሪን ማወቅና ማሳወቅ ተግባራችን፥
ሁሉም በእግዚአብሔር የሚጠቃለል መሆኑን ፥
ይህ ነው መጨረሻው - የምድራዊ ጉዞአችን፤
የሰው ልጅ እግዚአብሔርን እስኪመስልልን፥
"ጠላቶቹ" የእግሩ መቀመጫ እስኪሆኑልን ።

እነሆ! የወደፊቱን የሰብዓዊነትን መንፈሳዊ ጉዞ ለመገምገም፥ ወይንም ላጠቃላይ እውቀት "ለምንድነው ሃይማኖት ያስፈለገን?" በማለት፥ በተለይ የመካከለኛው ምሥራቅን መንፈሳዊ እንቅስቃሴ መነሻ በማድረግ፤ ቀጥሎም፥ ስለ ኢትዮጵያውያኖች የመንፈሳዊነታቸው ታሪካዊ ሂደት ከብዙው በጥቂቱ በመገምገም፥ ስለ መንፈሳዊ ማንነታችን ጉዳይ ማስታወሻ - ማሰላሰያ ይሆን ዘንድ ተጻፈ።

ሃይማኖተኛነትን እንደ ኋላ ቀርነት የሚመለከቱ ሰዎች የሃይማኖትን ጉዳይ በሳይንሳዊ ስነአመክኖአዊ አመለካከት ቢገመግሙት፥ ወይንም ከምድራዊ (አካላዊ) ስነአመክኖአዊ አመለካከት ውጪ በመንፈሳዊ ተመስጦ ቢመለከቱት፥ አንዳንድ ሃይማኖታዊ ምሥጢሮች ይገለጡላቸው ይሆናል።

ሳይንስ በልቦናችን - በውስጣችን (በመንፈሳችን) ያለውን አይነግረንም። ይኸው እድሜ ልካችንን ስለ ማእድናትና ስለ አለቶች አፈጣጠር ተማርን፤ ግን በነርሱም

ውስጥ አካላዊ ያልሆነ ነገር (ንቃተ ሕሊና - conceousness) ቢኖር አላወቅንም[22]።

የሃይማኖት ትምህርት እንደ ሳይንስ አንድ ወጥ ሆኖ ለሰው ሁሉ በአንድ አይነት መልክ ብቻ አይደለም የሚዳረሰው። ተናጋሪዎቹ - ሰባኪዎቹ - አስተማሪዎቹም ምንጊዜም የሃይማኖት ሊቃውንት ብቻ አይደሉም።

እግዚአብሔር የሰው ልጅ በጠቅላላ እንዲጠፋ ስለማይፈልግ፥ ግለሰቦችን በተለያየ መንገድ ያስተምራቸዋል። ይህንኑ በመንፈሳዊ ቅንአት ለሌሎች ለማካፈል የሚሹ ብዙዎች ናቸው። ከተራ ሰዎችም የሚፈልቁ መንፈሳዊ ሃተታዎችን በጥሞና ማስተዋል፥ አንድም የሰው ልጅ በተፈጥሮአዊ ጠባዩ ከእግዚአብሔር የተሰጠውን መንፈሳዊ የአመለካከት ጸጋ በገዛ ራሱ ያጎላው ዘንድ እንደሚችል ያመላክታል።

በነባር ሃይማኖታዊ ጽሑፎች የተደገፈ፥ በዚህ ምዕራፍ የተካተተ ሃይማኖታዊ ፍሬ ሃሳቦች አላማ- ከምድራዊነታችን ባሻገር የሚኖረን አመለካከት ከሞትን በኋላ ለሰማያዊ ኑሮ ብቻ ሳይሆን፥ ለምድራዊ ኑሮአችንም - ለሰላማችን፥ ለማህበራዊ ኑሮአችን እና ለአንድነታችንም ስለሚጠቅመን፥ የመንፈሳዊነታችን ነገር ችላ እንዳንል ለማስታወስ ነው። ዋናዋናዎቹን የሰብአዊነታችንን ሃይማኖቶች ጠቅለል ባለ መልክ ያቀረብነው፥ አንባቢያን ከአንዱ ሃይማኖት ዘለው ወደሌላ ሲሄዱ፥ በሁሉም ሃይማኖት ውስጥ ጊዜ የማይሽረው እውነት መኖሩን እንዲያስተውሉ፥ ሲሆን፥ በሰብአዊነታችን ታሪክ ውስጥ ከጥንት ጀምሮ አንድ ብቻ የሆነውን እና በሁሉም ሃይማኖት ውስጥ የሚገኘውን እውነት ለገዛ ሃይማኖት ማጠናከሪያ ማድረግም እንደሚቻል በአጽንኦት ለማመልከትም ጭምር ነው።

ሰው ከተፈጠረ ጀምሮ በአካላዊነቱ እንደኖረ ሁሉ፥ በመንፈሳዊነቱም እንዲሁ ኖሯል። ሰው እግር እና እጁን ለይቶ እንዳወቀ ሁሉ፥ ፈጣሪውንም በተለያዩ መንገዶች እንዲያውቅ (እንዲገነዘበው) ሆኗል፤ ሃይማኖትም ነበረው።

ሕዝቦች ለምድራዊ ችግሮች ሁሉ (ለበሽታ፥ ለሞት፥ ለጦርነት...ወዘተ) መፍትሔ ሊሆን የሚችል ታላቅ ኃይል ይኖር እንደሆን በማለት፥ በሚታዩ ነገሮች ሁሉ (በፀሐይ፥ በጨረቃ፥ በዛፍ፥ በልዩ ልዩ ምስሎች.. ...ወዘተ.) ማምለክ ጀመሩ። ቆይቶም፥ አካላዊ ካልሆነው አለም የመናፍስትን መኖር ሊገነዘቡ ችለዋል።

---

[22] ከምድራዊነታችን ባሻገር" ሦስተኛው መጽሐፍ፥ ምዕራፍ ስምንት ውስጥ እንደተገለጸው - ግዑዛን እና ረቂቃን ነገሮች የድቀታቸው መጨረሻ እንዳልታወቀ ሁሉ፥ በቁስ አካላት ውስጥ ፈጽሞ ንቃተ ሕሊና አለመኖሩን አላወቅንም።

በጥንት ዘመናት መናፍስት መኖራቸውን ሰዎች በደንብ ያውቁ ነበር፤ ይህ በሰው ልጅ መንፈሳዊ ታሪክ ውስጥ እንደ አንድ ታላቅ እድገት (እመርታ) መቆጠር ነበረበት። አንዳንድ ሃይማኖተኞች ግን ይህንን ቀዳሚ መንፈሳዊ ግንዛቤ ይንቁታል።

የሰው መንፈሳዊነት እስከ ዘመናችን ድረስ እያደገ ነው የመጣው። በጽሑፍ ስላልተመዘገበ ብቻ ለሁሉም ሳይዳረስ ቀረ እንጂ፥ ሕዝቦች በአለም ዙሪያ ስለ ምድር እና ስለ መንፈስ ጉዳይ ብዙ ጠቃሚ ምክሮችን ከትውልድ ትውልድ ሲያስተላልፉ ቆይተዋል። በሰው እየተበረዘ ሰውን ያስጨነቁ፥ ያገዳደሉ፥ እውነት መሳይ ውሸቶች የሌለባቸው፥ በሃይማኖቶች ሁሉ የሚገኙ እውነቶች - እነርሱ - የማይጮሁ "ሰላማዊ መንፈሶች" ከዚህ አደረሱን።

በምድር የሰሜን ዋልታ ዙሪያ (ሰሜን አሜሪካ፥ ግሪንላንድና ሩሲያ) የሚኖሩ ኤኑዊት (ወይም ኤስኪሞ) የተባሉ ነባሮች በኑሮአቸው እርስ በርስ ይተሳሰባሉ። እንዲሁም ከነርሱ መካከል የአንዱ ሰው ኃላፊነት ከቤተሰቡ አልፎ ወደ ሕብረተሰቡ የሚዘልቅ ነው።

የሰሜን ነባሮች ለተፈጥሮ አካባቢ ከፍተኛ እንክብካቤ የሚያደርጉ፥ መሪዎቻቸውን የሚያከብሩ፥ ያላቸውን ከሌላቸው ጋር በመካፈል የሚያምኑ ናቸው። ምድርን እና በውስጧ ያሉትን ሁሉ መንከባከብ እንደሚያስፈልግ እና የተፈጥሮ ሂደት ተዛብቶ ሰዎች ማደሪያ እንዳያጡ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ግዴታ እንደሆነ ያስተምራሉ።

ይህች ምድር ከሚገባው በላይ ሳትበዘበዝ፥ ብዙ እንድትቆይልን የሚያደርገውን የሰሜን ዋልታ ነባሮች ፍልስፍናዊ ትምህርት ሰለጠንን የሚሉ ሰዎች በንቀት ሲመለከቱ ቆይተው ነበር። አሁን አሁን ግን ይህቺን ምድር ካልተንከባከብናት ጉዳት ላይ እንደምንወድቅ ከነኚህ ነባሮች እየተማርን መጥተናል። ከቀና አስተሳሰቦቻቸውና እምነቶቻቸውም በጥቂቱ የሚከተለውን እንመለከታለን፦

እንስሳት እንደ ሰዎች ሳይነጫነጩ ከተፈጥሮ ጋር ስምም ሆነው ስለሚኖሩ፥ የተፈጥሮን ሂደት አያዛቡም። ሰው ግን፥ ስግብግብና ጸበኛ በመሆኑ፥ ከራሱም ከተፈጥሮም ጋር እየተጣላ የተፈጥሮን ሂደት እያዛባ (ተፈጥሮን እየገደለ) ነው ያለው።

ሕይወት ባላቸው ውስጥ ሁሉ መንፈስ አለ፤ ሰዎችም እንስሳትም እንደየአይነቶቻቸው የተለያዩ መናፍስት አሏቸው። ከእንስሳትም አይነት በመንፈሳቸው ከመጥፎ ሰው የሚሻሉ ደጋጎች አሉ።

ማንኛውም ተፈጥሮ በሥጋው ቢሞትም በመንፈሱ ለዘለአለም ይኖራል። አንዱ ሰው ብዙ መንፈስ አለው፤ የሚታመመውም ከሰውነቱ መንፈሶች እየተገነጠሉ

ሲጠፉ እንደሆነ ሁሉ፥ የሚድነውም ተገንጥለው የሄዱት መንፈሶች እንደገና ሲሰበሰቡ ነው።

የሰሜን ዋልታ ነባሮች አንጋኮክ (ወይንም ሻማን) የተባሉ አዋቂዎቻቸው ከመናፍስት ጋር የመገናኘት ችሎታ እንዳላቸው ያምናሉ። ሻማኖች እንደ ሐኪም ስለሚቆጠሩ፥ ሰው ሲታመም ከሚጠቀሙባቸው የቅጠላ ቅጠል መድኃኒቶች ሌላ፥ የታማሚውን መንፈሶች እየተጣሩና እያሰባሰቡ የማዳን ሥራ ያከናውናሉ።

የሰሜን ዋልታ ነባሮች (ኤኑዊት) ለመናፍስት ሁሉ የበላይ እንዳላቸው ያምናሉ፤ በተለይ የሚያመልኩባቸው አማልክትም አሏቸው። ይህ በዚህ እንዳለ፥ ከሁሉ በላይ ፈጣሪ እንዳለ ያውቃሉ። እውነተኛ ፈጣሪያቸውን አውቀውና አምነውበት ይሰግዱለታል።

አዎ! እግዚአብሔር ለፍጡራኑ ሁሉ (ለሰውም ለእንስሳም) ያስብላቸዋል እንጂ፥ ማንንም ለመኮነን ብሎ አልፈጠረም። ይህ በእያንዳንዳችን ሃይማኖት ተጽፎ ይገኛል። ለምሳሌ - እንስሳትን እንድንጠቀምባቸው ቢፈቀድልንም፥ ይህ ፈቃድ የተገኘው እኛ በመንፈሳችን እንጂ፥ በአካላዊ ፍጥረታችን ከእንስሳት ሁሉ ከፍ በማለታችን ሳይሆን፥ የሁላችንም ፈጣሪ ስለፈቀደልን ብቻ ነው። እግዚአብሔር ለፍጡራኑ ሁሉ የሚያስብ መሆኑን ከጥፋት ውሃ ታሪክ መገንዘብ እንችላለን (ዘፍ.7)።

እንስሳት - "ከመኖሪያችን ልቀቁ.." ብለው ዮሴፍና ማርያምን አላስቸገሯቸውም፤ በዚያን ወራት በቤተልሔም የሚበርድበት ወቅት ስለነበር፥ ጠጋ ብለው በእስትንፋሳቸው ሞቅታ ህጻን ኢየሱስን እንዳይበርደው ተከላከሉለት እንጂ።

እንስሳትን ካለአግባብ ማሰቃየት እንደማይገባ በሁሉም ሃይማኖት ዘንድ ታዋቂ ነው። በሃይማኖታዊ ትምህርትና ስነስርዓት መሠረት - ምግብ ይሆኑን ዘንድ የሚታረዱትን እንስሳት፥ በቅድሚያ የሁላችንም ፈጣሪ የሆነውን የአምላካችንን ስም በመጥራት - በስነስርዓት በመባረክ ነው። ሲታረዱም ነፍሳቸው ቶሎ እንዲወጣ፥ ብዙም እንዳይሰቃዩ - በሰላ ቢላዋ ጣደፍ ብሎ፥ ደማቸው በብዛት ከሚወጣበት ከአንገታቸው እንዲሆን ነው የተፈቀደው።

በአሁኑ ዘመን፥ እንስሳትን የሚራሩላቸው፥ ሥጋቸውንም የማይበሉ (vegeterians) በተለያዩ አህጉራት በብዛት ይገኛሉ። ከነኚህም መካከል አንዳንዶቹ ሃይማኖት የሌላቸው ናቸው።

የጄይን ሃይማኖት ተከታዮች፥ የጥቃቅን እንስሳትን ነፍስ ላለማጥፋት በማሰብ፥ ከቤታቸው ሲወጡ መጥረጊያ ይዘው ይወጣሉ፤ አፋቸውንም ይሸፍናሉ። ይህንን እና የመሳሰለውን ጉዳይ በጥልቀቱ ለመመርመር ይህ መጽሐፍ አቅም ያንሰዋል።

ሆኖም፥ ባጠቃላይ ስንመለከተው፥ ይህ ሁሉ የሚያሳየው - የሰውም የሆነ የእንስሳት ነፍስ ክቡር እንደሆነ፤ ሰዎችን ሁሉ በጋራ የሚያስተሳስር እውነት መኖሩንም ነው።

ልዩነቶች ከየት መጡ? ከራሳችን ወይንስ ከሰይጣን? በእርግጥ ልዩነቶች የምንላቸው ሁሉ ላይሆኑ ይችላሉ። እኛ ግን አጉል ልዩነቶችን እየፈጠርን ስንጨቃጨቅ በመቆየታችን እራሳችንን በራሳችን ሳንጎዳ አልቀረንም። ስለ መንፈስ ጉዳይ በግልጽ የማይታወቅ በመሆኑ፤ አለማወቃችንም ሳናውቀው ብዙ አሳወቆን ይሆናል፤ አለማወቃችን እያነጫነጨን ምንጊዜም በማወቅ ጉጉት ያንንም - ያንንም ስንነካካ፥ ብዙ እያወቅንም በምንም ሳንረካ እንኖራለን።

በጥንት ዘመናት የሚኖሩ ሰዎች ከዘመናውያኖቹ የማይተናነስ ሃይማኖት እንደነበራቸው፥ ኑሮአቸውም ሥጋዊ ብቻ እንዳልነበረ፥ ዛንግ ዛይ (1020 - 1077 ዓመተ አለም) ከተባለ የኮንፊዩስም ተከታይ የሚከተለው የረቀቀ - ሳይንሳዊና ሃይማኖታዊ ፍልስፍና ተገኝቷል፡-

“ሰማይ አባቴ ነው፤ መሬትም እናቴ ናት። ኢምንት የሆንኩ እኔ እንኳን በመካከላቸው ሥፍራ ተሰጥቶኛል። ስለዚህ ጠፈር - ሰማይን የገነባውን ሁሉ እንደራሴ አካል፥ የሚመራውን ኃይልም እንደ ተፈጥሮዬ መቁጠር ይኖርብኛል። ሰዎች ሁሉ ወንድሞቼና እህቶቼ ናቸው። ሁሉም ነገር ጓደኛዬ ነው።…

የገዛ ቤተሰብህን(ሽን) የሚያሳፍር ሥራ ብትሠራ(ሪ)፥ የሰማይና የምድርን ክብር እንደቀነስክ(ሽ) ይቆጠራል።

ሃብትና ክብር፥ ከድህነት፥ ሃዘን እና ትህትና ጋር ሆነው ሕይወቴን የተሟላ ያደርጉታል።

በሕይወት ሳለሁ ሰማይና ምድርን ሳገለግል እኖራለሁ፤ ስሞትም ዘለአለማዊ ሰላም አገኛለሁ።”

ከሰማይ ካልመጣ በስተቀር፥ በምድራችን ላይ ማወቅም ሆነ አለማወቅ አንጻራዊ ነው መሆን የሚችል እንጂ፥ ፍጹማዊ (ዘለአለማዊ) ሊሆን አይችልም። የማወቃችን እድገቱም ከዚሁ ከአንጻራዊነቱ ጋር አብሮ ነው የሚሄድ። ግን በአንድ የተወሰነች ወቅት ይህንኑ የማወቅም ሆነ የአለማወቅ አንጻራዊነት ተገንዝቦ በሕይወቱ የተሻለውን አማራጭ የሚወስድ ጠቢብ ነው።

ስለ አለም ሃይማኖቶች ሁሉ በመጠቃቀስ እውቀትን መሸመት አላማችን ስላልሆነ፥ በእስላም፥ በክርስቲያን (ፕሮቴስታንት፥ ካቶሊክ/ኦርቶዶክስ)፥ በአይሁድ እና በሂንዱ ሃይማኖቶች ውስጥ የሚገኙ እውነቶችን አጉልተን እንመለከታለን።

ከነልዩነትም በግንዛቤአዊነት በሰላም አብሮ መኖር የሚቻል መሆኑን በየሃይማኖቶቻችን ውስጥ የሚገኙ እውነቶች ያስተምሩናል። ሰዎች እርስበርስ በሃሳብ ተስማምተው በመንፈስ አንድነት እንዳይኖራቸው የሚያደርጉ አንዳንድ አበይት ጉዳዮችን ለይቶ ማወቅም ተስማምቶ ለመኖር ይረዳ ይሆናልና፤ ይህ ከሃይማኖቴ ጋር ይቃረናል የምንለውን በትእግስት እያሳለፍን፥ በግለሰቦች ውስጥ የሚገኘውን ፍጹም እውነት ለማጠናከር እንጂ ለመበርዝ እንዳይሆን ጥንቃቄ እያደረግን፥ በሰው ልጅ አንጎል የሚታሰብ ደስ የማይል (መጥፎ) ሃሳብ ሁሉ በበጎ መንፈስ የሚደመሰስ መሆኑን እያሰብን እንመልከተው።

ከጥንት ጀምሮ እስካሁን ድረስ፥ የሰው ሃይማኖቱ በጥልቀቱ (በወርቃማነቱ) ለጠቢባን ብቻ የሚገለጥ ስለነበረ፥ ጠቢባን ያልሆኑ ሰዎችም የሃይማኖትን ጥልቀት ተራ ከሆነ ገጽታው (ወርቁን ከሰሙ) መለየት ስለሚቸግራቸው፥ የሃይማኖታዊ ፍልስፍና ጽሑፎች በጥቂት ጠቢባን እጅ ብቻ ተወስኖ ቆይቶ ነበር። በዘመናችን ግን፥ በተለይ ድረ ገጽ (ኢንተርኔት) ከመጣ ወዲህ፥ ሰፊው ሕዝብ ከራሱ ሃይማኖት አልፎ፥ የሌሎችንም እያጠና ነው።

ጥበብ ከእግዚአብሔር የሚገኝ እንጂ በአንድ ውሱን ሃይማኖት ተመጻዳቂነት የማይገኝ መሆኑንም እናስበውና፤ በማንኛውም ሃይማኖት ውስጥ ለሰው ልጅ የሚጠቅሙ የጥሩ ሰላማዊ መንፈሶችን ነገር እንመርምር። በእርግጥ፥ ከማንኛውም ሃይማኖት ውስጥ ምድራዊነት ቢወጣለት ንጹሑ መንፈሳዊነት ቁልጭ እንደሚል፤ አይካድም። የሃይማኖቶች አንድነትና የሳይንስም ድጋፍ ለሰው ልጅ የወደፊት እምነትና መንፈሳዊነት ተጨማሪ እውቀት ያስገኝ ይሆናልና፤ በዚሁ አንጻር ሁሉንም እንመልከት።

ከተከታዮቻቸው ብዛት፥ ጥንታዊነታቸውና ታዋቂነታቸው አንጻር - በአለም ላይ ሰባት መደበኛ ሃይማኖቶች አሉ። እነኚህም - አይሁድ፥ ክርስቲያን፥ እስላም፥ ሂንዱ፥ ቡዲዝም፥ የቻይና አጠቃላይ መንፈሳዊና ባህላዊነት (ኮንፉሲያኒዝም፥ ዳኦይዝም እና ቡዲዝምን የሚያጠቃልል) እና የጃፓን አጠቃላይ መንፈሳዊና ባህላዊነት (ሺንቶይዝም እና ዳኦይዝምን የሚያጠቃልል) ናቸው።

የሂንዱ ሃይማኖትም በብዙ መቶ ንዑስ የሃይማኖት ዘርፎች የተከፋፈለ ሲሆን፥ የቡዲዝም እና የሲኪዝምን እምነቶችንም የሚያጠቃልል - ሰዎች በመንፈሳዊና በሥጋዊ ኑሮአቸው ወደ ከፍተኛ ሰብአዊነት የሚዘልቁበትን መንገድ የሚመራ “ሃይማኖት - የኑሮ ዘይቤም” ነው።

<u>ሂንዱ</u>

እግዚአብሔር ራሱን ለአይሁዶች እንደገለጸ፤ ለሌሎችም ሕዝቦች በተለያዩ መንገዶች ገልጿል። በጥንታዊው ጥበብ በሳንስክሪት ቬዳዎች (እውቀቶች) የተጠናቀሩ ጽሑፎች - የሰው ልጅ ለቤተሰባዊ፥ ለማህበራዊ፥ ለሕጋዊና ለሃይማኖታዊ ኑሮው እንደመመሪያ የሚያገለግሉ ናቸው። ከቬዳ ጽሑፎች ውስጥ፥ በተለይ ሃይማኖታዊ ፍልስፍናዊ ጽሑፎች (ኡፓንሻድ) በቀጥታ ከእግዚአብሔር እንደመጡ የሚያምን ነው የሂንዱ ሃይማኖት።

በብሃጋቫድ ጊታ[23] ውስጥ ሳይንስና ሃይማኖት አብረው እጅ ለእጅ ተያይዘው የሚሄዱ እንጂ፥ የማይለያዩ መሆናቸውን፤ ስለ ደቂቃን አካላት (ስለ አተሞችና ሌሎችም)፥ የዳርዊን አይነት ያልሆነው ዝግመተ ለውጥ፥ በጠፈር ውስጥ ያለነው እኛ ብቻ ስላለመሆናችን እና ነፍስ በጠፈር ሁሉ ስለመኖሩ፥ ..ወዘተ....በመጠኑም ቢሆን የሚጠቁም ሃሳብ ይገኝበታል።

በሂንዱ ሃይማኖት ውስጥ ብዙ አይነት የእምነት መከፋፈል ቢኖርም፦ ሥላሴዎች (ብራህማ፥ ቪሽኑ፥ ሺቫ) በሦስትነታቸውና በአንድነታቸው፥ ነፍስ ያላቸውን እና ነፍስ የሌላቸውን ሁሉ በማፈራረቅ እንደሚፈጥሩ፥ እንደሚያቆዩ እና እንደሚያጠፉ ይታመናል።

የተጠቀሱትን ሦስት የተፈጥሮ ክስተቶች (መፍጠር፥ ማቆየትና ማጥፋት) እስከ ጠፈር ድረስ በማተለቅ ወይንም እስከ ጥቃቅን የንጥረ ነገር አካላት በማሳነስ መመልከት ይቻላል። ይህ ጎላ ብሎ የሚታይ የሰው ልጅም ወደ ፍጹማዊነት እስኪጠጋ ድረስ፥ በተደጋጋሚ ይወለዳል፥ ይቆያል፥ ይሞታልም። ከተጠቀሱት ሦስት የተፈጥሮ ክስተቶች መካከል ለጊዜው ብቅ ብለን ብንታይ፥ መጥፋታችን፥ እንደገናም መፈጠራችን አይቀርም።

ይህንን ተደጋጋሚ መሞትና መወለድን ቶሎ ቀጭቶ - ፍጹም ሰላም፥ ፍጹም ደስታ፥ ፍጹም ፍቅር ወደሚገኝበት ዘላለማዊ ሕይወት ለመሸጋገር የሚያስችል ሃይማኖታዊ ትምህርትን የሂንዱ ሃይማኖት ያስተምራል[24]።

---

[23] ይህ ቅዱስ መጽሐፍ በክሪሽና በኩል የተሰጠ፥ ሰባት መቶ ጥቅሶችን የሚያካትት ነው። በክሪሽና ትምህርት ሌሎችንም ሃይማኖቶች ማጠናከር ይቻላል (እንደየእምነታችን)።

[24] http://www.Hinduism.about.com

በአንድ ወቅት ባለ አራት እጆች፥ ጥቁር ሰማያዊ የሆነ ህጻን - ሽሪ ክሪሽና ከንጉሣውያን ቤተሰብ፥ ካለ አባት ተወለደ። በዛን ወቅት የነበረ ንጉሥ ወንድ ልጅ ሲወለድ እንዲገደል ትእዛዝ አስተላለፈ። የክሪሽና ቤተሰቦችም ህጻኑ እንዳይገድልባቸው፥ ሴት የተወለደች ለማስመሰል በልዋጭ ሴት ልጅ ሲፈልጉ፥ የከብት ጠባቂዎች አለቃ ከሆነ ቤተሰብ ደረሱ። ህጻን ክሪሽና እንደ ማንኛውም ህጻን ባለ ሁለት እጅ ብቻ እንዲሆንና ለልዋጭ እንዲያመች ጸለዩ። ጸሎታቸው ተሳካ። ህጻኑን ለአሳዳጊ ሰጡና እነርሱ የአሳዳጊዎቹን ሴት ልጅ በልዋጭ ወሰዱ። ንጉሡ ግን ሴቷን ህጻንም ሊገድላት ቢሞክር፥ ከክሪሽና በመነጨ ኃይል ወደ ሰማይ እየተፈናጠረች፥ በጁ ሊይዛት አልቻለም።

ሽሪ ክሪሽና ከከብት ጠባቂዎች ጋር እየተጫወተ አደገ፤ በከብት ጭራ እየተንተተና፥ በጭቃ እየተጨማለቀ። ዋሽንት መጫወትን የሚያዘወትር ክሪሽና ከህጻንነቱ ጀምሮ፥ ሰይጣኖችና ጋኔሎችን እያጠፋ፥ የተለያዩ አያሌ ተአምራትን ይሠራ ነበር። በአንድ ወቅት ትልቅ ተራራ ከሥሩ በመፈንቀል በሕዝቦች ላይ የጎርፍ ጥቃት እንዳይደርስ አድርጓል።

እያስተማረ (እየሰበከ) አያሌ ተአምሮችንም እየሠራ እድሜው ዘጠና ዓመት በሆነ ጊዜ፥ የወንድማማች ልጆቸ፥ እኔ እነግሥ እኔ እነግሥ በማለት ተጣሉ። ይህንን ጠብ ለማቀዝቀዝና ሰላም ለማምጣት ክሪሽና ብዙ ጣረ። ነገር ግን በአንደኛው ወገን የነበሩት በብዛት መጥፎዎች ስለነበሩ፥ ጠቡን ማብረድ አልተቻለም። ጠቡ እያየለ መጣና፥ ማሃብሃራታ የተባለ ታላቅ ጦርነት ይቀሰቀስ ዘንድ ግድ ሆነ። ሽሪ ክሪሽናም ለጓደኛው ለአርጁና የፈረስ ሰረገላ ነጂ በመሆን፥ እርሱን በማደፋፈርና በማስተማር፥ ጨቋኝ - ፈላጭ ቆራጭ (ሰይጣናውያን) መንግሥታት ሥልጣን እንዳይዙ መጥፎዎቹ እንዲሸነፉ ጥሩዎቹ እንዲያቸንፉ የሚያስችለውን የስነ አይምሮ ዝግጅት በሚያደርግበት ወቅት - ሽሪ ክሪሽና ለአርጁና ያስተማረው ሃይማኖታዊ ፍልስፍና ነው፥ በብሃጋቫድ ጊታ ተመዝግቦ፥ ለኛም ትምህርት ለመሆን የበቃ። (ከብዙ እልቂት በኋላ፥ በጦርነቱ ያሸነፉት ጥሩዎቹ ነበሩ)።

ማንኛውም ከሰማይ የመጣ ትምህርት ለሰብአዊነታችን እንደሚያገለግል እና ጊዜ እንደማይሽረው፤ የእኛም ድርጊቶቻችን ሁሉ ከፍጹም መንፈሳዊነት - አምልኮተ እግዚአብሔር ጋር ካልሆነ በስተቀር የማይሳካ መሆኑን፥ ሽሪ ክሪሽና ለጓደኛው ለአርጁና እንዲህ እያለ ያስተምረው ነበር (ከብሃጋቫድ ጊታ የተወሰደ)።

"..ግዳጅህን ሳታወላዳ ፈጽም፤ ከመሸነፍ (ከመውደቅ) እና ከማሸነፍ (ከመነሳት) ጋር የተያያዙትን ሁሉ እርግፍ አድርገህ ጥለህ። እንዲህ ያለው መረጋጋት ነው ዮጋ ማለት።" ብ.ጊ. 2፡48

"....በሥራቸው ፍሬ መደሰትን የሚሹ ተጨናቂዎች ናቸው።" ብ.ጊ. 2፡49

"እውነተኛ ሰላምን የሚያገኝ ሰው - ግላዊ እርካታዎችን በመሻት የሚመነጩ ምድራዊ ፍላጎቶችን ሁሉ እርግፍ አድርጎ ይጥላል፤ ከውዳሴ ከንቱ (ከሰው ክብር) እና ከግለኝነትም እራሱን ያርቃል..።" ብ.ጊ. 2፡71

ሽሪ ክሪሽና በ3228 ዓመተ አለም ተወልዶ፥ በ3102 ዓመተ አለም (በመቶ ሃያ አምስት ዓመቱ) ሳያረጅ፥ በሥጋዊነቱ ሞተ። ጫካ ውስጥ እንዳለ፥ አንድ አውሬ አዳኝ እግሩን ሲያይ ድኩላ ያየ መስሎት፥ በጦር ወግቶ ገደለው። እርሱ ግን ወደ ዘለአለማዊ መኖሪያው - ወደ ሰማይ ሄደ። በእርሱ ግዛት ሥር የነበረች ድዋርካ የተባለች ከተማም ከባህር በታች ሰመጠች።

የክሪሽናን እና የኢየሱስ ክርስቶስን ታሪክ የሚያመሳስሉ ጽሑፎች - ሁለቱም ከሥላሴዎች መካከል ሁለተኛው እንደሆኑ፥ ሁለቱም ከሰይጣን ጋር የተዋጉ፥ መልካሙን ትምህርት ያስተማሩ፥ በሽተኞችን ያዳኑ፥ ሙታንን ያስነሱ እና ሌሎችም ብዙ ተአምራትን የሠሩ መሆናቸውን ያወሳሉ።[25] አንዳንድ አክራሪ ክርስቲያኖች ግን - "እንዴት የኛን ክርስቶስን፥ በጦርነት ከተሳተፈ፥ ከአስራ ስድስት ሺህ በላይ ሚስቶች ከነበሩት ጋር ታመሳስላላችሁ?" ብለው ይቆጣሉ።

ክሪሽና መሬት የወረደው ከሰው ልጅ የክፉነት ጠባይ ክፉውን ለማውጣት አልነበረም፤ የሰው ልጅ ከራሱ ክፉነት እንዲማር ለማድረግ ነበር እንጂ። ስለዚህ ጦርነት ግዴታ በሆነበት ወቅት፥ መጥፎው እንዳይነግሥ ከጥሩዎቹ ጋር ወገነ። ክሪሽና ያገባቸው ሴቶችም፥ ቀድሞ ባል የነበራቸው፥ በጦርነቱ ምክንያት ባሎቻቸውን በማጣታቸው፥ በህብረተሰቡ ተንቀውና ተጠልተው የተንከራተቱትን ነበር። በአንድ ጊዜ ከሁሉም ጋር እየሆነ፥ ከሃዘናቸውና ከውረደታቸው እያላቀቀ፥ ደስ ያሰኛቸው ነበር።

እግዚአብሔር ከፈለገ በአካላዊው አለም ውስጥም እንደሰው አካላዊ ሆኖ መገኘት ስለሚችል፥ ሽሪ ክሪሽና የእግዚአብሔር በሰውነት መገለጽ እንደሆነ ሁሉ[26]፤ የሰብአዊነት አካላዊ ሰውነቱ ቢቆራረጥ መንፈሳዊ ሰውነቱ የማይቆራረጥ መሆኑንም ነው ክሪሽና በአንክሮ ያስተማረ።

እግዚአብሔር በተለያዩ ምክንያቶች፥ በተለያየ ጊዜና ለብዙ ጊዜያት ወይንም ሁልጊዜ በሰው እየተመሰለ በመካከላችን ይገኛል። በጉልህ ከሚታየው በስተቀር፥ እኛ ብዙ አናውቅም።

---

[25] http://www:religeoustolerance.org

[26] http://www.krishna.com

"Whenever and wherever there is a decline in religious practice…at that time I descend myself." B.G. 4:7[27]

ትርጉም:- "ሃይማኖታዊ ግልጋሎቶች በቀነሱበት በማንኛቸውም ጊዜያቶች እና ሥፍራዎች...በዚያን ጊዜ እኔ ራሴ ወርጄአለሁ።" ብ.ጊ. 4:7

"ልበ ንጹሆች ብጹአን ናቸው፥ እግዚአብሔርን ያዩታልና።" ማቴ. 5፡8 እንዲል፥ የሂንዱ ሃይማኖት ተከታዮች፥ ክሪሽናም እንደ ክርስቶስ ለሚቀርቡት ይቀርባል፤ ንጹህ ልብ ላላቸው ይታያል በማለት ያምናሉ።

ከጊዜ በኋላ የተፈጠሩ ሃይማኖቶች ከመሠረታዊ የሂንዱ ሃይማኖት ጋር ምንም መሠረታዊ ቅራኔ ስለሌላቸው፥ የዚህ ሃይማኖት ፍልስፍና ሌሎች ሃይማኖቶችን ሁሉ የሚቀበል (የሚያቅፍ) ሆኗል። ሦስቱ ጠቢባንም ከምሥራቅ ተነስተው ኮከብን ተከትለው ህጻኑ ወደተወለደበት ወደ ቤተልሔም አመሩ። "..ሰብአ ሰገል:- የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ ወዴት ነው? ኮከቡን በምሥራቅ አይተን ልንሰግድለት መጥተናልና፤ .." ማቴ፡ 2፡ 2 በማለት። አሁንም ጠቢባን የክሪሽና ተከታዮች ለጌታችንና ለመድኃኒታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ይሰግዳሉ።[28]

አንዳንድ ሰዎች - "እናንተ በእግዚአብሔር እናምናለን ትላላችሁ፤ ነገር ግን እምነታችሁን የሚበትን፥ ትኩረታችሁ በእግዚአብሔር ላይ እንዳይሆን የሚያደርግ፥ ከእግዚአብሔር ሌላ የምታመልኩበት ብዙ አማልክት አሏችሁ" ይላሉ። ሂንዱዎች ለዚህ መልስ ሲሰጡ እንዲህ ይላሉ:-

"..ይህ ትክክል አይደለም፤ እኛ የምናምነው፥ አንድ ሁለት ብለው የማይቆጥሩት፥ ወንድ ሴት የማይባል፤ ከአማልክቶች ሁሉ የበላይ የሆነ አምላክ፤ እንዲህ ነው ተብሎ በሰው የማይገለጥ፤ በአንድ ፈጣሪ አምላካችን በእግዚአብሔር (በብራህማን) ነው።

የአንድ እግዚአብሔርን ኃያልነት ከሚገልጡ ቅዱሳን (የእግዚአብሔር አገልጋዮች) ጋር ብንተባበር ደግሞ፥ ወደ ጥሩው ተጠጋን እንጂ ወደ መጥፎ አልሄድንም።

ወርቅ በወርቅነቱ በሰዎች ዘንድ ተወዳጅና ተደናቂ የሚሆነው ለልዩ ልዩ ጌጣ ጌጥ ሲውል ነው። የእግዚአብሔርም ኃያልነት በልዩ ልዩ ጻድቃንና ቅዱሳን በየጊዜው

---

[27] Bhagavad Gita As is: by Devine Grace A.C. Bhaktivedanta Swami Prabhupada (1972, 19830.

[28] "በኢየሱስ ክርስቶስ አለማመን ሞኝነት ነው:" (የታላቁ የክሪሽና ሕሊንዊነት ንቅናቄ መሪ - የፐራሁፓዳ ንግግር (ከድረ ገጽ)።

ይገለጻል። እኛም ይህንኑ የእግዚአብሔርን ኃያልነት በተለያዩ መንገዶች አስተጋባን እንጂ፥ የምናመልክበት አምላካችን ብራህማን ብለን የምንጠራው አንድ እግዚአብሔርን ብቻ ነው።

የፍጹም እውነት ምንጭ አንድ ብቻ ነው ሊሆን የሚችለው። የእርሱም ስም ክርስቶስ ቢባል፥ ክሪሽና ቢባል፥ አዶናይ ቢባል ወይንም አላህ ቢባል ከፍጥረታት ሁሉ በላይ የሆነ አምላካችን የምናምንበት ለሁላችም አንድ መሆኑ አይቀርም። ምክንያቱም የፍጹማዊነትም ብዛቱ ከአንድ አይበልጥም፤ እርሱም ፍጹም የሆነው ፈጣሪ አምላካችን እግዚአብሔር ብቻ ነው።”

እግዚአብሔር የጠፈር ሁሉ - ለሚታይና ለማይታዩ አለማት ሁሉ ዋና አስተዳዳሪ ሆኖ፥ የእግዚአብሔር አገልጋዮች የተባሉት (demigods - ሰዎች ሆነው ግን ለእግዚአብሔር በመቅረባቸው እንደ ንዑስ እግዚአብሔሮች የተቆጠሩ) በእግዚአብሔር ሥር የተለያዩ ሥራዎችን እንዲሠሩ ኃላፊነት የተሰጣቸው ናቸው። ለምሳሌ፡- ኢንድራ የዝናብ ተቆጣጣሪ፥ ቫዩ የአየር ተቆጣጣሪ፥ ቫሩና የውሃ…ወዘተ።

ለተጠቀሱት ንዑስ እግዚአብሔሮች ሁሉ፥ አንድ ፍጹም አምላክ - የበላይ አስተዳዳሪ (እግዚአብሔር) ባይኖራቸው ኖሮ፥ ተፈጥሮ ምስቅልቅሉ የወጣ - ዘለአለማዊ ትርምስ ይሆን ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር ተፈጥሮን በስነ ስርዓት ያስተዳድራል፤ ሰውም የአግዚአብሔርን ፈቃድ እየፈጸመ እንዲኖር (እርሱ በሚፈልገው መንገድ እንዲሳተፍ) ተፈጠረ። አንዳንድ ሰዎች ግን ፈጣሪያቸውን ለራሳቸው ጉዳይ አስፈጻሚነት እንዲገለገሉበት ይሻሉ። “ይህንን አድርግልኝ፤ ይህንን ፈጽምልኝ” እያሉ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሳይሆን የራሳቸውን ምኞትና ፍላጎት ለሚሟላት ሲሉ ይጸልያሉ። ለጸሎታቸው መልስ ሲያጡም ያዝናሉ።

ሰው ምኞትና ፍላጎትን አሳንሶ፥ ተፈላጊ የሆነውን ተሳትፎውን በሚገባ እንዲያሟላ ቢጸልይ ደስታን ይሸምታል። ይህንን ጉዳይ በምሳሌ እንመልከተው፡-

ከእለታት አንድ ቀን እንጨት እየለቀመችና እየሸጠች ራሷን የምታስተዳድር አንዲት ድሃ ሴት ከመጠን በላይ እንጨት በራሷ ላይ ተሸክማ ስትሄድ፥ በድንገት እንጨቱ ከራሷ ላይ ወደቀ። ደክሚት ስለነበር፥ ጎንበስ ብላ እንጨቱን ለማንሳት ብትሞክር አልቻለችውም። ቀና ስትል፥ ከፊቷ ሰው ጠጠው ብሏል (ቁሟል)።

“አንተ ማነህ?” ብትለው፥

“እኔ እግዚአብሔር ነኝ” አላት።

እርሷም - “እንግዲያውስ አንተ በእውነት እግዚአብሔር ከሆንክ፥ የለቀምኩትን እንጨት ከመሬት አንስቼ ከራሴ ላይ እንዳስቀምጠው እርዳኝ” አለችው።

ሴቲቱ ወደ እንጨት ለቀማ በምትሠማራባት ወቅት ሁሉ - ምንም ሳይሠሩ፥ በትላልቅ ቤት ውስጥ የሚንፈላሰሱ የቤት እመቤቶች መኖራቸውን እያስተዋለች፥ እርሷም በልቧ በቅናት ስሜት ተገፋፍታ -

"እንግዲያውስ አንተ በእውነት እግዚአብሔር ከሆንክ፥ እባክህ እኔንም እንደነኚህ ሴት ወይዘሮዎች ሃብታም አድርገኝ.." ብላ አልለመነችም፤ እንጨቷን ተሸክማ ሄደች እንጂ።

"የእግዚአብሔር ፍላጎት - የእኔ የደሃይቱ ሴት እድል ፈንታ እንጨት ለቅሜ እንድኖር ከሆነ፥ እኔ በርሱ ሥልጣን አልገባም" ብላ፥ ሌላ ጥያቄ አላበዛችበትም፤ "እርሱ በእውነት እግዚአብሔር ከሆነ፥ ሁኔታዬን (ኑሮዬን) ሁሉ መመልከት አያቅተውም" ብላ፥ እምነቷን ሳታጓድል ሁሉን ነገር ለእርሱ ተወችለት እንጂ።

ድሃዩቱን ሴት እንጨት ለቃሚ ያደረጋት እግዚአብሔር አይደለም፤ በሕይወት ባለችበት ዘመንና ካዛ በፊት ያሳለፈችው ሕይወት ውስጥ የፈጸመቻቸው ድርጊቶች ሁሉ፥ በምክንያታዊ መነሻና፥ በድርጊቶች ፍጻሜ እየተፈራረቁ የአሁኑ ኑሮዋ ወስጥ ነከሯት እንጂ። ይህ ነው፥ ካለውጤት የማይቀር፥ ፍሬአማ እንቅስቃሴ፥ የሰውን ዕድል - ዕጣ ፈንታ የሚቀይስ፥ ወሳኝ የሰው እድሉ - ካርማው።

የምድር ስቃይና መከራ የእግዚአብሔር ቅጣት አይደለም፤ በሰው ልጅ ቁርጥርጥ ሥጋዊ ሕይወት ውስጥ የሚከሰት የድርጊቶች ሁሉ ውጤት ነው እንጂ። ሥቃይና መከራን የምንፈጥር እኛው እንደመሆናችን መጠን፥ ደስታንም የምንፈጥር - የዕድላችን መሃንዲሶች እኛው ነን። ይህንን ጉዳይ፥ ምድራዊ ፍላጎቶችን ሁሉ እርግፍ አድርገው፥ በየገዳማቸው ውስጥ ተደስተው ከሚኖሩ፥ ከባህታውያን ቡዲስት ወንድሞቻችን በበለጠ እንማራለን።

አንዳንድ ሰዎች፥ ሃይማኖታቸውን ላላ ያደርጉትና፥ ለጊዜያዊ ምድራዊ ጥቅም እየተደለሉ፥ ወደ እግዚአብሔር መጠጋትና ከርሱ ጋር የጠበቀ ግንኙነት መመሥረት ያቅታቸዋል። ከነኚህም መካከል፥ አንዳንዶቹ ለቀን ተቀን ኑሮአቸው ብቻ በማሰብ፥ መላእክትን "እንዲህ አድርጉልን፤ ይህንን ፈጽሙልን... " እያሉ ይማጸናሉ፤ ከአማልክት ጋር የጠበቀ ግንኙነት ከመመሥረታቸውም የተነሳ፥ አማልክትን እስከ ማምለክ ፈጣሪ አምላካቸውንም እስከ መርሳት የሚደርሱም አይታጡም። "የማሰብ ችሎታቸው ዝቅተኛ የሆኑ ሰዎች ለአማልክቶች ይሰግዳሉ፤ ፍሬአቸው ጊዜአዊና ውሱን ነው።..." ብ.ጊ. 7፡21 እንቅስቃሴዎቻችንን ሁሉ በሦስት አኳያ መመልከት ይቻላል።

1ኛ) በአጠቃላይ ምድራዊ ጥቅምን ከመሻት ጋር ያልተያያዘ እንቅስቃሴ - ወደ ጥሩነት የሚመራ ጥሩነት (ምድራዊ ጥቅምን የሚያስገኝም ቢሆን)።

2ኛ) ምድራዊ ጥቅምን ከመሻት ጋር የተያያዘ ምኞታዊ እንቅስቃሴ - ወደ ኃጢአት የሚመራ - ምድራዊነት።

3ኛ) ካለ ምንም መንፈሳዊ መመሪያና ሞራላዊ ግዴታ በግድየለሽነት የሚደረግ እንቅስቃሴ - ወደ ኃጢአት የሚመራ ድንቁርና።

እንቅስቃሴዎቻችን ሁሉ ከተጠቀሱት አቢይ መደቦች አይወጡም። የሰው ልጅ እንቅስቃሴዎቹን በመቆጣጠር፥ ከምድራዊ ፍላጎቶች እራሱን እያላቀቀ፥ ሁልጊዜ ስለ ፈጣሪ አምላኩ ካለማቋረጥ የሚያስብ ቢሆን የእንቅስቃሴዎቹ ሁሉ ጥሩነት ወደ እግዚአብሔር ያስጠጋዋል።

ዘለአለም የማይጠፋ - የተትረፈረፈ እውቀትና ችሎታ፥ ፍቅር፥ ሰላምና ደስታ፥ ሁሉን ማድረግ ከሚችል አምላክ ዘንድ የሚገኝ መሆኑን የተረዳ፥ የዚህን አለም ጊዜአዊ ፍላጎቶች ሁሉ እርግፍ አድርጎ ይተዋል።

ከምድራዊነታችን ባሻገር መመልከትን - ስለ ምድራዊ ችግርም ሆነ ደስታ አለማሰብን፥ በእግዚአብሔራዊ ንቃተ ሕሊና ውስጥ መግባትን እና ከፈጣሪ ጋር ግንኙነትን መመሥረትን፥ ባጠቃላይ ይህንን እና የመሳሰለውን ይመስላል ከብሃጋቫድ ጊታ የምንማረው።

ምድራዊ ፍላጎቶችን ሁሉ ሰርዞ፥ በመንፈስ አርቅቆ ከመሄድና በማያቋርጥ ጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት ከመመሥረት የበለጠ ምን አለ? ወደ እግዚአብሔር በመጠጋት ብቻ ሁሉ ነገር ይገኛል። ይህንን ነበር በአንክሮ ክሪሽና ያስተማረን፤ እንዲህ እያለ፡-

“እሳት በጭስ እንደሚሸፈን፥ መስተዋት በአቧራ እንደሚሸፈን፥ ወይንም ጽንስ (ሽል) በማሕጸን እንደሚሸፈን፥ እንዲሁም የሰው ልጅ ውስጣዊ ማንነቱ በምድራዊ ፍላጎቶች ይሸፈናል።” ብ.ጊ. 3፡38

“ከምድራዊ ፍላጎቶች የተነሳ በሚገኝ ስሜት የማይጠመድና ምንጊዜም አስተሳሰቡ ከእግዚአብሔር ጋር የሆነ ሰው፥ በውስጠ መነፈሱ የመጠቀ፥ ፍጹም ደስተኛነት እና ፍጹም ነፃነት የሚሰማው ነው።” ብ.ጊ. 5፡21

ታላቁ መሪያችን ማሐተመ ጋንዲ መሠረታዊ ፍልስፍናው ከክርስቶስ ትምህርት የተለየ አልነበረም። ምድራዊ ቁሳቁሶችን ሁሉ እርግፍ አድርጎ ትቶ፥ መጾም፥ መጸለይ፥ ሱባኤ መግባት፥ አሂምዛ (ጠብ አልባ) ኑሮ መኖር፤ የሳታያግራሃ (እውነትና ጽናት) መርሆ፥ የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት የተከተሉት፥ የሁላችንም መመሪያ መሆኑ ነው።

በእግዚአብሔር መስተዳድር ውስጥ የእያንዳንዳችን ተሳትፎ ተፈላጊነት ከየት ተነስቶ ወዴት እንደሚደርስ እኛ ለማወቅ ስለማንችል፤ ሁሉን ነገር ለእግዚአብሔር ጥለን፥ እርሱ የሚፈልገውን ተሳትፎአችንን በሚገባ እንፈጽም ዘንድ እየጸለይን ብንኖር ደስተኞች እንሆናለን። ጥሩ ጥሩውን እየተመለከቱ፥ ካለ እብሪተኛነት በትእግስት የሚኖሩ ብጹአን ናቸው።

ከምናውቃቸው በእግዚአብሔር መንፈስ ከሚመሩ እስላምና ክርስቲያን ወገኖቻችን ጋር እጅ ለእጅ ተያይዘን፥ የሰው ልጅ ለሃይማኖት ሳይሆን፥ ለእግዚአብሔር እንዲገዛ በአንድነት እንሰብካለን። የዚያን ጊዜ እውነተኛ ሃይማኖተኛ ሁሉ ከጎናችን ይቆማል። ለአንድ እውነተኛ አምላክ፥ ለቸሩ ፈጣሪ እግዚአብሔር አምላካችን በእውነት የምንሰግድ ሁሉ አብረን በእርቅ እና በሰላም መኖር አያቅተንም።

## <u>ከአይሁድ እስከ ክርስቲያን</u>

የምሥራቁን አለም ያጥለቀለቁ ሃይማኖቶች ከሂንዱነት ጀምሮ የነዋሪውን ሕዝብ መንፈሳዊ ኑሮ እንደቀየሱት ሁሉ፥ ከመካከለኛው ምሥራቅም ጀምሮ አለምን ያጥለቀለቁ ሦስት ሃይማኖቶች (አይሁድ፥ ክርስቲያን እና እስላም) የአብዛኛውን ሕዝብ መንፈሳዊ ኑሮ ቀይሰውታል።

ባለፉት ዘመናት ለምድራችን ከተላለፉት ሃይማኖቶች ውስጥ አንዳንድ ጠቃሚ እውነቶችን ለግል ሃይማኖት ማጠናከሪያ ማድረግም ታላቅ ጥበብ ነውና፤ የሚቻለንን ያህል እንነብኛቸው።

በኑሮአችን "በሚመሳሰሉ ነገሮች" ብዛት ምክንያትም መንፈሳዊ ንቃትን ሳናገኝ አልቀረንም። "የሚመሳሰሉ ነገሮች" መብዛታቸው ሁለት አለማት መኖራቸውን ማመሳከሪያም ሊሆን ይችላል። ግን አካላዊ ያልሆነው አለም ከዚሁ ካጠገባችን መኖር አለመኖሩን አላወቅንም። ስለዚህ በአለማችን ላይ ከግለሰብ እስከ ሕብረተሰብ ድረስ ምድራዊ ትርጉም የማይሰጣቸው ሁኔታዎች - ቁስ አካላዊ ገለጻ የማይገኝላቸው ድርጊቶች - በተደጋጋሚ ሲፈጸሙ እያየን፥ ግን እንዴትና ለምን እንደሆነ መግለጽ ስለማንችል ብቻ ያየነውን ማመን ያቅተናል።

በምድር ያለ አካላዊ ሕይወት በሰማይ ከሚኖር ሰማያዊ ሕይወት ጋር የሚገናኝበት መድረክ ምን አይነት ነው? ከማይታየው አለም የሚተላለፍልን ነገር ቢኖር፥ ያ ለእነርሱ ተራ ድርጊት፥ ለኛ ደግሞ ተአምር ይሆናል።

አጋጣሚዎችም ምድራዊና ሰማያዊ ምክንያቶች ሊኖራቸው ይችላል። ምክንያታዊ አካላዊ ሂደት እንዳይገታ መንፈሳዊ ክስተት ድጋፍ የሚሰጥ ቢሆን፥ የሁለቱን ግንኙነትና ልዩነት ማን ያውቃል?

ተአምራታዊ ድርጊቶች ከግለሰብ አልፈው ወደ ሕብረተሰብ እየገቡ አስተምረውናል። ለምሳሌ፡- በ175 ዓመተ አለም (ከክርስቶስ ልደት በፊት) የግሪኮችና የሦሪያ ወታደሮች፥ የኢየሩሳሌምን ቤተመቅደስ አፍርሰው በውስጡ የሚገኘውንም ንዋየ ቅዱሳት መዝብረው፤ ሰውንም በእግዚአብሔር እንዳያመልኩ (እንዳይሰግዱለት) ሲከላከሉ በነበረበት ወቅት፥ አንድ ማታትያስ የሚባል ሽማግሌ የአይሁድ ካህን እነኚህን ወራሪዎች ለመቋቋም ከመንፈስ ልጆቹና ግብረ አበሮቹ ጋር ተነሳ። ከሦስት ዓመት ውጊያ በኋላ፥ የግሪኮችና የሶሪያ ወታደሮችን አቸንፈው ቤተ መቅደሳቸውን ለማስመለስ በቁ።

ማታትያስ እና ግብረ አበሮቹም ይህንን ድል ምክንያት ድል በማድረግ፥ በቤተ መቅደሱ ውስጥ ገብተው መቅረዝ (ኩራዝ) አብርተው ለመጸለይ ፈልገው ሳለ፥ መቅረዛቸውን የሚያበሩበት ዘይት ከአንድ ቀን በላይ የሚያቆያቸው ሆኖ አልተገኘም። በዚያን ዘመን የመብራት ዘይት ተጨምቆ የሚዘጋጀው ከስምንት ቀን ባላነሰ ጊዜ ውስጥ ነበር።

ተስፋ ባለመቁረጥ - "ይህንኑ ዘይት ተጠመቅን ጸሎታችንን እንጀምር፤ እስከዛውም ስምንት ቀን የሚፈጀው የዘይት መጭመቅ ሥራ ይጀመር.." ብለው፥ ጸሎታቸውን ቀጠሉ። ያ ለአንድ ቀን ብቻ የሚበቃ ዘይት በተአምር ተበራክቶ፥ ልክ አዲሱ ዘይት ተዘጋጅቶ እስኪቀርብ ድረስ - ለስምንት ቀን ሲያበራላቸው ቆየ።

ይህ ሁኔታ የተፈጸመው እግዚአብሔር ምንጊዜም ከኛ ጋር በመሆኑ ነው በማለት ይህንን ታላቅ ተአምር እስከዛሬ ድረስ ሃኑካ በተባለው በዓላቸው፥ ስምንት ቀን ሙሉ መቅረዛቸውን እያበሩ ያከብሩታል። "የእግዚአብሔርን ሥራ እዩ - ተመልከቱ!.." የሚል መልእክታቸውንም ለእግረኛው ሁሉ ለማስተላለፍ ሲሉ፥ መቅረዙን የውጪ ተላላፊ እንዲያየው በየቤታቸው መስኮት ያስቀምጣሉ።

የሰውና የእግዚአብሔር ፈቃድ አንድ መስመር ይዞ በአንድ ላይ ሲስተካከል መንፈሳዊ ተአምር ይገለጻል። በቂ ምክንያትና የሰው ፈቃድ ከሌለ፥ የእግዚአብሔርም ተአምር አይሰጥም።

ይህ እና የመሳሰለውን ተአምር እንደ ሰብአዊነት (አለም አቀፍ) ተአምር በመውሰድ፥ መለኮታዊ ኃይል ስለመኖሩ ማስረጃ መሆን አለበት ብለን፥ የእስራኤል ሕዝቦች እንደ አንድ ሰው ሆነው ያስተላለፉልንን መንፈሳዊ ታሪኮች በማያያዝ፥ ለሃይማኖታችን መነሻ፥ ለእምነታችንም የጋራ ማረጋገጫ አደረግን። ይህንን የመሳሰሉ

መንፈሳዊ ታሪኮች በሁሉም አገር እንደሚፈጸሙ እሙን ሆኖ ሳለ፥ ሳይጻፍ በመቅረቱ ብቻ ሳይታወቅ ይቀራል።

አንዳንድ የመንፈሳዊነታችንን ነገር እንድንመለከተውና ከተጻፈው ውጪ ያለውንም እንድንፈላሰፍበት፥ ከዚህ የሚከተለውን የእምነታችንን መነሻ እጅግ በማሳጠር አቅርበናል።

ከሰዎች መካከል፥ አንድ ጥሩ ሰው ከሜሶፖታሚያ (ከኢራቅ) ተነስቶ በከንአን ምድር ላይ ድንኳን ጥሎ ይኖር ነበር። ይህ ሰው አብርሃም ይባላል። አብርሃም ጥሩ ሰው (ደግ ሰው) እግዚአብሔርን ከሙሉ ልቡ የሚያምን፥ ጻድቅ ስለነበር፥ እግዚአብሔር አብርሃምን ወደደው።

እግዚአብሔር ለአብርሃም፥ ሰማይና ምድርን የፈጠረ ኃያል አምላክ መሆኑን እንዲገባው አድርጎ አስረዳው። ሰማይና ምድርን የፈጠረ የኃያል አምላካችን የእግዚአብሔር መገለጥ፥ ይህ ለአብርሃም ከእግዚአብሔር የተነገረ ቃል - ከዘር ዘር እንዲተላለፍ ያህል ሆነ ማለት ነው (መሆኑን ከመንፈሳዊ ታሪካችን እናገኘዋለን)።

ግብጻውያን አውሬና ሰው በመሳሰሉ ጣዖታት ሲያመልኩ፥ የአብርሃም ልጆች (እብራይስጦች) ግን እስከ መጨረሻው ድረስ እምነታቸውን ከፈጣሪ አምላካቸው አላዛነፉም።

እግዚአብሔር ለአብርሃም ሁለት ልጆችን (እስማኤልን እና ይስሃቅን) ሰጠው። እግዚአብሔር አብርሃምን "የምትወደውን ልጅህን ይስሐቅን ይዘህ ወደ ሞሪያም ምድር ሂድ፤ እኔም በምነግርህ በአንድ ተራራ ላይ በዚያ መስዋዕት አድርገህ ሰዋው አለ።" ዘፍ. 22፡ 2 የሰው ልጅ፥ ካወቀ፥ ከገባው፥ በእውነትም ከልብ ሊያምን የሚችል መሆኑን - አብርሃም እግዚአብሔርን በመንፈሱ የሚመስለው መሆኑን አስመሰከረ (ሰው በጥሩው መንፈሱ እግዚአብሔርን ይመስላል - ማንም የሰው ልጅ እንደ አብርሃም ጥሩ ከሆነ፥ እግዚአብሔርን በመንፈሱ ይመስለዋል)።

ከይስሃቅ ሁለት ልጆች - ኤሳው እና ያዕቆብ - ተወለዱ። ኤሳው አውሬ አዳኝ ስለሆነ ከቤት አይቀመጥም ነበር። ያዕቆብ ግን ከቤት የማይጠፋ ብልጥ - ወንድሙን የሚያታልል ጥቅመኛ ነበር።

ያዕቆብ ከራሄልና ከሊያ አስራ ሁለት ልጆች ወለደ። የያዕቆብ አስራ ሁለቱ ልጆቹ ተባዝተው አስራ ሁለት ነገዶች ሆኑ (እስራኤል)። ከእስማኤልና ከኤሳውም የአብርሃም ልጆች በአፍሪካና በእስያ ተባዝተዋል።

ከያዕቆብ የመጨረሻው ልጁ ቀጥሎ ያለውን ዮሴፍን አባቱ (ያዕቆብ) ከሌሎቹ ልጆቹ ሁሉ አስበልጦ ይወደው ነበርና፤ ወንድሞቹ ቀኑበት። ሊገድሉትም አስበው ነበር፤

ግን ዮሴፍን በመሸጥ ተስማሙና ወደ ግብጽ ለሚመላለሱ ነጋዴዎች ሸጡት። ነጋዴዎቹም ግብጽ አገር ወሰዱትና ለአንድ ጌታ ሸጡት።

ጌታውም ዮሴፍን ወደደው። የቤቱን ሃብት ሁሉ አስረከበው። ዮሴፍም መልኩ ቆንጆ ስለነበረ፥ የጌታው ሚስት አብሯት እንዲተኛ አጥብቃ ለመነችው። እምቢ ሲላት በግድ ልብሱን አወለቀችበት። እርሱም ልብሱን ጥሎላት ሸሸ። ባሏም በመጣ ጊዜ - "ይኸውና ያንተ አሽከር ሊደፍረኝ ፈልጎ ሳለ፥ እኔ በፍርኃት ስጮህ፥ እርሱ ደንግጦ ልብሱን እዚህ ጥሎ ሸሸ.." ብላ በሃሰት ወነጀለችው። ጌታውም ተናዶ ከእስር ቤት አስገባው።

ዮሴፍ በእስር ቤት ሳለ በሕልም ፈቺነት ታውቆ ስለነበረ፥ ከቤተ መንግሥት ተጠርቶ ገባ። ከዚያም ግብጻውያንን ከረሃብ ያስወጣ ወሳኝ ሕልም ለንጉሡ ስለተረጎመለት ታላቅ ሹመት ተሰጠውና፥ ከንጉሡ ቀጥሎ እንደልቡ በግብጽ ምድር ያዝና ይገዛ ጀመር።

በከንአን ምድር ረሃብ ስለገባ፥ የያዕቆብ ልጆች (የዮሴፍ ቤተሰቦች) ድርቅ ወዳልደረሰበት አገር መሰደድ ግድ ሆነባቸውና፥ ጓዛቸውን ጠቅልለው ወደ ደቡብ ጉዞ ጀመሩ። ግብጽ እንደደረሱ ወደ ዮሴፍ ሄዱ፤ ዮሴፍም ቤተሰቦቹ ከፊትለፊቱ ቆመው ሲያያቸው እጅግ አዘነ። እርሱ አወቃቸው፤ እነርሱ ግን አላወቁትም ነበር።

በዮሴፍ ፈቃድ ያዕቆብና ልጆቹ ከግብጽ ምድር ተቀመጡ፤ ከዛም ተባዙ። የግብጽ መንግሥት እነኚህን እብራይስጦች (የያቆብ - የእስራኤል ዘሮች) በባርነት ቀንበር ውስጥ ከተታቸው። ከነርሱም ከፍተኛ ጥቅም ስላገኘ፥ ከሚችሉት በላይ የጉልበት ሥራ በማሠራት አደከማቸው። እነርሱም መከራ ስለበዛባቸው ተጎሳቆሉ፤ በመሪር ሃዘንም የሚያለቅሱ ሆኑ። "...እግዚአብሔር እባክህ ድረስልን!..." እያሉ በጩኸት ተጣሩ፤ ጸለዩ (ለመኑ)።

እግዚአብሔር የእስራኤሎችን ጩኸት ሰማ። የሙሴ መወለድ የእግዚአብሔር ፈቃድ የሚከሰትበት ሆነ። በዚያን ወቅት የእስራኤል ዘር መብዛት የግብጹን ንጉሥ አሳስቦት ስለነበር፥ ከእስራኤሎች የሚወለድ ወንድ ልጅ ሁሉ እንዲገደል አዘዘ።

እብራይስጢ የሙሴ እናት ልጇን (ሙሴን) በቅርጫት አድርጋ ቅርጫቱ ውስጥም ውሃ እንዳይገባ በቅርጣን ለስና፥ የንጉሡ ልጅ ገላዋን ወደምትታጠብበት ወንዝ ላይ አስቀመጠችው። የንጉሡ ልጅ ይህንን ልጅ ባገኘች ጊዜ ደስ ብሏት ልታሳድገው ፈለገች። ጡት የምታጠባ ሴትም ስትፈልግ፥ የገዛ እናቱን ከወንዙ ዳር ቆማ አገኘቻትና ቀጠረችለት።

ሕጻኑ ሙሴ፥ እርሱ ራሱ ከእብራይስጥ ወገን መሆኑን ሳያውቅ፥ ከቤተ መንግሥት አደገ። ነገር ግን በየጊዜው የሚያስተውለው የግብጻውያን ግፍ እጅግ ያሳዝነው ነበር።

ከእለታት አንድ ቀን፥ አንዱ ግብጻዊ አንዱን እብራይስጥ በግፍ እየደበደበ ሊገድለው ሲል ተመለከተ። ሙሴ የእብራይስጡን ሕይወት ለማዳን ያደረገው የጉልበት ትንንቅ (ትግል) የግብጻዊውን ሕይወት ማጥፋት ሆነበት። ይህ ድርጊት በቤተ መንግሥት አካባቢ የተሰማ መስሎት፥ ሙሴ ወደ በረሃ ኮበለለ (ተደበቀ)። ከዚያም ሆኖ ሳለ፥ እግዚአብሔር እንደ እሳት በሚነድ፥ ግን በማያቃጥል ሁኔታ ተገለጠለት።

ከዛን ጊዜ ጀምሮ ሙሴ በእግዚአብሔር መንፈስ ክልል ውስጥ በመሆን፥ ወደ ግብጽ እየተመላለሰ፥ ልዩ ልዩ ተአምራትን ለንጉሡ በማሳየት፥ ወገኖቹ የሆኑትን እብራይስጦችን ባህረ ኤርትራን ተሻግረው ከግብጽ ምድር እንዲወጡ አደረገ ። በሙሴ መሪነት ጠቅላላ የእስራኤል ልጆች ሲና ምድረ በዳ ገቡና ከዛ ሰፈሩ።

እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ለምክንያት ወደርሱ ጠራቸው፡- “..ሙሴም ወደ እግዚአብሔር ዘንድ ወጣ። እግዚአብሔርም በተራራው ጠርቶ አለው - ለያዕቆብ ቤት እንዲህ በል፤ ለእስራኤልም ልጆች እንዲህ ንገር፡- በግብጻውያን ያደረግሁትን፥ በንስርም ክንፍ እንደተሸከምኋችሁ፥ ወደ እኔም እንዳመጣኋችሁ፥ አይታችኋል። አሁንም ቃሌን በእውነት ብትሰሙ፥ ኪዳኔንም ብትጠብቁ፥ ምድር ሁሉ የእኔ ናትና፥ ከአሕዛብ ሁሉ የተመረጠ፥ ርስት ትሆኑልኛላችሁ። እናንተም የካህናት መንግሥት፥ የተቀደሰም ሕዝብ ትሆኑልኛላችሁ..።” ዘጸ. 19፡ 1-6

ሙሴ የእግዚአብሔርን ቃል ተናገረ። ሕዝቡም በአንድ ቃል እግዚአብሔር ያለውን ሁሉ እናደርጋለን አሉ። ሙሴም ሕዝቡን ቀደሳቸው። እነርሱም ልብሳቸውን አጥበው ከሦስት ቀንም በኋላ ወደ ሲና ተራራ ቀረቡ። ከዚያም እግዚአብሔር ራሱ አስርቱን ትእዛዛት ተናገረ።

ሕዝቡም የእግዚአብሔርን ንግግር ሲሰሙ በጣም ስለፈሩ፥ “ከዛሬ ጀምሮ አንተ አናግረን እንጂ፥ እግዚአብሔር አያናግረን” ብለው ሙሴን ለመኑት። እርሱም - “እሺ እናንተ ግን እግዚአብሔርን መፍራትን በልባችሁ ይዛችሁ፥ ኃጢአት ከመሥራት ተቆጠቡ፤ የእግዚአብሔርም እናንተን ማናገር ለዚሁ ነው...” አላቸው። ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር ሙሴን ጠራው። “.. ወደ እኔ ወደ ተራራው ውጣ፥ በዚያም ሁን፤ እነርሱን ታስተምር ዘንድ፥ እኔ የጻፍኩትን ሕግና ትእዛዝ የድንጋይም ጽላት እሰጥሃለሁ አለው።” ዘጸ. 24፡ 12

እግዚአብሔር ሙሴን ሲያነጋግረው አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ቆየ። በዚህን ጊዜ ሕዝቡ አጉረመረሙ። የሙሴን ወንድም አሮንን፡- በፊታችን የሚሄድ አማልክት አንተ

ሥራልን ብለው አስቸገሩት። እርሱም ወርቆቻችሁን አምጡ ብሎ ወርቆቻቸውን ሁሉ ሰብስቦ አቀለጠና የወርቅ ጥጃ ሠራላቸው። ሕዝቡም ከግብጽ ምድር ያወጣቸውን አምላክ ረስተው በጥጃ አመለኩ።

ሙሴ በሲና ተራራ እንዳለ፥ የእስራኤል ልጆች ሥራ፥ ድርጊታቸው ሁሉ እጅግ ያስቆጣው መሆኑን እና ሊያጠፋቸውም መፈለጉን እግዚአብሔር ለሙሴ ነገረው። ሙሴም እጅግ በማዘን በአምላኩ በእግዚአብሔር ፊት እንዲህ ብሎ ጸለየ፡-

"ቁጣህ በታላቅ ኃይልና በጽኑ እጅ ከግብጽ ምድር ባወጣኸው በሕዝብህ ላይ ስለ ምን ተቃጠለ? ግብጻውያንስ - በተራራ መካከል ሊገድላቸው፥ ከምድርም ፊት ሊያጠፋቸው፥ ለክፋት አወጣቸው ብለው ስለምን ይናገራሉ? ከመአትህ ተመለስ፤ ለሕዝብህም በክፋታቸው ላይ ራራ።" ዘጸ. 32፡ 12 - 13

እግዚአብሔርም በሙሴ ጸሎት (**አማላጅነት**) በሕዝቡ ላይ ያሰበውን ጥፋት ተወው። ሙሴም ከተራራ በተመለሰ ጊዜ፥ ያንን የወርቅ ጥጃ ሲያመልኩ ተመለከተ። ከድንጋጤ የተነሳ፥ በእጁ የያዛቸው ጽላቶች ከእጁ ወደቀው ተሰባበሩ። ዳግመኛም ሙሴ የድንጋይ ጽላቶች ሠርቶ አስርቱ ትእዛዛትን ይዞ ተመለሰ።

ሙሴ በተራራው ላይ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት በቆየበት ወቅት ስለ ታቦት አሠራር እግዚአብሔር ነግሮት ነበር።

"በመካከላቸውም አድር ዘንድ መቅደስ ይሥሩልኝ። እኔ እንደማሳይህ ሁሉ፥ እንደ ማደሪያው ምሳሌ እንደ እቃውም ሁሉ ምሳሌ እንዲሁ ሥሩት። ከግራር እንጨትም ታቦትን ይሥሩ..." ዘጸ. 25፡ 9 - 16

"መጋረጃውንም ከሰማያዊ ከሐምራዊም፤ ከቀይም ግምጃ ከተፈተለ ከጥሩ በፍታም (ሐር) አድርግ... "ዘጸ. 26፡ 31

እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከበረሃ እየመገባቸው፥ እነርሱም አምላካቸውን እያመለኩ፥ መስዋእትን እያቀረቡ፥ ትእዛዛቱን በመከተል በሚኖሩበት ወቅት፥ አንዳንድ ተንኮለኞች በሚያናፍሱት ምድራዊ ወሬ ብዙዎች ተታለሉ። የሚበሉትንም ከሰማይ የሚመጣላቸውን መና - "እኛ ይህንን መና በየቀኑ መመገብ ሰለቸን፥ ሰውነታችንም ሥጋ ባለማግኘቱ ደረቀ..." ብለው አማረሩ። ሙሴም የሕዝቡን ማጉረምረም ወደ እግዚአብሔር በወሰደ ጊዜ፥ እግዚአብሔር ተቆጣ፤ ከባህር ታላቅ ነፋስ እንዲነፍስና ድርጭቶች በየድንኳኑ እንዲፈሱ አደረገ። ሕዝቡም ድርጭቶችን እየለቀሙ ለመብላት ጎምጅተው፥ ሥጋውን ገና ሳያኙኩት፥ ከጥርሳቸው መካከል እንዳለ፥ መቅሰፍት መጣባቸውና ብዙዎች በበሽታ አለቁ።

በሲና በረሃ ሳሉ በውሃ ጥም የተቃጠሉበት ጊዜም ነበር። የዚያን ጊዜም ሙሴን - "..ከበረሃ ያመጣኸን በውሃ ጥም ልትጨርሰን ነውን?..." ብለው አማረሩበት። ሙሴና አሮንም እግዚአብሔርን ለመኑት። እግዚአብሔርም ሙሴ በበትሩ ድንጋዩን ሲመታ ውሃ ያፈልቅ ዘንድ እንዲቻለው ፈቀደለት። ሙሴና አሮን ሕዝቡን ካሰባሰቡ በኋላ፥ ሙሴ ደንጋዩን በያዘው በትር ሲመታው ለነሱና ለከብቶቻቸው ሁሉ የሚያረካ ውሃ ፈለቀ።

የሰውን ልቡን መርምሮ የሚያውቅ እግዚአብሔር - "ከድንጋይ ውሃ አፈለቅንላችሁ.." በማለታቸው፥ በሙሴና በአሮን ልብ ሥጋዊ - ደማዊ ትምክህት ያደረባቸው መሆኑን በማየት ተቆጣ።

የሰው ልጅ ሥልጣንን ይወዳል። በሰዎች ዘንድ ታላቅ መባልንና መከበርን የማይመኝ ማነው? ሙሴና አሮንም በእግዚአብሔር ፈቃድ የፈለቀውን ውሃ በራሳቸው የተገኘ በማስመሰል ሊከበሩበትና ሊወደሱበት ልባቸው ከጅሎ ሳለ፥ ፍጹም የሆነው እግዚአብሔር ነቃባቸው (አወቀባቸው)።

"እግዚአብሔርም ሙሴንና አሮንን፡- በእስራኤል ልጆች ፊት ትቀድሱኝ ዘንድ፥ በእኔ አላመናችሁምና፤ ስለዚህ ወደ ሰጠኋችሁ ምድር ይህን ጉባኤ ይዛችሁ አትገቡም አላቸው።" ዘኍ. 20፡ 12 - 13

ከሙሴ በፊት አሮን አስቀድሞ ሞተ፤ ሙሴም እንደ እግዚአብሔር ቃል በሞዓብ ምድር ሞተ። የሙሴን የመሪነት ሥልጣን ኢያሱ ወሰደ።

የእስራኤል ጎልማሶች የእግዚአብሔርን ፈቃድ ጥሰው በጦርነት ስለተሳተፉ እግዚአብሔር ተቆጣ።

"በግብጽ ምድርና በምድረ በዳ ያደረግሁትን ተአምራቴንና ክብሬን ያዩ እነዚህ ሰዎች ሁሉ፥ አስር ጊዜ ስለተፈታተኑኝ፥ ነገሬንም ስላልሰሙ፥ በእውነት ለአባቶቻቸው የማልኩላቸውን ምድር አያዩም፤ ከነርሱም የናቀኝ ሰው ሁሉ አያያትም። ባሪያዬ ካሌብ ግን፥ <u>ሌላ መንፈስ ከርሱ ጋር ስለሆነ</u>፥[29] ፈጽሞም ስለተከተለኝ፥ እርሱ ወደገባባት ምድር አገባዋለሁ፤ ዘሩም ይወርሳታል።" ዘኍ. 14፡ 22 - 25

ከግብጽ ምድር ከወጡት ውስጥ በእድሜያቸው ከሃያ ዓመት በላይ የሆኑት በበረሃ ተንከራተቱ፤ በዚያም አለቁ (ሞቱ)። ጎረምሶችና ወጣት ጦረኞች የሆኑት በኢያሱ መሪነት እየተዋጉና አገር እየማረኩ ከዮርዳኖስ ተራራ ባሻገር ያለውን መሬት ወረሱ።

---

[29] ካሌብን በሌላ መንፈስ የተለየ ያደረገው ምንድነው? ከራሱ ተፈጥሮ ውጪ ልዩ መንፈስ ተሰጥቶታል?

በበረሃ የሞቱት ሞተው፥ የተረፉት በኢያሱ መሪነት የሚኖሩበት መሬት ስላገኙ -

- ቃል ኪዳን ተሳክቷል፤
- በእስራኤል ልጆች በረሃ ለበረሃ መንከራተት፥ እኛ የተቀረነው እንድንማር የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆነ፤ (ምድር የተፈጠረችው ለሰው ልጆች መማሪያ እንደሆነ)፤
- የእስራኤል ልጆች (ሌሎችም ሕዝቦች ?) ከእግዚአብሔር ትእዛዝ በራቁበት ወቅት ሁሉ እየተጠቁ፥ የርሱን ፈቃድ ሲከተሉ ደግሞ እየቀናቸው፥ በየቀኑ ከእግዚአብሔር እየተማሩ ኖረዋል። (እኛም ከዚህ ታሪክ የሰው ልጅ መከራ ቢጸናበት ለምክንያት እንደሆነ፥ ከመከራው የማይማር ከሆነም የባሰ ቅጣት እንደሚመጣበት ተመለከትን)።

<u>ከዳዊት ዘር - ኢየሱስ ክርስቶስ</u>

እስራኤላውያን በወረሱት ምድር እምብዛም አልቀናቸውም። አልፎ አልፎ በዝናብ እጥረት (ድርቅ) ይጠቁ ስለነበር፥ ወደ ጎረቤት አገር መሰደድ ግዴታ ይሆንባቸው ነበር። በዚህን ጊዜ ውስጥ፥ አንዲት አይሁዳዊት - ናኦሚን የተባለች ሴት፥ አገሯን ለቃ፥ ከባሏና ከሁለት ወንዶች ልጆቿ ጋር ወደ ሞአብ አገር ተሰዳ ትኖር ነበር።

የሞአብ ሕዝብ በእግዚአብሔር የማያመልኩ ሲሆን፥ የሚያመልኩትን እስራኤላውያንን በዝቅተኛ ደረጃ ያዩአቸው ነበረ። የናኦሚን ሁለቱ ወንዶች ልጆቿ ለሞአብ አገር ሴቶች ተድረው ይኖሩ ነበር። ግን ያ የስደት ኑሮ አልተመቻቸውም፤ በችግርና በበሽታ ተሰቃዩ። ናኦሚን መጀመሪያ ባሏ ሞተባት፤ ቀጥሎም ሁለቱ ልጆቿ በማከታተል ሞቱባትና እጅግ ሃዘንተኛ ሆነች። ባሏንና ሁለት ልጆቿን አጥታ ብቻዋን ስለቀረች፥ የስደት ኑሮና ሃዘን፥ ችግርና መከራ ስለጠናባት፥ ከልጆቿ ሚስቶች (ከምራቶቿ) ተለይታ ወደ አገሯ ለመመለስ ቁርጥ ውሳኔ አደረገች።

ምራቶቿ ግን አብረን እንኼዳለን እንጂ አንለይሽም አሏት። ናኦሚንም - “ከእንግዲህ ከኔ ምን አላችሁ? ባሌም ሞቷልና፥ ዳግመኛም ባል አግብቼ፥ ለናንተ ባሎች የሚሆኑ ወንዶች ልጆች እንዳልወልድላችሁ አርጅቻለሁ። ሂዱ ተመለሱ፤ ከዘመዶቻችሁና ከወገኖቻችሁ ጋር ተቀላቀሉ። እኔንም ተውኝ አገሬ ልግባበት…።” በማለት አምርራ ተናገረቻቸው። እነርሱ ግን አንለይሽም ብለው የሙጥኝ አሉ።

ከብዙ ክርክር በኋላ አንደኛዋ ምራቷ ተመለሰች። ናኦሚንም - "ይኸው ጓደኛሽም ወደ ዘመዶቿ ተመልሳለችና፤ እባክሽ አንቺም ተመለሺ፤ አታስቸግሪኝ...፤" ብላ ሩትን ለመነቻት። ሩትም እንዲህ አለች፡-

"ወደምትሄጂበት እሄዳለሁና፤ በምታድሪበትም አድራለሁና፤ እንድተውሽ፥ ከአንቺም ተለይቼ እንድመለስ አታስቸግሪኝ። ሕዝብሽ ሕዝቤ፤ አምላክሽም አምላኬ ይሆናል። በምትሞችበት ሥፍራ እሞታለሁ፤ በዚያም እቀበራለሁ። ከሞት በቀር፥ አንቺንና እኔን አንዳች የሚለየን የለም.." ብላ ማለች። መጽሐፈ ሩት 1፡ 16 - 18

በዚህ ንግግር ናኦሚን ተረታች። የሩት ፍቅር ከሁሉ በላይ ሆነ፤ የሩት መንፈሳዊነት (ሞራላዊነት) ሥጋዊነትን ረታው።

ናኦሚንና ሩት ብቻ ተያይዘው ወደ ይሁዳ ገቡ። ከዛም ሩት ለናኦሚን ዘመዶች ስንዴ እያጨደች ከምትሰበስበው ጥቂት ስንዴ በደሞዝ መልክ እየተሰጣት፥ ከናኦሚን ጋር የችግር ጊዜ አሳለፈች። በኋላም ናኦሚን የገዛ ዘመዷን እንድታገባላት ሩትን ገፋፋቻት፤ ሩትም ቦአዝ የተባለውን የናኦሚን ዘመድ አገባች። ከእርሱም ኢዮቤድን ወለደች። ኢዮቤድ እሴይን ወለደ። እሴይም ዳዊትን ወለደ። ከብዙ ዘመናት በኋላ፥ ከዳዊት ዘር ኢየሱስ ክርስቶስ ተወለደ።

"እንግዲህ ትውልድ ሁሉ ከአብርሃም እስከ ዳዊት አስራ አራት ትውልድ፥ ከዳዊትም እስከ ባቢሎን ምርኮ አስራ አራት ትውልድ፥ ከባቢሎንም ምርኮ እስከ ክርስቶስ አስራ አራት ትውልድ ነው።" ማቴ. 1፡17

ከክርስቶስ በኋላም ቢሆን፥ እኛ አይሁዶች ሃይማኖታችንን ይዘን ቆየን - ይህ ሃይማኖት ያጸድቃል፥ ይህም ይኮንናል ሳንል።

"እኔ ሕያው ነኝና፥ ኃጢአተኛው ከመንገዱ ተመልሶ በሕይወት ይኖር ዘንድ እንጂ፥ ኃጢአተኛው ይሞት ዘንድ አልፈቅድም።" ሕዝ.33፡ 11 ባለው መሠረት፥ እግዚአብሔር ፍጡራኑ ሁሉ እንዲድኑ እንጂ እንዲኮነኑ አይፈልግም።

አንድ አይሁድ ገና ከልጅነቱ ጀምሮ የእግዚአብሔር ተከታይ እንጂ የሰው ተከታይ እንዳይሆን ነው የሚነገረው። ሁሉን መጠየቅና መረዳት፥ ማመዛዘንና ጥሩውን ከመጥፎው መለየት፤ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ብቻ በመፈጸም ፍጹም ሰው ለመሆን መታገልን ነው የኛ አይሁዶች ሃይማኖት የሚያስተምር። በአንድ ፈጣሪ አምላካችን በእግዚአብሔር እያመንን፥ በሃይማኖቶች መካከል ገንጠል - ፈንጠር ብለን መታየታችን ለምን እና እንዴት እንደሆነ፥ ምን ጊዜም እራሳችንን ከመጠየቅ አላቋረጥንም።

የእግዚአብሔር እውነት በመሬት ይገለጥ ዘንድ፥ ሰማያዊ እውቀትን በሕሊናችን ውስጥ የሚሰርጽልን አምላካችን እርስ በርሳችን እንድንማማር ይፈልጋል። ግን፡-

- የትኛው ሕብረተሰብ ነው በእውነትና በብርሃን ብቻ እየተመላለሰ ደግነትን ሲሠራ የቆየ?
- የትኛው ሕብረተሰብ ነው፥ አብሮ በመኖር እርስ በርሱ ተደጋግፎ፥ ተከባብሮ፥ በፍቅር የኖረ?
- የትኛው የሕብረተሰብ ታሪክ ነው እስከዛሬ ድረስ በሥራው ሁሉ የሚገባውን የራሱን ክብር በመቀዳጀት የእግዚአብሔር ልጅነቱን ያስመሰከረ?
- የትኛው ሕብረተሰብስ ነው፥ ፍጹም የሆነውን ፈጣሪውን ያስደሰተ? ወይንም ፈጣሪው እንደሚፈልገው ብቻ የሆነለት።
- በሥራችን አልጸደቅንም፤ በሃይማኖታችንም አልጸደቅንም።
- የፈጠረን እግዚአብሔርን በማመን ላይ ጸንተን፤ እርሱ በፈቀደ መኖራችን በቂያችን ነው።
- ከምድር ዋልታም ሆነ ከምድር መካከል፥ ሰዎችን በአለም ዙሪያ በጋራ የሚያቅፋቸው ሁለንተናዊ እውነት በምድር፥ በጠፈር፥ በሥፍራዎች ሁሉ አለ።
- እውነት አንድ፥ ምንጩ አንድ፥ አመንጪውም አንድ ነው። ግን እኛ እንደመላእክት የሰማዩ ስለማይታየን፥ ይህንን እውነት በጋራ መመልከት አልቻልንም።
- እያንዳንዳችን በሃይማኖት የተለያየን ብንመስልም የምንቀራረብበት ውስጣዊ እምነት አለን፤ ይኸውም በእግዚአብሔር ማመን ነው።
- ሁላችንም የእግዚአብሔርን ፈጣሪነትና ኃያልነት በተለያየ መንገድ የምንገልጽ በመሆናችን፥ እውነት በሁላችንም ውስጥ ይኖራል።

## የታቦታችን አመጣጥ - ወደ ኢትዮጵያ

እስራኤላውያን በወረሱት የከነአን ምድር ሲኖሩ፥ በሽማግሌዎች ሸንጎ ይተዳደሩ ነበር። መሪያቸውም ሳሙኤል ነበር። ኑሮአቸው የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በመጠበቅ ላይ ያተኮረ ሲሆን፥ ማህበራዊ ኑሮአቸውም ልክ እንደ ገዳም አይነት ኑሮ የተጠናከረ ይመስል ነበር።

ሳሙኤል ባረጀ ጊዜ ልጆቹን በእስራኤል ላይ ፈራጆች አደረጋቸው። እነርሱ ግን የሳሙኤልን ፈለግ ባለመከተል ጉበኞች ሆኑ። ሕዝቡም በዚህ ነገር ተበሳጭተው - "እንደ ሌሎቹ አገሮች ባለ ንጉሥ ሁነን ወደ ፊት እንራመድ እንጂ..." በማለት፥ በመንፈሳዊ መንገድ ሲመራቸው የነበረውን ሳሙኤልን ንጉሥ እንዲሾምላቸው ጠየቁት። እርሱም ወደ እግዚአብሔር ጸለየ። እግዚአብሔርም የሚከተለውን መለሰለት-

"በእነርሱ ላይ እንዳልነግሥ እኔን እንጂ አንተን አልናቁምና በሚሉህ ነገር ሁሉ የሕዝቡን ቃል ስማ። ነገር ግን ጽኑ ምስክር መስክርባቸው በእነርሱም ላይ የሚነግሠውን የንጉሡን ወግ ንገራቸው።" ሳሙ. ቀዳ. 8፡ 7 - 9

ሳኦል የተባለ ሰው በእስራኤል ላይ ነገሠ። ከሳኦል በኋላ፥ ንጉሡ ዳዊት ሕዝባዊ አስተዳደርን ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር ለማስተካከል ጣረ። ጠላቶች ቢከቡትም፥ ዘወትር ከመጸለይ ብዛት፥ ኃይልና ብርታትን ከእግዚአብሔር በማግኘቱ በእስራኤሎች ላይ ለረጅም ዘመን (ለአርባ ዓመታት?) ነገሠ።

ንጉሥ ዳዊትም ከኦርዮ ሚስት ሶሎሞንን ወለደ። ሶሎሞንም ንጉሥ ከሆነ በኋላ፥ ሰፊውን ሕዝብ ማስተዳደር ይችል ዘንድ፥ ጥበብን እግዚአብሔር እንዲለግሰው ጸለየ። እግዚአብሔርም ጸሎቱን ሰምቶ ጠቢብ አደረገው፤ በዛውም ላይ ሰሎሞን ያልለመነውን ባለጠግነትን ሰጠው። ንጉሥ ሶሎሞን በዳኝነቱ እና በጥበቡ እጅግ የሚደነቅ ንጉሥ ሆነ።

የንጉሥ ሶሎሞንና ማክዳ የተባለች የኢትዮጵያ ንግሥት ታሪክ "ክብረ ነገሥት" በተባለ መጽሐፍ ተጽፎ፥ በእንግሊዝኛ፥ በፈረንሳይኛና በአረብኛ ተተርጉሟል። ይህ መጽሐፍ መንፈሳዊ ታሪካችንን ያስታውሳል። ለክርስቲያን ሃይማኖት መሠረት የሆነው የአይሁድ ሃይማኖት እንዴት ወደ ኢትዮጵያ እንደገባ ይገልጻል፤ አያሌ ሃይማኖታዊ ጉዳዮችንም ያወሳል።

ይህ መጽሐፍ ብዙውን ጊዜ በሁለት ገጽታው ነው የሚታወቀው። አንዱ ገጽታው፡- ከንጉሥ ሶሎሞን እና ከንግሥት ማክዳ ከተወለደው - ከቀዳማዊ ሚኒሊክ ጀምሮ፥ የኢትዮጵያ ነገሥታትን የዘር ሐረግ የሚያረጋግጥ ነው።

ሁለተኛ ገጽታው ደግሞ- እግዚአብሔር አምላካችን ማደሪያውን ከሰዎች መካከል ያደርግ ዘንድ ታቦት ይሠራልኝ እንዳለ፥ ያ የርሱ ማደሪያ የሆነ ታቦት፥ እስራኤሎች እንደሚሉት፥ ናቡከደናጾር ያቃጠለው - ቤተ መቅደሱ ሲቃጠል እርሱም አብሮ የተቃጠለ ሳይሆን - ወደ ኢትዮጵያ የተሰደደ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው።

ይህንን ሁለተኛ ገጽታውን - የታቦቱን ወደ ኢትዮጵያ መምጣት ነገር - በእንግሊዝኛ ከተተረጎሙት መጽሐፍት መካከል[30] ከአንደኛው - ከHausman Gerald (1997) በማውጣጣት ለማስታወሺያ ያህል ከዚህ እንደሚከተለው በአጭሩ ተጻፈ፡-

ንግሥት አዜብ እጅግ የሚደነቀውን የንጉሥ ሶሎሞንን ጥበብ ከርሱ ለመስማት ፈለገች። "በእንቆቅልሽ ትፈትነው ዘንድ መጣች" 1ኛ. ነገሥት 10:1 እርሷም እንደ ንጉሥ ሶሎሞን ቆንጆ፥ ጠቢብ እና ባለጸጋ ነበረች። ለንጉሡ ብዙ ስጦታዎች ይዛ ኢየሩሳሌም ገባች። ንጉሡም በክብር ተቀብሎ አስተናገዳት። በየጊዜው ያናግራት ስለነበረ፥ ከንጉሡ ብዙ ተማረች። ከሁሉም በላይ፥ ከእግዚአብሔር በስተቀር በሌሎች አማልክት እንዳታምን - ፈጣሪዋን በደንብ እንድታውቅ አደረጋት።

ንግሥት አዜብ በኢየሩሳሌም ቆይታዋ የተደሰተች ብትሆንም፥ ወደ አገሯ መመለስ ስላለባት እንዲያሰናብታት ንጉሡን ጠየቀችው። እርሱም ትንሽ እንድትቆይ ስለተማጸናት ፈቃዱን ለመፈጸም ስትል ተስማማች።

ንጉሥ ሶሎሞን በንግሥት አዜብ ቁንጅና በመማረክ፥ ከርሷ ጋር የፍቅር ግንኙነት ማድረግን ፈልጎ ሳለ፥ ከእለታት አንድ ቀን ንግሥት አዜብ ጨው የበዛበት ምግብ በልታ በውሃ ጥም እንድትቃጠል፥ ውሃ ለመጠጣትም ከርሱ መኝታ ቤት መግባት ግድ እንዲሆነባት ንጉሡ ሁኔታዎችን አመቻችቶ ተኛ። ንግሥቲቱም በውሃ ጥም ስለተቃጠለች እንቅልፍ ሊወስዳት አልቻለም።

ንጉሡ እንደተኛ፥ ኢያየኝም ብላ ውሃ ለመጠጣት ስትል፥ ከንጉሡ መኝታ ቤት ገባች። እርሱ ግን የተኛ መስሎ የርሷን መምጣት ሲጠባበቅ ነበርና፥ ልክ እንዳሰበው ሆነለት። በዚህን ጊዜ ከመኝታው ተነስቶ -

"እንዳትነኪ ያልኩሽን እቃዬን ለምን ትነኪያለሽ?" ብሎ ውሃውን እንዳትጠጣ እጇን ያዛት። እርሷም - "በውሃ ጥም ተቃጥዬ ከምሞት የፈለግኸውን አድርግ.." ብላ ፈቀደችለት። ውሃውን ከጠጣች በኋላ ከርሱ ጋር ተኛች፤ በዚያን ሌሊት ቀዳማዊ ሚኒሊክን ጸነሰች።

በዚያን ሌሊት ንጉሥ ሶሎሞን ስለወደፊቱ ሁኔታ - ስለ ታቦቱ ከእስራኤል መውጣት፥ ለወደፊት የሚወለደውንም ታላቅ መሲህ - እስራኤሎች አሰቃይተው እንደሚገድሉት የሚያንጸባርቅ ሕልም ታየው።

---

[30] በቋንቋችን የተጻፈው ባይገኝ፥ ሌሎች ትርጉሞች ይኖራሉ፤ ለምሳሌ - Wallis Budge (1932) – The Kebra Negast.

ንግሥት አዜብ ጥቂት ከሰነበተች በኋላ፥ ወደአገሯ ለመመለስ የቆረጠች መሆኗን በመግለጽ፥ እንዲያሰናብታት ንጉሡን ጠየቀችው። እርሱም ከርሷ ጋር እንድትቆይ ለመናት። እርሷ ግን በሃሳቧ ስለ ጸናች፥ ንጉሡ ወዳገሯ እንድትመለስ በቅሬታ ፈቀደላት። ከጣቱም ቀለበቱን አውልቆ እንዲህ አላት-

"እንዳትረሺኝ ይህንን ውሰጂ፤ አርግዘሽም ከሆነ፥ ለሚወለደው ወንድ ልጅ ወይንም ለምትወለደዋ ሴት ልጅ ምልክት ይሆናል። በሕልሜ ፀሐይ ከእስራኤል ወጥታ ወደ አንቺ አገር ስትሄድ አየሁ። እግዚአብሔር ካንቺ ጋር መሆኑን፤ ባንቺም ምክንያት አገርሽ እንደምትባረክ ባየሁት ሕልም ተረድቻለሁ። ፈጣሪ አምላክሽን በሙሉ ልብሽ ከማመን፤ የርሱንም ፈቃድ ከመፈጸም ወደ ኋላ አትበይ። በይ ሂጂ፤ በሰላም ግቢ።"

ንጉሥ ሶሎሞን ለመንገዷ የሚያስፈልጋትን ሁሉ ሰጥቶ ሸኛት። ንግሥት አዜብ ረጅሙ ጉዞዋን ጀመረች፤ ገና የዛሬዪቱ የኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ሳትገባ፥ በጥንታዊት ኢትዮጵያ (ዛሬ ሱዳን) ውስጥ እንዳለች ወንድ ልጅ ወለደች። ልጇን ታቅፋ ከአክሱም ስትገባም የተደረገላት አቀባበል እጅግ ከፍተኛ ነበር።

ህጻኑም ባደገ ጊዜ፥ አባቴን አሳዪኝ እያለ እናቱን ይጨቀጭቅ ጀመር። እርሷም - "ያባትህ አገር በጣም እሩቅ ስለሆነ፥ እዚሁ ከኔ ጋር አርፈህ ተቀመጥ፤ እኔ አባትህም እናትህም እሆንሃለሁ...." እያለች ታባብለው ነበር።

ልክ እንደ አባቱ መልከ መልካም የሆነ ይህ ወጣት፥ ሃያ ሁለት ዓመት ሲሞላው አባቱን ለማየት ቆርጦ ተነሳ። እናቱም አባብላ ማስቀረት ስላልቻለች፥ በጉዞው ተስማማች፤ አባቱም ሲያየው ልጁ መሆኑን እንዳይጠራጠር ንጉሡ የሰጣትን ቀለበት ሰጠችውና የሚያስፈልገውን ሁሉ አዘጋጅታ ሸኘቺው።

ከረጅሙ ጉዞ በኋላ፥ ጋዛ የሚባል ሥፍራ እንደደረሰ፥ ንጉሥ ሶሎሞን የመጣ መስሏቸው ብዙ ሰዎች ተታለው ነበር። ኢየሩሳሌም ገብቶ ከሶሎሞን ቤተ መንግሥት እንደደረሰም ዘበኞቹ ንጉሥ ሶሎሞን መስሏቸው አሳለፉት። ንጉሥ ሶሎሞንም ንጉሥ ዳዊት እንደገና ተወልዶ ወደርሱ ለመምጣት የሚቀረበው መስሎት ደነገጠ።

ሚኒሊክ ካጠገቡ ሲደርስ የራሱ ልጅ ስለመሆኑ ምንም ሳይጠራጠር አቀፈውና፥ አፉን፥ ጉንጮቹን እና ግንባሩን ሁሉ ሳመው። ልጁም አባቱን ለማየት በመብቃቱ እጅግ ደስ ብሎት፥ እንደ ምልክት ይሆናል የተባለውን ቀለበቱን ለአባቱ አሳየው። አባቱም - "አንተ የኔ ልጅ ስለመሆንህ ማን የሚጠራጠር ይኖራል ብለህ ነው?..." አለው።

ሚኒሊክ ከሶሎሞን ቤተሰብ ጋር በሳቅ በጨዋታ እየተደሰተ ሰነበተ። አባቱም ልጁ አብሮት የሚኖርለት መስሎት እጅግ ደስ ብሎት ነበር። ነገር ግን - "ወዳገሬ እመለስ

ዘንድ አሰናብተኝ...” ብሎ አባቱን ጠየቀ። አባቱም - “እባክህ ልጄ ከኔ ጋር ሁን እንጂ፤ አትለየኝ..” ብሎ እንዲቀርለት አጥብቆ ለመነው።

ልጁም - “እኔ የተወለድኩት የሕግ ሚስትህ ካልሆነች ሴት ነው። ከሕግ ሚስትህ የወለድከው ሮብአም አለልህ። እኔም ከእናቴ ጋር እሆን ዘንድ፥ እባክህ ፍቀድልኝና ልሂድ...።” ብሎ ተማጸነ።

ሶሎሞንም - “ይህንን ካልክስ፥ እኔም ከአባቴ ከሕግ ሚስቱ አይደለም የተወለድኩት። ሁሉን ቻይ አምላካችን ከሕግ ውጪ በምንሠራው ሥራ ሁሉ አይኮንነንም። አምላካችን አባቴን ይቅር ስላለው፥ ከሕግ ሚስቱ ስላልተወለድኩ አባቴ ለኔ የነበረው ፍቅር አልተቀነሰም። ስለዚህ እኔም ሮብአምን እንደምወድድ አንተንም እንደምወድህ አትጠራጠር። ከኔ ጋር በመሆንህ ምንም የሚጎድልብህ ነገር ስለማይኖር፥ አባክህ አትሂድብኝ።” ብሎ ለመነ።

ልጁም - “አባቴ ሆይ! አመጣጤ አንተን አባቴን ለማየት፥ ድምጽህን ለመስማት፥ ምርቃትህንም ለመቀበል ነው እንጂ፥ እዚሁ ለመቅረት አይደለም። እንዳልቀርባት እናቴ አስምላኛለች። እኔም ከእናቴ እና ከአገሬ ተለይቼ መኖር የማልችል ስለሆንኩ፥ ወዳገሬ እመለስ ዘንድ እባክህ አሰናብተኝ...” ብሎ አባቱን ተማጸነ።

በዚህን ጊዜ ንጉሥ ሶሎሞን ከንግሥት አዜብ ጋር ያሳለፈውን ጊዜ ሁሉ እያሰበ፥ በጣም አዘነ። ከበኩር ልጁ በመለየቱ እየተቆጨ - “ከሌሎች አገር ሴቶች አንድ ሺህ ሚስቶች አግብቼ፥ አንድ ሺህ ልጆች ወልጄ...” እያለ በከንቱ ምኞታዊ ሃሳቦች ራሱን ያጽናና ጀመር።

ከልጁ ጋር መኖር አለመቻሉን ሲገነዘብ፥ በዙሪያው ያሉ የመንግሥቱ ባለ ሥልጣን፥ አማካሪዎች፥ ቀሳውስት፥ መኳንንቶች እና ያገር ሽማግሌዎች እንዲሰበሰቡ አደረገ። እንዲህም ብሎ ተናገረ -

“ከምወደው የበኩር ልጄ ጋር ብኖር ለደስታዬ ወደር የለውም ነበር። ከኔ ጋር እንዲኖር ብዙ ለመንኩት፥ እርሱ ግን - ከእናቴ እና ከአገሬ ተለይቼ መኖር አልችልም በማለት፥ ወዳገሩ ለመመለስ ቆርጦ ተነስቷል። ስለዚህ፥ ከእናቱ ቀጥሎ በኢትዮጵያ ላይ ንጉሥ መሆኑ አይቀርምና፤ ሳይሄድ በፊት ከዚሁ እናንግሠው።

የኔ የበኩር ልጄ ንጉሥ ሆኖ ከሚኖርበት አገር፥ የናንተም የበኩር ልጆቻችሁ ከዚያ ሄደው ቢኖሩ፥ ያ እነርሱ የሚኖሩበት አገር እንደራሳችን አገር ሆነ ማለት ነው። እናንተ እዚህ ከግራና ከቀኜ እንደምትቀመጡ፥ የናንተም የበኩር ልጆች በኢትዮጵያ መንግሥት ከልጄ ከግራውና ከቀኙ እንዲቀመጡ፥ ከበኩር ልጆቻችሁ ጋር በአንድነት እንሸኛቸው። ልጆቻችን ከኢትዮጵያ ሄደው ሲኖሩ፥ እኛም በተዘዋዋሪ ሁለት አገር - ሁለት መንግሥት እንደሚኖረን የሚቆጠር መሆኑን አስቡት...።”

ንጉሥ ሶሎሞን ንግግሩን እንደጨረሰ፥ ሁሉም በሃሳቡ መስማማታቸውን ገለጹለት። ከዚህ ከሶሎሞን ንግግር በኋላ፥ ወዲያውኑ ሚኒሊክን ለማንገሥ ከፍተኛ ዝግጅት ተደረገ። ሶሎሞንን ያነገሠው ሶዶቅ የተባለ ታላቅ ቄስ እንደሆነ ሁሉ፥ በዳዊት በቅሎ ላይ አስቀምጠው ወደ ግዮን እንዳመጡትና ሕዝቡም በዘፈን እና በታላቅ ደስታ ሶሎሞንን እንዳነገሡት ሁሉ፤ ሚኒሊክም ሲነግሥ ልክ እንደዚሁ ሆነ።

ቀሲስ ሶዶቅ የቅብአቱን ቀንድ ወስዶ ሚኒሊክን ቀባውና ዳዊት የሚል ስም ሰጠው። መለከትም ተነፋ፤ በሶሎሞንም በቅሎ ላይ አስቀምጠው፥ ከዘፋኞችና ከብዙ አጃቢዎች ጋር ከተማዪቱን በሙሉ እንዲዞር አደረጉ።

ሶዶቅ ዳዊት ብሎ ያነገሠውን ሚኒሊክን በየጊዜው ይመክረው ነበር፤ እንዲህ እያለ፡-

“...ልጄ ሆይ! ኑሮህ በእግዚአብሔር እምነት የጸና ይሁን። ኑሮህ በእግዚአብሔር እምነት የጸና ካልሆነ በስተቀር፥ ምንም ነገር አይሳካልህም። ነገር ግን ኑሮህ በእግዚአብሔር እምነት የጸና ከሆነ - ምን ጊዜም ከፈጣሪ አምላክህ ፈቃድ የማትወጣ ከሆነ - የምታደርገው ሁሉ ይሳካልሃል። አንተ ብቻ ሳትሆን የምትኖርባት አገርም ትባረካለች፤ ሕዝቦቿም ይባረካሉ።

ጥሩ ሰው ሁን፤ አንተ ጥሩ ስትሆን ከሥርህ ያሉት ሕዝቦችም ጥሩዎች ይሆኑልሃል። እንተ የምትላቸውን እንዲሰሙልህ ከፈለግህ፥ እነርሱም የሚሉትን ስማ።

ድሆችን ከሚጨቁኗቸው ግፈኞች ነፃ አውጣቸው። ሰውን ሁሉ በእኩልነት ተመልከት፤ በምትፈርድበትም ጊዜ አድሎአዊ እንዳትሆን ተጠንቀቅ...።”

ብዙ እስራኤላውያን የበኩር ልጆቻቸውን ወደ ኢትዮጵያ ለመላክ ዝግጅት ጀመሩ። ወደ ኢትዮጵያ እንዲሄዱ የተነገራቸው የበኩር ልጆች ሁሉ ከሚኒሊክ ጋር ጉዞ የሚጀምሩበት ወቅት እየተቃረበ ሲመጣ፥ ከአገራቸው ከእስራኤል መለየታቸው፥ በተለይም ከታቦተ ጽዮን ርቀው መሄዳቸው እያሳዘናቸው በየቀኑ እየተገናኙ እርስ በርስ ይመካከሩ ጀመር።

ከእለታት አንድ ቀን አዛርያስ የተባለ የሶዶቅ የበኩር ልጅ ጓደኞቹን ሰብስቦ እንዲህ አለ -

“ከአገራችን ርቀን፥ ከታቦተ ጽዮን ተለይተን ወደማናውቀው እሩቅ አገር ስንሄድ ምን እንደሚደርስብን አናውቅም። ነገር ግን፥ ህብረትና አንድነት ካለን፥ በማይነጣጠል በአንድ ሃሳብ የምናደርገው ሁሉ ይሳካል። ስለዚህ፥ ከዛሬ ጀምሮ እንደ አንድ አካል ህብረትና አንድነት ይኖረን ዘንድ እንማማል።

እንደምታውቁት የኔ፥ የአባቴ የሶዶቅ፥ እንዲሁም የሁላችንም ሕይወት ከታቦቱ ጋር የተያያዘ እንደሆነ ግልጽ ነው። የሚቻለን ቢሆንስ፥ ከታቦታችን ጋር ብንሄድ ነበር የሚሻለን። ጉዞአችን የተቃና እንዲሆን፥ ከምንደርስበትም ሥፍራ ሁሉ በሰላም እንድንኖር ታቦተ ጽዮንን ይዘን ብንሄድ ምን ይመስላችኋል?"

ይህንን መልካም ሃሳብ አዛርያስ ስላቀረበ፥ ሁሉም በደስታ እየተነሱ ይስሙት ጀመር። ከመካከላቸውም አንዱ ተነስቶ እንዲህ አለ -

"ከምንወዳት ከአገራችን ተለይተን መሄዳችንን የሚያካክሰን ታቦቱን ይዘን መሄዳችን ብቻ መሆኑ ግልጽ ነው። ግን ይህንን ማድረግ እንዴት ይቻለናል? ከአዛርያስ አባት ከሶዶቅ በስተቀር ወደ ታቦቱ የሚቀርብ ሰው የለም።"

ሌላውም ቀበል አድርጎ እንዲህ አለ -

"አንተ አዛርያስ ታቦቱ ያለበትን ቁልፉን ከአባትህ ብትወስድ፥ ታቦቱን በቀላሉ ማውጣትና ወደ ኢትዮጵያ መውሰድ ይቻለናል። ነገር ግን እኛ ከታቦቱ ጋር ወደ ኢትዮጵያ ሄደን ደስተኞች ስንሆን፥ አባቶቻችን ከዚሁ ሃዘንተኞች ሆነው መቅረታቸው ነው። ይህ ነገር በኛ መንፈስ ላይ ስለሚያስከትለው ስሜት አብረን ብናስብበት ይሻላል። አይመስላችሁም?.."

አዛርያስም ቀበል አድርጎ እንዲህ አለ -

"አባቶቻችን ሃዘንተኞች ሆነው እንዳይቀሩ ለማድረግ፥ ልክ በታቦቱ አምሳያ ሌላ ታቦት ሠርተን፥ በምትኩ እናስቀምጣለን። በአባቴም ሆነ በሌላ ሰው ምንም ጥርጣሬ እንዳያስከትል፥ የታቦቱን አሰራር፥ አልባሳቱን ሁሉ ልክ እንደነበረ አድርገን እናስቀምጥላቸዋለን። ይህንን ካደረግን፥ አባቶቻችን ከዚሁ ሃዘንተኞች ሆነው አይቀሩም።"

በድጋሜ ይህንን መልካም ሃሳብ አዛርያስ ስላቀረበ፥ ሁሉም በደስታ ተስማሙ። ወዲያውም እቅዳቸው እንዲሳካ ምን ምን መደረግ እንዳለበት ቀኑን ሙሉ ሲመካከሩ ውለው ተለያዩ።

አዛርያስም ከቤቱ ሄዶ፥ እራቱን በልቶ እንደተኛ፥ ስለ እቅዱ እያሰበ እንቅልፍ ወሰደው። በዛኑ ሌሊት አዛርያስን በህልሙ መልአክ አናገረው፤ ታቦቱን ይዞ ለመሄድ መደረግ ያለበትን ሁሉ በዝርዝር አስረዳው። ከእንቅልፉም ሲነቃ፥ እግዚአብሔር በሃሳቡ የተስማማ መሆኑን ስለተረዳ እጅግ ደስ እያለው፥ ወደ ጓደኞቹ ዘንድ ገሰገሰ።

አዛርያስ ጓደኞቹን አሰባስቦ በህልሙ ያየውን ሁሉ ነገራቸውና፤ የታቦቱ አምሳያ ተዘጋጅቶ እንዲቀመጥ አደረገ። በህልሙ የተገለጠለት መልአክ እንደነገረው፥

እውነተኛውን ታቦት ከቤተ መቅደስ አውጥቶ ለመውሰድ እንዳይቻኮሉ፤ ልዩ የመስዋዕት ማቅረቢያ ቀን እስኪደርስ ድረስ በትእግስት እንዲጠብቁ መከራቸው።

ንጉሥ ሶሎሞንና ሕዝቡ ታላቅ መስዋዕት የሚያቀርቡበት ቀን ደረሰ። ሕዝቡም በዚያን የመስዋዕት ቀን ከታቦተ ጽዮን ጋር ሲደሰቱ ውለውና አምሽተው ደከሚቸው ተኝተዋል።

አዛርያስም እንደተኛ በህልሙ መልአክ ከፊት ለፊቱ እንደ የእሳት አምድ ቆሞ ታየው። መልአኩም -

"ተነስ! ተነስ! የታቦቱን አምሳያ ያዝና እንሂድ፤ ተነስና ወደ መቅደሱ እንግባ፤ እኔ በሩን እከፍትልሃለሁ...." ብሎ ቀሰቀሰው።

አዛርያስም ወዲያው ከእንቅልፉ ተነስቶ፥ ጓደኞቹን ቀሰቀሳቸው። የተሠራውንም የታቦት አምሳያ ይዘው ወደ ቤተ መቅደስ ገሰገሱ። በዚህን ጊዜ መልአኩ ይመራቸው ነበር። በሩን መልአኩ ከፍቶ ታቦቱ ካለበት አስገባቸው። አምሳያውን ታቦት አስቀምጠው፥ አልባሳቱን ሁሉ ልክ እንደነበረ አድርገው እውነተኛውን ታቦት ይዘው፥ የቤተ መቅደሱንም በር ዘግተው ሄዱ።

በማግሥቱም እውነተኛው ታቦት በመንገደኞቹ ልብሶች ተሸፋፍኖ በሰረገላ ተቀምጧል። ሕዝቡም ሁሉ ሊሸኛቸው ከየቤቱ ወጣ።

ህጻናት፥ ሽማግሌዎች፥ እናቶችና አባቶች፥ እህቶችና ወንድሞች፥ ሁሉም ሊሰናበት ከየቤቱ ወጣ። እናቶችና አባቶች ከልጆቻቸው ሲለዩና ማልቀስ ሲጀምሩ፥ ጠቅላላ ሕዝቡ ሁሉ ልክ አገር እንደተቃጠለ ተሰምቷቸው በታላቅ ሃዘን ይላቀሱ ጀመር።

ከሕዝቡም ጋር እንስሳትም - ውሾችና አህዮችም በተለያየ የጩኸት (የማላዘን) አይነት፥ የሃዘን ድምጾቻቸውን በከፍታ ማሰማት ጀመሩ። ሁሉም (ሰውም እንስሳቱም) የታቦተ ጽዮንን ከኢየሩሳሌም መውጣት - እነርሱ ሳያውቁት በልባቸው እንደተሰማቸው ሆነው - ምርር ብለው አለቀሱ (ተላቀሱ)።

ንጉሥ ሶሎሞን ከባልኮኒው ቆሞ የሕዝቡንና የእንስሳቱን ጩኸትና ልቅሶ ሲመለከት፥ ታላቅ ሃዘን ተሰማው።

ፀሐይ ከእስራኤል ወጥታ ወደ ኢትዮጵያ ስትሰድ ያየው ህልሙ ትዝ አለው። አባቱ ስለ ኢትዮጵያ የተነበየውንም አስታወሰ።

"በፊቱም ኢትዮጵያ ይሰግዳሉ፤ ጠላቶቹም አፈር ይልሳሉ።" መዝ. 72፡ 9

"ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች።" መዝ. 68፡ 31

ንጉሥ ሶሎሞን ለልጁ የሚያስፈልገውን ሁሉ ከሰጠው በኋላ፥ ለንግሥት ማከዳ የጣቱን ቀለበት እንደሰጣት፥ እንዲሁም ለልጁ መታሰቢያ ይሆን ዘንድ አንድ ሌላ ተጨማሪ ነገር ሊሰጠው ፈለገ። ጥሩ ነገር ሲያስብ - ከጣት ቀለበት የሚበልጥ፥ ከብርና ከወርቅም የሚበልጥ፥ ለአንድ ሰው ብቻ ሳይሆን፥ ለኢትዮጵያ ሕዝብም የሚሆን ከታቦቱ ጋር የተያያዘ ነገር መሆኑ ገባውና፥ ከታቦቱ አልባሳት አንዱን ሶዶቅ አንስቶ እንዲሰጠው አዘዘ።

ሶዶቅም ቶሎ ወደ ቤተ መቅደስ ገብቶ ከታቦቱ አልባሳት አንዱን አንስቶ ለሚኒሊክ ሰጠው። ይህንን ሲያደርግ ግን፥ የታቦቱን አልባሳት ሁሉ አንስቶ ከሥሩ ያለውን እንዳያይ፥ አይኖቹ ተጋርደውበት ነበር።

ንጉሥ ሶሎሞን ልጁን በሃዘን ተሰናበተው። መንገደኞች ሁሉ ተገናኝተው በአንድነት ጉዞአቸውን ጀመሩ። በቅዱስ ሚካኤል መሪነት መንገዳቸው የተቃና ሆነ። በጥቂት ቀናት ውስጥ ከተከዜ ወንዝ ደረሱ። በዚህን ጊዜ ሁሉ ሚኒሊክ የታቦቱን አብሮ መምጣት አላወቀም ነበር።

አዛርያስ የታቦቱን ታሪካዊ አወጣጥ - የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ፥ በመልአክ እርዳታ እንዴት ከቤተ መቅደስ ወጥቶ ከነርሱ ጋር እንደተጓዘ፥ ሁሉንም በዝርዝር ለሚኒሊክ ነገረው። ሚኒሊክም ይህንን አስደናቂ ታሪክ በሰማ ጊዜ ከደስታው የተነሳ ቁና ቁና እየተነፈሰ እንዲህ አለ -

“አ! ፈጣሪያችን አምላካችን፥ ማደሪያህን በሕዝቦችህ መካከል ለማድረግ አንተ ኢትዮጵያን መርጠክ። ከእንግዲህ የኢትዮጵያ ሕዝብ ባንተ የተባረከ፥ የተቀደሰም ይሆናል።”

ሚኒሊክም ከአባቱ እንደ ገጸ በረከት የተሰጠውን የታቦት አልባስ አውጥቶ ለእስራኤላውያን መንገደኞች ባሳያቸው ጊዜ፥ እነርሱም በመደነቅ -“ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ?” ብለው ሚኒሊክን ጠየቁት። ሚኒሊክም - አባቱ ሶሎሞን ከታቦቱ አልባሳት አንዱን ሶዶቅ አንስቶ እንዲሰጠው ያደረገ መሆኑን ሲነግራቸው፥ እጅግ በመደነቅ እንዲህ አሉ -

“ሶዶቅ የታቦቱን አልባሳት ሲያነሳ፥ ታቦቱን እንዳያስተውል አይኑን የጋረደ፥ እኛ ትተን የሄድነው የክብር ልብስ እንኳን ከታቦቱ እንዳይለይ ያደረገ፥ በእውነት ፈጣሪ አምላካችን ከኛ ጋር ነው። በእውነት እኛም የፈጸምነው የእግዚአብሔርን ፈቃድ መሆኑን አሁን በጣም እርግጠኞች ሆን…” በማለት ፈጣሪአቸውን አመሰገኑ።

ታቦቱን ከተደበቀበት አውጥተው፥ የክብር ልብሱን ካለበሱ በኋላ፥ ከታቦቱ ሥር ከመሬት ላይ እየተደፉ፥ እጃቸውንም ወደ ሰማይ እየዘረጉ፥ ለዚህ ላበቃቸው አምላክ ታላቅ ምስጋና አቀረቡ። ለደስታቸውም ወሰን አልነበረውም።

የዛን ጊዜ ሚኒሊክም ሳያስበው ልክ እንደ አያቱ እንደ ንጉሥ ዳዊት ትንቢት ይናገር ጀመር እንዲህ እያለ-

“አንቺ የእግዚአብሔር ማደሪያው የሆንሽ አንቺ ጽዮን፥ አንቺ ንግሥት፥ እንግዲህ ብድግ በይ ለእኛም ብርታትን ስጪን።

ታቦቱን ይዘው ከኢትዮጵያ ደረሱ፤ ሕዝቡም በደስታ ተቀበላቸው። ንግሥት አዜብም በልጇ መመለስ እጅግ ደስ ብሏት ወዲያው እንዲነግሥ - የኢትዮጵያ ንጉሥ ሆኖ እንዲተካት አደረገች።

ይህንን እና የመሳሰለውን - የማንነታችን መሠረት የሆነውን ሁሉ (እውነተኛ የኢትዮጵያዊነታችን ገጽታ የሆነውን ሁሉ) መመርመርና ማወቅ ስለራሳችንም በደንብ ለመረዳት ይጠቅማል።

በተለይ ይህንን እግዚአብሔር ጠቅላላ የኢትዮጵያን ሕዝብ እንደሚወድ የሚያረጋግጥ የመንፈሳዊነታችንን ማስታወሺያ ታሪክ - እውነተኛ ስለመሆኑ በቂ ማረጋገጫ የለውም ብሎ፥ በንቀት እየዘለሉ ከማለፍ ይልቅ፥ ከተቀረው የመንፈሳዊነታችን ታሪክ ጋር አያይዞ መመልከት ይገባል።

## ወሳኝ ትንቢቶች

እስከ ዘመናችን የደረሰውን መንፈሳዊ - ሃይማኖታዊ - ባህላዊ - ማንነታችንን፥ በተለይ ታቦቱንና ክርስቲያናዊነታችን የሚያስተሳስረውን ጥልቅ መንፈሳዊ ምሥጢር፥ ከየት ተነስቶ ከዚህ እንደደረሰ ማገናዘብ ግድ ስለሚለን፥ ወደ ቀድሞ ነገራችን ተመልሰን የመንፈሳዊነታችንን ነገር በማስታወስ፥ ከየት ተነስተን የት እንደደርስን እንመራመር። የምናመልክበት ፈጣሪ አምላካችን ሁሉን ነገር በቅድሚያ አስተካክሎ ለምክንያት እንዳስቀመጠ፥ ይህንንም ነቢያቶች አስቀድመው እንደነገሩን እንመልከት።

የዳዊት ልጅ ንጉሥ ሶሎሞን በምእራብ እስከ ግብጽ ድረስ፥ ሊባኖስን፥ ሶሪያንና ጆርዳንን ሁሉ ይገዛ ነበር። ግን፥ ከእግዚአብሔር የሚሰጠውን የቀና አስተዳደር ኃላፊነት በራሱ የግል ፍላጎት ለወጠው። ከጊዜ በኋላ የልዩ ልዩ አገሮች ቆነጃጅቶችን ሚስትና ውሽማ በማድረጉ ተታለለ። እግዚአብሔር ሶሎሞንን ተቆጣ።

“እግዚአብሔርም ሶሎሞንን አለው - “ይህን ሥርተሃልና፥ ያዘዝኩህንም ቃል ኪዳኔንና ስርዓቴን አልጠበቅህምና መንግሥትህን ከአንተ ቀዳድጄአለሁ.... ነገር ግን ስለ ባርያዬ ስለ ዳዊትና ስለ መረጥኋት ስለ ኢየሩሳሌም ለልጅህ አንድ ነገድ እሰጠዋለሁ እንጂ መንግሥቱን ሁሉ አልቀድድም።” መጽ. ነገ. ቀዳ. 11፡ 11 -13

ያ ሁሉ የንጉሥ ሶሎሞን ግዛት ተቆራርጦ ቀረ። ከሶሎሞን በኋላ ይሁዳ ተገንጥሎ ወጣ። እስራኤል ሁለት ተከፈለች።

ኢየሩሳሌምን በናቡከደናጾር የሚመራ የሜሶፖታሚያ (ኢራቅ) መንግሥት ወረራት። ኢየሩሳሌም ተቃጠለች። ንጉሡ ሶሎሞን ያሠራውም ታላቁ ቤተ መቅደስም ፈረሰ (ታቦተ ጽዮን በኢትዮጵያ)።

እስራኤላውያን ተሰደዱ፤ እንደገናም ከተሰደዱበት ተመልሰው ተሰባሰቡ። ቤተ መቅደሱንም እንደገና ገነቡት። ከዚያም፥ በሮማውያን ይገዙ ጀመር። በዚህን ጊዜ ሁሉ ምድራዊ ነፃነትን የሚያጎናጽፍ ታላቅ ንጉሥ ይጠባበቁ ነበር። ቀደም ሲል የተተነበየለት ማን እንደሆነ አልገባቸውም።

“በእሴይ ግንድ በትር ይወጣል፥ ከሥሩም ቁጥቋጥ ያፈራል። .. " ኢሳ. 11፡ 1

“.... እነሆ ድንግል ትጸንሳለች፤ ወንድ ልጅም ትወልዳለች፤ ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች።” ኢሳ. 7፡ 14

“ህጻን ተወልዶልናልና፥ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና፥ አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል፤ ስሙም ድንቅ መካር፥ ኃያል አምላክ፥ የዘለአለም አባት፥ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል። ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘለአለም ድረስ በፍርድና በጽድቅ ያጸናውና ይደግፈው ዘንድ በዳዊት ዙፋንና በመንግሥቱ ላይ አለቅነቱ ይበዛል፥ ለዘላሙም ፍጻሜ የለውም ..።” ኢሳ. 9፡ 6 - 7

እስራኤላውያን ምድራዊ ነፃነትን የሚያጎናጽፍ ታላቅ ንጉሥ ሲጠባበቁ፥ ዘለአለማዊ ሕይወትን እባካችሁ እንኩ የሚል ከዳዊት ዘር ህጻን ተወለደ።

በዚህ ግፍ በሚፈጸምበት ሥፍራ እግዚአብሔር ከሰማይ ፍቅር አወረደ፤ መንፈሱን ከድንግል ማርያም አሳደረ፤ እንደ ሰው ሆኖ ተወለደ (ፍጹም ሰው፥ ፍጹም አምላክ)።

በምድር ላይ ኑሮ እየከፋ በሄደ ቁጥር ሰዎች ፈጣሪያቸውን ያማርሩታል።

“አሕዛብ ለምን ያጉረመርማሉ? ወገኖችስ ለምን ከንቱ ይናገራሉ?..” መዝ. 2፡ 1 - 2

ሕዝቦች ቢያጉረመርሙም፥ አምላካችን፥ እርሱ ራሱ በልጁ በኩል ወደ ፍጡራኑ (ወደ ልጆቹ) መጥቶ፥ አንድ ሰው በተፈጥሮ ችሎታው ሊቋቋመው የማይችለውን መከራና ሥቃይ ተቀበለ። እኛም ብዙ ሰማንና፥ ብዙ አሰብንና፥ በሕይወታችንም ብዙ ነገር ተመለከትንና ለማመን በቃን (በዚህ ምክንያት የሚሰማንን ሁሉ ሳንደብቅ እንናገራለን)።

ኢየሱስ ክርስቶስ በሰዎች መካከል ያለውን ልዩነት በፍቅር ለማጥፋት የጀመረው መንፈሳዊ ተግባር፥ የእኛ የክርስቲያኖች ዘወትር ልንጠቀምበት የሚገባ፥ መመሪያችንና አላማችን ሆነ።

ክርስቶስ በወቅቱ ነበሩትን ሰዎች ሊገባቸው በሚችል መንገድ ሁሉ ብዙ ብዙ ተአምራትን እየሠራ አስተማረ። አንድ ሰው በሥጋ መልሶ መላልሶ ቢወለድም ከሥጋዊነት እንደማያመልጥ - አካላዊ ሥጋና መንግሥተ ሰማያት ተቃራኒዎች መሆናቸውን፤ ማንም ሰው ዳግመኛ በመወለድ መንፈሳዊ ሕይወቱን ማጠናከር እንዳለበት በግልጽ አስረዳ። እራሱን ዝቅ አድርጎ፥ የሐዋርያትን እግር አጠበ፥ ..ወዘተ..።

ክርስቶስ በሰዎች መካከል ያለውን ልዩነት በፍቅር ለማጥፋት ሲሠራ፥ በርባን የተባለ ኃይለኛ ግን በጉልበቱ እየተጠቀመ፥ ወንጀሎችን ይፈጽም ነበር።

የክርስቶስ የመጨረሻ የፍርድ ቀን በደረሰ ጊዜ፡- በርባን ከእስር ቤት እንዲለቀቅ፥ ክርስቶስ በመስቀል እንዲሰቀል ተደረገ። ግን ይህ አሰቃቂ ትርኢት የተስፋችን መጨረሻው ሳይሆን የተስፋችን መጀመሪያ ሆነ። "...እግዚአብሔር የሁላችንንም በደል በእር ላይ አኖረ.." ኢሳ. 53፡ 4 - 7

ሕዝቦች አጉረመረሙ፤ ክርስቶስ ግን ከሥጋዊነት ጋር የተያያዙ ችግሮችን ሁሉ (አካለ ስንኩልነት፥ ህመም፥ ሞት) ከፍጡራት (ከልጆቹ) በማስወገድ በተግባር ላሳየው ርህራሄ፥ እርሱ ያተረፈው በገዛ ፍጡራት (ግን ልጆቹ ባልሆኑት) ተሰቃይቶ መገደልን ነበር።

በመስቀል ላይ ሆኖ፥ "ኤሎሄ ኤሎሄ ላማ ሰበከታኒ" ብሎ ጮኸ። ሰይጣንም የክርስቶስን ጩኸት ሰምቶ ነፍሱን ሊያጠፋ ወደ ክርስቶስ ተጠጋ። ክርስቶስም በመለኮታዊ ኃይሉ ሰይጣንን አስሮ፥ እርሱ ሕዝቦች በሰይጣን ወደታሰሩበት ሥፍራ - ወደ ሲኦል ወረደ።

"እነሆም የቤተ መቅደስ መጋረጃ ከላይ እስከ ታች ከሁለት ተቀደደ። ምድርም ተናወጠች፥ አለቶች ተሰነጠቁ፥ መቃብሮችም ተከፈቱ፥ ተኝተው ከነበሩትም ከቅዱሳን ብዙ ሥጋዎች ተነሱ፤ ከትንሳኤውም በኋላ ከመቃብሮች ወጥተው ወደ ቅድስት ከተማ ገቡና ለብዙዎች ታዩ። .." ማቴ. 27፡ 51 - 54

ክርስቶስ ወደ ሲኦል ወርዶ በሰይጣን የታሰሩትን የሰው ልጆች ሁሉ ነፃ አወጣቸው፤ በሦስተኛውም ቀን እንደገና በአካላዊነት ተገለጸ (ትንሳኤ)። ብዙ አይሁዶች ወደ ክርስቲያንነት ተቀየሩ።

መስቀሉ ላይ በተቸነከረው በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ሐዋርያት ተነሳስተው አውሮፓንና እስያን፥ እንዲሁም ሰሜን አፍሪቃን ክርስቲያን አደረጉት። የክርስቲያን ሃይማኖት ምሥጢር በዚህ የእግዚአብሔር ፍቅር ላይ የተመሠረተ ሆነ።

<u>የእስራኤሎች መበተን እና እንደገና መሰባሰብ</u>

ከክርስቶስ በፊት በ586 ዓመተ ዓለም ናቡከደናጾር ኢየሩሳሌምን እና ንጉሥ ሶሎሞን ያሠራውን ቤተ መቅደሱን ካፈራረሰ በኋላ አይሁዶች ለሰባ ዓመታት በባቢሎን በግዞት ይኖሩ ነበር። ከሰባ ዓመታት በኋላም፥ ንጉሥ ጢሮስ በፐርሺያ (በኢራን) እንደነገሡ፥ አይሁዶቹን ነፃ አወጣቸው። ወደ አገራቸውም ተመልሰውና ተሰባስበው ቤተ መቅደሳቸውን እንዲሠሩ ፈቀደላቸው።

ሁለተኛው ቤተ መቅደስ ተሠርቶ ብዙ ቆየላቸው። ከጊዜ ብዛት አርጅቶ የነበረውን ቤተ መቅደስ በይሁዳ ላይ የነገሠ ሄሮዱስ አድሶት ስለነበረ፥ በክርስቶስ ዘመን እጅግ የሚደነቅ ነበር። ሄሮድስ ከሞተ በኋላ የሮማውያን ቅኝ አገዛዝ በአይሁዶች ላይ ስለጸናባቸው፥ አይሁዶች በየጊዜው ያምጹ ነበርና፥ በ66 ዓመተ ምህረት ታላቅ አመጽ ተቀሰቀሰ። በ70 ዓመተ ምህረት ሮማውያን ኢየሩሳሌምን፥ ቤተ መቅደሱንም አፈራረሱ።[31]

ከሥጋቸው መንፈሳቸው የሚያመዝንባቸው እስራኤላውያን “እንዲህ በባርነት ከመኖር መሞት ይሻለናል” ብለው ማሳዳ ከሚባል ገደል እየዘለሉ ተፈጠፈጡ - ሞቱ። ይህም ማሳዳ የተባለ ሥፍራ በኢትዮጵያ ትግራይ ክፍለ አገር ያለውን ደብረ ዳሞን የመሰለ ነው። ዙሪያው ሁሉ ገደል ስለሆነ፥ ለእስራኤል ጀግኖች ጥሩ ምሽግ ሆኖላቸው ነበር። ሮማውያን ይህንን ምሽግ ሊያስለቅቁአቸው ሲመጡባቸው ህጻን ሽማግሌ - ሁሉም ከገደል እየዘለሉ ሞቱ።

ጥቂት ሰይጣናውያን አይሁዶችና ግብረ አበሮቻቸው ለጥያቄዎቻቸው ሁሉ ክርስቶስ መልስ እንዳይሆንላቸው አስቀድመው በመስቀል ላይ አሰቃይተው ገድለውታል። በመለኮታዊ ኃይሉ ከተፈጥሮ በላይ መሆኑን ሲያሳያቸው፥ በሥጋ የታመሙትን ሲያድን እና ሙታንንም ሲያስነሳ፥ እነርሱን ግን ከቅኝ ግዛት አውጥቶ አለማዊ ነፃነትን ስላላጎናጸፋቸው፥ ይህ መሲህ ነው እየተባለ የተነገረለት ማን እንደሆነ አላወቁም። ነገር ግን፥ የክርስቶስ እቅድ በእስራኤላውያን ላይ ብቻ ሳይወሰን ጠቅላላ የአለምን ሕዝብ ነፃ ለማውጣት መሆኑን አልተረዱም።

---

[31] ማቴ. 24፡21፤ ማር. 13፡2፤ ሉቃ/ 19፡44

በ135 ዓመተ ምህረት አይሁዶች ከያለበት መንጫጫት ጀመሩ፤ "…..ከያዕቆብ ኮከብ ይወጣል፥ ከእስራኤል በትር (ሰው) ይነሳል፥ የሞአብንም ማዕዘኖች (አለቆች) ይመታል፥ የሤትንም ልጆች ያጠፋል (ይማርካል)፥…." ኦሪት ዘኍልቁ 24፡ 17 የሚለውን ጥቅስ እያብሰለሰሉ ያጠኑታል። እንደገና በአንድ ማእከላዊ ኃይል መሰባሰብን እየፈለጉ፥ ግን ይህ ጥቅስ ማንን እንደሚያመለክት አልገባቸውም።

በዚያን ዘመን አይሁዶችን በማስተባበርና በሮማውያን ላይ እንዲያምጹ በማድረግ፥ በጀግንነቱ የታወቀ ሺሞን ባር ኮክባ የተባለ ሰው ተነሳ። የተጠቀሰውን ትንቢት በማስመልከት "ይህ ነቢያት የተነበዩለት ሺሞን ባር ኮክባን ነው እንጂ፥ ሌላ አደለም…" በማለት አኪባ የተባለ ሊቅ ለሕዝቦች ሁሉ አሳወቀለት። ባር ኮክባም የአኪባን ድጋፍ በማግኘቱ ብዙ ተከታዮች አፈራ።

በአንጻሩ፡- ያችናን ቤን ቶርታ የተባለ የከፍተኛ ፍርድ ሸንጎ መሪ - ይህ መሲህ የተባለ ሰው ባር ኮክባ አለመሆኑን አጋለጠ። እንዲህም ብሎ ለአኪባ ተናገረው - "ከጉንጮችህ ላይ ሳር ከበቀለ በኋላ እንኳን ቢሆን[32]፥ የመሲሁ የዳዊት ልጅ መምጫው ገና ነው።"

ዳሩ ግን የባር ኮክባ ገናናነት፥ የሕዝቡም የጦርነት ስሜት እጅግ ስላየለ፥ ባር ኮክባና በዙሪያው ያሰለፋቸው ወታደሮች ሮማውያንን በጦር ለመግጠም ተነሳሱ። ባር ኮክባም ከቆራጥነቱ በስተቀር ባለጌ በመሆኑ፥ እንዲህ ብሎ ጸለየ እየተባለ ይነገራል -

"….እግዚአብሔር ሆይ፥ አትርዳን፤ ግን አታግደን…..።"

በዚሁም አንጻር - "…አምላክ ሆይ እባክህ እርዳን…" እያሉ የሚጸልዩ ብዙዎች ነበሩ። ከነኚህም መካከል፥ እራሱን በጆንያ ውስጥ አድርጎ፥ አመድ ላይ ተቀምጦ፥ እግዚአብሔርን ካለማቋረጥ የሚለምን አላዛር የተባለ ምስኪን ሰው ነበር። አይሁዶችም፥ "አላዛር ከአመድ ላይ ተነስቶ ጸሎቱን እስካላቋረጠ ድረስ፥ ድል የኛ ናት.." ይሉ ነበር።

ከእለታት አንድ ቀን፥ ሰይጣን በሰው ተመስሎ ወደ አላዛር ሲቀርብ ባር ኮክባ ያስተውላል። ይህ ሰው ወደ አላዛር ጆሮ ተጠግቶ ምሥጢር የተናገረ በመምሰል አንሾካሾኮ ጥፍት ሲል ለባር ኮክባ ይታየዋል። ባር ኮክባም-

"ይህ ለአላዛር አንሾካሽኮ ይሄደ ሰው ከሰማይ የተላከ መሆን አለበት፥ ለአላዛር ያቀበለውን ምሥጢር ማወቅ አለብኝ.." በማለት አላዛርን ቢጠይቀው፥ አልአዛርም በድንጋጤ -

[32] ሞተህ በስብሰህ ማለት ነው።

"ኸረ! ማንም ከኔ ዘንድ የቀረበ ሰው የለም! ኸረ! እኔ ምንም የማያውቀው - የሰማሁትም ነገር የለኝም..." ብሎ በፍርኃት መለሰለት።

በዚህን ጊዜ ያው በሰው ተመስሎ የታየው ሰይጣን -

"በል እንግዲህ ምን ትጠብቃለህ? እንዲህ አይን ባይን ሲዋሽህ። በለው! እርገጠው።" በማለት መከረው። ባር ኮክባም የሰይጣን ምክሩን ሰምቶ አልአዛርን አንድ ጊዜ በእርግጫ ቢመታው፥ አላዛር በጾምና በጸሎት ሰውነቱ ደክሞ ስለነበረ፥ ወዲያውኑ ሞተ።

በዚህን ጊዜ ከሰማይ ድምጽ ተሰማ ይባላል። ይህም ድምጽ -

"ባር ኮክባ እድልህን በራስህ አጠፋኸው።"

ጀግናው ባር ኮክባ የሮማን ወታደሮች ፈጃቸው፤ ነገር ግን መጨረሻው አላማረም። በዚህ የአይሁዶች ጦርነት ሮማውያን አሸነፉ። ባር ኮክባንም ሰው ስለማይገድለው፥ እባብ ነክሶት ሞተ ይባላል።

እንዲህ አይነት ታሪክ በእስራኤሎች ዘንድ ይተረካል (አፈ ታሪክም ሊሆን ይችላል)። ከዛ በኋላ እስራኤላውያን ያንን አካባቢ እየለቀቁ ሸሹ፤ በአለምም ዙሪያ ተበተኑ። ከጥንትም ቢሆን፥ እነርሱ ከእግዚአብሔር እየራቁ የሚያደርጉት ነገር ሁሉ ውጤቱ እንደማያምር ከታሪካቸው የታወቀ ሆነ። ያለው አማራጭ አንድ ነው። ይኸውም - ከበታኝ ኃይል መራቅና፥ ወደ ሰብሳቢው ማእከላዊ ኃይል መጠጋት ነው።

ባለ ታሪኮቹ በሥጋም በመንፈስም፥
አንድ ነገድ - አንድ ሕዝብ ተብለው፥ ከጥንት ከአብርሃም፥
ለእግዚአብሔር የቀረቡቱ፥ እንዳልተወደዱ፥
ካገራቸው ወጡ፥ በአለም ተሰደዱ።
አገር አለኝ ብሎ መኖር አልተቻለም፥ በሰላም በርጋታ፥
መቅኖ ቢስ የሆነው፥ ከዚህም ከዚያም ቦታ፥
የአንድ ሕዝብ ታሪክ ሆነ የውሃ ሽታ።
የሚያማልድ ጠፍቶ፥ ኩቶም የሚማጸን፥
የእስራኤል ሕዝብ ጩኸት ቆየ ብዙ ዘመን።
በእውነት የእግዚአብሔር ልጆች፥ ተስፋ የማይቆርጡ፥
በትንቢቱ መሠረት[33]፥ ከያለበት መጡ።

[33] ትንቢተ ሆሴዕ 3፡ 4-5፤ 6፡1 ሕዝቅኤል 20፡34፤ አርምያስ 32፡44 ኢሳያስ 11፡11 – 12፤ 66፡8

ቤተ እስራኤሎችም የኢትዮጵያ ዜጎች፥
ኢየሩሳሌም ገቡ፥ ሊፈልጉ ጌታን፤
ሁላችን በየማእከላችን - በየእምነታችን፥
የማይቀር ነው መሰባሰባችን።
ንዑስ ማእከሎቻችንም ይጠጋጋሉ፤
በአንድ በእግዚአብሔር አንድ ይሆናሉ።
የሰው ልጅ እድሉ እንደሰም አይቀልጥም፥
ችሎታው ቢቀበር መብቀሉ አይቀርም።
በታኝ ምድራዊነት ቢያራርቀንም፥
ደካማው ጎናችን፥ ቢለያየንም፥
በመንፈሳዊነታችን መሰብሰብ አይቀርም።

<u>ኦርቶዶክስ</u>

ከጥንት ጀምሮ፥ አንድ ወጥ የሆነ የክርስቲያን ሃይማኖት እስኪሰበክ ድረስ፥ በአንዳንድ የኢትዮጵያ ክልሎች ውስጥ ሕዝቦች የየራሳቸው እምነት ነበራቸው። ባህላዊ ኑሮአቸውና የቀን ተቀን ኑሮአቸውም ከዚሁ ከእምነታቸው ጋር የተያያዘ ነበረ።

የክርስትና ሃይማኖት ወደ ኢትዮጵያ እስከገባ ድረስ፥ እና ከዚያም በኋላ፥ እስከ ዮዲት ጉዲት ዘመን መጨረሻ (አስረኛው መቶ ክፍለ ዘመን) ድረስ በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል የአይሁድ ሃይማኖት ከንግሥት አዜብ ጀምሮ፥ ከልጇ ከሚኒሊክ እና አብረውት ከመጡትም የእስራኤል የበኩር ልጆች ቀጥሎ የተስፋፋ እንደነበረ ይታወቃል። እግዚአብሔር በቀጥታ የሚያነጋግራቸው ጻድቃንና ነብያት የእግዚአብሔርን ንግግር ለሕዝቡ በቀጥታ እያስተላለፉ፥ ሕዝቡ ከእግዚአብሔር ፈቃድ እንዳይወጡ ብዙ- ብዙ ምክር መከረዋቸዋል፤ ይህም ምክር ወደኛ ተላልፏል።

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰውን ዘር በፍቅር ለማስተሳሰርና በሰዎች መካከል ያለውን ልዩነት በፍቅር ለማጥፋት የጀመረው መንፈሳዊ ተግባር፥ አሁንም እኛ ዘወትር ልንጠቀምበት የሚገባ መመሪያችንና አላማችን ይሆን ዘንድ፥ ሐዋርያት በአለም ዙሪያ እየሄዱ አስተማሩ። እነርሱ በመጀመሪያ ለአይሁዶች ሲያስተምሯቸው መንፈሳዊ ታሪካቸውን በማስታወስ፥ የሚያውቁትንና ዘወትር የሚያነቡትን እየጠቀሱ ነበር። አስቀድሞ የተተነበየለትንም እያመሳከሩ፥ እነርሱ

በእንጨት ላይ የሰቀሉት በእውነት እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ሲነገሯቸው - በግልጽ ያዩትንና የሆነውን መልሰው ሲተርኩላቸው ላለማመን ያስቸግራቸው ነበር።

ከአይሁዶችም ብዙዎች አመኑ። ግን በውሱን ሥጋዊ አመለካከት ምክንያት፥ ክርስቲያንነት እና ክርስቲያናዊ አመለካከት ሁለንተናዊ (አለም አቀፍ) ሊሆን አልቻለም።

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ (ሰላሳ ዓመታት አካባቢ)፥ የኢትዮጵያ ጃንደረባ (የንግሥት ህንደኬ ባለሟል) ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ ነበር። መንፈስ ቅዱስም ፊሊጶስ ከተባለው የክርስቶስ ሐዋርያ ጋር አገናኘው። ጃንደረባው በትንቢተ ኢሳያስ የተጠቀሰውን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ አለም መምጣትና ስለ ሰዎች ኃጢአት መሞት በመደጋገም አነበበ።

“እንደ በግ ወደ መታረድ ተነዳ፤ የበግ ጠቦትም በሰላቹ ፊት ዝም እንደሚል፥ እንዲሁ አፉን አልከፈተም። በውርደቱ ፍርዱ ተወገደ፤ ሕይወቱ ከምድር ተወግዳለችና፤ ትውልዱንስ ማን ይናገራል?” የሐ.ሥራ 8፡32

ጃንደረባው የአዲስ ኪዳንን የድኅነት ምሥጢር ሳይሰማ ቀረ እንጂ፥ ብሉይ ኪዳንን ጠንመቆ የሚያውቅ ነበር። ነገር ግን የዚህ ጽሑፍ ትርጉም ግራ አጋብቶት ሳለ፥ ፊሊጶስ በድንገት ከተፍ አለለት።

ፊሊጶስም ይህ ጃንደረባው የሚያነበው የነበረው በእርግጥ የተፈጸመ መሆኑን ለጃንደረባው በደንብ አድርጎ አስረዳው - እስከ መጠመቅም የሚያበቃ ክርስቲያናዊ ትምህርትን በጥቂት ጊዜ ውስጥ መግቦ አጠገበው። ጃንደረባውም ፊሊጶስን -

“ይኸው ውሃ ካለበት ደርሰናልና፤ ያስተማርከኝ ሁሉ አሁን ስለገባኝ አጥምቀኝ፤ እኔም ካሁን በኋላ የክርስቶስ ተከታይ ልሁን..” አለ።

ፊሊጶስም ጃንደረባውን አጠመቀው። ጃንደረባውም ክርስቲያን ሆኖ በመጠመቅ ወደ ኢትዮጵያ ተመለሰ። የክርስትናም ሃይማኖት ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ ገባ።

“የተርሴስና የደሴቶች ነገሥታት ስጦታን ያመጣሉ፤ የዓረብና የሳባ ነገሥታት እጅ መንሻን ያቀርባሉ። ነገሥታት ሁሉ ይሰግዱለታል፥ አሕዛብም ሁሉ ይገዙለታል።” መዝ. 72፡ 10 11 የተባለለትን ንጉሥ አስቀድሞ በመንፈሳቸው ያወቁት ሕዝቦች በቀጥታ ሲነገራቸው በቶሎ የማያምኑበት ምክንያት ሊኖር አይችልምና፤ ጃንደረባው ቶሎ እንደገባው እንዲሁም የኢትዮጵያ ሕዝቦች ቶሎ ክርስቲያን ለመሆን አላዳገታቸውም።

የክርስቶስን ትምህርት ቶሎ ተቀብለው በሥራ ላይ ያዋሉ ኢትዮጵያኖች በዙ። ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ ከገባ ጀምሮ እስከ ሦስት መቶ ሃምሳ ዓመት ድረስ የክርስትና

ሃይማኖት እየተስፋፋ ብዙ ሰው ክርስቲያን ቢሆንም፥ በኢትዮጵያ ሥጋ ወደሙ መቀበልና ጥምቀት መጠመቅ አልነበረም። ከአንድ ነጋዴ ጋር ወደ ኢትዮጵያ የገባ ፍሬምናጦስ ከሊቀ ጳጳሱ ከአባ (ቅዱስ) አትናቴዎስ "ኤጲስ ቆጶስ ዘአክሱም ወዘኩላ ኢትዮጵያ" ተብሎ በ330 ዓ.ም. ተሾመ።[34]

ፍሬምናጦስም አባ ሰላማ በመባል ብዙዎችን በክርስቲያንነት አጠመቀ፤ ሥጋ ወደሙ አቀበሉ። እኛም በእግዚአብሔር ትእዛዝ (ፈቃድ) የተዋሕዶ ኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታዮች እንሆን ዘንድ መደረግ ያለበትን እያደረግን ቆየን። ቀደም ሲል የታቦቱን አመጣጥ ጠቅሰናል። ምንድነው ይህ የመንፈሳዊነታችን ነገር - ጥንት የነበረው፥ ዛሬ ያለው፥ ለወደፊትም የሚኖረው - በየቤተ ክርስቲያናቱ በየመቅደሱ የሚገኘው፥ የጻህሉና የጽዋው ማረፊያ፥ የመስዋዕቱ መከበሪያ ታቦት ምሥጢር።

ምንድነው ይህ የመንፈሳዊነታችን ነገር - ከዘመነ ሙሴ እስከ ድንግል ማርያምና ልጇ፥ እስከ ዛሬና ለወደፊት የሚቀጥለው የቅዱስ ቁርባን ነገር - ከጊዜአዊው መና እስከ ዘለአለማዊው የሕይወት እንጀራ።

በኦርቶዶክስ፥ ጻህሉና ጽዋው፥
ምንጊዜም ከታቦቱ የማይለየው፥
እንዲህ የጊዜን ጽንሰ ሃሳብ የሚደመስሰው፥
የጥንቱን ከዛሬውና ከወደፊቱ የሚያገናኘው፥
በእኛ ውስጥ (በአገራችንም) ተቀርጾ ያለው፥
እንዲህ ምሥጢሩ የበዛው፥
የምድሩን ከሰማይ ያገናኘው፥[35]
የእውነት እውነትነት ጊዜ የማይሽረው።

> ከእንግዲህስ ይህ ጉዳይ በደንብ ባይገባኝ፥
> ምሥጢሩም እጅግ ጥልቅ ቢሆንብኝ፥
> "ደስ የሚያሰኝህን ፍሬ እሠራ ዘንድ ስጠኝ።
> (ሃበኒ እግበር ፍሬ ዘያሰምረከ)።

---

[34] አባ ጎርጎርዮስ፥ 1978፤ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ፥

[35] ወደ እብራውያን 9፡ 1-5

በሃይማኖት ጉዳይ የተቀሰቀሰ ጭቅጭቅ[36] የተወሰኑ ቅዱሳንን ከሚኖሩበት ሥፍራ አፈናቀላቸው። በተለይ ዘጠኝ ቅዱሳን (አባ አሌፍ፥ አባ ጽሕማ፥ አባ አረጋዊ፥ አባ አፍጺ፥ አባ ገሪማ፥ አባ ጴንጠሌዎን፥ አባ ሊቃኖስ፥ አባ ጉባ፥ አባ ይምዓታ)፥[37] ከሮምና ከግብጽ፥ "ጸጥታ ወደሚገኝበት ሰላማዊ አገር እንሂድ.." ብለው ወደ ኢትዮጵያ መጡ። ከነኚህም መካከል በኋላ አባ አረጋዊ የተባሉት (አባ ዘሚካኤል) የደብረ ዳሞን ገዳም የመሠረቱ ናቸው።

የተጠቀሱት ቅዱሳን የኢትዮጵያን ሕዝብ በማስተማር፥ ቅዱሳት መጻሕፍትን በመተርጎም እና ገዳማትን በመመሥረት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረጉ ጻድቃን ናቸው። ከነርሱም በኋላ፥ ከጥንት ጀምሮ እስካሁንም ድረስ፥ እንደ ሐረግ በመያያዝ፥ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያናት ሃይማኖታዊ ትምህርት ታንጸው በመንፈስ የመጠቁ በኢትዮጵያ (በኤርትራም) ብዙ ጻድቃንና ቅዱሳን ነበሩ (አሉ)።

አያሌ ቤተ ክርስቲያናት ታነጹ፤ ቁሶችና ዲያቆናት ተበራከቱ፤ በየጫካውና በየገደሉ ገዳማት ተመሠረቱ።

ከመንፈሳዊ ታሪካችን ባሻገር፥ በመንፈሳዊ ጉዞ ውስጥ - መንፈሳዊ ክስተቶችን እንዴት የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚፈጽሙ መላእክት ከሰዎች ጋር ሆነው ብዙ ብዙ እንደታገሉ አያሌ ማስረጃዎችን ከመጽሐፍ ቅዱስ መመልከት ይቻላል።

እስከዛሬ ድረስ የሰው ልጅ መንፈሳዊ ጉዞ ከማይታየውና ከማይነካው አለም ጋር አንድ አይነት ግንኙነትን ለመመሥረት የተደረገ ጥረት ይመስላል። አጠቃላይ እንቅስቃሴዎች ሁሉ ለአንድ እግዚአብሔር አምልኮት መንገድ ሲጠርጉ እናስተውላለን። ለምሳሌ፥ በመንፈሳዊው አለም ውስጥ፥ እርኩሳን መናፍስት ከቅዱሳኖቹ ጋር እየተጋጩ በመጨረሻ እርኩሶቹ ሲሸነፉ፥ ቅዱሳኖቹ ሲያቸንፉ እንገነዘባለን (ምንጊዜም ከመጠፋፋት የሚተርፈው እውነት ነውና)።

እስከ ንጉሡ ቆስጠንጢኖስ ድረስ ብዙ መጠፋፋቶች ተካሂደዋል። ንግሥት እሌኒ ኦና ልጇ ቆስጠንጢኖስ ከዚህ መጠፋፋት የተገኙ ናቸው። በንጉሥ ቆስጠንጢኖስ ዘመንና ከዚያ በኋላ፥ ሰዎች ወደ ባህር እየሄዱ ሲጠመቁ፥ ቤተ ክርስቲያናት በያለበት ሲመሠረቱ፥ ሰይጣን በአልጋው ላይ ተኝቶ አላንቀላፋም፤ እንደ ሰው እየሆነ ሰዎችን ያታልል ነበር እንጂ።

---

[36] ስለዚህ ጭቅጭቅ በደንብ ለመረዳት ከአባ ጎርጎርዮስ፥ 1978፤ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ፥ የተሰኘውን መጽሐፍ ያንብቡ።

[37] ገድለ አቡነ አረጋዊ

በአንድ ወሳኝ በሆነ ወቅት፥ ሰዎች ከበስተኋላቸው ያሳለፉት ከንቱ ጊዜ እየቆጫቸው ቶሎ ብለው የሚያምኑ ይሆናሉ። ጻድቃን በፈጣሪ አምላካቸው ስም አንድ ትንሽ ተአምር ሲሠሩ፥ በአንድ አገር የሚኖሩ ጣኦት አምላኪዎችም ይህንን የተሠራ ተአምር ሲመለከቱ፥ እነርሱ ለጣኦት መስገዳቸውን ይተውና - "እናንት ሰዎች ከዛሬ ጀምሮ በእናንተ አምላክ እናምናለን..." በማለት፥ እምነታቸውን ወደ ፈጣሪ አምላካቸው ያደርጉታል።

የእግዚአብሔር ታማኝ አሽከሩ የሆነ ሚካኤልም በሰው እየተመሰለ ሕዝቦች ዘላቂውን እውነት እንዲያዩ ይረዳቸው ነበር (ድርሳነ ሚካኤል ዘመጋቢት)። ይህ የሚያመለክተው፥ በአሁኑ ጊዜ በአለም ተስፋፍቶ የሚገኝ ሃይማኖት በሰዎች ትግል ብቻ የተገኘ አለመሆኑን፥ ከምድራዊነት ባሻገር እኛ የማናየው ብዙ - ብዙ መንፈሳዊ ክንውኖች የነበሩበት መሆኑንም ነው። እነኚህ መንፈሳዊ ክንውኖች - ምንጊዜም ከመጠፋፋት የሚተርፈው እውነት እንዲሆን ያደርጋሉ። ለዚህ ነው፥ ለፈጣሪ አምላካችን እየሰገድን፥ ተራዳኢ ለሆኑ መላእክትም ምስጋና የምናቀርብ። ለዚህ ነው፥ በችግር ውስጥ ስንገባ - ተናዳፊ ጠላት (ሰይጣን) ሲያስጨንቀን፥ ሚካኤል አለልኝ፥ ገብርኤል ይከተለኛል የምንል።

ከስድስተኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ የእስልምና ሃይማኖት በአለም እየተስፋፋ መጣ። የዚያን ጊዜ ኢትዮጵያ ከአለም በመገንጠል በሯን ዘጋች። ቅዱሳን ሰዎችም እንደልብ ወደ ኢትዮጵያ መግባት አቃታቸው።

በእስልምና መስፋፋት፥ በግራኝ መሐመድ ወረራና ጥፋትም ሆነ በጣልያን ፋሺስታዊ ግፍ፥ የኢትዮጵያ ሕዝቦች የቀን ተቀን የመንፈሳዊ ጉዞአቸው አልተሰናከለም፤ ማንኛውንም የጠላት ኃይል ከመላእክት ጋር ሆነው ተቋቋሙት እንጂ። ሰው ቢገደል፥ ሃብት-ንብረት ቢወድም፥ ባገሪቷ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ቢደርስ፥ ይህ ሁሉ ጥቃት ተደማምሮ የሕዝቡን ሃይማኖት አልበረዘውም፤ እምነቱን አጠናከረው እንጂ።

የፕሮቴስታንት ሃይማኖት በጃንሆይ - በንጉሠ ነገሥቱ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ተስፋፋ። ብዙ ሚሲዎናውያን በተለይ በደቡብ ኢትዮጵያ በመሰማራት፥ ትምህርት ቤትና ቤተ ክርስቲያን እየከፈቱ፥ ሰዎች መንፈሳዊነታቸውን በክርስቲያናዊነት እንዲያድሱ (እንዲያጠናክሩ) አደረጉ። ከዚሁም ጋር ያካባቢው ሕዝብ በዘመናዊ ትምህርት ተሳታፊ ለመሆን በቃ። በዚህ መልካም ሥራ እግዚአብሔር ደስ ይለዋል። "ለምን የኔ ሃይማኖት ብቻ አልተሰበከም.." ብሎ የሚያጉረመርም በዛው በምድራዊ ክፋት የተጠመደ ሰው መሆን አለበት።

ጀንሆይም፥ "የኦርቶዶክስን ሃይማኖት እስካልነካችሁ ድረስ አንከለክላችሁም.." በማለት፥ የሚሲዮናውያን ጥቅማቸውን እንጂ ቅራኔያቸውን እንዳያመጡብን በማስጠንቀቅ ነበር ወደ አገር እንዲገቡ የፈቀዱላቸው።

ነገር ግን አንዳንድ ፕሮቴስታንቶች የጃንሆይን ማስጠንቀቂያ በመጣስ፥ የኦርቶዶክስን ሃይማኖት እያጥላሉ፥ የራሳቸውን ከፍ እያደረጉ ይሰብካሉ። ከተከታዮቻቸውም መካከል አንዳንዶቹ ወደ ኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታዮች ይሄዱና "የኛን ሃይማኖት ካልተከተላችሁ በስተቀር መንግሥተ ሰማይን አትወርሱም..." እያሉ ይሰብካሉ።

የሚጸደቀው በሥራ ሳይሆን በሃይማኖት ቢሆን፥ ከዚህ ሁሉ የአለም ሃይማኖት መካከል፥ የሚጸድቁት የአንደኛው ሃይማኖት ተከታዮች ብቻ ይሆናሉ ማለት ነው። ታዲያ የትኛው ነው ያ ሃይማኖት? ወደኛ ሃይማኖት ተቀየሩ በማለት ፋንታ እንዲሁ ደግ መሥራትን ቢያስተምሩ በተሻለ ነበር።

ፋሺስት ጣሊያን ወደ ኢትዮጵያ ከመግባቱ በፊት፥ ከህጻን እስከ ሽማግሌ ቅዱስ ቁርባን እየተቀበሉ፥ የቤተሰብ ክብር በመንፈሳዊነት እየታደሰ የሚኖርበት ዘመን ነበር ማለት ይቻል ይሆናል። ፋሺስቶች የሰው ሕይወት አጥፍተው፥ መሬት ነጥቀው፥ እነርሱ ተደላድለው ሲኖሩ፥ አርበኞች ጫካ ሲገቡ፥ ሴቶችም የጣልያን ውሽማ ሲሆኑ፥ ሴትኛ አዳሪነት በዛን ጊዜ ተጀመሮ ሲቀጥልና እጅግ ሲስፋፋ፥ የሰውም ልጅ ክብሩ ሲቀንስ፥ ሃይማኖታቸው ካቶሊክ የሆኑ ፋሺስቶች ግፍ እየሠሩ ሲቀርቡ፥ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ተከታዮች በካቶሊክ ሃይማኖት ላይ ዝቅተኛ ግምት አደረባቸው (ፋሺስታዊነትንና ካቶሊክነትን የማይገነጣጠሉ አስመሰሉት)። ከጥንት ጀምሮ የሮማ ቤተ ክርስቲያን በኢትዮጵያና በግብጽ ላይ ሲያካሄድ የነበረውን የሃይማኖት ተጽንኦ (አባ ጎርጎርዮስ፥ 1978) በፋሺስት ኢጣልያም ተባባሰ።

ብዙ ኢትዮጵያውያን (በተለይ ወጣቱ) ፋሺስት ጣልያንን ላለመምሰል ሲባል፥ እና/ወይንም እንዲሁ በተለያዩ ምክንያቶች፥ ቤተ ክርሰቲያን ሄዶ ቅዱስ ቁርባንን ከመቀበል ያመነታ ጀመር።

ፕሮቴስታንቶችም እነርሱ የማያደርጉትን ልክ እንዳልሆነ ወይም እንደማይጠቅም ስለሚቆጥሩት፥ የቅዱስ ቁርባን ጠቃሚነት ጠንካራ ኦርቶዶክሳዊ አቋም በሌላቸው ሰዎች ስነአይምሮአዊ ግንዛቤ ውስጥ ጥርጣሬን አስከተለ። ከህጻናት በስተቀር ቆራቢዎች - ጎስቋሎች፥ አሮጊቶች፥ ሽማግሌዎች፥ ደካሞችና ህመም የጠናባቸው፤ የማይቆርቡትም፥ ጎረምሶች፥ ልታይ ባዮች - የአለም ሰዎች ሲሆኑ በመመልከት፥ ወጣቱ ይህንን መንፈሳዊ እርምጃ መውሰድ እየፈራ፥ እያፈረ፥

እርግጠኛም ሳይሆንም እየተጠራጠረ መጣ፤ ንስሐ መግባትና መቁረብ እንደ አንዱ የመንፈሳዊነታችን መገለጫ መሆኑ ተዘነጋ።

ከክርስቶስ በኋላ ለአያሌ ዓመታት፥ ታላላቅ የአለም መሪዎች ሕዝቦቻቸውም በጣኦት የሚያመልኩ ነበሩ። የክርስትና ሃይማኖት ከሐዋርያት የጀመረ ቢሆንም፥ ከተለያዩ እምነቶች መካከል ብዙ መዳቀልና መደፍረስ ነበረበት። የኮንስታንቲን ወታደሮች በጋሻዎቻቸው ላይ የመስቀል ምልክት አድርገው በመዋጋት ድልን ከተጎናጸፉ በኋላ፥ የክርስቲያን ሃይማኖት ሕጋዊነት በመንግሥት ደረጃ ተረጋገጠ። ከኒቂያ ጉባኤ በኋላ፥ የሃይማኖታችን መገለጫ (ዶክትሪን - ዶግማ) ተረጋገጦ፥ የማይጨመርበት - የማይቀነስለትም እንደሆነ ታመነበት (ጸሎተ ሃይማኖት)።

ቤተ ክርስቲያናት መሠረታዊ ከሆነው የሃይማኖት መገለጫ (ዶክትሪን - ዶግማ) በተጨማሪ በቤተ ክርስቲያን ሕግጋት (ቀኖና) ይለያያሉ። ቀኖና ባይኖር ኖሮ፥ የእኛም የተዋሕዶ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ስርአቱንና ሕግጋቱን ጠብቆ ከዘመናችን አይደርስም ነበር። ዶግማውን እንጂ፥ ቀኖናውን አልቀበልም የሚል ቢኖር፥ ጸሎተ ሃይማኖትን እየደገመ ከቤቱ ቁጭ ማለት ነው ያለው ምርጫ።

በጊዜ ብዛት፥ ሃይማኖት እየጠራ መጣ እንጂ አልደፈረሰም። እስከዛሬ ድረስ አያሌ ጽሑፎች ተቃጥለዋል፤ ከነኚህም ከተቃጠሉት መካከል ስለ ዘላቂው እውነት የሚያወሱ ጽሑፎች ይኖራሉ። አያሌ ወንጌልን የመሳሰሉ ጽሑፎች ተጽፈውም ነበር። ከሰብአዊ አይምሮ የፈለቁ ወይንም ምድራዊነትንና ሰማያዊነትን አጣምረው የያዙ አያሌ ጽሑፎች በየሥፍራው ተበትነዋል። እነኚህ ጽሑፎች በተለያየ ቋንቋ ተጽፈው ባገራችንም በግዕዝና ባማርኛ ተተርጉመዋል። የአብዛኛዎቹ መንፈሳዊ ጽሑፎች አላማ ጽሑፎቹ በተጻፉበት አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች አምልኮት ወደ ፈጣሪያቸው ወደ እግዚአብሔር ብቻ እንዲያተኩር ለማድረግ ነበር። የጽሑፎቹም ይዘት - ታሪካዊነት፥ ትህምርታዊነት፥ መንፈሳዊነት እና ሰብአዊ ስሜታዊነትን አጣምሮ የያዘ በመሆኑ፥ እንደ ጊዜውና አካባቢው ከፍተኛ መንፈሳዊ አስተዋጽኦ ነበረው። በአሁኑም ወቅት ቢሆን፥ በተለያየ የእድገተ ሕሊና ደረጃ ላይ ላሉ ሰዎች፥ እንደየአስተሳሰባቸው እና ጠባያቸው፥ መጠነኛ ወይም ከፍተኛ መንፈሳዊ ድጋፍ ይሰጣል። ግን ወሳኙ፥ በጊዜ ውስጥ በየጊዜው የሚያድገው የሕዝቦች መንፈሳዊ ንቃት መሆኑን ልብ ይሏል።

አሁን ካሉትም ከወደሙትም ጽሑፎች መካከል መገኘት ያለበት እውነት መርቶን ነው ከዚህ የደረስን፤ እውነት የሆነ ሁሉ ቢጻፍም ባይጻፍም እያደር እየጎላ ይመጣል እንጂ አይጠፋምና። በእርግጥ አንዳንድ መንፈሳዊ የሚመስሉ ጽሑፎች ውስጥ ከሃይማኖታችን (ከእምነታችንም) ጋር የሚጋጭ ነገር አይታጣም። ሆኖም፥ ፍጹም ባልሆነ ሰው የሚጻፍን ሁሉ ለምን እንከን ተገኘበት ብሎ በመከራከር ጊዜ

ማጥፋት ግንዛቤ ማጣት ነው፤ የሰውን አቅሙን አለመረዳት፥ እራስንም አለማወቅ ነው።

በምድራዊነት ከሚነካካ ከማንኛውም ነገር (ጽሑፍም፥ ንግግርም) የሚበልጠው ፍቅር ነው። ይህንኑ ፍቅር በተለያየ መንገድ ለማስተማር በተጻፉ አንዳንድ ጽሑፎች ውስጥ እንከን ቢገኝባቸውም ፍቅር ካለ፥ እንከኑ ሁሉ በፍቅር ይደመሰሳል። ይልቅስ ትችት በማብዛት የወገኖቻችንን መንፈሳዊ ቅንአት እንዳናሰናክል ብንጠነቀቅ እና ፍቅርን ብናስቀድም ይሻላል።

<u>ኢትዮጵያችን - መንፈሳዊት</u>

በጥንት ዘመን የኢትዮጵያ መንግሥት ታዋቂ ስለነበረ (2ኛ ነገሥት 19፡9፤ ኢሳ.37፡ 9..ወዘተ..)፥ እንዲሁም የኢትዮጵያ ሕዝቦች ይህንን ለክርስቲያን ሃይማኖት መሠረት የሆነውን የአይሁድ ሃይማኖት ተቀብለው በመቆየታቸው ኢትዮጵያ የሚለው ስም በመጽሐፍ ቅዱስ በተደጋጋሚ ተጽፎ ይገኛል።

ኢትዮጵያ የተባለችው አገር የቷ ናት? ሕዝቦቿስ እነማን ናቸው? በሚል አርእስት ላይ ሰዎች እንደየግል አስተሳሰባቸው (እንደየሃይማኖት እና የፖለቲካ ተቋማቸውም ጭምር) የተለያየ አስተያየት ይሰጣሉ። በጥንት ጊዜ በምሥራቅና በሰሜን አፍሪካ ታዋቂዎች የሆኑት ግብጽና ኢትዮጵያ (ሱዳንን ጨምሮ) ነበሩ።

በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሰችው ኢትዮጵያ ግን፥ ዛሬ አነስ ብላ ብትታይም፥ አያሌ አፍሪካውያን ብሔረሰቦችን የምታጠቃልል፥ ያቺው ድሮ አንድ ታላቅ አገር የነበረችዋ፥ ዛሬ ተቆራርሳ ትንሽ የሆነችዋም ናት።

በመጽሐፍ ቅዱስ ኢትዮጵያ የሚለው ቃል የሚያመለክተው የአሁኗን ኢትዮጵያ እንደማያጠቃልል አድርገው የሚያወሩ አሉ። በጥንት ጊዜ የነበረው የጂኦግራፊ ክልል በአሁኑ ጊዜ ካለው የተለየ መሆኑ ግልጽ ነው።

ስለ ሰሳራ የአየር ጠባይ መለወጥና ስለ አፍሪካውያን ከበረሃማው ሰፍራ ወደ አባይና የኢትዮጵያ ከፍተኛ ሥፍራዎች መሰደድ፤ ከአየር መለዋወጥና የሕዝቦች ስደት በመነሳት፥ ሰዎች ከየት ተነስተው ወዴት እንደሄዱ፥ በየትኛው የጂኦግራፊ ክልል ተወስነው እንደቀሩ መገመት ይቻላል (ይህንን “ከምድራዊነታችን ባሻገር” - በሦስተኛው መጽሐፍ ይመለከቷል)።

ከኖህ ዘመን በፊት ጀምሮ ከፍተኛ ሥልጣኔ የነበራቸው፥ ከኖህ ዘመን በኋላ የአየር ጠባይ ሲለወጥና እጅግ ሞቃት ሲሆንባቸው ወደ ሰሜንና ምስራቅ አፍሪካ

ተሰደው ከዛ የኖሩ ብሔረሰቦች በሙሉ ኢትዮጵያውያን በመባል፥ ከፍተኛ የሥልጣኔ እድገት ያሳዩ መሆናቸውን ከታሪካዊ መረጃዎች ጋር ማመሳከር ይቻላል።

ሰሃራ በረሃ ሲሆንባቸው ተሰደው የሚሄዱት ውሃ ከዓመት ዓመት ወደሚፈስበት፥ እንዲሁም ቀዝቀዝ ወደሚለው ተራራማ ሥፍራ መሆን አለበት። ይህም ሥፍራ ሊሆን የሚችለው የነጭ እና የጥቁር አባይ ወንዞች ከሚመነጩበት ጀምሮ፥ የሚፈሱበትን ምድር ሁሉ ተከትሎ፥ እስከሚጠልቁበት ባህር ድረስ መሆን አለበት።

በተጠቀሱት ሥፍራዎች አካባቢ ኢትዮጵያና ግብጽ በጥንታዊ ባለ ታሪክነት ይታወቃሉ። በጥንታዊት ኢትዮጵያ የሚኖሩ ሕዝቦች ወንዝ ተከትለው ከትመዋል፤ በአለም የታወቀ መንግሥታዊ አስተዳደር መሥርተዋል፤ ከልዩ ልዩ አህጉራት ጋር የንግድ ልውውጥ አድርገዋል፤ በሥልጣኔም ታዋቂ ሆነዋል።

ይህንን የከፍተኛ የአባይ ወንዝ ክልል የተባለውን አካባቢ በበለጠ የሚገልጠው ኩሽ የተባለው ቃል ሳይሆን ኢትዮጵያ የተባለው ነው። ኩሽ የተባለው ቃል የኢትዮጵያን አገሩን ሳይሆን ሕዝቡን ነው የሚገልጸው። የሰውን ዘር እና ጂኦግራፊን ለያይቶ ማስቀመጥ ይገባል።

መጽሐፍ ቅዱስ - ኢትዮጵያ የሚለው ቃል የጂኦግራፊ አካባቢን ሲያመለክት፡ - ዘፍ. 2፡13፥ 2ኛ ነገሥት 19፡9፥ አስ. 1፡1፥ አስ. 8፡9፥ ኢዮ. 28፡19...። ኩሽ በሚለው ቃል ደግሞ፥ ዘርን ሲያመለክት፥ "ኩሽም ናምሩድን ወለደ.." ዘፍ. 10፡8 በማለት ይለየዋል።

አንዳንድ ሰባኪያን እንዲህ ለየብቻ የተቀመጡትን ሁለት ስሞች ካላግባቡ ይጠቀሙባቸዋል።

ኢትዮጵያ (ኤርትራንም፥ ሱዳንንም ጨምሮ) ድሮ የነበረች፥ አሁንም ያለች፤ መንፈሳዊ ታሪካችንም ከጥቁር አፍሪካውያን መንፈሳዊ ታሪክ ጋር የሚዛመድ ነው።

ከፍጥረት ጀምሮ እስከ ሙሴ ድረስ፥ ከሙሴ ጀምሮ እስከ ዳዊት ድረስ፥ ከዳዊት ጀምሮ እስከ ክርስቶስ ዘመንና ከዛም በኋላ፥ እንደ እስራኤል የኢትዮጵያም ስም የተጠራ መሆኑ፥ ኢትዮጵያውያን (ጥቁር አፍሪካውያን ሁሉ) - ሁላችንም የእግዚአብሔር ሕዝቦች መሆናችንን ያመለክታል።

ከጥንት ጀምሮ መንፈሳዊ ታዋቂነት ያገኘች ይህች አገርም ለጥቁር ሕዝቦች መመኪያ መሆኗን ታቦተ ሕጉን በአካል የሚታቀፉ ቤተ ክርስቲያኖቿ ይመሰክራሉ።

አንድ አገር እና ሕዝቦቿ ጭልጥ ብለው በመንፈሳዊነት ይጓዛሉ፤ የሚጓዙበትንም ሥፍራ ምድራዊነት አያሳያቸውም። ወይንም፥ ምድራዊት ኢትዮጵያ ሰማያዊ - ናትና፥ እርሷን በምድራዊ ቋንቋ ለመግለጽ ስንሞክር፥ የመንፈሳዊ ጉዞአችንን ታሪክም ስናወራ፥ ምድራዊ አመለካከትን እየደመሰስን (አለዚያም ወደ ኋላ እያስቀረን) ካልሆነ አይሳካልንም። እንዴት ነው ምድራዊነታችንን ከመንፈሳዊነታችን ጋር ማጣጣም የምንችለው?

ፍትሐ ነገሥት የተባለውንም መጽሐፍ በደፈናው ስንመለከተው፥ የምድራዊነትና ሰማያዊነትን ተጻራሪነት ለማስታረቅ የሚሞክር ነው የሚመስለው። ኢትዮጵያ ክርስትናን ከመቀበሏ በፊት የምትስተዳደርበት መንግሥታዊና መንፈሳዊ ሕግጋት መመሪያ በብሉይ ኪዳን ላይ የጸና ነበረ። የክርስትናን ሃይማኖት ከተቀበለች በኋላም፥ እስከ አስራ አራተኛው ክፍለ ዘመን ድረስ በጽሑፍ ረቆ የተቀመጠ፥ በክርስቲያን ሃይማኖት ላይ የተመሠረተ መንግሥታዊና መንፈሳዊ መመሪያ አልነበራትም።

ይህ ጉዳይ በወቅቱ (በ14ኛው ክፍለ ዘመን) የነበረውን ንጉሥ ዘርዓ ያዕቆብን እጅግ እያሳሰበው ቆይቶ ሳለ፥ ለክርስቲያኖች መገልገያ እንዲሆን የተዘጋጀ የምድራዊነትና የመንፈሳዊነት መመሪያ ጽሑፍ መኖሩን እንደሰማ፥ ይህ ጽሑፍ (ፍትሐ ነገሥት) ከአረብኛ ወደ ግዕዝ በአስቸኳይ እንዲተረጎም አደረገ። በኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት ተረቆ በሥራ ላይ እስከዋለበት እስከ 1948 ዓ.ም. ድረስ፥ ፍትሐ ነገሥት በኢትዮጵያ ውስጥ ሥጋዊና መንፈሳዊ መመሪያ ሆኗል። ከዛም በኋላ ቢሆን መሠረታዊ ግልጋሎቱ አልተቋረጠም።

ሥጋዊ ሰው ከመንፈሱ ጋር በሁለትነት የሚኖር ሆኖ ሳለ፤ ምድራዊነቱንና መንፈሳዊነቱን አንድ ላይ የሚያገናኝ ፍልስፍና፤ ከዚህም ፍልስፍና የሚመነጭ ስነ ስርዓት እና ሕግ እንዴት ይገኝለታል?

ሰማያዊ መሰል ምድራዊ ወይም ምድራዊ መሰል ሰማያዊ ሕይወት ውስጥ ለምንኖር ሰዎች ምን አይነት ሕግ ነው የሚስማማን?

በእርግጥ ሰው ሁሉ መንፈሳዊ ስላልሆነ፥ ለብዙሐኑ ማስተዳደሪያ የሚጠቅም ሕግ መኖር አለበት። ግን ሙሴን፥ ሳሙኤልን እና ሌሎችም መንፈሳውያን መምራት ያስቸገራቸውን ሕዝብ በጥቅሉ ለማስተዳደር የሚጠቅም ሕግ ከሕግነቱ አልፎ የሰውን ልጅ ውስጣዊ ተፈጥሮአዊ ጠባይ ሊለውጠው አይችልም።

ክርስቶስ ስለ ፍጹምነት (ሰማያዊ ስለ መሆን) አስተማረን እንጂ፥ በሰዎች ምድራዊ አኗኗር ላይ ጊዜውን አላጠፋም። እርሱ የደቀ መዛሙርቱን እግር አጠበ፤ እርሱ "ቀኝ ጉንጭህን ለመታህ ግራ ጉንጭህን ስጠው " ብሎ አስተማረ። ይህ እንዲህ ያለው

ትምህርት ለምድራውያን ይከብዳል። የእኛም ስነአይምሮአዊ እድገት ለዚህ የደረሰ አይመስልም።

ክርስቶስ የተወሰኑ ሰዎችን ክርስቶሳዊ ለማድረግ፤ በእነኚህም ሰዎች አማካኝነት፥ የአለም ሕዝብ ክርስቶሳዊ እንዲሆን ለማድረግ ሲል ከሁለት ሺህ ዓመታት በፊት መጣ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ብዙ ሰዎች ክርስቲያን ቢሆኑም፥ የክርስቶስን ትምህርት በተግባር በመተርጎም ክርስቶሳዊ መሆን አስቸጋሪ እየሆነ፥ በምድር ላይ ሰላምና ፍቅርን ማምጣት አስቸግሯል። ይህ ሁሉ ከሰዎች አለመብቃት፥ ከምድርም ክፋት የተነሳ ቢሆንም፥ ይህንን ሁኔታ ፍትሐ ነገሥት ሊያስታርቀው (ሊያርቀው) አይችልም። ታዲያ፥ የሥጋ ነገር ካላበቃ ሰው ሥጋዊ ሆኖ መንፈሳዊነትንም አጣምሮ መኖር የሚችለው በእንዴት አይነት መንገድ እንደሆነ ግራ ያጋባል።

አብዛኛው የአለም ሕዝብ በቀጥታ ክርስቶሳዊ መሆን የሚችልበት ደረጃ ላይ ቢደርስ ኖሮ፥ ይህች አለም አንድ ትልቅ ገዳም ትሆን ነበር። በውስጧም የሚኖር የማስተዳደሪያ ደንብም የገዳም አይነት ይሆን ነበር። ካልሆነም፥ የሚከተሉትን ጥያቀዎች ያስከትላል።

የሰው ሃይማኖቱ:-

1ኛ) ሥጋዊ ኑሮውን ለማሻሻል ብቻ ነው ወይ?

2ኛ) ለምድራዊነቱም ለመንፈሳዊነቱም ነው ወይ?

3ኛ) መጪውን ዘላለማዊነቱን በምድር በሚኖረው ኑሮ እየተለማመደ፥ ለፍጹማዊነትም የበቃ እንዲሆን ነው ወይ?

ማንኛውንም የጋራ ሃይማኖት፥ ከግል እምነት ጋር እያስተያዩ፥ ከተጠቀሱት ሦስት ጥያቄዎች ጋር ማገናዘብ ይቻላል።

ሰዎች እራሳቸውን ዝቅ አድርገው፥ ሃይማኖታቸውን የጋራ፥ እምነታቸውንም የግል አስመስለው (አድርገው) እርስ በርስ ስምም ሆነው በሰላም ሲኖሩ፥ የልባቸው ቅንነት ወደሚመራቸው ይሄዳሉ።

እንከን በበዛበት ምድር ውስጥ ለምን እንከን ተገኘ ብሎ የሚጮህ አክራሪ ነው። በመጨረሻ የሚያቸንፈው እውነት መሆኑን አምኖ በግንዛቤአዊ አመለካከት የሚታገስ ግን ጊዜውን በከንቱ የማያጠፋ ብልህ ነው። በውሸቶች መካከልም እውነት የሚገለጽላቸው ሰዎች ብጹአን ናቸው።

የሃይማኖት ግልጋሎቱ ለምድራዊነት ከሆነ፥ መንፈሳዊ ግብም ከሌለው፥ መመጻደቂያ እንጂ፥ እውነተኛነት የሌለው ውዳሴ ከንቱ ነው የሚሆን።

ቤተ ክርስቲያን ሥጋዊነትን ማደንዣ መንፈሳዊነትን ማጎልመሻ ናት፤ ግን የሰው ተፈጥሮ የተለያየ እንደመሆኑ መጠን፥ መንፈሳዊ እድገቱም የተለያየ ነው። የአንድ ሰው እድገቱ ከህጻንነት ጀምሮ እስከ ሽምግልና ድረስ፥ በተለያየ ምድራዊና ሰማያዊ እውቀት ይከፋፈላል። ከሥጋዊነት ወደ ፍጹም መንፈሳዊነት ለመሸጋገር ብዙ - ብዙ ፈተናዎች ይኖራሉ።

ቤተ ክርስቲያን የሁሉ ናት፤ ነገር ግን በግለሰብ ደረጃ ከሥጋዊነት ወደ መንፈሳዊነት ቀስ በቀስ እየተፈተኑ የሚያድጉ ብዙዎች እንደመሆናቸው መጠን፥ ምድራዊነታቸውን ከደው ለነፍሳቸው ብቻ ያደሩም ይኖራሉ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከጥንት ጀምሮ አንድ ወጥ ናትና፤ የቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪዎች ማህበርተኞቻቸውን በፍቅር ያቅፋሉ፤ ሁሉን እንደየደረጃው፥ ከምድራዊነት ጋር የተዛመደ፥ ባህሉንና ልምዱንም በመንፈሳዊነት ያቀኑለታል (በሰማያዊነት ያድሱለታል) እንጂ አያወድሙበትም።

የሰዎች ሁሉ አንድ ወጥነት በመንፈሳዊነትና ሥጋዊነት የሚካተት እንጂ መንፈሳዊነቱን ከሥጋዊነቱ ለይቶ፥ ይህ ነው ሃይማኖቴ ሥጋዊነት (ምድራዊነት) የሌለበት ማለት ያስቸግራል። ለምሳሌ፥ ኢትዮጵያውያን በአንድነት ክብረ በዓላትን ሲያከብሩ፥ በደስታ ሲጨፍሩ፥ ተሰባስበው ታቦቱን ሲያጅቡ፥ ሁሉም እንደየችሎታው ስሜቱን በተለያየ ዜማ ሲገልጽ -

“እሰይ ስለቴ ሰመረ፥ ለሚካኤልዬ ነግሬው ነበረ። ...አለው አለው ሺ ፈረስ፥ ሚካኤልዬ ሲነግሥ.... ”እየተባለ ሲዜም... እልል ሲባል፥ ጥሩንባ ሲነፋ...፤ ይህ ስሜት ከሰማይ ወደ ምድር፥ ከምድር ወደ ሰማይ የሚመላለስ ይመስላል፤ ሃይማኖት የኑሮ ዘይቤና ባህል ሆኖ፥ ለጥሩነትና ለመንፈሳዊ ኑሮ ሲያገለግል፥ በምድር እየኖሩ ሰማያዊ ደስታን እንደመሸመት ይቆጠራል።

ይህ የኛ መንፈሳዊ ባህል ለሃይማኖታችን ማጠናከሪያ ስለሆነም ነው፥ ከብዙ እንቅፋቶች ሁሉ ባሻገር ዘልቀን ከዚህ የደረስነው። በክርስቲያናዊነታችን በውስጠ ሕሊናችን የሚታሰበን ሁሉ ከእግዚአብሔር ደጅ እንደሚጥለን እያመንን ስንጓዝ፥ የኛ ቀስቃሽ መንፈሳዊ ባህሬአችን እውነቱን ሳያስጨብጠን አይተወንም።

አብዛኛው ሰው ቤተ ክርስቲያን በመሄድ በምድር ሥጋዊ ኑሮው፥ በሰማይም መንፈሳዊ ኑሮው እንዲስተካከልለት ነው የሚፈልግ። ይህንን ማንኛውም ሃይማኖት ሊቃወም አይገባውም፤ እምነት ከግለሰብ ልብ ይመነጫልና። ታዲያ፥ ቤተ ክርስቲያናችን ባንድ በኩል በመንፈስ ስታጠናክረን፥ በሌላ በኩል ደግሞ ለማህበራዊ ኑሮአችን የሚጠቅመንን ባህላችንን ብትጠብቅልን፥ ይህ ጥበቃ ልክ እንደ ግርግዳ ሆኖ

እርኩሰት ከሞላበት አለም ይከላከልልናል። ይህንን መልካም ጥበቃ የሌሎች ሃይማኖት ተከታዮችም አይተው አደነቁ።

ሆኖም፥ ሃይማኖታችን ይህንን ያህል የቆየው በመንፈሳዊ ጎኑ እንጂ በምድራዊ ታሪካዊነቱና ባህሉ ብቻ አይደለም። በግብጽ አገር የሚገኙ መንፈሳዊ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን በእስልምና ሃይማኖት ተጽንኦ ቢደርስባቸውም፥ እነርሱ እንዳልጠፉ፥ እኛንም ከዮዲት ጉዲትና ከግራኝ መሐመድ ወረራ ጠብቆ እዚህ ያደረሰን የመንፈሳዊነታችን ብርታት ነው። ይህም ብርታት የተቀሰቀሰው በሃይማኖታችን ቀናነትና በእምነታችንም ጽናት ነው እንጂ፥ በሌላ - በምድራዊነታችን አይደለም።

አሁንም ሃይማኖታችንን ፈረንጅ አገር ያመጣው፥ ከዚያም ሥፍራም ብዙ እንዲቆይና እንዲያድግ - እንዲስፋፋ፥ ታቦቱንም በአለም ዙሪያ እንዲዞር የሚያደርግ ይኸው ኦርቶዶክሳዊ መንፈሳዊ ጥንካሬአችን ነው።

በድሮ ጊዜ የሰዎች ሃይማኖትና ኑሮ (ባህላቸውም) የተያያዘ መሆኑን ከታሪክ እንረዳለን። ርቀትና ቅርበት የማይመለከተው መንፈስ፥ በሕብረተሰብ ውስጥ የነገሠበት፥ የሰው ኑሮው በብዛት ሰማያዊ የሆነበት ጊዜ ነበር። ታዲያ ባሁኑም ጊዜ እንዲሁ - የሰው ልጅ ሃይማኖቱና ባህሉ ባንድነት ተጣምረው ኑሮውን የሚያዘልቁለት ቢሆን መልካም ነበር። ነገር ግን እንዲህ አይነቱ አኗኗር፥ ፍቅረ ነዋይ እና ሌሎችም የምድራዊነት ስሜቶች እየተባባሱ በመጡበት ባሁኑ ዘመን እጅግ አስቸጋሪ ሆኗል።

በቀድሞ የኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የሕዝቦች ኑሮ ከምድራዊነቱ የበለጠ መንፈሳዊው ያመዘነ ስለነበረ ይሆናል ጠንካራ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ውሕደትን ያገኙ። የድሮውን ሳንለቅ፥ የዛሬው ባህላችንን ከዛሬው መንፈሳዊነታችን ጋር ለማጣጣም ስንታገል ነው እንቅፋት የበዛብን።

ሰው እውነትን ፍለጋ ደከመ፤ ደግሞም በብዛት ያደከመው፥ እውነትን ለመፈለግ ሲሯሯጥ እርስ በርስ መጋጨቱ ነው። በሃይማኖት ክርክር አንዱ ሌላውን በጉልበቱ ጥሎ ስለማያሸንፈው፥ ታጋዮች ሁሉ እርስ በርስ እየተሻሹ የመንፈስ ሰውነታቸው ዛለ፤ በሃሳብ ድካምም ደነዘዙ።

የክርስቶስ ተከታዮች ሲበዙለት ልዩነትም በዛ። በተለይ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ላይ ትችት የበዛው - የኛ ሃይማኖት በኦሪቱ ላይ የተመሠረተ በመሆኑ፤ መሠረታዊ ሃይማኖታችን የኦሪቱን እየተከተለ፥ ከወንጌሉ ቃል የራቅን ስለሚመስል ይሆናል። ግን አይደለም። ክርስቲያኖች መባላችን - ወንጌል በብሉይ ላይ ሙሉ ሥልጣን ያላት መሆኑን አምነን ነው። ለኦሪትና ለወንጌል የምንሰጠውን ሚዛንና መጠን በደንብ ለይተን የምናውቅ መሆናችንን ያላወቁ ናቸው ትችት የሚያበዙብን። ግን በአገራችንም ሆነ በውጪ አገር የኢትዮጵያውያን መንፈሳዊ

አንድነት እና እድገት እጅግ ከፍ ከፍ እንዲል የምታደርግ ቤተ ክርስቲያናችን ካለችልን ካለማቋረጥ እየተማርን መንፈሳዊ ጉዞአችንን እንቀጥላለን።

አንዳንድ በምናደርጋቸው ድርጊቶች ግራ የሚጋቡና የሚሰናከሉ አሉ። ስላልታወቀ ነው እንጂ ሁሉም ረቂቅ ፍቺ አለው። ለምሳሌ -

"የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ክርስቲያኖች በቤተ ክርስቲያን ስርዓት መሠረት ወንጌሉ ተነበ ሲያበቃ፤ ቆሱም ሆነ ዲያቆኑ እየዞረ ወንጌሉን ያሳልማል። ይህም ማለት የተነበበውን ቃል ተቀብዬዋለሁ፤ ሕጉን ትዕዛዙን ለመፈጸም ቃል ገብቻለሁ ማለት ነው።" አባ ኤልያስ፥ ሊቀ ጳጳስ፥ 2009

እስቲ የሩቁን ወደፊት እናስበው፤ የትላንትናውና የዛሬውን ወንጌል መሳለም ከወደፊቱም ጋር እያመሳሰልን። ከዚህ ቀጠል በማድረግ ጳጳሱ እንዲህ ብለዋል - "በመጨረሻው ዘመን የትምህርተ ወንጌል ሕግ በረቂቃን መላእክት የሕግ አስከባሪነት ይከበራል፤ እውነት ወይንስ ውሸት በሚል ከባድ ጥያቄ እያፋጠጡ።" ታዲያ እኛ ዛሬ ወንጌሉን ስንሳለም ለወደፊት ለምንጠየቀው ጥያቄ ካሁኑ መልሱን መስጠታችን መሆኑ እኮ ነው።

ሰዎች በከንቱ ይንጫጫሉ፤ ኃይል የእግዚአብሐር ብቻ መሆኑን ይስታሉ። መላእክትም በሰማይ ይሠራሉ፤ ሰውን ለመርዳት ይሯሯጣሉ። ጻድቃንም በመንፈስ ህያዋን ሆነው ይኖራሉ፤ ለቋሚዎች ሥጋዊ ደህንነት እና መንፈሳዊ ድኅነት ይጸልያሉ።

ጻድቃንና ቅዱሳን ማህበርተኞቻችን በሞት ቢለዩንም፥ መንፈሶቻቸው ምን ጊዜም ከኛ እንደማይለይ አድርገን ነው የምንቆጥረው። መንፈስ ከአካል ሲለይ፥ የጻድቅ ሞቱ ክብሩ ነው እንደምንል ሁሉ፥ የነርሱ ሃይማኖት ሃይማኖታችን፤ የነርሱም እምነት እምነታችን ነው እንላለን። ማህበራችን አንድ ነው፤ መንፈሶቻችንም የተሳሰሩ በመሆናቸው አይለያዩም። በውስጣችን ያለ የግል የሆነ እምነታችን ምንጊዜም የኛ ሆኖ ይቀራል።

ሃይማኖታችን ወዶም ሆነ ሳይወድ (በማወቅም ሆለ ባለማወቅ) ከዚህ ደርሷል። ከበላይ ሆኖ ሁሉን በሚያይ በፈጣሪ አምላካችን ፈቃድ እንጂ፥ ለኛ የሚጠቅመን ሃይማኖት ይህ ነው ብለን እኛ ሃይማኖታችንን አልመረጥንም።

ከጥንት ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ፥ ኢትዮጵያውያን በጥምቀት እለት ታቦቶችን ከየቤተ ክርስቲያናት ይዘው ከሜዳ ሲያድሩ፤ በሃይማኖታቸው ያልጸኑ፥ ዘመናይ የሚመስሉ ኢትዮጵያውያን ታቦቱን ተከትለው ከሜዳ አላደሩም ነበር። እነርሱም ይህንን የጥንት ሃይማኖት - ግማሽ የአይሁድ ግማሽ የክርስቲያን የመሰለ፥ ከሃይማኖቱ ባህሉ ያመዘነበት ነው በማለት መንፈሳቸውን ከቤተ ክርስቲያናቸው አርቀውት ነበር።

አሁን አሁን ግን ከስደት በኋላ፥ እነኚሁ ዘመናውያን የሚመስሉ ኢትዮጵያውያን (የተማሩ ሳይንቲስቶች፥ መሃንዲሶች፥ ዶክተሮች..ወዘተ..) ይህንን በኢትዮጵያ ምድር እንጂ ሌላ ቦታ የማይታይ ታቦት በአለም ዙሪያ ሁሉ በክብር እንዲታይ አደረጉት። ፈለጉት - ፈለጋቸው። ከሕዝቦች መካከል እግዚአብሔር የቃል ኪዳኑን ምልክት የሚሸከሙትን ይመርጣል።

የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታቦት በዘመነ አሪት በአካል ተገኘ። ከዛ በኋላ ጠፋ (አክሱም ተቀመጠ)።

ከብዙ ጊዜ በኋላ ድንግል ማርያም እናታችን ተወለደች፤ ክርስቶስም ከርሷ ተወለደ፤ እንደ እኛ ሰው ሆኖ በአካል ተመላለሰ።

"በዚያ ዘመን፦ የእግዚአብሔር የቃል የኪዳን ታቦት ብለው ከእንግዲህ አይጠሩም፤ ልብ አያደርጉትም፤ አያስቡትምም፤ አይሹቱምም.. " ኤር. 3፡ 16 የሚለው፥ ይህንንም ዘመን የሚያመለክት ቢሆን፥ ኢትዮጵያውያን ግን ታቦተ ሕጉን በአለም ዙሪያ ሁሉ በክብር እንዲታይ አደረጉት። ይገርማል፤ ከዚህ የሚከተለውን ማን ያውቃል?

"በሰማይም ያለው የእግዚአብሔር መቅደስ ተከፈተ፥ የኪዳኑም ታቦት በመቅደሱ ታየ፥.. " ዮሐ. ራዕይ 11፡ 19

በአካላዊ አለም ውስጥ ስንኖር ለኛ በመንፈስ ከሚታየን ሌላ በአካልም ከመካከላችን ሆኖ ያሰባሰበንን ታቦት ሁላችንም እያከበርን፥ ለክርስቲያንነታችን ማጠናከሪያ እናደርገዋለን፤ ለምድራዊ ክብር እና ለመመጻደቂያ ሳይሆን።

የተዋሕዶ ኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ቤተ ክርስቲያን ሄደው ድንጋዩን፥ አጥሩንና መሬቱን ይስማሉ። አንዳንድ የሌሎች ሃይማኖት ተከታዮችም ከሩቅ ሆነው እንዲህ ይላሉ፦ "እስቲ ተመልከቷቸው እነኚያን አላማኞች፥ እንደ አሕዛብ ጣኦተ አምልኮትን ሲያከናውኑ።"

ምዕመን ወደ እግዚአብሔር ቤት በሄዱ ጊዜ፥ ለእግዚአብሔር መንፈስ ማደሪያነት ምሳሌ የሆነውን ታቦት በማክበር፥ ሥጋቸውን ጣል፥ ምድራዊ ክብራቸውንም ዝቅ አድርገው፥ ከመሬት ላይ ተደፍተው፥ መሬቱንም ሳም አድርገው - " የፈጠርከኝ ቸሩ አምላክ እግዚአብሔር ሆይ! እኔ ባንተ አምኘለሁና ላንተ እሰግዳለሁ፥ እያሉ ይጸለያሉ።"

"… ራሳቸውንም አዘነበሉ፤ በግንባራቸውም ተደፍተው ለእግዚአብሔር ሰገዱ.." ነህሚያ 9፡8 እንዲል፥ እነርሱም በቃላት በማይገለጽ መንፈሳዊ ንግግር

ከፈጣሪ አምላካቸው ጋር ተነጋግረው፥ ከተደፉበት መሬትም በእውነት የመንፈስ ሰው እንደሆኑ (እየመሰላቸው) ቀና ብለው ይቆማሉ።

ቁም ነገሩ ያለው ሥጋን ጣል አድርጎ በመንፈስ ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገሩ ላይ ነው እንጂ፥ ድንጋይ በመሳምና ባለመሳም ላይ አይደለም። ለፈጣሪአችን የአምልኮት ስግደት እንሰግዳለን፤ ለእግዚእትነ ማርያም የጸጋ ስግደት እንሰግዳለን፤ ለጻድቃን፥ እንዲሁም ለማንኛውም ለምናከብረው ሰው ሁሉ የአክብሮት ስግደት እንሰግዳለን።

"እግዚአብሔር አምላኩ የሚሆንለት ሕዝብ ምስጉን ነው።" መዝ. 33፡ 12

የሰውን ድክመቱን ከሃይማኖቱ እየለየን፤ ትኩረታችን በሰው የእምነት ጽናት ላይ ቢሆን ይሻላል። አቅጣጫችን አንድ ነው፤ የወንጌሉን ቃል በመከተል፥ ከፊት ለፊታችን የክርስቶስን መስቀል እየተመለከትን ነው የምንጓዘው። ስለዚህ መንገዳችን ጠማማ ሊሆን አይችልም።

"እመቤታችን ከተወደደው ልጇ ጋር ሁና፥ ጻዲቁ ዮሴፍና ሰሎሜም በስደታቸው ወራት በግብጽ አገር አድርገው ወደ ኢትዮጵያ ከገቡ በኋላ በደብረ ቢዘን ለጥቂት ወራት ተቀመጡ።" ተአምረ ማርያም ገጽ 150 ከዚያም ታቦተ ሕጉ ወደ ተቀመጠበት ወደ አክሱም ሄዱ። ከዚያም ወደ ጣና ደሴት ሄዱ። ከዚያም በደመና ላይ አሳርጎ የኢትዮጵያን ጠቅላላ ክፍለ አገር አሳያት።

"እናቴ ማርያም ሆይ ስሚኝ፤ ሕጻናትን ካስፈጀ ከሄሮድስ ፍርሃት የተነሳ ከአገርሽ ከኢየሩሳሌም ወጥተሽ ወደ ግብጽና ወደ ኢትዮጵያ ተሰደሽ ስቃይና ችግር ከኔ ጋር በደረሰብሽ ፈንታ የኢትዮጵያን አውራጃዎች በሙሉ ዓሥራት ይሆኑልሽ ዘንድ ሰጥቼሻለሁ።" ተአምረ ማርያም ገጽ 160

እንግዲህ ማነው(ነች) ኢትዮጵያዊ(ት) ክርስቶስን የወለደች ማርያም የመንፈስ እናቱ(ቷ) የማትሆንለት (ላት)? ሃይማኖት የጋራ ነው፤ እምነት የግል ነው።

ሰማይ ዙፋኑ፥ ምድር የእግሩ መርገጫ፤ የሰው ልጅ በምድር ሳይፈጠር በፊት፥ የሰማይ መላእክት እስኪንጫጩ ድረስ ርቅቅ ብሎ የጠፋባቸው፤ እራሱን ማተለቅና ማሳነስ፥ በሁለቱ መካከልም አካላዊ ሆኖ መገኘት የሚቻለው፤ ሲፈልግ የሚገዝፍ፥ ሲፈልግ የሚረቅ፤ ሲፈልግ እንደ እሳት፥ ሲፈልግ እንደ እርግብ መሆን የሚችል፤ አካላዊ ሆኖ፥ በጠባብ ደረት ተወስኖ፥ በሰዎች መካከል የሚመላለስ፤ ከጻድቃንና ከቅዱሳን ጋር እየሆነ፥ አካላዊ ትርጉም የማይገኝለትን ተአምራትን የሚሠራ፤ ለሁላችንም የጋራ የሆነ ማእከላዊ እውነት ፈጣሪ አምላካችን ብቻ ነው።

ገደብ የሌለው ትልቅነት እና ገደብ የሌለው ትንሽነት በአካላዊነት አይገኝም። እንደ ሰው ሆኖ መከራን የተቀበለ፤ የሞተ፤ የተቀበረ፤ እንደገናም ኅላ ብሎ የታየ፤

ቀጥሎም ወደ ሰማይ ያረገ ክርስቶስ ነው። ሁሉን መሆን፥ ሁሉን ማድረግ በሚችል በአንድ እግዚአብሔር (በሥላሴዎች) እናምናለን።

እንደኛው አካላዊ ሆና፥ ለማህደረ መለኮትነት የተመረጠች ይህች ክብርት - ቅድስት ድንግል ማርያም፤ ለኛ እመቤታችን ናት። ከምትወደው፥ ከሚወዳት ልጇ ታማልደናለች፤ መላእክትም ሆኑ ቅዱሳን ያማልዱናል ብለን እናምናለን።

መላእክት ፍጹም መንፈሳውያን (ሰማያውያን) ሲሆኑ፤ ጻድቃን እና ቅዱሳን ሰዎች ደግሞ፥ በምድር በኖሩበት ዘመን ዝንባሌአቸው ከምድራዊነት ወደ መንፈሳዊነት (ሰማያዊነት) ያመዝናል። ስለዚህ የጻድቃን ምድባቸው ከመላእክት ነው። በአካል ባይገኙም (ቢሞቱም) “በሌላ ሥፍራ - በሰማይ” በሕያውነት የሚኖሩ ስለመሆናቸው እናምናለን።

ሕያውነት ማለት በአካላዊነት መታየት ነው እንጂ፥ ሌላ ሊሆን አይችልም የሚሉ በሙታንም መነሳት የማያምኑ ናቸው። እኛ ግን ሕያውነት ማለት በአካላዊነት ከመታየት ባሻገር፥ ርቅቅ ባለ ሰማያዊነት የሚከሰትም ነው እንላለን።

“ለእኔ ሕይወት ክርስቶስ ነው፤ ሞትም ጥቅም ነውና፤...” ወደ ፊሊጲስዩስ 1፡ 21 የፈጠረን እግዚአብሔር ነው፤ የሚያሳድገንም እርሱ ነው። ከዘመነ ፍዳ ወደ ዘመነ ምህረት ተሸጋግረን እዚህ ደረስን። በሥጋዊ አፈጣጠራችን ውሱኖች ስለሆንን በምድራዊነታችን እንዳንቸገር፤ በመንፈሳዊ አፈጣጠራችንም በክርስቶስ እንኖር ዘንድ ይህ ነው ሃይማኖታችን። ሰዎች ከዋና ዋና የእምነት ምሰሶዎች (ዶግማዎች) በተጨማሪ የሚሰካኳቸው ፍሬ ሃሳቦች ቢኖሩም፥ ከሁሉም በላይ የመሠረታዊ ሃይማኖታችንን ምንጭ (ዘዳ. 4፡ 39፤ ዘዳ. 6፡ 4=8፤ ኢፌ፥ 4፡8፤ ዮሐ. 3፡ 5 እና 16፤ ፊሊ. 2፡ 10፤ 1ኝ ቆሮ. 15፡4፤ ማር. 16፡ 16፤ ዮሐ 6፡ 27 - መጨረሻ፥ ወ.ዘ.ተ..) ማስተዋል ይገባል።

“እንግዲህ የሰማዩ አባታችሁ ፍጹም እንደሆነ፥ እናንተ ፍጹማን ሁኑ።” ማቴ. 5፡ 48 ሲል፥ እያንዳንዱን ሰው ፍጹም የሚያደርገውን ነገር የጋራ በሆነ ሃይማኖታዊ ሕግጋት (ቀኖና) ማካተት አይቻልም። እንደ መንፈሳዊ መመሪያ ሆኖ የሚቀርበውን ሁሉ እንደ መጽደቂያ መውሰድ አይገባም።

በሰው የተሞከረው ሁሉ ወደ መጨረሻው ተቃርቧል። ካሁን በኋላ ምንም ቢደረግ የሃይማኖትን ዶግማውን ቀርቶ ቀኖናውን እንኳን መለወጥ አይቻልም። ከሁሉም በላይ የራስን ሃይማኖት አጥብቆ መያዝና ጽድቅን እየሠሩ መጪውን እየተጠባበቁ መኖር ነው ደጉ።

“እነሆ ፈጥኜ እመጣለሁ፤ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው እከፍል ዘንድ፥ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ። አልፋና ኦሜጋ ቀዳማዊና ደኃራዊ መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ” ዮሐ. ራዕይ 22፡ 12- 13

ሕብረተሰብ - አገር - ሕዝብ - ካለበት ሁሉ የእግዚአብሔርም መንፈስ ይኖራል። ህንዶችም የእግዚአብሔር መንፈስ ወደአገራቸው እንደገባ በቅዱስ መጽሐፎቻቸው በክብር ስላስቀመጡ፥ እንዲህ ይላሉ - "የእግዚአብሔር መንፈስ በእውነት ወደእኛ መጥቷል፤ ሰውን ብቻ ሳይሆን፥ እንስሳቱን፥ ጫካውን፥ ወንዙን ሳር ቅጠሉን ሁሉ ባርኮልናል....።"

በኢትዮጵያም የእግዚአብሔር መንፈስ እንደገባ፥ የሰው ልጅ ባፉ ባይናገር ታቦቶቻችን ይመሰክራሉ። እጅግ የሚያሳዝነው ግን እኛ አካላዊ በሆነው በምድራዊ ኑሮአችን ላይ አተኮርንና፥ የኢትዮጵያችንን ታሪክ ስንጽፍ በብዛት የኢትዮጵያን ምድራዊ ኑሮ በሚያንጸባርቀው ላይ ሆነ። እስራኤሎች - የሰው ልጅ መከራ ቢጸናበት ለምክንያት መሆኑን፥ ከመከራው የማይማር ከሆነ ደግሞ የባሰ ቅጣት እንደሚቀጣ፥ ቁልጭ አድርጎ በሚያሳየው ታሪካቸው ላይ የመንፈሳዊነታቸውን ነገር በሚገባ ስላስቀመጡልን፥ እኛ ከነርሱ ተማርን። እኛ ከኛ የተማርነው ምንድነው?

በታሪካችን ትንሽ ወደኋላ መለስ ብለን፥ ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጀምረን፥ እስካሁን ድረስ የነበረውን ታሪካችንን ከመንፈሳዊነታችን አንጻር ብንመረምር፥ በእውነት እግዚአብሔር ጣልቃ እየገባ እንዳስተማረን፤ እኛ ኢትዮጵያኖች መከራ ቢጸናብን ለምክንያት መሆኑን፥ ከመከራ የማንማር ከሆነም እንደምንቀጣ መገንዘብ አያቅተንም።

የእግዚአብሔር መንፈስ በኛ ምድራዊ ኑሮ ጣልቃ እየገባ፥ አጥፊውን ቢቀጣ፥ እኛ በራሳችን መቋቋም ያለብንን (የሚገባንን) የምድራዊነታችንን ድርሻ አይወስድብንም፤ በውስጣችን እራስን በራስ ማሻሻል ስለፈጠረልን፥ ጥሩውን ከመጥፎው እየለየን በራሳችን እንድንታገል ትቶናል እንጂ።

አዎ ! እጅግ ሲበዛ በደል፥ የቅዱስ መንፈስን እንቅስቃሴ የሕዝቦች ጩኸት ያባብሰዋል። ይህንን ነው በተደጋጋሚ ያየነው። እስካሁን ድረስ የደርግ መንግሥት ቢገዛ ኖሮ፥ ወይንም ከደርግ በኋላ የአምባገነን መንግሥት ለወደፊት የሚቀጥል ቢሆን ኖሮ ብለን እናስበው እስቲ። በቀን ተቀን የምሬት ጩኸት፥ የመንፈስን ጣልቃ ገብነት ለመመልከት እንችል ዘንድ ባገራችን ብዙ ብዙ መንፈሳዊ ክስተቶች ተፈጽመዋል፤ ይህም ይቀጥላል።

የሕዝቦችን ጩኸትና የመንፈስን ምላሽ ከመንፈሳዊነታችን ታሪክ ጋር በማያያዝ፥ ይህ መጽሐፍ ይህንን ጉዳይ በዝርዝር ለመጻፍ ብቃት ስለማይኖረው ለመንፈሳዊ ታሪክ ተመራማሪዎች እንተወው።

ብዙ ምድራዊነት (ፖለቲካም) የተቀላቀለበት ወሬ እየተወራ እውነቱን ማወቅ አልተቻለም። ስለዚህ እውነት ሁለንተናዊ ሆኖ የሚገለጥበት ጊዜ እስኪመጣ ድረስ የእውነት እውነቱ ለሚገለጥላቸው ብቻ እውነት ሆኖ ይቆያል።

ይህንን በዝርዝሩ ሳይሆን፥ በጥቅሉ ያቀረብነውን የመንፈሳዊነታችንን ማስታወሺያ ታሪክ፥ ማንም ኢትዮጵያዊ (እስላም፥ ካቶሊክ፥ ፕሮቴስታንት፥ አይሁድ ወይም ሌላ) በጥሞና ይመልከቱው። ሁሉም የእናትና ያባቱን መንፈሳዊ ታሪክ አመጣጥ ያጥና። በተለይ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታዮች የአባትና የእናታችንን ሃይማኖት በጥልቀት እንመለከተው። ይህንን ንጹህ ሃይማኖት በጠባቡ ሳንመለከት፥ ሌሎች ሃይማኖቶችን ሁሉ በፍቅር ለማቀፍ እንነሳ።

ፖለቲካ ቢለያየን እግዚአብሔር ያቀራርበናል ብለን፥ ቤተ ክርስቲያንን የመንፈሶቻችን መናኸሪያ ሥፍራ አደረግነው። የፈጣሪያችን ክብሩ ለአሕዛብም ሁሉ ይገልጥ ዘንድ፥ የታቦተ ጽዮን ምሳሌ ከቅድስተ ቅዱሳን እየወጣ በአይን እንዲታይ እናደርጋለን፤ በማህጸኗ ፈጣሪዋን ከታቀፈችው ቅድስት እናታችን ጋር እያመሳሰልን። ኢትዮጵያን የባረካት - ለእናቱ ዓስራት የሰጣት - ከእናቱ ጋር በአካል እንደጎበኛት፥ ተመልሶ ያያት ይሆናል።

እንዲህ የሚያኮራ መንፈሳዊ ታሪክ አለኝ ብሎ የሚመጻደቅ፥ የራሱን ከፍ አድርጎ የሌሎቹን የሚነቅፍ፥ እርሱ ምድራዊ ተመጻዳቂ እንጂ መንፈሳዊ ሊባል አይችልም። የብዙ ሺህ ዓመታት መንፈሳዊ ታሪክ- ይቅር መባባልን፥ ፍቅርን እና አብሮ በሰላም መኖርን በተግባር የሚገልጽ ካልሆነ፥ ምንም ግልጋሎት እንደማይሰጥ፥ ግን በክብር እንደተቀመጠ ባዶ እቃ ይቆጠራል። እንዲህም እንዳይታሰብ፥ እንዲህም እንዳይሆን ሁላችንም በመንፈስ ነቃ ብለን በጎ ምግባርን እንለማመድ።

ኑሮአችን ከጊዜአዊ ምድራዊ ስሜት የሚረቅ፥ መንፈሳዊነታችንም ከምድራዊ ክብር የሚላቀቅ ይሁን።

ማወቃችን ለትህትና እና ለጽድቅ ሥራ እንጂ ለጥፋት (ብሎም ለኃጢአት) እንዳይሆንብን የእግዚአብሔር መንፈስ ይርዳን።

የመንፈሳዊነታችንን ታሪክ የአለም ሕዝቦች እስኪያውቁት ድረስ የማይተወን መንፈሳዊ ክስተት አለ።

የሚታየው ይታየዋል። ይህንን ጉዳይ በስፋት ይመለከቱት ዘንድ ለመንፈሳዊ ታሪክ ተመራማሪዎች እንተወውና፥ የያዝነውን አርእስት በሚከተሉት ሁለት ጥያቀዎች እንደምድም፡-

በአሁኑ ጊዜ ከቤተ ክርስቲያን መሄድን የሚያዘወትሩ የተወሰኑ ሰዎች ናቸው። እግዚአብሔር የሚፈልጋቸው ግን የፈጠራቸውን ሕዝቦችን ሁሉ ነው።

- ለምን ሰውን ሁሉ የሚያቅፍ ቤተ ክርስቲያን አልተሠራም?
- ሁላችንም በእግዚአብሔር መንፈስ ከተፈጠርን፥ ለምን በመንፈስ አንድ አንሆንም?

<u>ካቶሊክ/ኦርቶዶክስ</u>

አንድ ሰው በራሱ አካላዊና መንፈሳዊ ጠባዩ ብቻ ተጠቃሎ እሱነቱ የሚታወቅበትን ለማመልከት ግለሰብ ተባለ። እንዲሁም፥ ብዙ ሰዎች በህብረት፥ በራሳቸው አካላዊና መንፈሳዊ ጠባያቸው ብቻ ተጠቃለው እነሱነታቸውን በጥቅሉ ለማመልከት ሕብረተሰብ ተባለ። የነኚህ የሁለት ቃላት ትርጉም በመሬት ላሉ ሕዝቦች እንጂ ለሰማያዊው አለም ስለማያገለግል፥ በሰማይ የሚኖሩትን ዘለአለማዊ ህያዋን አኗኗር፤ አንድነታቸውን እና ህብረታቸውን አያሳውቀንም። አራት መላእክት መሬት ላይ ቆመው ብናያቸው የአራቱን የብቸኛ ጠባዮቻቸውን እየለየን፥ በምድራዊ አመለካከት እገሌና እገሌ ማለት አንችልም።

ሰማያዊ ክብር ከአንድ ሥፍራ ብቻ ነው የሚመነጨው፤ አመንጪውም እግዚአብሔር ነው። እመቤታችንም ካጠገቡ መኖሯ ጸጋን የተመላች አድርጓታል። እኛም ብንሆን፥ የመጨረሻው አላማችን ይህ ምድራዊ ግለሰብአዊነታችን ተደምስሶ ፍጹም ከሆነው ከእግዚአብሔር ጋር በመንፈስ አንድ ለመሆን ነው። ድንግል ማርያም እንዲሁም መላእክትና ጻድቃን በተናጠልና በግላዊነት የሚያከናውኑት ተግባር አይኖርም። ሁሉም የእግዚአብሔርን ክብር ነው በተለያየ መንገድ የሚያንጸባርቁት።

በምድር መኖራችን፥ እስኪገባን ቆይታችን፤ ምንድነው የጋራ የሆነ ለሁላችን? ምስጉን እግዚአብሔር እርሱ በሚመርጣቸው ሰዎች አማካኝነት ይመሰገናል። ማንም ሰው ክርስቶስን መሆን አይችልም፤ ግን ማንም ሰው የእርሱን ምሳሌ መከተል ይችላል። ክርስቶስ ወደ ምድር መውረዱ፥ ከእርሱ ያለውን ለሚከተሉት (ብሎም ለሰዎች ሁሉ) ሊሰጥና፥ እነርሱም እንዲጠቀሙበት ፈለጎ ነው (የሐዋ. ሥራ ምዕራፍ 2)።

በመጨረሻዎቹ ሰዓታት ክርስቶስ ስለ መንፈሳዊ አንድነት በመጸለዩ ፥ አስራ ሁለቱ ሐዋርያት በመንፈስ ቅዱስ በዙ፤ በዝተውም ተጠናከሩ፤ ተጠናክረውም ከምድር በማይገኝ መንፈሳዊ ፍቅር ሰዎችን አቀራረቡ። ስለዚህ፥ በየመንፈሳዊ ማህበራትና መሪዎቻችን ዙሪያ እየተሰባሰብን የእምነታችን መሠረት የሆነውን ክርስቶስን በልቡናችን ይዘን መቆየታችን፥ ወደ ዘለአለማዊው አንድነት ለመሸጋገር ነው። የሰው አምልኮ

የሌለበት፥ የሃይማኖት መሪ (ፓትሪአርክ፥ ፓፓ፥ ጳጳስ፥....) አስፈላጊነት ምሥጢሩ ይህ ነው።

ክርስቶስን የሚወዱ እናቱንም እንደሚወዷት አንጠራጠርም። ከጉያችን የወጡ ፕሮቴስታንቶች የክርስቶስን ቃል ስለሚናገሩ እንወዳቸዋለን። ግን፥ በክርስቶስ መቀራረብ ሲገባን በአንዳንድ ልዩነቶቻችን ምክንያት መራራቃችን ቅር ያሰኛል።

ከእግዚአብሔር ድንቅ ሥራዎች መካከል ዋነኛው እኛን ሰዎችን ከድንግል ማርያም ተወልዶ ያዳነበት ጥበቡ በመሆኑ፥ ቅድስት ድንግል ማርያም - ወላዲተ አምላክ እንዴት የሁላችን እናት ልትሆንልን ትችላለች ብለን እናስበው። የእርሷ እናትነት በሥጋዊነቷ እንዳልሆነ ሁሉ፥ የክርስቶስ እናት እንደ ሌሎች ሴቶች ማህደረ ሰብ ሆናለች ብለው ሲያስቡት ደስ አይልም። ሲታሰቡ ደስ የማይሉ ሃሳቦች ተያይዘው ተያይዘው መጨረሻቸው የማያምር (ውሸትም) ይሆናሉ። ቅድስት ድንግል ማርያም ማህደረ መለኮት እንጂ ማህደረ መለኮት አይደለችም።

የእመቤታችን ክብር የሰው ሁሉ ክብር ነው። መንፈሳዊ ስሜታችን ከእመቤታችን ጋር የተያያዘ ስለሆነ፥ የርሷ ክብር ሲቀነስ የሁላችንም ክብር ይቀነሳል። ማህደረ መለኮት የሆነች ንጽሒት ድንግል ሴት - ክብሯን ዝቅ አድርጎ፥ እርሷ ተመልሳ ማህደረ ሰብ ሆናለች በማለት፥ ከሌሎች ሴቶች ጋር ሲደምሯት በጣም እናዝናለን። በድንግልና ጸንሳ በድንግልና የወለደች፥ በድንግልና እንዳትቆይ ምን ያግዳታል? እንደ ጥንቱ ባህላዊ ሰው የማያስብ (የዘመኑ ሰው) በድንግልና መቆየቷ ከክብሯ ጋር የተያያዘ መሆኑን አይረዳም።

“እግዚአብሔርም፡- ይህ በር ተዘግቶ ይኖራል እንጂ፥ አይከፈትም፥ ሰውም አይገባበትም፤ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ገብቶበታልና ተዘግቶ ይኖራል።” ሕዝቅኤል 44፡ 2

እግዚአብሔር ለአዳም በገባው ቃል ኪዳን መሠረት፥ እንዲሁም በነቢያት አድሮ እንደተናገረ፥ ጊዜው ሲደርስ፥ በሥጋዊነቷ ፍጽምት ከሆነች ድንግል ማርያም እኛን መሰለ (እግዚአብሔር ከኛ ጋር ሆነ)።

ከመጨረሻው እራት ጀምሮ ሥጋ ወደሙ (ቅዱስ ቁርባን) መቀበል የተቻለው፥ አንድም እንደኛ አካላዊ በሆነች እናታችን አማካኝነት መሆኑ ለሁላችንም ግልጽ ነው። ማርያም እንደኛ ሰው ሆና ግን በመላእክት ዘንድ “ልዩ” ሰማያዊ ክብር በማግኘቷ እጅጉን የምትደነቅ፥ የምትከበርና የምትወደድ ሆነች። ለዮሐንስ እናት ሆና እንደተሰጠች ሁሉ፥ እኛም ቅድስት ድንግል ማርያምን እናታችን አድርገን በመቀበላችን እራሳችንን ከዮሐንስ እና ከክርስቶስ ጋር አዛመድን ማለት ነው።

በሥጋም በነፍስም ንጽሒት ከሆነች ድንግል እናታችን ጋር በመንፈስ አንድነትን መሥርተናል። የእግዚአብሔር ጸጋን የተመላች፥ ከሴቶች ሁሉ ተለይታ የተባረከች እናታችን በልጇ ያገኘችውን ሰማያዊ ክብሯንና ማዕረጓን አረጋገጠችልን (ሃይማኖታችንን አጸናችው፤ ማህበራችንን ባረከችው)። በመንፈስ ታጠናክረናለች፤ በሃይማኖት ታጸናናለች።

ቅድስት ማርያም በልጇ ምክንያት የጠፈር ንግሥት በመሆኗ፥ የኛ የሰብአዊነት - የባህሪአችን ማመሳሰያችንም ስለሆነች እንኮራባታለን፤ እናፈቅራታለንም።

የሁላችን ድኅነት የተገኘው በመስቀሉ ላይ ደሙን ባፈሰሰው በጌታችን እና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ነው። “በእንተ ማርያም መሐረነ ክርስቶስ” ብለን መጸለያችንም፥ ከመስቀሉ ሥር ቆማ ያለቀሰች እናቱን ስንጠራበት፥ በፍጹም ሰውእነቱና በፍጹም መለኮታዊ እሱነቱ የገዛ እናቱን በሙሉ ርህራሄው ሲያስባት፥ እኛንም አብሮ ደምሮ እንዲያስበን በመሻታችን ነው።

በጸሎታችን ቅድስት ማርያም እባክሽ ጸልዩልን (አማልጂን) ብለን የምንለምናት፥ ለእግዚአብሔር በቀጥታ ብንጸልይ እርሱ አይሰማንም ብለን ሳይሆን፥ በጸሎታችን ላይ የማርያም ፍቅርና ርህራሄ እንዲታከልበት ብለን ነው። እርሷም እኛን ስለሆነች፥ ስንጸልይ እርሷም አብራን ትጸልያለች - ስናለቅስ እርሷም አብራን ታለቅሳለች - ስንለምን እርሷም አብራን ትለምናለች። እምዬ ማርያም እንላታለን፤ ፍቅሯን ለመግለጽ ቋንቋ ያጥረናል..።

አንድም፥ ድንግል ማርያም እንድታማልደን ለርሷ መጸለያችን - ማርያም የድኅነታችን ምክንያት፥ የሕይወታችን መንሰላል፤ የቃል ኪዳን - የተስፋችን ምልክት (ቀስተ ዳመናችን) በመሆኗ፥ እና እርሷም ለሚወዳትና ለሚማጸናት ሰው ድኅነት እንደምትጸልይ ስለምናምን ነው።

እኛ በሰማይ የሚኖሩትን ሁሉ ከኛ ጋር በመንፈስ እንደሚኖሩ አድርገን ነው የምንቆጥረው። ባጠገባችን ያለውን ሰው ጸልይልን (ጸልዩልን) እንደምንል ሁሉ፥ ሰማያውያንንም ጨምረን - ማርያምን፥ መላእክትን እና ጻድቃንን ሁሉ እባካችሁ ጸልዩልን ብለን እንለምናቸዋለን። ይህም በምድር እየኖሩ ሰማያዊ ኑሮን መለማመድ ነው።

ከምድራዊ ችግሮች ሁሉ ባሻገር፥ በመንፈሳዊነታችን በሚሰማን ሰማያዊ ፍቅር ደስ እያለን መኖር ስለምንወድ፥ በኛና በእናታችን በማርያም መካከል ምንም አይነት የፍቅር እንቅፋት እንዳይፈጠር እንመኛለን። በእውነት እኛ የማርያም ወዳጆች ስለማርያም ፍቅር የሚሰማንን ሌሎችም አውቀው ከኛ ጋር አንድ ቢሆኑ የበለጠ ደስ ይለናል።

መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው በተለያዩ ዘመናት በምድር ለሚኖሩ ሰዎች እንዲገባቸው ስለሆነ፥ ለኛ ለዘመኑ ሰዎች - ከሳይንስ ድጋፍ ጋር እና በትርጉም ጭምር (ሰምና ወርቁን - የተደበቀውን ምሥጢር ሁሉ እየለዩ) ብዙ- ብዙ ካልተፈላሰፉበት በስተቀር በቀላሉ አይገባም።

ከሰማያዊ አለም የሚመጣ ሁሉ እንደአካል ቁልጭ ብሎ ባለመታየቱ ምክንያት፥ ቶሎ የማይገቡን ጉዳዮች በረከቱ። አንዱን ሃይማኖት ከሌላው በግድ በመለየትና አከራሪ አቋም በመውሰድ ሰዎች የሚከራከሩባቸው ጉዳዮች ሁሉ፥ በአስተያየትና በትርጉም የሚለያዩባቸው ከመሆናቸው በስተቀር፥ በውስጣቸው መሠረታዊ ቅራኔ የላቸውም።

ከመጽሐፍ ቅዱስ አንዳንድ ጥቅሶችን በመቃረም እና፥ እነኛን ጥቅሶች እንደ ብቸኛ እውቀት (እውነት) በመውሰድ እምነትን ከመመሥረት ይልቅ፥ በትንቢት ስለተነገረው የህጻኑ አወላለድ ጀምሮ ስለ እናቱ የተጻፉትን መጻሕፍት ሁሉ ማመሳከርና ወደ እውነተኛው እውነት ለመጠጋት በመሞከር ልዩነቶች ይጠባሉ።

በሳይንስም ሆነ በሃይማኖት ስነአመክኖአዊ አስተሳሰቦች ቀጥ ብለው - ፈር ሳይለቁ (ወዲያ ወዲህ ሳይሉ) መዝለቅ ይገባቸዋል እንጂ፥ የተጻፈውን ብቻ በደረቁ ይዘው አንዴ አንዱን ሌላም ጊዜ ሌላውን ይዘው ሲጓዙ፥ የሃሳብ ግጭት ይፈጠራል። በዚህ አይነት ከብሉይ ኪዳን እስከ አዲስ ኪዳን የተጻፈውን ሁሉ ብንመረምር - በልጇ የከበረች፥ "ጸጋን የተመላሽ" የተባለች የማርያምን ክብር የሚቀንስ ሰብአዊ ኃይል አይኖርም።

የመንፈስ ሥራ እስከዘመናችን እና ለወደፊትም ይቀጥላል (ዮሐ. 14፡ 15 – 17፤ ሉቃ. 1፡ 34። ብርሃን ከጨለማ ጋር ሕብረት የለውምና፤ በሁለት ሃሳብ ማነከስ እንዳይሆን (1ኛ ነገሥት 18፡ 21)፥ ከማያስፈልጉ ሃሳቦች ሁሉ መራቅ - በአንድ ልብ መጽናት ያስፈልጋል (መዝ፡ 118፡ 97። ሚዛናዊ አስተሳሰብና እምነት በጽሑፍ ከቀረበው ባሻገር አልፎ ይሄዳል፤ የእምነት ዝምድና ከማወቅ ጋር ብቻ ሳይሆን በስነአመክንዮ ከመመርመርና በአይነ ሕሊና ከመመልከት ጋርም ነው።

ሐዋርያት እንኳን በጊዜው ሙሉ በሙሉ ያላወቋቸው ጉዳዮች ስለነበሩ እንዲገለጽላቸው ሲሉ ሱባኤ (ለምሳሌ ፍልሰታ...) ይገቡ እንደነበር ልብ ይሏል።

የምናውቀው ሁሉ ካለማወቅ ጋር ቢሆንም፥ የመንፈሳዊ ክስተቶችን ሂደት በማጥናት፥ በራሷ ሳይሆን በማህጸኗ በተጸነሰው ልጇ የከበረች ይህች ሴት ተመልሳ ማህደረ ሰብ እንድትሆን አለመፈጠሯን፥ ሱባኤ ሳይገቡም ልብ በማለት ሊታወቅ ይቻላል። እርሷ ከክርስቶስ ሌላ አልወለደችም፤ ማህደረ መለኮት በመሆን፥ ይህንን ታላቅ ክብሯን ይዛ ቆየች እንጂ።

"እግዘአብሔር ጽዮንን[38] መርጧታልና፥ ማደሪያውም ትሆን ዘንድ ወድዶአታልና..።" መዝ. 131፡ 13

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወንድሞች ነበሩት። ግን፥ "ወንድም" የተባለው ቃል ከእናት ለሚወለድ ብቻ የሚያገለግል አለመሆኑን፤ ይህ ቃል እንደየአገሩ ሕብረተሰብ ከአባት ልጅ እስከ አክስትና ያጎት ልጅ ድረስ ሊያጠቃልል እንደሚችል፤ ማገናዘብ ያን ያህል ከባድ አይሆንም[39]።

የጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስንም ከእግዚአብሔር መንፈስ መወለድ፥ ካመንን፥ "ድንግል ትወልዳለች" የሚለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃልም ጊዜ የማይሽረው መሆኑንም አብሮ መቀበል ያስፈልጋል።

ድንግል ወላዲት አምላክ የሁላችንም እናት መሆኗን በማመን፥ በመካከላችን እንደ ግርግዳ የለያየን ቅራኔ ይፈርሳል።

በቁርአንም እንደተጻፈ፥ የሁላችንም አምላክ አንድ መሆኑ በቂያችን ነው። "..የእናንተ እና የእኛ እግዚአብሔር አንድ ነው...።" ሱራ 29፡ 46

ከሐዋርያት ጀምሮ ክርስቲያኖች የአንጋፋዎቻቸውን ታሪክ መዘገቡ። ስለ ጻድቃንና ቅዱሳን ክርስቲያኖች እድገትና እርምጃዎች በጽሑፍ፥ በመናገርም ሆነ በስዕል ለተቀረው አለም አሳወቁ። በእግዚአብሔር መንፈስ የተንቀሳቀሰውንና አለምን ያዳረሰውን የመንፈስ ቅዱስ ኃይል በተለያየ አይነት መንገድ ስለገለጹ መኖሩ ሊታወቅ ቻለ፤ ሌሎችም ይህንን ተመልክተው አወቁ፤ አመኑ። በቅርብ ጊዜ የተፈጠሩ ሃይማኖቶች ግን፥ ከዚሁ አጠቃላይ ሃይማኖታዊ እውቀት በመነሳት፥ ይህ አያስፈልግም፥ ይህ አይጠቅምም እያሉ የሚስማማቸውን መረጡ፤ ሊቀበሉት የፈለጉትን (የሚችሉትን) በመውሰድ የተቀረውን ጣሉ። ይህንን ማድረግ ለምን እንዳስፈለገ የሚያውቁ እነርሱ ናቸው።

አዳዲስ ሃይማኖቶች አዳዲስ መልኮች፥ ቀለሞችና ዘርፎች ወጡላቸው። ሰዎችም በተለያዩ ሃይማኖቶች እራሳቸውን ማሰለፍ ይቀላቸው ጀመር። ሁሉም ጥሩ ነው።

[38] አንዱ አለም ዳግማዊ (መምህር)፡ 1998፡ ወላዲተ አምላክ በነገረ ድኅነት (ገጽ 261 – 280) ይመልከቱ።

[39] አንዱ አለም ዳግማዊ (መምህር)፡ 1998፡ ወላዲተ አምላክ በነገረ ድኅነት (ገጽ 230 – 242) ይመልከቱ።

<u>እስላም</u>

ኢትዮጵያ ሰላማዊ እስላሞች ስደተኞችን አስተናግዳና ጠብቃ እንዳቆየች ሁሉ፥ የእስልምና ሃይማኖትም ሃይማኖቷ ሆኗል። ስለዚህ፥ የኢትዮጵያውያኖችን መንፈሳዊ ታሪክ፥ በክርስቲያኖች ሃይማኖት ብቻ አጠቃሎ ማስቀመጥ ልክ አይደለም (ወይም በቂ አይደለም)። በሰዎች መካከል ሰላምን፥ ፍቅርን፥ ህብረትና አንድነትን የሚያመጣውን እውነተኛውን - በእስልምና ሃይማኖት በኩል አገራችን የገባውን - የመንፈሳዊነታችንን ታሪክም ማጥናት ያስፈልጋል።

ከሕዝቦች ስደትና ምድራዊ ሥልጣኔ ጋር መንፈሳዊነቱም በየጊዜው እያደገ መጥቶ ከፍተኛ ደረጃ ቢደርስም፥ በአንዳንድ ሥፍራዎች ከውጪ (ከሰው በላይ ካለ ኃይል) ካልመጣ በስተቀር ሰው የራሱን ሃይማኖት በራሱ ፈጥሮ ማሳደግ አልቻለም።

በአንዳንድ ሥፍራዎች (ለምሳሌ በመካከለኛው ምሥራቅ) በጣኦት ማምለክ እያየለ መጣ፤ ሴቶችን ከነነፍሳቸው እየቀበሩ ማሰቃየት እጅግ በዛ፥ (ስለዚህም) - ሰማያዊ ጣልቃ ገብነት አስፈለገ።

"For We assuredly sent among every People a Messenger …" Sura 16: 36

ትርጉም - "በእውነት እኛ ለሕዝቦች ሁሉ መልእክተኛ (ነቢይ) ላከንላቸው…። " ሱራ 16፡36

የእስልምና ሃይማኖት መሠረታዊ አላማው ሥጋና ነፍስን ለእግዚአብሔር (ለአላህ) ማስገዛት ነው። የሰው ሥጋና ነፍሱ ለእግዚአብሔር የተገዛ ከሆነ፥ ጦርነት አይኖርም፤ እርስ በርስ መገዳደልም ይጠፋል፤ በሰዎች መካከል ጸብና ጭቅጭቅ ጠፍቶ ሰላም ይሰፍናል። "ሰላም" የተባለው ቃል ሥጋና ነፍስን ለእግዚአብሔር በማስገዛት የሚገኝ ውጤት መሆኑ ነው።

ሕዝቦች በየጊዜው ሃይማኖታዊ መመሪያ ሲ<u>ሰ</u>ጣቸው፥ ግን አልገባ እያላቸው ወደ ስህተት በሚያመሩበት ጊዜ ሁሉ፥ እግዚአብሔር መሬት እየወረደ አያስተምርምና፤ ለዚህ ነው የመልእክተኛው የነቢዩ መሐመድ መምጣት ያስፈለገ።

በእስላም ሃይማኖት ላይ ትችት ይበዛል። እስላሞችም እንዲህ ይላሉ -

"አንዳንድ ክርስቲያኖች እንደሚያስቡት፥ የእስላም ሃይማኖት የተሳሳተ፥ በእርኩስ መንፈስም የሚመራ ቢሆን ኖሮ፥ ሰዎች ሲጠፉ ዝም ብሎ አያይም እግዚአብሔር። ይልቅስ፥ የእስላም ሃይማኖት የምድር እርኩሳን መናፍስት፥ መሪያቸውም ሰይጣን ባየለበት ዘመን የተሰጠ፤ የእግዚአብሔርን ኃያልነት፥ የሰይጣንን መቸነፍ የሚያበስር እንደሆነ ታሪካዊ ሂደቱ ይመሰክራል።

በነቢዩ መሐመድ አማካኝነት ቁርአን ከእግዚአብሔር ተሰጠን። ይህም መጽሐፍ ሰዎችን ለማሳሳት፥ ከእርኩስ መንፈስ ወይንም ከሰይጣን የመጣ ቢሆን ኖሮ፥ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች በተግባራቸው ሁሉ ክፉዎች ይሆኑ ነበር። ግን ይህ አለመሆኑ ለሁሉም ግልጽ ነው።

እስልምናም እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ፥ ለድሆችም መጽውቱ በማለት፥ ሰዎች ሁሉ በአንድ እውነትና በአንድ እምነት እንዲመሩና መንፈሳዊ አንድነት እንዲኖራቸው ይጥራል እንጂ፥ በእግዚአብሔር አትመኑ፥ መጥፎም እየሠራችሁ ኑሩ አይልም።

በየመስጊዶቻችን "አላህ ወክበር" እያልን እግዚአብሔርን ስናመሰግን እና ስንጣራ፥ ይህም ጥሪ - ይህም ጩኸት - ይህም ጸሎት ወደ ሰዎች ጆሮ ሲገባ፥ የሁላችንም ፈጣሪ የሆነውን አምላካችንን በጋራ አምልኮት ስናመልክ፥ የዛን ጊዜ የእግዚአብሔር ፈቃድ በምድር መፈጸሙን እናስታውሳለን።

እስካሁን ድረስ የእስልምናን ሃይማኖት እንዳናስፋፋ እያገዱን ያሉት ሕዝቦች፥ እነርሱም የራሳቸውን ሃይማኖት ለመጠበቅ እንደሆነ እናውቃለን። ወደኛ የሚጠጉትን ለማስጠጋት እንጥራለን እንጂ፥ ሁሉም በእምነቱ ተከባብሮ ሊኖር ይችላል።

እኛ እስላሞች ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ አዳም ካለ አባት፥ ከአንድ ንጽሒት ድንግል ሴት መወለዱን እናምናለን። የሰዎችን ሃይማኖት ከቶራ ቀጥሎ ወደ ወንጌል በማሻገር ኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱሱን መጽሐፍ በከፍታ (አዲስ ኪዳን) እንዲያድግ ማድረጉንም እናምናለን።

ከዚያም በኋላ ነቢዩ መሐመድ በቀጥታ ከእግዚአብሔር ያመጣልን ቅዱስ ቁርአን የአይሁድና የክርስቲያን ሃይማኖት በእድገቱ መድረስ ያለበትን ደረጃ ነው የሚያመለክተን። ነቢዩ መሐመድ የቀደሙ ነቢያት ከእግዚአብሔር መልእክት እየተቀበሉ እንደሚያስተላልፉ ያለ ነቢይ ነው እንጂ፥ እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ በቀጥታ ከሰማይ ያልመጣ መሆኑንም እናውቃለን።

በራስ ስነ አመክንዮ መተማመን እና መንፈሳዊ ምሥጢሮች በማይጣጣሙበት ሥፍራ ሁሉ፥ የሃይማኖት ልዩነት እየከረረ መጣ። ነቢዩ ሙሐመድ ክርስቲያኖች ሃይማኖታቸውን ቅጥ አሳጡት እያለ ይወቅሳል። ግን ነቢዩ ሙሐመድ አሁን ቢኖር - በቁርአን ውስጥ የተጠቀሱ፥ ከሰው አይምሮ የፈለቁ አንዳንድ ሰብአዊ አስተያየቶች የእስልምናን ሃይማኖት ቅጥ ያሳጡት መኖራቸውንም ይረዳዋል።

አንዳንድ እስላሞችም - ሁሉን ማድረግ የሚችል አምላክ ሲፈልግ ሰው መሆን እንደሚችል እያወቁ፥ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው ሲባልም፥ በሰዎች መካከል እንዳለው አይነት ዝምድና አለመሆኑን ስተው - "ሰማይና ምድርን የፈጠረ፥ እንዴት

ልጅ ሊኖረው ይችላል፥ ሚስት ሳይኖረው?” ሱራ 6፡ 101 የሚለውን እየጠቀሱ፥ “እንዴት እግዚአብሔር ልጅ ሊኖረው ይችላል?” ይላሉ።

የእስላሞች ሃይማኖት በእስላሞች ዘንድ በደንብ አልታወቀም። እንዲሁም፡- የክርስቲያኖች እምነት በእስላሞች ዘንድ በደንብ እንዳልታወቀም። እኛም ክርስቲያኖች እርስ በርሳችን በደንብ አልተዋወቅንም። ማወቅ የሚገባንን ሳናውቅ ለቀረነው ሁሉ እግዚአብሔር አይነ ልቡና ይስጠን።

በቁርአን መመሪያችን መሠረት፥ ምድራዊነታችንን ጣል አድርገን የምናስተውለው ሰማያዊውን ነው። ይህ የኛ ሃይማኖት የመጨረሻውና እውነተኛው ነው ብለን እናምናለን። ይህም ባይሆን ኖሮ የሰው ልጅ በጠባብ እውቀቱ ሊጽፈው የማይችል ቁርአን ባልተሰጠን ነበር። በእምነታችን፥ በኑሮአችንና በድርጊታችን ሁሉ በቀጥታ ከእግዚአብሔር በነቢዩ መሐመድ በኩል የተላለፈልንን እየተከተልን፥ እኛ አንዱን ፈጣሪ አምላካችንን በደንብ አውቀን ለርሱ ብቻ እየሰገድን እንድንኖር ነው በቁርአን እና ሃዲት በተባሉት መጻሕፍት የተማርነው። ይህንን ኢየሱስ ክርስቶስ የሚቃወም አይመስለንም፤ “ለምን ለኔ መስገድ ትታችሁ ለእግዚአብሔር ብቻ ሰገዳችሁ?” ቢል፥ “አባ - አባቴ..” እያለ ከሚጠራው ከእግዚአብሔር ጋር ፉክክር ይሆንበታል።

እግዚአብሔር በፈለገ ጊዜ የፈለገውን ያደርጋል። የሰዎች ተቃውሞ ለእግዚአብሔር በሚሰግዱ ሰላማዊ ሰዎች ላይ ከሚሆን ይልቅ፥ በምድራዊ ኑሮአቸው ሁሉ የሰይጣንን ሥራ እየሠሩ በሚኖሩት ላይ ቢሆን ይሻላል።

በአሁኑ ዘመን ብዙ ሰዎች (ከማንኛውም ሃይማኖት) ለምድራዊነት ብቻ የሚያገለግል የሰይጣንን መንፈስ እያናፈሱ ነው። የዛሬውና የወደፊቱ እንደ ቀድሞው እንዳይሆን፤ የእስልምና ሃይማኖት ከተሰጠን ጀምሮ፥ ለአንድ ፈጣሪ አምላካችን እየሰገድን እርሱ በሚፈቅደው መንገድ እንድንኖር ግድ ይለናል።

በዚህች ምድር በሰይጣናዊ መንገድ እንድንኖርባት አልተፈጠርንም። ፍጡራን ሁሉ ካለ ምክንያትና ካለ አላማ እንዳልተፈጠሩ፥ ካለ ምክንያትና ካለ አላማ መኖር አይገባቸውም። የሰብአዊነት ክብር ሲረክስ - እግዚአብሔር የማይወደው ብልግና ሁሉ በምድር ላይ ሲፈጸም፥ ገለልተኛ ሆኖ በመመልከት ፋንታ፥ የአለም ሕብረተሰብ በሰላም፥ በፍቅርና በወንድማማችነት እንዲኖር መታገል ይበልጣል።

በእስልምና ሃይማኖት ውስጥ ከሰው እንጂ ከእግዚአብሔር ያልመጣ ትምህርት ስለመኖሩ ማንም ሰው በቀላሉ ማወቅ ይቻላል። ግን፥ የትኛው ሃይማኖት ነው በውስጡ ከእግዚአብሔር ያልመጣ ትምህርት የሌለበት?

ስለተለያዩ ሃይማኖቶች እንጂ ስለ ተከታዮቻቸው መናገር ጊዜ ማጥፋት ይሆናል። በአይሁዶች ወንድሞቻችንም ይህ ጥያቄ ይነሳል -

"የትኛው ሕብረተሰብ ነው በእውነትና በብርሃን ብቻ እየተመላለሰ ደግነትን ብቻ ሲሠራ የቆየ?" የአጠቃላይ ሕዝቦችን ግብዝነት ከሃይማኖቶች መለየት ተገቢ ነው።

የትኛው ሃይማኖት ነው ከሌላው ሁሉ ተለይቶ የተከታዮቹን ምዕመናን ያጸደቀ? በሁላችንም ሃይማኖት ተከታዮች ዘንድ ኃጢአተኛም ጻድቅም ይኖራል። በእስልምና ተከታዮች ላይ ብዙ ጉድፍ ቢታይም፥ የእስልምና ሃይማኖት እንደዛ አይደለም። አክራሪዎች ባይኖሩብን ኖሮ ይህንን ያህል የጎላ ልዩነት በመካከላችን አለመኖሩ ግልጽ ይሆን ነበረ።

ለእውነት የሚቀርበውን የሚያውቅ እግዚአብሔር በፈቀደ፥ ከነልዩነቶቻችን ተከባብረን መኖር ነው የሚበልጠው። የኛ ሃይማኖት ከአይሁድና ከክርስቲያን ሃይማኖት የፈለቀ ባይሆን ኖሮ፥ የኛ እግዚአብሔር ከናንተ እግዚአብሔር ይለያል ማለት ይቻል ነበር። ግን ቁርአንን ላነበበ፥ በእውነት ሃይማኖታዊ መሠረታችን አንድ እግዚአብሔር (የአብርሃም አምላክ) መሆኑ ግልጽ ነው። አዎ! እውነተኛውን እውነት - ያንን አንድ እግዚአብሔር ከአይሁዶችና ከክርስቲያኖች እግዚአብሔር ለይቶ መመልከት የማይቻል ነው። የሁላችንም ምንጩ አንድ ስለሆነ፥ ይልቅስ የምንጠጣውን ውሃ የሚያደፈርሱብንን በአንድነት ሆነን እንከላከል።

በእርግጥ በመካከላችን ጥቂት ልዩነቶች ይኖራሉ። በሃይማኖት ብንለያይም ተከባብረን በሰላም አብረን መኖር እንችላለን። የእስልምና ሃይማኖት ክርስቲያኖችን አጥፉ አይልም። ምድራዊ ፖለቲካን ከሃይማኖት ለይተን ብናወጣ፥ ምናልባት የበለጠ እንቀራረብ ይሆናል።

ፍጹማዊነት በተግባር እንጂ በሃይማኖት አይለካም። የጥሩነት መንፈስ የሚመነጨው ከእግዚአብሔር ከሆነ፥ የማንም ሰው እምነቱ የተለያየ ቢሆንም፥ ጥሩ በመሆን ከተቀራረበ፥ ሁሉም በአንድ የብርሃን ጎዳና ይመላለሳል፤ የጉዞውም መጨረሻው ዘለአለማዊ ጥሩነት ካለበት ሥፍራ የሚያመራ ይሆናል።

በመንፈስ ከመለያየት ይልቅ፥ በመንፈስ አንድነትን ማግኘት ነው (ቢቻል) የበለጠ ደስ የሚያሰኝ፤ በሰዎች መካከል የተፈጠረ የሃይማኖት ቅራኔ ሲጠፋ፥ የዛን ጊዜ ሰው ሁሉ ቆንጆ፤ እምነቱም ያማረ ይሆናል።

"በተለያዩ ሃይማኖቶች የታቀፍን እኛ፥ በመንፈስ አንድነትን ማግኘት እንዴት ይቻለናል?" ብለን መጠየቃችን አይቀርም። ግን "ሃይማኖት የጋራ ነው፤ እምነት ግን የግል ነው" የምንል ከሆነ ይቻላል።

<u>ፕሮቴስታንት</u>

ክርስቲያኖች መባላችን፥ የክርስትና ሃይማኖት ከክርስቶስ መስዋዕትነት የቀጠለ፥ በእግዚአብሔር ፍቅር የጸና በመሆኑ ነው። ሰማያዊው አለም ለአካላዊ ሰው ሳይታይ እንዳይቀር ሲል፥ እግዚአብሔር ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ልጁን ወደ አካላዊ አለም እንዲገባና እንዲያስተምር አደረገ። ታዲያ በሃይማኖቶች መካከል የተፈጠረው አለመግባባት የእግዚአብሔር መንግሥት ለጊዜው ከምድር ባለመኖሩ ይሆናል። ክርስቶስ ዳግመኛ ሲመጣ የሃይማኖት ልዩነት ቀርቶ፥ አንዱ ያወቀውን ለሌላው እያሳወቁ ተከባብሮ መኖር ይችላል።

የአንድ ሃይማኖት አላማና ግቡ የሰውን ልጅ ጠባይ እየለወጠ፥ ደግነትን፥ ፍቅርን፥ እርስ በርስ መተሳሰብን፥ መረዳዳትን፥ አለመጣላትን፥ አለመተማማትን፥ ባጠቃላይ ክርስቶስን መምሰልን ማስተማር መሆኑን እናምናለን። የእግዚአብሔር ፈቃድ ሰው ሁሉ በእርሱ እንዲያምን መሆኑን እናውቃለን (እናምናለን)።

ትኩረታችን በወንጌሉ ቃል ላይ ነው እንጂ፥ በጥንት ጊዜ አማኞችን ለማሳመን በተጻፉ፥ ምንጮቻቸውም ባልተረጋገጡ፥ እውነተኛነታቸውም አጠራጣሪ በሆኑ ስነ ጽሐፎች ላይ አይደለም። ዘመን አልፎ ዘመን ተተክቷልና፤ ያለፈው ዘመን ላለፉት ነው። ምድራዊ እድሜ አጭር ናትና፥ ሃይማኖታዊ ትኩረታችን (ትምህርታችን፥ ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴዎቻችን፥ ባህላችንና አኗኗራችንም) በወንጌሉ ላይ የጸና ቢሆን ይሻለናል።

ባሁኑ ዘመን ጥያቄው - "ጥሩ ሰው ለመሆን (ክርስቶስን ለመምሰል) ምን መደረግ አለበት?" ነው። የወንጌሉን ቃል ሰምተን፥ የክርስቶስን መስቀል ብቻ እየተከተልን፥ በአንድ አላማ - በመንፈሳዊነት ወደፊት በመገስገስ ነው ክርስቶሳዊ ፍጹምነትን የምንቀዳጀው።

ሃይማኖትን እንደ ስም መጠሪያ፥ እንደ አለማዊ ክብር፥ እንደ ምድራዊ ልብስ ማድረግ ምድራዊነት እንጂ መንፈሳዊነት አይደለም፤ ሥጋዊነትና መንፈሳዊነት ተጻራሪሪዎች ናቸውና። ቤተ ክርስቲያን ሥጋዊነትን ማደንዘዣ፥ መንፈሳዊነትን ማጎልመሻ መሆን ይገባታል።

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ - "እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ ወደ እኔ ኑ፤ እኔም አሳርፋችኋለሁ።" ማቴ. ፲፩፥ 28 ሲል፥ ማእከል የምሆን እኔ ነኝና በኔ ዙሪያ ተሰብሰቡ፤ ከኔ የሚገኝ ፍቅር ጠቅላላ የአለምን ሕዝብ ሁሉ በመንፈሳዊ ፍቅር ሊያስተሳስር ይችላል ማለቱነው እንጂ፥ እኔ ከመካከላችሁ በሥጋ ባልገኝ፥ በኔ ምትክ (ምስል) ሌላ ሰው (ጳጳስ፥ ፓትሪአርክ...ው.ዘ.ተ.) ምረጡና እርሱ ያሰባስባችሁ ማለቱ አይመስለንም።

አንድ ቄስ ከሚስቱና ከቤተሰቡ አልፎ የአንድ ቤተ ክርስቲያን አባላትን በመንፈሳዊ ፍቅር ቢያጠጋጋ፤ አንድ መነኩሴ፥ ራባይ ወይንም ሼክ በዙሪያው ተከታዮቹን በመንፈሳዊ ፍቅር ቢያቀራርብ፥ ለጊዜው ውጤቱ ያማረ ቢመስልም፥ በሰው ላይ ብዙ መተማመን ወደማይፈለገው አቅጣጫ ሊያመራ ይችላል። በምድር ላይ መንፈሳዊ ህብረተሰባዊ አንድነትን ሊመሠርት ከሚችል ከክርስቶስ ሌላ ማንም አይኖርም።

በፕሮቴስታንትነት የታወቁ ሃይማኖቶች ብዙኃን ሆነው ሳለ፥ ሁሉንም በአንድ ላይ በማጠቃለል፥ ሁሉንም የማርያም ጠላት ማስመሰል አይገባም። እኛ ፕሮቴስታንቶች ሁላችንም አንድ አይነት አመለካከት የለንም። የሃይማኖት ክርክር ሲበዛ - እርግጠኛ ሆኖ፥ አውቆ - ከሃይማኖቶች ሁሉ መካከል አንዱን መርጦ መከተል ምንኛ ከባድ መሆኑን ነው የሚያሳየው። በአንዳንድ በደንብ ባልተገለጹ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ላይ ትክክሉ ይህ ነው ብሎ መከራከር ደግሞ መጨረሻ የሌለው ክርክር ነው የሚሆን፤ አያዛልቅም።

የማርያም ወንድሞች የተባሉት የክርስቶስ ወንድሙ መሆናቸውን እንጂ፥ በምን አይነት መንገድ ወንድሙ እንደተባሉ መጽሐፍ ቅዱስ አይገልጽም። በዚህም ሆነ በዛ ወንድም ከተባሉ ክርስቶስ ወንድም ነበረው ብሎ መቀበልና በተዘዋዋሪ የማርያምን ክብር የሚቀንስ ሃሳብ ማሰራጨት ለየቅል ናቸው።

ማህደረ መለኮት የሆነች ማርያም፥ የዮሐንስ እናት እና የሰው ልጅ ሁሉ እናት ልትሆን የምትችለው በተለየ መንገድ (በድንግልናዋ) መሆኑን ብዙዎቻችን እየገባን መጥቷል። የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ትምህርት ስንከታተል፥ ስለ ፍጹም ሰውነቱና መለኮታዊ ባህሬው፥ የሰውን ዘር ስላስከበረች ስለእናቱም ባንድነት እያሰብን እንዲሆን እየተማርን ነው። እንዲህ ያለውን አመለካከት የፕሮቴስታንት ሃይማኖት መሥራቾች እነ ማርቲን ሉተር እና ጆን ካልቪን፥ እና ሌሎችም ታላላቅ የሃይማኖት መሪዎቻችን አልተቃወሙም።

ከመካከላችን አንዳንድ ግለሰቦች በጥራዝ ነጠቅነት “ጸጋን የተመላች” የማርያምን ክብር ሲቀንሱ እናዝናለን። የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ እናቱ ናት ድንግል ማርያም ፤ አይሁዶች እንደሚሉት የዮሴፍ ልጅ አይደለም ክርስቶስ፤ የእግዚአብሔር ልጅ ነው እንጂ።

በእርግጥ ስለ ማርያም ያለን እውቀታችን ውሱን ነው። ማህደረ መለኮት የተባለች ማርያም በብሉይ ኪዳን የቃሉ ማደሪያ ታቦተ ጽዮን መባሏ ቀጥ ያለ ስነ አመክኖአዊ ሃይማኖታዊ አስተሳሰብ የሚያስከትል ቢሆንም፥ እኛ ማርያምን በቀጥታ ከጽዮን ጋር አለማመሳሰላችን ብቻ የሚያጣላ መሆን የለበትም። ሆኖም፥ ማርያምን፥

ክርስቶስን እና እግዚአብሔርን ኃጢአት ከሚሠራ ሰው ለይቶ መመልከት እንደሚያስፈልግ፥ ይህንን እኛም አውቀን የምናምንበት ነው።

"ማርያም ታማልደናለች" ብለን ስሟን በየጊዜው አለመጥራታችን ነው እኛን የተለየን ያስመሰለን እንጂ፥ እኛም ለጌታችን ለክርስቶስ እናቱ ለሆነችው ቅድስት ማርያም ወዳጆቿ ነን።

ከታሪካዊ ሂደቶች ተገንጥሎ የማይታየው እምነታችን ከዚህ ቢያደርሰን፥ ጸረ ሰይጣን እንጂ ጸረ ማርያም አላደረገንም። አንዳንዶች ግን፥ እኛን እንደ ማርያም ጠላት ይቆጥሩናል፤ ሌሎችም በሙሉ አፋቸው - "ጸረ ማርያም.." እያሉ ይሰድቡናል። ማርያም ግን፥ አዳኛችን በሆነው ልጇ ላይ በመማጸናችን ትወደናለች እንጂ አትጠላንም (ሰዎች እኛን የማርያም ጠላት ቢያደርጉን ማርያም እኛን ጠላቷ አታደርገንም)።

የሰብአዊነት ሃይማኖታዊ እድገት የሚለካው የክርስቶስን ቃል በተግባር ላይ በማዋል ስለሆነ፥ ክፉውን በደግ መለወጥን እና እንደገና በመንፈስ መወለድን እየተማርን የክርስቶስን ዳግመኛ መምጣት እንጠባበቃለን።

የጥንት ክርስቲያኖች የተወሰኑ ሕግጋቶችን እና ልምዶችን ተከትለው ይጓዛሉ። ተከታዮቹም ከልጅነት ጀምሮ በተደነገገው ሕግ ውስጥ ስላደጉበት፥ ሃይማኖታቸውን እንደ ባህል ማጠናከሪያ አድርገውታል። የነኚሁ የጥንት ክርስቲያኖች ሕብረተሰብ ይህንኑ ሃይማኖታዊ የጋራ ልምድ ተከትሎ ሲጓዝ - "ለመሆኑ የኛ ክርስቲያናዊ አላማ ምንድነው?" ብለው የጠየቁ ሃቀኛ ክርስቲያኖች ናቸው የፕሮቴስታንትን ሃይማኖት የመሠረቱት።

አሁንም ቢሆን፥ ጊዜው እየመሸ፥ የክርስቶስም መምጪያ ከቀን ወደ ቀን እየተቃረበ ሲመጣ፥ "እኛ ምን እናድርግ? ወግ እና ስነስርዓቱን ብቻ ተከትለን እንጓዝ? ወይንስ የወንጌሉን ቃል በአለም እናዳርስ?..." በማለት፥ መንፈሳዊ ቅንዓት ያደረባቸው ክርስቲያኖች እጅግ በዙ፤ ተበራከቱ፤ የነርሱ መንፈሳዊ ጥንካሬ ነው የፕሮቴስታንትን ሃይማኖት ከዚህ ያደረሰው።

የጥንት ክርስቲያኖች እውነተኛነት ጥርጥር የለውም። ሕግና ስነስርዓት ያበዛሉ ቢባሉም፤ እነርሱ ይህንን ማድረጋቸው ትክክል አይደለም ማለት አይደለም፤ ይህንን ባያደርጉ ኖሮ ሃይማኖታቸው ቆይቶ ከዚህ አይደርስም ነበርና። ነገር ግን፥ እኛ በአንክሮ መግለጽ የምንወደው - እውነተኛ ሆኖ መቆየትና ሃይማኖትን በተግባር ላይ ማዋል የተለያዩ መሆናቸውን ነው።

እኛም "የእውነተኛው ሃይማኖት ተከታዮች ነን..." በማለትና እራሳችንን በማሞካሸት ብቻ ተወስነን እንዳንቀር መንፈሳዊ ቅንአታችን ነው ከዚህ ያደረሰን።

የሃይማኖቶችን አመጣጥና ልዩነት ስንመለከት፥ ለሁሉም በቂ ምክንያቶች እንደነበሩ ሁሉ፥ እኛ ፕሮቴስታንቶች ከጥንት ክርስቲያኖች ተገንጥለን፥ በጊዜ ብዛት እጅግ ተጠናክረን፥ በአለም ዙሪያ እንዲህ በዝተን መታየታችንን መላው የክርስቲያን ቤተሰብ በደስታ የሚቀበለው መሆን አለበት። ምንጊዜም በመካከላችን ቅር የሚያሰኝ የቃል ልውውጥ ቢኖር እርስ በርሳችን ይቅር እንባባል።

## አንድነታችን

ትላንት፥ ዛሬና ለወደፊትም በምድር ያለነው እኛው ነን። አካላዊ ሰውነታችን ይቆራረጣል፤ ነፍሳማ ሕያውነታችን ግን አይቆራረጥም። እንኳን ለዚች ምድር በዚህች ጊዜ ይቅርና፥ ለጠፈር ምድሮች፥ ለዘመናትም የምንቆይ ዘላለማውያን ነን። ስለዚህ ከዛሬው ሁኔታ ተነስተን፥ የሰውን እድገቱን፥ ረቂቅ የማይታይ ውስጣዊ ጠባዩን፥ ተስፋ የማይቆረጥበት የወደፊት ተስፋውን - እድሉን፥ አቅጣጫውን - መጨረሻውን- መጥፊያውን - እልቂቱን፥ ከዚያም አዲስ ትውልድ መተካቱን በአይነ ሕሊና እንመልከት።

ለወደፊት አለማችንን ከጥፋት የሚያድናት አለም አቀፋዊ መንፈሳዊ አንድነት ብቻ ነው። ለወደፊት ዘረኛነት ጠፍቶ አብሮ መሥራትና አብሮ ማደግ አለም አቀፋዊ መልክ ያወጣል። ይህም ሥራ ተጀምሯል።

በተለያዩ ምክንያቶች ተበታተንን። ግን፥ በእያንዳንዱ ሰው ውስጥ (በክርስቲያኑም፥ በእስላሙም፥ በሂንዱውም..ወዘተ.) የእግዚአብሔር መንፈስ መኖሩን አውቆ፥ በከፍተኛ ግንዛቤአዊ መከባበር ሰው ሰውን ሲያናግረው፥ እግዚአብሔር እንዳናገረው ቢቆጥረውና፥ ሰውና ሰው ቢደማመጥ መሰባሰባችን አይቀርም።

በሕይወታችን የምድራዊነታችን ሁለገብነት የእድገታችን ማነቆ እየሆነ፥ ሥጋዊና መንፈሳዊ ኑሮአችንን አስጨናቂ ቢያደርገውም፥ ከምድራዊነታችንም ለቀቅ እያልን እንድንሄድ የሚያስችል መንፈሳዊ ጠባይ አለን። በምድራዊነታችን ብቻ ተወስነን የምንቀር አይደለንም በእውነት። እያንዳንዳችን እንደየሃይማኖታችን በእምነት እንጽና እንጂ፥ ካለንበት ሥፍራ እግዚአብሔር አለ።

የአለም ሕዝቦች ባለ ብዙ ሃይማኖት ሆነውም አምላካቸውን (ፈጣሪያቸውን) ይፈልጉታል። ለዚህም የእውቀት መብዛትና ማነስ ትርጉም አይኖረውም። ስለዚህ፥ ሰው ሁሉ አሰባሳቢ የሆነውን ማእከሉን - የገዛ እምነቱን እየፈለገ መሰባሰቡ አይቀርም። እኛም ክርስቲያኖች በአይነ ሕሊና ክርስቶስን እና መስቀሉን ስንመለከት፥ በእግዚአብሔር የሚያምኑ የሌሎች ሃይማኖቶች ተከታዮችም እንዲሁ ወደ እግዚአብሔር መንፈስ ሲጠጉ፥ ሁላችንም ባንድነት እንገናኛለን (እንሰባሰባለን)።

“እንግዲህ በሰማያት ያለፈ ትልቅ ሊቀ ካህናት የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ስላለን ጸንተን ሃይማኖታችንን እንጠብቅ..።” ወደ ዕብራውያን 4፡14

ሃይማኖቶች ሁሉ እውነት ካልሆኑ፥ ሁሉም ውሸት መሆን አለባቸው ማለት ይቻል ይሆናል። አሁንም ሃይማኖቶች ሁሉ እውነት ካልሆኑ፥ አስቀድመው በመምጣታቸው፥ ወይንም በኋላ በመምጣታቸው እውነትነታቸው ሊቀንስ፥ ሊጨምርም ይችላል። ይህንን ነው ይህ መጽሐፍ ችሎ የማይመልሰው። ነገር ግን ሃይማኖቶች ሁሉ እውነት ከሆኑ፥ አስቀድመው በመምጣታቸው፥ ወይንም በኋላ በመምጣታቸው እውነትነታቸው አይቀንስም ወይም አይጨምርም፤ እውነትን ጊዜ አይወስነውምና።

ሆኖም፥ የሰው አስተሳሰብ፥ ከምድራዊ ፍላጎቶች - ከገንዘብም ጋር ስለተዛመደ፥ እውነቶች ስለተወላገዱ፤ ጽሑፎች ስለተበረዙ፤ አንዳንድ መንፈሶችም አብረው ስለተጣመሩ፥ ሃይማኖቶች በዙና እርስ በርስ መግባባት አስቸገረ። ግን የሁላችንንም ሃይማኖት ስንመረምረው፥ መሠረታዊ ፍልስፍናው (እምነቱ/ዶግማው) በመጠኑም ቢሆን ይቀራረባል። ሆኖም፥ አንዳንድ ተፈላሳፊዎች ልዩነቶቻችንን የሚያሰፉ ሃሳቦች በመካከላችን ያሰራጫሉ።

ምንጊዜም በታኝ ሃሳቦች ከአዋቂዎችና ከፈላስፎች መሰንዘራቸው አይቀርም። ግን ሕልም ተፈርቶ ሳይተኛ አይታደርም እንደሚባለው ሁሉ፥ የአዋቂዎችን ትችት በመፍራት ወደኋላ አንልም። ሦስት ምሶሶዎች (**እምነት**፥ **ተስፋ** እና **ፍቅር**) ያጸኑናል። 1ኛ ቆሮ 13፡13

አንዳንድ ሰዎች - “ቶሎ ብዬ ሃይማኖቴን ልለውጥ፤ የማያጸድቀውን ትቼ የሚያጸድቀውን ልከተል...” በማለት ይጨነቃሉ። የሐዋርያው ጳውሎስ ግን አንዱ ለሌላው መሰናከል እንዳይሆን በማስጠንቀቅ - “ለአንተ ያለህ እምነት በእግዚአብሔር ፊት ለራስህ ይሁንልህ..” ሮሜ 14፡22 በማለት አስገንዝቧል።

አንድ የሕግ አዋቂ - “መምህር ሆይ፥ ከሕግ ማነኛይቱ ትእዛዝ ታላቅ ናት? ብሎ ጠየቀው። ኢየሱስም እንዲህ አለው - “ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ፥ በፍጹም ነፍስህ፥ በፍጹም አሳብህም ውደድ። ታላቂቱና ፊተኛይቱ ፊትእዛዝ ይህች ናት። ሁለተኛይቱም ይህንን ትመስላለች። እርስዋም፡- ባልንጀራህን እንደ ነፍስህ ውደድ የምትለው ናት..።” ማቴ 22፡35 - 40

ሃይማኖቶች (መሪዎቻቸው ሁሉ) ይህንን አይቃወሙም፤ ደግመው ደጋግመው የሚሰብኩት ይህንኑ የክርስቶስን ቃል ነው። የእግዚአብሔር አብ ቃል ከልጁ ከኢየሱስ ክርስቶስ ቃል እስካልተለየ ድረስ፥ ከፉውን በከፉ አትቃወሙ የሚለው ቃል የትም ሥፍራ ስለሚያገለግል፥ ከሥጋዊነት ለሚመነጭ ጥቃቅን ልዩነት ክፍተት

ሳንሰጥ፥ የሚቀርቡንን ብናቀርብ፥ የራቁትንም ለማቅረብ ብንተጋ፥ ሁላችንም በመሰባሰብ አንድላይ እንሆናለን።

የሰው ልጅ ከሥጋው አካሉ እስካልተላቀቀ ድረስ፥ በተግባር ባይሆንም፥ በአስተሳሰብ ኃጢአት ከመሥራት ላይቆጠብ ይችላልና፤ ለጊዜውም ቢሆን፥ በያለበት ከመ እንስሳ ሆኖ እንዳይቀር፥ በዛች በተሰጠችው ጭንቅላቱ ሁሉም በያካባቢው ተስማምቶ እንዲኖር (ሁሉም እንደየችሎታው በተለያየ መንገድ እግዚአብሔርን ማምለክ ይችል ዘንድ) እግዚአብሔር እራሱ የተለያዩ ሃይማኖቶችን እንደፈቀደለት፥ በተለያዩ ጊዜያት የተጻፉት ቅዱሳት መጻሕፍት ምስክሮች ናቸው።

ሰዎች ፍጹሙን የእግዚአብሔር እውነት እንደየጊዜውና እንደየሥፍራው በጥቂት በጥቂቱ እንደየችሎታቸው እንዲቀስሙ ተደረገ እንጂ፥ እንኳን ባለፉት ዘመናት ይቅርና፥ ለወደፊት ከሙቶ ሺህ ዓመታት በኋላ እንኳን የሚፈጠር ትውልድ ፍጹሙን የእግዚአብሔር እውነት ችሎ አይረዳውም።

በአለም ሃይማኖቶች ሁሉ መካከል መሠረታዊ የሃይማኖታዊ ፍልስፍና ልዩነት ሳይኖር፥ እኛ በራሳችን የአስተሳሰብ ዝንባሌዎች ምክንያት አላስፈላጊ ልዩነቶችን እየፈጠርን፥ እርስ በርስ እስከመጣላትና እስከመገዳደል እንደርሳለን። የፈጣሪያችንን ማንነት ጥቂት (ማለትም እጅግ ጥቂት) የተገለጸልን ቢኖር በዛችም እንጣላለን።

ለሰው ጉልበት የሚያጎበድድ አይኖርም፤ የሰላ ጎራዴ ሃይማኖት አያስቀይርም፤ የገንዘብ ብርታትም የሰውን ውስጣዊ እውነትን አይቀብረውም። ነገር ግን ውሸት ከሁላችንም ዘንድ ስላለ፥ ሰውን ከሰው የሚያበጣብጠው የእውነትና የውሸት መደበላለቅ ነው።

በአንድ ማእከላዊ ኃይል ስበት ወደ ፈጣሪ የሚሳብ ይሳባል። በሌላም ማእከላዊ ኃይል ስበት ወደ ሰይጣን የሚሳብ፥ ወደዛው ይሳባል (ሁለት ማእከል)።

የእያንዳንዱ ሰው እምነት ቢመረመር (በተለይ ባሁኑ ዘመን፥ እንዲሁም ወደፊት፥ መጨረሻው እስኪቃረብ ድረስ) የተለያየ ሊሆን ይችላል። በአንድ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ፥ በአንድነት የሚቀድሱ ቀሳውስት በዛ በመቅደስ ውስጥ ሁሉም አንድ ናቸው። ሃይማኖታቸው አንድ፥ እምነታቸውም አንድ ነው (ለእነርሱ ሃይማኖትና እምነት አንድ ነው)። ከመቅደሱ ሲወጡ ግን፥ መሠረታዊ ሃይማኖታቸው አንድ ቢሆንም፥ እያንዳንዳቸው የሚለያዩበት ውስጣዊ እምነትና አመለካከት ሊኖራቸው ይችላል። ስለዚህ ሃይማኖት የጋራ፥ እምነትም የግል ሊሆን ይችላል።

የጋራ የሆነ ሃይማኖት የሚያስፈልገው ሰዎች ባህር ላይ እንደወደቀ ኩበት በግለኝነት እንዳይዋልሉ ነው - አንድ ሰው የገዛ እምነቴ ያድነኛል ቢልና ለብቻ የራሱን እምነት ይዞ ቢጓዝ፥ በእርኩስ መንፈስ ነፋስ ጨርሶ የመጥፋት እድል ሊያጋጥምው

ይችላል። አንዳንድ ጊዜም እንዲህ አይነቱ ጥፍት ማለት ሰውን ሰይጣናዊ ያደርገዋል፤ ወይንም ከአጠቃላይ ሰብአዊ ግንዛቤአዊነት ያወጣዋል - የአይምሮ መታወክ ይደርስበታል (እንዲህ ጥፍት ካሉት መካከል በማከታተል ሰውን የሚገድሉ - serial killers ይወጣሉ)።

ሰዎች በአንድ ሃይማኖት ጥላ ሥር ሲቆዩ መንፈሶቻቸውም አንድ ላይ ይሆናሉ። ዞሮ ዞሮ ግለሰቦች ለግላዊ ስሜቶቻቸው ቅድሚያ በመስጠት ፋንታ መንፈሳዊነትን ቢያስቀድሙ፥ ከሌሎች ወንድሞቻቸው (እህቶቻቸው) ጋር በመንፈስ መተሳሰራቸው አይቀርም። ይህም መንፈሳዊ መተሳሰር (መንፈሳዊ ማህበር) የአካላዊነት ሕግ የማይገታው ስለሆነ ረቂቅ ነው።

የአክራሪዎች ጩኸት ሰውን ሲያደናቁር፥
ጥሩው ሰው ገለል አለ ከአማኞች መንደር።
በዚህ የሰይጣን ወጥመድ ወድቀን እንዳንቀር፥
ሳይጀመር ይቅር፥ የሃይማኖት ክርክር፤
ዳኛው እስኪመጣ ተከባብረን እንኑር።
ከሰው ማንም የለም፥ ፍጹም በፍጥረቱ፥
ስለዚህ ተሰጠው፥ ሃይማኖት ለሕይወቱ።
ከሂንዱ - ጠፈራዊ ግንኙነቶችን፥..
ከቡድሃ - ባህታዊነትን እና ሰላማዊ ኑሮን፥..
ከክርስቲያን - ይቅር መባባልን፥...
ከእስላም - ለድሆች መለገስን፥...
ተመስገን፤ ይህን ሁሉ ተማርን።
ሁሉም ሃይማኖት እየመራ ከዚህ አደረሰን።
ከእንግዲህም እውቀትን፥ ፍቅርን፥ ሰላምን ከፈለግን፥
ሁሉም ሃይማኖት ነው የሚያስፈልገን።
ግን ይህንን መመልከት ሲያቅት፥
በግንዛቤ ጉድለት ሽንፈት፥
በፍቅር ፋንታ ጦርነት፤
እስኪገባን ድረስ ቅጣት።
ከእንግዲህ አያቋርጥ መመልከታችን፥

መልከ ሰማይን፥

የእግዚአብሔርን የዙሪያውን፥

የጻድቃን፥ የመላእክቱን፥

ከዚያው ነውና መሄጃያችን፥

መሰባሰቢያ ጽዮናችን።

ሁሉን አቃፊ የሆነ እግዚአብሔር ሁላችንንም ጠብቆ ለመንግሥቱ ያብቃን፤ አሜን።

# ምዕራፍ ስድስት

## በአንድ አለም ሁለት አለም

በእውነት በዚች ምድር የሚሠራውን ስንመለከት፥ ባንድ አቅጣጫ ሥጋዊ ብቻ ይመስላል፤ በሌላውም ጎኑ የመንፈስ ሥራ ይመስላል። መንፈስ ህልውናውን በሥጋ ውስጥ ደብቆ ይኖራል። የመንፈስ መደበቂያው አይምሮ ውስጥ ይሆን? አይምሮ የሚታየውንም የማይታየውንም መመዝገብ የሚችል ስለመሆኑ በስነአይምሮ ተመራማሪዎች ዘንድ ታዋቂ ሆኗል። አይምሮ ይህን ያህል ችሎታ ባይኖረው ኖሮ፥ ካለ አንዳችም አካላዊ ሞገድ - ከምድራዊነታችን ባሻገር የሚከሰት - በእርግጥ እንደ አካል ቁልጭ የሚል የመንፈስ ነገር ሊታወቅ አይችልም ነበር። ለሚያምኑ - ለነርሱ አይምሮአቸው ነው የሚነግራቸው፤ ለማያምኑ - ለነርሱም አይምሮአቸው ነው የሚነግራቸው፤

በአይምሮ ውስጥ የሚመዘገበው ስዕል ባለ ቅርጽ ሆኖ ወደ አይምሮ የሚሰርጽ፥ ከብርሃን ሞገድ ብቻ የሚመጣ አይደለም። እንዲህማ ቢሆን ኖሮ ከልጅነታቸው ጀምሮ አይነ ስውር የሆኑ በአይምሮአቸው የሚቀረጽ ስዕል አይኖርም ነበር። ሳናውቀው ባለብዙ ስሜቶች በመሆናችን ነው ከአካላዊ ትርጉም ፈቀቅ እያልን የመንፈስን ሥራ ለመመርመር የምንሞክር።

ስለሰው ስናወራ በቶሎ የሚታየን ሥጋዊነቱ ነው፤ መንፈሳዊውን ሰው ስለማናየው እንደሌለ አድርገን ነው የምንቆጥረው። ለምሳሌ - የመንፈስ ልጅነት ከሥጋ ልጅነት ጋር አብሮ ማደግ እንዳለበት በሥጋ የወለዱን እናትና አባታችን ስለሚያምኑ፥ ገና ሦስት ወር ሳይሞላን (በአርባ ቀን ለወንድ፥ እና በሰማንያ ቀን ለሴት) ያጠምቁናል። ይህንን ምሥጢረ ጥምቀት በተለይ የትዋሕዶ ኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች ያምኑበታል - ፍጥረታችን በመንፈስና በሥጋ መሆኑን ገብቷቸዋል። ከተጠመቅን በኋላም፥ ድርጊታችን ሁሉ የሚያንጸባርቀው ሁለቱንም (ምድራዊም ሰማያዊም) ነው። ስለዚህ፥ አንድ ህጻን ሲወለድ በሥጋ ሦስት ወር ባይሞላውም እንኳን፥ በመንፈስ ከተወለደ (በክርስቶስ ክርስቲያን ከሆነ) ቆይቷልና፤ ያን ክርስቲያናዊ እሱነቱን ከአካላዊነቱ ጋር ለማዛመድ ሲባል ነው የሚጠመቀው። ክርስቲያንነቱም ጸንቶ እንዲቆይ ለማድረግ የክርስትና አባት (ለወንድ)፥ የክርስትና እናት (ለሴት) ይመደባል።

በእያንዳንዱ ሰው ውስጥ ሰማያዊነትና ምድራዊነት እየተሚገቱ፥ ሰዎች እርስ በርሳቸው በጦርነት ሲጨራረሱ - ይህ ታሪክ የኛ (የሰብአዊነት) ብቻ ላይሆን ይችላልና፤ በታሪካችን ውስጥ "የመናፍስትም ትግል አለበት" በሚል አንጻር ለመመልከት ብንነሳ፥ ምናልባት አንዳንድ ድብቅ ሃሳቦች ከቦታቸው ተንቀሳቅሰው፥ ለአንዳንድ ተማራማሪ አይምሮ የሚከስቱት ነገር ይኖር ይሆናልና፣ እስቲ ይህንንም ጉዳይ እንመልከተው።

በእርግጥ በሃይማኖት መጻሕፍት ስለ ሥጋዊነት የተገለጸውን ያህል ስለ መንፈሳዊነትም የተገለጸ ይኖራል፤ ሆኖም፥ እኛ ምንጊዜም አስተሳሰባችን ወደ ሥጋዊነት ስለሚያዘነብል፥ ይኸው ሥጋዊነታችን ማወቅ የሚገባን ሁሉ ሸፍኖብናል (ለብዙዎቻችን)።

አብዛኛው የአለም ሕዝብ ፍዝዝ ያለ ኑሮ ይኖራል። በሕዝቦችም መካከል አልፎ አልፎ ነቃ ነቃ ያሉ ሰዎች ይወለዳሉ። ለጥሩም ሆነ ለመጥፎ ታሪክ ሠሪዎቹ እነርሱ (ነቃ ነቃ ያሉት) ይሆኑና፤ ሰብአዊነት በአካሉ (በምድራዊነቱ) መልክ አውጥቶ፥ ደምቆ እንዲታይ ያደርጉታል።

ጥንት የነበረ ለወደፊትም የሚኖር፥ በሕይወታችን ውስጥ ዋና ተዋንያን መንፈሳችን እየሆነ፥ የማንወደውን የሚያሠራ፥ የምንወደውንም ቢሆን ለጥፋት ሲሆን የሚያፋጥን፥ ለበጎ ሲሆንም የሚያጓትት፥ .. ሰውም እንደ መንፈስ፥ መንፈስም እንደሰው ሲሆን አስተውለናል።

በዚህ አለም ላይ ብዙ ነገር እንደሚሠራ ሁሉ፥ የግለሰብም ሕይወት በዚህ አለም ላይ ከሚሠራው ሥራ ጋር ሁሉ ይያያዛል። በዚህ አለም ላይ ብዙ ነገር ብዙ ነገርን ይመስላል፤ የግለሰብም ሕይወት በዚህ አለም ላይ ከሚመስለው ሥራ ጋር ሁሉ ይያያዛል። እና፥ የግለሰብ መፍጨርጨር ብቻውን ምድራዊ ሕይወትን አያሻሽለውም። ለዚህ ነው ሕይወታችን የዙሪያችን (የሚሠራውንም ሁሉ፥ የሚመስለውን እና የማይመስለውን ሁሉ) ከማጥናት ጋር አብሮ መሄድ ያለበት።

የሰይጣን በጠፈር ውስጥ ሁሉ መኖር በጠፈር ሁሉ የቅራኔን መኖር ያመለክታል። በጠፈር ሁሉ ከሚኖር ቅራኔ የማናመልጥ ነውና፤ የኛም የቅራኔአችን ታሪክ በሰማይ ከመላእክት አለቆች መካከል ሉሲፈር ከተባለ መልአክ ታሪክ የቀጠለ መሆን አለበት።

ሉሲፈር ፈጣሪውን እግዚአብሔርን ፈልጎ ሲያጣው ጊዜ - "ከኔ በላይ ማንም የለም.. " ብሎ አወጀ፤ እራሱን ከመላእክት ሁሉ በላይ በማድረግ ለኔ ስገዱ አለ። እግዚአብሔርም ብቅ ሲልበት በጥፋቱ ተጸጽቶ ይቅርታ በመጠየቅ ፋንታ በጥፋቱ ቀጠለ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ከጭፍሮቹ ጋር ሆኖ ከሰማይ ተባረረ።

“አንተ የንጋት ልጅ አጥቢያ ኮከብ ሆይ (ሉሲፈር) እንዴት ከሰማይ ወደቅህ? ወደ ሲኦል ወደ ጉድጓዱም ጥልቅ ትወርዳለህ....። ” ኢሳ. 14፥12 -16

ሰይጣናዊ መንፈስ (እርኩስ መንፈስ) ከሰማይ ወደ ምድር እንደገባ፥ በእርኩስ መንፈስ ሕያውነት የተወለዱ የሰይጣን ልጆችም በምድራችን በዝተዋል። እነኚህም - በሰይጣናዊ ልባምነት በምድር ለብዙ ዘመናት የቆዩ ጋኔሎች፥ ጂኒዎች፥...ወዘተ. ናቸው።

ማንነታችንን የሚገልጸው ጥሩው መንፈሳችን ከሆነ፥ እርሱን ከእግዚአብሔር ጋር እናገኘዋለን። ማንነታችን የሚገልጸው መጥፎው መንፈሳችን ከሆነም፥ እርሱን ከሰይጣን ጋር እናገኘዋለን።

“ ከዚህም በኋላ በግራው ያሉትን እንዲህ ይላቸዋል፡- እናንት የተረገማችሁ ለሰይጣንና ለመልእክተኞቹ ወደተዘጋጀው ወደ ዘለአለም እሳት ሂዱ።” ማቴ. 25፥ 41

የመንፈስ ትግል በመኖሩና የአለም ሕዝቦችም ታሪክ የመንፈስን ሥራ በአካላዊነት የሚያንጸባርቅ በመሆኑ፥ የሰዎችም ዝንባሌ ሳያስቡት ወደ ቅዱሱ ወይም ወደ እርኩሱ እንዲያዘነብል ይገደዳል። ይህም፥ የአለም የመጨረሻያው መጨረሻያ ሆኖ የሰይጣን ሥራ ሁሉ ቀጥ እስኪል ድረስ ነው። የዚያን ጊዜ እርሱ ወደሚሄድበት ወደተዘጋጀለት ሥፍራ ይሄዳል፤ እኛም ወደተዘጋጀልን ሥፍራ - ወደ አምላካችን።

ይህቺ አለማችን ለሁሉም ሰው አንድ ስላልሆነች፥ አንድ ሰው ስለአለም የሚሰጠው አስተያየት ጠባብና ግላዊ ነው የሚሆን። ሆኖም፥ አለማችንን በሁለት ከፍሎ - እንደ ሰማያዊ መንግሥት የመሰለ “ጻጻድቃን ” መኖሪያ፥ እንደ ገኃነምም የመሰለ የኃጥአን መኖሪያ፥ በሁለቱ ተቃራኒ አለሞች መካከልም ያሉ፥ ብዙ አለማትን የሚያካትት ከዚሁ ከምድራችን አንድ አለም አለ ማለት ይቻላል።

“ጻድቃን ” የተባሉት ጥቂቶች ናቸው። ስለዚህ በተቀሩት ሕዝቦች መካከል ምድራዊ - ገኃነማዊ - እሳታዊ አስተሳሰብ ተባዝቷል፤ በሚኖሩበት ሥፍራም ሰይጣናዊነት ነግሷል። በሃይማኖትም በፖለቲካም፥ በሁሉም ሥፍራ እየገባ መከፋፈልን የሚያመጣ ምንድነው?

ምድራዊ ክንውኖች ከኃጢአት ጋርም የሠራሉ - አንዳንድ የተዳፈኑ ኃጢአቶች ሲቀሰቀሱ፥ ሌሎችም ከሥር ሲያቆጠቁጡ ይታያሉ። ዘረኛነት እና የሃይማኖት አክራሪነት በመሠረታዊ ጠባያቸው ይመሳሰላሉ። ሁለቱም ከአድሎአዊነት ጠባይ ይመነጫሉ።

እግዚአብሔር ሰውን በአምሳሉ ፈጠረ፤ ከዛም በኋላ፥ ይህን መልካም ሥራ ለማበላሸት ሰይጣን በሰዎች አይምሮ ይጫወታል - ሰዎች ኃጢአትን እንዲሠሩ፥ ይታገላል። እግዚአብሔር ግን ፈጥሮ አልተወንም።

የአለም ሕዝቦች እውነቱ ሲገባቸው፥  በተሠሩት ኃጢአቶች ሁሉ እየተጸጸቱ ወደ ከፍተኛ ሰብአዊነት ይሸጋገራሉ። የዛን ጊዜ (ከዛም በኋላ) እግዚአብሔር ሰውን እንደገና ይፈጥረዋል። የዛን ጊዜ ሰይጣን ምንም ማድረግ አይችልም። “ተኩላ ከበግ ጠቦት ጋር ይቀመጣል፥ ነብርም ከፍየል ጠቦት ጋር ይተኛል.።” ኢሳ. ፲፩፡ 6

<u>የምድራዊ አድሎአዊነት - ዘረኛነት</u>

ይህ አለም ቆንጆ ሥፍራ ነው፤ ግን ለምድራዊነት ብቻ የሚያገለግል ብልጭልጭ ነገር በዝቶበታል። በዚህም ላይ የዘረኛነት ተውሳክ ሰውን ለሁለት ከፍሎ በአንድ አለም ውስጥ ሁለት አለም ያለ አስመስሎታል።

የምድር ሰዎች ሁሉ (ጥቁር፥ ነጭም ሆነ ቢጫ) የጋራ ኑሮአቸው ተደማምሮ እኮ ነው ለሰብአዊነት አንድ ወጥ እድገት የሰጡት። በአንድ ዘር ውስጥ ግለሰቦች - “ እኛ ብቻ ነን ለአለም ሕብረተሰብ ሁሉ እድገት ያመጣን... ” እያሉ በራሳቸው ሲኩራሩ፥ የዛን ጊዜ ዘረኛነት ተቀሰቀሰ ማለት ነው።  እንዲህ አይነት ጠባብ አመለካከት ያለው ሰው - ተመጻዳቂ፥ በዘሩ የሚመካና የሚኮራ ስለሆነ፥ ዘረኛ ይባላል።

የዘረኛነት ኃጢአት ከክርስቶስ በፊት ጀምሮ ይሠራ ነበር። ሆኖም ከፍተኛ ደረጃ የደረሰው በሁለተኛው የአለም ጦርነት ወቅት ይሆናል።  ከዛን ጊዜ ጀምሮ እንዲህ አይነቱ ኃጢአት በአጠቃላይ በአለም ዙሪያ ተሠርቶ ወደማለቁ የተጠጋ ይመስላል። ሆኖም፥ ባሁኑ ጊዜ እንደ ጥንቱ የአለም ጦርነት መቀስቀሺያ ሊሆን ባይችልም፥ በአንዳንድ ሥፍራዎች አንዳንድ ግለሰቦችን እያጠቃ ብዙ ጉዳት አድርሷል።

የአንድ ሰው ሰብአዊ መብቱ -  የግለሰቡን ዘር፥ ሃይማኖትና ጾታ የሚያካትት በመሆኑ እዚህ እኛ በምንኖርበት (ሰሜን አሜሪካ - ካናዳ) አካባቢ ዘረኛነት በሕግ የተወገዘ ነው። ሆኖም፥ አንድ ዘረኛ በቀን ተቀን ግንኙነት ውስጥ የሰብአዊ መብት ተጻራሪ የሆነው አስተያየቱ በየጊዜው ቀስ በቀስ ወደሌላው ሲወረወር፥ ሰውን በድንጋይ ከመውገር አይተናነስም። ከተዛባ አስተሳሰብ በመነጨ ትችትም ቢሆን፥ አንድ ዘረኛ ሌላውን በነገር ያቆስለዋል።

አርቆ ካለማሰብ፥ የኋላ ቀርነትና የተዛባ አመለካከት የተነሳ ዘረኞች በአለም ዙሪያ መጥፎ ባህሬአቸውን በሚገልጡበት ጊዜ ሁሉ፥ በነርሱ መጥፎነት ክፉኛ የሚጎዱ ብዙዎች ናቸው።

“ጠላትነቱን በተንኮል የሚሸሽግ፥ ክፋቱ በጉባኤ መካከል ይገለጣል። ጉድጓድን የሚምስ ይወድቅበታል፤ ድንጋይንም የሚያንከባልል ይገለበጥበታል።” ምሳሌ 26፡26 - 27

ሥጋዊ ኑሮአችንን ከሚያስጨንቅብን ከአድሎአዊ ጠባዮቻችን አንዱ - የምድራዊነት አንዱ መለዮ የሆነው ዘረኛነት - የቀን ተቀን የፈረንጅ አገር የሩጫ ኑሮአችን የይይስሙላ ሆኖ እውነተኛውን የምንጠባበቅ አስመስለን። “ እኔ በምድር ላይ መጻተኛ ነኝና፥ እንደ አባቶቼም እንግዳ ነኝና ወደማልመለስበት ሳልሄድ አርፍ ዘንድ ተወኝ።” መዝ. 39፡13

በሄድንበት ከተማ ሁሉ በየመንደሩ እየዞርን ቤት ስንፈልግ - ለኛ የሚስማማ ጎረቤት እንፈልጋለን። ላገሩ ባዳ፥ ለሰው እንግዳ ሳይኮን፥ ተደላድሎ የሚኖሩበት አገር ከወዴት ይገኛል? በአለም ያሉ ከተሞችን በሙሉ እየዞርን ብንኖርባቸው፥ በሁሉም ሥፍራ አንድ የሚጎድል ነገር ይኖራል። መንፈስ አካላዊ ጠባዮችን ተከትሎ አይሄድም፤ የሚያምር ሁሉ ወርቅ አይደለም።

ወይ ጉድ! የሰውን ክፋውን ሳያዩ የሚኖሩበት አገር የት ይሆን? አንዳንድ ሰዎች በፍርኃት ሳይሆን፥ እንዲሁ የሰውን ክፋውን ላለማየት ሲሉ ይሸሻሉ፤ ይደበቃሉ፤ ከሰው ተነጥለው ይኖራሉ፤ ይሰደዳሉ። “ የሰባ ፍሪዳን ጥል ካለበት ሥፍራ ከሙብላት፥ የጎመን ወጥ በፍቅር ሙብላት ይሻላል።” ምሳሌ 15፡17

ይህች አለም አንድ ወጥ እንዳትሆን፥ እግዚአብሔር ሆነ ብሎ “ለምክንያት” ፍጥረታትን ዥንጉርጉር አድርጎ በመፍጠሩ፥ የሰው ዘር የተለያየ መልክ አወጣ። ይህ ተፈጥሮአዊ ቁንጅና - መደሰቻ፥ የእግዚአብሔርን ሥራ ማወደሻ እንጂ፥ ሰውን ከሰው የሚያጣላ መሆን አልነበረትም። የሰው ዘር እንደ አበቦች ቀለም መለያየት እንደ አንዱ የተፈጥሮ ቁንጅና መቆጠር ሲገባው፥ የቆዳው ቀለም የጠቆረ፥ ጸጉሩም የከረደደ፥ ከአንድ ነጭ - ባለ ጸጉረ ብዥት፥ ወይንም ቢጫማ ቀይ ሰው የጎላ ልዩነት ቢታይበት፥ ይህንን ልዩነት መካድ የተፈጥሮን ቁንጅና እንደ መካድ፥ የእግዚአብሔርንም ሥራ እንደ ማቃለል ይቆጠራል።

የእግዚአብሔር ፍጡር የሆነችዋን ጥቁር ኢትዮጵያዊት ለምን ሙሴ አገባት ብላ የሙሴ እህት ስለተናገረች ብቻ እግዚአብሔር ተቆጥቶ ለምጻም እንደ አደረጋት (ኦሪት ዘኁልቁ 12) - በአፈጣጠር እገሌ ከገሌ ይበልጣል ብሎ መናገር በእግዚአብሔር ሥራ ውስጥ ጣልቃ መግባት፥ እርሱንም ማስቆጣት መሆኑን ያመለክታል።

ትዳር ይዣለሁና ስለውጪው አለም ሳልጨነቅ ከራሴ ቤተሰብ ጋር ብቻ ደስ ብሎኝ እንድኖር የሚያደርገኝን እያሰብኩ እኖራለሁ ማለት አልተቻለም። ባጠቃላይ፥

ይህች ምድርና በውስጧ የሚሠራው ሁሉ የሚያስጠላ ነው ባይባልም፥ አልፎ አልፎ የሚታየው ዘረኛነት በጣም ያሳዝናል፤ ያስፈራልም።

እኛም አዎንታውያን ስለሆን፥ የበጋ፥ ክረምት፥ በልግና ጸደይን መለዋወጥ እየተመለከትን፥ የምድር ክፋቶችና ደግነቶችም እንዲሁ የሚፈራረቁ ናቸውና፤ ምንም ይሁን ምንም እንኑርበት በማለት ቆይተናል። ሆኖም፥ በዘር ልዩነት ሳቢያ፥ በየጊዜው ከመካከላችን ስነአይምሮአዊ ድንጋጤ ውስጥ የሚገቡ ወንዶችና ሴቶች ወገኖቻችን ብዙዎች መሆናቸውን ስንገነዘብ መንፈሳችን ይታወካል።

የሰውን ልጅ እንስሳዊ ጠባይ መንፈሳዊነቱ እየሸፈነለት ነው እንጂ፥ ያ መንፈሳዊነቱ ባይኖር (ቢሰወር፥ ቢጠፋ፥ ቢዳከም) እንስሳዊ ጠባዩ ቁልጭ ብሎ፥ በግልጽና በጉልህ መታየቱ አይቀርም።

መከራና ጭንቀት የደረሰበት ጠባየ ለስላሳና የዋህ ሰው የሰዎችን እንስሳዊ ጠባይ ከገጽታቸው ቢመለከት፥ ሊደነግጥ (ስነአይምሮአዊ ድንጋጤ ውስጥ ሊገባ) ይችላል፤ የዚህም መዘዙ ብዙ ነው።

አንድ ሰው ሆድ የሚብሰው ለመኖር አስፈላጊ ከሆኑት (ከመብልና ከመጠጥ) ሌላ የጎደለበት ስለሚኖር ነው። ከጎናችሁ ያለ ሰው መንፈሱ ሲደነግጥ ዝም አትበሉ፤ አይዞህ፥ አይዞሽ እያሉ ማደፋፈር ያስፈልጋል።

ከብዙ ዓመታት ጀምሮ የተገፉ ወገኖቻችን እያሰብን የምድር ክፋቷን መናገሩ ጥሩውን መርሳት (መደበቅ) አይደለም፤ ግን በሄድንበት ዘርፈጥ ብለን ከመቀመጣችን በፊት አስቀድሞ ዙሪያችንን መመልከት ይበጃል። አድሎአዊነትን - የዘረኞች ተንኮልና ግፈኛነትን በጥሩነት ለውጦ ይህቺን ምድር ሰማያዊ ማድረግ (ወይም ማስመሰል) የሚቻለው እንዴት ነው ማለትም ተገቢ ነው።

ሰውን ሁሉ ምንጊዜም በአዎንታዊነት ብቻ መመልከት ብዙ ችግሮችን ይከላከላል። እኛ እንደ ንስር አሞራ ከላይ ሆነን በከፍታ የምንመለከት ብንሆን፥ ጥቃቅን ችግሮች አያስጨንቁንም። ሆኖም፥ ዘረኞች የሰውን እኩልነት እንዲማሩና እንዲያውቁ የማድረግ ኃላፊነት አለብን።

ክፋትና ጥላቻዎችን ሁሉ ችለን፥

አብረናቸው ሰነብትን፥ ለመቆየታችንም ዋጋ እየከፈልን፤

ኑሮን ለማሸነፍ፥ ከሁለት ከሦስት ቦታ ሠርተን፥

ከተራ የቀን ሠራተኛነት እስከ ሳይንቲስትነት ደረጃ ተሠማርተን፥

ከነጭ በልጠን እንዳንታይ እየተኮረኮምን፥

ሥጋችንን፥ አይምሮአችንንም አድክመን....፤

ግን ምንድነው ዋስትናው - ይህ ኑሮአችን፥
ምንጊዜም እንግዳ - ባይተዋር መሆናችን።
በገዛ ኃጢአታችን አልጠቆርንም፥
እግዚአብሔር እኛን ከነጭ በታች አድርጎ አልፈጠረንም።
በሰው ዘር ውስጥ ሁሉ ያለ የሰብእነት ምልክት፥
እንዲህ ሲዋረድ በዝቅተኛ አመለካከት፥
የአለም ሕዝብ ተጎድቷል በዚህ ወገናዊ ኃጢአት፤
ግን በመጎዳታችን እንድንነቃበት፥
በድካማችንም እንድንከብርበት፥
ካለማቋረጥ በመበርታት - ከፍ ብሎ - በልጦ ለመታየት ጥረት፥
ይህ ብቻ ነው የኛ ምርጫ በእውነት።

ሰው በሃይማኖታዊ ፍልስፍና የተራቀቀው፥
በተፈጥሮውና በኑሮው፥ የራሱ እውነት ሲርቀው፥
የአካላዊነት (ሥጋ) ጠባዩ አይኑን ሲያሳውረው፥
እርስ በርሱ መተዋወቅ እንኳን ሲያቅተው።
ግላዊና ማህበርዊ አስተሳሰቡ፥
ሃይማኖቱ (እምነቱም) ተለያይተው፥
ከፋቶች ሁሉ በያይነቱ ተደማምረው፥
ተስፋ በመቁረጥ - ሁሉን ነገር እርግፍ አድርጎ ሲተወው፥
ከጤንነት እብደት ሲሻለው፤
ልዩነቶች ጥላቻን ሲፈጥሩ - እጅግ በጣም ተካረው፥
ጠብና ጭቅጭቅ ወደ ሞት ሲመራው።
ይህን ሁሉ ማሰብ ያስጠላል፤
ከመታየት መደበቅን ያስመኛል።
አንዱን ካንዱ ማበላለጥ፥
በልብስ፥ በሃብት፥ በመልክ - በውጫዊነት፥
የተውነው መስሎን ነበር ካገር ቤት፥
ዝቅ ብሎ በመታየት መጠላት።

እዚህም ቢሆን ፈረንጅ አገር፥
ሰው ሰርቶ በድካሙና በወዙ ከሚኖርበት፥
ተጠናክሯል እንጂ አልጠፋም - ልዩነት በዘረኛነት።
ዘመኑ የፈጠረውን፥ ኮትኩቶ ያሳደገውን፥
ይህን ጠባይ - ልዝብ ሰይጣናዊነት፥
ማነው የሚያጠፋው? እንዴት?
ምንድነው ይህ የሰው ፍጥረት?
ቢያጥቡት የማይጠራ ውስብስብ አይነት።

ለዚህ ላፈር ክምር፥ ጉርብጥጥ ሰውነት፥
ግልጋሎቱ ለመሬት፥ ጥቅሙ ለምድራዊነት፥
ምንም አይረባንም በሥጋ ላይ ትኩረት፤
በገላችን አንኩራራበት፤
በመልካችን አንመካበት።
እንደ ዛፍ ቅጠል ከሚረግፈው፥
ዘላቂ መንፈሳችን ነው የሚሻለው።

እኛ ካገራችን የወጣነው - ወገኖቻችን በድህነት ውስጥ ተነክረው ሳለ፥ እኛ ከነርሱ ተለይተን የተዝናና ኑሮ ከምንኖር ይልቅ፥ ሰዎች አምረው፥ አጊጠው፥ እየተደሰቱ ከሚኖሩበት ሥፍራ ብንኖር ይሻላል በማለት አይደለም፤ መሰደዳችን ያገራችን ሁኔታ የሚያስረሳ፥ አዲስና ደስተኛ የኑሮ መድረክ የሚከፍትልን አለመሆኑን ጥንትም የምናውቀው ጉዳይ ነውና።

ፈረንጅ አገር የመጣነው፥ ይህችን አጭር የሥጋ ሕይወታችንን ዘላለማዊ አስመስለን ልናጣጥማት ብለን ሳይሆን፥ ለጊዜው ከዛ ከተነከርንበት የፖለቲካ ቀውስ ውስጥ ራሳችንን ለማውጣት፤ በቅጥያም፥ በዝተንና ተባዝተን ምድራዊ ግዳጃችን ለመፈጸም ነበረ። በየትኛውም አቅጣጫ ሲታይ፥ የዚህ አለም ነገር “ ሁሉ ” ፍሬ ከርስኪ ሆነብን። “ከፀሐይም በታች የተሠራው ሥራ ሁሉ ከብዶኛልና፥ ሕይወትን ጠላሁ፤ ሁሉም ከንቱ ነፋስንም እንደመከተል ነው።” መክብብ 2፡17

የሰብአዊነት የመቆያ ምሥጢር ከሰው ልጅ አጠቃላይ ጠባይ (ከሥጋዊነቱና ከመንፈሳዊነቱ አንጻር) ጋር እንጂ፥ ለብቻው በዘረኛነት ጠባይ ብቻ የሚወሰን አይደለም። ወደፊት በምድር ላይ የጋራ ችግር ሲበዛ፥ ሰዎች ከምንጊዜውም የበለጠ ካልተቀራረቡ በስተቀር፥ የጋራ ችግር በተናጠል የማይቃለል ይሆናል። ስለዚህ፥

ለወደፊት ሕዝቦች ሁሉ በአንድ ላይ እየሠሩ እንዲኖሩ፥ በአንድነት እንዲያስቡም የሚገደዱበት ሁኔታ ይፈጠራል (ተፈጥሯልም)። ታዲያ፥ አብሮ እየኖሩ፥ እየተለዩም እንዴት ይዘለቃል?

መጪውን መጥፎ ጊዜ እንዴት እናልፈዋለን? ከአገራችን፥ ከወገኖቻችን ተለይተን በአለም ዙሪያ የመበተናችን ምሥጢር ምንድነው? የሰብአዊነትን የመቆያ ምስጢር ማን ይረዳዋል?

የኛ ልጆችና የልጅ ልጆቻችን በያሉበት ቀርተው፥ አገራችን የሚሉትን የባእድ አገር እየሠሩ በማሳደግ ላይ ስለሚቆዩ፥ የአለም ማህበራዊ፥ ኢኮኖሚና የፖለቲካ ሁኔታ ይሻሻላል። እኛ ተሰደን በተሰደድንበት ሌላውን አገር ማሳደጋችን (የአለም ስደተኞች ሁሉ ይህን ማድረጋቸው) አጠቃላይ ሉላዊ (global) ግንባታ ነው። ታዲያ በዚህ ሉላዊ ግንባታ አገራችን ኢትዮጵያ ምን አተረፈች? በያለንበት ልጆቻችን እና የልጅ ልጆቻችን አባቶቻቸውና አያቶቻቸው የሚኖሩበትን አገራቸውን ትተው ሌላውን አገር ሲያሰለጥኑ፥ አገራችን ኋላ ቀር ሆና ትቅር?

እነኛ ያስጠጉን ሰዎች ግን - “ተቸግራችሁ ስለመጣችሁ፥ ተቀብለን ስለረዳናችሁ (ከችግር ስላወጣናችሁ) ምስጋና ይገባናል...” ይላሉ እንጂ፥ እናንተ አገራችን ስላሳደጋችሁልን (በናንተም ሥራ የኢኮኖሚ እድገት ስላገኘን) ለናንተ እና ለመጣችሁበት አገር ምስጋና ይገባል አይሉም።

ምንም አይደል። ለኛም የምንኖርበት አገር (የባእድ አገር ቢባልም) አገራችን ነውና፤ ምስጋናውም ይቅር። ደግ መንግሥት እና ደጋግ ሕዝቦች ተባብረው፥ ስደተኞችን ረድተው በማስጠጋታቸው፥ መልካም ለሆነው መንፈሳቸው ምስጋና ይገባል።

የሰዎች ደግነት ክፋትን መደበቅ ሲያቅተው አቢይ ችግር እንደሚከሰት ሁሉ - እራስን ከፍ ከፍ ማድረግና ሌላውንም በዝቅተኝነት መመልከት በተለመደበት ሥፍራ ሁሉ፥ ሰውን ማክበር፥ ትህትና፥ ሰላምተኛነት፥ እራስን ከሌላው ዝቅ በማድረግ ለሌላው ክብር መስጠትና አለመስገብገብ፥ ባጠቃላይ ሰውን ጥሩ የሚያሰኙ ጠባዮች እንደ መጥፎ ተቆጠረ (ያሳዝናል)።

ከሰማይ ሰማያት ወርዶ፥ ራሱን ከሰዎች በታች ዝቅ አድርጎ፥ በበረት የተወለደ ኢየሱስ ክርስቶስን ለሚከተል አንድ ክርስቲያን፥ እራስን እያተለቁ ሌላውን ማሳነስ እንደ ትልቅ ኃጢአት ነው።

ጻድቃንን የሚመስሏቸው ሁሉ ሕይወታቸውን ከመንፈሳዊነታቸው ጋር አጣጥመው ሲኖሩ እራሳቸውን ዝቅ ያደርጋሉ። ግን አንድ ሰው ራሱን ዝቅ ሲያደርግ፥ ሌላው ሰው ደግሞ የባሰ ዝቅ ያደረገው እንደሆነ፥ መሬት ቆፍሮ ከነ ነፍሱ እንደቀበረው

ያህል ይሰማዋል። ራሳቸውን ዝቅ የሚያደርጉ ትሁታን ራሳቸውን ከፍ ከሚያደርጉ እብሪተኞች ጋር እንዴት መኖር ይችላሉ?

የምድርን ለምድር የሰማይን ለሰማይ ከፋፍሎ በመመልከት ብቻ፥ ይህቺን አድሎአዊ አለም ሰማያዊ ማድረግ (ወይም ማስመሰል) አይቻልም። የዘረኛነት አመጣጡ እንዴት ነው ከማለት ይልቅ - "በምድር የሚሠራ ክፋት መነሻው ምንድነው ? " ማለት ይቀላል።

በዘር የሚቀሰቀስ ጥላቻ መሠረቱ የምድራዊነት መለዮ ጠባይ እንደመሆኑ ሁሉ፥ በመንፈሳውያን መካከል ምንም አይነት የዘር ልዩነት ሊኖር አይችልም።

ምድራዊነት የቆዳ ቀለምን ያያል፥ መንፈሳዊነት ግን ከቆዳ ቀለም ዘልቆ የሰውን ጥሩነት ይመለከታል። ምድራዊነት የሰውን አስተሳሰብ ወደ አካላዊነት (ውጫዊነት) እንዲያዘነብል ያደርጋል - የሰውን ዘር በቆዳ ቀለም፥ በቁመና፥ " በቁንጅና " አንዱን ከሌላው አስበልጦ ያያል። መንፈሳዊነት ግን የሰውን አስተሳሰብ ከምድራዊ መበላለጥ ያወጣዋል፤ በሰዎች መካከል የሚኖር ግንኙነት ሁሉ በእኩልነትና በፍቅር ላይ የተመሠረቱ እንዲሆን ያደርጋል።

እግዚአብሔር በፈጠረው ሰው መካከል ልዩነት የሚፈጥር ምቀኛ ሰይጣን ነው እንጂ ሰው አይደለም። አንዳንድ ዘረኞች የአስተሳሰባቸው ዝንባሌ ጥቁርን ሰው እንደ ዝቅተኛ አድርገው እንዲመለከቱት ቢያደርጋቸውም፥ ይህ ከሰይጣን የመጣ መሆኑ የገባቸው ከዚህ ምድራዊ አመለካከት ተላቀው የሰውን ዘር ሁሉ እኩል ሲወዱ ይታያል።

" እግዚአብሔር ለሰው ፊት እንዳያዳላ፥ ነገር ግን በአህዛብ ሁሉ እርሱን የሚፈራና ጽድቅን የሚያደርግ በእርሱ የተወደደ እንደሆነ በእውነት አስተዋልሁ።" የሐዋ. ሥራ 10፡34

በፈረንጅ አገር የቅዱስ ፓትሪክ ቀን ሲከበር፥ እርሱ ማን እንደሆነ በመገንዘብ፤ በሥራውም እርሱን ለመምሰል ከመሞከር ጋር ቢሆን ይሻል ነበር።

ቅዱስ ፓትሪክ እራሱን ከሰው በታች ዝቅ ሲያደርግ እንዲህ አለ - " እኔ ፓትሪክ ነኝ - ኃጢአተኛ፥ ያልተማርኩ፥ በሰዎች የተጠላሁ። አባቴ ቄስ ነው፤ እኔ ግን እግዚአብሔርን የማላውቅ ኃጢአተኛ ሆኜ፥ በአስራ ስድስት ዓመቴ ከብዙ ሺህ ሰዎች ጋር በባርነት ከብሪታንያ ተማርኬ ወደ አየርላንድ ተወሰድኩ።

የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ስላላከበርን፥ ቄሶቻችንም የሚነግሩንን ባለመስማታችን ተበተን። እኔም ፓትሪክ ተሰድጄ፥ ዝቅተኛነቴ ጎልቶ ከሚታይበት የባእድ አገር መጣሁ። ነገር ግን በወጣትነቴ የሠራኋቸውን ኃጢአቶቼን ሁሉ

በማስታወስ፥ በኃጢአቶቼ ተጸጽቼ፥ ተናዝዤ፥ ይቅርታ ጠይቄ፥ በሙሉ ልቤ ወደ እግዚአብሔር እቀርብ ዘንድ አይኖቼ ተከፈቱልኝ። ስለዚህ፥ ክፉና ደጉን ባልለየሁበት በድንቁርናዬ ሁሉ ሲጠብቀኝ ለነበረ፥ አሁንም ለሚጠብቀኝ  አምላኬ ታላቅ ውለታ አለብኝ።"

ቅዱስ ፓትሪክ  በእግዚአብሔር ያለውን የራሱን እምነት ካረጋገጠ በኋላ፥ ይህን እምነቱን በባርነት ከተወሰደበት አገር ለማስተማርና ለማሳወቅ ሲል እንዲህ አለ።

"ኃጢአተኛም፥ አላዋቂም ብሆን - "ውሸትን የምትናገር አፍ የገዛ ነፍሷን ታጠፋለች.. " ብሎ በዳዊት መዝሙር በተጠቀሰው መሠረት፥ የልቤን እውነት በፍርኃት እጽፋለሁ። በዝቅተኛ እውቀቴ የምጽፈው የሰዎች መሳቂያና መሳለቂያ እንዳይሆንብኝ ስፈራ እስካሁን ቆይቻለሁ። አሁን ግን በወጣትነቴ የሠራኋቸውን ኃጢአቶች በስተርጅና ለማካካስ መጣደፍ ይኖርብኛልና፤ እንደምሁራን መጻፍ ባልችልም፥ አይምሮዬና መንፈሴ የሚፈቅድልኝን ያህል እጽፋለሁ። የልቤም ምኞት ሰዎች ለእግዚአብሔር ምስጋና ያቀርቡ ዘንድ ስለሆነ፥ ከመናገር አልቆጠብም..። "[40]

በተመጻዳቂዎች ፊት ከሰዎች በታች በዝቅተኝነት ሲታይ የነበረ ይህ ታላቅ ሰው ቅዱስ ሰው እንዲባል ያደረገው መልካሙ ሥራው ነው። ብዙ ሰዎችን አስተምሮ፥ በአብ፥ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቀ ክርስቲያኖች አደረጋቸው፤ ብዙ የመንፈስ ልጆችንም አፈራ።

ጣኦት አምላኪ የነበሩት የአየርላንድ ሰዎች ክርስቲያኖች ሆነው፥ የንጉሦቻቸው ወንዶችና ሴቶች ልጆች እንኳን በድንግልና እየመነኮሱ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ሆነዋል። ቅዱስ ፓትሪክም በመንፈስ ቅዱስ ከወለዳቸው ልጆቹ መለየት ስላልቻለ፥ ወደ አገሩ ወደ ብሪታኒያ ተመልሶ ከገዛ ዘመዶቹ ጋር ሳይቀላቀል፥ እስከ እድሜው ፍጻሜ ድረስ አየርላንድ ኖረ።

ሰዎች የቅዱሳንን ታሪክ እያነበቡ፥ በተግባራቸውም ቢመስሏቸው ምናለበት? ጻድቃን ዘረኞች ሊሆኑ አይችሉም፤ የጻድቃን ሁሉ አስተሳሰባቸው አንድ አይነት ስለሆነ፥ በተግባርም አንዱ ሌላውን ይመስላል። ለምሳሌ፥ እማሆይ ቴሬዛ ትውልዳቸው አልባንያ፥ ዜግነታቸው ህንዳዊ፥ እምነታቸው ካቶሊክ፥ ልባቸው የክርስቶስ። ዘወትር በማለዳ ይነሱና፥ ቅዱስ ቁርባን ከተቀበሉ በኋላ መቁጠሪያቸውን ይዘው ወደ ድሆች መንደር ይገባሉ። ከዚያም የህጻናትን ቁስል ሲያጥቡና ሲያክሙ፥ በረሃብና በበሽታ የማቀቁትን፥ የደከሙ ሽማግሌዎችን እና አሮጊቶችን ሲንከባከቡ ያመሻሉ። የምንኩስና እድሜአቸውን በዚህ አይነት ፈጹት።

---

[40] ከቅዱስ ፓትሪክ ድረ ግርጽ

በግለሰብ፥ በሕብረተሰብና በአህጉር ደረጃ አንዳንዶች ምድራዊነት ሰምሮላቸው ኑሮአቸው ተሻሽሎ፥ በአንጻሩም ሌሎች ምን ቢታገሉና ቢጥሩ፥ ምንም አልሆን ሲላቸው እናያለን። ይህ የሆነው ምድራዊነትና መንፈሳዊነት ተጻራሪ ስለሆኑ፥ አንዳንድ ሰዎች ለምድራዊነት፥ ሌሎችም ለመንፈሳዊነት የተመደቡ በመሆናቸው ነው ብሎ መደምደም አይቻልም። የሁላችንንም እድል የምትወስን ይህች ጠባብ ምድራችን የግድ ምድራዊ ሁኑ ብላ አላስገደደችንም። በራሳችን መንፈሳዊነታችንን መቀስቀስና ማጎልቅስ እንችላለን። ሁላችንም ከልብ ከጣርን፥ ይህቺን አድሎአዊ ምድር ሰማያዊ ማድረግ (ባይሆንም ማስመሰል) አያቅተንም።

ደግ ደጉን ብቻ እያሰቡ፥ በሳቅና በጨዋታ ማሳለፍ ነው ደጉ። በሰው ውስጥ የሚኖር አዎንታዊነት ዘረኛነትን ይሠብራል። መጥፎውን ጥሩ የሚያደርግ የተደበቀ መልክ አለን።

ካለ በቂ የቋንቋ ችሎታ በአዎንታዊነት ብቻ የሚግባቡ ሰዎች አሉ። እነርሱ የሰውን መጥፎነቱን በአዎንታዊነት መደምስስ የተቻላቸው ናቸው። ይህ የአሁኑ የሰው ዘር ጠፍቶ ሌላ አዲስ የሰው ዘር እስኪተካ ድረስ፥ ለዚህ አንድ የሰው ዘር ሕብረትና አንድነት ያልተቋረጠ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል።

በሁሉም ሰው ዘንድ ያለውን ጥሩነት እያየን እንጂ፥ መጥፎነቱን ብቻ ከተመለከትነው ኑሮአችን በከንቱ አሉታዊነት ይበረዛል። የተጨቆኑትን ሕዝቦች ሁሉ እግዚአብሔር ብድግ ሲያደረጋቸው፥ ሰብአዊነትም በአንድ ሰማያዊ መልክ ሲካተት፥ መጨረሺያው መጥፎ አይሆንምና፤ መጥፎ መጥፎውን በመመልከት ብዛት ኑሮ እንዳይበላሽ ከእግዚአብሔር መንፈስ አንራቅ።

በአለም ሁሉ እግዚአብሔር አለ፤ በጠፈርም ሁሉ እግዚአብሔር አለ። በቤት ውስጥ እግዚአብሔር አለ። ከውጪ እግዚአብሔር አለ። በሁሉ ሥፍራ እግዚአብሔር አለ።

ዘረኞች ቢያሳንሱህ(ሽ)፥ በሥራ ቦታ ጥቃት ቢደርስብህ(ሽ)፥  
በጾታ ልዩነት ውርደት ቢደርስብህ(ሽ)፥  
በሃይማኖት ልዩነት፥ በሃብት፥ በእውቀት መበላለጥ፥  
በቋንቋ፥ በባህል ልዩነት ጥቃት ቢደርስብህ(ሽ)፥  
ብቸኝነት ቢሰማህ(ሽ)፥ ምንም ሃዘን ቢገባህ(ሽ)፥  
ምንም ቢከፋህ(ሽ)፥ አጽናኝ መንፈስን የሚልክልህ(ሽ)፥  
እግዚአብሔር አለልህ(ሽ) - አምላክ አለልህ(ሽ)።

ለወደፊት - ልዩነት በመንፈሳዊ ፍቅር ሲካተት፥

ሰው ሁሉ በአንድነት፥ ለፈጣሪው ሲሰግድ በታላቅ እምነት፥
እውነትም ወገግ ብሎ ሲታይ በእምነት፥
አ ! ሰላም! ....ሰላም ይምጣ ለሁላችን፥ ሰላም ይሁን በያለበት።
የእግዚአብሔር ፈቃድ ይደርብን፥
ሰይጣናዊነት ይቀተል  በጥሩነታችን።
እንዲሁም አያቋርጥ መተሳሰባችን፥ መተዛዘናችን፥
ከነልዩነቶቻችን፥ እንዳይቀንስ ፍቅራችን፤
እንዳይወቃቀሱ መንፈሶቻችን።
ጠባያችን እና እውቀታችን መጣሊያ እንዳይሆን፥
በማንኛውም ሥፍራ ቢሆን መንፈስ ቅዱስ ይክበበን፥
ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ የእግዚአብሔር ስም የተመሰገነ ይሁን።

<u>ስለ አለማችን ምድራዊና መንፈሳዊ ገጽታዎች</u>

ከጥንት ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ አንዳንድ ሰዎችና አንዳንድ አካባቢዎች ከአካላዊ ሕይወት ይልቅ መንፈሳዊ ሕይወት ያመዝንባቸዋል። አንዳንዶቹ ደግሞ ከመንፈሳዊ ሕይወት ይልቅ አካላዊ ሕይወት ያመዝንባቸዋል። ይህ ሁኔታ ከትላንት ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ እንዴት እንደነበር፥ ከሥጋዊ አለም ውጪ የሚከናወኑትን በአይነ ሕሊና እየተመለከትን፤ ለጥቃቅን የማይታወቁ ጉዳዮች ሳንጨነቅ፥ እጅግ ቅልል ባለ መንገድ ለመገምገም እንነሳ።

በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ብዙ ከግንዛቤአችን ውጪ የሆኑ ጉዳዮች አሉ። የሚታወቀውን በጥቅሉ እያስቀመጥን፥ ይህን የማይታይ ታሪካዊ ክስተት ባጠቃላይ አብረን እንመልከት።

ሰይጣን ምድራቱን በእርኩስ መንፈስ ሲያጣብባት፥ በየቤቱ ሲገባና ሲያስጨንቅ፥ ይህን የዋህ - ሰው የተባለ ፍጥረት - ሥጋ በመልበስም ሰው መስሎ ሲያሳስት፥ እኛ ለራሳችን ጥበቃ ብለን የመንፈስን ሥራ እናውራ -  በምድራችን የነበረውን - ያለውንና የሚቆየውን ለማየት፥ እንዳው  ዘና ብለን እንነጋገር በነፃነት። አንባቢ የትላንትናውን ገምግቅህ(ሽ)፥ የዛሬውን አይተህ(ሽ)፥ የነገውን አንተው(ቺው) ፍረደው(ጂው)።

አዳምና ሔዋን ኃጢአት በመሥራታቸው ከእግዚአብሔር ራቁ። ከእግዚአብሔር መራቅ፥ ኃያልና ፍጹም አምላክን አለመታዘዝ፥ አለማክበርና

አለመፍራት፥ ይህ ራሱ ትልቅ ፍዳ፥ ትልቅ ኃጢአት ነውና፤ ሰብአዊነት ለብዙ ሺህ ዘመናት የኃጢአት ተሸካሚ ሆነ።

ከብዙ ጊዜ በኋላ - የሰው ልጅ ፈጽሞ ከሰይጣን ተንኮል እንዲርቅ፥ አስርቱ ትእዛዛት በበረሃ ውስጥ ለእስራኤሎች ተሰጡ፤ ግን አሁንም እርኩስ መንፈስ እየመጣ፥ እስራኤሎችን ይከብባቸው፥ በየቀኑም ያስታቸው ነበር። በየጊዜው እያታለለና በተንኮሉ እየቆሰቆሰ፥ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እንዳይፈጽሙ ያደርጋቸው ነበር።

ከእግዚአብሔር መራቅ፥ ዘለአለማዊና ኃያል፥ ፍጹምና ትእግስተኛ የሆነ አምላካችንን አለመታዘዝ፥ አለማክበርና አለመፍራት፥ እርሱ የሚለውንም የአለመስማት ውጤቱ ጥሩ ስለማይሆን፥ ከግብጽ ምድር የወጡት ሁሉ (ከበረሃ ከተወለዱት በስተቀር)፥ ከዛው ከበረሃ ሞቱ፤ ከዛውም ተቀበሩ።

እግዚአብሔር እስራኤላውያንን በሃዘኔታ ቀረባቸው፤ ስለተቸገሩ ሊረዳቸው፤ “እናንተ ልጆቼ ናችሁ..” እያለ ከጭንቀታቸውም ሊያጽናናቸው፤ ካካባቢው ሁሉ እነርሱ በቁጥር ትንሽ ስለሆኑ፥ በሌሎች ተጠቅተው ዘራቸው እንዳይጠፋ፥ መኖሪያ ሥፍራም እንዲያገኙ ሊረዳቸው፤ እርሱ በሚሰጣቸው መመሪያ መሠረት ወደ ከንአን ገብተው ለነርሱ መኖሪያ ሥፍራ አዘጋጅተው፥ ከሌሎች ሕዝቦችም ጋር ተጎራብተው እንዲኖሩ ፈለገ። እነርሱ ግን ከምድራዊ ስግብግብነት የተነሳ በራሳቸው ፈቃድ እየተመሩ ካላግባብ ጦርነት እየቆሰቆሱ ሌሎችን እየወጉ እነርሱም ያልቁ ነበር።

እስራኤላውያን ጦርነት ማድረግ ግዴታ ቢሆንባቸውና እግዚአብሔርም በጦርነቱ ቢረዳቸው፥ ተሸናፊዎቹ - “ እሺ በቃ አብረን እንኑር.. ” እስኪሉ ድረስ - አብሮ ለመኖር የሚያበቃ ስምምነት መሥርቶ በሰላም ለመኖር ነበር እንጂ፥ የሌላውን ዘር እያጠፉ ተንሠራፍቶ ለመኖር - ሃብትና ንብረታቸውን ቀምቶ ለራስ ጥቅም ለማዋል አልነበረም።

ወደ ከንአን ምድር የገቡትን የእስራኤል ልጆች ሰይጣን ስለ ምድራዊነት አስተማራቸው እንዲህ ብሎ - “ምድራዊነት ማለት እኔ ልኑር፤ ሌላው ይሙት ማለት ነው። ይህን የምድራዊነት ፍልስፍና በደንብ እንድታውቁ ለናንተ ለምወዳችሁ ልጆቼ የማስተላልፈውን ትምህርት በጥሞና አዳምጡ፡-

እናንተ ምድራውያን ናችሁ፤ የምትኖሩትም በምድር ላይ ነው እንጂ በሰማይ አይደለም። ከበረሃ ተንከራታችሁ ከሰውነት ውጪ ሆናችኋል። በምድር ስትኖሩ የሰውነታችሁን የደም ግባት የምታገኙት በምድር ከሚገኝ ምግብ - ከማርና ከወተት ነው እንጂ ከሰማይ ከሚበተን ዱቄት አይደለም። እስቲ ተመልከቷቸው ሌሎቹን ምድራውያን ሰዎች። እነርሱም እንደናንተ ሰዎች ናቸው። እንዲህ አምረው የሚታዩት ምድራዊነት ማለት እኔ ልኑር፤ ሌላው ይሙት መሆኑን በደንብ ስለተገነዘቡ ነው።

እናንተም ይህንን ፍልስፍና ዛሬ ካልተቀበላችሁና የሚበጃችሁን ካላደረጋችሁ በስተቀር ከዚሁ ማለቃችሁ ነው.....፡ ”

እንዲህ በተንኮለኛው ምክር በየጊዜው እየተታለሉ እስራኤላውያን ከፈጣሪያቸው ይጣሉ ነበር። ዳሩ ግን፥ ይህች አለም ጭራሽ ጨለማ ሆና እንዳትቀር፥ የቀደሙ ጻድቃን እና ነቢያትን ትምህርት፥ ምክር እና ታሪካቸውን እያጠኑ በልባዊ ግንዛቤ ያቀፉ ደጋግ እስራኤላውያን እና ሌሎችም ሕዝቦች ነበሩ (አሉ)። ይህች የምንኖርባት አለማችን ምድራዊ ብትሆንም፥ ዘልቆ የሚቆየው ሰማያዊነቷ ምንጊዜም ያለና የሚኖር መሆኑን አውቀናል።

ሥራው ብዙ ሰይጣን ምድርን የራሱ ለማድረግ ፈልጎ ሳለ፥ እንደ ኢዮብ ያለ ጻድቅ መኖሩ አስፈርቶታል። ይህስ ሰው ስለሆነ አያቅተኝም በማለት ሊተናኮለው፥ ታግሎ ሊጥለውና ደብድቦ ሊገድለው ፈለገ።

“እግዚአብሔርም ሰይጣንን ከወዴት መጣህ? አለው። ሰይጣንም፡- ምድርን ዞርሁአት በእርሷም ተመላለስሁ ብሎ ለእግዚአብሔር መለሰ።” ኢዮብ 1፡7

እኛ ሰዎች በእርኩስ መንፈስ እየተጎበኘን መሆኑ ግልጽ የመሆኑን ያህል፥ በምድር ለመንቀሳቀስም መብቃታችን፥ በእውነት አቸናፊ የሆነ የእግዚአብሔር ኃይል በውስጣችን ስላለ ነው። ይህንን በደንብ እንድናውቅ - ለኛ መማሪያ ይሆን ዘንድ፥ ኢዮብ በሰይጣን እንዲፈተን እግዚአብሔር ፈቀደ።

የኢዮብ ሃብቱ - ንብረቱ ቢወድም፥ ልጆቹ ሁሉ በሞት ቢቀጠፉ፥ ሰውነቱም በቁስል ደዌ ቢመታ፥ ኢዮብ ለእግዚአብሔር ያለው እምነትና ታማኝነት የማይበገር ሆነ። ሚስቱም፡-“ ..እግዚአብሔርን ስደብና ሙት አለችው።” ኢዮብ 1፡9

የኢዮብ ሚስት እንዲህ የምትናገር አይደለችም፤ እርኩስ መንፈስ በሚስቱ ውስጥ ገብቶ ተናገረ እንጂ። ከሚስቱ አፍ መጥፎ ንግግር በድንገት አፈትልኮ ወጣ እንጂ፥ የኢዮብ ሚስት መጥፎ ሴት አልነበረችም። “ይህን እንዴት ማወቅ ይቻላል? ”

በመልካሙ መንፈሷ እርሷም ሰይጣንን የታገለች በመሆኗ ነው የመጨረሺያውን የአቸናፊነት ድል ከባሏ ጋር የተቀዳጀችው እንጂ፥ እንደ ተናገረቺው ቢሆን ኖሮ አስቀድማ የምትጠፋ እርሷ ትሆን ነበር።

ሰይጣን አልሆነለትም፤ በኢዮብ መንፈሳዊ ጥንካሬ ተረታ። ለኢዮብና ለሚስቱ ምህረት ወረደ። የኢዮብ ሰውነት ከቁስል ደዌ ዳነ፤ ሃብቱም እጥፍ - ድርብ ሆኖ ተመለሰለት። ነገር ግን፥ ልጆቹ እንደጠፉ ቀርተዋል። ታዲያ ከዚያ በኋላ ኢዮብ ልጆቹን አጥቶ የሚኖረውን ኑሮ የሃብት መትረፍረፍ ያካክሰዋል?

የቀን ተቀን ኑሮአቸውን ለማስተካከልና ቤተሰቦቻቸውንም ለማስተዳደር ሲሉ ከሆድ እቃቸው ኩላሊታቸውን እያስወጡ የሚሰጡ ሰዎች እንዳሉ እናውቃለን። ታዲያ ሰይጣን የኢዮብን ልጆች ሁሉ ገድሎ ስለጨረሰ ተንኮሉን በተዘዋዋሪ በኢዮብ ላይ ፈጽሟልና፤ እግዚአብሔርን አሸንፎታል ማለት አይቻልም? ይባል ይሆናል። ግን፥ በመንፈሳዊና በሥጋዊነታችን መካከል የምድር ኑሮአችን የዘላለማዊው ሕይወታችን ቁራጭ መሆኑን - ከሥጋ መንፈስ ሙብለጡን ለመመልከት እንድንችል ነው ይህ ታሪክ የሚያስተምረን።

ኢዮብስ በሥጋው ተፈትኖ ፈተናውን ቢያልፍ፥ ሽልማቱ ለዘለአለም ደስታ፥ ከጠፉት ልጆቹ ጋር መቀላቀሉ ነበር እንጂ፥ ልጆቹ ተመልሰው ነፍስ ቢዘሩለት ኖሮ፥ ያቺ ምድራዊ ደስታ ለስንት ዓመታት ትዘልቅለት ነበር? ነገር ግን ኢዮብም የሚሄደው ወደ ሰማይ ነበርና፥ በልጆቹ ላይ ነፍስ መዝራትና ዳግመኛ በምድር እንዲኖሩ ማድረግ አላስፈለገም።

አዎ! ኢዮብስ በሥጋው ተፈትኖ ፈተናውን ስላለፈ፥ ለእግዚአብሔር ወግኖ፥ ተንኮለኛውን አቸንፎ ስለተገኘ፥ የተቀበለው ሽልማት ዘለአለማዊ ሕይወትና ደስታ ነው እንጂ፥ ምድራዊ ሃብት ብቻ አልነበረም።

በእውነት የኢዮብ ልጆች በሥጋ እንደጠፉ በመንፈስም ጥፍት ቢሉ ኖሮ፥ የዛን ጊዜ ሰይጣን አሸነፈ ይባል ነበር። ኢዮብ ያገኘውን ሽልማት የሚያውቅ የለም፥ ከራሱ ከኢዮብ በስተቀር። የኢዮብ ልጆች በሥጋ እንደጠፉ፥ በመንፈስም ጥፍት አለማለታቸውን ያውቅ ዘንድ፤ ለኛም ለአካላውያን ይገባን ዘንድ (ለሥጋዊ ትርጉም እንዲያመች)፥ ለኢዮብ ምድራዊ ሃብቱ ሁሉ እጥፍ ድርብ ሆኖ ተመለሰለት፤ በሞቱት ልጆቹ ምትክ ሰባት ወንዶችና ሦስት ሴቶች ተወልደውለታል (በምድራዊነቱ መጽናናትን እንዲያገኝ)።

ኢዮብ የእግዚአብሔርን አቸናፊነትና ሥልጣን በሰማይ እንደሆነ፥ በምድር ላይም እንዲሁ መሆኑን እየመሰከረ ኖረ። በዚህ አንድ ታሪክ፥ በምድራዊ ኑሮአችን ውስጥ የሚያብበው መንፈሳዊነታችን የወደፊት ወሳኙ ሕይወታችን እንደሚሆን፥ የሰይጣንም ሥራው ከእግዚአብሔር የመጨረሺያ ፈቃድ ውጪ እንደማይወጣ፥ የእግዚአብሔር ሥልጣን በሰማይ እንደሆነ በምድር ላይም መኖሩን ተማርን። የኢዮብ ታሪክ ለኢዮብ ብቻ አይደለምና፤ ሰይጣን መኖሩን አውቀን፥ እኛም እንደ ኢዮብ መንፈሰ ጠንካሮች እንድንሆን፥ የጀመርነውን የሰይጣን የተንኮል ሥራ ማውራት እንቀጥል።

ወደ ከንአን ምድር ከገቡት እስራኤሎች (ልጆቻቸውና የልጅ ልጆቻቸው) መካከል - እግዚአብሔርን የሚያከብሩና የሚፈሩትም እንኳን በዚሁ በእርኩስ መንፈስ እየተከበቡ በብዛት ተታለዋል - ለምሳሌ ታላቁ ንጉሥ ዳዊት እንኳን ሳይቀር።[41]

ሰይጣን ጥቂት ሰዎች አገኘ፤ እነኚህም ገና ከቀድሞው የክርስቶስ ያልሆኑትና የማይሆኑት ናቸው። ንጉሥ ዳዊት ግን ኃጢአትም ቢሠራ፥ ከሚወደው አምላኩ የሚለየው አልነበረም፤ የሰይጣን ኃይል በዳዊት የመንፈስ ኃይል ተረቷልና።

ከብዙ ጊዜ በኋላ፥ እስራኤላውያን ከተሰደዱበት ሥፍራ ሁሉ ቀስ በቀስ ከኢየሩሳሌም ገብተው ተሰባሰቡ። ሁሉም እንደ አንድ ሰው ሆነው፡- ይህን በናቡከደናጾር የፈረሰ ቤተ መቅደስ መልሰን እንገንባው በሚል ተስማሙ። የቤተ መቅደሱም መሠረት በተጣለ ጊዜ ታላቅ ደስታ ሆነ።

“ደስ ብሏቸው የሚጮሁትን ድምጽ፥ ከሕዝቡ ልቅሶ ድምጽ መለየት የሚችል አልነበረም፤ ..።” መጽሐፈ ዕዝራ 3፡13

ሰዎች እርስ በርስ የማይስማሙበትን ትንሽ ቀዳዳ ካገኘ፥ እርኩስ መንፈስ በዚያ ስተት ይልና ሊያጣላ ይሞክራል። በዛ የትርምስ ሥፍራ ሰይጣን መጣ። መናፍስቶቹም በሚያለቅሰውና በሚስቀው መካከል ትልቅ ልዩነት ፈጠሩ -

ሰይጣን በተለመደው ተንኮሉ እንዲህ አለ፡- “ሰዎች ሆይ! እስቲ ተመልከቱት፥ እኛ ቤተ መቅደሳችንን ለመሥራት ስንዘጋጅ እነኚህ - ቤተ መቅደሱ እንዳይሠራ የሚከላከሉ የውስጥ ጠላቶቻችን - በታላቅ ሃዘን ያለቅሳሉ...”።

የሚያለቅሱት ሰዎች ከሚስቁት የበለጠ የቤተ መቅደሱ መሠራት የሚያስደስታቸው ሆኖ ሳለ፥ ችግር ፈጣሪዎች (መጥፎ መንፈሶች) በሰዎች መካከል አሉባልታ በመንዛት ሰዎችን እርስ በርስ አጣልተው፥ ሌላም ብዙ ብዙ ነገር ፈጽመው፥ ቤተ መቅደሱ እንዳሠራ ጣሩ። ነገር ግን፥ የሰይጣን ተንኮል ግቡን ሳይመታ ቀረ፤ ቤተ መቅደሱ ተገነባ።

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲወለድ መላእክት ሲዘምሩና ሲደሰቱ፥ ሰይጣን ከጭፍሮቹ ጋር ወደ ቤተልሔም ገብቶ ህጻኑን ለመውሰድ ከጅሎ ነበር። ጭፍሮቹን አስከትሎ ወደ ቤተልሔም ቢመጣ፥ የመላእክት መልካም መንፈስ እንደ እሳት አጥር ሆኖ ገታው። ምንም ማድረግ እንደማይችል ሲገነዘብ ወደ ንጉሡ ሄዶ የቤተልሔምን ህጻናት ሁሉ ንጉሡ እንዲያስገድላቸው መከረ። ከማርያም ከዮሴፍና ከሰሎሜ ጋር ያለ መልካም መንፈስ ግን፥ ህጻኑን ይዘው ወደ ግብጽ እንዲሄዱ አደረጋቸው።

---

[41] መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ ም. 11

ህጻኑና ቤተሰቡ፥ ወደ ግብጽ፥ ወደ ደቡብም እስከ ኢትዮጵያ ድረስ ተመላልሰው ከሰነበቱ በኋላ ወደ ናዝሬት ተመለሱ። ህጻኑም በናዝሬት አደገ፤ ወቅቱም በደረሰ ጊዜ ማስተማር ጀመረ።

ባካባቢው የነበሩ ሰዎች በእርኩሳን መናፍስት ተታለሉ። “እስቲ ተመልከቱት ይህንን ክርስቶስ የተባለ ኢየሱስ፥ በሰንበት ቀን ሰዎችን ከደዌ ሲያድናቸው። እስቲ ተመልከቱት ይህን የማርያም ልጅ፥ እራሱን እንደ እግዚአብሔር ሲያደርግ…” በማለት፥ እርኩሳን መናፍስት ሰዎችን በስህተት መሯቸው።

ክርስቶስ የሚታየውንና የማይታየውን ሁሉ ለኛ እንዲገባን አድርጎ መከረን። ለሰው ጠላቱ ሰይጣን እንጂ ሌላ ሰው አለመሆኑን እንደሚከተለው አስረዳ-

“ዓይን ለዓይን፥ ጥርስ ለጥርስ እንደ ተባለ ሰምታችኋል። እኔ ግን እላችኋለሁ፥ ክፉውን አትቃወሙ። ዳሩ ግን ቀኝ ጉንጭህን በጥፊ ለሚመታህ ሁሉ ሁለተኛውን ደግሞ አዙርለት።…ጠላቶቻችሁን ውደዱ፤ የሚረግሚችሁንም መርቁ፤ ለሚጠሏችሁም መልካም አድርጉ፤ ስለሚያሳድዷችሁም ጸልዩ፤ እርሱ በክፉዎችና በደጎች ላይ ፀሐይን ያወጣልና …።” ማቴ. 5፡38 – 48

መልካም መሥራት የሚጎዳው መጥፎዎችን ብቻ ስለሆነ፥ ጥሩ በመሥራት ጠላታችሁን ሰይጣንን ውጉት ብሎ ስለ ክርስቶሳዊ አመለካከትን አስተማረን። አዎ ! ጠላት ሰይጣንን ለመርታት ጥሩ መሥራት።

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በመስቀል ተሰቃይቶ እንዲሞት ሰይጣን እየመከራቸው - “እኛ ለዚህች አለም የማይሆን ሰው አንፈልግም… ” ብለው ከፊታቸው እንዲያጠፉትና እውነተኛ ንጉሣቸውን እንዳያውቁት አደረጋቸው።

ከምክር ተቀባዮቹም መካከል ጥቂቶቹ በትክክል የሰይጣን ልጆች ሆነው እስከ ክርስቶስ ዘመን ዘልቀው ነበርና፤ እነኚህን የሰይጣን ልጆች እንዲህ ብሎ ክርስቶስ ተናግሯቸዋል።

“እናንተ እባቦች፥ የእፉኝት ልጆች፥ ከገሃነም ፍርድ እንዴት ልታመልጡ ትችላላችሁ?”[42]

ጌታችንን የገደሉ ሰይጣናውያን (እባቦች፥ የእፉኝት ልጆች) - እነርሱ ሰዎች ሆነው ሰይጣን ያደረባቸው ወይንም፥ በሰይጣን እየተታለሉ ለብዙ ጊዜ ስለቆዩ፥ በመምሰል በሽታ የታወሩ - ናቸው።

[42] ማቴ 23፡33 (እንዲሁም፥ ማቴ 3፡7፤ ማቴ 12፡34፤ ሉቃ 3፡7)

"ከሰማይ አባሮ ቢጥለኝ፥ ከመሬት ሸሽቼ የምሄድበት ሥፍራ የለኝምና እርዱኝ..." ብሎ ሰይጣን ስለተማጠናቸው፥ እነኛ ሰይጣናውያን (እባቦች፥ የእፉኚት ልጆች) ረዱት።

በሰዎች መካከል የሚገኝ የመንፈስ ልዩነት ታላቅ ነው። በግልጽ ከሚታዩ - የቆዳ ቀለም፥ የገጽታና የቁመና አካላዊ ልዩነቶች ይበልጣል። እኛ ግን ከአካላዊነታችን በስተጀርባ ያለውን ማየት ያቅተናል። የሰይጣን መንፈስ ያደረባቸው ሁሉ፥ ጠላታቸውን ለይተው ስለሚያውቁ፥ ክርስቶስን ባዩ ጊዜ ተቅበዘበዙ።

"በምኩራብም የርኩስ ጋኔን መንፈስ ያደረበት ሰው ነበረ፤ በታላቅ ድምጽም ጮሆ - "ተው የናዝሬቱ ኢየሱስ ሆይ! ካንተ ጋር ምን አለን? ልታጠፋን መጣህን?.." ሉቃ. 4፡33-34

በጨለማ ቤት ውስጥ ያለ እቃ ሁሉ (ጠረቤዛው፥ ወንበሩ፥..) ቁልጭ ብሎ የሚታየው ብርሃን ሲበራበት እንደሆነ ሁሉ፥ ያ ክርስቶስ የተባለ ብርሃን በጨለማው አለም ሲያበራበት ጊዜ ከአይሁድ ምሁራን ጀምሮ እስከ ወንበዴዎች ድረስ በውስጣቸው ውስጥ ያለው እርኩስ መንፈስ ተለይቶ ይታይ ጀመር።

ጻፎችና ፈሪሳውያን ንጹሓን (ጻድቃን) መስለው ተራውን ሰው ኃጢአተኛ ሲያስመስሉትና ትእዛዛት እያበዙበት ሲያስጨንቁት፥ ክርስቶስ አይቶ እንዲህ ብሎ ተናገረ - " ከባድና አስቸጋሪ ሸክም ተብትበው በሰው ትከሻ ይጭናሉ፤ እነርሱ ግን በጣታቸው እንኳን ሊነኩት አይወዱም።" ማቴ. 23፡4

ለተራው ሰው ጻድቅ መስለው የሚታዩትን የእነኚህን ምሁራን ተመጻዳቂዎች ውስጠ ልቡና ክርስቶስ መርምሮ ስለሚያውቅ እንዲህ አላቸው - " እናንተ ግብዞች፥ ጻፎችና ፈሪሳውያን መንግሥተ ሰማያትን በሰው ፊት ስለምትዘጉ ወዮላችሁ፤ እናንተ አትገቡም፤ የሚገቡትንም እንዳይገቡ ትከለክላላችሁ።" ማቴ. 23፡13

እነኚሁ ንጹሓን (ጻድቃን) የሚመስሉቱ ናቸው ክርስቶስን ለሞት አሳልፈው የሰጡት። ከጥቂቶቹ ሰይጣናውያን በስተቀር አብዛኛዎቹ አዝነዋል። በአይምሮአቸው ላይ የሰይጣን ኃይል የበረታባቸውን እና ሳይወዱ ከስህተት የወደቁትን - "ጌታ ሆይ ይቅር በላቸው፥ የሚሠሩትን አያውቁምና.. " ብሎ ጸለየላቸው።

ክርስቶስ ሲሞት፥ ያ በትግል የተገነባው ቤተ መቅደስ ውስጥ የነበረ መጋረጃ ከሁለት ተሰነጠቀ። ክርስቶስም በመለኮታዊ ኃይሉ ሞትን ድል ነስቶ ተነሳ። በምድር ላይ መቆየቱም አስፈላጊ ስላልነበረ፥ ተከታዮቹን ወክሎ ከመጣበት ከሰማይ ተመለሰ፤ ከእግዚአብሔርም ጎን በቀኙ ተቀመጠ (አብ ወልድ ወመንፈስ ቅዱስ - ሦስት አካል አንድ ባህሪ - አንድ አምላክ - አሜን)።

ክርስቶስም ከሰማይ ተቀምጦ ምድርን አልተዋትም፤ ቅዱስ መንፈስን በምድር ላይ አፈሰሰ። “በዓለ ሃምሳም የተባለው ቀን በደረሰ ጊዜ፥ ..መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደሰጣቸው በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር።” የሐዋ. ሥራ 2፥1 - 4

ቅዱስ መንፈስ ከሰማይ ወረደ፤ ይህ ከአዳምና ሔዋን ተጀምሮ ኃጢአት ተሸካሚ የሆነ ሰብአዊነት ምህረትን ያገኝ ዘንድ ሐዋርያት በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተው ስለ ክርስቶስ እና ስለ ክርስቶሳዊነት ማስተማር ጀመሩ።

እስጢፋኖስ ስለ ክርስቶስ ሲናገር፥ የእግዚአብሔርንም ኃይል ተቀናጅቶ ብዙ - ብዙ ተአምራቶችን ሲሠራ፥ ሰዎችም ሲያደንቁ ሰይጣን ተናደደ። ከእለታት አንድ ቀን፥ ያ እርኩስ መንፈስ እንደልማዱ ከተፍ ብሎ፥ በተወሰኑ ተመጻዳቂ አይሁዶች ውስጥ ገባ።

የቀደሙ ነቢያቶች ሕዝቡን ወደ እግዚአብሔር ሲመልሱ ሰይጣን እየቀና፤ አይሁዶች ቀጥቅጠው እንዲገድሏቸው ያደርግ ነበርና፤ እንደልማዱ እስጢፋኖስንም ቀጥቅጠው እንዲገድሉት መከራቸው።

እነርሱም (አይሁዶች) የሃሰት ምስክሮች አቁመው፥ እስጢኖስ ያላለውን አልከ ብለው ከሰሱት። “ይህ የናዝሬቱ ኢየሱስ ይህን ሥፍራ ያፈርሰዋል፤ ሙሴም ያስተላለፈልንን ይለውጣል ሲል ሰምተነዋል፤.. ” ብለው የሃሰት ምስክሮች እንዲናገሩበት አደረጉ። በዚህም እነርሱው በጠነሰሱት ክስ ፈረዱበትና ከከተማው ወደ ውጪ አውጥተው ወገሩት። እስጢፋኖስም - “ጌታ ኢየሱስ ሆይ! ነፍሴን ተቀበል” ብሎ ሲጣራ ይወግሩት ነበር። ነፍሱ ልትወጣ ስትል ተንበረከከ “ጌታ ሆይ ይህን ኃጢአት አትቁጠርባቸው.. ” ብሎ በታላቅ ድምጽ ጮኸ። ይህንም ብሎ አንቀላፋ (ሞተ)። ” የሐዋ. ሥራ 7፡1-60

እስጢፋኖስ - “እግዚአብሔር እባክህ ኃጢአታቸውን ይቅር በላቸው.. ” በማለት ጸለየ፤ ከክርስቶስ የተማረውን ክርስቶሳዊነትን በሥራ ተረጎመው።

ይህ የእስጢፋኖስ ክርስቶሳዊነት፥ ለሰይጣን ተንኮል እና የወደፊት እቅድ እጅግ ታላቅ እንቅፋት ነበር። ስለዚህ ይቅር የአለማለት ድንቁርና እስካሁን ድረስ እንዲቀጥል፥ በየጊዜውና በየሰዓቱ - ዘወትር ሰይጣን ሰዎችን ስለሚሰብክ፥ ክርስቶሳዊነትን - ክፉውን በደግ መመለስን - እስካሁን ድረስ ሊቀበሉ ያልቻሉት አሁንም ለክፉው አጸፋውን በክፉ ይመልሳሉ - ሰዎችን በድንጋይ ይወግራሉ።

ክርስቶሳዊነት በምድር እስኪነግሥ ድረስ አለም ሰላም እንደማታገኝ ሆና ቆይታለች። ኦ! ክርስቶሳዊነት መቼ ይሆን በአለም የሚነግሥ?

ከእስጢፋኖስ በኋላ ክርስቶስን በመሰሉ ሐዋርያት ብርታት እኛ ክርስቲያን ለመባል በቃን። ስለ ክርስቶስ የተቆረቆሩት አይሁዶችም ክርስቲያኖች ሆኑ። የክርስትና ሃይማኖት በቅዱስ መንፈስ ኃይል በአለም ሁሉ ተስፋፋ።

ንግስት እሌኒ፥ ቆስጠንጢኖስ፥ አጼ ካሌብ፥ አቡነ ተክለ ሃይማኖት፥ አጼ ዘርዓ ያዕቆብ እና የመሳሰሉ ክርስቲያኖች የክርስትናን ሃይማኖት አጠናከሩት። ከጊዜ በኋላም፥ ቅዱስ መንፈስ ለሰዎች ጽኑ ሃይማኖትን ሰጣቸው። ብዙ ሰዎች ወደ ሃይማኖት ተሳቡ - በሃይማኖት ወደ እግዚአብሔር ቀረቡ፤ አምልኮተ ጣኦታትም ተወገዱ።

የሰዎችን ከአረመኔነት ወደ ጥሩ ሰውነት መለወጥ እየተመለከተ፥ ሰይጣን አስችሎት አልተቀመጠም። በምድር ያሉ ሰዎች ሁሉ ወደ እግዚአብሔር ሲሰግዱ ሲያይ፥ የነበረው አማራጭ፥ ሰዎችን ከፋፍሎ ለመግዛት ያመቸው ዘንድ፥ አንዱን ሃይማኖት ከሌላው ጋር ማጋጨት ነበር።

ከንግሥት እሌኒ እና ከልጇ ከቆስጠንጢኖስ በፊት ክርስቲያኖች በገፍ ሲገደሉ - ሲጨቆኑና ሲረገጡ ቆይተው ነበር። በነርሱ ጊዜና ከነርሱ በኋላ ግን፥ ክርስቲያኖች ነፃነታቸውን አግኝተው ትንሽ መረጋጋት ጀምረው ነበር። ዳሩ ግን፥ ከጊዜ በኋላ፥ ትኩስ የእስልምና ሃይማኖት ከታች እየገፋ መጣ፤ እራሱንም ለማስፋፋት ሲል ክርስቲያኖችን ከበባቸው።

የዛን ጊዜ ኢትዮጵያ በእስልምና ሃይማኖት እንዳትዋጥ- "እነኚህ ሕዝቦች ፈሪኃ እግዚአብሔር ያደረባቸው፥ እንግዳ ተቀባዮች ስለሆኑ፥ እጃችሁን በነርሱ ላይ አታንሱ.." የሚል መንፈስ ተከላከለ። ሆኖም፥ ይህ መንፈስ ከወደ ሰሜን አፍሪካ አካባቢ ያሉትን ክርስቲያኖች ስላልተከላከለላቸውና በራሳቸው ስለተዋቸው፥ የሃይማኖት ጦርነት ማድረግ ግዴታ መሆኑን፥ የክርስቲያን አህጉራት መንግሥታትና ጳጳሳት ሁሉ ባንድነት ሆነው ተስማሙ፤ እንዲህም ብለው መከሩ-

"እነኚህ ትኩስ ኃይላት በጊዜው ካልተቀጩ እጅግ አደገኞች ናቸው፤ የክርስቲያን ሃይማኖት እንዳይስፋፋ ያደርጉታል፤ አደገኞች ስለሆኑ፥ እነርሱን ቶሎ ለማዳከም እንነሳ... " ይህንን ሃሳብ ብዙ ክርስቲያኖች ስለደገፉት ለጦርነት መዘጋጀት ጀመሩ።

በእስላሞቹ በኩልም ቅስቀሳው ተካሄደ - "ለእግዚአብሔር መስገድና ይህን ትክክለኛ ሃይማኖት ማስፋፋት አይነካጠሉም.. " ተባለ።

በመናፍስት ምክር የተነሳ፥ ከሁለቱም ወገን ብዙ ለጦርነት የተዘጋጁ ወታደሮች ተመለመሉ። በመብረቅና በነጎድፍድ የሚመሰል የሃይማኖት ጦርነት፥ በእስላሞችና በክርስቲያኖች መካከል ለሰባት ጊዜ ተከናውኗል (ሰይጣንና ጭፍሮቹ ስለ ስምንተኛው ጦርነት ያስባሉ)።

ከእልቂት ባሻገር ሰዎች በመንፈስ ስለተጠናከሩ፥ ሁሉም በበኩሉ በእምነቱ የጸና ሆነ - ብዙ ሕዝቦች ሃይማኖቶቻቸውን የቀን ተቀን ኑሯቸውን የሚቀይሱበት መሳሪያ አደረጉት። የክርስቲያኖች ቁጥር ሁለት ነጥብ አንድ ቢሊዎን አካባቢ፥ የእስላሞችም ቁጥር አንድ ነጥብ አራት ቢሊዎን አካባቢ ሆኗል።

የሰይጣን ተንኮሉ ሁሉ ስለከሸፈበት የወደፊት ታክቲኩንና እስትራተጂውን በመለወጥ፥ ለጊዜው ከዚህ የሃይማኖት ጦርነት ወጣ ብሎ የተለየ ሴራ ወጠነ። ይህም የቅኝ ግዛት ማስፋፋትን እና ዘረኛነትን በተመለከተ ነበር።

በምድር ላይ እርኩሳን መናፍስት በሰዎች ውስጥ አድረው ተንኮል ሲሸርቡ፥ ሕዝቦችን እርስ በርስ እንዲጨራረሱ ሴራ ሲጠነስሱ፥ ሰዎችም በተዘረጋው ወጥመድ ሲጠመዱ፥ ይህ እንዲህ ያለውም የማይታይ ክስተት እጅግ ሲጎላ ነበር ሁለት የአለም ጦርነት ያየነው።

በአገራችን ወራሪ ጦር ሲገባ፥ የኢትዮጵያ ካህናት ጠብ መንጃ ወይም ጦር ሳይሆን፥ መቆሚያና ጽናጽን ይዘው ነበረ ከቤተ ክርስቲያን ወጥተው ወደ ጦር ሜዳ የሚዘምቱት። እስራኤሎች ወደ ጦርነት ሲሄዱ ታቦታቸውን ይዘው እንደነበር ሁሉ፥ የኢትዮጵያ ካህናትም እንዲሁ ያደርጉ ነበር። በመንፈስ እርዳታ ሲያቸንፉም፥ በአካል የማይገለጸውን ለመግለጽ አልሞከሩም። የተዋጋውን ስለሚያወቁ፥ የጀግኖቻቸው ወኔ እንዳይነካባቸው በማሰብ፥ ለማይታዩ ኃያላን መላእክት ምስጋና እያቀረቡ ዝም አሉ እንጂ፥ እነርሱ ምንም አልፎከሩም፥ አላቅራሩም፥ አልሸለሉም።

እርኩሳን መናፍስት ሁለት መመሪያዎችን (ዘረኛነትን እና ቅኝ ግዛት ማስፋፋትን) ይዘው ዘመቻውን ቀጠሉ፤ ሴራው ሁሉ ሰመረላቸው። ተንኮላቸውን አለም አቀፍ አደረጉትና ብዙ ሕዝብ አጨራረሱ።

እነኚሁ መናፍስት በተለይ ለእንግሊዞች ወዳጅ መስለው ምስጢር አካፈሏቸው። እንግሊዞችም እራሳቸውን ከፍ - ከፍ ማድረግ ጀመሩ፤ ከሰው በላይ የሆኑ መሰላቸውና በቅኝ ግዛቶቻቸው ውስጥ ያሉትን ሰዎች ሁሉ እንደ እንስሳ ቆጠሯቸው። በድርጊቶቻቸው ሁሉ ሰዎችን እንደ ከብት ሲገድሉ መናፍስት አበረታቷቸው - “ ልክ ነው! ልክ ነው! እናንተን ያላከበረ መገደል አለበት... ” እያሉ ወደ ከፋት መሯቸው።

እንግሊዞች ታመሙ፤ ህንዶችንም እንስሳት እንጂ ሰዎች አይደሉም ብለው እንግሊዞች ስላመኑ የአይምሮ በሽተኞች ሆኑ። በዚህን ጊዜ፥ የክርስቶስን ትምህርት የተከተለ፥ መንፈስ ቅዱስ ያደረበት፥ መሐተመ ጋንዲ የተባለ ታላቅ ሰው ለእንግሊዞች አዘነላቸው። ይህንን ሰው መንፈስ ቅዱስ ቀረበውና እንዲህ ብሎ መከረው -

“እርኩሳን መናፍስት ከእንግሊዞች ይርቁ ዘንድ መድኃኒቱ ቅዱስ መንፈስን ማቅረብ ነው፤ አንዱ ካለበት ሌላው አይገኝምና። ስለዚህ፥ ጠላቶቻችሁን ውደዱ፤ የሚረግሟችሁንም መርቁ፤ ለሚጠሉአችሁም መልካም አድርጉ፤ ስለሚያሳድዷችሁም ጸልዩ የሚለውን ክርስቶሳዊ ቃል አክብረው። ይህ ቃል ኃይል ይሆንሃል። ይህን ቃል እንደመሳሪያ ተጠቀምበት፤ ከመጨረሺያ አላማህ ጋር በማዛመድ፥ ሕዝቦችህን በመልካም ምግባርና በጥሩነት ለማሰማራት ታጥቀህ ተነሳ... ” አለው።

ጋንዲም ይህን ቃል ተቀብሎ ይጠቀምበት ጀመር። ለህዝቦቹም ሲያስተምር - “ጠላቶቻችሁ ላይ አትሰንዝሩ፤ ሊገድሏችሁ ሲመጡ ለመታረድ እንደሚሄድ በግ ሁኑላቸው... ” አለ።

ጋንዲ ይህን ሲናገር መንፈስ ቅዱስ ወደ ህዝቦቹ ሄደ፤ በዙሪያቸውም ከበባቸው። በዚህን ጊዜ ጋንዲ ሲነጋገር ሕዝቡ በጣም ይገባው ጀመር።

ከእለታት አንድ ቀን፥ የእንግሊዝ ወታደሮች እንደወትሯቸው መግደል ሲጀምሩ፥ ለመገደል የሚሰለፉ ሰዎች ቁጥር እየጨመረ መጣ። እናቶችና አባቶች ልጆቻቸውን ይዘው፥ ሽማግሌዎችና አሮጊቶችም ለመገደል ወደፊት ገሰገሱ፤ ግድያውም ቀጠለ።

የጋንዲ ንግግር ከልቧ ሰርጾ የገባ፥ የእውነት እውነትነት ቁልጭ ብሎ የታያት፥ ከእርሷ ቀጥሎ ወገኖቿ ነፃነትን ሲቀዳጁ የታያት (የተገለጸላት)፥ እጅግ ያማረችና የተዋበች አንዲት ሴት ግድያው ወዳለበት ሥፍራ ገሰገሰች። ያች ልበ ንጹህ - ቆራጥ እናት እንደ በግ ወደ መገደያው ሥፍራ አመራች። የሰውን ፍጹማዊ (ሰማያዊ) ፍቅር የምታንጸባርቅ፥ ለሰዎች ፍቅር ስትል ለወገኖቿ መስዋዕት ለመሆን ብላ ሮጠች - ያቺ እንቁ (ያቺ አልማዝ)።

ይህ በእውነት በአካላውያን የሆነና የተፈጸመ ቢሆንም፥ እኛ በአንክሮ የምናስተውለው እንደ መናፍስት ግጭት ቆጥረን ነው። በመልካሚቷ ሴት በኩል ቅዱስ መንፈስ፥ በእንግሊዝ ወታደሮችም በኩል ደግሞ እርኩስ መንፈስ ተጋጩ። ሴቲቱን በጥይት ገደሏት! ሴቲተን በጥይት ገደሏት! ሴቲተን በጥይት ገደሏት፤ ሥራቸው ይኸው ነውና፤ መግደል፥ መግደል፥ መግደል...።

አንቺዬ..እናትዬ.. እጆችሽን ዘርግተሽ፥ ደረትሽን ገልጠሽ፥

በጥይት ተመታሽ፥ ለዘላቂ ሰላምና ነፃነት ብለሽ፤

አይረሳም ይህ ውለታሽ፥ ለሰው ፍቅር ብለሽ መሞትሽ።

አንቺ ደግ ሴት፥ ቢወድቅ ሰውነትሽ፥

በጠመንጃ ፋንታ፥ ፍቅር በመዝራትሽ፤

አቸናፊ ሆነሽ ለምንጊዜም ትከበሪያለሽ።

ከደግ ሥራ በስተቀር ክፋትን የማያስቡ ሰዎች ሲገደሉ፥ ይህንና የመሳሰሉ ግፎች በምስኪን ሰዎች ላይ ሲፈጸም፥ በክፉ ሰዎች ውስጥም ያለ ደግ መንፈስ (ውስጠ ልቦና) ተቀሰቀሰ። የእንግሊዝ ባለስልጣኖች ማስተዋል ጀመሩ፤ ውስጣዊ ደግነታቸው አነቃቃቸው፤ ልባቸውንም የርህራሄ ጦር ወጋው። በመጨረሻም እንግሊዞች ገባቸው፤ በእውነትም ህንዶችም እንደነሱ ሰዎች መሆናቸውን መንፈስ ቅዱስ ገለጸላቸው። እነርሱም በደንብ ገባቸው፤ ግን ገዳዮች ስለሆኑ፥ እነርሱ ወደ እንስሳነት የተለወጡ መሰላቸውና ልክ እንደ አዳምና ሔዋን በራሳቸው አፈሩ፤ ሽምቅቅ አሉ፤ በውስጠ ህሊናቸውም ተደናገጡ።

የእንግሊዝ ባለስልጣኖች ቀስ በቀስ እየገባቸው ሲመጣ - " እኛም እንደ ህንዶች ሰዎች መሆናችንን ለማረጋገጥ ምን እናድርግ?" ብለው አሰቡ። መንፈሶቻቸውም - ከሁሉ አስቀድመው ህንድን ለህንዶች ሰጥተው ወዳገራቸው መመለስ እንዳለባቸው ነገሯቸው። እንግሊዞች ህንድን ለህንድ አስረክበው ወጡ - በዚህን ጊዜ ህንድ ነጻነቷን ተቀዳጀች።

ታሪክ ከጥንት ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ይደጋገማል። ግን ሰዎች የመናፍስትን ሥራ ስላልተረዱት ይሆን ከታሪካቸው የማይማሩት? የዚህች ደግ ሴት መንፈስ ስላልተገደለ ይናገራል። የሰው ልጅ ክፉም ቢሆን ጠባዩን ለውጦ ጥሩ ይሆን ዘንድ፥ የዚህች ደግ ሴት መንፈስ ስለ ሰብአዊ ርህራሄና ፍቅር ሲያስተምር ለዘለአለም ይኖራል።

ይህ አልፎ - አልፎ በየአገሩ፥ በየመንደሩና በየቤቱ የሚከሰት መስዋዕትነት፥ አንዱ ለሌላው መቆያ - ሕይወት እየሆነ፥ በክፋት የሚበጣጠሰውን ሰብአዊነት በደግነት ገመድ እየቀጠለ እዚህ አድርሶናል።

ከዚያን ጊዜም በኋላ በምድር ላይ እርኩሳን መናፍስት በሰዎች ውስጥ አድረው ሕዝቦችን ማጨራረስ ቀላል አልሆነላቸውም። በእንግሊዞችም ውስጥ ደጋግ ሕዝቦች ተበራከቱ፤ የደግነታቸውም ደግነት፥ እነርሱም እራሳቸውን እስከመስዋዕት ድረስ የሚያደርስ ሆነ። እንግሊዞች በየአህጉራቱ ሁሉ እየዘመቱ የተጨቆኑ ሕዝቦችን ነፃ ለማውጣት ሲሉ ደማቸውን አፍስሰዋል። በኢትዮጵያም ቢሆን ለሕዝቦች ሲሉ ደማቸውን ያፈሰሱ እንግሊዛውያን የማይረሱ ናቸው።

በዚሁ አኳያ፥ በያንዳንዱ አገር ውስጥ እንደ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ (ዘረኝነትን የታገሉ የኢትዮጵያ ንጉሥ)፥ ቅዱስ ዳላይ ላማ (የቲቤት መነኩሴ ሰላምን የሚሰብክ)፥ ማርቲን ሉተር ኪንግ (የአሜሪካ ሰብአዊ መብት ታጋይ) እና ኔልሰን ማንዴላ (የደቡብ አፍሪካ የነፃነት ታጋይና መሪ) የመሳሰሉ፥ ሁሉም የክርስቶስን እና የእስጢፋኖስን ፈለግ

ተከትለው የሚጓዙ ደጋግ ሰዎች እጅግ ተበራከቱ። ባጠቃላይ የቅዱስ መንፈስ ሞቅታ ምድርን ከቅዝቃዜ አወጣት።

ይህ ነው የቃሉ ኃይል፥ መጥፎውን በጥሩ መልሱት የሚለው፥ ቀጥታ ከእግዚአብሔር የመጣ እውነት፤ ከሴቶች ሁሉ የተባረከች፥ ከደግ ሴት እናቱ፥ ሰው ሆኖ የተወለደ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተማረው - በጊዜና በቦታ የማይወሰን ሁለንተናዊ እውነታ፤ ለሰዎች ሁሉ የተሰጠ ጸጋ። ይህ ነው ክርስቶሳዊነት፥ የአለም ሕዝቦች ሁሉ በፍቅርና በሰላም ተስማምተው እንዲኖሩ የሚያደርግ መንፈሳዊ መመሪያ። ይህ ከአህጉር አህጉር የሚዛመት የክርስቶስ ትምህርት፥ የእስጢፋኖስ እና የሌሎችም ሐዋርያት አርአያነት በሰው ልጅ መንፈስ ውስጥ ሰርጎ እየገባ ምድር ሰላም አገኘች።

የሰይጣን መንፈስ አሁንም በእስራኤሎች መካከል እየተመላለሰ እርስ በርሳቸውም በውስጣዊ ቅራኔዎች እንዲሻኮቱ ያደርጋል። ከተለያዩ የአለም ክፍላት ስለመጡ፥ እንደመጡበት አካባቢ በራሳቸው ላይ የቅጽል ስም እያወጡ - አሽኪናዚ - አስፋራዲም - ሳብራ እየተባባሉ አይስማሙም። ግን ይገርማል፤ ከጥንት ጀምሮ እስካሁን ድረስ የቆየ የደጋግ እስራኤላውያን የአብሮ መሆን መንፈስ (የእግዚአብሔር መንፈስ) ስላለ፥ አብረው በመኖር መንፈሳዊ አንድነታቸውን እንዲያጠናክሩ ይመከራቸዋል።

ይህ በዚህ እንዳለ፥ በሃይማኖታቸው አይሁዳውያን የሆኑትን ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችንን በዘር መድልኦ የሚጨቁኑብን እንዳሉም ይነገራል። ግን እነኚህን ደጋግ የእግዚአብሔር ሰዎች (ትሁታን፥ እንግዳ ተቀባይ፥ ርህሩህ..) በቆዳቸው ቀለም ጠቁረው ስለታዩ ብቻ በዝቅተኛ ደረጃ የሚያዩአቸው እነኛው በአለም ዙሪያ የተበተኑ ዘረኞችና የሰላም ጠሮች፥ የጥሩ ነገር ሁሉ ጠላቶች፥ ሰይጣናውያን - የእፉኚት ልጆች ናቸው እንጂ፥ የተቀረው ሕዝብ አሁንም የእግዚአብሔር ስለሆነ፥ ወገኖቻችን ከቤታቸው ነው የገቡት፤ ባገራችን ግድያ ስለበዛ፥ ደጋግ ዘመዶቻቸው አወጧቸው።

ምንም እንኳን የዘረኞቹ መርዛማ ባህሬ ቢያሳዝናቸውም፥ የደጋግ እስራኤላውያን የአብሮ መሆን ጠባይ፥ ለቤተ እስራኤላውያን ወገኖቻችን ደስ የሚል፥ ሞቃት የቤተሰብ ኑሮ እንዲሰማቸው አድርጓል። ለወደፊት፥ በአገራችን በኢትዮጵያም የአብሮ መሆን ስሜት ከዳር እስከዳር ሲያስተጋባ፥ ቤተ እስራኤሎች ወገኖቻችን ከኢትዮጵያውያን ወገኖቻቸው ይቀላቀላሉ።

እርኩሳን መናፍስት አሁንም ለከፍተኛ ተንኮል ሲዘጋጁ፥ በተለይ በእንግሊዞችና በአሜሪካኖች ላይ አትኩረዋል። ብዙ ብዙ ምስጢር ይነግሯቸዋል። ግን በእንግሊዞችና አሜሪካኖች ውስጥ እጅግ ደጋግ የሆኑ ሰዎች ስለሚበዙባቸው እንደተፈለገው አልሆኑላቸውም።

በመጨረሻያም በሃይማኖት ሊቃውንት፥ በመጽሐፍትም በቴሌቪዢንም ውስጥ ሰርገው በመግባት፥ ስለ እንግሊዞችና አሜሪካኖች ታላቅነት መስበክና ማሰበክ ተጀምሯል። በተለይ ለደጋግ አሜሪካኖችና እንግሊዞች እንዲህ ብለው መከሯቸው - "በአሁኑ ወቅት፥ በእውነት እንደ ሰማይ መላእክት መሬትን የምትጠብቋት እናንተ የያዕቆብ ልጆች፥ የኤፍሬምና የምናሴ ዘሮች ናችሁ። ይህችን አለም እናንተ ካልመራችኋት ትጠፋለች። አለም ለናንተ ተሰጥታለች፤ ስለዚህ የናንተ ናትና ግዟት"

እነኛ ለበጎ ምግባር የተሰለፉ የሚመስላቸው ሰባኪዎችም ይህንኑ የተንኮለኛ መንፈስ ቃል ተቀብለው ያስተምራሉ። ተከታዮቻቸውም - "የሰውን ዘር እየመራን ከዚህ ደረጃ ያደረስን - እኛ የኤፍሬምና የምናሴ ልጆች፥ ለአለም ህብረተሰብ አባወራዎች ነን። በምድር የማይፈለጉ ሰዎችን ብንገድላቸውና ብንጨርሳቸው፥ ትክክል ያልሆኑ አስተሳሰቦችና እምነቶችን ብናጠፋ፥ ይህን እግዚአብሔር የሰጠንን ኃላፊነት ማነው የሚቀማን?... " ብለው በኩራት ይናገራሉ። አይ ስው!.... ለካስ የሰው ልጅ ሳያውቅ በእርኩሳን መናፍስት እየተገፋፋ ይለፈልፋል።

ምናልባት ከነኚህ መካከል ሳይሆኑ አይቀሩም እነኛ ግደሉ ግደሉ የሚያሰኝ የእርኩስ መንፈስ ጠባይ የሚያመዝንባቸው ጥቂት ሰዎች - በሃብት የከበሩ፥ በአለም ፖለቲካም ከፍተኛ ሚና የሚጫወቱ። የአለም ሕዝብ እነኚህን ተንሎለኞች በደንብ አላወቃቸውም። ግን እስካሁን መቆየታችን ወደፊትም መሰንበታችን ለምድራችን የሚያስቡላት ደጋግ መንፈሶች ምንጊዜም የበላይ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤ ምድራዊት አለም በሰማያዊ ጎኗ ጸንታ ትቆያለች።

በአለማችን በድብቅ የሚሠራውን ሁሉ ገልጠን ለማውራት ሳይሆን፥ የወደፊቱን ከሚቀይሱ አስጨናቂ ነገሮች መካከል - " እንግዲህ በቃ!... " ሲባል እንሰማለን። ያለፈው አለፈ፤ የዛሬውም ይታያል፤ የነገውም በአለም ቋንቋዎች ሁሉ በቃ! በቃ! በቃ! ይባላል። በአለም ላይ በሚሠራው ሥራ ሁሉ ደግነት በየቀኑ ወገግ ብሎ ሲታይ፥ ክፋት ግን በጣም ሲከፋ ይደበቃል እንጂ አይታይም፤ ተደብቆም የጥፋት እቅዶች ያወጣል፤ ያደፍጣል፤ ተንኮል ይሸርባል።

የደግነት ደግነት ግልጥልጥ ሲል፥ በአንጻሩ ያ የከፋው ክፋት ለበለጠ ክፋት እየተዘጋጀ ለብዙ ዘመናት ሥር እየሰደደ ይቆያል። አልሞት ያለ የዘረኛነት ጥንስስ፥ በሳይንሳዊ መልኩ ከዳርዊን አይምሮ የፈለቀ፥ በጽሑፍም የቀረበ፥ ይህን አንዳች ሰይጣናዊ ሃሳብ ተከትለው፥ ዘራችንን ለማቆየት ብቻ እንታገል የሚሉ - " በቃ! በቃ! በቃ! እኛ ብቻ እንኑር... " ብለው፥ የነርሱ ወገን ያልሆነውን የሰው ዘር ሁሉ ለማጥፋት ታጥቀው እንዲነሱ የሚቀሰቅስ ሰይጣን በመላከላችን አለ፤ በቴሌቪዢን ይታያል። እርሱ ግን - ክርስቶስ ቶማስን፡- እኔ እኮ ነኝ፤ እጆቼን ተመልከት እንዳለ (ዮሐ. 20፡27) እኔ

ሰይጣን እኮ ነኝ፤ ተመልከተኝ የሚል አይደለም፤ ለሰው አሳቢ ጥሩ ሰው እየመሰለ ከመሃላችን እየገባ ሲያበጣብጠን ይቆያል እንጂ።

ካለ ምክንያት እዚህ አልደረስንም። ባለፉት ዓመታት ውስጥ፥ በአንዳንድ ሰዎች (አገር) የእብሪተኛነት ጠባይ ምክንያት ብዙ ሚሊዎን ሕዝቦች አልቀዋል (ሞተዋል)። በሰላም ስም - በገንዘብ ኃይል - የጥቂት ሰዎችን ፍላጎት ለማሟላት ብዙሓን እየተጠቁ ናቸው።

መጥፎ ጠባይን እያንጸባረቁ ደግ መሥራት ይቻላል? እየገደሉ ማዳን እንዴት ይሆናል? ጦረኞችን በጦር ሜዳ ቢገጥሚቸው ገዳይ ከገዳይ ተገዳደለ ይባላል። ህጻናትን የታቀፉ እናቶችን እና ሴቶችን ከቤታቸው ሳይወጡ፥ አሮጊቶችና ሽማግሌዎች ካልጋቸው ሳይነሱ - እነኚህን የዋሆች የሚገድሉ እብሪተኞች ልባቸው እንደ ፈርኦን ልብ ደንዳና ሆኗል።

ደጋግ ሕዝቦች - “ሁላችንም ተያይዘን እንዳንጠፋ፥ በጋራ ምን እናድርግ?” ብለው ሲያስቡ፥ እነርሱ ግን - “እኛ ብቻ እንድንተርፍ ምን እናድርግ?” ብለው ያስባሉ። ደግ ደጉን የሚያስቡ ሰዎች በመጥፋት ላይ ያለውን የተፈጥሮ ኃይል ይንከባከባሉ። ተንኮለኞቹም ባንድ በኩል በሳይንቲስቶች የሚቀርበውን በምድር የመቆያ እቅድ ሲደግፉና ከፍተኛ ትብብር ሲያሳዩ፥ በሌላ በኩል ደግሞ፥ ይህ ብቻ በቂ አይደለም በማለት የበኩላቸውን ሌላ የተንኮል እቅድ አውጥተዋል።

እስከዛሬ ድረስ እንደታየው፥ የሰው ዘር በመሳሪያ ብዛትና በጦርነት አያልቅም። ሆኖም እንደ ጦርነት የመሰለ ጸብ መጫሪያ መንገድ የለም። ስለዚህ ከጦርነት ጋር አብሮ የሚሄድ፥ ሰውን በብዛትና በቶሎ የሚጨርስ ልዩ ዘዴ መኖር አለበት በማለት ታስቧል፤ በተግባርም ሲፈጸም አልፎ አልፎ ይታያል።

ብልጥ ሰው ከሌሎች የሚፈልገውን ነገር በቅድሚያ አይናገርም፤ ችግሩን በተዘዋዋሪ ካወራ በኋላ፥ መፍትሔው ከሌሎች እንዲመጣለት ሲል - “ታዲያ እንዴት ይሁን ጃል? ” እያለ ያናግራል እንጂ። ሰይጣንም እንዲሁ ስለሆነ፥ በምድር ላይ ያለውን ችግር ተቆርቋሪ በመምስል እያናገረን ነው ያለው፤ ግን ይህ የርሱ ተንኮል ከተገለጠበት ተንኮሉ ሁሉ ይሰናከልበት ይሆናል።

ምድር ብዙ ስለምትቆይ በሰው የደረሰባትን ጥፋት ሁሉ በጊዜ ብዛት በራሷ ታስተላክለዋለች። ሆኖም፥ ደጋግ ሰዎች በጋራ እንድናስብ፤ መፍትሔውንም በጋራ እንድንፈልግ ነው የሚመክሩት። ሁሉን ነገር ለምዕራቡ አለም (የኤፍሬምና የምናሴ ልጆች ነን ለሚሉት) ከተውነው፥ ዘመድ ከዘመዱ አህያ ካመዱ እንደሚባለው ይሆንና እንደገና እርስ በርስ መጨራረስ ይከተላል።

እኛ የእግዚአብሔር ወታደሮች ነን የሚሉ ቶርቶራዎች[43] (ሽብር ፈጣሪዎች) በአለም ተሰራጭውዋል፤ ለተዳፈነ እሳት መቆስቆሻነት ያገለግሉ ዘንድ ተዘጋጅተዋል። ቶርቶራዎች የሁለተኛውን የአለም ጦርነት ያላዩ ልጆች ስለሆኑ፥ ክፉና ደጉን ሲመዝኑ ይቸኩላሉ፤ አብሯቸው የሚሰለፍ ሲያጡ፥ የገዛ ወገኖቻቸውንና ሰላማዊውን ሕዝብ ቦምብ እያጠመዱ በገፍ ይገድሉታል። ሰውን ወደ ጦርነት ለመገፋፋት ሲጣደፉ፥ ስምንተኛውና የመጨረሺያው መብረቅ (ጦርነት - ጀሃድ) ቀኑ ዛሬ ነውና ተነሱ! ተነሱ! እያሉ ይሰብካሉ። ዳሩ ግን፥ ከጥቂቶች በስተቀር የሚሰማቸው አያገኙም።

ከጥንት ጀምሮ፥ የመንፈስ ሥራ እና እንቅስቃሴው በምድሪቱ ሁሉ አልተቋረጠም። ሥጋዊ ጠባዮች ከዘር ዘር እንደሚተላለፉ ሁሉ፥ በቤተ መቅደሶች፥ በቤተ መስጊዶችና በቤተ ክርስቲያኖች ሁሉ ሲነገር - ሲሰበክ የቆየ መንፈሳዊ እውነታ በውስጣችን ቆይቶ፥ የመንፈሳዊነት ጠባይ በሁላችንም ውስጥ እንዲኖር ሆነ።

እነሆ! እኛ የዚህቺን ምድራችንን መሬቷን፥ ውሃውንና አየሯን እየተጋራን አብረን ኖረናልና፤ ማንኛውም አገር፥ ዜጋ፥ ዘር፥ ወገን፥ ከሌላው ተገንጥሎ እንደማይኖር ሁሉ፥ ለጠቅላላ የአለም ሕዝቦች የሚጠቅመው፥ እርስ በርስ ተሳስቦ፥ የጋራ ችግሮችን በጋራ መፍታት እንጂ፥ በኃይል መጠቀም አለመሆኑን ሰው ሁሉ የሚገነዘብበት ጊዜ ውስጥ ነው ያለነው። ከእንግዲህስ የወደፊቷ አለማችን እንዳትበላሽ ሁላችንም በጋራ እናስብ የሚሉ ብዙዎች ይሆናሉ (ሆነዋልም)። እውነተኛ ሰዎች ዝም አላሉም፤ ይናገራሉ፤ ይጽፋሉ፤ ሰላማዊ ሰልፍም ያደርጋሉ። መንግሥታት የሕዝቦችን ቀና አስተሳሰብ መመልከት ሲያቅታቸውና፥ ከሕዝቦች ፍላጎት ውጪ ብዙ ድርጊቶች ሲፈጸሙ፥ የዚያን ጊዜ ችግሮች ይቀሰቀሳሉ። ሕዝቦች የሚሉትን መንግሥታት ሲሰሙ ነው የሰይጣን ተንኮል የሚሰበር።

ማንም ሰው (ክርስቲያኑም እስላሙም) ቶርቶራ የመሆን ዝንባሌ አለው። ቶርቶራ ሲባል አክራሪ ማለት አይደለም። ነገር ግን አንድ አክራሪ ቶርቶራ የመሆን ዝንባሌ ይኖረዋል። ታዲያ፥ አንድ አክራሪ ቶርቶራ ሲሆን መመለሻ የለውም። ምድራዊና መንፈሳዊ ኑሮን በማጣመር የሚኖሩ ሰዎች ባንድ በኩል ሰማያዊ መንፈሳዊነታቸው፥ በሌላ በኩል ደግሞ ምድራዊ ሰብአዊነታቸው ሲነካባቸው የህልውና ጥያቄ ይሆንባቸዋል። በዚህን ጊዜ ነው አክራሪዎች የሚያይሉት። እንደ ባህር ጥልቅ ከሆነው እውቀታቸው ጋር፥ የሰዎችን ልዩነት የሚያጋንን ፍልስፍና እያናፈሱ፥ እንደ ጨለማ ከጠቆረው ድንቁርናቸው ጋር፥ በምድር ላይ ኃይለኞች የሚሆኑት እነርሱ ናቸው።

የዛሬ ዘመን ሰው ሰላምን ፈላጊ ቢሆንም፥ የእርኩሳን መናፍስት ቅስቀሳ በተፋፋመበት ወቅት ውስጥ ነው ያለነው። ኃያላን መንግሥታት ወሳኝ ለሆነው ጦርነት

[43] በዚህ መጽሐፍ ቶርቶራ ማለት አክራሪ - እስከ ነፍስ ማጥፋትም የሚደርስ ማለት ነው።

ተዘጋጅተዋል። ለአለም ጦርነት ቅቀስቀላ ተዘጋጅተው ከተቀመጡት ከፓለስታይን እና እስራኤል መካከል በእግዚአብሔር የማያምን በሌለበት በአሁኑ ወቅት - ሁሉም ለአንድ አምላክ እየሰገዱ በፍቅር መኖር እንደሚቻል አላወቁም። በሕዝቦች መካከል ለረጅም ዘመን የቆየ ጦርነት ሲቀጥል፥ ለዛ ሥፍራና ለዚያ ሕዝብ እንዲሁ እርስ በርስ ከማገዳደል በስተቀር ሌላ መፍትሔ ያለ መስሎ አልታያቸውም - እርኩሳን መናፍስት በመልካም መንፈስ እንደሚቸነፉ አልገባቸውም።

እስራኤሎችና ፍልስጤሞች፥ የዘር ግንዳቸው ከአብርሃም የሆኑ የአጎት ልጆች ናቸው። ሁለቱም የሴም ዘሮች ለየወገኖቻቸው የሚቆረቆሩ፥ ከፍተኛ የሕብረተሰብና የቤተሰብ ፍቅር ያላቸው ናቸውና፤ ከመካከላቸው ሰው ሲገደል፥ ከመገደል የተረፈው ዘመዱ የብቸኝነት ኑሮ ያቅተውና ያለው ምርጫ ገድሎ መሞት ወይም ማበድ ብቻ ይመስለዋል።

ሰው በተገደለ ቁጥር፥ የተገደሉ ሰዎች የመንፈስ ኃይል ይጨምራል። በሁለቱም ወገን ያሉ መንፈሶች ቀሪ ዘመዶቻቸው የሥጋን ከንቱነትና ጊዜአዊነት ይረዱ ዘንድ፥ ሰማያዊ ትምህርት እየተማሩ ሰማያዊ ሰላም እንዲያገኙ የሚጠሯቸው የሚመስላቸው ብዙዎች ናቸው (?)። ስለዚህ እርስ በርስ መገዳደሉ ካለማቋረጥ ይቀጥላል። ይህ ነው የማይታይ መንፈሳዊ ክስተት፤ በሰይጣናዊ ልባምነት የሚኖሩ ሰዎች ሰላም እንዳይኖር ሲከላከሉ፥ በቅዱስ መንፈስ ልባዊነት የሚኖሩ ሰዎችም ለሰላም ሲሉ የሚደክሙበት።

እስራኤላውያን ከግብጽ ምድር ከወጡ ጀምሮ እግዚአብሔር የሚነግራቸውን ሁሉ እንዳይገባቸው ሰይጣን ነገር እያጣመመ፥ ከሰው ሁሉ ጋር ካለ ጦርነት ተስማምቶ መኖር የሚቻልበትን መንገድ ሁሉ እያጠረባቸው ቆይቷል።

ጥንትም ቢሆን እግዚአብሔር በርሱ የማያምኑትን ጠላ እንጂ፥ በርሱ የሚያምኑትን ሁሉ የግድ እስራኤላውያን ካልሆናችሁ ብሎ አይጠላም።

“.. …በእናንተም መካከል ልጆችን ለሚወልዱ መጻተኞች[44] ርስት አድርጋችሁ በዕጣ ትከፋፈላላችሁ። እነርሱም በእስራኤል ልጆች መካከል እንዳሉ <u>የአገር ልጆች</u> ይሆኑላችኋል። በእስራኤል ነገዶችም መካከል ከእናንተ ጋር ርስትን ይወርሳሉ። <u>መጻተኛውም በማንኛውም ነገድ መካከል ቢቀመጥ በዚያ ርስቱን ትሰጡታላችሁ ይላል ጌታ እግዚአብሔር።</u>” ሕዝ. 47፡21 - 23

---

[44] በእንግሊዝኛው - King James Bible – to the strangers that sojourn among you - ይለዋል።

እግዚአብሔር ምድሪቱን አንዴ ፈጥሯታልና፥ ለእስራኤላውያን ብሎ ሌላ አዲስ መሬት እንደማይፈጥርላቸው ሁሉ፥ ካለ ጦርነት ተስማምቶ መኖር የሚቻልበትን ይህን መንገድ ነገራቸው፤ እነርሱ ግን እስካሁን ድረስ ይህ አልገባቸውም።

እግዚአብሔር ሰውን በሰው አይለውጥም። አገር አልባ የነበሩ - እነርሱ በተሰደዱበት ሥፍራ ሁሉ ሲያለቅሱ እንዳልነበሩ ሁሉ፥ አሁን እነርሱ ፍልስጤሞችን ማስለቀሳቸውን የአለም ሕዝቦች አይተው አዝነውባቸዋል።

እውነት እየቆየ ሲሄድ እየደመቀ ሰዎችን በመልካም መንፈስ ያነቃል። ስለዚህ ለወደፊት ክፉ ሥራ የሚሠራውን ሁሉ የአለም ሕዝብ ያወግዛል። እነርሱ ከፍልስጤሞች በጉልበታቸው የነጠቁትን መሬት መልሰው፥ በየአገሩ የተሰደዱትን ፍልስጤማውያን ሁሉ ተመልሰው በነፃነት እንዲኖሩ ካላደረጉ በስተቀር፥ በክፉ አድራጊነት የሚታወቁ ይሆናሉ፤ የሰላም ጠንቆች ከመባልም አያመልጡም።

ፍልስጤሞችም አይሁዶችን በዚች ምድር ላይ በሰላም እንዳይኖሩበት የሚያደርጉት ማንኛቸውም እንቅስቃሴ ይኋላ ኋላ ጉዳት ላይ የሚጥለው የነርሱን - የራሳቸው ልጆችና የልጅ ልጆች ነው። ሰውን የሚያስለቅስ ሁሉ (በያለበት) የኋላ ኋላ ልቅሶ በርሱ ላይ እንደሚጸናበት ልብ ይበል።

ሰው ሁሉ የምድራዊነት መሟጠጫ ጊዜ እስኪቃረብ ድረስ እያለቀሰ እንዳይኖር፥ መልካሙን አማራጭ ይፈልግ። በማልቀስ ላይ ያሉትን ወንድሞቻችንን ሁሉ (በያሉበት) ቀርበን ማነጋገር እና በሰላም አብሮ ስለመኖር ጉዳይ መምከር ይገባል። ምንም ቢሆን ሰውን ሰው መጥላት የለበትም። በጥላቻ መቆየት ሰውን ይጎዳል።

ፓለስታይን ነጻነቷን ተቀዳጅታ፥ ሕዝቦቿም ሲፈልጉ ከፓለስታይን፥ ሲፈልጉም ከእስራኤሎች ጋር በሰላም መኖር እንዲችሉ ለማድረግ ያለው ምርጫ፥ የፓለስታይኖች ወይንም የእስራኤሎች በጎ መንፈስ ብቻ ሳይሆን፥ በሰው ልጅ በጠቅላላ በውስጡ ያለው በጎ መንፈስ ሲቀሰቀስ ስለሆነ፥ የሰውን ልጅ በእኩልነት ማየት፤ የሚበጀውን ማሰብ፤ ያሰቡትንም በተግባር መፈጸም ያስፈልጋል። እንዲሁም ይህንን በጎ መንፈስ የሚከላከል መጥፎ መንፈስ ረግቶ እንዳልተቀመጠ መገንዘብ ያስፈልጋል።

ሰይጣን የሚያሰራጨውን የክፋት አይነት ዘርዝሮ መጨረስ ካቅም በላይ ነው። ከሁለተኛው አለም ቀጥሎ እስራኤሎች እና ፍልስጤሞች የአለም ጦርነትን መቀስቀሺያ እሳቶች እንዲሆኑ ተዳፍነው ተቀምጠዋል። በተለይም ከጠባዮቻችን አንዱ - ዘረኛነታችን የሦስተኛው አለም ጦርነትን ለመቀስቀስ ሲያቆበቁብ - ሁኔታዎች ሁሉ ይህንን አስከፊ ሂደት ሲጠቁሙ - እኛ ይህንን እያየን ዝም ማለት አንችልም።

እግዚአብሔር ከሰዎች መካከል እስራኤላውያን ለይቶ፡- እናንተ የምወዳችሁ ሕዝቦቼ ናችሁ ቢል፥ ጠቅላላ የሰው ዘር እንዳይጠፋበት አስቦ ያደረገው የመከላከያ

ዘዴው ነው እንጂ፥ የምድራዊነት ጠባይ የሌለበት እግዚአብሔር አንዱን የሰው ዘር ከሌላው አብልጦ የሚመለከት ሊሆን አይችልም።

ሻሎም፥ ሻሎም፥ ሻሎም፥ ሻሎም አሌኩም፥
ከአራቱም ማዕዘን የምትመጡ፥ ሁላችሁም፥
ጀሩ - የሩ - የርሱ - የርሷ ሳሌም፥
ጥላቻ በፍቅር ሲቀየር፥ ቆንጆ እንዳንቺ የለም።

አንቺ እስራኤል የአራት ባህሮች[45] አገር፥
የምድርና የሰማይ መጋጠሚያ ድንበር፥
ቤተልሔም፥ ናዝሬት፥ ቢታንያ፥ የሁለት አለም መንደር፥
አንቺ አለም የአብርሃም ተስፋ፥[46]
አንቺ የሩሳሌም የኢሳያስ ራእይ[47]፥
የዮሐንስ ምስጢር፥[48]
አንቺ ቆንጆ ለምለም፥ አዲስ እርስት፥ ሰማያዊት ምድር፥
መንግሥታት ሲገባቸው፥ ሲያቆሙልሽ የአለም ወታደር፥
ያለማወቅ ጨለማ እንዲገፈፍ፥ ድንቁርና እንዲሰበር፥
ውበትሽ እንዲገለጥ፥ ነፃነትሽ እንዲከበር።

አንቺ ሥፍራ የሰው ዘር ሁሉ የረገጠሽ፥
መድኃኒ ዓለም - ክርስቶስ የተመላለሰብሽ፥
ከሰማይ መላእክት የወረዱብሽ፥
በእውነት ለሁሉም የሁሉም መሆንሽ ሲታወቅልሽ፥
የዛን ጊዜ - ፍጹም ሰላም ይሰርጻል ከውስጥሽ።

አዲሲቷ እስራኤል፥ በጣም ደስ ይበልሽ፤
የምድር ነገዶች ሁሉ ባንቺ ተባረኩልሽ፤

---

[45] የገሊላ ባሕር፥ የሙት ባሕር፥ የቀይ ባሕር

[46] ዘፍ. 12፡1 – 3

[47] ኢሳ. 65፡ 17 – መጨረሻ

[48] ዮሐ. ራዕ. 21

በክርስቶሳዊነት ሰው ሁሉ አንድ ሆነልሽ።

በዘመናችን የምዕራቡ አለም በሦስተኛው አለም ላይ አምባገነን መሆንን አውቆበታል። ለጦርነት ከሚወጣው ገንዘብ ግማሹ እንኳን ለደግ ሥራ ቢውል ኖሮ፥ በምድር ላይ የተሻለ ኑሮ መኖር ይቻል ነበር። ተከብረውና ተፈርተው እንዳይኖሩ፥ በመጥፎ ጠባያቸው ከቶርቶራዎች የባሱ ቶርቶራዎች ሆኑ። እብድን ሰው - "አንተ እብድ.. " ብሎ የሚሳደብ፥ እርሱ ከእብድ የባሰ እብድ መሆኑ ነው። ስለዚህ ሁሉም አብዷል ማለት ነው።

ይህች አለማችን ሰላም የምታገኘው ሁሉም የራሱን ቤት ሲያጸዳ ነው እንጂ፥ የአንዱን ቤት ሌላው እየሄደ ላጽዳ ቢል፥ ጭቅጭቅ፥ ጸብና ጦርነት መፈጠሩ አይቀርም። " በወንድምህ ዓይን ያለውን ጉድፍ ስለ ምን ታያለህ? በዓይንህ ያለውን ምሰሶ ለምን አትቅለከትም?.. " ማቴ.7፡3-4

እነሆ! የአንድነታችን ተቀናቃኝ ኃይላት በሕዝቦች እንቅስቃሴና እድገት ላይ ከፍተኛ ሚና ሲጫወቱ፥ ለሰው ሁሉ የእብደት ፍልስፍና እየተሰበከ፥ ጤነኛው ሰው እብድ ሲባል፥ እብዱ ጤነኛ ሲባል - አዎ! ከእንግደ&ህ ከየትኛው ወገን የሚሰርጽ መንፈስ ነው እርኩስ፤ ከየትኛው ወገን የሚሰርጸው መንፈስ ነው ቅዱስ? የአለም ሕዝብ በእውነት በመምሰል በሽታ አይኑ እየታወረ፤ ቀኑም እየደበዘዘ ነው ያለው።

ምንጊዜም ወደ ምድራዊ ሃብት - ወደ ገንዘብ የሚሮጥ ከእውነት መራቁን ይወቅ። ኃጢአት እየተሠራ እያየነው፤ ከኃጢአታችን መለስ ማለትን ፈርተን እርስ በርስ የምንተላለቅ መሆናችን እስኪገባን ድረስ እንቀጣለን።

ሁለት አይነት አክራሪዎችን አለማችንን በሁለት አቅጣጫ እያጠፏት ነው። አንደኛው አክራሪ ባይኖር ኖሮ ሌላውም አክራሪ ባልተፈጠረ ነበር። እነዚህ እርስ በርስ የሚጨራረሱ ኃይሎች የማይፈለጉ ምድራዊ እውነታዎች መሆናቸውን ልብ ይሏል።

የአለም ሕብረተሰብ ከሁላችን በላይ በሆነ የመንፈስ ኃይል ይናወጣል። የአለም ሕብረተሰብ ሲናወጥ፥ ድሃው ሃብታም፥ ሃብታሙም ድሃ እየሆነ፥ የሰው ዘር ሁሉ በጊዜ ውስጥ ከዚህች ምድር የሚኖረው ድርሻ እኩል ሲሆን፥ የዚያን ጊዜ ነው ሰላምና ጸጥታ የሚኖር፤ የዚያን ጊዜ ነው አብሮ መሥራትና አብሮ ማደግ ተፈጥሮአዊ ግዴታ የሚሆን። የዚህ ትውልድ መጨረሺያው በተለያዩ መንገዶች ይፋጠናል። በየወቅቱ የሚቀሰቀሱ ጦርነቶች መንፈሳዊ ግንዛቤን ያፋጥናሉ። ካለ ጦርነት መቆየትም፥ ከሥልጣኔ ጋር የሕብረተሰብ እድገትንና መንፈሳዊ ግንዛቤን ስለሚያፋጥን መጨረሺያውን ያቀርበዋል።

ከሁለተኛው የአለም ጦርነት መጨራረስ የተረፉት ለመጪው አለም የተሻለ ሁኔታን ፈጠሩ። ከእንግዲህስ ሕዝቦች በሰላም እንጂ በጦርነት የሚያምኑ እንዳይሆኑ፥

አንጋፋ መሪዎች እየመከሩና እያስጠነቀቁ ቆይተዋል። እነርሱ የሁለተኛውን የአለም ጦርነት እንዳሳለፉ፥ የነርሱ ትውልድ ሦስተኛውን የአለም ጦርነት እንዳያይ ይመክራሉ። ነገር ግን እነኛ ከሁለተኛው የአለም ጦርነት የተረፉት አዛውንት አርጅተው እየሞቱ ማለቃቸው ነው። ተተኪው ትውልድ የሰላምን ምንነት እንደ አባቶቻችን በደንብ አላወቀውም።

ይህች ምድራችን መጨረሺያዋ እየተፋጠነ ነው የመጣው። በምድር ላይ ያለው ምግብ የተወሰነ ነው። በላተኛ እየበዛ ሲመጣ ከምድሪቱም የሚመረተው ሰብል ለሰዎች ሁሉ አልዳረስ ሲል፥ ይህ የመጨረሺያውን መፋጠን ነው የሚያመለክተው። ግን፥ ምድር እራሷን መሆን እስኪያቅታት ድረስ ጊዜው ረዥም ነው።

ከእንግዲህስ የሰው ቁጥር እየበዛ ሲሄድ፥ የምድርም ሃብት ወደ ተወሰኑ ሥፍራዎችና ሰዎች ዘንድ ብቻ ሲቆይ፥ በደኸዩ አገሮችም ከመሬት የሚመረተው ሰብል በማንኛውም አይነት መንገድ ቢከፋፈል የማይበቃ ሲሆን፥ ሰዎችም ሆዳቸውን ለመሙላት የሚያባክኑት ኃይል ከምግብ ከሚያገኙት ኃይል ሲበልጥ፥ መደህየት፥ መቸገር፥ ጭንቀትም ሲከታተል፤ ይባስ ብሎ በነኛው በተዳከሙቱ ላይ የተፈጥሮ ጉዳት ሲጸና፥ ከትንቢቶች ሁሉ ባሻገር፥ ለሰው ልጅ የሚበጀው በመንፈስ መጠናከር መሆኑ የማይገባው አይኖርም።

አለም አቀፋዊ ጦርነት እንደገና ሲቀሰቀስ፥ ይህም ጦርነት የተካረረ ሲሆን፥ የዚያን ጊዜ አዲስ ነገር ይታያል። ከቋሚው ሟቹ ይበዛል፤ ከሚታየው አካል የማይታየው መንፈስ ያመዝናል፤ ሰው ከመኖር አለመኖርን ይመርጣል፤ የዛን ጊዜ ኑሮ ማለት ከምድራዊነታችን ባሻገር መሆኑ በደንብ ይታወቃል። ለወደፊት የእድገት መመዘኛው ምድራዊ (አለማዊ) ሥልጣኔ ብቻ ስለማይሆን፥ የአለም ሕዝቦች ሁሉ በአንድ በኩል ለአንድ ምድራዊ ኢኮኖሚ እና የጋራ ብልጽግና ባንድነት ይሠራሉ፤ በሌላ በኩል ደግሞ መንፈሳዊ አንድነታቸውን ያጠናክራሉ።

የሰው እምቢተኛነት የእግዚአብሔርን መለኮታዊ ፈቃዳዊ ነፃነትና ፍላጎት አያሳጣውም - አያዳክመውም። ስለዚህ የርሱ ፈቃድ በዚህች በምናውቃት ምድር ላይ በምሥራቅ፥ በምዕራብ፥ በሰሜንና በደቡብ፥ ሁሉ ይሰፍናል። የዚያን ጊዜ የዚህች የምናውቃት አለም መጨረሺያ ይሆናል። ይህም ማለት "የእግዚአብሔር መንግሥት" ይመጣል ማለት ነው።

"የጌታም መንፈስ ባለበት፥ በዚያ አርነት (ነፃነት) አለ።" 2ኛ ቆሮ. 3፡17

“የእግዚአብሔር መንግሥት” ይመጣል ማለት ሰይጣን በዚህች በምድር እንደነገሠባት እንዲሁ ለዘለአለም አይቀጥልም ማለት ነው። አዲሱ ትውልድ ከሰይጣን ቁራኛነት ነፃ ይወጣል ማለት ነው።”

ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሕይወቱ ሲያልፍ ቀኑ ጨለመ፤ በዚያው እንደጨለመ ሊያስቀረው ይችል ነበር፤ አላደረገውም። የሚሆነውን እና የማይሆነውን ለይቶ የማያውቅ ሰው ስለወደፊት እድሉ ማወቅ ስለሚፈልግ፥ በሰው አንጎል የሚታሰብ ሁሉ እንደ ትንቢት ሆኖ ሲነገረው በጉጉት  እየሰማ እንደቆየ - ጨለማው ብርሃን ሆኖልን፥ ከክርስቶስ በኋላ አዲስ ትውልድ ተተካ፤ ወደፊትም ሌላ አዲስ ትውልድ ይተካል።

በዘመናችን እና ለወደፊትም የሰው ዘር ሁሉ አብሮ በመኖሩ እየተቀራረበ ሲመጣ፥ ሰውን ሁሉ እንደ አንድ የሰው ዘር መቁጠርና መንከባከብ ይገባል። ይህም እናትና አባት ለልጆቻቸው ከሚያደርጉት እንክብካቤ ተለይቶ አይታይም።

እግዚአብሔር የሕዝቦችን ጩኸት ያዳምጣል፤

ጉልበተኛው ሲያይል፥ እጅግ ሲበዛ በደል፥

ማነው ልክ? ማነው ሃሰተኛ ሳይል፥

ጻድቁን ከኃጢአተኛው ሳይለይ፥

ወደርሱ የጮኸውን ሁሉ ይሰማዋል።

ሁሉ ነገር አንድ ሁለት ብሎ ያድጋል፤

የሚያዘግም ከሚፈጥን ጋር በጊዜ ውስጥ አብሮ ይነጉዳል፤

የሚደሰት የሚከፋም አብሮ ይጮሃል።

ሁለት እውነቶች ተፋጠዋል፥

ያንዱ አስመሳይ እውነት ከሌላው በልጦ ይታያል፤

ሁሉን እየተረዳን - እያወቅን መታወራችን፥

ይህንም ያንም መስለን መኖርን መርጠን ይሆን?

ግን የሚመስላቸው አንዳይመስላቸው፥

ተጽፏልና ብዙ ምሥጢር ለሚገባቸው፥

የኛ እግዚአብሔር አይደለም የተደበቀው፤

በጊዜ ውስጥ እውነት እየተገለጠ ነው ያለው።

# ምዕራፍ ሰባት

## እውቀት ወይንስ ጥበብ

የአገር መሪዎችና አስተዳዳሪዎች በሥልጣን ላይ ጉብ ብለው፥ የራሳቸውን ኑሮ ሲያመቻቹ፥ ግን ለውጥ መምጣት ግድ ሲሆን፥ ጦርነት ሲነሳ፥ ሕዝቦችም በብዛት እየተገደሉ ሲያልቁ፥ ለዚህ ሁሉ ችግር መንስኤው ምንድነው ? መፍትሔውስ ጥፍት የሚለው ለምንድነው? ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም መኖር ሲቻል፥ በማህበራዊ ኑሮ እራሳችንን ማሻሻል የሚያቅተን ለምንድነው ?

በምድራችን አዋቂዎች በዝተውላታል፤ በዛው መጠን ጠቢባን ተቀንሰውባታል። ታላላቅ የአገር መሪዎች አላት፤ በዛው መጠን፥ እራሳቸውን እንጂ ሕዝቡን የሚያዳምጡ የላትም።

ብዙ አውቀው፥ ብዙም የሚናገሩ፥ አንደበተ ርቱዕ የሆኑ - ተሰሚ መሪዎች አላት፤ ግን በሕዝቦች መንፈስ (በእግዚአብሔር መንፈስ) እየተመሩ ቀናውን መንገድ የሚከተሉ ጥቂቶች ናቸው።

ብዙ ሰው ያወቀውን (የሚያውቅ የሚመስለውን) እየሆነ፥ ልባምነቱን (በውስጡ ያለውን የእግዚአብሔርን መንፈስ - እውነተኛው ማንነቱን) ይረሳዋል።

እኛ በምንኖርባትን የአለማችን (የኢትዮጵያችንም) ሥጋዊና መንፈሳዊ ጎን፥ ካንዱ ወዳንዱ ስንገላበጥ፥ ለይተን ያላወቅነው ምንድነው?

ባለ ብዙ ብሔረሰቦች በሆነች በኢትዮጵያችን ሰዎች ሁሉ በአንድ የወንድማማችነት መንፈስ ሊጠቃለሉ የማይችሉ የሚመስለን፥ ብዙ አይነት እውነት፥ ብዙ አይነት ውሸትም የሌለ እየመሰለን ይሆን?

የጋራ ጥቅም የግል ጥቅምን የሚቃረን የሚመስለን ለምንድነው? አብሮ መሆን ብቸኝነትን የሚያጠፋው የሚመስለን ለምንድነው?

ፖለቲከኞች (በአለም ዙሪያ፥ በተለይም ዲሞክራሲ በሌለበት አገር) የመንግሥት ሥልጣን ሲጨብጡ የሕዝቦችን ጆሮ እየኮረኮሩ የሚያሰቃዩት፥ ከአገር ጥቅም ይልቅ የራሳቸውን ፍላጎት ለማርካት ስለመረጡ ነወይ?

ምን ይደረግ? ዘወትር እየተማርንም ቢሆን፥ ይህቺ አለም የማትታወቅ እየሆነች ተቸግረናል። ምንጊዜም ለዚህች አለም ባይተዋር እየሆን ግራ እንጋባለን፤ ሳናውቀውም ከስህተት ላይ እየወደቅን በራሳችን ላይ ጸጸት እናበዛለን።

በየሳምንቱ ወደ ቤተክርስቲያኖች (ወደ ቤተ መቅደሶች ወይም ወደ መስጊዶች) እየሄድን የምንሰበከው ሁሉ አልበቃ ብሏል።

በዚህ አለም የሚሠራው ሥራ ሁሉ ከመምሰል ጋር አብሮ መሄዱም ይህቺን አለም የማትታወቅ፥ የማትለመድ (ባይተዋር እና ጉራማይሌ) አድርጓታል። እንዳው ባጠቃላይ፥ ይህች አለም የተፈጠረችው በውስጧ የሚኖሩትን ሁሉ በእንግድነት ለማስተናገድ እንጂ ለማስኖሪያ አይመስልም።

እንግዲህ የምንናገረው፥ የምንጽፈው ሁሉ ለአጠቃላይ ግንዛቤአዊነታችን ይሁነን - ለእውቀት ሳይሆን ለጥበብ።

## <u>ግንዛቤአዊነታችን</u>

ግንዛቤአዊነት ከአካባቢ ጋር (ነፍስ ያለውም የሌለውም) ስምም ሆኖ በሰላምና በፍቅር ለመኖር የሚያበቃ የረቀቀ አስተዋይነት ነው። ግንዛቤአዊነት በሌላው እግር ሆኖ ነገሮችን መመልከት እና ስለ ሌላው ሰው ስነ አይምሮአዊ ሁኔታ ቶሎ መረዳትም ስለሆነ፥ ከሰዎች ሁሉ ጋር በስምምነት ለመኖር፥ ለማህበራዊ ኑሮም የሚጠቅም አመለካከት - አንድ የመንፈሳዊነት ባህሬ ነው።

ሰዎች ሁሉ በችሎታ የተለያዩ መሆናቸውን በማስተዋል፥ ሌላውን የማያስቀይም፥ ከሰው ሁሉ ጋር መኖር የሚያውቅ፥ እርሱ መንፈሳዊነትን ከግንዛቤአዊነት ጋር ያዋሃደ መልካም ሰው ነው።

ለጥቃቅን ምድራዊ ችግሮች ጭንቀት የሚያበዛ ግንዛቤአዊነት የጎደለው ነው፤ ሰው ሁሉ በምድራዊ ችግሮች እየተፈተነ እንደሚኖር አላወቀምና።

ከግንዛቤ ጉድለት ጋር የተያያዙ አያሌ ምሳሌዎችን መጥቀስ ይቻላል። ለምሳሌ - ቀጠሮ የማያከብሩ ሰዎች - በዚህ ሩጫ በበዛበት አለማችን ውስጥ - ጊዜ ሰውን ወደ ኋላ እየተወ ወደፊት የሚሮጥ መሆኑን አልተገነዘቡም። እምነት የማይጣልባቸው ሰዎችም ኑሮአቸው ለምን እንደማይሻሻል ስለማይገነዘቡ - ከመጥፎ ጠባዮቻቸው (ለምሳሌ - በቃል አለመርጋት፥ መዋሸት፥ ማታለል፥ ወ.ዘ.ተ...) አይታረሙም።

አለም የሁሉም መሆኗን የሚገነዘብ እራስን ወዳድ አይሆንም፤ ከሰው ሁሉ ጋር ሲኖር ለራሱ ብቻ ሲል ባለመሆኑ፥ የሌላውን መብት እንደራሱ መብት አድርጎ ያከብራል እንጂ።

ቁጣ ከሰማይ ሲወርድ - ባንድ ጊዜ ብዙ ሰው ሲሞት፥ ይህ ለምን ተፈጸመ? ምን ኃጢአት ተሠራ? ሰው ምን በደለ? መንግሥት ምን አጠፋ? ብሎ የማይጠይቅ (ግለሰብም ሆነ መንግሥት) ግንዛቤአዊነት የጎደለው ነው፤ ሁሉን የሚቆጣጠር ሰው ብቻውን ይመስለዋልና።

በሕዝቦች ላይ ችግር ሲደርስ፥ እግዚአብሔር ተቆጥቶ ነወይ? ብሎ የማይጠይቅ ግንዛቤአዊነት የጎደለው ነው፤ አባት ልጁን ሲያጠፋ እንደሚቀጣው፥ እግዚአብሔርም እንዲሁ የሚያደርግ መሆኑን አላስተዋለምና።

እግዚአብሔር አያየኝም ብሎ ኃጢአት የሚሠራ ግንዛቤአዊነት ይጎድለዋል፤ የጠፈር ስፋቱ ከጥበቱም ጋር እንደሆነ ሁሉ፥ እግዚአብሔርም የትልቅነቱን ያህል ትንሽ መሆንም እንደሚያውቅበት አልተረዳምና።

ሽማግሌዎችንና አሮጊቶችን የማያከብር፥ ከቁጥጥር በላይ በሆኑ ሁኔታዎች ውስጥ ሲዘፈቁ በርህራሄ የማይመለከታቸው - ሲቻለውም የማይረዳቸው (ግለሰብም ሆነ መንግሥት) ግንዛቤአዊነት ይጎድለዋል፤ እድሜ ቆዳን ቢያጨራምተው፥ ሰውን የረቀቀ (የከበረ) እንደሚያደርገውም አልገባውምና።

የሰውን ምክር የማይሰማ፥ ለመተቸትም ሆነ ለመወቀስ ክፍተት የማይሰጥ ትእግስተ ቢስ - እራሱን ማሻሻል የሚያቅተው ተመጻዳቂ ነው። በሌሎች ላይ ወቀሳ የሚያበዛም፥ ማንም ሰው ወቀሳ ሲበዛበት ጉዳት ላይ ሊወድቅ እንደሚችል አያገናዝብም።

ሲቆጡት መልሶ በመቆጣት ፋንታ የሚታገስ፥ እራሱን በቶሎ ያሻሽላል። መልሶ የሚቆጣም ግልፍተኛ ባለጌ ከመሆኑም በላይ፥ እራሱን ከጉዳት ላይ የሚጥል ሞኝ ነው፤ በርሱ ላይ ሰው ሲጮህበትና ሲቆጣው እርሱ እንደሚናደድ፥ ሌላውም እንዲሁ የሚናደድ መሆኑን ማገናዘብ ተስኖታልና። ስለሌላው ችግር የማይረዳ (የማይገነዘብ) በጥቃቅን ምክንያቶች ሁሉ እንደተቆጣና እንዳኮረፈ ይኖራል።

ግንዛቤአዊነት ያለው በሌላው ላይ ነቀፌታ አያበዛም። መጠነኛ ተግሳጽና ምክር፥ ሂስና ግለሂስ በየጊዜው ማድረግ ሰውን በጠባዩ ወደ ከፍተኛ ደረጃ ያደርሰዋል፤ ግን ይህም ቢሆን ከግንዛቤአዊነት ጋር ሲሆን ነው ወደ ጥሩ የሚያመራው፤ በውስጡ መንፈስ ያለው ሰው ሁሉ ስህተት ላይ ሲወድቅ እራሱን መውቀሱ አይቀርምና።

ምንጊዜም ተግሳጽና ምክርን በመጠኑ ማድረግ ያስፈልጋል። የሚመክር ሰው ለተመካሪው ሰው በራሱ ለማረሚያ የሚሆን በቂ ቦታ መተው አለበት እንጂ፥ ሰውን ጭቅጭቅ ማድረግ ያደናቁራል፤ ያናድዳልም። እናትና አባትም ልጆቻቸውን በመጠኑ ሲወቅሱ ነው ጥሩ ውጤት የሚያመጣው። ወቀሳ ከማብዛት ምርቃት ማብዛት ይሻላል።

ቀደም ሲል ባሪያ ይገዙ የነበሩ - የሰውን ነፃነት የገፈፈ እንደ መጥፎ ሰው የሚቆጠር እንደሆነ በተለያየ መንገድ ሲነገራቸው፥ ከራሳቸው የማስተዋል ችሎታ ጋርም ስለቆዩ፥ አሁን - አሁን ገብቷቸው እራሳቸውን መለወጣቸው፥ በሰው ልጅ ውስጥ ሥር የሰደደ ክፉት ሁሉ በግንዛቤአዊነትና በፍቅር እንደሚረታ ያመለክታል።

እስከዛሬ ድረስ በሕዝቦች ሕብረተሰብአዊ እድገት ውስጥ ግንዛቤአዊነትም አብሮ ስላደገ፥ ሕዝቦች ከጥቂት የጸጥታ አስከባሪዎች (ፖሊሶች) ጋር ሆነው እርስ በርሳቸው ተስማምተው ይኖራሉ። ለወደፊት ካለ ምንም ጠብ መንጃና ካለ ፖሊስ መኖር የሚቻልበት ዘመን ይመጣል። የጠብ መንጃን (ጠቅላላ የጦር መሳሪያዎችን ሁሉ) አስፈላጊነት የሚያስቀር ሕብረተሰብአዊ ግንዛቤአዊነት ምንኛ የረቀቀ ነው።

አንዱን ከፍ ሌላውንም ዝቅ (አንዱን ኃጢአተኛ ሌላውንም ጻድቅ) በማድረግ ላይ ግንኙነት የሚመሠርት መንፈሳዊ ነኝ ባይ ሰው ቢኖር፥ እርሱ ገና ከምድራዊነቱ ያልተላቀቀ ነው፤ በእግዚአብሔር ፍጡራን መመካከል ልዩነትን መፍጠር የእግዚአብሔርን ሥራ እንደመናቅ መሆኑን አልተገነዘበምና።

እኔ ከሌላው እበልጣለሁ (እሻላለሁ) ብሎ የበላይነቱን ለማሳየት የሚጥር፥ ከፍ ብሎ መታየት ከውድቀት ጋርም የተያያዘ መሆኑን ባለመገንዘቡ፥ እርሱ በሥልጣን ጥም እየተቃጠለ እራሱንና ሌሎችን እረፍት የሚያሳጣ፤ የሰውን ሰብአዊ መብት በተለያዩ መንገዶች የሚጎዳ ኃጢአተኛ ነው። እንዲህ አይነት ሰው እራሱን ትልቅ እያደረገ ሌላውን የሚያንቋሽሽ ስለሆነ፥ ከመስማማት ይልቅ ጸበኛነት ይቀናዋል።

ክፉውን ሁሉ በክፉ ለመቋቋም ሲል ተንኮል የሚሸርብ ግንዛቤአዊነት ይጎድለዋል፤ ሰው ሁሉ እንደርሱ ክፉ አለመሆኑን አላወቀምና።

ግንዛቤአዊ ፍቅር እና መስዋዕትነት ተቀራራቢዎች ናቸው። ፍቅር ማለት ራስን ብቻ መውደድ ስላልሆነ፥ ፍቅር ሰውን ከራሱ ያወጣዋል፤ ለሌሎችም አሳልፎ ይሰጠዋል፤ (መስዋዕት ያደርገዋል)። ርህራሄም ከግንዛቤአዊነት ይመነጫል፤ ከግንዛቤአዊነት ጋር የተዋሃደ ፍቅርና ርህራሄም በደንብ ይገለጻል እንጂ አይደበቅም።

አለመግባባቶችን እያስወገዱ በስምምነት አብሮ መኖር እና አብሮ መሥራት የሚያውቁበት ግንዛቤ ያላቸው ሰዎች ናቸው። እነርሱ ከራሳቸው ይልቅ ለሌላው ማሰብ ስለሚቀናቸው፥ የታመሙትን በመጠየቅ፥ ዘመድና ጓደኛ በመጎብኘት ብዙውን

ጊዜያቸውን ያጠፋሉ። ኑሮአቸውን የጋርዮሽ ስለሚያደርጉትም፥ ከሰው ጋር ጨዋታ ያውቁበታል፤ ቶሎ ይግባባሉ። በራሳቸው ችግር ከመዋጥና ከመበሳጨት ይልቅ፥ ለሌላው የሚያደርጉትን ሁሉ ለራሳቸውም እንዳደረጉት ሆኖ ይሰማቸዋል፤ ሁሉን ነገር እንዳገኙ ቆጥረው በኑሮአቸው ይረካሉ፤ በመንፈስም ደስተኞች ሆነው ይኖራሉ፤ ጤነኞችም ይሆናሉ።

ግንዛቤአዊነት ላይ የተመሠረተ ህብረተሰባዊ ባህል፥ ማንኛውንም በተፈጥሮው አፈንጋጭ (አመጸኛ) ያልሆነ ግለሰብ፥ በተወሰኑ ልምዶችና ስነስርአቶች ውስጥ ተስማምቶ እንዲኖር ያደርጋል።

ባህልና ሃይማኖት አንድ ላይ ቢዋሐዱም በውስጣቸው ለግለሰቦች ሁሉ የሚያስብ እናታዊ ግንዛቤአዊነት ከሌለ፥ ያ ሕብረተሰብ ለጋራ ጥቅም በሚሆኑ ቀና አስተሳሰቦች ላይጠናከር ይችላል። በዚች ምድር ላይ እናታዊ ግንዛቤአዊነት በያለበት ቢኖር ኖሮ፥ እኩልነት፥ ሰላም፥ ፍቅር፥ ደስታና የጋራ ብልጽግና ይኖር ነበር።

ይህንን የሚያብራራን አንድ ጥሩ ምሳሌ ከመጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ ምዕራፍ 25 እንመልከት፡-

አንድ ናባል የተባለ፥ ሦስት ሺህ በጎችና አንድ ሺህ ፍየሎች የነበሩት እጅግ ሃብታም ሰው ነበረ። ይህ ሰው በጠባዩ አስተዋይነት የጎደለው - አገናዝቦ መመልከትን የማያውቅ፥ ሞኝ፥ ባለጌ እና ክፉ ነበረ። በአንጻሩ አቢግያ የተባለች ሚስቱ ግንዛቤአዊነት ያላት ቆንጆ፥ አስተዋይ ነበረች።

በዚያን ዘመን ዳዊት ከወታደሮቹ ጋር ምድረበዳ ገብቶ ነበርና፤ የናባልን በጎችና ፍየሎች - ሃብቱን ንብረቱን ሁሉ ወንበዴዎች እንዳይዘርፉበት በነፃ ይከላከልለት ነበረ፤ ይኸንን አድርጌልሃለሁና ይህንን ስጠኝ ሳይል።

ከእለታት አንድ ቀን ናባል የበጎቹን ጸጉር የሚሸልት (የሚቆርጥ) መሆኑን ዳዊት ሰማና፥ ለበጎቹ ሸላቾች ከሚያደርገው ታላቅ ግብዣ በጥቂቱ እንዲያካፍል በትህትና እንዲለምኑት ጎልማሶቹን ላከ። ጎልማሶቹም ወደ ናባል ቀርበው በትህትና ለመኑት። እርሱ ግን የዳዊትን ጀግንነት ያልተረዳ፥ የተደረገለትን ውለታ ሁሉ ማስተዋል የማይችል፥ ክፉ ባለጌ ስለሆነ፥ ለዳዊት የትህትና ጥያቄ ጎልማሶቹ የንቀት እና የስድብ መልስ ይዘው እንዲመለሱ አደረገ። ይህንንም ዳዊት በሰማ ጊዜ፥ ዳዊት በቁጣ ነደደ፤ ናባልን ከነዘመዶቹ ሊጨርሳቸው ወታደሮቹን አሰለፈ።

የናባል አሽከሮች (እረኞች) የተፈጠረውን ግርግር በሰሙ ጊዜ፥ ጠቅላላ ሁናቴውን ለአቢግያ አስረዷት። በእውነት ዳዊትና ወታደሮቹ ሌትና ቀን እንደ አጥር በመሆን ከጠላት ወራሪዎች (ወንበዴዎች) እየተከላከሉ መቆየታቸውን በማስረዳት፥

በጌታቸው በናባል ላይ ክፉ ነገር እንዳይመጣ፥ ማድረግ የሚገባትን እንድታደርግ መከሯት።

አቢግያም ቶሎ ብላ ለጠቅላላ ወታደሮቹ ምግብና መጠጥ በአህዮች አስጭና፥ በጎችም እየነዳች ወደ ዳዊት ገሰገሰች። ከርሱም ዘንድ በደረሰች ጊዜ በግንባሯ ወድቃ -

"ጌታዬ ሆይ ይህ ኃጢአት በኔ ላይ ይሁን፤ እኔ ባርያህ በጆሮህ ልናገር፤ የባሪያህንም ቃል አድምጥ። በዚህ ምናምንቴ ሰው በናባል ላይ ጌታዬ ልቡን እንዳይጥል እለምናለሁ። ... በጌታዬ ላይ ክፉ የሚሹ ሁሉ እንደ ናባል ይሁኑ።...። ..ባርያህ ወደ ጌታዬ ያመጣቺው ይህ መተያያ ጌታዬን ለሚከተሉ ጎልማሶች ይሰጥ።" መጽ. ሳሙ. ቀዳ. 25፡24-31

ይህንን ተናግራ፥ አቤጊያ በለሰለሰ አንደበቷ፥ የዳዊትን ቁጣ አበረደችና ሰላም አወረደች። ዳዊትም- "ወደ ደም እንዳልሄድ፥ በእጄም በቀል እንዳላደርግ ዛሬ የከለከለኝ አእምሮሽ የተመሰገነ ይሁን፤ አንቺም የተመሰገንሽ ሁኚ።" መጽ. ሳሙ. ቀዳ. 25፡33 እያለ መረቃት።

ይህ ታሪክ ግንዛቤአዊነት በጎደላቸው እና ግንዛቤአዊነት ባላቸው ሰዎች መካከል ያለውን የአስተሳሰብ ልዩነት ያንጸባርቃል። እርስ በርስ በመተሳሰብ (በግንዛቤአዊነት) ካልሆነ በስተቀር፥ ሁላችንም በአንድ አለም መኖር የማንችልበት ሁኔታ እየተፈጠረ ነው ያለው።

በዘመናችን የአለም ሃብት በጥቂት ሰዎች ተይዟል። ብዙ አገሮች ግንዛቤአዊነት በጎደላቸው ስግብግብ ባለ ሥልጣኖች ይመራሉ። እነርሱ እንደ ናባል ለራሳቸው ብቻ የሚያስቡ ስለሆኑ የሕዝቡን መጎዳት አያስተውሉም።

ግንዛቤአዊነት የጎደላቸው እጅግ የበለጸጉ ሰዎች ሃብታቸውን ሁሉ ያገኙት በእነርሱ ልፋትና ጥረት ብቻ ይመስላቸዋል፤ በዝቅተኛ ደምወዝ ባገለገሉ ብዙ ሰዎች ምክንያት መሆኑን ይረሱታል። የአብዛኛው ሕዝብ የቀን ገቢ ቢጨመርና ኑሮአቸው ቢሻሻል የበለጠ ምርት እንደሚከማች፥ ብልጽግናም የጋራ እንደሚሆን የሚገባቸው ግንዛቤ ያላቸው ናቸው።

ኦክሲጂን የሚባል ጥሩ የአየር አይነት ከጠራው ሰማይ - እኛ በምድሪቱ አለን፥ ከቆንጆው አየር እየተነፈስን - እንኖራለን፤ ሰማይ ሰማዩን እያየን፥ ኮከብ እየቆጠርን። ምንድነው የምንገነዘበው? ምድራችን በቀለማት አሸብርቃ - አረንጓዴው አረንጓዴ፥ ቢጫው ቢጫ፥ ቀዩም ቀይ ሆኖ እንዲታየን የሚያደርግ ምንድነው? እስቲ አጠቃላይ ግንዛቤአዊነታችንን እንመርምር።

ለሁሉም ነገር ቆንጆ መልክ አለው፥ እስቲ በግንዛቤአዊነት እንመልከተው። አዋቂዎችም ከነጉድለቶቻቸው ነው አዋቂ የሚመስሉት። በመልክ ቆንጆዎቹ ቁንጅናቸውን በራሳቸው ጥረት አላገኙትም። የዋሆች፥ ቂሎችና እብዶች፥ ሁሉም እንዲህ በመሆናቸው ከሰውነት ደረጃ አልወጡም። ጤነኛው የሚያገኘውን ምድራዊ ተሳትፎ ለማግኘት ያልበቁ ህመምተኞች ገና ከምድር አልተሰናበቱም። በልዩ ልዩ ምክንያት፥ አካለ ጎዶሎ የሆኑ ሁሉ እንደማንኛችንም ምድራዊ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ይሻሉ።

እንግዲያውስ ሁላችንም የእግዚአብሔር ልጆች ስለሆን፥ ለመጨረሻው መንፈሳዊ አንድነት ብለን ልዩነቶቻችን አናጉላ። ከምድራዊ ወጣ ገብ ልዩነቶች ባሻገር፥ እርስ በርሳችን በመንፈሳዊ እይታ እየተያየን እንከባበር፤ እንቀራረብ፤ እንዋደድ።

"በሰላም ማሰሪያ የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ ትጉ..።" ኤፌሶን 4፡3

በእርግጥ ልዩነቶችን ሁሉ ማጥፋት ሰውን ሁሉ እንደማጥፋት ይቆጠራል። ምን ጊዜም የአለም ሕዝብ በአስተሳሰብ፥ በባህል፥ በኢኮኖሚ፥ በሃይማኖትም የተለያየ መሆኑ አይቀርም። ሆኖም በግንዛቤአዊነት ለተመለከተው፥ የልዩነቶች መኖር አንዱ ጥንካሬአችን ከመሆኑም በላይ፥ ልዩነቶቻችን ኑሮአችንን እንደሚያጣፍጡትም እንገንዘብ።

ማንም ሰው ከጎኑ ካለ ሰው ጋር በመንፈስ መቀራረብ የሚችለው፥ በትእግስት በመነጋገርና ሃሳብ ለሃሳብ ግንኙነት በማድረግ ነው። ባልና ሚስት በአካልና በመንፈስ አንድ ይሁኑ እንጂ ለየብቻ አይሁኑ። በሃሳብ ላለመታመም ሁልጊዜ ማውራት ያስፈልጋል። ሰዎች በሃሳቦቻቸው ሁሉ አንዱ ከሌላው እየተማረ፥ ለሁሉም ሰው የሚስማማ ሃሳብ ማቅረብ ሲቻል፥ ከሰው ሁሉ የተለየ መሆን፥ ማፈንገጥና ተለይቶ ለብቻ መሆን አይጠቅምም። ማንም ሰው በኑሮው ቀለል ብሎት በሰላምና በፍቅር ሊኖር የሚችለው ከጎኑ ወዳለው ሰው እየተጠጋ፥ አብዛኛውን ሰው እየመሰለ ነው እንጂ፥ ገለል (ፈንጠር) ካለ፥ ጉዳት ላይ ይወድቃል (ይጠቃል)።

ብዙውን ጊዜ እናቶች ከእናታዊ ፍቅራቸው ጋር ግንዛቤአዊነታቸውም የተፈጥሮ ጠባያቸው ስለሆነ ከነርሱ መማር ያስፈልጋል። አስታማሚዎች ብርቱዎች፥ ታጋሾች፥ ሆደ ሰፊዎችና በቶሎ ተስፋ የማይቆርጡ መሆናቸው በሽተኛውን ያጠናዋል፥ ያክመዋል፥ ያድነዋልም። በሆስፒታልም ሆነ በቤት አስታማሚዎች፥ እነርሱ ባለመታመማቸውና ለማስታመምም በሙብቃታቸው እግዚአብሔርን እያመሰገኑ፥ በሙሉ ተስፋና በእምነት ለበሽተኛ የሚያደርጉት እንክብካቤም እንደ ፈዋሽ መድኃኒት ይቆጠራል።

የግንዛቤአዊነት አስፈላጊነት በየሥራ ቦታዎች ሁሉ፥ በትምህርት ቤት፥ በሆስፒታል..ወዘተ. ሲታወቅ የሰዎች የቀን ተቀን ግንኙነት ይሻሻላል፤ ጸብና ጭቅጭቅም ይጠፋል። ለወደፊት ማንም ሰው የሚሠራውን ሥራ እየሠራ ብቻ በሰላም እንዳይኖር እስከዛሬና ለወደፊት ከአይምሮው የሚሰረጹ ሃሳቦች ያስጨንቁታል።

የከፋ ቀን ሲመጣ የግለሰቦችም ጠባይ ቅይር ማለቱ አይቀርምና፤ የሰውን ውስጠ መንፈሱን መርምራችሁ ውደዱት እንጂ፥ በአፋዊ የቃል ምልልስ ልባችሁ አይቀየም። ለመውደድ የፈጠናችሁ ለመጥላት የዘገያችሁ ሁኑ።

ሰው ለሰው መድኃኒት ነው የሚባለው በግንዛቤአዊነት መደማመጥ ሲኖር ነው። አንድ ግለሰብ እንዲህና እንዲያ ቢያስብና በሕብረተሰብ ዝቅተኛ ደረጃ ቢሰጠውም፥ ምን ጊዜም በውስጡ ስለሚኖረው ፍጹም እውነት እያሰባችሁ አክብሩት። አንዱ ሌላውን ያክብር እንጂ አይስደበው።

ሰውን ድሃ ብላችሁ አታንቁት፤ ሞኝ አትበሉት፤ በሞኝነቱ ውስጥም ቢሆን ደግነቱን እዩለት። እግዚአብሔር የሚፈልገው ከሁሉ ነገር ጥሩ ጥሩውን መሆኑን አስተውሉ። ማንም ሰው (የአይምሮ መታወክ የደረሰበትም ቢሆን) እሱነቱን እያወቁለት - ሁኔታውን ሁሉ ከእሱነቱ አንጻር እየተገነዘቡለት ሲረዱት ይረዳል። አለበለዚያ እሱነቱን እያጠፉበት ቢረዱት አይጠቅመውም። የማንኛውም ሰው ህልውና የተጠበቀለት መሆኑ ሲረጋገጥለት፥ ያ ሰው መጽናናትን ያገኛል። የገዛ ራሱን ህልውና የሚያሳጣ ምድራዊ እውነታ ውስጥ በግድ እንዲገባ ሲገፋፉት ግን፥ ያ ሰው ካልታሰበ ጉዳት ላይ ሊወድቅ ይችላል።

በእግዚአብሔር ግንዛቤአዊነት ምክንያት ነው ያልጠፋነው። እግዚአብሔር በኛ ላይ ግንዛቤአዊነት ባይኖረው ኖሮ፥ ኃጢአተኞችን ሁሉ አጥፍቶ፥ ይህችን ምድር ለጻድቃን ብቻ ያደርጋት ነበር። ከነኃጢአታችን ታግሶን ያቆየን፥ መዳኛችንም ያዘጋጀልን፥ የእያንዳንዳችን ድክመት፤ በምድራዊነታችንም ያለብንን ተጽንኦ ስለሚገነዘብ ነው።

ግንዛቤአዊነታችን ለራሳችን፥ ለኢትዮጵያችን፥ ለምድራችንም ሁሉ ይሁን። ምድራችን ግንዛቤአዊነትን ከመንፈሳዊነት የሚያዋህድ - ከሰው ሁሉ ጋር ተቻችሎ የሚኖር ሰላማዊ ሰው ያስፈልጋታል። ስለዚህ፥ የመጨረሻ አላማችን የሆነውን የወደፊቱን ሰው ለመሆን እንጣር።

ሕይወት አጭር ናት፤ ሁሉም ይሆን ዘንድ የጌታ ቃል መፈጸሙ አይቀርም። የሚራዱ መንፈሶች ይመጣሉ። ጠላት ሰይጣን እና በምድር ላይ የሚታየው እርኩስ ሥራ ሁሉ በእግዚአብሔር ኃይል ውድም ብሎ መጥፋቱ አይቀርም።

በጋራ ችግር ተረዳድተን፥
እርስ በርስ ተግባብተን፥
በመንፈስ ተቀራርበን፥
እግዚአብሔር ይርዳን፥
እንድንፈጽም ፈቃዱን፥
አንድነት እና ፍቅር ሳይለየን፥
እስኪያልፍ ድረስ ሕይወታችን።

## <u>የሰብአዊነት ወደፊት</u>

ያለፈውን እና የዛሬውንም በሰፊው አውርተን ስናበቃ - በዚህ ተስፋ በማንቆርጥበት አለም ውስጥ "መጻኢአችን - የወደፊቱ እንዴት ይሆን?" ብለን መጠየቃችን አይቀርም።

ተስፋ የማይቆረጥበት የሰብአዊነት ወደፊት የምድራዊና የሰማያዊ ሂደቶች ቅንጅት ስለሆነ፥ በሰዎች ዘንድ ሊታወቅ ላይታወቅም ይችላል። ግን ለምድራዊ ኑሮአችንም ቢሆን፥ የወደፊቱን ማሰላሰሉ ሳይበጅ አይቀርምና፤ እስካሁን በእውቀት ብዛት ሳይሆን በምናብ - በሃሳብ ብዛትና በስነ አመክንዮ ቅንብብር እንደቆየን ሁሉ፥ አሁንም ከዚያ ትንሽ ፈቀቅ ብለን የሰብአዊነትን ወደፊት እናስተውላለን።

ትንቢት እሙን መነሻ ቢኖረውም፥ በተለያየ መንገድ ይተረጎማል። ለምሳሌ፡ - የሰማይ መንግሥት በምድር ላይ እንደሚሆን ትንቢት አለ። ግን ይህ መንግሥት ምን አይነት መንግሥት ነው? የሚቆየውስ ለምን ያህል ጊዜ ነው?

የመጨረሻው መጨረሻ ሲቃረብ፥ ሰዎችን ለሰማያዊ ኑሮ ለማዘጋጀት ሲባል፥ ሰላምና ፍቅር ለትንሽ ጊዜ (ምናልባት ለሺህ ዓመታት ብቻ) በምድር ላይ የሚሰፍንበት ዘመን ይመጣ ይሆናል።

የሰማይ መንግሥት በምድር ላይ ቢሆን፥ ይህንን አካላዊ ምድራዊ ችግር (የምድራዊነት ሥረ መሠረት) ያቃልለዋል ወይ? ይህ የምናውቀው አካላዊ ክስተት የሚቀጥለው እስከመቼ ድረስ ነው?

ከጥቃቅን የወደፊት ድርጊቶች በስተቀር፥ ስለአጠቃላይ የሰብአዊነት ወደፊት ሰው ሊያውቅ ባይችልም፥ የሂደቶችን አቅጣጫ ተመልክቶ፥ ከዚህስ ይህ ሳይከተል አይቀርም በማለት፥ የትላንትና እና የዛሬው በወደፊቱ ሲተርጎም ምን እንደሚመስል ለማየት ይሞከራል።

ስለ ኑሮ፥ ስለ ጊዜ፥ በጠቅላላ ስለ አለማችን መጨረሻዋ ጉዳይ፥ ተደስተው የሚኖሩና እየተሰቃዩ የሚኖሩ ሰዎች እኩል እንደማይሰማቸው ሁሉ፥ ስለወደፊቱ የተነገረ ትንቢትም በአንድ አይነት መንገድ አለመተርጎሙ አያስደንቅም።

መጨረሻ የሚለው ቃል አንጻራዊ ነው። የምንኖረውም እየሞትን ነው። በትንሹና ከትንሹ የምናውቀው ለጠቅላላ ጠፈር ያገለግላል? እና፥ ታዲያ መጨረሻው ለጠፈር አካላውያን ሁሉ ነው? ወይንስ ለምድራችን ብቻ?[49]

ስለ ሰማያዊው አለም የተነገረ እጅግ በጣም ጥቂት ነው፤ ብዙ ቢነገረንም ላይገባን ይችላል። ለአንዱ የሚገባውን ያህል ሌላው ላይገባው ይችላል፣ ምክንያቱም ከማይታይ አለም ወደ አይምሮ ሰሌዳ ገብቶ ሊመዘገብ የሚችል አካላዊ ያልሆነ ነገር፥ ለተወሰኑ ሰዎች ብቻ ሊሆን ስለሚችል። ነገር ግን፥ እምነት ለአንድ ግለሰብ እውነት ከሆነለት፤ ያ እምነት የግሉ ይሆናል።

ወደፊት[50] ስለሚጠብቀን ቤታችን በግልጽ ልናውቅ ያልቻልንበት ምክንያት፥ ከእውቀት ማነስ አይደለም (እውቀት ሁሉ  ነበረ፤ አለ፤ ይኖራልም)። ከአምስቱ ስሜቶቻችን መካከል፥ በማየት የሚመጣ ግንዛቤ ሊኖር የሚችለው፥ የብርሃን ነጸብራቅ ወደ አይምሮ ሰሌዳ ሲገባና የማየት ስሜቶቻችንን ሲያንቀሳቅስ ነው። አይምሮ ሊመዘግብ የሚችለው ደግሞ ከሞገዶች ውስጥ የተወሰነ ጠባይና ፍጥነት ያላቸውን ብቻ ነው። ከዛ ውጪ ከሆነ፥ አይምሮ መመዝገብ ያቅተዋል፤ ሰውም አይገባውም። አዎ! ከዛ ውጪ የሆነ ነጸብራቅ - አካል ማለት ነው። አካላዊ ያልሆነስ “ነገር” ወደ አይምሮአችን ሰሌዳ ሊገባ አይችልም?

መናፍስት ከፊትለፊታችን ቢመላለሱ አናያቸውም፤ ምክንያቱም የሰው አይምሮ አይቶ ሊመዘግበው ከሚችለው ጠባይና ፍጥነት በላይ (ውጪ) ስለሚነጉዱ ይሆናላ? ባጠገባችን ቢገተሩም፥ በአይን አይታዩም፤ እነርሱ እጅግ ረቂቃን ናቸውና።

የሁኔታዎችን መፈጸም ለማወቅ ከብርሃን ፍጥነት አስቀድመው የሚያዩ ስለወደፊት ቤታችን ተናገሩ፤ የሁሉም ቃል አንድ ሆነ። ካላየሁ አላምንም የሚል ሁሉ በብርሃን ሞገድ ብቻ የሚተማመን ስለሆነ፥ ጊዜው እስኪደርስ ይጠብቃል።

---

[49] ከምድራዊነታችን ባሻገር ሦስተኛ መጽሐፍ ላይ በምዕራፍ ሦስት ስለ የጠፈር መሰብሰብ ከተገለጸው ጋር ያገናዝቧል።

[50] የወደፊቱን ከሁለት ከፍለን - የቅርቡና የሩቁ ወደፊት ብንል፥ ቅርቡ ሩቅ፥ ሩቁም ቅርብ ሊሆን ስለሚችል፥ ባጠቃላይ፥ ነገን፥ የዛሬ ወርን የዛሬ 1000 ዓመትን፥ የዛሬ ሚሊዮን ወይንም ከዚያም በላይ፥ ሁሉንም ወደፊት ማለቱ ይሻላል።

ሳይንቲስቶች ሞገዶችን በመሳሪያ ሲመዘግቡ - ከበጣም ፈጣን እስከ በጣም ዝግተኛ ድረስ ያለውን ነው፤ "ሞገድ የሆነ ሁሉ ከሳይንሳዊ መሳሪያ አያመልጥም..." እያሉ። ግን ሞገድ የአካል መግለጫ በመሆኑ ሳይንቲስቶች ሊመራመሩበት ቢችሉም፥ የመርገብገብ ጠባያቸው በሰኮንድ ከሁለት ትሪሊዎን በላይ ሲሆን፥ ከሰብአዊ ግንዛቤ ውጪ ይሆናል።

ሳይንቲስቶች ከጠፈር ወደ መሬት የሚገቡ የኮስሞስ ጨረሮች (cosmic rays) መኖራቸውን ሲነግሩን እናምናለን፤ ከጎናችን ያለው ወገናችን በምልክት የሚታየውን ሁሉ ሲናገር ግን የሚያምነው ሰው ይጠፋል። ክርስቶስም ለኒቆዲሞስ እንዲህ አለው፡- "ስለ ምድራዊ ነገር በነገርኋችሁ ጊዜ ካላመናችሁ፥ ስለ ሰማያዊ ነገር ብነግራችሁ እንዴት ታምናላችሁ?" ዮሐ. 3፡12

ከድምጽ ሞገድ ይልቅ የብርሃን ሞገድ ስለሚፈጥን የመብረቅን ብልጭታ ካየን በኋላ ነው የነጎድጓዱን ድምጽ የምንሰማው። ስለዚህ፥ የአንዱ ሞገድ ከሌላው ሞገድ መፍጠን የድርጊቶችን መፈጸም አንዱን ከሌላው አስቀድሞ ያሳውቀናል ማለት ነው። ስለዚህ፥ የማየት ችሎታ ኖሮት መስማት የተሳነው እና የመስማት ችሎታ ኖሮት ማየት የተሳነው የመብረቁን መኖር በተለያየ ጊዜ ነው የሚያውቁት። የማየት ችሎታ ኖሮት መስማት የተሳነው ሰው መብረቅ ቢጮህ፥ ከማየት በስተቀር አይሰማውም። የመስማት ችሎታ ኖሮት ማየት የተሳነው ደግሞ፥ መብረቅ ጮኸታም መሆኑ እንጂ፥ ምን አይነት መልክ ያለው አውሬ መሆኑን አያውቅም።

የተጠቀሱት ሁለት ሰዎች በአራት ስሜቶቻቸው ብቻ ጠፈርን መተርጎም እንዳቃታቸው በቅርብ ተከታትለው የተመለከቱ ሰዎች ቢኖሩ፥ እነርሱ ባለ አምስት ስሜቶች በመሆናቸው ኩራት ይሰማቸው ይሆናል፤ ግን ባለ አስር ስሜት ያለው ሰው ቢኖርስ?

የሰው ልጅ ባፈራው ሥልጣኔ አማካኝነት ከአምስቱ ስሜቶቻችን ሁለቱን ብቻ በተለያዩ መሳሪያዎች አጎላናቸው። የሩቁን አየን፤ ከሩቅ ሰማን። ግን አሁንም የማሽተት ችሎታችን ከውሾች የማሽተት ችሎታ አይበልጥም። ጣፋጬን ቀመስን፤ ግን ረሃብ የማንችል ነን። ለቆዳችን ተስማሚ የሆነ አካባቢ ፈጥረን ተለሳልስን፤ ግን በራድ ዘመን ቢመጣ ከሞት ሊያድነን የሚችል ሥልጣኔ የለንም።

እኛ ጠፈርን የምንተረጉመው በአምስት ስሜቶቻችን ብቻ ነው። ይገርማል! ታላቁ ጠፈር በአንድ ታናሽ ፍጡር እና በአምስቱ ስሜቶቹ ብቻ ሲተረጎም። ከዛሬ አንድ ሺህ ዓመታት በፊት የነበረ ኮከብ ዛሬ ይታየናል። የዛ ኮከብ ብርሃን ወደ አይናችን ለመድረስ ብዙ ሺህ የብርሃን ዓመታት ፈጅተውበታል። ብርሃኑ አይናችን በደረሰ ጊዜ ይህ ኮከብ ያውና እንላለን። ግን ባሁኑ ወቅት ያ ኮከብ ሞቶ ሊሆን

ይችላል። በአይናችን የማየት ችሎታ ስንኮራ፥ አይናችን የሌለውንም ያሳየናል ማለት ነው።

ባሁኑ ወቅት አዳዲስ የተወለዱ ከዋክብት ቢኖሩም፥ ብርሃናቸው ወደ አይናችን ካልደረሰ በስተቀር አናያቸውም። ስለዚህ አይናችን ያለውንም ይደብቅብናል። ታዲያ ምንድነው የኛ ኩራትና ትእቢት? ሁሉን እናውቃለን ማለት።

የሰው ጥበብ በእግዚአብሔር ፊት እንደ ዜሮ ይቆጠራል። ማንም ሰው ያሻውን ቢቀባጥር ምንም ለውጥ አያመጣም። ጠቢብ የተባለው ሳይንቲስት፥ ጻዲቅ የተባለውም ሃይማኖተኛ፥ ወይም ሞኝ የተባለው መሃይም፥ ሁሉም የሚመስለውን ይነጋገር እንጂ፥ ይህ ሰው ነው ነቢይ - ሁሉን የሚያውቅ የወደፊቱን መተንበይ የሚችል ማለት ከንቱ ነው።

ለወደፊት እንዲህ ይሆናል ማለት - አንተ እግዚአብሔር እንዲህ ታደርጋለህ እንደማለት ይቆጠራል። ነገር ግን ማንኛውም ወሬአችን ሰውን ከሰው የሚያቀራርብ፥ ውይይታችንም ሰውን በጋርዮሽ እንዲያስብ፥ በበለጠም እንዲግባባ የሚያደርግ ከሆነ፥ እኛ የአለምን ሕዝብ በጠቅላላ የጋራ ችግር ውስጥ የሚከት ሁኔታ ከመምጣቱ በፊት ማሰባችንን እግዚአብሔር ይወዳል።

ስለ መጪው ዘመን እና መሄጃችን በትንሹም ቢሆን እያገናዘብን እንድንመለከት ይህ የክርስቶስ ቃል ያደፋፍረናል - “ምሳሌውንም ከበለስ ተማሩ፤ ጫፍዋ ሲለሰልስ፥ ቅጠሏም ሲያቆጠቁጥ፥ ያን ጊዜ በጋ እንደቀረበ ታውቃላችሁ፤..” ማቴ. 24፡32

<u>ተስፋችን - እስከ ሰማያዊ መኖሪያችን</u>

ያለፈው ባይኖር ኖሮ የዛሬው እንደማይታወቅ ሁሉ፥ ካለፈውና ከዛሬው የተነሳ ሂደት በይቀጥላል ቢታሰብ የወደፊቱን ያሳየን ይሆን? ስለምንኖርባት ምድር በተለያየ መልክ (በሃይማኖት፥ በፖለቲካ፥ በኢኮኖሚ) ጥልቅ ግምገማ እየተደረገ፥ መጪውን ጊዜ እያየነውና እየተዘጋጀንበት ለመኖር እንፍጨረጨራለን፤ አይናችን እያየ ገደል ከምንገባ ብለን።

እንዳው በጥቅሉ - ይህች ምድር ቅራኔ የበዛባት ናትና፤ መጨረሻዋ የሚካተተውም እርሷ እና ቅራኔዎቿ አብረው ሲጠፉ መሆን አለበት እንላለን። ቅራኔ ግን፥ ከጅምሩ ይበረታና የሚቀንስበትና የሚያይልበት ጊዜ ይኖራል። ሆኖም፥ ከመጥፎነት ይልቅ ጥሩነት የሚበልጥ ስለሆነ፥ በመጨረሻ የሚያቸንፍ ጸንቶም የሚቀረው ጥሩው መሆን አለበት።

ጥሩነት ሰማያዊ ሆኖ ለዘለአለም ይኖራል፤ ክፉም ቀን ቢመጣና ሰውም ስቃይ ቢበዛበት እግዚአብሔር አምላክ መጨረሻውን ያሳምረዋል። ሆኖም፥ ለማያቋርጥ መቆየት (ዘለአለማዊ መሰንበት)፥ ከአንዱ ወደሌላው መለወጥ (መቀየር) ግዴታ እንደሆነ ልብ ይሏል።

ስለ ምድራችን የሚጠቅመውን ከማሰብ ባለማቋረጥ፥ እንደ ገና ይህቺን ምድራችንን ከጠፈር አካላት ከሚመጡ ኃይላት ጋር እያገናዘብን፥ የወደፊቱን በአይነ ሕሊና ስንቃኝ፥ ሁሉም (ነፍስ ያለውም የሌለውም) ወደ ፊት የሚጓዝ መሆኑን ብቻ እናውቃለን እንጂ፥ የጠቅላላ ሰብአዊነትን ጉዞ (ከአዳም ጀምሮ) በሦስት ከፍለን፥ የመጀመሪያ፥ የመካከለኛና የመጨረሻ ለማለት አንችልም። ግን እንዳው በጥቅሉ፥ መወለድና መሞት ለዘለአለም ስለማይቀጥል፥ ይህ አካላዊ አለም መጀመሪያ እንደነበረው ሁሉ መጨረሻም ይኖረው ዘንድ ግዴታ ነው እንላለን።

ጠፈር ከተዘረጋ ጀምሮ አያሌ ምድሮችና በውስጣቸውም የሚኖሩ አካላዊ ህያዋን ነበሩ ማለት - አያሌ ምድሮች - አካላውያን ህያዋኖችም ጠፍተዋል ማለት ነው። ታዲያ፥ እስከዛሬ ድረስ ለአካላውያን ሕያዋኖች ሕይወት የሰጡ ስንት ጸሐዮች ሞተው ይሆን? በዛውስ መጠን የስንቱ ጠፈራዊ ህያዋን ህልውና የውሃ ሽታ ሆኖ ቀርቷል።

ብርሃንና ሙቀት በሚሰጡ በጸሐዮች ውስጥ የሚገኙ ነዳጆች (ሁለት የሃይድሮጂን አተሞች አንድ ሂሊየም እየፈጠሩ የሚቀሩ ኃይሎች) ሊያልቁ ሲል፥ የጸሐዮቹም ሰውነቶች ጠባሳዎች ሲያበጁና ግልጥልጥ ሲሉ፥ ጠፈራዊ ምድራዊያን - አካላዊ ህያዋን ሁሉ ባሉበት ጥፍት ይላሉ።

ከብዙ ሺህ (ወይም ከብዙ ሚሊዎን ዓመታት) በኋላ፥ የኛም ፀሐይ አንዴ ቦግ ብላ ከመጥፋቷ በፊት፥ የመጨረሻ የመሰናበቿያዋ ወቅት በአንዳንድ ምልክቶች ይታወቅ ይሆናል። ዛሬ በአይን የማትታየዋ ጸሐያችን፥ በኋላ በደረቅ አይን አካላቷ በግልጽ ሲታይ፥ ነዶ - ነዶ ቀሪው ነዳጅ ምን ያህል ጊዜ እንደሚቆይ በደንብ መገመት ይቻል ይሆናል። ግን ማነው እስከዚያ ድረስ የሚኖር?

የኛ ፀሐይ የምትጨልመው ከብዙ ሚሊዎን (ወይንም ቢሊዎን) ዓመታት በኋላ ይሁን እንጂ፥ ጠፈር እጅግ ቀዝቃዛ ስለሆነ፥ ፀሐይ ጨርሶ ከመጥፋቷ በፊት፥ ሙቀቷ ትንሽ በሚቀንስበት ወቅት (በቅርብ ጊዜ ወስጥ - ከሚቀጥለው ወይንም ከሚቀጥሉት ብዙ የበራድ ዘመናት በኋላም ቢሆን)፥ አካላዊ ህያዋን ሁሉ ጭራሹንም ከምድር ገጽ መጥፋታቸው አይቀርም።

በዘመናችን ሙቀትን በተለያዩ ዘዴዎች ለማግኘት በቅተናል፤ ግን የክረምት ብርድን መቋቋም የተቻለው በዓመት ውስጥ ለጥቂት ወራት ነው እንጂ፥ ዓመቱን ሙሉ የሚቀጥል ቢሆን ካቅም በላይ ነው የሚሆን።

ባጠቃላይ፥ ለወደፊት ለአካላዊ ህያዋን ከመሬት ይልቅ የባህር ኑሮ ነው የሚሻላቸው። ይህንን የባህር አለም እንደ ትልቅ ተስፋ የሚቆጥሩት ሳይንቲስቶች ጥናትና ምርምራቸውን ገና ካሁኑ እንደጀመሩ ሁሉ፥ በባህር ውስጥ ካሁኑ መኖሪያ ማዘጋጀት ለወደፊት ነዋሪዎች ዋና አማራጭ መሆኑ ነው። ከመሬትም ሆነ ከባህር አንዳንድ ለህያዋን የወደፊት መቆያ ሥፍራዎች ተብለው የሚታሰቡትን ሁሉ ማጥናት፥ አንዱ ተስፋ የማይቆረጥበት የወደፊቱ እድል ፈንታችን ነው።

ሥጋዊ ሞት ለሰው ሁሉ የሚዳረስ ቢሆንም፥ በምድር የአካላዊ ህያዋን ሁሉ መጨረሻ እስኪሆን ድረስ፥ የሞቱት ሞተው፥ የተረፉትም ለዘመናት ከትውልድ ትውልድ እራሳቸውን ያቆያሉ። በመጠነኛ ብርሃንና ሙቀት ውስጥም ለኑሮ አስፈላጊውን እንቅስቃሴ ማድረግን ሳይወዱ በግድ ይለምዱታል።

ሙቀት ለተወሰነ ጊዜ በምድርም በባህርም የሚቆይ ከሆነ፥ የሚቀረው ችግር ጨለማነት ስለሆነ፥ ይህንኑ ችግር ተቋቁመው አብዛኛውን ጊዜ በባህር፥ ለጥቂት ጊዜም ወደ ምድር ብቅ እያሉ የሚኖሩ፤ እንደ አሳ የሚዋኙ፥ እንደ ጅብ በጨለማ የሚያዩ፥ በመጠኑ የሚተነፍሱ፥ በመጠኑ የሚበሉና የሚጠጡ..ወዘተ. ፍጥረታት (ሰው አይሉት አውሬ?) ትንሽ በምድር ይቆዩ ይሆናል።

ዛሬ እኛ የምናውቃቸው ሕዝቦች ሁሉ፥ ረሃብና ጥማት የማይችሉ፥ ጥቂት ቢቀዘቅዛቸው ወይንም ቢሞቃቸው በቀላሉ የሚሞቱ ለስላሳዎች ናቸው። እግዚአብሔር ሁሉን አስተካክሎ ፈጥሮላቸው ነው እንጂ፥ በራሳቸው ተፈጥሮን ተቋቁመው ብዙ ሊኖሩ አይችሉም። በሰሜን ዋልታ የሚኖሩ ድቦች ግን ከሦስት እስከ አምስት ወራት ድረስ በትንሽ በትንሹ እየተነፈሱ፥ ካለ አንዳች ምግብ፥ የክረምቱን ወራት ተኝተው ያሳልፉታል (hibernation)።

የኛይቱ ምድር ፀሐይ ስትጨልም፥ ከጠፈር ውስጥ ከሚገኙ ሌሎች ምድሮች መካከል በአንዳንዶቹ ላይ ሕይወት ያብባል ተብሎ ስለሚታሰብ፥ አልሞት ባይ ተጋዳይ የሆነ የሰው ዘር ለወደፊት የሚያዋጣው ወደ ባህር ውስጥ በመግባትም ቢሆን፥ ወደ ቬኑስ እና ወደ ሜርኩሪ በመዝመትም ቢሆን፥ ወይንም እዛው ፀሐይ ላይ ጉብ ብሎ እንጨት አቀጣጥሎ እሳት እንደመሞቅ ያለውንም ሃሳብ ቢመኝ፥ አካላዊ ሕያው ሆኖ የሚቆይበትን ከማሰብና ከማድረግ ወደኋላ አይልም - ተስፋ የማይቆረጥበት የወደፊቱ እድል ፈንታችን - አካላዊ ህልውናችን።

መፈጠር ማለት ካለመኖር ወደመኖር መሸጋገር ከሆነ፥ የተፈጠረ ሁሉ (ነፍስ ቢኖረውም ባይኖረወም) ሲፈጠር እራሱን ሆኗል ማለት ነው። እራሱን መሆን ያቃተው ሁሉ ይሞታል (ይፈርሳል)። ታዲያ፥ ማንኛውም የጠፈር አካል ከተፈጠረ ጀምሮ እስካሁን ድረስ እራሱን ሆኖ ቆይቷልና፤ እራሱን ሆኖ መቆየት ሲያቅተው ይሞታል (ግን አይጠፋም)። እንደገና አካል ሆኖ ይወለዳል፤ ወይንም በሰማያዊ አካልነት (በፍጽምተ አካላዊነት) መኖር ይጀምራል።

ምድር እራሷን መሆን እያቃታት ስትለዋወጥ እንደቆየች ሁሉ፥ ለወደፊትም እንዲሁ እየተለዋወጠች ትቆያለች። ግን ከጠፈር አካላት ሁሉ ጋር ባላት ግንኙነት፥ ተለውጣ - ተለውጣ ፈጽሞ እራሷን (ምድራዊ አካላዊነቷን) መሆን ቢያቅታት፥ የመጨረሻ እድሏ እራሷን ከምድራዊ አካላዊነት ወደ ሰማያዊ አካላዊነት (ንጽረ አካላዊነት) መለወጥ ነው። እንዴት?

ስለ ጠፈር መሰብሰብ ባወሳነው መሠረት፥ ጊዜው ይርዘምም ይጠርም፥ ይህ አካላዊነት ቀጥ የሚልበት ወቅት ይመጣል (ይሆናል?)። ቀኑ ቢፋጠንም/ባይፋጠንም፥ አንድ ቀን ወደ ሰማያዊው አለም ግቡ - ግቡ የሚባልበት ወቅት ይመጣል (ይሆናል?)። ከዛ በፊት ግን፥ ይህ የተበታተነ ሕብረተሰብ በፈጣሪ አምላኩ የቅዱስ መንፈስን እንድነትን ለማግኘት እርስ በርሱ እንዲፋቀር የሚያደርጉ ሁኔታዎችን ለመፍጠር መትጋት ይኖርበታል፤ ማንኛውም ሃይማኖት የበኩሉን ያደርግ ዘንድ ውዴታው ወደ ግዴታ መለወጡ አይቀርምና።

<u>ኃጢአት ተሠርቶ ሲያልቅ?</u>

የሰውን ውስጣዊ ክፋት የሚያባብሰው ምድራዊነት (ለሥጋ ብቻ ማሰብ - ሰይጣናዊ መንፈስ) መሆን አለበት እንጂ፥ ሰው ያን ያህል መጥፎ ሆኖ አለምን ለማጥፋት አይችልም። እንግዲያውስ፥ እያንዳንዱ ሰው የሚሠራው ሥራ ሁሉ በሰማይ ቤት ከተጻፈ፤ የአለምም መጨረሻ በሰማይ ቤት ከታወቀ፤ መሆን ያለበት እንዲሆን ግዴታ ነው። ይህም ማለት - ዛሬና ለወደፊት የሚሠራ ኃጢአት የተጻፈ ስለሆነ፤ መሠራት ያለበት ኃጢአት ሁሉ ይሠራል[51]።

[51] መጽሐፈ ዕዝራ ሱቱኤል ምዕራፍ 3ን ከኦርቶዶክስ መጽሐፍ ቅዱስ ይመለከቷል።

ኃጢአት ተሠርቶ ሲያልቅ፥ የጻድቃን ቁጥራቸው የተፈለገውን ያህል ሲሆን (መሬትን የመሳሰሉና ሌሎች ከመሬት የተሻሉ ሥፍራዎች ሲዘጋጁ ማለትም ሊሆንም ይችላል)፤ የዚያን ጊዜ "የዚህ ትውልድ መጨረሻ" ይሆናል።

መሠራት ያለበት ሁሉ (ኃጢአትም ቢሆን) ይሠራል። እርስ በርስ መደባደብ፥ መጣላት (ጦርነት) የማይቀር ነው፤ ግን ሁሉም ፍጻሜ ይኖረዋል። መታሰብ ያለበት ሁሉ (ክፉውም፥ ጥሩውም) ይታሰባል፤ ከዚያም ቀጥሎ (ከማሰብ ጋር ተያይዞ) መደረግ ያለበት ሁሉ ይደረጋል። መበተን ያለበት ሁሉ ይበተናል፤ መለየት ያለበት ሁሉ ይለያል። ይህ ሁሉ ለምንድነው? አካላዊ - ሃሳባዊ (ምናባዊ) ልዩነቶች ሁሉ ቁልጭ - ቁልጭ ብለው እንዲታዩ እኮ ነው። ጥቁሩ ጥቁር ብሎ፥ ነጩም ንጥት ብሎ፥ ቢጫውም ብጭጭ ብሎ መታየት አለበት።

በአካላዊ አይናችን ብቻ ሳይሆን፥ በመንፈሳዊውም እንመልከትና፥ የምድራችንን አካላዊና ሰማያዊ ገጽታ እያሰላሰልን - ወደ ተጠቀሰው ቁልጭ ቁልጭ ብሎ መታየት ደረጃ ተደርሷል ወይ? ብለን እንጠይቅ። ታዲያ ስንመለከተው - የአለም ሕዝብ በአካላዊ ቁመናው፥ በአስተሳሰቡ፥ በሃይማኖቱ፥ በሥልጣኔው፥ ባጠቃላይ ፍጥረቱና ሥራው ሁሉ ቁልጭ - ቁልጭ ብሎ ታይቷል። ከእንግዲህ የተቀረው መሰባሰብና አንድ መሆን ነው።

በምድር በመኖር የሚሠራ ሥራ (ከንውን) ሁሉ፥ እስከሞት የሚያደርስ ቢሆንም፥ ለሰው ልጅ አስፈላጊ በመሆኑ፥ ይኸው ሰው ሁሉ በሕይወት ይኖራል፤ ወይንም (እና) ይህ ለሰው ልጅ አስፈላጊ የተባለው ምድራዊ ሥራ (ከንውን) ወደ ልዩ አለም የሚከተው ይሆናል። "ይማረክ ዘንድ ያለው ማንም ቢኖር ወደ ምርኮነት ይሄዳል፤ በሰይፍ የሚገደል ማንም ቢኖር ራሱ በሰይፍ እንዲገደል ይገባዋል።" ዮሐ. ራዕ. 13፡9

የአስቆሮቱ ይሁዳ በልቡ ያሰበውን ቶሎ ያደርግ ዘንድ ክርስቶስ ለይሁዳ እንዲህ አለው - "የምታደርገውን ቶሎ ብለህ አድርግ።" ዮሐ. 13፡27 ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህንን ያለው የርሱ መያዝ - መገረፍ - በመስቀልም ተሰቃይቶ መሞት የሚከተለው ይሁዳ ከሸጠው በኋላ መሆኑን ስለሚያውቅ ነው። (መሠራት ያለበት ኃጢአት መሠራት አለበት፤ ከዚያ በኋላ ለሚፈጸመው አስፈላጊ ከሆነ)።

አካላዊ ሃሳባዊ ልዩነቶች ቁልጭ - ቁልጭ ብለው መታየታቸው ሲያበቃ፥ መቀራረብ (መሰብሰብ) ይከተላል። ግን እስከዛው - "ዓመጸኛው ወደፊት ያምጽ፤ ርኩሱም ወደፊት ይርከስ፤ ጻድቁም ወደፊት ጽድቅ ያድርግ፤ ቅዱሱም ወደፊት ይቀደስ አለ.." ዮሐ. ራዕ 13፡14

እስከዚህ ግልጽ ከሆነ፥ የመቀራረብን (የመሰባሰብን) መልካም ጎን እንመልከተው። መሥራት ያለበት ኃጢአት ተሠርቶ ካላለቀ፥ በእርግጥ እቸናፊው ቅዱስ መንፈስ መሆኑ በግልጽ አይታወቅም።

ግን፥ እግዚአብሔር የሰዎችን ጩኸት ይሰማል። ቅዱስ መንፈሱን በጎ ወደሚያስቡ ሰዎች ይልከላቸዋል። እግዚአብሔር ለተጎዱ ሰዎች ሁሉ (አዋቂ/አላዋቂ ሳይል፥ እውነተኛ/ሃሰተኛ ሳይል፥ ነጭ፥ ጥቁር፥ ሂንዱ፥ አይሁድ..ወዘተ. ሳይል) ያስብላቸዋል።

የአለም "መጨረሻው" የተወሰነ ከሆነ፤ ይህንንም የሚወስነው የሰው መጥፎነት ወይም ጥሩነት ከሆነ፥ የሰውን መጥፎነት ወይም ጥሩነት የሚያጎለምስ የውጭ ኃይል መኖር አለበት። ይህም የውጭ ኃይል ሥራውን ከሠራ፥ የአለም መጨረሻ ልክ በተወሰነለት ወቅት ሊፈጸም እርግጠኛ ይሆናል። ይህም ማለት፥ አቅጣጫ ቢስ ከሆነው የሰዎች እንቅስቃሴ፥ የበላይ ሆኖ አቅጣጫ የሚያስይዝ መንፈስ አለም በተወሰነ አቅጣጫ አምርታ፥ መጨረሻዋ እንደተፈለገው እንዲገባደድ ያደርጋል ማለት ነው።

ይህንን መሠራት ያለበት ኃጢአት ሁሉ ይሠራል፤ የሚለውን ኃይለ ቃል ከእስራኤላውያን መሰደድ እና አራት ትውልድ ያህል ከግብጽ መቆየት፥ እስከዛው ድረስም ለእስራኤላውያን በሚሰጥ መሬት ላይ አሞራውያን ኃጢአታቸውን እየሠሩ ከመቆየታቸው ጋር ማመሳከር ይቻላል።

" ...በአራተኛው ትውልድ ግን ወደዚህ ይመለሳሉ፤ የአሞራውያን ኃጢአት ገና አልተፈጸመምና።" ኦሪት ዘፍ. 15፡16

በምድራችን ኃጢአት ተሠርቶ የሚያልቀው መቼ ነው? የሰው ልጅ ክፋም ደግም ነውና፤ ክፋቱ በውጪ ኃይል (እርኩሳን መናፍስት) የከፋ፥ ደግነቱም በውጪ ኃይል (ቅዱሳን መናፍስት) የጎላ ስለሆነ፥ ሰው በሁለት ተከፍሎ እርስ በርሱ ይጨራረሳል።

ሰውን ሰው ሊያጠፋው አይችልም። ለወደፊት በቦንብ የሚበተኑ በስባሽ ቁስ አካሎች በጨረር መልክ የአካላዊ ህያዋንን ሲጠቀጥቁ ከሞት የሚተርፉት በመባዛት ኑሮአቸውን ይቀጥላሉ። በዚያን ጊዜ በተራራማ ሥፍራዎች ውስጥ፥ በባህር አካባቢ በሚገኙ ዋሻዎች ውስጥም ተደብቆ የሚኖር ሰው መደበኛ ምግቡ አፈር ቢሆን፤ ሳርና ቅጠልም የተለየ በዓል ሲከበር የሚበላ የክብር ምግብ ቢሆን፥ የአካላዊ ህያዋን በምድር የመቆያ ጊዜ ከተራዘመ፥ የሰው ልጅ እየተቸገረም ቢሆን ኑሮውን ይቀጥላል።

## አዳዲስ ዜማዎች - መንፈሳዊ መዝሙሮች

ሕዝቦች አለማዊና መንፈሳዊ ስሜቶቻቸውን በዜማ - በጩኸት ሲገልጹ እንደቆዩ ሁሉ፥ ለወደፊትም ይህ ይቀጥላል። አሁን አለማዊ ዘፈን የሚባለው ቀስ በቀስ እየተለወጠ፥ ፍጹም መንፈሳዊ ይሆንና፥ የዛን ጊዜ ሙዚቃ ለሰው ልጅ እንደ አየር፥ ውሃና ምግብ አስፈላጊ ይሆናል። ብሶት ግን በልፍለፋና በጩኸት ብዛት ይቃለላል እንጂ ፈጽሞ አይሰናበትም።

መንፈሳዊ መዘምራንም ከምድራዊነት ወደ ሰማያዊነት በሚያመዝነው መንፈሳዊ ስሜቶቻቸው ተስፋ ካለመቁረጥ፥ በጩኸት የማያውቁትንና ያላዩትን ሲጣሩ - ሲጣሩ ነው እዚህ የደረሱት። ለወደፊትም የጸሎት፥ የጥሪና የምስጋና መዝሙሮቻቸውን ይቀጥላሉ። "በክብር ከፍ ከፍ ብሎአልና፥ ለእግዚአብሔር እዘምራለሁ፤.. ..ጉልበቴ ዝማሬዬም እግዚአብሔር ነው...." ዘጸ. 15፡1-2 እያሉ ይዘምራሉ።

የአለም ሕዝብ በሁለት ተቃራኒ ስሜቶች ሲወጠር፥ ሃዘንና ደስታም ይቀላቀሉና፥ አንዱን ከሌላው መለየት ያቅታል፤ ዘፈን እያስመሰለ ብሶቱን ሁሉ የሚለፈልፍ ይበዛል። በአለም ዙሪያ የሙዚቃ ዜማዎች (ኖታዎች) ቀስ በቀስ ይህንን አሳዛኝ ሰብአዊ ስሜት በማጠቃለል የሚገልጹ ስለሚሆኑ፥ እንዲህ አይነቱ አሳዛኝና አስደሳች ዜማ ለሁሉም ሰው አንድ አይነት ይሆናል። ይህም የሚያበስረው የዚህ ትውልድ ሰው ከራሱ የመሰናበቻው ወቅት መቃረቡን ነው።

".. ..የእግዚአብሔርን ስም እጠራለሁና፤ ለአምላካችን ታላቅነትን ስጡ። እርሱ አምላክ ነው፤ ሥራውም ፍጹም ነው፤ መንገዱም ሁሉ የቀና ነው፤ የታመነ አምላክ፥ ክፋትም የሌለበት እርሱ እውነተኛና ቅን ነው።" ዘዳ. 32፡1 እያለ ሙሴ እንደዘመረ፤ ከሙሴ እስከ ዛሬ ዘልቆ፥ ለወደፊትም እና ለምንጊዜም እግዚአብሔር በመዝሙር እንደሚመሰገን ዮሐንስ ሲገልጽ- "የእግዚአብሔርን በገና ይዘው በብርጭቆ ባህር ላይ ሲቆሙ አየሁ።" ብሎ - "ሁሉን የምትገዛ አምላክ ሆይ ሥራህ ታላቅና ድንቅ ነው፤ ..." ዮሐ. ራዕይ 15፡3 እያሉ ዘመሩ ብሏል። እኛም እያዜምን፥ እየቀደስን፥ እየዘመርን፥ እየዘፈንን፥ እያንጎራጎርን መጪውን እንጠባበቃለን።

## አዲስ ሰው - አዲስ ሃይማኖት - አዲስ ንቃተ ሕሊና

ለወደፊት የሰው ልጅ በአይምሮው ህመምተኛ እንዳይሆን፥ ሃይማኖት ለስሜትም መቆጣጠሪያም ሆኖ በየትምህርት ቤቱ ይሰጣል። ሃይማኖት በምድራዊነት ላይ አለመተማመንን እና በሰማያዊ ተስፋ መደሰትን፥ ምድራዊ ሃዘንን መለማመድና፥ በሚያናድድ ሁኔታ ውስጥም ሁሉ ትእግስተኛነትን የሚያስተምር ነው። ይህ ትምህርት

- ቋሚዎች መጪውን የከፉ ጊዜ ለመቋቋም፤ ስሜቶቻቸውንም መቆጣጠር እንዲችሉና እንዲጠናከሩ ያደርጋል።

ማንኛውም ምድራዊ አመለካከት እስኪጠፋ፥ ወይንም ሕዝቦች ሁሉ በአንድ በእግዚአብሔር ሃይማኖት እስኪጠቃለሉ ድረስ፥ ይህቺ አለም በራሷ ሕዝቦችና ከውጪ በሚመጣ ኃይል ትቀጠቀጣለች። አከራሪዎችና ግብረአበሮቻቸው እስኪጠፉ ድረስ ታላቅ እልቂት ይሆናል።

ማንኛውም አይነት አድሎአዊነት (ዘረኛነትና ማንኛውም አይነት የበላይነት ስሜት) እስኪጠፋ ድረስ፥ ይህቺ አለም በራሷ ሕዝቦችና ከውጪ በሚመጣ ኃይል ትቀጠቀጣለች።

በጥቅሉ ስንመለከተው፥ ለወደፊት ሕዝቦች ሁሉ በምድራችን በሚገኙ ሃይማኖቶች የታቀፉ ቢሆኑም፥ ጥሩውን ሰው ከመጥፎው ለመለየ፥ ለወሳኙ የቅዱስና የእርኩስ መንፈስ ጦርነት ነው እንጂ፥ በሃይማኖቶች መካከል የጎላ ልዩነት ኖሮ እርስ በርስ አያጋድልም።

ከሚመጣው ታላቁ የጥፋት ዘመን ቀጥሎ የሚቀጥለው ትውልድ ከምድራዊነት አልፎ የሚሻገር እስከ ጠፈር የሚዘልቅ ከፍተኛ ንቃተ ሕሊና ይኖረዋል። የዛን ጊዜ እግዚአብሔር ለሚያምኑበትና ለሚሰግዱለት ሁሉ (እስላም፥ ክርስቲያን፥ አይሁድ፥ ሂንዱ..ወዘተ..) አምላካቸው ይሆናል። ‹‹እግዚአብሔር ጽዮንን ይሠራታልና፤ በክብሩም ይገለጣልና።” መዝ. 102፥16

በአንዲት ወቅት (ከብዙ ሺህ ዓመታት በኋላም ቢሆን) አካላዊ ህያዋን ሁሉ (እንስሳትም፥ እጽዋም) ውድም ብለው የሚጠፉበት ወቅት መምጣቱ አይቀርም፤ ግን ከዛ በፊት ብዙ መለዋወጦች ይኖራሉ። ዝግመተ ለውጥ ያይደለ፥ እንደ ቅጽበተ ፍጥረት የመሰለ ለውጥ መምጣቱ አይቀርም።

እግዚአብሔር እንደገና አዲስ ሰው ቢፈጥር፥ ያ አዲስ ሰው ቀጥቅጠው ቢገድሉትም በገዛ ኃይሉ ነፍስ ዘርቶ የሚነሳ ባይሆንም፥ ከሁለት ሺህ ዓመታት በፊት የተወለደውን ኢየሱስ ክርስቶስን ይመስላል ብንል እንዲህ ነው፡- “እርሱ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ፥ ከእግዚአብሔር ጋር **<u>መተካከልን መቀማት እንደማይገባ</u>**[52] ነገር አልቆጠረውም። ነገር ግን የባርያውን መልክ ይዞ፥ በሰው ምሳሌ ሆኖ፥ ራሱን ዝቅ አደረገ።..” ፊሊጵስዩስ 2፥7

[52] ይህ ጠለቅ ያለ ትርጉም ስለሚኖረው፥ በሠፊው ካልተብራራ ቶሎ ላይገባ ይችላልና፤ ከሃይማኖት ምሁራን ጋር መወያየትን ይጠይቃል።

ምድራዊ አስተሳሰብን ለአንድ ጊዜ ወደኋላ ብለን - የሥጋን ነገር ትተን፥ የመንፈስን ነገር እናስበው። የሰው ልጅ እንዲህ እንደተጠቀሰው አይነት ጠባይ ሲኖረው (በመንፈሱ ክርስቶስን ሲመስል)፥ ሰብአዊነት በአንድ ፍቅር (One Love)፥ አንድ ልብ እና አንድ ሃሳብ ወደፊት ብቅ ይላል፤ ያብባል፤ በደስታም ወደፊት ይጓዛል።

ትንቢት ያልሆነ - እንዳው በደምሳሳው ለውጥ ይመጣል ማለት - ለወደፊት የሰው ልጅ የበለጠ እግዚአብሔርን (መንፈሱን - ጥሩነቱን) እየመሰለ ይመጣል እንደማለት ይቆጠራል። ይህንን ማንም ሊያውቀው እንደሚችል ሁሉ፥ ይህ እንደሚሆን አምነን፥ እግዚአብሔርን ካሁኑ በበለጠ በመንፈስ ለመምሰል የምንጥር ደስ ይበለን።

መላው ጠፈርን እንደ አንድ ትንሽ ኳስ በእጁ ይዞ ማቆየት የሚችል፥ ጠፈርን መዘርጋትና ማቆየት፥ ካቆየም በኋላ ማጥፋት የሚቻለው እግዚአብሔር የኛን ህልውና ለዘለአለሙ የሚያስከብርበት ልዩ አለም እያዘጋጀልን መሆኑን ወንጌሉ አሳውቆናል። "..እኔ ባለሁበት እናንተ ደግሞ እንድትሆኑ ሁለተኛ እመጣለሁ፤ ወደ እኔም እወስዳችሁኣለሁ.." ዮሐ. 14፡3

ከምድራዊነታችን ባሻገር - በአካላዊነት ከሚታየው ጠፈር አንጻር ሲተያይ እጅግ ትልቅ የሆነ ሌላ አለም ይኖራል፤ የዘለአለም ደስታ ወዳለበት እንሄዳለን ብለን አምነናል።

ይህ ያሁኑ ሁኔታ ለዘለአለም እንደማይቆይ ለማንም ሰው ግልጽ ነው። ለወደፊት የተፈጥሮ ሁኔታዎች ይለዋወጣሉ። ስለዚህ፥ ወይንም አምላካችን በፈቀደ እንለወጣለን።

አምላካችን ለሚሠራው ሥራ ሁሉ ጠፈራዊ ምክንያት ይኖረዋል። ከእንግዲህስ፥ ሰውና ምድር አብረው (ተያይዘው) ይጠፋሉ እንጂ፥ ሰውም እንደ ዳይናዞሮች ምድር ከመጥፋቷ በፊት አይጠፋም። እንዲሁም የምድራዊነት የመጨረሻው መጨረሻ ሲገባደድ ብቻ ነው ምድራዊነት ጭልጥ ብሎ ጠፍቶ ሰማያዊነት የሚተካው። የዛን ጊዜ ሰው በአካላዊ ሰውነቱ መቆየቱ ያከትማል።

"እነሆ አንድ ምሥጢር እነግራችኋለሁ፤ ሁላችንም አናንቀላፋም፤ ነገር ግን፥ የኋላኛው መለከት ሲነፋ፥ ሁላችንም በድንገት በቅጽበተ አይን እንለወጣለን፤ መለከት ይነፋልና፤ ሙታንም <u>የማይበሰብሱ</u> ሆነው ይነሳሉ፤ እኛም እንለወጣለን።" 1ኛ ቆሮ. 15፡52-53

የዛሬው ሰው ብዙ የሚበላ፥ ቶሎ የሚደክመው፥ ቶሎ የሚሞትም ነው። ታዲያ፥ መቼ ነው እግዚአብሔር ይህንኑ የተዳከመ አካላዊ ሰው የሚያድሰው - በጥበቡ አዲስ አካላዊ ሰው የሚፈጥረው?

በዘመኑ ጄኔቲክ ኢንጂኒሪንግ - ዲ ኤን ኤዎችን በመነካካት አንዳንድ የሰውነት አብራኮችን መለዋወጥ የሚቻልበት ዘመን ይመጣ ይሆናል። በሽታዎችን መቋቋም የሚያስችል ኬሚካል ቢፈጠርና ሰውም ጤነኛ ሆኖ፥ ዕድሜው ቢራዘምለት፥ ይህ ሁሉ ለወደፊት የሚፈጸም ሊሆን ይችላል።

የዘመኑ ሰው የሚገባው፥ ሰው የሚያውቀውን የዲ ኤን ኤን ሥራ ነው። ከዚህ በበለጠ ረቂቅ የተፈጥሮ ምሥጢር፥ እግዚአብሔር ይህንን አካላዊ ሰው ቢለውጠውና አዲስ ሰው ቢፈጥር፥ ይህ አዲስ ሰው በአየር ላይ የሚንጠለጠል፥ በባህር ላይ የሚንሳፈፍ፥ በባህር ውስጥም መኖር የሚችል፥ በትንሹ የሚበላ፥ ለፍጥረታት ሁሉ የሚያስብ፥ በዚህች ምድር ላይ ከእንስሳት፥ ከአውሬዎችና ከእጽዋቶች ሁሉ ጋር በስምምነት ለመኖር የሚችል ቢሆን፤ የዘመናችን ጄኔቲክ ኢንጂኒሪንግ እንዲህ አይነቱን ጥበብ ከየት ያገኘዋል?

የዛሬው ዘመን ሰው በሽተኛና ደካማ ከመሆኑም በላይ በጠባዩ ብልሹ ነው። እንዲህ ያለ ሰው ቶሎ መጥፋት አለበት። በምትኩ በመልኩና በቁመናው አንድ ወጥ - ቆንጆ፥ በአስተሳሰቡና በእምነቱ ቀና፥ ደግ፥ በአጠቃላይ ጥሩ - አዲስ ሰላማዊ - ክርስቶሳዊ ሰው ይፈጠራል (ይሆን?)። ይህ አዲስ ሰው ብዙ ዓመታት የሚኖር - በመቶ ዓመቱ እንደ ማይክል ጃክሰን የሚደንስ ጠንካራ ይሆናል (ይሆን?)።

በአለም ዙሪያ የተበተኑ ዘሮች ሁሉ ባንድነት ሲሰበሰቡ - በአንድ የሰው ዘር ብቻ ሲጠቃለሉ፡- ሃይማኖት፥ ቋንቋ ባህልና ስነአይምሮአዊ አመለካከቶች ሁሉ አንድ አይነት ሲሆኑ፥ ይህ ሳይሆን አይቀርም የአዲሱ ሰው መፈጠሪያ ቅድመ ዝግጅት።

<u>*ገሃነም*</u>

በምድራችን ላይ አንድ መንግሥት ሌላውን ለመገልበጥ ሲነሳ፥ የደጋፊዎችና የተቃዋሚዎች ጦርነት ተካሂዶ ነው። አቸናፊው መንግሥት፥ ተሸናፊው እንደገና እንዳይነሳበት ለማረጋገጥ ሲል፥ ተቃዋሚዎቹን ወደ እስር ቤት ይከታቸዋል። ከዚያም እንደፈጸሙት ጉዳት እየታየ ፍርድ ይሰጣቸውና ይቀጣሉ።

የተቀጡት እንደተቀረው ሕዝብ በሰላም የሚኖሩ ከሆነ ምህረት ይደረግላቸዋል፤ ዳግመኛ በመንግሥት ላይ አመጽ በማስነሳት አገር የማያውኩ ሁሉ

በነጻ ይለቀቃሉ። በምድራችን ላይ የጠባይ ማረሚያ (እስር ቤት) ያስፈለገው ለዚህ ነው። ይህንን የመሰለ ቅጣት በሰማይም ሊኖር እንደሚችል አንባቢ ያስተውል።

<u>ሰማያዊ ድንጋጌ እና ሰብአዊ ግንዛቤ</u>

ሠፊውን አካላዊ ጠፈር የሚገዛ የተፈጥሮ ሕግ መኖሩን እናውቃለን፤ ግን ይህንን ሕግ ከእግዚአብሔር በስተቀር ማንም አያውቅም። አዎ! በምድር ላይ ሕብረተሰብን የሚያስተዳድር ሕግ እንደመኖሩ ሁሉ፥ በሰማይም ተመሳሳይ ሕግ ሊኖር ይችላል። እንዲሁም ቅራኔዎች በጠፈር ውስጥ ሁሉ እንደሚኖሩ ሁሉ፥ በሰማይም ይኖሩ ይሆናል።

“ይህ ከሰማያዊ ድንጋጌዎች አንዱ የሆነ የገሃነመ እሳት ነገር (ምሥጢር) ምንድነው?” ሲሉ ሰዎች ይጠይቃሉ’ “ፍጠረን ሳንለው ፈጥሮን፥ በምድር የተሰቃየነው አንሶ፥ እንደገና በሰማይ ቤት ለዘለአለም እንድንቃጠል ገሃነመ እሳትን ለሰዎች ያዘጋጀ አምላክ እጅግ ጨካኝ መሆን አለበት...” ይላሉ።

በሚዋደዱ ባልና ሚስት መካከል የቅሬታ መንፈስ ቢፈጠር፥ እርስ በርሳቸው በሠፊው ለመወያየት በር ቢከፍቱ ቅሬታው ወደ ፍቅር እንደሚለወጥ ሁሉ፥ እኛም በፍርኃት ስለማናነሳው ስለ ገሃነመ እሳት ጉዳይ ብንወያይ፤ ለኛ ለሰዎች ከእግዚአብሔር ከጭካኔው እና ከፍቅሩ የትኛው እንደሚበልጥ ለማወቅ ይረዳን ይሆናል።

ምድራዊ ችግሮችን (አለማወቅንም) እየረሱና ችላ እያሉ  መኖር ሲያቅተን እና ከችግር ለማምለጥ ስንሻ፥ ከአይምሮአችን የሚመነጨው ሃሳብ ወሰን አይኖረውም። ግን፥ ዛሬም ነገም እኛው ስለሆንን፥ ወደራሳችን እንመለስና፥ በስነአይምሮአችን የሚጉላላውን እንበትነው።

የምናምንበትን እንድናውቀው ወይንም ባናውቀውም ለምናምንበት ነገር ማጠናከሪያ ይሆንልን ዘንድ፥ በብዙ ሰዎች አይምሮ ስለሚጉላላ ስለ ገሃነመ እሳት ጉዳይ በሚከተሉት ጥያቄዎች እንጀምር፡-

- የገሃነመ እሳት ዘለአለማዊነት ከሰው የክፋት ዘለአለማዊነት (የሰይጣን መኖር) ጋር የተያያዘ አይደለም ወይ?
- መንግሥተ ሰማይ የማይገባ ነፍስ ካለ፥ እስኪገባ ድረስ ተፈላጊውን ትምህርት ይወስድ ዘንድ፥ የተዘጋጀለት ማረፊያ ሥፍራ ይኖር ይሆናል እንጂ፥ እኛ የሰው ልጆች ይህች ምድራችን በሥጋ ያቃጠለችን አንሶ ለምንድነው ለሁለተኛ ጊዜ በእሳት የምንቃጠለው?

- የገሃነመ እሳት ከዚህ ቁርጥርጥ የግለሰብ ሕይወት ጋር ያለው ግንኙነት ምንድነው?
- የገኃነም እሳት መኖር በጠፈር ለሚኖሩ ሁሉ እርግጠኛ ቢሆን፥ እኛን ሰዎችን በተመለከተ፥ ቅጣት የሚደርሰን በዚሁ በምድር ላይ ነው ወይንስ ሌላ ቦታ ሄደን ነው የምንቀጣው?
- በሚገባን ቋንቋ ሲነገር - ገሃነመ እሳት ማለት የሚያቃጥል ማለት ሲሆን፤ ይህም ምድራዊ ኃጢአቶችን እየሠራ ለሚኖር ሰው ኃጢአት መሥራቱን እስኪተው ድረስ ዘለአለማዊ ቅጣት መኖሩን እንዲገነዘበው ብቻ የታቀደ ይሆን?
- በሰማይ ቤት መፈጠር በምድር ላይ ሞት ነው ካልን፥ ሰማይና ምድር የተለያዩ እንደመሆናቸው መጠን፥ መቃጠል የሚለው ቃል ትርጉሙ ሰማያዊ ከሆነ፥ እኛ እንደምናስበው አይነት የሥጋ ማቃጠል አይነት ላይሆን ይችላል። ታዲያ ምን አይነት ማቃጠል ሊሆን ነው? ይህስ ማቃጠል ያማል ወይ? ማመምስ ሥጋዊ አገላለጥ አይደለምን? ወይስ ለነፍስም የሚያገለግል አገላለጥ ነው?
- በምድራችን ላይ እሳት ቢኖር፥ የሚያጠፋው ውሃም ይኖራል። የገሃነመ እሳት የማቃጠል ባህርዩ ሥጋዊ ካልሆነ፥ "ያቃጥላል" ለሚለው ቃል ትርጉም አይገኝለትም። እሳት አካላዊ ሆኖ ማቃጠልም ምድራዊ ትርጉም ቢኖረው፥ ስለ ነፍስ መቀጫ ማወቅ የማንችል መሆናችንን አይደለም ወይ የሚያሳየው?

የሚሆን ነገር ሁሉ፥ እውነት የሚሆነው እንደየፍላጎታችን ሳይሆን፥ መሆን ያለበት (እግዚአብሔር የፈቀደው) ብቻ ነው። የማይመስልም ነገር ካለ፥ የመኖሩ እውነት የእምነታችን ማረጋገጫ ይሆን ነበር፤ ግን እውነቱን ለይቶ ማወቅ ነው የተሳነን።

ሥጋ ቢቃጠል ከመቅጽበት ተኮማትሮና አሮ ያልቃል፤ ታዲያ የሚቃጠለው ነፍስ ከሆነ፥ መቃጠል የሚለው ቃል ለነፍስ አያገለግልም፤ ነፍስ ቢቃጠልም እንደ አካል ህመም የማያውቅ ነውና (ነወይ?)።

"The Soul can never be cut to pieces by any weapon, nor burned by fire, nor moistened by water, nor withered by wind " B.G.:2:23

ትርጉም- "ነፍስ በመሳሪያ አይቆራረጥም፥ በእሳት አይቃጠልም፤ በውሃ አይርስም፤ በነፋስ አይዝግም።"

ስለ ገሃነመ እሳት የምንነጋገረው ከምድራዊነት ወይንም ከሰማያዊነት አንጻር መሆኑ ተለይቶ ካልታወቀ፥ በቋንቋ አለመግባባትም ይኖራል ማለት ነው።

የቋንቋ ችግር ስለመኖሩ እንመልከት - "እነሆ ነፍሳት ሁሉ የእኔ ናቸው...ኃጢአት የምትሠራ ነፍስ እርሷ ትሞታለች።" ሕዝቅኤል 18፡4

ትሞታለች አለ እንጂ፥ ትቃጠላለች አላለም። ዮሐንስም "በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘለአለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ.." ዮሐ. 3፡6 አለ እንጂ፥ እንዳይቃጠል አላለም።

በትርጉም ካልተለየ በስተቀር፥ "ለዘለአለም" የሚያቃጥል እሳት እና "ለዘለአለም" የሚቃጠል ሰው (ነፍስ) መኖር ከስነ አመክንዮ ውጪ ነው (በእርግጥ)።

ገኃነም የተባለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ በተለያየ መንገድ መገለጹን እንመልከት።

"እሳት ከቁጣዬ ትነዳለችና፥ እስከ ሲኦል ድረስ ታቃጥላለች..." ዘዳ. 32፡22

"ነፍሴንም ከታችኛዪቱ ሲኦል አድነሃታልና.." መዝ. 86፡13

"ሲኦልና ጥፋት በእግዚአብሔር ፊት የታወቁ ናቸው፤ ...።" ምሳሌ 15፡11

"ሲኦልም ሆዷን አስፍታለች፤ አፍዋንም ያለ ልክ ከፍታለች፤ ከበርቴዎቻቸውና አዛውንቶቻቸው፥ ባለጠጎቻቸውም፥ ደስተኞቻቸውም ወደ እርሷ ይወርዳሉ።" ኢሳ. 5፡1

በምድር ላይ ጥፋት ያጠፋ ሰው መቀጫው ብዙ አይነት እንደሆነ፥ በሰማይም እንዲሁ ሊሆን ይችላል። ግን በዝርዝር እንዳይነገር ተብሎ - ባጠቃላይ ገሃነመ እሳት ተባለ (ይሆን?)።

ከጥንት ጀምሮ፥ ኢየሩሳሌም ውስጥ ጌሄኖም የተባለ ቆሻሻ ሥፍራ አለ። እስካሁን ድረስ ከዚህ ሥፍራ የሚኖሩ እንደዝቅተኛ ሰው ይቆጠራሉ - ጌሄኖም (ገኃነም) የመጥፎ ሥፍራ መግለጫ ቃል።

ዮሐንስም - በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘለአለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ ሲል፥ ዘለአለማዊ ሕይወትን ያላገኘ (ከሰማይ መንግሥት ያልገባ) እንደጠፋ የሚቆጠር መሆኑን ለመግለጽ ይሆናል (የሚቃጠል ሳይሆን)።

ለሁለት አለም የሚያገለግል ቋንቋ እንዴት ሊኖር ይችላል? ካሁን በፊት የተጻፉት የሃይማኖት መጻሕፍት፥ በድግግሞሽ ስለ ገሃነመ እሳት መኖር ያመለከቱ ቢሆንም፥ ሰው በየዋህነቱ የሚመስለውን ይቀበላል።

ለሦስት መቶ ዓመታት በጠፈር ሲመላለስ፥ በሥጋዊ አይኑ (ወይም በመንፈሳዊ አይኑ?) ያየውን ሲናገር - ሄኖክ እንዲህ አለ - "በዚያም ቦታ ዓይኖቼ ጥልቅ ቁላን አዩ፥ አፉም የተከፈተ ነው። .. ይህም ጥልቅ ቁላ አይመላም።" ሄኖክ 14፡ 12 -13

"እነዚያም ሰባው ነገሥታት መምራኑ ተወቀሱ፤ ኃጢአተኞችም ሆኑ፤ እነሱም ወደዚሁ ጥልቅ ገኃነም ወደቁ። እንደዚሁ እሳትን በተመላ ምድር መካከል አንድ ገኃነም ተከፍቶ አየሁት።" ሄኖክ 34፡9 - 10

ይህንን በሄኖክ የተገለጸውን ገሃነመ እሳት በሁለት መልኩ እንመልከተው። ሄኖክ ይህንን እሳት ያየው በሥጋዊ አይኑ ከሆነ፥ ይህ ገሃነመ እሳት አካላዊ ነው። በጠፈር ውስጥም (በሰማይ ያይደለ!) ገሃነመ እሳትን የመሳሰሉ፥ ብዙ አስፈሪ አካላዊ ሥፍራዎች ይኖራሉ። ነፍስ በእንዲህ ያለ አካላዊ ሥፍራ የምትቃጠል ቢሆን፥ አሁንም ነፍስን አካላዊ ማስመሰላችን ነው።

ሄኖክ የገለጸው ገሃነመ እሳት በመንፈሳዊ አይኑ ያየውን ከሆነ - እነዚያም ሰባው ነገሥታት ...ወደዚሁ ጥልቅ ገኃነም ወደቁ ሲል፥ በገኃነም የሚገቡ አካላዊ ያልሆኑ ኃጢአተኛ መላእክት መሆኑን ይገልጻል። ይህስ ለኛ ስላልሆነ፥ ቃጠሎው ለነርሱ እንዴት እንደሆነ ማወቅ አይጠቅመንም።

ሄኖክ በጠፈር የተመላለሰ ሰው ስለሆነ፥ የርሱን ጽሑፍ በቀላሉ መመልከትና፥ ስለኛ ስለመሬት ሰዎች ብቻ እንደሚያወራ አድርጎ መውሰድ ትክክል ላይሆን ይችላል።

የሰማይ ቤት መኖሪያችን ሰው እንደየሥራው ከሚሰጠው ፍርድ ጋር የሚያያዝ ቢሆን፥ ይህም ምድራዊ ኑሮ በሌላ መልኩ ከሰማይም የሚቀጥል ቢሆን፥ መቀጫ ሥፍራ (ገሃነመ እሳት) የግድ መኖር አለበት። ለጥሩነት ተቃራኒ ካለው፥ መንግሥተ ሰማይም ጥሩ ከሆነ፥ ተቃራኒው ገሃነመ እሳትም ይኖራል። ስለዚህ የሄኖክ ጽሑፍ - ገሃነመ እሳት ለመጥፎ መናፍስት (ለሰይጣን)፤ ከሰዎችም መካከልም ለሰይጣን ምልምሎች መቀጣጫ የተዘጋጀ ሥፍራ መሆኑን ይጠቁማል - ይህንን ብቻ ማወቁ ይበቃን ይሆን?

ገና ሰው ሳይፈጠር፥ እስካሁን ድረስና ለወደፊትም፥ ሰይጣን ይቀጣል። የሰው ልጅም ባጠፋ ቁጥር እንዲሁ ይቀጣል፤ ይህም የገሃነመ እሳት ህልውና የጸና - ሰማያዊ እና ዘለአለማዊ መሆኑን ያመለክታል። ይህ ገሃነመ እሳት (መቀጫ ሥፍራ)

ዘለአለማዊ ይሆንና፥ ማንም አካላዊ ያልሆነ ሰው (ሰማያዊ - ሚሻክላዊ ሰው) ባጠፋ ቁጥር ይቀጣበታል።

ሰው ሰማይ ቤትም ከገባ በኋላ ኃጢአት የሚያሠራ ሁኔታ ቢያጋጥመው፥ ለጥፋቱ መቀጫ ሥፍራ (በካቶሊክ ፐርጋቶሪ) መኖሩ የዘለአለማዊነትን እውነታ ያረጋግጣል። የሰማይ ሰው ዘለአለማዊ ከሆነ፥ ኃጢአት በሠራ ቁጥር መቀጫ ሥፍራ - ጥልቅ ቁላ - ጥልቅ ገኃነም - ገሃነመ እሳት (እስር ቤት) አለለት ማለት ነው።

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ አለ - "እጅህ ወይም እግርህ ብታሰናክልህ ቆርጠህ[53] ከአንተ ጣላት። ሁለት እጅ ወይም ሁለት እግር ኖሮህ ወደ ዘለአለም እሳት ከምትጣል ይልቅ፥ አንካሳ ወይም ጉንድሽ ሆነህ ወደ ሕይወት መግባት ያሻልሃል። ዓይንህ ብታሰናክልህ፥ አውጥተህ ከአንተ ጣላት፤ ሁለት ዓይን ኖሮህ ወደ ገሃነመ እሳት ከምትጣል ይልቅ፥ አንዲት ዓይን ኖራህ ወደ ሕይወት መግባት ይሻልሃል።" ማቴ. 18፡8 - 9

ይህ ጥቅስ ገሃነመ እሳት መኖሩን እና ገሃነመ እሳት ምን ያህል መጥፎ እንደሆነ በሥዕላዊ መንገድ ይገልጻል። "ወደ ዘለአለም እሳት ከምትጣል..." ሲል ለዘለአለም "የሚነድ" እሳት መኖሩን ይገልጻል፤ ግን ለዘለአለም የሚቃጠል ሰው ይኖራል ለማለት አይደለም።

አካል እስኪጠፋ ድረስ ቅራኔ ስለሚኖር፥ አካልና አካላዊ ሕይወት ባለበት ሥፍራም የእርኩስና የቅዱስ መናፍስት ቅራኔና ትግል መኖር አለበት፤[54] ስለዚህ ሰይጣን በጠፈር ሁሉ አለ።

በመጽሐፍ ቅዱስ ዘለአለም የሚለው ቃል የአነጋገር ዘይቤ ሆኖ በረጅም ዘመን የሚፈጸም ሁኔታን (ድርጊትን) ለማመልከት ሊሆን እንደሚችልም የሚጠቁሙ ጥቅሶች ስላሉ፥ እነርሱንም እንመልከታቸው።

"......ስለዚህ ለዘለአለም ባሪያ ይሆነኛል ብሎ ዳዊትን አመሰገነው።" ማቴ. 18፡8 – 9 እስኪሞት ድረስ ማለቱ ነው እንጂ ሰው ለዘለአለም ባሪያ ሊሆን አይችልም።

እንዲሁም በእንግሊዝኛው King James version:- "Let the king live for ever.." ሲል በአማርኛው ደግሞ፡- "..ንጉሡ ሺህ ዓመት ይንገሥ።" ነህምያ

---

[53] ከእግዚአብሔር የሚያርቁህን ሁሉ ከአንተ አርቅ ማለት ነው፤ ከከእግዚአብሔር በመራቅ የሚገኝ ጥቅም ሁሉ ጊዜያዊ ነውና።

[54] በማንኛውም አካል ባለበት ሥፍራ ሁሉ ሁለት ተጻራሪዎች የግድ መገኘት አለባቸው።

2፥3-12 ይላል። አሁንም ንጉሡ ለረጅም ጊዜ ይኑር ማለቱ ነው እንጂ፥ ሰው ለዘለአለም ወይንም ሺህ ዓመት አይነግሥም።

ገሃነመ እሳት ለመጥፎ መናፍስት (ለሰይጣን) መቀጣጫ ሲሆን፥ ሰውም ከነርሱ ጋር ከተባበረ፥ ተመሳሳይ ቅጣት እንደሚደርስበት ክርስቶስ ተናግሯል።

"በዚያን ጊዜ በግራው ያሉትን ደግሞ ይላቸዋል - "እናንተ ርጉማን ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀ ወደ ዘለአለም እሳት ከእኔ ሂዱ። ተርቤ አላበላችሁኝምና፥ ተጠምቼ አላጠጣችሁኝምና ..." ማቴ. 25፥41 - 42

ለኛ ለእግዚአብሔር ልጆች መጥፎ መሥራት ቃጠሎ፥ ለመጥፎ ሰው መጥፎ መሥራት ጨዋታ እንደሚሆን ሁሉ፤ ይህ ገኃነም የተባለው ሥፍራ ለመጥፎዎቹ መኖሪያ ሥፍራቸው ቢሆን፥ ለጻድቃን ግን በመኖሪያነት ሲታይ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት የበዛበት ይሆናል፤ ከእግዚአብሔር መራቅም እንደ እሳት ማቃጠል ይቆጠራልና።

በምድር ላይ ሳለች ኃጢአት የሠራች ነፍስ ቅጣቷን በምድር ሳትፈጽም የዘለአለም ሕይወት ወደሚገኝበት ወደ ሰማይ እሄዳለሁ ብትል፥ ሳትታሰርና ሳትቀጣ አይሆንላትም። ከጉድለቷ ጋር ብዙ መቆየትም ስለማትችል፥ ሞትን፥ ጥፋትን፥ ኃጢአትን፥ ባጠቃላይ መጥፎ ነገርን ሁሉ ባንድነት ከውስጧ አስወግዳ መው ሕያው ሆና መኖር የምትችል፤ ለዘለአለም የሚቆይ ፍጹማዊ እውነት ብቻ ነውና።

ቅጣት በሰማይ ያስፈለገው በምድር ላይ የሚሰጥ ቅጣት አድሎአዊ ስለሆነ ይሆናል። በምድር ኃጢአት ያበዛ ሰው በምድር ላይ ባይቀጣ፥ ከሞት በኋላ ቅጣት አይቀርለትም። ለምሳሌ፡- አንድ ጨካኝ አረመኔ አንድ ሺህ ሰው ገድሎ እርሱ ግን በምድር ላይ ሳይሰቃይ በድንገት ቢሞት፥ ያንን ሰው የሰማይ መንግሥት አይለቀውም።

"የሰው ልብ ከሁሉ ይልቅ ተንኮለኛ፥ እጅግም ክፉ ነው፤ ማንስ ያውቀዋል? እኔ እግዚአብሔር ለሰው ሁሉ እንደ መንገዱ፥ እንደ ሥራው ፍሬ እሰጥ ዘንድ፥ ልብን እመረምራለሁ፤ ኩላሊትንም እፈትናለሁ።" ኤር. 17፥9-10 እንዲል፥ በምድር ላይ ትክክለኛ ፍርድ አይኖርም፤ የሰውን ኃጢአት ሰው መርምሮ ሊደርስበት አይችልምና።

ሰው ሲሞት፥ ያ ጥንድ ሰው ሲነጣጠል፥ የዚያን ጊዜ ለዛ ተገንጥሎ አንድ ወጥ ለሚሆን ሰው (ሰማያዊ ሰውነት ያገኘች ነፍስ) የሚሰጥ ፍርድ ትክክለኛ ይሆናል። ስለዚህ ኃጢአት ሠርታ በምድር ላይ ዕዳዊን ሳትከፍል አምልጣ ሰማይ የገባች ነፍስ፥ በግድ ዕዳዋን መክፈል ስላለባት፥ ወደ ዕዳ ማስከፈያ ሥፍራ (ሲኦል፥ ጥልቅ ቁላ - ጌሄኖም - ገኃነም..) ትገባለች።

ይህንን ጉዳይ የተለያዩ ሃይማኖቶች በተለያየ መንገድ ይገልጹታል። አንባብያን ከሂንዱዎች ስለ ሁለት አለማት - ስቫራጋም እና ናራካም፥[55] እንዲሁም ከካቶሊኮች ስለ ጊዜአዊ መቆያ ሥፍራ - ፐርጋቶሪ[56] ጉዳይ ቢመለከቱ - በሰፊው ጠፈር ውስጥ ያለነው እኛ ብቻ ካልሆንን፥ የገሃነመ እሳትም ጽንሰ ሃሳብ የዛኑ ያህል ሊሰፋ እንደሚችል - እንደ ሂንዱዎች ናራካም (ከመሬት ትንሽ ለየት ያለ ሥፍራ) ሊሆንም እንደሚችል መገመት አያስቸግርም።

የጠፈር አካላት ሁሉ ከመጠፋፋት የተረፉ በመሆናቸው፥ ከመጥፋት የተረፉት ሁሉ አጥፊዎቻቸውን እንደ ዘለአለማዊ አጥፊ ከመመልከት በስተቀር ሌላ ምርጫ የላቸውም። በተቃራኒውም እንዲሁ ነው።

ገሃነመ እሳትን እንደ አጥፊው መጥፎ አድርገን ብንመለከተው፥ ቅራኔ እስካለ ድረስ፥ የገሃነመ እሳት ህልውናውም የጸና መሆኑን ያረጋግጣል።

ከመጠፋፋት ተርፈን መኖራችን ከዚህ ቢያደርሰን፥ አሁንም አጥፊያችን ከውስጣችን አልጠፋም። አጥፊው እንዳይበረታብን መከላከያ ዘዴውን ሁሉ ከሃይማኖት በየጊዜው እየተማርን እንኑር።

በምድራዊነታችን ውስጥ ሰማያዊውንም በቅንነት ለማየት ስንሞክር፥ የመጨረሻው ማረፊያችን ጥሩ (መንግሥተ ሰማይ) ይሆናል። “የምናመልከው አምላካችን ከሚነድደው ከእሳቱ እቶን ያድነን ዘንድ ይችላል።” ዳን. 3፡ 17

በማናውቀው ውስጥም የሚያስከፋና የሚያስደስት ይኖራል። ሆኖም ያ የሚያስከፋ ወይንም የሚያስደስት ነገር በምን አይነት መንገድ ወደኛ እንደሚመጣና ስሜቶቻችንን እንደሚለዋወጥ አላወቅነውም። ግን፥ በዚችው በምድራችን ሊገባን የሚችለውን በስሜት ከተገነዘብን፥ የኛ ምርጫ ለመከፋት ምክንያት ከሆኑት ነገሮች መራቅ እና ወደሚያስደስቱ ነገሮችም መቅረብ ይሆናል። ይህንኑ በምሳሌ እንመልከት።

እነሆ በአንድ የአፍሪካ አህጉር፥ በአንዲት መንደር ውስጥ፥ ሁለት ባርያዎችን እየገረፈና እያሰቃየ በማሠራት የከበረ አንድ መጥፎ ነጭ ሰው ነበር። ከሁለቱ ባሪያዎች አንደኛው በተፈጥሮው ጥሩ ነበር። ሌላኛው ግን በተፈጥሮው መጥፎ ነበር።

---

[55] ስቫራጋም - ናራካም - ከማንኛውም ምድራዊ እንቅስቃሴ በስተጀርባ ፍርድ ይኖራል (ለጥሩ ሥራ ሽልማት፥ ለመጥፎ ሥራም ቅጣት)። የሰው ልጅ በምድራዊ ኑሮው የፈጸማቸው ሁሉ የግለሰቡን ምድራዊና ሰማያዊ ኑሮ ይወስናሉ። ስለዚህ፥ ሰው ሲሞት ጥሩ ሰዎች ሳይቀጡ በደስታ ወደሚኖሩበት የብርሃን አለም - የሰማይ መንግሥት (ስቫራጋም) ይገባል። ወይንም፥ መጥፎ ሰዎች እየተቀጡ እና በየጊዜው እየታረሙ ወደሚኖሩበት የጨለማ አለም (ናራካም) ይገባሉ።

[56] ፐርጋቶሪ - የሰው ልጅ ሲሞት ነፍሱ ለጊዜው የምትሰነብትበት ሥፍራ።

ከእለታት አንድ ቀን ሁለቱ ባሪያዎቹ ተጣሉና፥ መጥፎው ባሪያ ጥሩውን ባሪያ ደብድቦ ገደለው። ያም ነጭ ከበርቴ ባርያውን ባርያው ስለገደለበት ተናዶ ገዳዩን ባርያ አሰቃይቶ ገደለው። እርሱም ከጥቂት ቀናት በኋላ ታመመና ሞተ።

ሁለቱ ገዳዮች (ባርያና ባርያ ገዢ) ኃጢአተኞች ስለሆኑ ለሰይጣን በተዘጋጀ ሥፍራ (ገኃነመ እሳት) ገቡ። ያ ጥሩ ሰው ግን ከመልካሙ ሥፍራ (መንግሥተ ሰማይ) ገባ።

ከእለታት አንድ ቀን፥ ይህ ጥሩ ሰው በመንግሥተ ሰማያት ደስ በሚሉ ሥፍራዎች ሲመላለስ፥ ከሩቅ የሚነድ እሳት አየ። ወደ እሳቱ ቀረብ ብሎም ለማስተዋል አካባቢውን ለቆ ተጓዘ። ግን ከኋላው አንድ ጠባቂ መልአክ ይከተለው ነበር። ወደ እሳቱም በተጠጋ ጊዜ በውስጡ የሚመላለሱ ሰዎች ተመለከተ። እሳቱ ይነዳል፤ በውስጡም ያሉ ሰዎች ህያዋን ናቸው። ይህ እንዴት ይሆናል ብሎ ሲጠጋ አንድ ጥቁርና አንድ ነጭ ሲደባደቡ ተመለከተ። እነኚህም በምድር ላይ ነጩ ጌታውና ጥቁሩ ገዳዩ መሆናቸውን ሲገነዘብ፥ እጅግ በመገረም ወደ እሳቱ የበለጠ ተጠጋ፤ መልአኩም ተከትሎት ከጎኑ ቆመ።

ጥቁሩ ሰው በመሬት ላይ የነበረው ጉልበት ከዚህም ሥፍራ ያለ ይመስላል። በነጩ ሰው ላይ በረታበት፤ በጥፊ በጡጫ በእርግጫ እየደበደበ እረፍት አሳጣው። በዚህን ጊዜ ያ ጥሩ ሰው ሃዘን ተሰማውና ከጎኑ የቆመውን መልአክ - "ይህ ድብድብ እስከ መቼ ድረስ ይቀጥላል?" አለው። መልአኩም - "ለዘለአለም ቢቀጥል አንተ ምን አገባህ!" አለው።

ጥሩው ሰው - "ይህ ትክክለኛ ፍርድ አይደለም.." በማለት ለመልአኩ መለሰለት። ይህንን ስለተናገረ መልአኩ ተናደደና - "አንተ ማነህ የእግዚአብሔርን ፍርድ የምታቃልል!..." ብሎ ዘለፈው። ጥሩውም ሰው - "እኔ የእግዚአብሔርን ፍርድ ማቃለሌ አይደለም፤ የገኃነም እሳቱ እያቃጠላቸው፥ እርስ በርስ መደባደቡም ሲጨምር እጅግ አሳዝኖኝ ነው እንጂ!..." ብሎ መለሰለት።

መልአኩ ዝም ሲል፥ ጥሩው ሰው እንዲህ አሰበ - የገሃነመ እሳት ማቃጠልና ዘለአለማዊነት ይቅርታ ለማያደርጉ ሰዎች ብቻ መሆን አለበት። ሰው ቂምና በቀልን ከልቡ ካጠፋ በእሳት መቃጠል የለበትም። ምናልባት እነኚህ ሰዎች ይቅር ቢባባሉ፥ ከሁለቱ አንዱ ችግር ይቃለልላቸው ይሆናል። ለማንኛውም ከመሃላቸው ገብቼ ልገላግላቸው።

እኔን በባርነቱ ጌታዬ የነበረ በድሎኛል፤ ይኸኛውም የተበደለ ባሪያ ደብድቦ ገደለኝ። ሁለቱንም ይቅር ብላቸው ድብድባቸውን የሚያቆሙ መስሎኛል በማለት፥

እራሱን ለመሰዋትና እነኚህን ሁለት ሰዎች ለማዳን ቆረጠ። ወዲያውም - "ወደ እሳቱ ገብቼ ልገላግላቸው..." ብሎ ሲናገር፥ መልአኩ እጅግ ተናደደ።

"አንተም ገኃነም እሳት ውስጥ ገብተህ ለዘለአለም በገዳይህ መገደል፤ ለዘለአለሙም በባሪያ ገዢህ መደብደብና መሰቃየት ትፈልጋለህ?" ብሎ በመቆጣት፤ ይልቅስ ከመጣንበት እንመለስ ብሎ አዘዘው። ዳሩ ግን ጥሩው ሰው በመንፈስ ቅዱስ እየተገፋፋ ወደ ገሃነመ እሳት ውስጥ ገባ። መልአኩም እየተመለከተ፥ ምንም ማድረግ ሳይቻለው፥ እንደ ፈዘዘ ቀረ።

ጥሩው ሰው ከእሳቱ ውስጥ ሲገባ፥ እነኛ የሚደባደቡ ጥቁርና ነጭ ድብድባቸውን አቆሙና ወሬ ማውራት ጀመሩ። ይህም ጥሩ ሰው ብዙ- ብዙ ነገር ይነግራቸው ጀመር። በመጀመሪያ፥ ይህ ጥሩ ሰው በምድር ላይ ባርያ የነበረውን ገዳዩን ይቅር ብዬሃለሁ አለው። ገዳዩም እኔ የገደልኩት ሰው እኔን ይቅር ካለኝ እኔስ ለምን ገዳዬን ይቅር አልለውም ብሎ፥ በምድር ላይ ባርያ ገዢ የነበረውን ነጩን ሰውዬ ይቅር አለው። ቀጥሎም ነጩ ሰው ይጸጽተው ጀመር። "ምድራዊ ሕይወታችሁን በሙሉ በባርነት ቀንበር ስላንገላታኋችሁ ይቅር ትሉኛላችሁ ወይ?" ብሎ ጠየቃቸው። እነርሱም በአንድነት ሆነው ይቅር ብለንሃል አሉት። ሦስቱም በይቅርታ ፍቅር ተሳሰሩ። ከዛን ጊዜ በኋላ ያ ገኃነም የነበረው ሥፍራ ተለውጦ የሳቅና የደስታ ሥፍራ ሆነ።

መልአኩም ከውጭ ሆኖ ሦስት ሰዎች ስምም ሆነው ሲጫወቱ አስተዋለ። እነርሱም - "ለእግዚአብሔር ምን ይሳነዋል፤ ለእግዚአብሔር ምን ይሳነዋል፤ ገኃነምን ወደ መንግሥተ ሰማያት የለወጠ.....፤" እያሉ ይዘምሩና ይቀድሱ ጀመር።

መልአኩም ይህን ሁሉ ሁኔታ በመመልከት ተደናገረ። ያ ሥፍራ ገሃነመ እሳት መሆኑ ቀርቶ ከፊቱ ልውጥ ሲልበት ሊያምን አልቻለም። ይልቅስ ይጠብቀው የነበረውን ሰው ከቁጥጥሩ ውጪ ሆኖ ስለሄደበት፥ የተሰጠኝን ሥራ አላከበርኩም በማለት፥ ከዳር ሆኖ ተጣራ፤ የሚሰማውም በማጣቱ ተደናገጠ። ፈጣሪዬ እኔን በቸልተኛነቴ ይቀጣኛል ብሎ ለራሱ ፈራ።

ደጉም ሰው ከእሳቱ መካከል ወጥቶ ለመልአኩ አንድ አዲስ ነገር በፈገግታ ይነግረው ጀመር። "ሰዎች በምድር ላይ ሲኖሩ፥ የበደለ ይቅርታ ለመጠይቅ፥ የተበደለም ይቅር ለማለት እድል ሳያጋጥማቸው በሞት ይቀጠፋሉ። ግን ከዚህ ሥፍራ ሲመጡ፥ ይህ ይቅር የአለማለት ዕዳ ከምድር ባይከፈል፥ የግድ ከዚህ መከፈል እንዳለበት፥ አለበለዛ እሳቱ እንደማይጠፋ ተገንዝብኩ..፡" አለ። በመቀጠልም ፈገግ በማለት - "ይህንን በምድር ሳይከፈል የቀረውን ታላቅ ዕዳ እንዲከፈል ለማድረግ እንድችል የመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ መሆኑ እጅግ ደስ ብሎኛል።"

መንፈስ ቅዱስም ወደ መልአኩ ቀረበና ስለማያውቀው ጉዳይ መከረው - ከእርሱ የማወቅ ችሎታ በላይ ሌላ ነገር መኖሩን ገለጠለት። መልአኩም - "በእግዚአብሔር ፍርድ ውስጥ ጣልቃ አትግባ ብዬ ስናገር ካለማወቅ ጋር መሆኑን ተገነዘብኩ። በእውነት ይህ ገሃነመ እሳት እኔ እንዳሰብኩት አይነት ላይሆን ይችላል፤ ገሃነመ እሳት መቀጫ ሥፍራ ቢሆንም፥ ቅጣቱ በምን አይነት መንገድ እንደሚካሄድ አልገባኝም ነበር። የእግዚአብሔር ፈቃድ በሌለበት ሥፍራ ሁሉ የርሱ ፈቃድ እንዲኖር ለማድረግ መንፈስ ቅዱስ የማይደርስበት ሥፍራ የለም። ማንኛውም ነገር እንደየአስፈላጊነቱ፥ በጊዜ ውስጥ ሊቀየር ሊሻርና ሊለወጥ እንደሚችል መንፈስ ቅዱስ ገለጠልኝ። ከሰው ልጅ ኃጢአት ትንሿም ብትሆን ሳትጠፋ፥ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ገብቶ ተደስቶ መኖር እንደማይቻል፤ በምድር ያልተከፈለ ዕዳ ከዚህም ሊከፈል እንደሚቻል አሁን ገባኝ..." ብሎ ጭጭ አለ።

ይህንን ምሳሌ ያመጣነው ስለ "ገሃነመ እሳት" ጉዳይ እንኳን ሰው መላእክት እንኳን ላያውቁ እንደሚችሉ፥ አዋቂና አላዋቂ በተጻፈና በተነገረ ላይ እንዲመዘን፥ ባልተጻፈና ባልተነገረው ላይ ግን ማንም ከማንም የበለጠ እንደማያውቅ ለማመልከት ነው።

በሰማይም በምድርም ሊሆን የሚችለውንና ሊሆን የማይችለውን ሁሉ እንዴት የሰው ልጅ ሊያውቅ ይችላል? መቼም ከሃሳባዊ ምሳሌ በመነሳት ይህ ከሆነ ይህ ይሆናል አይባልም። ግን፥ በምድር ያለ ጥሩነት በሰማይም ቢቀጥል፤ የሰማይ ሰው ጥሩነቱን ለመግለጽ ሲል እራሱን እስከመሰዋት ሊደርስ አይችልምን?

የማይረሱና ይቅርታ የማያደርጉ ሰዎች ይቅር አለማለታቸው የውስጥ በሽታ ሆኖ ሲያቃጥላቸው፤ በአንጻሩም ሰዎች ምድራዊ ችግሮችን እየረሱና ችላ እያሉ፤ ይቅርታ እያደረጉ ሲኖሩና ምድራዊ ኑሮአቸው ሲሻሻል እናያለን። እንደ እሳት የሚያቃጥል ነገር በይቅርታ እንደሚጠፋ ከዚሁ ከምድራዊ ኑሮአችን ከገጠመን ተረድተናልና፤ ይህ ምሳሌ ለዚሁ ለምድራችን የሚያገለግል ከመሆኑም በላይ፥ የሰው ልጅ ይቅር እያለና እየረሳ መኖር እንዳለበት፥ አለበለዛ ይቅር አለማለቱና ያለመርሳቱ ኃጢአት እንደ እሳት ሆኖ እንደሚያቃጥለው ግልጽ ነው።

"እግዚአብሔር መሃሪና ይቅር ባይ ነው፤ ከቁጣ የራቀ ምህረቱም የበዛ። ሁልጊዜ አይቀስፍም፤ ለዘለአለምም አይቀጣም።" መዝ. 103፡8

"ምህረትን ይወድዳልና፤ ቁጣውን ለዘለአለም አይጠብቅም።"ሚኪያስ 7፡18

እስከዛሬ ድረስ ስለ ገሃነመ እሳት ሲነገረን በመቆየቱ ማወቅ የሚገባንን ያህል ስናውቅ ቆይተናል። ነገር ግን ማወቃችን በሥጋዊነታችን ምክንያት ከስሜታዊነታችን ጋር የተያያዘም ሊሆን ይችላል። እኛም የምናውቀው በገደብ እንደሆነ፥ የገዛ

አስተሳሰባችንም ምን ያህል በውስጡ አንጻራዊነት እንዳለበት ከሚከተለው ምሳሌ እንመልከት።

አንድ ህጻን እንዲህ ብሎ አባቱን ጠየቀ - “አባቴ ሆይ፥ ሰው ሲሞት የሚሄድበት አለም ምን ይመስላል?” አባትዬውም ለልጁ እንዲህ ብሎ መለሰለት - “ይህንኑ በምድር ላይ ያለውን ነው የሚመስለው። እዚህ የምታያቸውን ሰዎች ሁሉ ከዛም በልዩ መልክ (ልዩ አይነት የመንፈስ ሥጋ ለብሰው) ታያቸዋለህ። ከህጻንነትህ ጀምሮ አርጅተህ እስከትሞት ድረስ፥ ከሰዎች ጋር የሚኖርህም ግንኙነት፥ በልዩ መልኩ ከዚያም ይጠብቅሃል። ይህም ማለት፥ ከዛ ሥፍራ ሕይወት ዘለአለማዊ ስለሆነ፥ እዚህ ያስደሰትከው ሰው እዛ ለዘለአለም ያስደስትሃል፤ ከዚህ የጎዳኸው ሰው ደግሞ ከዛ ለዘለአለም ይጎዳሃል” አለው።

ልጅዬውም ተንኮለኛና ተደባዳቢ ስለነበረ - በጥፊ፥ በጡጫ፥ በእርግጫ የተማታውን፥ የተሳደበውን፥ ያደረገውን የተንኮል ሥራ ሁሉ በማሰብ ላይ እንዳለ ላብ አሰመጠው። መጥፎ ድርጊቶቹ ሁሉ በዘለአለማዊነት ሲያጠቁት ታሰበውና እየተንቀጠቀጠ ልፍስፍስ ብሎ መሬት ላይ ወደቀ።

አባትዬውም በመጨነቅ - “ልጄ ምን ሆንክብኝ? ምን ሆንክ?...” ብሎ ጠየቀው። ልጁም በተዳከመ አንደበት - “አባቴ ሆይ! ከዚሁ ሳለሁ ተሰማኝ...” አለው። አባትዬውም - “ምንህን ነው የተሰማህ? እጅህን ነው? እግርህን ነው? እራስከን ነው?....” ብሎ በሃዘን ይጠይቀው ጀመር። ልጅዬውም በቀሰስተኛ ድምጽ፡- መንፈሴን ነው ብሎ መለሰለት።

አባትዬው ልጅዬውን እንዲያውቅ አደረገው። ምንህን ነው የተሰማህ ሲለው ልጅዬው መንፈሴን ነው ያለው አባትዬው - ሰዎችን ሁሉ በመንፈስ ታያቸዋለህ ብሎ ስለነገረውና መንፈስ ምን እንደሆነ በራሱ መንገድ ስለተረጎመውና በገዛ ራሱ ግንዛቤ ስለተመራ ነው።

አባትዬው ልጁን እንዲያውቅ ያደረገው ሲያድግ ጥሩ ሰው እንዲሆንለት ብሎ ነበር። እምነት ሰው ከተነገረውና እንዲያውቅ ከተደረገው ውስጥ የሚመነጭ ከሆነ፥ እግዚአብሔርም ማን - ምን እንደተነገረው እና ማን - ምን እንዳወቀ ያውቃል።

ሰብአዊነት የጋራ እውቀቱ፥ መንፈሳዊ ግንዛቤውም እጅግ ከፍ ከፍ እያለ ያድጋል። በዚህን ጊዜ፥ የግለሰቦች የጋራ ግንዛቤ እንደ ገሃነመ እሳት ሆኖ ኃጢአተኛውን ያሰቃየዋል እንጂ፥ ገሃነመ እሳት “በራሱ ህልውና የሚጸና” ነው ለማለት የሚያበቃ እውቀት የለንም። ምናልባት የሚከተለው በኢትዮጵያ ቅዱሳት መጻሕፍት (መጥምቀ መለኮት ዮሐንስ) የተጻፈ ታሪክ (ተአምር)፥ ለማለት የፈለግነውን ነገር ለየት ባለ መልክ ይገልጸው ይሆናል።

የንጉሥ ልጅ የሆነች ዓመተ ዮሐንስ እጅግ የምትወደው ወዳጇ ፈረስ ሲጋልብ ድንገት ወድቆ ሞተባትና እጅግ አዘነች። የወዳጇን ነፍስ ለማዳን በበኩሏ የሚቻላትን ሁሉ አሰበች። ከመጥምቀ መለኮት ዮሐንስ ጋር አንድ ለኛ የማይገባ የመንፈስ ዝምድና ስለነበራት፥ አስተሳሰቧ ወደዚሁ ወደ ዮሐንስ መጥመቁ መንፈስ መራትና እንዲህ አሰበች - አያቴ ዘርዓ ያዕቆብ የጌታችንን መስቀል ከኢየሩሳሌም ባመጣ ጊዜ፥ የብዙዎችን የቅዱሳንን አጽም አብሮ አምጥቶ አስቀምጧል። ከአጽሞቹም መካከል፥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ያጠመቀ የዮሐንስ አጽም ይገኛል። ስለዚህ ይህ የወዳጄ ሬሳ የመጥምቀ መለኮት ዮሐንስ አጽም ከሚገኝበት፥ ስሙም ከሚጠራበት ሥፍራ ሄዶ ቢቀበር የወዳጄ ነፍሱ መንግሥተ ሰማይ ይገባልኛል። ይህንንም ከፍቅሯና ከደግነቷ የተጸነሰ ሃሳቧን ለብዙሰዎች አካፈለች።

ነገር ግን ባካባቢዋ ያሉ ሰዎች - ዘመድ አዝማድ ሁሉ - "ይህ አንቺ የምትዪው ሥፍራ ግሽን ደብረ ከርቤ ነው፤ ካለንበት በእግር ተጉዞ ብዙ ቀናት የሚፈጅ ስለሆነ፥ ሬሳው እዛ እስኪደርስ ይበሰብስና ይሸታል፤ ይህ ሊሆን የማይችል ሃሳብ ነውና ከአይምሮሽ ይውጣ። ሬሳው እዚሁ ይቀበር" ብለው መከሯት። ቄሶችና ሊቃውንትም የዓመተ ዮሐንስን ሃሳብ አላጸደቁላትም። እርሷ ግን በሃሳቧ ስለጸናች፥ ሬሳውን በቁርበት አስጠቅልላ፥ በነጭ ጨርቅም አስገንዛ፥ ከጥቂት ሰዎች ጋር ጉዞ ጀመረች።

ከሦስት ቀናት ጉዞ በኋላ፥ በመጥምቀ ዮሐንስ ስም የተሠራ ቤተ ክርስቲያን ካለበት ከአንዲት መንደር እንደደረሱ፥ አስከሬኑን ከቤተ ክርስቲያኑ ቅጽር ውስጥ አሳርፈው፥ እነርሱም ከድካማቸው አረፍ ብለው ተቀመጡ።

የቤተ ክርስቲያኑ ካህናት ሁኔታውን ካጠኑ በኋላ፥ ሬሳው ሳይቆይ ቶሎ እንዲቀበር አሳሰቡ። ዓመተ ዮሐንስ ግን - "ቤተ ክርስቲያኑን ከፍታችሁ፥ እጣን አጢሳችሁ፥ ቅዳሴ ቀድሳችሁ፥ ሥጋ ወደሙን ሰውታችሁ ለወዳጄ ነፍስ ደህንነት ለምኑልኝ.." አለች። በዚህን ጊዜ ከካህናት ከፍተኛ ተቃውሞ ደረሰባት። እንዲህም ብለው አስጠነቀቁ - "ሰው በነፍሱ እያለ ኃጢአቱን ተናዞ፥ ሥጋ ወደሙን ለመቀበል አምኖ ለመጣ እንሰዋለን እንጂ፥ ከነኃጢአቱ ለሞተ ሰው ሥጋ ወደሙን አንሰዋም። ይህማ ፈጣሪያችንን መፈታተን ይሆንብናል፤ ሐዋርያትም እንዲህ ያለውን ስርዓት አላዘዙንም" አሏት።

እርሷም በዚህ ቁርጥ ውሳኔ እጅግ አዝና ስታለቅስ ሰውነቷ ደክሞ እንቅልፍ ወሰዳትና ተኛች። በህልሟም (ከብዙው በጥቂቱ) ቅዱስ መጥምቀ መለኮት ዮሐንስ በነጭ ወፍ ተመስሎ ወዳጇን ከእሳት ጉማሬ ሆድ ውስጥ አውጥቶ ሲሰጣት፥ ነፍሱንም ወደ ሰማይ ሲያሳርግላት አየች። በማግስቱም ይህንን ሕልም ለካህናትና ሊቀ ካህናቶች በማብራራት አስረዳች። እነርሱ ግን፥ ሰው ከነ ኃጢአቱ ከሞተ በኋላ፥ እርሱ

ባልሠራው መልካም ሥራ እንዲህ አይነት ምህረት ይደረግለታል ብለው ሊያምኑ አልቻሉም።

ሊቀ ካህናቶቹም እንዲህ አሉ - "ሕልም በሰው ልጅ ጭንቅላት ውስጥ የሚታይ ትርእይት ነው። መናፍስትም ሰው እንቅልፍ ሲወስደው ጭንቅላቱ ውስጥ ድርጊቶችን እንደ ትያትር በአይምሮው ይከቱበት ይሆናል። ምንጊዜም የሕልም አመጣጡ ሁለት አይነት ስለሆነ፥ ይህ አንቺ ያየሺው ሕልም አመጣጡ ከቅዱስ መንፈስ ካልሆነ፥ አንቺን እና ሕዝቡንም ወደ መጥፎ ለመምራት የታቀደ ሊሆን ይችላል።

ሰው በምድር ሲኖር በሠራው ሥራ ይጸድቃል እንጂ፥ ከሞተ በኋላ ሬሳው የተቀበረበት ቤተ ክርስቲያን ነፍሱን መንግሥተ ሰማይ ያስገባዋል ብሎ ማመን ሃይማኖታችንን የሚቃረን ከመሆኑም በላይ፥ ለአንድ የተወሰነ ተንኮል የተጠነሰሰ መሆን አለበት። በእውነትም ሕልምሽን ስንመረምረው ከእምነታችን ጋር የሚቃረን ነው እንጂ፥ ከቅዱስ መንፈስ የመነጨ አልመሰለንም.." በማለት አስፈራሁት።

እርሷ ግን በውስጧ ልክ መጥመቁ ዮሐንስ እንደሚለፈልፍ እየለፈለፈች፥ ያየችው ሕልም በቀጥታ ከቅዱስ መንፈስ የመጣ መሆን አለበት ብላ፥ ላንቃዋ እስኪደርቅ ድረስ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን እየጠቀሰች ተከራከረች።

በዚህን ጊዜ ካህናትና ሊቀ ካህናቶች ተመካከረው - "በእውነት ይህ ያንቺ ሕልም አመጣጡ ከቅዱስ መንፈስ የመጣ ከሆነ፥ ሕዝቡ ሁሉ እንዲያምን እግዚአብሔር ተአምራቱን ይግለጽልን..." ብለው ሄዱ።

በማግስቱ፥ የሚከተለው አስገራሚ ትእይንት ተፈጸመ፡-

በዛች መንደርና አካባቢዋ ሁሉ በክፉ አድራጊዎች እጅግ የተከበረ፥ ጋኔል እየጎተተ ብዙ ሰዎችን ወደ እርኩስ መንፈስ በመምራት ያሳሳተ ጠንቋይ ነበር። ይህ ጠንቋይ ብዙ ሕዝበ በተሰበሰበበት ሥፍራ በአደባባይ ተሰቅሎ ሲንፈራገጥ ታየ። ይህንን አስደንጋጭ ትእይንት የተመለከቱ የጠንቋዩ ተከታዮች ሁሉ በታላቅ ፍርኃት ፈርተው ሸሹ። ሕዝቡም እንዲህ ያለ አስደንጋጭ ነገር በማየታቸው በድንጋጤና በፍርኃት መንፈሳቸው ታወከ።

ቄሶችና ሊቃውንት በጠቅላላ ይህንን ተአምር በተመለከቱ ጊዜ - "በእርግጥ ለዓመተ ዮሐንስ የቀረባት መንፈስ አመጣጡ ከእርኩስ መንፈስ ቢሆን ኖሮ ከዚህ ጠንቋይ ጋር ይወዳጅ ነበር እንጂ፥ እንዲህ በአደባባይ እስኪሰቀል ድረስ ዝም አይልም ነበር። ስለዚህ፥ ይህ በተቃራኒ መንፈስ ላይ ብርታቱን ያሳየን ኃይል የዓመተ ዮሐንስ ሕልም አመጣጡ በእውነትም ከቅዱስ መንፈስ መሆኑን ያመለክታል..." በማለት አመኑ።

ከዚያም በኋላ - ቤተ ክርስቲያኑን ከፍታችሁ፥ እጣን አጢሳችሁ፥ ቅዳሴ ቀድሳችሁ፥ ሥጋ ወደሙን ሰውታችሁ ለወዳጇ ነፍስ ደህንነት ለምኑልኝ ባለችው መሠረት፥ ለዓመተ ዮሐንስ የምትፈልገውን አደረጉላት።

አንዳንድ ሰዎች የተጠቀሱትን ተአምራታዊ ድርጊቶች በማስመልከት እውነተኛ አይደለም በማለት ለመከራከር ይቃጣቸው ይሆናል። ውሸት ወይንም እውነት መሆኑ ከማይታወቅ ከዚህ ተአምር ከታሪኩ ይልቅ ትምህርቱን እንመልከት።

ይህ ታሪክ በእርግጥ እውነት ከሆነ፥ ሁለት ኃይላት - ሁለት አለማት መኖራቸውን፥ እኛም በመሃል ተመልካቾች (ወይንም ሳንወድ ተሳታፊዎች) መሆናችንን፤ እግዚአብሔር እያንዳንዱን ሰውና እምነቱን እንደሚመለከት፤ ሲዳኝም በግለሰብ ደረጃ እንጂ፥ በጋራ፥ በሕብረተሰብ፥ በዘርና በወገን፥ ባካባቢና በአገር ደረጃም እንዳልሆነ፤ በእግዚአብሔር እና በአንድ ግለሰብ መካከል ስለሚኖር ግንኙነት፥ ከግለሰቡና ከእግዚአብሔር በስተቀር የሚያውቅ ማንም ሊኖር እንደማይችል እናስተውላለን።

መሠረታዊ እምነታችን ከአምላካችን የመጣ ስለሆነ፥ የማይጨመርበት፥ የማይቀነስለት፥ የማይለወጥና የማይሻር ነው። እግዚአብሔር የሰውን ሥራውን እንጂ፥ ሃይማኖቱን (ቀኖናውንም ሆነ ዶግማውን) የማይመለከት መሆኑን ከዚህ ታሪክ ማገናዘብ ይቻል ይሆናል።

ካህናትና ሊቀ ካህናቶች ባንድነት፥ ከተለመደው ምግባራቸው ውጪ ለዓመተ ዮሐንስ ሲሉ ፈቃዷን ፈጸሙላት እንጂ፥ ከኛ በላይ የሚያውቅ የለም በማለት የርሷን እውነት አላወደሙባትም፤ መንፈሳዊ ቅንዓቷንም አላኮሰሱባትም። ለወዳጇ ያላት ፍቅር እና እምነት ወደ ሌላው አለም ሊሸጋገር እንደሚችልም የሚያበስር ተስፋ መገቧት እንጂ፥ በሃሳቧና በጉልበቷ የደከመችበትን ሁሉ በመናቅ፥ ተስፏ አስቆርጠው አልሸኟትም።

የእግዚአብሔርን ፈቃድ (ዳኝነቱንስ) ማን ይረዳዋል? ሁሉም ሰው አርጅቶ አይደለም የሚሞተው። ታዲያ፥ ኃጢአቱን ተገንዝቦ፥ ተናዞ (ንስሃ ገብቶ)፥ ቅዱስ ቁርባንን ለመቀበል ያልበቃ ገና በወጣትነቱ በድንገት ቢሞት፥ ከሞተ በኋላ ምህረትን የማያገኝ ስለመሆኑ ማን ያውቃል?

ወደ ሰማይ ተነጥቀው ከሚሄዱት ሌላ በምድር ላይ የሚቀሩት የመጨረሻውን መጨረሻ እየተጠባበቁ ይኖራሉ ብንልም፥ ይህንን እንዲሆንም እንዳይሆንም የሚያደርገው እግዚአብሔር ነው። የፈለገውን ማድረግ የሚችል እግዚአብሔር፥ እርሱ የፈለገውን ያደርጋል። እግዚአብሔር ሰው በአቅሙ ከሚያስበው ሁሉ በላይ ያስባልና እንዲህ ያለውን ተአምር ስናይ እንኳን አወቅን የምንለውን፥

ልናውቅ ከማንችለው ጋር ማመላከትና፥ እኛም እንደ ቀሳውስቱ እና ሊቀ ካህናቶቹ ሁለት ጊዜ ማሰብን ብናስብ ወደ እውነት እንጠጋ ይሆናል።

የሚኞችን ነፍስ ከጳድቃን ጎን እንዲያስቀምጥልን ቀሳውስት ይጸልያሉ፤ እኛም በእምነት እንጸልያለን፤ የማዳኑ ሥራ የእግዚአብሔር ነው። ሰው ቢሞትም ቀሪ ዘመዶቹና ወዳጆቹ ጥሩውን እስካሰቡለት ድረስ - እግዚአብሔር ለአንዱ ብሎ ሌላውን እንደሚምር፥ ከመጽሐፍ ቅዱስ በተደጋጋሚ ተጠቅሷል[57]።

ሙሴም ለወገኖቹ ጸለየ። "አቤቱ ቁጣህ በታላቅ ኃይልና በጽኑ እጅ ከግብጽ ምድር ባወጣኸው በሕዝብህ ላይ ስለ ምን ተቃጠለ?..." ዘጸ. 32፡11 ሙሴን እግዚአብሔር እንደ ሰማው፥ እኛንም ይሰማናል።

እውነት የምትገኝበት ሥፍራ ይህ ብቻ ነው ብሎ፥ ተደላድሎ ከመቀመጥ ይልቅ፥ እውነትን ለማግኘት መሮጥ ይበልጣል። እውነትን ለማግኘት ብቻ የሚሮጡ ከአንድ ሥፍራ ይገናኛሉና፤ እርሱም እግዚአብሔር የሚገኝበት ነው።

ሰው በሃሳቡ የማይደርስበት ሥፍራ የለም፤ የሚያውቀው - ሊያውቅ የሚችለውም ትንሽ ነው። ግን ሚዛናዊ አስተሳሰባችን (ሳይንቲስቶችም ብንሆን) ከእምነታችን ጋር አይጋጭም[58]።

እውነት የሚመስለውንና የማይመስለውን በስነ አይምሮ ለመመዘን ቋንቋ አያስፈልገውም። ቢናገሩት ለገለጻ የሚያስቸግር ነገርን ሁሉ፥ በዝምታ አርቅቆ በማሰብና በመንፈሳዊ ዝንባሌ ለመተርጎም መሞከር ሳይሻል አይቀርም - ማንም ሰው ከሚያውቀው (እንዲያውቅ ከተደረገው) ተነስቶ ወደ እግዚአብሔር በሚወስደው ጎዳና ትንሽ ከተራመደ፥ የመንፈስ ኃይል ያዘልቀዋልና።

እግዚአብሔር ፍጡራኑን ሁሉ (ሁሉንም) ይፈልጋቸዋል። "ምን ይመስላችኋል? ለአንድ ሰው መቶ በጎች ቢኖሩት፥ ከእነርሱም አንዱ ቢባዝን፥ ዘጠና ዘጠኙን በተራራ ትቶ፥ ሄዶም የባዘነውን አይፈልግም?" ማቴ. 18፡12

የሰው ልጅ ኃጢአተኛነት በምድራዊነቱም መሆኑን እያወቅን፥ ይህ ሰው ለምን ይህንን እምነት አልተከተለም በማለት፥ በሃሳባዊ እምነታችን እራሳችንን ወደ

[57] ዮናስ አሳ ነባሪ ሆድ ሦስት ቀን ካደረ በኋላ፥ ወደ ነነዌ ሄዶ ሰበከ፤ ጮኸ፡- በሦስት ቀን ነነዌ ጥገለበጣለች አለ። የነነዌም ሰዎች፥ ንጉሡም የነቢዩን ቃል ሰምተው ፈሩ። በጾምና በጸሎት ተጸጽተው ወደ እግዚአብሔር ቀረቡ። እግዚአብሔርም ያደርግባቸው ዘንድ በተናገረው ክፉ ነገር ተጸጽቶ አላደረገውም።" ትንቢተ ዮናስ 3፡10

[58] ከምድራዊነታችን ባሻገር ሦስተኛው መጽሐፍ በጠቅላላ ይህንኑ ያበስራል።

ጽድቅ ሌላውንም ወደ ገኃነም ስንከተው፥ ይህ የኛ የርህራሄ ጉድለት - ከኛ የመነጨ ገሃነመ እሳት .. የሚያቃጥል።

በኔ ሃይማኖት ውስጥ ምንም የማይታወቅ ነገር የለም የሚል ሰው ግን ተመጻዳቂ፥ አክራሪም ነው። ስለ ነፍስ መቃጠል በሥጋዊ አመለካከት የሚገባንን ያህል ገብቶን ግን፥ አሁንም ስለ ነፍስና ሥጋ አንድነትና ልዩነት፥ ሙታን ከመቃብር ሲነሱ ስለሚኖራቸው ሰውነት፥ ሰዎች በየቀኑ ሲሞቱ የመጨረሻውን ዘለአለማዊ ሕይወት እስኪያገኙ ድረስ ስለሚቆዩበት ሥፍራ ሁሉ - እኔ አውቃለሁ የሚል ማነው?

አዋቂና አላዋቂ በተጻፈና በተነገረ ላይ ይመዘናል፤ ባልተጻፈና ባልተነገረውስ ላይ ማን ከማን የበለጠ ያውቃል? ስንትስ ያልተጻፈና ያልተነገረ ነገር ይኖራል? ከአፋዊ ትረካዎች (ስብከቶችና ትምህርቶች) ሁሉ በስተጀርባ ለግለሰቦች የሚጠጋ መንፈስ ቅዱስ ከሕሊና ዳኝነት ጋር ለአንባብያን የሚበጃቸውን የሚሰጥ እርሱ እግዚአብሔር ብቻ ነውና፤ አንባብያን በዚህ ጽሑፍ በግልጽ ከማይገለጡት ጉዳዮች በስተጀርባ እውነቶችን በራሳቸው ይመርምሩ። ከሁሉም በላይ በእግዚአብሔር ያለን እምነት የጸና ይሁን። አሜን።

<u>የመሰባሰባችን ግዴታዊነት</u>

በተፈጥሮ ውስጥ ሂደት ሁሉ ማለቅን (መጨረስን) የሚያሳይ ነው። ለምሳሌ፥ በምድር ላይ እሳተ ገሞራዎች በያለበት በብዛት የፈነዱበት ዘመን ነበር፤ የተራራዎች ግንባታ የተጣደፈበት ዘመንም ነበር። ሁሉም ሲጀምር ጣደፍ ጣደፍ ይልና ቀጥሎ ቀርፈፈ....ፍ ይላል።

ጠፈር እየሰፋ ሲሄድ ካጀማመሩ ፈጠን ፈጠን ብሎ ካጨራረሱም የተንቀረፈፈ መሆን አለበት። በምድራችን ውስጥም ስነምድራዊ እንቅስቃሴዎች ካጀማመራቸው ፈጠን ፈጠን ብለው ካጨራረሳቸው የተንቀረፈፉ መሆን አለባቸው።

ለምሳሌ፦- ውሃ ወደ ማረፊያው ሳይከማች በፊት፥ በአለም ዙሪያ ልውጠ አለቶችን የፈጠሩ ስነምድራዊ እንቅስቃሴዎች (በታላቅ ግፊትና ሙቀት መጨፍለቅ፥ መጉበጥ፥ መሰንጠቅ፥ መተጣጠፍ፥ ወዘተ..) ከፍተኛ ነበር፤ ከጊዜ ብዛት እየቀነሰ መጥቶ፥ አሁን የዛን ጊዜ የነበረው አይነት እንቅስቃሴ የለም።

እንዲሁም፥ እሳተ ገሞራዎች በአለም ዙሪያ እሳት ወለድ አለቶችን ባከማቹበት ወቅት ስነምድራዊ እንቅስቃሴ ከፍተኛ ነበር፤ አሁን ዝቅተኛ ነው፤ ለወደፊትም እየቀነሰ ይመጣል (ጭራሹኑ ያከትማል ማለት ግን አይቻልም፤ ምክንያቱም የእንቅስቃሴው አቅጣጫ ሊለውጥ ስለሚችል)።

እንዲሁም፥ የሰው አካላዊ እድገቱና እንቅስቃሴው ካጀማመሩ ፈጠን ፈጠን ብሎ ካጨራረሱ (በሽምግልና ጊዜ) ይንቀረፈፋል (ሰው ሲሞት እንቅስቃሴው ጭራሹኑ ያከትማል ማለት ግን አይቻልም፤ ምክንያቱም የእንቅስቃሴው አቅጣጫ ሊለውጥ ስለሚችል)።

ጠፈር መሰብሰብ እንዳለበት ሁሉ፥ ተለያይተው የተቀመጡ ሁሉ መገናኘት (መሰብሰብ) አለባቸው። የሰውም እድገቱ በመንፈሳዊ አንድነቱ ከሚያደርገው እንቅስቃሴ ጋር የተያያዘ ከሆነ፥ ይኸው እንቅስቃሴአችን ወደ መሰባሰባችን ነው የሚመራን። በመሰብሰብ ውስጥ መበተን፤ በመበተን ውስጥም መሰብሰብ ቢኖርም፥ መሰብሰብ የሚያመዝንበት ጊዜ ይመጣል (ተጀምሮም ይሆናል)።

ከዋክብት የመሰባሰባቸውን ሁኔታ የአገረ ከዋክብት ማዕከላዊ የስበት ኃይል ሲያጣድፍ፥ የከሰሙ ከዋክብት በአንዳችነት ተሰባስበው ሲገዝፉ፥ በጠፈር ውስጥ ማእከላዊ የስበት ኃይሎች የአገረ ከዋክብት ማእከሎችን ሲያገናኙ፥ እኛ ከዚህ ሁሉ እንቅስቃሴ የተለየን አይደለንም። ስለዚህ የማመሳሰልን ነገር ከዚሁ ከህብረተሰባችን ጀምረን እንመልከተው። በመካከላችን ማእከላዊውን የስበት ኃይል እንፈልገውና እንጠጋጋ፤ ሰብአዊነት ከፍተኛ ደረጃ ላይ መድረሱን የምናውቀው የዛን ጊዜ ነውና።

በአለም ዙሪያ የሚከሰቱ የኢኮኖሚ ቀውሶችና መበላለጦች፥ እንዲሁም የአየር ለውጦችና የተፈጥሮ አደጋዎች በስነ አይምሮአችን ውስጥ የመሰባሰብን ጠቃሚነት ይሰብካሉ። እኛም ችግሮቻችንን አብሮ ለመካፈልና ለማቃለል ከመሰባሰብ የተሻለ አማራጭ የለንም።

የምድር ተፈጥሮአዊ ሃብት እየቷመጠጠ ነው ያለው። የሕዝብ ብዛት በዚሁ ከቀጠለ፥ ከጥቂት ዓመታት በኋላ ምግብ ለሰው ሁሉ አይዳረስም። በባህር ላይ መኖርና ከባህር ውስጥም እየተመገቡ መቆየትም የሚቻለው እስከተወሰነ ዘመን ድረስ ነው። ተፈጥሮ እራሷን ለማደስ ብዙ ሚሊዎን ዓመታት ያስፈልጋታል። ታዲያ እስከዛውስ የሰው ልጅ እንዴት ሊሆን ነው?

በዘር፥ በሃይማኖትና በርዕዮተ አለም ልዩነቶች ሳቢያ ክፋቶች ሲቀሰቀሱና በአለም ዙሪያ ሲዛመቱ፥ የፖለቲካ አምባገነኖችም ሁኔታዎችን ሲያባብሱት፥ የዛሬው ዘመን ሰውስ እንዲህ አይነት ሆነ፥ የወደፊቱ ትውልድ ሰውስ እንዴት ይሆናል? ብዙውን ተፈጥሮአዊ ችግር መቋቋም ይቻል ይሆናል። በውስጣችን ያለውን የማይታየውን ልዩነት ተቋቁሞ፥ በጋራ ማሰብና በአንድነት መሥራት ነው ያስቸገረው።

ዘረኞች ያልሆኑ አንዳንድ በምግባራቸው የተመሰገኑ ታላላቅ ሰዎች ከአሜሪካ፥ ከአውሮፓ፥ ከእስያ፥ ከአፍሪካና ከአውስትራሊያ አለምን እየዞሩ ጥሩ ጥሩ ሥራ እየሠሩ ናቸው። ማንም ሰው እንዲህ ጥሩ ለመሥራት ሲነሳሳ፥ እኛም በመንፈስ ስንተባበር፥

በአለም አቀፍ ደረጃ፥ ከአህጉራት ሁሉ የተውጣጡ ደጋግ ሰዎች ሲበራከቱ፥ ምድራዊት አለማችን ሰማያዊ ትሆናለች።

ምድራዊ ሕይወት ባንድ በኩል ከምንጊዜውም ይልቅ ምድራዊ ሲሆን ይታያል፤ በሌላ በኩል ደግሞ ሰማያዊ እየመሰለ መጥቷል። ሁላችንም የምንሄደው ወደፊት ብቻ ከሆነ፥ ማንኛውም የምንሠራው ሥራ ሁሉ የወደፊቱን የመሰባሰባችንን ሁኔታ የሚያጠናክር ነው የሚሆነው - ሰብሰብ ማለታችን ከህልውናችንም ጋር የተያያዘ ነውና።

የጠፈርን መሰብሰብ የሚያፋጥነው የማእከላዊ እፍጋታው እየጨመረ መሄድ እንደመሆኑ መጠን፥ በእኛም መካከል የመንፈሳዊነታችን መጠናከር እንደ እፍጋታ ሆኖ መሰባሰባችንን ያባብሰዋል።

ከዘር ዘር የምናስተላልፈው ጠባያችን በአካላዊነታችን እዚህ እንዳደረሰን፥ ከዚህ ቀጥሎ ይህ አካላዊነታችን ቀጥ የሚልበት ጊዜ መድረሱ አይቀርም። ከዛ በፊት፥ አለም አቀፋዊ ፍቅር እና የመንፈስ አንድነት ግዴታ ነው።

<u>ሰብሳቢአችን - ማእከላችን - ኃይላችን</u>

ሕዝቦች ከቦታ ቦታ ሲዘዋወሩ፥ ሲበተኑና ሲሰባሰቡ እንደቆዩ ሁሉ፥ ሰብሳቢያቸውን (እምነታቸውን) አግኝተዋል። ምዕመን በመንፈስ እንዳይጠናከሩ የሚያደርጓቸው አስተሳሰቦች ቢበራከቱም፥ ከምድራዊ አመለካከት ወጣ እያሉ፥ በመንፈስ የመቀራረብን ጥሩነት የተረዱ፥ ልዩነትም ቢኖር፥ በአንድ ማእከላዊ ኃይል ዙሪያ መስማማት እንደሚቻል የተረዱ ሰዎች ተበራክተዋል።

በአሁኑ ዘመን እኛ ኢትዮጵያኖችም በአለም ዙሪያ ተበትነናል። ፖለቲካ እንደበተነን፥ ምድራዊ የሆነው ሁሉ እንደለያየን፥ የሕብረተሰብን መንፈሳዊ ጤንነት የሚጠብቅ መድኃኒት - የመንፈሳዊነታችን ኃይል እያጠጋጋን ነው ያለው። ስለ መንፈሳዊነታችን በተነጋገርን ቁጥር እርስ በርሳችን እየተቀራረብን ነው የመጣነው። በጉልሁም ቢሆን በረቂቁ፥ ግለሰብ ለሕብረተሰብ፥ ሕብረተሰብም ለግለሰብ - አንዱ ለሌላው ሲያስብለት፥ ይህ ነው መንፈሳዊ አንድነት ማለት፤ የሁሉንም ስሜት የሚጠብቅ - ፍቅር የሚገለጽበት ደስተኛ ሕይወት።

ከሁሉ በላይ ፍጹም፥ ከሁሉ በላይ እውነት፥ አንድ እግዚአብሔር ብቻ ስለሆነ፥ እርሱን ለማግኘት ስንል ወደ ማደሪያው እንሄዳለን። ከዚህ ከተቀደሰ ሥፍራ፥ በአንድ በክርስቶስ ፍቅር፥ በአንድ መንፈስ ቅዱስ ቅኝት፥ ከፈጣሪ አምላካችን ከእግዚአብሔር ፊት ቆመን እናመሰግነዋለን፤ እንጸልያለን፤ እንሰግድለታለን። ማን አለን

ማእከላዊ ሰብሳቢ ለእኛ (ለእስላሞች፥ ለክርስቲያኖች፥ አይሁዶች፥ ለሂንዱዎቸች..ወዘተ) ካለ እግዚአብሔር።

ምድራዊ የሆነ ነገር ሁሉ የአለምን ሕዝብ አንድ ሊያደርገው ካልቻለ፥ ሰማያዊ የሆነ ነገር የአለምን ሕዝብ አንድ ሊያደርገው ይችላል። አለም አቀፋዊ መንፈሳዊ አንድነትን በአንድ ጊዜ፥ በአንድ ትውልድ ማምጣት ያስቸግራል፤ ግን ቀስ በቀስ ይቻል ይሆናል። ሰው ሁሉ የራሱን ሃይማኖት ሳይለቅ፥ በአንድ አለም አቀፋዊ ክርስቶሳዊነት ለመቀራረብ ቢሞክር፥ ይህ የምናስበው ሉላዊ መንፈሳዊ አንድነትና ሰላም ለወደፊቱ ትውልድ ይቀል ይሆናል።

ሃይማኖትን በጥልቀቱ ሲመለከቱት ከምድራዊነት ባሻገር አርቅቆ የሚያስኬድ፥ ሳይንስን በእመርታ የሚያሳድግ ሊሆን ይችላል። ሁላችንም የጋራ በሆነው እውነት ከተስማማን፥ የሳይንቲስቶችና የሃይማኖት መሪዎችም ዝንባሌ በአዎንታዊነት መንፈሳዊ አንድነትና ሰላምን ከመፈለግ ጋር ከሆነ፥ በሳይንስና በሃይማኖት፥ እንዲሁም በተለያዩ ሃይማኖቶችም መካከል የተገነቡ ግርግዳዎቻ ይፈርሳሉ።

ለሳይንስም ለሃይማኖትም ማእከላዊ ኃይል ሊሆን ይችላል እግዚአብሔር። የክርስቶሳዊነት አላማው በሰዎች መካከል ልዩነቶችን በፍቅር ደምስሶ፥ ለእግዚአብሔር እየሰገዱ መኖር ነው። በምድር ላይም ጥሩነት በፍቅር ይቀሰቀሳል። ካለ ፍቅር ወደ ሰማያዊ አለም ተሸጋግረን ከእግዚአብሔር መንፈስ ጋር ሰማያዊ አንድነትን ለመመሥረት አንችልም።

መጀመሪያ የነበረ፥ በኋላም ያው የርሱ የሆነ አንድ ቃል፥
የርሱና እሱው የሆነ አንድ ማእከል፥
ወደር የሌለው እፍጋታ፥ ታላቅ የመንፈስ ኃይል።
አይቀሬ ነው መሰባብሰባችን፥
የሰው ልጅ የድኅነትን ምልክት ሲያስተውል፥
በፍቅር ስበት መቀራረባችን ሲቀጥል፥
ሁሉም በእግዚአብሔር ሲጠቃለል..።

# ምዕራፍ ስምንት

## ፍቅር መንፈሳዊነትን ይቀሰቅስ

በምንኖርበት አካባቢ ሞት በሞት ላይ እየተደራረበ መጣ። የሚያስታምሙ ታማሚውን የሚያደፋፍሩና የሚያጽናኑትም ከሆነ የመሞቻ ጊዜውን ያራዝሙለታል። የሰውን መንፈሱን የሚንከባከቡ የተመሰገኑ ናቸው። የሰው ሥጋዊ አካሉ እንደ እንጨት እየተቆራረጠ የሚጠገን ቢሆንም፥ ታማሚ በከፍተኛ ጥንቃቄና ክብር፥ በርህራሄና በፍቅር መያዝ ስላለበት፥ ውስጠ መንፈሱን ቀስ በቀስ በማዋራትና በማጫወት፥ የእግዚአብሔርን ቃል በማሰማትና በጸሎት ይጠግኑለታል።

ህጻን ልጅ ሞቃት ከሆነው ከእናቱ ማህጸን ሲወጣ እንዳይበርደው፥ በቶሎም በጨርቅ እንደሚጠቀለል፥ በዚህች ብርዳማ ምድር እንዳይበርደን ለሁላችንም የሚበቃ የእግዚአብሔር መንፈስ በዙሪያችን አለ። ይህ ቅዱስ መንፈስ ነው ከመድኃኒት ቤት (ከፋርማሲ) የማይገኝ - በገንዘብ የማይገዛ መድኃኒት። ይህ ቅዱስ መንፈስ ነው፥ ከብርዳማው ምድር (ከምድራዊ ውጣ ውረድ) ባሸገር፥ በመንፈሳዊ ሞቅታ ደስታን የሚሰጠን።

አዎ! ጊዜን ጊዜ ጥሎት ሲሄድ፥ ያለፉ መከራዎች ሁሉ ይረሳሉ። እኔስ እውነት በግርግር እንዳይደመሰስ ስል፥ ሁሉን ላለመርሳት እታገላለሁ። የተለያዩ ስሜቶች በአይምሮዬ ይሰርጉና እረፍት ያሳጡኛል፤ ከፊት ለፊቴ የማልወጣው ቅጣት እንደተዘረጋብኝ ሆኖ ይታየኛል[59]። (አንብያን እንደዚህ አይነት ሰው አትሁኑ - ለሰው የማይስማማ ወሬ ሃሳብም ወደ እናንተ አይቅረብ)።

በእውነት ከልቤ የማፈቅራት ባለቤቴ ጤንነቷን አጣች። ኮከብዬ ስትታመም እኔም በብዙ አይነት ጥቃቅን በሽታዎች ተወረርኩ። በዚህ የተፈጥሮ ውጥረት - የተውሳኮች ፍላት - የሥራ ብዛት - አንጎሌ መላ ሰውንቴም ተዳከመ። ሰው ሲታመም - በጣም ሲያመው - "በቃህ - በቃህ፥ ከዚህ አለም ሂድ - ተሰናበት.."። የሚባል ይመስለዋል። ካልመሰለውም፥ የቀኑ መርዘም መኖሩን ያስጠላዋል። እባካችሁ እናንት ጤነኞች ለታመሙት እዘኑላቸው።

---

[59] ከስሜቶች ብዛት (anxiety) የተነሳ ሊሆን ይችላል።

"ከእናንተ መካከል የታመመ ማንም ቢኖር የቤተ ክርስቲያን ቀሳውስትን ወደ እርሱ ይጥራ፤ በጌታም ስም እርሱን ዘይት ቀብተው ይጸልዩለት..።" ያዕቆብ 5፡14

ብቻዬን ደፋር ብዬ፥ ከቤተ ክርስቲያን ሄጄ ጸልዩልን እባካችሁ አለማለቴ ይቆጨኛል፤ የምዕመንን የመንፈስ ኃይል ረሳሁት። ባል ሲታመም ሚስት፥ ሚስትም ስትታመም ባል ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄደው ጸልዩልን እባካችሁ ቢሉ፥ ከምድራዊ ሐኪሞች በላይ ችሎታ ያለው አምላክ በቶሎ ሊያድን እንደሚችል እያወቅሁት ዘነጋሁት።

አባት ልጁ ሲያጠፋ ይቀጣዋል እንጂ፥ በከረሜላ እያባበለ አያስተምረውም። እግዚአብሔርም ገና ሳይቀጣኝ የሚቀጣኝ መስሎ ይታየኝ ጀመር። የቅጣቱንም አይነት ስመርጥለት፥ በሥጋዊ ቅጣት ከምትጎዳኝ በማይጎዳ መንገድ አስተምረኝ እለው ጀመር።

እያንዳንዱ ሰው በውስጡ የወደፊቱን በተለያየ መንገድ የሚያሳውቀው፥ የራሱን ሃሳብ የሚተረጎምበት ልዩ ዘዴ አለው። ለወደፊት የሚሆነው አስቀድሞ በግልጽ ሲታይ - ይህ ነገሮች ከመፈጸማቸው በፊት አስቀድሞ የማየት ችሎታ - ይህ "ቅድም አየሁ" ምርቃት ይሁን እርግማን አልገባኝም።

እንግዲህ አስተሳሰባችን ሁሉ ወደ ኃጢአት እንዳይመራን እንጠንቀቅ" በምልክት አንሂድ። "...አስማተኛም፥ መተተኛም፥ በድግምት የሚጠነቁልም፥ መናፍስትንም የሚጠራ፥ ጠንቋይም፥ ሙታን ሳቢም በአንተ ዘንድ አይገኝ..።" ዘዳ. 18፡11 - 12

በተለያዩ ምልክቶች ምክንያት የወደፊቱ ለኔ የማያምር መስሎ ተሰማኝ። አይምሮዬ እየፈጠነ የወደፊቱን ችግሬን ሁሉ ቁልጭ አድርጎ እያሳየ አስቸገረ።

"ነገር ግን እያንዳንዱ በራሱ ምኞት ሲሳብና ሲታለል ይፈተናል። ከዚህ በኋላ፥ ምኞት ጸንሳ ኃጢአትን ትወልዳለች፤ ኃጢአትም ካደገች በኋላ፥ ሞትን ትወልዳለች...።" ያዕቆብ 1፡14 - 15

በሁለት አቅጣጫ የመጣ ቁስል ሕሊናዬን አዳከመው። "የኮከቤ መታመም ቅጣት ይሆን? ምንድነው ጥፋቴ?.." እያልኩ ተበሳጨሁ። እኔን ግራ የሚያጋባኝ ጥፋቴን ለይቼ አለማወቄ። ለመከራ መቋጠሪያ የተሰጠኝ ከረጢት ለሸንቴ መቋጠሪያ ከተሰጠኝ ከረጢት የጠበበ ሆኖ፥ የማይገለጽ ውጥረት ውስጥ ገባሁ። ከኮከቤ ህመም የኔው ባሰ።

ምንድነው ይህ? መፈናፈኛ የሚያሳጣ - ተስፋ የሚያስቆርጥ፥

ታሞ መዳን ብርቅ ከሆነበት አገር።

ከዚህ አጥር፥ ከዚያም አጥር፥
በዚህ ቢሞከር፥ በዚያ ቢሞከር፤
የችግር አዙሪት፥ እንደ አውሎ ነፋስ የሚሽከረከር።

የሰውን ምኞቱን የሚያሳካ ቢኖር፥
እኔስ የሚያሰኘኝ ክንፍ አውጥቶ መብረር፤
ሰማይ ላይ ስወጣ በደስታ እንድሰክር፥
ሲቀርልኝ መሬት፥ ጭቃና አፈር፤
ቢያጥቡት የማይጠራ፥ ግራ የሚያጋባ ነገር።

በሕልም አለም ውስጥ ገባሁና ሰውነቴ ሁሉ ተለዋውጦ ከውስጤ ሌላ ሰው ሲወጣ ተሰማኝ፤ ድንገት በመስተዋት እራሴን ሳይ እጅግ ተደናገጥሁ። ይህ ከፊትለፊቴ በመስተዋት ውስጥ የማየውን ሰው አላውቀውም፤ በእውነት እኔ ልሁን አልሁን - ይህንን ልትነግረኝ የምትችል - የማንነቴ ማረጋገጫ (ማመሳከሪያ) ባለቤቴ ብቻ ስለሆነች  እርሷን ልፈልግ ብዬ በድንጋጤ ፈለግኋት፤ እርሷ የለችም፤ እኔም እኔ አለመሆኔ እየታወቀኝ ተጨነኩ፤ በድንጋጤ ውስጥ ሆኜ ጮህኩ! ብዙ ጮህኩ።

ከዚህ ሕልም በኋላ በዙሪያዬ የማየው ሰው ሁሉ ልዩ እየሆነብኝ ተቸግሬ ነበር።  እራሴን እንዳላጣው ብሆን፥ ለብቻዬ መኖር የማልችል ስለሆንኩ የመሞቻዬ ጊዜ የተቃረበ መስሎኛል። በውስጤ ተስፋ ስቆርጥ፥ መጨረሻዬም ሲታወቀኝ፥ በእኔነቴ ከተደበቀ ሰው የሚወጡ ቃላትና ዜማዎች ይታወሱኛል። እራሴን ዝም ለማሰኘት ሞከርኩ። ግን ስሜቶቼን ሁሉ መቆጣጠር አቃተኝና፤ በልቤ ውስጥ የሚርገበገብ ድምጽ ወደውጪ እየወጣ፥ የሚያሳዝን ዜማ የሚዘምር (የሚዘፍን) ሆነ፤ ለብዙ ቀናት። በውስጡ (በልቡ) የእግዚአብሔርን መንፈስ የተማመነ ፍርኃት አይደርስበትም፤ እኔ ግን ፍርኃት ያዘኝ፤ ይህም ፍርኃት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ ሄደ።

የሌለ ነገር፥ አልፈጠርኩም እኔ፤
ቀባጣሪ አትበሉኝ፥ እያየሁት ባይኔ፤
የማይነገር ነው፥ የማይገባ ለሰው፤
እንዳው ዝም ቢሉ፥ እራስ የሚያዞር ነው።

እስቲ ስሙኝ ሰዎች፥ አድምጡኝ እኔን፤
እንዳው ጭጭ አትበሉ፥ ስጡኝ ምክራችሁን፤
ጎዶሎ መሆኔ ታውቆኛል አሁን፤
እኔ እኔን አጥቼ ከቶ ሰውም አልሆን።

እናንት በሰማይ ያላችሁ መላእክት ለሰው ልጅ መላ ፍጠሩለት፤ እመቤቴ ማርያም አማላጃችን፥ ችግር ላይ ወድቀናልና ተመልከችን፤ ቅዱስ ሚካኤል ዝም አትበል፤ ከእግዚአብሔር አምላካችን አማልደን።

ችግር ሲመጣና በራሳችን የምናደርገው ውሱን ሲሆን - "እባካችሁ በጸሎታችን ተራዱን ብሎ መላእክትን መለመን ይጠቅማል። በቅዱስ መንፈስ ተገፋፍተው መልከ ሰማይን ወደ ምድር ለማንጸባረቅ የሚቻኮሉ መላእክት፡- ቅዱስ ሚካኤል፥ ቅዱስ ገብርኤል፥ ቅዱስ ዑራኤል እና ሌሎችም ምን እንርዳችሁ፥ ይኸውና መጥተናል እኛ የእግዚአብሔር አሽከሮች ይሉናል። እነርሱ ትምክህተኞች ስላልሆኑና የሥልጣናቸውን ወሰን ስለሚያውቁ፥ የእኛም ትኩረት በእግዚአብሔር ላይ መሆኑን ስለሚገነዘቡ፥ በመልእክተኛነት ደረጃ ብቻ እግዚአብሔርን ምን እንጠይቅላችሁ ብለው ይቀርቡናል። እኛም የኃጢአታችን ብዛት እያስፈራን፥ መላእክትን ብቻ ሳይሆን፥ ቀሳውስት፥ ጻድቃን ሁሉ እግዚአብሔርን እንዲለምኑልን እና እንዲያማልዱን እንጠይቃቸዋለን።

በምድር ላይ ጦርነት ቢቀሰቀስ፥ ረሃብና የተለያዩ ችግሮች የሰውን ልጅ ቢያስጨንቁት፥ ሰዎች የመዳኛ መንገዶቻቸውን ቢያሰፉ ይሻላቸዋል። መላእክት እንርዳ ነው እንጂ ለእኛ ስገዱ አይደለም የሚሉት።

መንፈሱ ከሥጋው ተለይቶ ወደ ሰማይ የሄደ ጻድቅ ሰው ሁሉ፥ ልክ እንደ መላእክት ሰውን ይረዳል፤ የሰዎችንም ጸሎት ወደ እግዚአብሔር ያቀርባል (ያማልዳል)። እግዚአብሔርም ለምን በቀጥታ ወደ እኔ አልመጣችሁም ስለማይል፥ በደግነት እና በቅንነት የመጣውን ሁሉ እንደየአመጣጡ ይቀበላል።

የባለቤቴ ህመም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ ሄደና ወደ መጨረሻ እረፍት ተጠጋች። እግዚአብሔር ከሁላችን ጋር ሆኖ፥ በሰማይም በምድርም እንዲጠብቀን እየተመኘች፥ ወደመጨረሻ ስንብት ተቃረበች። የኮከብዬ ሕይወት መጨረሻው ደረሰና አረፈች። ኮከብዬ ተለየች፤ ሞተች፤ ከሰማይ ቤት ሄደች፤ ቅዱስ ሚካኤል ወሰዳት።

## <u>በመንፈሳዊነት ፍቅር አይሞትም</u>

ሞት በሥጋና በመንፈስ መካከል ያለ ድልድይ ነው እንጂ፥ እኛን በእግዚአብሔር እስትንፋስ የተፈጠርን ሰዎች ሞት አይገድለንም። ሥጋ ቢሞት መንፈስ አይሞትም። ኮከቤም አለች፤ አልሞተችም።

ሰው ቢሞት የማይሞተው (የማይሸነፈው) መንፈሱ ስለሚቀር፥ ለዚህ መንፈስ ማደሪያነት የሚያገለግል ምድራዊ አካል ካልኖረለት የግድ ሰማያዊ አካል

(ፍጽምተ አካል) መኖር አለበት። የዚህም ሕያው መኖሪያ ሥፍራ አካላዊ አለም ካልሆነ፥ የግድ ሰማያዊ አለም መሆን አለበት።

ወንድማችን ፍራቼስኮ (Francis of Assissi) ሞትን እህታችን ብሎ ይጠራታል፤ ወደ ዘለአለማዊው ሕይወት የምታሻግር በር ናትና።

በነገረ ሃሳብና ሃይማኖታዊ ፍልስፍና ውህደት፥ የሰውን ልጅ መሄጃ የሚመራመር አይምሮ ብዙ ሥፍራ ደርሶ ይመለሳል (በሕልም)።

ህልሞች ሁሉ ከገዛ አይምሮ ጋር የተያያዙ መሆናቸው ግልጽ ቢሆንም፥ አይምሮ ከጠፈር ሁሉ ተገንጥሎ ለብቻው የሚኖር አካል አለመሆኑን እንገነዘባለን። የሰው አይምሮው "ክፍት" ነው እንጂ "ዝግ" አይደለም። አይምሮ ሌትና ቀን ከማሰብ ስለማያቋርጥ፥ ሃሳቦችን በተለያየ መንገድ ሲሰበስብና ሲበትን፥ በሕልም አማካኝነት የሚፈጠረው ትእይንት ለኑሮ ዘይቤ - መመሪያ ሊሆን አይገባም። ሆኖም፥ አይምሮ በነፃነቱ የሚታሰበውን ከውጪ ኃይላት ጋርም ያለውን ግንኙነት ማገድ የሚችል ማነው? ይልቅስ ከውሱን ምድራዊ ሕይወት ዘለአለማዊው የሰማይ ሕይወት የሚበልጥ ከሆነ፥ ከዚያ ለመኖርም ትምህርት የሚሰጥ ቢሆን፥ የምድርና የሰማይ ንኪኪም ካለ፥ በሰማይ ከሚሰጠው ትምህርት አልፎ አልፎ ወደ ምድር የሚተላለፍ ይኖራል ማለቱ ይቀላል። ታዲያ፥ የሰማይና የምድር ንኪኪ በሕልም[60] ካልተገለጸ (የሰማይም ትምህርት በሕልም ካልተላለፈ) በሌላ መንገድ እንዴት ይቻላል?

"እግዚአብሔር በአንድ መንገድ፥ በሌላም ይናገራል። ሰው ግን አያስተውለውም፤ በሕልም በሌሊት ራእይ፥ አፍላ እንቅልፍ በሰዎች ላይ ሲወድቅ..." ኢዮ. 33፡14 - 15

ኮከቤን በሕልሜ ከሰማይ በር ቆማ አየሁአት። "ና! ግባ ብላ አስገባችኝ። ብዙ ተንሸራሸርን። ብዙ ሰዎች ያሉበት ሥፍራ ነው። እዚህ ያሉ ሰዎች በሕብረት መኖር ይወዳሉ። ሰላምና ፍቅር የመላበት ሥፍራ በመግባቴ እጅግ ደስ አለኝ። ማሕበራዊ ኑሮ ማለት እንደ "ባለ አንድ ሕያው ነፍስ" ሆኖ መኖር መሆኑ ገባኝ።

ኮከቤን ከሰማይ ጓደኞቿ ሁሉ ነጥዬ ወሰድኳትና ስለ መሬት ኑሮአችን (የግል ምሥጢሮቻችን ሁሉ) አንድ ሳይቀር አወራን። በጣም የደነቀኝ፥ ወሬአችን እንደ ምድር አይነት አይደለም። አንዱ ስለሚያወራው ሌላው መቶ በመቶ ይረዳዋል። መሬት ተሠርተው የተረሱ ጉዳዮች ሁሉ እዚህ በግልጽ ይታወሳሉ። ወሬአችንን አቋርጬ፥

---

[60] ስለ ሕልም በተጨማሪ የሚከተሉትን ጥቅሶች ይመልከቱ፡- (ዘፍ. 20፡ 3 ዳን. 2፥ ማቴ. 1፡20 ፥ ማቴ. 2፡12፥ ማቴ. 1፡ 20 የሐዋ ሥራ 2፡17 ..)፡፡

እዚህ ሁሉ ነገር ግልጽልጽ ብሎ ስለመታወቁ ጉዳይ ጠየቅኋት። "አዎ! ሁሉ ነገር ይታወቃል..." አለች፤ ሌላም ብዙ ነገር ነገረችኝና ሄደች።

የሰው ሕይወቱ በምድር ከሥጋዊነቱ አልፎ ትንሽ ረቀቅ ያለ ቢሆን፥ እራሱን ለእውነተኛ ሰማያዊ ፍቅር ያዘጋጀዋል። ባለቤቴን በሥጋዊ ምድር ከማፈቅራት የበለጠ ነው አሁን የማፈቅራት። ይህም ንጹህ ሰማያዊ ፍቅር ለዘለአለማዊ ሕያውነታችን ሰማያዊ ሞቅታ የሚሰጥ ነው።

ባለቤቴ በብዙ ህልሞች ስትታየኝ፥ እኔ ይህንን እንደ መንፈሳዊ መቀስቀስ ቆጠርኩት። የሰማያዊው አለም ከምድራዊው የሚለይበት አንዱ ጠባዩ በአካላዊነት የሚከሰት የግለኝነት ጠባይ ተደምስሶ፥ በጋርዮሽ ጠባይ እንደሚቀየር፤ ይህም ልዩ "ሰማያዊ አንድነት" ደስ ወደሚል መንፈስ እንደሚመራ፥ ይህን እና የመሳሰለውን በቋንቋ እየጻፉ ለመግለጽ ቢከብድም ለኔ ግልጽ ስለመሰለኝ እንደ መንፈሳዊ መቀስቀስ ቆጥሬዋለሁ።

ከእለታት አንድ ቀን (ወይ ግሩም! ይህስ እጅግ በጣም ይገርማል)፥ ከብዙ የሕልም ኑሮዎቼ መካከል በአንደኛው ሕልሜ ውስጥ፥ ኮከቤ የሚከተለውን አጽናኝ ምክሯን በደንብ እንዲገባኝ ብላ፥ በግርግዳ ላይ ጽፋ አሳየቺኝ።

"እኛ እግዚአብሔርን በምንፈልግበት ጊዜ ብቻ ወደ እርሱ እየተጠጋን፤ ሲያሻንም ከእርሱ እየራቅን ለመኖር የማንችል መሆናችንን፤ እግዚአብሔር ምን ጊዜም - እኛ ከርሱ እንድንርቅበት የማይፈልግ መሆኑን አሳወቀን።"

ከሕልሜ ስቀሰቀስ (*በዚያን ቀን*)፥ ይህን ጽሑፍ ጻፍኩት። በሌላ ቀንም፥ ልክ በሕልሜ ያየሁትን አስመስዬ እንደገና ጻፍኩትና በመስተዋት ውስጥ አድርጌ (*ቀኑንም ጽፌ*) በክብር አስቀመጥኩት። ይህስ ብዙ ነገር የሚያስታውሰኝ ስለሆነ እስካሁን ድረስ አለ። አዎ!! በዚችው ባጭር ዘመናችን ውስጥ፥ እግዚአብሔርን በምንፈልግበት ጊዜ ብቻ ወደ እርሱ እየተጠጋን፤ ሲያሻንም ከእርሱ እየራቅን መኖር አንችልም።

ልጆቻችን በሰላም፥ በጤንነት፥ በደስታና፥ በፍቅር አሳድጎ፤ በዚህ መጽሐፍ የእናታቸውን ደግነት ያባታቸውንም ምክር እያስታወሱ፥ በኑሮአቸው ሁሉ ከእግዚአብሔር የመንፈስ ጎዳና እንዳይወጡ ያድርግልን። አሜን።[61]

[61] ለአንባቢ እንዳይበዛ ወደ አባሪ ተሸጋሽጓል።

# ምዕራፍ ዘጠኝ

## የማንነት ግንዛቤ - ከቶማስና ከዮሐንስ

የራሴ ማንነት አልገባኝም ብሎ የሆዱን መናገር የደፈረ፥ ብዙ ጊዜ ሰዎች ማውራት የማይፈልጉትንም የአደባባይ ምሥጢር ያደርገዋል፤ ግን በዚህን ጊዜ - "እኔ'ኮ ይህን የምመስል ሰው ነኝ..." ከሚል ሰው ሌሎችም ይማራሉ። እና፥ እኔኑ እንደ ሁለት አይነት መንፈስ - ከውጪ (እንደ ቶማስ) እኔኑ ከውስጤ (እንደ ዮሐንስ) - ወይንም እኔኑ ምድር በቀል (እንደ ቶማስ)፥ እኔኑ መጤ ከሰማይ (እንደ ዮሐንስ) - አንዱን ሰው ከሁለት ከፍሎ በማናገር የማንነታችን ጥያቄ ይመለስ ይሆን? ።

የአንድ ሰው ማንነት፥ በትምህርቱና በእውቀቱ፥ በሃብቱ በንብረቱ በማንኛውም ምድራዊ በሆነ ነገር ሲገመት፥ የት ላይ ነው ያለው ያ የተደበቀው፥ ምድራዊ ተጽንኦ የሌለበት፥ ተፈጥሮአዊ ማንነቱ -

<u>ቶማስ</u>

"መኖር ሲባል ከፍትጊያ ጋር ነው፤ የምድር አስተዳዳሪም ወደሞት የሚመራ። እኔስ ሽማግሌ ነኝና፥ ንግግሬ ለልጆች የማይጥም ነው። ለብዙ ትውልድ እንደኖረ ሰው፥ ከምድር ያገኘሁት የመኖር ጂምላስቲክ ለሰማይ ቤት የሚያዘጋጅ ከሆነ ጥሩ ነበር፤ ግን ግትር ነኝና ቶሎ አልማርም። ኧረ! ለመሆኑ ምን አይነት መጥፎ ሰው ሆኜ ብፈጠር ነው ይህን ያህል ትምህርት ያስፈለገኝ።

ያፈጣጠሬ ጉድለት ወደ ምድራዊ ምሬት እየመራኝ ተቸገርኩ። ምድራዊ እውነታ ለምድራዊነት፥ ሰማያዊ እውነታም ለሰማያዊነት ስለሆነ፥ ሁለቱም ባሉበት ያንዱ እውነታ ከሌላው አይተናነስም። እኛ ግን በሁለት "እውነት" ተጠምደን አጉል ተንገላታን።

በምድር የሞተ ሕይወት ሁሉ በሰማይ ነፍስ ሲዘራ፥ ምድራውያን የሚማሩበት መንገድ ቢኖር ማን ያውቃል? እውቀት ብቻውን በቂ ስላልሆነ፥ ስሜቶችን (መንፈሳዊ?) በጎን የሚያነቃቃ መኖር አለበት፤ አለማችን (ምድራዊነታችን)

በቀላሉ የማትገለጥ እንቆቅልሽ ናትና። እና፥ ሁሉንም ነገር በአይምሮ የሚታሰብ ብቻ አድርጎ መገመት አይቻልም።

“አለሁኝ እኔ - አይምሮዬ ለኔ የበቃኝ..” ብሎ የማሰብ ሰው፤ ከአይምሮ በላይ በመንፈስ አርቅቆ መሄድ ይችላል፤ ርቅቅ ማለት ከትህትና ጋር ይሄዳልና (ይመስለኛል)።

የአካል ግንኙነት ምን ጊዜም ከአካል ጋር ብቻ አይደለም፤ በሞት የተሰናበቱ ሁሉ ለዘመዶቻቸው በመቆርቆር፥ ሰው በአካሉ ሠርቶ የማይችለውን ሥራ ይሠራሉ። ሰዎችም ይህን እና በመሳሰሉ፥ ከአካላዊ ገለጻ ውጪ በሆኑ ሁኔታዎች (ሂደቶች) ውስጥ - ወደውም ሆነ ሳይወዱ ይሳተፋሉ። ከሚታየው ውጪ በግድ እንድናይ የሚያደርገን ነገር ቢኖር ነው ከዚህ የደረስነው (ይመስለኛል)።

የምድራዊነት እውነታ ሰውን በደስታና በሃዘን ቶሎ ቶሎ ሲቀያይረው፥ የማያቋርጥ ስሜት እንዴት ሳይነገር ዝም ይባላል? ሳልወድ “አንድ ልዩ አይነት” መንፈስ አልለቅህ እያለኝ ተቸግሬአለሁ (አንድ ነጥብ - መንፈሳዊ ክስተት ይመስለኛል)።

ሰው በራሱ ላይ ጠላትነት የሚያበረታው በመናፍስት የኃይል ክልል ውስጥ ሲገባ እንደሆነ ሁሉ፤ በማያገባኝ ውስጥ ገብቼ ማሰቤ እኔን ከእኔ ለይቶኝ እንደሆነም አላወቅሁትም - ሥጋዬን የሚጎዳውን ሁሉ በቀላሉ ልረሳ የምችል ብሆንም እንኳን፥ እንዳልረሳ የሚያደርጉኝ መንፈሳዊ ክስተቶች ይቆረቁሩኛል - ለኛ ለአካላውያን የማይገባ፥ በሰዎች መካከል የተለያዩ መልእክቶችን የሚያስተላለፍ፥ የሰው ኑሮውን የተለያየ አቅጣጫ የሚያስይዝ፤ ወዘተ.. ይኖራል (ይመስለኛል)።

ሰው በምድራዊ ጠባዩ ተውጦ፥ ከተፈለገው (ከተደነገገለት ገደብ) ውጪ ሲሆን፥ በተለያየ መንገድ የሚቀጣውና መስመር የሚያስይዘው መንፈስ አይኖርም ማለት ይቻላል?

ሁለት አለማት ቢኖሩ፥ አንዱ ከሌላው ሊያይል ይችላል። የተለያዩ ኃይላት ከሚያይለው አለም፥ ለተለያዩ አላማዎች - ተግባራተ ሰማይን (ሰማያትን) ለመፈጸም ወደዚህች ምድር ቢገቡ ማን ያውቃል?

ሰው ከሰው ጋር ቢጣላ አንዱ ሌላውን እያጠቃ ምድር ገኃነም እንዳትሆን ይቅር በመባባል መኖር እንደሚቻል፤ ይህ በሃይማኖታዊ ፍልስፍና ታዋቂ ሆኗል። ነገር ግን አጥቂው ከሰው ችሎታ በላይ ኃይለኛ ሲሆን፥ በግራም በቀኝም፥ ለደግነትና ለጥሩ

ሥራም ዕድል አልሰጥ ብሎ ከሞት በስተቀር ምርጫ ሲያሳጣ፤ ይህን እንቆቅልሽ የሚፈታ ማነው?

ሰው በራሱ ላይ ያለው ስልጣን የተወሰነ አይደለም ወይ? የሰው ልጅ ጠባዩ ከፍጥረቱ የመነጨ በመሆኑ፥ ምድራዊነቱ ለገዛ አካሉ እንኳን የማይበጀው መሆኑን ተረድቶ፥ አስተሳሰቡን ወደ ሰማያዊነት ዘንበል አድርጎ፥ በሰላም በመኖር ፋንታ፥ እንደ እንስሳ ሆኖ በየጊዜው እርስ በርሱ ሲተላለቅ፤ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ የጣሱ መላእክትም የጦር መሳሪያ ከሰማይ ሲያከፋፍሉ፤ እርኩሳን መናፍስት ነገር ሲቆሰቁሱ፤ “በል - በል” እያሉ የጥፋት መልእክተኞችን ሁሉ ሲያሰማሩ.....፤

እህ! ምግብ ሲደፋ፤ ጥሬ ብር ሰው ሲገድል...፤ ምድር ወደ ራሷ ጥፋት ስታመራ፤ የመጥፎነት መጥፎነት፥ የጨለማ ጨለማነት፥ የሃዘን ሃዘን...ሥር እየሰደደ በየቤቱ ሲገባ........።

እህ! ሁሉም ወሰን የለሽ ሲሆን፤ ሰው ሞትን የሚናፍቅበት ጊዜ ሲቃረብ፤ ይህ ሁሉ የመናፍስት ሥራ ሲታየኝና ልቤ በሃዘን ሲታወክ፤ እኔ ስለ ሌላው ሰው አልናገርም፤ እኔን ባዶ አድርጌ ከሰብአዊነት ማህደር የታየኝን ብቻ ልናገር አልኩ። ከራሴ ወጣ ብዬ በመንፈሳዊ አይኖቼ ለመመልከት ብጥርም፥ በአንድ ሺህ አደነጋጋሪ ጉዳዮች እውነትን ሳላገኝት እሞታለሁ።

እህ! አንዱ ሰው ሁለት እየሆነ የሰው ቁጥር ሲበዛ.....፤ በቀንም በሌሊትም በየመንገዱ የሚንገላወዱ ሰዎች ሲበራከቱ፤ በየቡና ቤት ቁጭ ብለው የሚዶልቱትም ከህጻን እስከ ሽማግሌ። የመገበያያው ሥፍራ ሁሉ በመናፍስት ብዛት ሲጨናነቅ፤ የሚያውቁት ሰው ሁሉ አንዱ ሁለት እየሆነ ሲታይ..ይህን የመሰለ የሁለት ተቃራኒ መንፈሶች ስሜት - የቅዠት አለም - ምን ብለው ይገልጹታል?!

መንፈስ ዝም ስለማይል፥ ከፖለቲካም፥ ከሃይማኖትም በብዛት ሲወራ፤ ብዙ ሰባኪዎች በከተማው ሲለቀቁ፤ ተሳዳቢዎችና ሰውን የሚዘልፉትም እንዲሁ። የሰዎች ጩኸትና ቁጣ ከቁጥጥር ውጪ በመሆን የእርስ በርስ ግጭት ሲፈጠር፤ ይህም ሲባባስ፤ የሃይማኖት ክርክር የወቅቱ ፖለቲካ ሲሆን፤ ሁሉም እየወገነ ሲጣላ፤ ያንዱ ወገን ከረገጠው መሬት - ያንዱ ወገን ከደረሰበት ሥፍራ ድርሽ የሚል በሕይወቱ የቆረጠ ብቻ ሲሆን...፤

ሁሉም አዋቂና ተከራካሪ ሲሆን - በየአቅጣጫው መመጻደቅ! መመጻደቅ! መመጻደቅ.....። ይህች አለም ተለውጣ፥ በዚህ መልኳ ነገር ክርር ሲልባት፤ በሰማይ ያለ የፍርድ ሚዛን መሬት ላይ ቁጭ ሲል፤ “እገሌ ከቤተ ክርስቲያን አይቀርም - መንፈስ

ቀርቦታል፤ እገሌ ከቤተ ክርስቲያን ርቋል - መንፈስ ርቆታል.....” ሲባል፤ ገኃነም የሚጣሉትና መንግሥተ ሰማያት የሚገቡት በደንብ ተለይተው በሰዎች ሁሉ ዘንድ የታወቁ ሲሆኑ - እህ! የቅዠት አለም..።

ማነው እርኩስ? የሰው አይምሮ ወይንስ ከሰው አይምሮ ውጪ የሆነ መንፈስ? በዚች አለም ውስጥ ያለ፥ በሰውም ውስጥ የሚገኝ፥ ካንዱ ወዳንዱ የሚሸጋገር እርኩስ መንፈስ ነው? ወይንስ የሰው “መጥፎው” ሃሳቡ። ሃሳብ እንበለው መንፈስ በቀንም በሌትም ይጓዛል - ይነጉዳል፤ አላማውን ለማሳካት በትጋት የሚሠራ እንጂ ሰነፍ አይደለም።

አንድ ሰው ከምድራዊና ሰማያዊ እውነታ አንዱን ብቻ ቢወስድ፥ በምድር ሊኖር የሚችለው ለምን ያህል ጊዜ ይሆን? አንድ ወጥ የሚያደርገውን ሃሳብ ከገዛ ራሱ ማፍለቅ ቢችልና በዚሁ ሃሳብ ልኑርበት ብሎ ቢነሳ፥ ከሰውነት ውጪ ያወጣው ይሆን?

እስቲ ላንዳፍታ እራሴን ከራሴ ላውጣና ልሂድ ብል ሥጋዊነቴ እሺ አይለኝም። ከምድራዊ ውጥረት እንድላቀቅ ብዬ፥ ከራሴ ወጥቼ ለመሄድ ከፍተኛ ፍላጎት አድሮብኝ የምቀባጥር እንጂ፥ በእውነት ለእውነት ፍለጋ የምፈላሰፍ አልመስልም።

ግን እኮ በሥጋዬ የትልቋ መሬት ሽራፊ ነኝ። ነጻነት ጠምቶኝ በሃሳብ ምጥቀት ጠፍቼ ይሆን? የአንድ ሰው ሁለትነት የሚያመጣውን ቀውስ እንዳልረሳ ብቻ ተርፌአለሁ። ሰብእነት (እንደ ሰው ሆኖ መፈጠር) ከምድራዊነት እንዴት ይላቀቃል? ሁላችንም በሁለት ኃይላት ተጠምደናል - በሁለት ኃይላት ተጠምደናል - በሁለት ኃይላት ተጠምደናል።”

<u>ዮሐንስ</u>

“ሰላም ለአብ ገባሬ ኩሉ አለም፤ ለወልድ ሰላም፤ ለመንፈስ ቅዱስ ሰላም፤ ለማርያም ሰላም፤ ወለመላእክት ሰላም። ሰላም ለነቢያት ወለሐዋርያት፤ ሰላም ለሰማዕታት፥ ሰላም ወለጻድቃን ሰላም። ሰላም ለሁላችንም ይሁን። የእግዚአብሔር መንፈስ አይለየን።

እኔም ይገባኛል። “ይሄንንም ያንንም” አስታውሳለሁ፤ መስሎ ማደርንም አውቅበታለሁ። ስለ እውነት ብዬ የሚመስለኝን እናገራለሁ። ሰው በልዩ ልዩ ምክንያቶች ከራሱ መንፈስ ጋር (ከሌላ ሳይሆን) መጣጣም ያቅተዋል። በተለይ

የሃይማኖት ልዩነት መኖሩ አንዳንድ ሰዎችን ሲያስጨንቃቸው፥ በሕይወታቸውም ውስጥ ጥርጣሬ ሲፈጠርና ተስፋ ሲያስቆርጥ አስተውለናል። ነገር ግን፥ ሁሉም በጌታ የተማሩ የሚሆኑበት ቀን እስኪመጣ ድረስ፥ ማንም ሰው ምንም ቢያውቅ ጨርሶ ሊያውቅ አለመቻሉን ተገንዝበ፥ በማንኛውም አቅጣጫ የአለማወቅ ፍርኃት እንዳያስጨንቀን፥ በእግዚአብሔርና በጌታችን በኢየሱስ እውቀት ጸጋና ሰላም ይብዛልን። "አምላካችንና ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን በማወቅ ጸጋና ሰላም ይብዛላችሁ።" 2ኛ ጴጥ. 1፡2

መንፈሳዊነት ለመንፈሳዊ ሰው የቀን ተቀን ኑሮው (ተግባሩ) ነው። ከሁለት አቅጣጫ (ንቃተ ምድር ወይም ንቃተ ሰማይ) ወደ አንዱ ማድላት ግዴታ የሚሆንበት ወቅት ሲመጣ ነው ፈተና። ንቃተ ሰማይ "ሰማያዊ እውነታ" ነው እንጂ ሕልም አይደለም። ግን ይህ "ሰማያዊ እውነታ" በመንፈሳዊነት የሚቀሰቀስ ስለሆነ፥ ምርጫን ማስተላከል የግለሰቡ ፋንታ ነው።

የሰው ልጅ በገዛ ራሱ አንድ ወጥ አለም ሊመሠርት አይቻለውም፤ ስለዚህ ማንም ግለሰብ ፊቱን ወደአለም መልሶ ሌላውን ሁሉ እየተመለከተ (እየመሰለም) ይኖራል እንጂ፥ አለም ፊቷን ወደ ግለሰቡ መልሳ ልክ ግለሰቡ እንደሚፈልገው ልትሆንለት አትችልም።

በምድር ላይ ውሸት ቢያይል፥ ለሕያው መንፈስ ማደሪያ መልካም ሰው ቢጠፋ፥ አንድ ሰው ይሞታል፤ ያም ሰው ሲሞት አንድ እውነት ይገለጣል። አዎ! ጉዞአችን ከሥጋዊነት ወደ መንፈሳዊነት እስከሆነ ድረስ ሁሉም መልካም ነው። ሁለት ከሆነው አንደኛው ከሌላው ተለይቶ፥ በጊዜ ውስጥ መለዋወጦችን ማድረግ ይኖርበታል። ይህንም ሲያደርግ መለዋወጡ ያደከመው እንደሆነ፥ በቁም እስከ መሞት ድረስ ሊደርስ ይችላል። ይህ ክስተት ተፈላጊና አስፈላጊ እየሆነ ብዙ ሰዎች በቁማቸው ይሞታሉ።

መንፈስና ሥጋ የማይጣጣሙ ቢሆኑም እንኳን፥ "ልዩ ኃይል" መጥቶ በሞት እስካልለያያቸው ድረስ፥ አንድ ላይ መቆየት ግዴታ ነው። ስለዚህ በሕልም፥ በቅዠት፥ በእውንም የምታደርገውን መንፈራገጥ (ፍትጊያ) ተው።

መጠፋፋት ቢኖርም፥ ምድር የውሸት ርጋፊ ብቻ ሆና አትቀርም፤ ትራፊ እውነት አታጣም - ውሸት ነግሦ እውነት አይጠፋም (አይሞትም)። እምነት በፍጹም ትህትና ተግባር ላይ ሲውል ትእግስትን ያስተምራል። ስለዚህ፥ የሚቆረቁሩ ጉዳዮችን

የግድ ችላ ብለን መተው ነው እንጂ፥ በስሜት ብቻ እየተመሩ በራስ ላይ አጉል ጭንቀት ማብዛት አይገባም።

ሃቁን ትናገራለህ፤ ግን ያንተ ችግር ግላዊና ውሱን ከሆነ ከአንተ አይምሮ የሚመነጨውን ፍልስፍና ሁለገብና ሁለንተናዊ ለማስመሰል መሞከርህ ነው። በስተእርጅና ብዙ - ብዙ የሃይማኖት መጻሕፍት አነበብኩ ብለህ ልብህ ውልቅ ብሏል፤ ሳይገባህ የገባህ መስሎሃል። ሃይማኖት ምድራዊ እውነታን የሚያስለቅቅ አድርገህ ትወስደዋለህ።

ያን ለብዙ ዓመታት በምድራዊ አንተነትህ የሸፈንከውን፥ አንተ የማታውቀውን እርሱ የሚያውቅህን ሃይማኖትክን ሁኔታዎች ፈቅደው ልታገኘው ስትጠጋ፥ በስሜት ተዋጥክ፤ እራስህን ያገኘህ መስሎህ የራሴን ለራሴ አደረግሁ ብለህ ጮህክ፤ በኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተኩራራህ፤ ውዳሴ ከንቱ አበዛህ።

"...ፈጣሪአቸውንም የወደዱ ሰዎች ብርና ወርቅን አይወዱም። ሥጋቸውን ለመከራ የሰጡ፥ ራሳቸውን እንደ ሞቶች ሰውነት አደረጉ እንጂ። ከተፈጠሩ ጀምሮ በዚህ አለም ያሉ መብሎችን ያልወደዱ ሰዎች የዚህን አለም ሹመት ሽልማት አልወደዱም።" ሄኖክ 42፡9

ይህን ትሁት ሃይማኖት ልትገለገልበት ሲገባህ የክብር ልብስ አደረግኸው። ከእምነት ጉድለት የተነሳ፥ ክብርህ የሚወልቅብህና እራቁትክን የምትቀር እየመሰለህ በራስህ የምታፍር ሆንክና ምድራዊ ሰቆቃ ታሰማለህ። ስሜታዊነት የሚያመዝንብህ ሰው ነህ። ሃይማኖትክን ከግላዊ ጥቅሞችህ ጋር ለማዋሃድ በምትሞክርበት ጊዜ ምድራዊነትህ ሳበህ። ምድራዊነትህ ሲስብህ፥ ሕይወትህ ከማይጣጣሙ ሁለት አለሞች መካከል ዋለለ፤ የመኖር ቀውስ አንገላታህና በሃሳብ ቅዠት ውስጥ ገባህ። በሃሳብ ስትቃዥ፥ ከምድራዊነት ባሻገር ያለው ወለል ብሎ እንዲታይህ ፈለግህ። አልታይ ሲልህም ጭንቀት ያዘህና ተቸገርክ፤ ጥርጣሬ ውስጥም ገባህ። በውስጠ ልቦናህ ያለው ሰማያዊ የተስፋ ብርሃን ደበዘዘ። ይህም ሲሆን መንፈሳዊነትህ ላላ። መንፈሳዊነትህ ሲላላ፥ ምድራዊ ፈተናዎችን ማለፍ እያቃተህ፥ ለጥቃቅን ጊዜያዊ ችግሮች ሁሉ በቀላሉ የምትጠቃ፤ መንፈሳዊ ጥንካሬም ስለጎደለህ በቀላሉ የምታዝን፤ ሆደ ባሻ ሆንክ።

መንፈሳዊነትን እንደ "ባጣ ይቆየኝ" ቆጠርከው። ምድራዊ ኑሮ አልስተካከል ሲልህና ስትቸገር - መንፈሳዊ ፍልስፍና ውስጥ ልስጠም፤ መጽሐፍ ቅዱስን ላንብብ፥ ልጹም፥ ልጸልይ፥ ወደ እግዚአብሔርም ልቅረብ አልክ። የሥጋ መጎዳት፥ የአይምሮ

ጭንቀት፥ የኑሮ አለመስተካከል፥ ከሰው ጋር ለመግባባት ያለመቻል፥ እነኚህና እነኚህን የመሳሰሉ ሥጋዊ መሰናክሎች ባንተ ላይ ሲከሰቱ አይተህ "ለችግሮች ሁሉ መፍትሔው ምን ጊዜም ሥጋዊ ላይሆን ይችላልና መንፈሳዊ መፍትሔዎችን ልፈልግ እንጂ፥ ሌላ ምን ምርጫ አለኝ?" ብለህ ተነሳህ። መልካም አስበሃል፤ መልካምም አድርገሃል። ግን ለምን ቶሎ ይደከምሃል? ለምንስ ቶሎ ተስፋ ትቆርጣለህ?

ሰው እራሱን "ለማወቅ" ባለመቻሉ፥ እንደ አሻንጉሊት የሚጫወትበት ኃይል ቢኖር፥ ያ ኃይል ካለ ቅዱስ መንፈስ አይፈታም። የሰውን ደካማነት አስተውል፤ "እኔስ አሻንጉሊት ሆኛለሁ ወይ?" ብለህ ራስህን ጠይቅ።

በተለይ እንዳንተ በቀላሉ የሚጠቃ ሰው መንፈሳዊ ብርታት ያገኝ ዘንድ በመንፈሳዊ ትምህርት ውስጥ ስምጥ ማለት አለበት። ይህ ትምህርት ለማንኛውም ሰው የውዴታ ግዴታ ነው። አንተም የጎደለህ መሠረታዊ የሃይማኖት ትምህርት ስለሆነ፤ ይህንኑ እንድትከታተል (እንድታጠና) እመክርሃለሁ። የተማርከውንም በሥራ ላይ አውለው፤ በጸሎት በርታ፤ "በስመ አብ፥ ወወልድ፥ ወመንፈስ ቅዱስ" እያልክ ፊትህንና ሰውነትክን በመስቀሉ ምልክት አማትብ እግዚአብሔር ይርዳህ።"

<u>ቶማስ</u>

"የምትነግረኝ ሁሉ እኔን ከራሴ የሚያስወጣኝ፤ በአካላዊነት አለመኖርን የሚያለማምደኝ ቢሆን (ከሆነ!?) ደስ ባለኝ ነበር። ሁለት ሆኜ በምኖርበት ወቅት፥ በመንዳቴ የተጨነቅሁት አንሶኝ ሌላውን አላስጨንቅም በማለት ከሰዎች ተገለልኩ። ይገርመኛል፤ በጭንቀት የተፈጠረ ንግግር ከጊዜ ብዛት ርቅቅ ሲል ተራ ንግግር ሁሉ ያስጠላል። መጥፎውን እየደበቁ በጥሩው ብቻ ለመዝለቅ መሞከር ደግሞ፥ ምድራዊ እውነታን እንደመካድ ይቆጠራል።

መንፈስና ሥጋ ተባለ - "የተቃራኒዎች ጣምራዎች"[62] በግለሰብ ሕይወት ውስጥ - ሁለቱ እንደ አንድ ሆነው በጠበጡን፤ ማሸነፍ እና መሸናነፍ በሌለበት - የማያቋርጥ ድብድብ - የእሱና የእሷ የህልውና ምልክት።

አይ ጎበዝ! እየተባለ ያደገ ልጅ ጉብዝናውን ጠብቆ ከቆየ፥ ከዚች አለም ያተርፍ ይሆናል። ሰዎች በዝቅተኛነት የሚመለከቱት ደግሞ፥ ዝቅተኛ አለመሆኑን

[62] በሁለተኛው የግጥም መጽሐፍ ውስጥ ከገጽ 161 ጀምሮ "ቅራኔዎች ከጠፈር እስከ መሬት" በሚል ርዕስ የተጻፈውን ይመለከቷል።

ሳያረጋግጥ ብዙ ስለቆየ በኑሮው እንደ ከሰረ ነጋዴ ሆኗል። ባጭሩ፥ መንፈሳዊነት እና የሰው ጠባይ (ስነ አይምሮም ቢሆን) ከምን ላይ እንደሚገናኝ እና ከምን ላይ እንደሚለያይ - መንፈሳዊነት በሰው ጠባይ ላይ (ስነ አይምሮም ቢሆን) ያለው የበላይነት ምን ያህል እንደሆነ አልገባኝም።

አስመስሎ መኖር ይሰጣል ወይ ፋይዳ?
ተለማምጦ ኑሮ ማንንም አልረዳ።
ከሙብላት ጋር ረሃብ፥ ጠጥቶም ጥማት፥
ከደስታ ጋር ሃዘን፥ ከዚህ ከዛም ቤት፤
ምንድነው ዝምታ እልል ባሉበት፥
ጸጥታው ከየት መጣ ባጨበጨቡበት፤
መጪውን እንዳላይ አይኔን አሳወሩት።

ልቀቁት ይናገር - ሁሉን በያይነቱ፥
ትርፉ ትዝታ ነው - ሃብትና ንብረቱ።
ደብለቅ ያለ ሕይወት - ኑሮ ከሁለት ሲሆን፥
ራሴን ስፈልግ - ጭልጥ የምልበት፥
ሳልተኛ እኖራለሁ፥ የሆንኩትን ሳልሆን፥
ስተኛ እኖራለሁ ያልሆንኩትን ስሆን።
በእውኔ እና በሕልሜ ደብለቅ ያለ ሕይወት፥
ቁሱ ወታደር፥ ወታደሩም ቁስ እንደሚሆን አይነት።

ያንተን እውነት - እውነት መስሎህ ተናገርክ - ዮሐንስ (የኔ መንፈስ መሳይ ሰው!)። እኔስ (ቶማስ የተባልኩ የኔ ሥጋ መሳይ ሰው!) እንዲሁ በራሴ ፍልስፍና ተጠምጄ፥ ከባለቤቴና ከልጆቼ ጋር ከቤተ ክርስቲያን ሳልሄድ ሰነበትኩ። ብዙ ጊዜ አለፈ። እግዚአብሔርም እኔን አልፈልግህም ያለኝ እየመሰለኝ፥ እኔነቴና እውነቴም እየተጋጩ ያሳፍረኝ ጀመር። ለብቻ ቀረሁና የራሴን እውነት በአንክሮ ስመለከት ከድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ጭልጥ ብዬ የገባሁ መሰለኝ።

በደረቅ ምድራዊ ፍልስፍና ወይንም ባልታወቀ ኃይል ተጽእኖ፥ በመጨረሻ የባለቤቴን መንፈሳዊ ስሜት የማዳከም ኃጢአተኛ ሆንኩ። እርሷም ገርና የዋህ በመሆኗ እኔን ተከተለችኝ።

የምዕመናንን መንፈሳዊ ግፊት፥ ከራሴ እምነትና አስተሳሰብ ጋር ትይዩ ባለመምጣቱ በተዘዋዋሪ መንገድ ለሌሎች እንቅፋት የሆንኩ እየመሰለኝ፥ እኔ ግን በዚሁ መጥፎ ምግባሬ ቀጠልኩበት - ስነ አይምሮዬ በምድራዊና ሰማያዊ አለማት ሁለት ተከፍሎ ስንገላታ፥ ሳላስበው ጥቂት ዓመታት በዋዛ ፈዛዛ አለፉ። እኔ ግን ብዙ ዘመን ያለፈ ነበር የመሰለኝ። አዎ! በኃጢአት ለረጅም ጊዜ መቆየት ዘመኑን ያስረዝመዋል።

ይህ ሁሉ ሆኖ፥ እስከዛሬ የጎደለኝ መንፈሳዊነቴ እየጸጸተኝ መጽሐፍ ቅዱስን ከማጥናት አላቋረጥኩም። በየቀኑ የኋላዬን ስመለከተው፥ መንፈሳዊ ኋላ ቀርነቴ ያሳፍረኛል፤ እኔነቴን እየታዘብኩት እኖራለሁ። ወደ መንፈሳዊነት ሳመራ ከግትር ጠባዬ ጋር አንድ እራሴን ሆኜ ቀጥ ብሎ መጓዝ ያቅተኛል።

በጨካኝ የባሪያ ገዢ ሥር ሥጋውን ለጌታው አስገዝቶ የሚኖር ባሪያ እንኳን አንዳንድ ጊዜ እርሱም እንደጌታው መንፈሳዊ ሕይወት እንዳለው ሲያስታውስ ደስ እያለው ይኖራል። ካጠገቤ ሳለህ የምታሳውቀኝ ሁሉ ደስ አሰኝቶኛልና እስቲ ተናገር ጃል።"

<u>ዮሐንስ</u>

"የመጨረሻውን የሚያሳምረው እግዚአብሔር ነው። መጨረሻውም የሚያምርለት ጻድቅ ሰው ነው። መጨረሻው እንዲያምርለት የሚፈልግ ሰው ምንጊዜም የገዛ ሕይወቱን (ሥራውን ሁሉ) ይመረምራል።

የማንም ሰው መንፈሱ እንደራሱ ሆኖ ይከተለዋል፤ በሕይወቱ ሁሉ ይመራዋል። ከተለያዩ ምድራዊ መንፈሳዊ ዘገባዎች መካከል (ስሜቶችም ቢሆን) ከጎን ሆኖ የሚጠብቀው ለማንም ሰው መንፈሱ አለለት። ሥጋ ቢጎዳም፥ ምንጊዜም ደስ የሚያሰኝ መንፈስ ነው።

በአጠቃላይ ስንመለከተው - ማንም ሰው የሚያደርገውን ሁሉ አቅሙን ካልመጠነ፥ በእራሱ ላይ ጉዳት ማምጣቱ አይቀርም፤ የአንድ ግለሰብ ጠባዩ (ንዴት፥ እልኸኛነትና ግትረኛነት) የወቅታዊ ሕይወቱን ሂደት እንደሚወስን ታዋቂ ነውና።

ወደ መንፈሳዊነት የሚመራውን ጎዳና እንዳታይ የሚከላከል ኃይል ላገርህና ለወገኖችህ ሳትጠቅም እንድትሞት ይገፋፋሃል። ግን በአንጻሩ፥ በምድራዊነትህ

ምክንያት መንፈሳዊነትህ የተዘጋ ሆኖ እንዳይቀር፥ እግዚአብሔር ለሕይወትህ ሌላ አንድ የሕይወት ምዕራፍ ከፍቶልሃል። ስለዚህ የሚከተለውን እመክርሃለሁ።

ሰውን ለማወቅ እራስን ማወቅ ያስፈልጋል፤ ሰውን ለማክበር እራስን ማክበር ያስፈልጋል። ሰው ሁሉ እየመሰለው ነው እንጂ፥ የራሱ የሆነና የራሱ ያልሆነ ሕይወቱን ነው ባንድ ላይ እየደረበ የሚኖርበት። አንተ ይህን ታሪክ በምትጽፍበት ወቅት በእውነት ምክንያቱ ምን እንደሆነ ማወቅ፥ መጨረሻውንም ማየት አትችልም። ነገር ግን፥ ያንተ ሕይወት ያንተ ብቻ ባለመሆኑ ብዙ እንድታወራ ተፈቀደልህ፤ ካንተም የሚማር ስለሚኖር።

የሰው ልጅ ሕይወቱ በልዩ ልዩ ምዕራፍ ስለሚከፋፈል፥ አንዳንድ ጊዜ ሥጋዊ ሕይወቱ፥ ሌላ ጊዜ ደግሞ መንፈሳዊ ሕይወቱ እያመዘነ ይኖራል። በዚህ ምክንያት ብቻ እንኳን ቢሆን፥ “ማሸነፍ እና መሸናነፍ በሌለበት - የማያቋርጥ ድብድብ - የእሱና የእሷ የህልውና ምልክት” ያልከው የማይደገፍ ይሆናል።

ሰዎች ብዙውን ጊዜ ከምድራዊ ሕይወታቸው ይማራሉ፤ ወደ እርጅናቸውም አካባቢ መንፈሳውያን ይሆናሉ። ብዙውን ጊዜ አቅጣጫው የሚያመራው፥ ቀስ በቀስ ከሥጋ ወደ መንፈስ ነው። ከልጅነታቸው ጀምሮ መንፈሳውያን ሆነው፥ በዚሁ አድገውበት፥ ጎልምሰውና አርጅተው የሚሞቱ አሉ። አንዳንዶቹ ደግሞ ልክ እንዳንተ - እስከ እርጅና እድሜአቸው ድረስ ሳይገባቸው ይቆዩና፤ በኋላ ሲገባቸው ያሳለፉት ኑሮአቸው ይቆጫቸዋል።

እግዚአብሔር አንተንም ሆነ ማንንም ማጣት አይፈልግም። እስካሁን ድረስ ያንተ ሥጋዊ ሕይወት ከመንፈሳዊ ሕይወትህ ያመዘነ ነው። ወደ መንፈሳዊነት ታመራ ዘንድ፥ ታጋሽና ሰውን አፍቃሪ አምላክ ለሕይወትህ ሌላ አንድ ተጨማሪ ክፍል ስለሰጠህ ነው ያለኸው። ያለፈውን ክፉውን ለመርሳትና የወደፊቱን ጥሩውን እያየህ ለመኖር በርታ።

ምድርን ልትኖርባት ከመረጥካት፥ ልትኖርባት ስትል ኑርባት እንጂ ልትለውጣት ብለህ አትኑርባት። ይህም ማለት ለመኖር ስትል ብቻ የምትችለውን ከማድረግ ተቆጠብ ማለት አይደለም። ነገር ግን፥ ምድርን ከሰዎቿ ጋር ልንለውጣት ብንፍጨረጨርም፥ እርሷ (ተፈጥሮ) በፈቀደችልን እንጂ፥ እኛ በፈቀድነው አለመሆኑ እንዲገባንም ያስፈልጋል።

የመኖር ዕድልህ ገና አላከተመም፤ ሕይወት ይቀጥላል። ከሰው ሁሉ ተለይቶ መኖር አይቻልም። ከዛፎች መካከል ዛፍ፤ ከቅጠሎች መካከል ቅጠል፤ ከሳሮች

መካከል ሳር፤ ከከብቶች መካከል ከብት፥ ከሰዎች መካከል ሰው.......፤ አንተ አንድ ፍጡር ከማንኛውም አካላዊ ሕያው ያልተለየህ መሆንህ ሲገባህ፥ የዛን ጊዜ ከፍጡራን ሁሉ ጋር ተስማምቶ መኖርን (መስሎ ማደርን) ታውቅበታለህ።

መጥን፤ ለምታደርገው ሁሉ መጠን አብጅለት። አንድ እንግዳ ከቤትህ ቢመጣ፥ ከሌማት ያለውን እንጀራ ሁሉ በገበታው ላይ አድርገህ፥ በድስቱ ውስጥ ያለውንም ወጥ በላዩ ዘርግፈህ በል ብላልኝ ብትለው፥ በድንጋጤ ቤትክን ጥሎ ይሄዳል። ግን እንዳቅሙ አንድ እንጀራ ብታቀርብለት፥ ወጡንም በትንሽ በትንሹ እየጨለፍክ ብታወጣለትና በፈገግታ - "እባክህ ብላልኝ እስቲ..." እያልክ፥ ብትጋብዘው እየጣፈጠው ይበላል። ስለዚህ መጥን። ምድራዊ ችግሮችን ለመቋቋም አቅምን እየመጠኑ፥ ሚዛናዊ እርምጃ መውሰድ ከማንም ግለሰብ የሚጠበቅ ነው።

አንዳንድ ጊዜ ችግር ሲደራረብ በአንድ ግለሰብ አቅም የማይገፋ ይሆናል። በሥጋዊነት (አካለዊነት - አለማዊነት) መቋቋም የማይቻለው ሁሉ በመንፈሳዊነት ይቻላል።

አሉታዊነት ሲበዛ ጉዳት ላይ ይጥላል። ብዙ ማሰብ እራስን ካለመሆን ጋር ሲሆን ያደናግራል። እራስን እየሆኑ የሚያስቡትና የሚያደርጉት ሁሉ አያደናግርም፤ እራስን ማወቅና እራስን መሆን የተያያዙ ናቸውና። በአዎንታዊነትና በምስጋና እንድትኖር ነው የኔ ምክር።"

<u>ቶማስ</u>

"ማንነቱ የሚያስፈራው ሰው ሌላውን እየመሰለ ይኖራል፤ ግን የግለሰብ መለዮው መልኩና ቁመናው ብቻ እንዳልሆነ ሁሉ፥ አንድ ሰው ምንም ሌላውን ለመምሰል ቢጥር፥ ወደደም ጠላም፥ ዞሮ - ዞሮ የገዛ መንፈሱ ወደራሱ ይስበዋል፤ አለበለዚያም ከራሱ አስወጥቶ ይጥለዋል፤ ያጠፋዋልም።

ከልጅነታችን ጀምሮ አካባቢያችን የሚያፈልቃቸውን ሃሳቦች እየተመገብን አደግን። ከምድራዊነታችን ያልጠበቅነውን ሽመትን፤ ያሳዝናል! እጅግ ያሳዝናል..........። በዘር መድልኦና በሃይማኖት አለመግባባት ምክንያት አንድነት ሲጠፋ፥ የሚያቀራርቡ ሃሳቦች ሲርቁ፥ የሚያራርቁ ሃሳቦች ጡት ሲጣቡ፥ ከአይምሮ በማይጠፉ ነገረ ሃሳቦች የሰዎችን ሕይወት ሲያወኩ፥ ይህ የብዙሐኑ ነገረ ሃሳብ ሁለንታዊ ኃይል ሆኖ ሲገላበጥ.....፤ እኔስ በሃሳቦቼ ተቀሰቀስኩ እንጂ፥ ሃሳቦችን አልቀሰቀስኩም (በሕብረተሰብ መካከል ምንም ችግር አልፈጠርኩም)።

የሰውን መንፈሱን ከሃሳቡ ለይቶ ይህ ነው መንፈሴ - ይህ ነው ሃሳቤ የሚል ማነው? የሰው አስተሳሰብ (መንፈሱ ያይደለ) በአይምሮ ህዋሳት ይንቀሳቀሳል፤ ከአንጎሉ እየመጠቀ የሚሄደው ሃሳቡም አካላዊ አይደለም። ስላልሆነም፥ የሰው አስተሳሰብ (ከመንፈሱ ጋር ያለ ወይም የሆነ) የአይምሮ ህዋሳትን ያንቀሳቀሳል ማለት ይቀላል። ግን ይህ እውነት ከሆነ፥ የሰው አስተሳሰብ ከአይምሮ ውጪም ውስጥም - ማንኛውም ሥፍራ ይገኛል ማለት ነው።

በጭንቅላት ህዋሳት ውስጥ ብዙ የተለያዩ ንጥረ ነገሮች በተለያየ መንገድ የኬሚካልና የኢሌክትሪክ እንቅስቃሴ (ንዝረት/ምጥቀት) ያካሂዳሉ። ንጥረ ነገሮቹ ከተጓደሉ፥ ወይንም አልኮል ሲጨመርባቸው ወንም ናርኮቲክ እና የመሳሰሉ አደንዛዥ ነገሮች ሲገባባቸው  በአይምሮ ውስጥም የሚካሄደው የኬሚካልና የኢሌክትሪክ እንቅስቃሴ ይዘበራረቃል። ሰውም "በትክክል" ማሰብ ያቆምና ለመኖር እንኳ የሚያበቃ ዝቅተኛ የሆነ ምድራዊ እውቀት ከአይምሮው ይሰረዛል።

ከሰዎች ጋር የማያቋርጥ  ያይምሮ ግንኙነት የሚያደርግ "ኃይል" ምንድነው? ሰው ጥሩ ሲሠራ መጥፎ መንፈሶች ይርቁና ጥሩዎቹ ይሰበሰባሉ፤ እነርሱው እንደሰው ይሆኑና ለበለጠ ጥሩ ሥራ መካሪዎች ይሆናሉ። በአንጻሩም እንዲሁ  ሰው መጥፎ ሲሠራ ጥሩ መንፈሶች ይርቁና መጥፎዎቹ ይሰበሰባሉ፤ እነርሱው እንደሰው ይሆኑና ለበለጠ መጥፎ ሥራ መካሪዎች ይሆናሉ።

ሰውና ሰውም እርስ በርሱ ልብ ከልብ እንዳይተዋወቅ የሚያደርጉ "ሁኔታዎች" ይኖራሉ - በሰዎች መካከል ወሬ የሚያመላልሱ፥ ፍቅረኞችን የሚያጣሉ፥ ጭራሽ ያልታሰበ ሁኔታ ፈጥረው የሰውን ሕይወት የሚያሰናክሉ።

አውቃለሁ፤ የሰው አይምሮም የራሱ የሆነ አስተሳሰብና እምነት ስለሚኖረው፥ እነኚህን ኃይላት (መንፈሶችን) በገዛ ራሱ ሊያርቅና ሊያቀርብ ይችላል። መንፈሶችም በበኩላቸው የሚያቀርቡትና የሚያርቁት የሰው አይምሮ ይኖራል (አይደለም?)። የሰው አንጎሉ (አይምሮው) ኳስ ሜዳ ወይም ትያትር ቤት።

መንፈስ ሁሉ አንድ እንዳለመሆኑ መጠን፥ በዙሪያችን በምናያቸው አካላውያን መካከል ያለ ልዩነት በመንፈሶች መካከልም እንደሚኖር እንገነዘባለን። ጥሩና መጥፎ መንፈሶች ወዲያና ወዲህ ሲንጎራደዱ፥ በመሃሉ የሰው አይምሮ ለብቻው አስቦ የሚፈጽማቸውን ጉዳዮች ሁሉ መቶ በመቶ በራሱ ቁጥጥር ውስጥ ለማድርግ ሲደክም ይታያል። ይህም ድካም አንዳንድ ጊዜ ውጤት አልባ ይሆናል።

ተፈጥሮን በቁጥጥራችን ውስጥ ማስገባት አንችልም፤ እውነትን (ዘላለማዊውን) እና እውነታን (ምድራዊና ጊዜያዊውን) ማገናኘት ካቅማችን በላይ ነው። አካባቢያችንንም እንኳን በደንብ መረዳት ያቅተናል።

ይህች አለም በሚታወቁና በማይታወቁ ሕግጋት ስለምትመራ፥ የምድር ኑሮአችን ቆንጆ እየመሰለ ይቆይና፤ ሊገለጽ በማይቻል መንገድ እየተበላሸ (እየተሰነካከለ) ችግር ውስጥ ይከተናል (እስቲ ከዚሁ ጋር ኢትዮጵያችንንም እናስባት)። ለምን ይህ ይሆናል? የሰማይን ደግነት ከምድሪቱ እውነታ ጋር እያጣጣሙ መኖር ስለሚያቅተን ነው? ወይንስ ኑሮአችንን እኛ ሳናስበው የሚነካካብን (ጎንተልተል የሚያደርግብን) አለ።

ማንኛውም ሰው ወደሞት የሚያደርሰው ሁኔታ ሲፈጠር - የምድር ገጽታ ለዛ ሰው ልውጥ ብሎ - እጅግ አስፈሪ እና አስከፊ ይሆናል። ሰውን ከሰው እየለየ ወደመጥፊያው የሚያቃርብ ምንድነው? ሁለት ሰላማዊ ሰዎች በድንገት ተጣልተው ይጋደላሉ፤ ሁለት የሕብረተሰብ ወገኖች (ብሔሮች) በጦርነት ይጠፋፋሉ።

ሰውን ቶሎ እየገደለ የሚጨርስ በሽታ ሲጠፋና ሰው ቶሎ አልሞት ሲል፥ በዚህም ሆነ በዛ ሞት አስፈላጊ የሚሆንበት ወቅት የሚመጣው ሞት ምድራዊ እውነታ ስለሆነ ነው? ወይንስ ሰማያዊ ድንጋጌ በመሆኑ ነው?

ሰው ቶሎ ይሞት ዘንድ ከአይምሮው መሰረዝ ያለባቸው "ነገሮች" ካልተሰረዙ ሞት በቀላሉ ስለማይመጣም በእርኩሳን መናፍስት ጣልቃ ገብነት ሰላማዊው ሰው ጠበኛ እየሆነ፤ ፖለቲካም ሃይማኖትም ተካሮ ሰውን ከሰው እያጋጨ...።

በአጽንኦት ለመግለጽ የፈለኩት፡- የሰብአዊነት ታሪኩን በአካሉ እንደምናየው በመንፈሱም ማየት እንዳለብን - "የህብረተሰቦች ታሪካዊ ጉዟቸው እንዴት ነው በመንፈሳቸው?" ብለን መጠየቅ እንዳለብን ነው።"

<u>ዮሐንስ</u>

"ሰፋ ያለ ባሕረ ሃሳብ እገባ ዘንድ ጊዜ የለኝም፤ ባንተው ላይ ባተኩር ይሻለኛል። ለኢትዮጵያችንስ ከሁሉም በላይ ሆኖ የሚያየት - የሕዝቦችን ጩኸት አይቶ የሚዳኛት አለላት።

በስሜት የሚቀሰቀሰውን አንተነትክን እውን ለማድረግ ስሜታዊነትህን ከንግግርህና ከተግባርህ ጋር ለማጣጣም ሞክር። የዛን ጊዜ ስህተቱን እና ትክክሉን አንተው እራስህ ለይተህ ታውቀዋለህ።

እውነትን ስትናገር በመጀመሪያ እራስህን ረስተህ መሆን አለበት፤ የዚያን ጊዜ አንተ ኃጢአተኛ ብትሆንም እውነት ለሰብአዊነት መተላለፏ (መነገሯ) ብቻ ነው የሚፈለገው።

እንዳይዙት እንዳይለቁት ግራ የሚያጋባ እየሆነ፥ በሃሳብ ባህር ውስጥ የሚከት ብዙ ጉዳይ አለ። ምን ጊዜም ጥሩ ጥሩውን ማስቀደም የሰውን ሕይወት ያሳምረዋል። ማንም ሰው ብርታትና ድክመት አለው። ሰውን ሲመክሩ አስቀድሞ ብርታቱን ተናግሮ ሲሆን፥ የታቀደው ምክር ግቡን ይመታል።

ዛሬ ስለ ደካማ ጎኑ ብቻ ልንገረው፤ በሌላ ቀን ስለ ብርቱ ጎኑ ስነግረው፥ ባጠቃላይ ከእኔ የሚያገኛቸው ሃሳቦች ይህን ሰው ያሻሽለዋል ብሎ አይምሮ ያስባል። መንፈስ ግን ጊዜ ሳይሰጥ፥ አይምሮ የሚያስበውን በጥሩም ሆነ በመጥፎ ያጎላዋል። ለምሳሌ፥ አንድ ሰው ጓደኛው ሲያጠፋ አይቶ ለመምከርና ለመገሰጽ በአይምሮው ያሰላስላል፤ በዚህን ጊዜ አይምሮ የሚያተኩረው ጓደኛው ባጠፋው ጥፋት ላይ ስለሆነ፥ በቀጥታ ጓደኛው ከዚህ ጥፋት የሚታረምበትን ምክርና ተግሳጽ ነው የሚያስበው። ታዲያ፥ አስቀድሞ ስለጓደኛው መጥፎ ሥራ ከነገረው፥ መጥፎ መንፈስ ሁለቱንም ይከባቸዋል። በዚህን ጊዜ፥ በጓደኛው ውስጥ የሚመለከተው መጥፎ ሥራው ይጋነንበታል። ያ ምክር ሊሆን የታሰበ ሁሉ በአንድ የመጀመሪያ አረፍተ ነገር ይበላሻል።

ይህ በስነአይምሮ ተመራማሪዎች ዘንድ ታዋቂ ሆኖ ሳለ፥ ብዙዎች ግን የመንፈስን ነገር ከጨዋታው ያገሉታል። ምንጊዜም ጥሩ መንፈስን እያስቀደሙ፥ በጥሩ ያልተጀመረ ነገር መጀመሪያውም መጨረሻውም አያምርም። ባል ሚስቱን፥ ሚስትም ባሏን፥ ጓደኛም ጓደኛውን ጥሩ ሥራቸውን አስቀድመው ከተናገሩ ጥሩ መንፈስ ይከባቸዋል። ያ ምክር ሊሆን የታሰበ ሁሉ በአንድ የመጀመሪያ አረፍተ ነገር ይሰምርና ውጤቱም ያማረ ይሆናል። የሚከተለውም አባባል ይህንኑ ነው የሚያመለክተው፡-

"ኮሶና ቁም ነገር ይመሳሰላሉ፤

ካለ ማጣፈጪያ እጅግ ይመራሉ፤

ኮሶን ለልጅ መስጠት በማር ጠቅልሎ ነው፤

ማሩ እየጣፈጠ ኮሶው እንዲያድነው።"

የእሳት ቃጠሎን በውሃ መከላከል እንደሚቻል ሁሉ፥ እኛም በትእግስት መሳሪያ ተጠቅመን ይቅር እንባባል፤ ጸብና ቁጣን ከመሃላችን እናጥፋ። በአሁኑ ጊዜ በእያንዳንዱ ሃይማኖት ውስጥ የጎደለው፥ እውቀት፥ እምነት ወይንም ደግ መሥራት ሳይሆን ፍቅር ነው። ስለዚህ ሁሉም በገዛ ሃይማኖቱ ቢጸና እና የጎደለውን ፍቅር ቢያሟላ፥ የሰይጣን የጥፋት እቅድ በቶሎ ይቀጫል።

በመላእክትም ሆነ በሰዎች ዘንድ፥ ንግግር ያው ያለና የሚኖር ሃሳብን መግለጫ ነው፤ ልዩነቱ - አካላውያን በአካላዊነታቸው፥ እንደ ነጎድፍድ በሚጮህ ቋንቋቸው ያንኑ ያለና የሚኖር ሃሳብ ያጎሉታል። የመላእክትና የመንፈስ ድምጽ የተለየ ነው። መንፈስ ዝም ብሎ ይናገራል፤ ዝም ብሎ የሚናገር መንፈስ ነው። የመንፈስ ድምጽ በዝምታም ቢሆን ይሰማል።

"ቀን ለቀን ነገርን ታወጣለች፤ ሌሊትም ለሌሊት ጥበብን ትናገራለች፤ ቃላቸው ያልተሰማበት ነገር የለም፤ መናገርም የለም፥ ቃላቸው ወደ ምድር ሁሉ ወጣ። ነገራቸውም እስከ ዓለም ዳርቻ ደረሰ።" መዝ. 18፡2 - 4

የቋንቋ አመጣጡ ከሰማይ ስለሆነ ፍጹም ነው፤ ግን ከዚህ ከምድራችን ሲደርስና ጥቅም ላይ ሲውል ይበላሻል።

ዝም የማለት ንግግር ከመለፍለፍ ንግግር የበለጠ ትርጉም የሚሰጥ ሊሆን ይችላል። ሰዎች ግን ከሚያወሩት ቁም ነገር በከንቱተ የሚለፈልፉት ይበልጣል[63]።

የሕብረተሰብአዊ ኑሮአችን በመንፈሳዊነታችን ይለካል፤ በአለም የኢኮኖሚ እርከን ስንታይ ዝቅተኞች - ድሆች ብንባልም እንኳን አኗኗራችን ወደመንፈሳዊነት ካዘነበለ፥ በምድራዊነታችን ያጣናውን በመንፈሳዊነታችን እናገኘዋለን (በሃብት የከበሩት የማያገኙትን ደስታ)።

ብዙውን ጊዜ ሽማግሌዎች ብዙ ከመኖር የተነሳ ብዙ ያውቃሉ። ምክንያቱ ገባንም/አልገባንም አንዳንድ የሽማግሌ ምክሮችን በተግባር ላይ ማዋል ይጠቅማል። ለምሳሌ፡-

[63] ምሳሌ 15፡1፤ 15፡18፤ የያዕቆብ መልእክት 3፡6-10፤ 1፡19 - 20

1ኛ) መጥፎ ጠባዮች ጎልተው ከሚታይባቸው ሰዎች (ተንኮለኞች፥ ምቀኞች፥ ሃሜተኞች፥ ንፉጎች፥ እራስን ወዳጆች፥ ሃሰተኞች፥ ሌቦች፥ ወዘተ..) መራቅ፡፡

2ኛ) አካላዊ ህያዋን ሁሉ (ዛፍ፥ ሳርና ቅጠል፥ ወፍ፥ ዝንጀሮ፥ ወዘተ..) ከምድር የሚኖራቸው ድርሻ የሁላችንንም ህልውና በጋራ የሚያስጠብቅ ስለሆነ፥ እነርሱም የምድራችን ተጋሪዎች መሆናቸውን ማወቅና መንከባከብ።

3ኛ) በተለይ ሰው በእግዚአሔር የከበረ ስለሆነ፥ ሲሞትም ለአካል ሰውነቱ ተገቢውን ክብር መስጠት።

የሰው ልጅ ከመንፈሱና ከሥጋው ጋር በምድር ሲኖር (ለግዳጃዊ ተሳትፎ የተሰለፈም ቢሆንም/ባይሆንም)፥ ዞሮ ዞሮ ምድራዊ አኗኗሩ በሰማይ ቤት የተወሰነ በመሆኑ፥ የተደነገገለትን (በሰማይ ቤት የተጻፈ ታሪኩን) ወደተፈለገው አቅጣጫ እንዲያመራ የሚያደርግ ኃይል በመኖሩ፥ በግንዛቤው ክልል ውስጥ ወይንም ከግንዛቤው ውጪ ይህንም ያንም እየነካካ ይኖራል።

በሁለት አለም የሚከናወን ማንኛውም “ነገር” ለየራሱ ቢሆንም፥ ጠፍተን እንዳንጠፋ ወደዚህች አለም ብዙ ምልክቶች ይገቡልናል። እኛም የእነኚህን ምልክቶች ትርጉም በመንፈሳዊ ምርምር ለመረዳት ስንጥር ነው ከሥጋዊነታችን ወጣ እያልን ለመንፈስ የቀረብን የምንሆን።

እኛኮ በሁለት ተጻራሪ ኃያላት መካከል የምንገኝ የመኖር (የመሆን) ምልክቶች ነን (እንደዚሁ እንዳለን)።

በሕይወት መቆየታችን በአንድ በኩል ለራሳችን፥ በሌላም በኩል ለጠባቂያችን ስለሆነ፤ ድርብ ኃላፊነት አለብን።

በአንድ የተወሰነ ወቅት ጥቂት ሕዝቦች (እስራኤሎች) በአንድ አካባቢ ሲኖሩ፥ ሌሎች ብዛት ያላቸው ሰዎች በየጊዜው እየመጡ ያጠቋቸው ነበር። እስራኤሎችም እንዲሁ ጭንቅ ብሏቸው፥ ሕይወታችን ተፈጥሮአዊ ሞት እስኪወስደው ድረስ እንዴት እንኑር ብለው ፈጣሪያቸውን ጠይቀዋል።

ጌዴዎን የተባለ፥ የኢዮአስ ልጅ በጊዜው የተጨቆኑ ወገኖቹን ከጭንቅ ለማውጣት በቅንነት ተነሳ፤ ታላቁ እግዚአብሔርም የእስራኤሎችን መጨቆን አይቶ በጌዴዎን በኩል ሊረዳቸው ፈለገ። ጌዴዎን ግን የእግዚአብሔርን ከርሱ ጋር መሆን ስለተጠራጠረ፥ እግዚአብሔርን ፈተነው። አዎ! ፈተና አቀረበለት። እግዚአብሔርም

እሺ ብሎ ለዚህ ለአንድ ታናሽ ወታደር ተፈተነለት። ይህ ታላቅ አምላክ ከፈለገ ምን ያህል ትንሽ መሆን እንደሚችል አሳወቀን። ከዚያም ፈተና በኋላ (መሳፍንት ምዕራፍ 6) ገዴዎን ከእግዚአብሔር ጋር መሆኑን ተገነዘበ - አመነ። ከዚያም በኋላ ጌዴዎን በሦስት መቶ ወታደሮች ብቻ ሥፍር ቁጥር የሌላቸውን ጠላቶቹን ለማቸነፍ በቃ[64]።

ሰዎች እንዴት እንኑር ብለው ፈጣሪያቸውን ይጠይቃሉ። ለዛ መልስ ተሰጥቶናል። እግዚአብሔር ለጊዜው እስራኤሎችን ቢረዳቸውም፥ እርሱ ለአንድ ወታደር ያደረገው ለጠቅላላ የአለም ሕዝብ መሆኑን፤ እራሱን ትንሽ ቢያደርግም ካለምክንያት እንዳልሆነ፤ የእርሱ እርዳታ በአንዲት የተባረከች ሴት አማካኝነት ለጠቅላላ የአለም ሕዝቦች እንደሚተላለፍ በምሳሌ ተገለጸልን[65]። ታዲያ ከጌዴዎን ጋር የማይታዩ ወታደሮች (መላእክት?) ተሰልፈው የተጨቆኑትን እስራኤላውያን እንደረዱቸው ካደረገ፥ እኛንም የሚረዳበትን መንገድ ካሳወቀን፥ የሰው ችግር ከሰብአዊ ግንዛቤ በላይ ቢሆንም እንኳን - ከፈለግን - ከለመንን ሰማያዊ እርዳታ እንደማናጣ ግልጽ ነው።

በምልክት ሲነገረን አልገባ ሲለን፥ አደጋ ሲመጣ መጠየቅ ስንጀምር፥ አሁንም አልገባ ሲለን፥ ካጠገባችን ሰው በሞት ሲለየን፥ ከዛም በኋላ ነገሮች ሲገለጡልን......። ሁሉም እኩል አይማርም፤ ሁሉም ባንድ ላይ አይሞትም። እግዚአብሔር የፈጠራቸውን ልጆቹን ሁሉ በጋራም ሆነ በግል እያስተማራቸው ነውና፤ በዚህም በዚያም በቂ ትምህርት ስለሚሰጥ፥ ማንም ሰው የተቀደሰ ኑሮ መኖር ይችላል። ስለዚህ፥ መጥፎ ነገር ሲደርስብን ሁሉ፥ በጥሩ ነገር አጸፋውን ለመመለስ ብንተጋ፥ በእውነት ፍጹምና ኃያል፥ ስሙ ክቡር፥ ለዘለአለምም የተመሰገነ ፈጣሪ አምላካችን - እርሱ የጨለመውን ያበራልናል፤ ቀናውንም መንገድ እርሱ ያሳየናል።

ረቂቁን የሰውን ፍጥረቱን፥ እንመልከት መንፈሱን፤
እንጠንቀቅ፤ ትኩረት በአንድ እራስ - በሥጋ ላይ ብቻ እንዳይሆን፥
ለኛ ተስፋችን - አለማችን፥ ከምድራዊነት ባሻገር መኖሪያችን፥
ፍቅር የሞላበት የጋራ ህልውናችን - በቅዱስ መንፈስ አንድነታችን።
ይህ እንዲሆን መጨረሻው፥
ጥሩው እያለልን፥ መጥፎውን አናጉላው።

---

[64] መሳፍንት 6
[65]መሳፍንት 6:36-40

የጠላት አላማው እንዳይሰምር፥
መሰዳደብ፥ መተማማት፥ መጣላትም ይቅር።
አናስቀይም ወገናችንን፥ አንመልከት ደካማ ጎኑን፥
ምንም ቢሆን ምንም፥ ሰው ለሰው ጠላት አይሁን።”

<u>ቶማስ</u>

“ምድራዊነት በየቀኑ ወደክፋት የሚመራ መሆኑን አውቄአለሁ። እውነተኛው እኔ እስኪገለጥ ድረስ ዝም ልበል ብዬ ተደብቄአለሁ፤ ከእንግዲህስ የሥጋ ሕይወቴ ለመንፈሳዊ እድገቴ ማነቆ እንዳይሆንብኝ፤ እኔ መንፈሳዊ ሕይወቴን ላቅና (ልጠግን፥ ላዳብር) በማለት ተነሳስቻለሁ፤ ለራሴ መንፈሳዊ ንቃት ያገኘሁ መስሎኛል።

በጠፈር ውስጥ በቀንም በሌሊትም ብርሃን አለ። ግን በምድር ላይ ባጠቃላይ በብዙ ሺህ ዓመታት ውስጥ፥ የሌሊት ጨለማ የሚሆንበት እና የቀን ብርሃን የሚሆንበት ተደምሮ ቢወዳደር አንድ ሴኮንድ እንኳን የማይበላለጥ (እኩል) ይሆናል። የምድር ክፋቶችና ደግነቶችም በተመሳሳይ ቢደመሩ እንዲሁ እኩል ቢሆኑ አይገርምም።

ደብዘዝ ያለ እውነትም የተስፋ ጭላንጭል ይሰጠናል።  እንደ ቀን የፀሐይ ብርሃን፥ ሌትና ቀን እውነት የሚፈስበት ምድር ውስጥ አይደለም ያለነው። ታዲያ በአስተሳሰቡ ፍጹም የሆነ ሰው እንዴት በምድር ሊኖር ይቻላል? ይልቅስ  የእውነትና ውሸት መኖር አስፈላጊነት ምርር - ክርር ያለ እውነት መሆኑን እንቀበል። በምድራችን የጨለማ መኖርን ያህል፥ የስነአይምሮአዊ ጨለማ ከሚፈጥሩ ሁናቴዎች ጋር ሳንወድ ትንንቅ እንገባለን፥።

የዚህን አለም ነገር ሁሉ በሚዛን እየመዘኑ መኖር እያስቸገረ፤ በሰው ውስጥ ያለው መንፈስ ግራ ተጋባ፤ ምድራዊነት አልበጀውም። ልጅ የአባቱን ጠባይ እንደሚወርስ ሁሉ፥ ሰውም ይህች ምድር በየጊዜው የምታሳየውን የጭካኔ መንፈስ ይወርሳል።

የሰው ልጅ የበራድ ዘመን ሲመጣ ሲሰደድ፥ ዝናም ሲጠፋ - የፀሐይ ሙቀት ሲያቃጥለው - በረሃብና በውሃ ጥም ሲሰቃይ፥ ይህች ምድር በየጊዜው የምትፈጥርበትን ችግር ለመቅረፍም ሲል፥ ሳያስበው ወደ ኃጢአት ውስጥ ይገባል፤ አካባቢውን ለመምሰል፥ ወይንም አካባቢውን በቁጥጥሩ ሥር አድርጎ ለመኖር ሲልም የገዛ ጠባዩን ወደ ጥሩም ሆነ ወደ መጥፎ ለመለወጥ ይታገላል።

በሰማይ የሚበሩ ወፎች፥ የሁለት አይኖቻቸውን ትኩረት ከኩንቢያቸው ጫፍ እና መድረስ ከሚፈልጉበት ሥፍራ ትይዩ አድርገው፥ ምንም ገልመጥ ገልመጥ ሳይሉ፥ ካለ ፍርኃት ይበራሉ። በሰማይ ላይ ምግብ ስለሌለ፥ ወደ መሬት ሲያተኩሩ፥ ምግብ ያዩ እንደሆን፥ ቀጥታ ከምግቡ አጠገብ ያርፉና ምግቡን ከመመገባቸው በፊት ገልመጥ - ገልመጥ በማለት ያካባቢውን ሰላም ያጠናሉ፤ ሰላም ከሌለ ምግቡን ጥለው ወደ ሰማይ ይበራሉ። አለበለዚያም መሬት ላይ በተበተነ ጥራ ጥሬ እርስ በርሳቸው ይጣላሉ።

ትልቁ አሳ ትንሹን አሳ እየበላው፤ ከባህር ውስጥም ቢሆን ከመሬት የባሰ ጭካኔ ይታያል። አውሬ ለአውሬ ይፈራራል፤ ሰው አውሬን ይፈራል፤ አውሬም ሰውን ይፈራል፤ ከሁሉም በላይ ሰው እርስ በርሱ ይፈራራል።

ሰው የራሱን ህልውና ለመጠበቅ ሲል ያደረገው እርምጃ (የጦር መሳሪያ ግንባታ)፥ በምድር ከሚታየው የሥልጣኔ እርምጃ ሁሉ ጉልህ ሆኖ ይታያል። ታዲያ፥ የምድር ጭካኔ ተፈጥሮዊ አይደለም ማለት ይቻላል?

ሰው ደንቁሮ - አውቆ፤ ተቅበዝብዞ - ረጋ ብሎ፤ ተቆጥቶ - ታግሶ፤ አኩርፎ - ይቅር ብሎ፤ ጨክኖ - አዝኖ፤ በእንዲህ አይነት ዥንጉርጉር ጠባዩ፥ ግማሽ ጎኑ ጨለማ ግማሽ ጎኑ ብርሃን ሆኖ ነው የተፈጠረው። ሰው ፈጽሞ ጥሩ እንዳይሆን፥ ጥሩነትም በምድር ላይ እንዳይሠራ ተከላላይ ያለበት ሥፍራ ነው ያለነው። ሰው በፍጥረቱ (በአፈጣጠሩ) ከተነከረበት ማጥ እንዴት በራሱ ጉልበት ሊወጣ ይችላል?

የያንዳንዱ ሰው መንፈሱ ከሥጋው ተገንጥሎ ሲታይ እውነትን ያስተጋባል ብለን በደፈናው እንናገራለን። ነገር ግን መንፈስም ቢሆን ከሥጋ ጋር ሲመሳጠር የራሱ የሆነ ፍላጎት ስለሚኖረው ፍጹም እውነተኛነቱ ይላላል።

የሥጋ ሕይወት በሞት ይቆራረጣል፤ ታዲያ የማይሞተው መንፈስ ኃጢአትን ካልተሸከመ በስተቀር እንዴት ኃጢአት ከዘር ወደ ዘር ይተላለፋል? ኃጢአት ራሱ አካል ስላልሆነ፥ በአካል የማይተላለፍ ነው። ስለዚህ፥ መንፈስ ምንም እንኳን ሥጋ ለባሽ ባይሆንም ኃጢአትን ተሸካሚና አስተላላፊ መሆኑ ነው (አይደለም?)።

ሥጋ ሆድን ለመሙላትና ለመባዛት ሲል ኃጢአት ይሠራል፤ መንፈስም ከሥጋ ጋር ሆኖ ሥጋዊ ፍላጎቶችን ያስተጋባና ኃጢአት ይሠራል (ነወይ?)።

እኛ አካላውያን ሆዳችን ለመሙላትና እርስ በርስ ለመባዛት ስንል ኃጢአት ስንሠራ እንገኛለን፤ በውስጣችን ያለው መንፈስ ደግሞ፥ ከኛ ከአካላውያን ጋር ለመኖር ሲል እውነትን ያጣምማል (ነወይ?)።

መናፍስት ግን፥ ለነርሱ ማደሪያ እስከተጠቀሙብን ድረስ በማይታወቅ (በማይለይ) እውነት (አንዴ ጥሩውን አንዴ መጥፎውን) ከፊት ለፊታችን እየደቀኑ እንዳሻቸው ይመሩናል። እነርሱም ከአካላዊ ሰው ሞራላዊ ግዴታ በላይ ሆናው ለመገኘት አንጎላችንን ለመቆጣጠር ይቃጣቸዋል።

በዚህ ሲሞት ግዑዝ በሚሆን አካላዊ ሰው ውስጥ ጊዜያዊና ምድራዊ ሕይወት የምትሰጥ ነፍስ ለፍርድ በምትቀርብበት ወቅት፥ ከሁለት በኩል (ከመንፈስና ከሥጋ) የተሠራ ኃጢአት ነው ለፍርድ የሚቀርበው (አደለም ወይ? ማን ሊያውቅ ይችላል ይሄንን?)።

በሰውና በእንስሳ መካከል ያለውን ልዩነት እስቲ እንመልከት። ከሰው ጠባይ የእንስሳትን ጠባይ ሲቀነስለት፥ ያ የሚቀረው ነው መንፈስ ብንል፤ ሰው ከላዩ መንፈስ ቢነሳለት እንስሳ ነው እንደማለት ይቆጠራል። ይህ ትክክል ነው?

ተኩላና በግን ብናወዳድር፥ ሁለቱም ምድባቸው ከእንስሳ ነው። ተኩላ በዱር ትናንሽ አውሬዎችን እያሳደደ በጭካኔ ይበላል፤ በግ ግን የሚታረድበት ጊዜ እስኪደርስ ድረስ ሳር እየበላ ይኖራል። ታዲያ፥ ከሰው መንፈሱ ቢወጣለት እንደ ተኩላ ነው የሚሆነው? ወይንስ እንደ በግ።

የአንበሳ፥ የእርግብ፥ የጅብ፥ የዝሆን፥..ወዘተ ጠባያቸው ከሰው ጋር የሚመሳሰለው፥ ሁሉም እየበላና እየተባዛ የሚኖር በመሆኑ ነው። ሰው ከጥንቱም ከአፈጣጠሩ ከእግዚአብሔር በተሰጠው መንፈሱ መንፈሳዊ ቢሆን በምድራዊነቱ እንስሳዊ ጠባዩ አይለቀውም። ይህም ማለት - በአንድ በኩል አይምሮውን በመጠቀም እንደ አንበሳም እንደበግም እየሆነ በአካላዊው ጠፈር ውስጥ ለመኖር የሚያስችለውን ሁሉ ያደርጋል፤ በሌላ በኩል ደግሞ፥ ከእግዚአብሔር በተሰጠው መንፈሱ በአካላዊነቱ የማይገዛ፥ የራሱ የሆነ ልዩ መንፈሳዊ ምግባር እያከናወነ፥ ሰማያዊ ህልውናውን እያደሰ ይኖራል ማለት ነው።

ከብዙ የሃሳብ ትርምሶች ባሻገር፥ የተረጋጋ መንፈስን የሚሰጥ እውነት ይገኝ ይሆን? የሚገባን እና የማይገባን እንኳ ለይተን የማናውቅበት የተዘበራረቀ አለም ውስጥ እንኖራለን። ለምን - እንዴት ሆነ ማለት እናበዛለን። ሰው ከጥንቱም ከአፈጣጠሩ ከእግዚአብሔር በተሰጠው ጠባዩ እንጂ፥ የመንፈስ ከእንስሳ ጋር መቀላቀል ወይም መዋሐድ ብቻ ላይሆን ይችላል ሰውን ጥሩ ወይም መጥፎ የሚያደርገው። የሰውን ኃጢአት የሚመዝን እግዚአብሔር ነውና፤ በርሱ ሥራ አንገባም።

ሰው ከሚሠራው ኃጢአት እና ምድር በሰው ላይ ከምትሠራው ኃጢአት የትኛው ያመዝናል? ብሎ ምድሪቱን መፋረድ[66] ካቅም በላይ ነው። በሃሳብ ጠልቀን ልናገኝ የምንችለው እውነት ትንሽ ስለሆነ፤ ይህን ለጊዜው በዚሁ እንተወው።"

<u>ዮሐንስ</u>

"እውነት ከሰው እውነትን የመቀበል ችሎታ በላይ ግልጥልጥ ቢል ያለንበትን አሳጥቶ የሚያደናግር ሁኔታ ውስጥ ሊከተን ይችላል።

እስካሁን ድረስ "አንቺ እውነት ከተደበቅሽበት ውጪ፤ አገር ሰላም ብለሽ ተደላድለሽ አትቀመጪ ለማለት ፈልገሃል። ጥፋቴና ኃጢአቴ ሁሉ ከምድራዊነቴ ወይንም ከውጪ ኃይል ነው እንጂ ከራሴ ብቻ የተቀሰቀሰ አይደለም ለማለት እየቃጣህ ብዙ ተፈላስፈሃል። ለአዲስ ሕይወት ዝግጅት - እንደገና ለመወለድ አስበህ የተናገርከ ቢሆን ነው ጥሩ።

እንግዲህ የሰው ልጅ በፍጥረቱና በአስተዳደጉ (እራሱን በራሱ ለመቆጣጠር መቻሉ) እዚህ ላይ ነው ብቃቱ። ባጠቃላይ፥ በምድር ላይ ለመኖር የሥጋን ፍላጎት ከመንፈስ ኃይል ጋር በአንድ በተወሰነ መንገድ ማጣጣም እንደሚያስፈልግ እንረዳለን። የምድሪቱን ቆንጆና አስቀያሚ መልክ ለያይቶ ማስቀመጥ ነው ያስቸገረው። የማይገባን ሁሉ (ስለ ሁለት አለም ሚዛን) በሚከተለው ጥያቄ ማጠቃለል ይቻል ይሆናል፡-

የሰው ልጅ በእግዚአብሔር ፍቅር ተጠምዶ - ለመንፈስ ቅዱስ የቀረበ በመሆን፥ ከራሱም ከመንፈሱም ጋር በዋሃሐድ ደግ ሥራ ብቻ እየሠራ እንዲኖር የሚያደርገው፥ ከራሱ ተፈጥሮአዊ ጠባይና ከምድራዊነትም ተጽንኦ ውጪ ሌላ ምንድነው?

ለዚህ ጥያቄ መልሱን የሰው ልጅ በራሱ ሊያውቅና ሊረዳ እንዲችል (እንደሚችል?) - ከሰማይ መንፈሳዊ እውቀቶችን ከምድራዊ እውነታዎች ጋር እያገናዘበ እንዲኖር - ኃላፊነቱ (ጫናው) ባለ አይምሮ በሆነ ሰው ሁሉ ላይ ነው።

እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ጥሩነትን በውስጡ ፈጥሮለታል። "መልካም መሥራትን የሚያውቅ የማይሠራትም ኃጢአት ትሆንበታለች።" ያዕቆብ 4፡17

---

[66] ይህንኑ በተመለከተ - የእንፋረዳለን ቅዠት (ግጥም) - ከምድራዊንውታችን ባሻገር - ሁለተኛው መጽሐፍ - ምዕራፍ አንድን ይመልከቱ።

ክርስቶስም ለደቀ መዛሙርቱ ምድራዊ እውነታን ከመንፈሳዊነታቸው ጋር እየመዘኑ እንዲኖሩ ሲመክራቸው እንዲህ አላቸው፡- “እነሆ እኔ እንደ በጎች በተኩላዎች መካከል እልካችኋለሁ፤ ስለዚህ እንደ እባብ ልባሞች፥ እንደ ርግብም የዋሆች ሁኑ።” ማቴ. 10፡16

ለሰማይም ሳይሆን ወይም ለመሬት፥

በጅምር የቀረ - ቅዥቅዥ ያለ ሕይወት፥

ካለ ቅዱስ መንፈስ ከቶም እንስሳዊነት።

ነፃ ፈቃዳዊ ፍላጎት ተሰጥቷልና በዚች አለም፤

የመንፈስና የሥጋ ሚዛን ካንዱ ወዳንዱ ቢያዘምም፥

በምድር ላይ ሥጋ የበላይ ሆኖ መንፈስን አይገዛም።

ሥጋዊ አይምሮ በውስጡ መንፈስ አለው፤

መንፈስም ጥሩና መጥፎውን ከሚለይ ሃሳብ ጋር ነው፤

ለዚህ ነው ሰው - ሰው የተባለው።

ሃይማኖታዊ ፍልስፍናም የራሱ የሆነ መዝናኛ ሥፍራዎች ይኖሩታል። ድኩላና አንበሳ፥ በግና ተኩላ፥ አህያና ፈረስ፥ በፍቅር የሚኖሩበት፥ ህጻናት ልጆች ከነብሮች ጀርባ ወጥተው የሚጋልቡበት፥ ሰዎች ከአንበሶች ጋር የሚጫወቱበት፥ ዝሆን አስራ ሁለት ሰዓት ሙሉ ሆዱን ለመሙላት ሳርና ቅጠል በማግበስበስ ፋንታ፥ ትያትር በመሥራት፥ ተዋንያን እያስተባበረ ወዲያ ወዲህ ሽር ጉድ ሲል የሚታይበት፥ ባጠቃላይ ደስታ ብቻ የሚገኝባቸው ኪርያተ ሰማያት በቁጥር ሚሊዎን እና ከዛም በላይ ይኖራሉ ብለን በምናባዊ (ሃሳባዊ) ፍልስፍና ውስጥ ስምጥ ብለን፤ የምሬታችን ግልባጭ ሆኖ ደስታን (ተስፋን) ይሰጠን ይሆናል። ይህ ምኞታዊ ወይም ቅዠታዊ አስተሳሰብ ላይሆን ይችላል፤ ምክንያቱም፥ እግዚአብሔር ሲፈጥርም በፍጡራኑ ውስጥ የእድገትና መሻሻል ጠባዮችን እያደረገ ነውና፤ የመጨረሻው መጨረሻ ሲቃረብ፥ ይህ እድገትና መሻሻል ከዛ ሊያደርሰን ይችላል።

አዎ! በዙሪያችን የከበበን እውነት ትንሽ ነው፤ እንድናውቅ የሚፈለገውም እውነት ትንሽ ነው። ጥሩነትን አናርቅ፤ ከንቱነትን አንጋብዝ። ለፈጣሪ አምላካችን ብቻ የአምልኮት ስግደት እየሰገድን ስንኖር፥ ከቅንነት፥ ከትእግስተኛነት፥ ከደግነት፥ ከመንፈሳዊ ደስታ እና ከምስጋና ጋር ይሁን።

ሰው ከመንፈሱ ጋር ተዋህዶ እንዲኖር ነው የእግዚአብሔር ፍላጎት። ለሚታየው የምናደርገውን ሁሉ ለማይታየውም እያሰብን ቢሆን፥ እኛም ከተፈጥሮአዊ - መንፈሳዊ ክስተቶች ጋር ተስማምተን እና ሰምረን አብረን ብንጓዝ፥ ይህ ሰብአዊነትን ያሳድገዋል እንጂ አያኮስሰውም።

ሰዎች እጅግ ሃይማኖተኞች/መንፈሳውያን ሆነው ስለ መጪው ኑሮአቸው ሲያስቡ፥ በዚህ አለም የመኖርን እውነታ ይዘነጉታል የሚሉ አሉ። መንፈሳዊ ለመሆን የሚጥር ሰው ትግሉ ከምድራዊነት ጋር መሆኑን እናውቃለን። ችግሩ ያለው የሁለቱን አለም ሚዛን አለማወቁ ላይ ነው እንጂ፥ ስለ አለማዊ ኑሮአችን ብዙ ከማሰባችን ጋር መንፈሳዊነታችንንም ብናጠናክር፥ አለማዊ ኑሮአችን ሰላማዊ ሆኖ ይሻሻላል፤ የማይነካው የእድገት ጣሪያው - ያ ፍጹማዊነት - ወደ እግዚአብሔር መቅረብ - ለኛ ለሰዎች ተሰጥቷልና።

እነሆ! ይህች ምድር (አለማችን) በሁለት ተጻራሪ ኃይላት ተወጥራለች፤ ግን ብዙዎቻችን ከሃዘን እና ከምሬት በስተጀርባ ግልባጩ - ተስፋ መኖሩን ስለምንዘነጋ፥ ከአካላዊው ምድር (ጠፈርም ቢሆን) መንፈሳዊው መኖሩንም ለማመን እንቸገራለን።

"‥ ምንም እንኳን በለስም ባታፈራ፥ በወይንም ሐረግ ፍሬ ባይገኝ፥ የወይራ ሥራ ቢጎድል፥ እርሻዎችም መብልን ባይሰጡ፥ በጎች ከበረት ቢጠፉ፥ ላሞችም በጋጡ ውስጥ ባይገኙ፥ እኔ ግን በእግዚአብሔር ደስ ይለኛል፤ በመድኃኒቴ አምላክ ሐሴት አደርጋለሁ።" ዕንባቆም 3፡17-18

ምድራዊነትን ከራሳችን ተፈጥሮ ጋር አስታርቀን መኖር ስለሚያስቸግረን - "ወደ ፈተናም አታግባን፤ ከክፉ ሁሉ አድነን እንጂ..." ብለን በየጊዜው እንጸልያለን። ምን ጊዜም ከአካል ጋር በመጣመር አብረው የሚጓዙ የክፋት መናፍስት (ከምድር) የደግነት መናፍስት (ከሰማይ) እንዳሉ ይገባናል። ሁለቱም በአንድነት ተገናኝተው ጦርነት ሲገጥሙ አላየንም። እንዳው በቁንጽሉ - ምድራዊነት ይህ ነው ብለን በአካላዊነት በምናየው ላይ መነጋገሩ ምንም አይጠቅምም። ሆኖም፥ ይህች ምድር ለሰው ሁሉ አንድ ስላልሆነች፤ በሚከተሉት በሦስት ገጽታዋ እንመልከታት፡-

1ኛ) በምድር ላይ በሚሠራው የኃጢአት ሥራና በአስተዳዳሪዋ (በገዢዋ) በሚመራው ክፋት ሁሉ፤

2ኛ) በምድር ላይ በሚኖሩ ሰዎች፡- በፈቃዳዊ ፍላጎት እና ግዴታዊነት (የሁለቱ ሚዛን) የተመሠረቱ የሰዎች የበላይነት፤

3) በምድሪቱ ምግብነት።

በምድር ላይ የሚኖረን ቅሬታ በተራ ቁጥር አንድ (በምድር ላይ በሚሠራው የኃጢአት ሥራና በአስተዳዳሪዋ (በገዢዋ) በሚመራው ክፋት ሁሉ ላይ ቢሆን፤ ይህ ለጻድቁም ለኃጥኡም የሚቀርብ ፈተና መሆኑ ነው።

የሰው ልጅ እውቀት ደስ የሚል ሰላማዊ ሥልጣኔ አላተረፈላትምና፤ ከጥንት ጀምሮ፥ ምድር ከማርና ከእሬቷ ጋር ቆይታለች። ጥንትም ሆነ አሁን፥ እድለኛ ሰው ማሯን ሲበላ ይወዳታል፤ እድለ ቢስ ሰው እሬቷን ሲቀምስ ይጠላታል።

በተራ ቁጥር ሁለት እንደተጠቀሰው፥ ሰው በፈቃዳዊ ፍላጎት እና ግዴታዊነት (የሁለቱ ሚዛን) የተመሠረቱ የበላይነት ስላለው፥ ምድሪቱን ለጥሩም ሆነ ለመጥፎ ሊለውጣት ችሎታ አለው። ሰው በውስጡ ሚዛን አለው፤ በዚህም ሚዛን ጥሩና መጥፎውን እየመዘነ፥ ከመጥፎው ጥሩ ሲያመዝን ጥሩ እያለ፤ ከጥሩው መጥፎው ሲያመዝን መጥፎ እያለ ይኖራል።

ምድር በላይዋ ላይ ለሚገኙ አካላውያን ምግብ ትሆን ዘንድ ተፈጠረች፤ እኛም እራሳችን ከሌሎች ተጠቃሚ እንስሳዎች ጋር ምግብ ሆና ስለበላናት፥ እርሷን ልናመሰግናት እንጂ ልንራገም አይገባም። እርግማኑ ለዛ ለእርጉም የምድራዊነት ምልክት ወደ ሆነው ወደ እርኩስ መንፈስ (ወደ ሰይጣን) ይሂድ።

የሰው መንፈሱ አደጋ ላይ ሊጥል የሚችል ሁኔታ ሲመጣ ያውቃል፤ ግን የአካላዊነት ጠባይ ስለሌለው ለብቻው የመከላከል ችሎታ ይጎድለዋል። ከፍተኛ ጥበብና ጥንቃቄ የሚጠይቅ ሥራ ሁሉ የሚሳካው በሥጋና በመንፈስ ውህደትና ስምምነት ነው፤ ከዚሁ መሠረታዊ የመንፈስና ሥጋ ውህደት በመነሳት ነው ከፍተኛ ደረጃ የሚደረስ።

ሰው በጥሩነቱ መንፈሱን ከሥጋው ጋር ሲያዋህድ፥ በመጥፎነቱ ደግሞ ይለያየዋል ማለት ባይሆንም፥ የመንፈስና የሥጋ አለመጣጣም በየጊዜው ሲከሰት እናያለን፤ ለምሳሌ፡- ሰው ከሰው ሲጣላ፥ ወይንም ምድራዊ ችግሮችን ለመቅረፍ በሚታገልበት ወቅት የተለያዩ ስህተቶችን የሠራል።

ሰው የሚያሰክር መጠጥ ሲጠጣና ሲሰክር መንፈስና ሥጋው ይቃረናሉ፤ ለጤንነት ያህል መጠነኛ መጠጥ ጠጥቶ ከራስ ጋር መቆየት ሲቻል፥ ከልክ በላይ መጠጣትና መስከር እራስን ለአደጋ ማጋፈጥ፥ ከራስ መገንጠል (የመንፈስና የሥጋ አለመጣጣም) ነው። የሰው እንቅስቃሴ ሁሉ ከመንፈስ ንቃት ጋር የተያያዘ ስለሆነ፥ ሥጋውን ከመንፈሱ ጋር ማስተባበር - በምድር እየኖሩ ራስን ለሰማያዊ ኑሮ ማዘጋጀት እንደሚያስፈልግ ከተገነዘብን ይበቃል።”

# ምዕራፍ አስር

## ሰማያዊ ተስፋ - ከጥፋትና ከኃጢአት ባሻገር

<u>ቶማስ</u>

“እነሆ! ማንም ሰው በሃሳቡ ብቻ አለምን የሚቀይር ቢሆን ኖሮ፥ እኔ የምወደው ሥራ ስለሚሆን ለእጩነት እሮጥ ነበር።

ፀሐይ ከአድማስ ጀርባ ተደብቃ ጮራዋን በከፊል ወደ ሰማይ ስትፈነጥቅ፥ ምድር የጋረዳት ጨለማ ሲገፈፍ፥ ውበቷም ሲከፈት፤ በጧት ከሰማይ እንደ ውሃ ጎርፍ የሚፈስ ብርሃን ከሙቀት ጋር ሰዎችን በልዩ ስሜት ሲያርስ፤ በማለዳ የሚነሱ ሰዎች በልዩ ተስፋና ደስታ ተቀስቅሰው ከሞት እንደተነሳ ሰው ሲንጠራሩ፤ ብድግ ብለውም ወደ ሥራ ሲሰማሩ፤ በአለም ማህበር ውስጥ ተሳታፊ በመሆን ኑሮአቸውን በከፍተኛ ስሜት ሲመሩ፤ እኔ ቀሰስተኛ ኑሮ ያስመለከተኛል፤ መንፈሳዊነትም ውስጥ ስምጥ ማለት ያሰኘኛል።

ሰው በውስጡ ተናጋሪ - አናጋሪ መንፈስ ከሌለው፥
እንዴት ይታወቃል - የማይጨበጠው የማይነካው?
በአይን የማይታይ - መንፈስ ከጎናችን ጠጠው[67] ቢል፥
እንዴት ማወቅን ያሳውቀናል አካል?
ግን ሃሳብ እንደ ሕልምም ቢመስል፤
እስቲ እናስበው ስለ ሕያው ነፍስ - ወደ መሬት ስለ መጣል።
ምንድነው ይህ ምልክት? እኔው በኔ የታቀፍኩበት፥
ይህ ምስል (ሰው) ያንተው ነው ሲለኝ የሰማሁት።
እንዴ! ይገለጥ እንጂ ምሥጢሩ የአንዱ ሰው ሁለትነት፥
አንዱ ከሰማይ ሌላውም ከመሬት።
አፈርና እጽዋት - ተስተካክሎ ተቀምጧልና ሁሉም ከመሬት - ለምግብነት፥

---

67 **ቀጥ ብሎ** መቆም (**በትግሪኛ**)

ስለዚህ፥ መሬት መሬቱን ነው የሚያዩት የዱር አራዊት፥
የሰማይ ወፎችም በከፍታ ሆነው መሬት መሬትን ነው የሚያዩት፥
ግን ሰው ቢያንጋጥጥ ወደ ሰማይ፥
የመጣበትን ሊያስተውል - የህልውናውን ጉዳይ፥
ናፍቆት የሆነው ከምግቡም በላይ፤
ሌላኛው ሕይወቱ ሳይበላ የሚያጠግበው፥
አብሮትም ያለ - ግን በደንብ የማያውቀው።
　　ሥጋዬስ ይታየኛል፥ መንፈሴ ከወዴት ነው ያለው?
　　ሽማግሌው እኔ፥ መንፈሴ የትኛው ነው?
　　እዛም እዛም ቀዥቀዥ የሚለው፥ የማይገመት ዕድሜው፤
　　አይ ሰው! አይ ሰው! አይ ሰው!  ከቶ ማንነቱ የማይለየው!
ምድራዊነት -  ነፍስን ከሰማይ ተበድሮ፥
ሥጋን ቆንጆ አስመስሎ፥
ይህንንም ያንንም መስሎ፥
ለትርጉም እንዲያመች አስተካክሎ...።
　　ግን ንፍስና ሥጋ ያዙኝ ልቀቁኝ ይላል፥
　　ሰው ብቻውን - ራሱን ችሎ መቆም አቅቶታል።
የምድሪቱም መጋቢነት - ካለ ክፍያ የማይገኝ፥
ውጪ ነፍስ - ግቢ ነፍስ የሚያሰኝ።
የውሃ ጎርፍ ሰውን ነጥቆ፥
በጭራሮ - በእንጨት ሁሉ ተማቶ፥
ከድንጋይ ጋር አላትሞ፥ ነፍስ አጥፍቶ...።
አውሎ ነፋስም - የሰማዩም መብረቅ፥
ሁሉም ኃይለኛነቱን አሳይቶ፥
ሰው አደብ ሲገዛ ዝም ብሎ፥
ሲያጠፋም ተቆጥቶ......።

ለሁሉም ከጥቅሙ ጋር - ምክንያት ቢኖረው ነው እንጂ ፍጥረት፥
ምግብ ብቻ ያይደለች፥ ለልጆቿ ሁሉን ተሸከማለች መሬት።
ኤሊ እንቁላሎቿን ከአሸዋ ሥር ቀብራ ስትተዋቸው፥
ልጆቿ ይወጣሉ በራሳቸው፥ እንቁላሉን ፈልቅቀው፤
ካለ አባት - ካለ እናትም ያድጋሉ ለብቻቸው፥
ነፋሱን ብርዱን ሙቀቱን - ሁሉን በራሳቸው ተከላክለው፥
ረጅም እድሜ ይኖራሉ - ቤታቸውን ተሸክመው።
እና - እኔም እንደ ኤሊ የምችለው መስሎኝ - ሁሉንም በራሴ፥
ከአካላዊነት ሳልላቀቅ ከምድራዊው መንፈሴ፥
ኑሮ በሁለት ተከፍሎ ሆነብኝ፥
ሰው መሆኔ (ሰብእነቴ) ራሴን አሳጣኝ።
አይምሮም በታማኝነት ሥራው፥
አካል ያልሆነ ሃሳቡ ሲታገለው፥
ለስነ አመክኖአዊ አስተሳሰቡ ድጋፍ እንዲሆነው፥
"መንፈስ ከውስጥም ከውጪም - ሁሉም ቦታ አለ" ብሎ ነገረው።
አዬ! መላስ የብቻውን ነፍስ ሲያወጣ፥
"እንዲህ ነው - እንዲያ ነው" ብሎ መለፍለፍን ሲያምረው፥
እስቲ እኔም ከውጪ ሆኜ ሰውን ልታዘበው፥
የሃሳብ ጉም ሥፍራውን ሲመላው።
እስቲ እኔም ከውጪ ሆኜ ሰውን ልታዘበው፥
ተሳታፊ ሳልሆን ከሩቅ ልመልከተው፤
አራጅና በሬ በሥራ ላይ ሆነው፥
ከአንዱ ሰው ሁለት ሰው፥
ሲሮጡ ባንደላይ፥ ፈረስ - ፈረሰኛው፤
ሲደብቅ - ሲገለጥ እስካሁን የቆየው፤
ግቡ ያው - ግቡ ያው - የመንፈስና ሥጋ ባንድነት ማደግ ነው?

ድምጽ ጎርነን ሲል፥ ጨለማ በብርሃን ላለመጥፋት ሲክለፈለፍ፥
የሰው መልኩ ሲለዋወጥ፥ እውነት በመሬት መናፍስት ሲጠለፍ።
የእግዚአብሔርን አለመፍቀድ ለመሥራት ተጣድፈው፥
በሠለጠኑበት ተሰማርተው፥
ሥፍራና ቦታ ጠብቀው፥
ሰውን ከሰው ለማጋጨት ተቻኩለው፥
ከደቂቅ እስከ ግዙፍ ሁሉን  ነካክተው።
በደረቀ አፈር እንደሚሰርግ ውሃ፥
በቀዳዳ እንደሚሾልክ ጢስ፥
ከዚህ እስከዛ ድረስ፥
ሁሉን የሚያዳርስ፤
ሰው የማይሠራውን ሁሉ የሚሠራ፥
እስከመጨረሻ ግቡ ድረስ...።

በአይን ለማየት የማይፈለገውን ነገር አይን እንዳያይ አይን ይከደናል፤
በጆሮ ለመስማት የማይፈለገውን ነገር ጆሮ እንዳይሰማ ጆሮም ይደፈናል፤
አፍም ይሎገማል - መላስም ይገታል፤
በምድራዊም በሰማያዊም ክስተቶች ስንንገላታ እንዴት ዝም ይባላል?
እኸኸ! ይበቃኛል።

ብዙ መኖር ብዙ ያሳያል፤ በደል ሲከብድ ይገድላል። የጊዜው ሁኔታ መንፈሴና ሥጋዬ የተለያየ ሥራን እንደሚሠሩ አደረገብኝ (አስመሰለብኝ)። አሁንም አንድ እራሴን መሆን አቅቶኝ ተቸገርኩ (ለዚህ ነው ሁለት የተከፈልኩት)፤ የሰው የመንፈሱ ስሜት ከሥጋው ሲበልጥበት፤ እኔ በእርግጥ በሁለት አለም ውስጥ ነኝ እንድል የሚያደርገኝ ሁኔታ፥ ለሰው የማይገባውን እንድናገር ገፋፋኝ።

ለመሆኑ የመንፈስ ድርጊቱ (ክንውኑ) እስከምን ይደርሳል? የራሳችን ሥጋዊ ስሜት እናውቀዋለን፤ ከሥጋ በላይ የረቀቀ የመንፈስ ኃይልስ ምን አይነት ስሜት ቢኖረው ነው ሰውን በሥጋው ከሚችለው በላይ የሚያንገላታው።

የማንም ሰው በሰማይ የምትቀጥል ሕያው ሕይወቱ ከምድራዊ ኑሮ የምታገኘው ደስታ በሰማይ ከምታገኘው ሃዘን የማትሻል ልትሆን ትችላለች፤ ታዲያ፥ ለምድራዊ ኑሮ መስገብገብ ምን ያደርጋል?

በሰው ልጆች ግንዛቤ ውስጥ የሚገቡ “ፍሬ ሃሳቦች” ሁሉ ሲነገሩ “ለምክንያት” መሆኑ እንዲታወቅ፤ “እንዲመስል” እየሆነ “እንዲያሳውቅ”፤ እና ጊዜው ሲደርስ ከምድራዊነት በሰላም ለመላቀቅ እንዲረዳ - ልንሞት ስንል ደስ እንዲለን እንጂ እንዳንከፋ፥ ቋሚም በሙታን መለየት ደስ እንዲለው እንጂ ሃዘን እንዳይገባው ብዬ ለፈለፍኩ።

አሁንም የማይገቡኝን ጉዳዮች ለመግለጽ የቻልኩ አይመስለኝም። የድሮ ሰዎች ለጊዜ ሳይሳሱ ስለሚወያዩ፥ በሃሳብ ይቀራረቡ ነበር። እኛ ግን ጊዜ ያነሰበት ዘመን ተፈጥረናልና፤ በሰዎች ስሜቶች ውስጥ ዘብረቅረቅ እያሉ የሚሰርጉ ሃሳቦችን አመጣጥ ለመመርመርም ጊዜ እናጣለን። አዎ! አንዱ ሰው ሁለት ከሆነ፥ አንዱ ከሌላው ተለይቶ ይታወቅ ዘንድ ተናገርኩ። በቃኝ፤ መድረኩን ልልቀቅ፤ መንፈሳዊ መስሎ ምክር የመስጠቱን እድል ዮሐንስ ይውሰድ።”

<u>ዮሐንስ</u>

“መላእክት ወደማይደፍሩበት ሥፍራ ከመሄድ ይልቅ ወደራሳችን ብንመለስ ይሻለናል። ከአንድ ግለሰብ ውስጣዊ ጠባይ በመነሳት ጠቅላላ የሰውን ፍጥረት መግለጽ አይቻልም። ግን ለጥቂት ሰዎች በምሳሌነት የሚያገለግል ከሆነ፥ ከሁሉ በፊት የተፈጸሙትን መንፈሳዊ ክስተቶች ሁሉ፥ ካጋጠሙህ ምድራዊ ችግሮች ጋር በማጣመር አጭር መልእክት እናስተላልፍ። እኔ አንተን ነኝ፥ አንተም እኔን ነህ ካልክ፥ የተቀበረው ይውጣ።

መሳሳት ያለ ነውና - እንኳን ከሰው ጋር በምድር ያለ መንፈስ ይቅርና፥ በሰማይ ቤት ያሉ መላእክቶች እንኳ የተሳሳቱበት ወቅት እንደነበረ ሁሉ፥ ከእኔም ካንተም የተሠራ ኃጢአት ካለ ይነገር። የሰው ኃጢአቱ የሚታወቀው ውስጣዊ ክፋቱ ከአፉ ሲወጣ፥ ሲሰርቅ፥ ሲያመነዝር ወይንም ሲደባደብ በመታየቱ ብቻ አይደለም። ይህ ሁሉ ለሰዎች በግልጽ የሚታይ ስለሆነ እንዲህ አይነቱን ኃጢአት አይደለም ኃጢአትህ ይነገር ያልኩት። ለብዙ ዓመታት የቆሸሸን ቤት ማጽዳት ቀላል አይሆንምና፤ ሌላ ለሰዎች የማይታይ ኃጢአት ስላለ ይውጣና ይነገር።

የሰው ኃጢአቱ ባይታይም፥ መኖሩ በአካላዊ መንገድ ባይከሰትም ይኖራል። ለምሳሌ፡- ቀደም ሲል ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄደህ የምትማረው መንፈሳዊ ትምህርት ካንተ ግንዛቤ ጋር ባለመጣጣሙ፥ አጉል በሃሳብ ስትፈናጠር ቆይተሃል። ማንም የሃይማኖት አስተማሪ አንዱን ሃይማኖት ከሌላው አስበልጦ ማስተማር የለበትም በማለት ውስጠ መንፈስህን ምርር አድርገኸዋል። ውስጠ መንፈስህ ምርር ሲል፥ አንተ ባትናገርም አላስፈላጊ ሞገዶች ወደ ሌሎች ሰዎች ይነጉዳሉ። እኔ አላልኩም ብትልም ውስጠ መንፈስህ በድምጽ አልባ ሹክሹክታ ለሌላው የማይስማማ ሃሳብህን ልዩ ትርጉም ሰጥቶ ያሳብቅብሃል።

በአዎንታዊነት ሲታይ፥ ሰው ሁሉ ደግ ነው፤ የኛ ኃላፊነት ለበጎ ምግባር ብቻ ወደፊት መጓዝ ነው። ሁለት ደጋግ ሰዎች ይጣላሉ፤ አህያውን ትቶ ዳውላውን እንዲሉ፥ የሚያጣላቸውን እውነተኛ ጠላት (እርኩስ መንፈስ) ትተው እርስ በርስ ይጠቃቃሉ። በእርግጥ ሰው በሰይፍ እንደሚቀተል (እንደሚገደል)፥ ሰይጣንም በበጎ ምግባር ይቀተላል።

እራስህን በራስህ ግልጽ ሳታደርግ ወደ እውነት መቅረብ አትችልም፤ ለሰዎችም እራስህን ግልጽ ስታደርግላቸው ነው የምትናገረውን በጥሞና የሚሰሙህ። ተናግረህ፥ ተናግረህ ሃሳቦችህ ቁበቻ (ማረፊያ) ቦታ ካላገኙ፥ እንደ ባዶ ታኒካ የምትንኳኳ ለፍላፊ ቀባጣሪ ነው የምትቆጠረው።

እኔም ካንተ ጋር እስካለሁ ድረስ፥ ኃጢአትህን (ያንተንም የኔንም) ሳትናዘዝ፥ የመንፈሳዊነትን እመርታ ልሰጥህ አልችልም። ከምድራዊነት ተላቀህም የምታደርገው ሰማያዊ ጉዞ ዘለቄታ ሊኖረው የሚችለው በቅድሚያ ልብን አንጽቶ መሆን ስላለበት፥ ለዚህ ረጅም ጉዞ የሚያስፈልገውን ቅድመ ዝግጅት ለመመጀመር እንገደዳለን።

ምድራዊነት ማለት ሥጋዊ ክብር ነው። ይህ ሥጋዊ ክብር ለሰማያዊ ሕይወት ስለማይበጅ፥ ይልቅስ ለሰው ልጅ ትምህርት፥ ላንተም ለራስህ ንጽህና ይሆንህ ዘንድ ተናገር። ቀጥተኛነትና መንፈሳዊነት የማይነጣጠሉ ስለሆኑ፥ በመጀመሪያ ያን የደበቅኸውን፥ ከሃያ ዓመታት በፊት የጻፍከውን አውጣ።

ቀደም ሲል፥ በሰዎች ግንዛቤ ውስጥ በቀላሉ የማይገቡ ሐተታዎችን፥ ታሪክህን ለማያያዝ ስትል ብቻ ጣደፍ ጣደፍ እያልክ ተናገር ብዬህ ነበር። አሁን ደግሞ፥ ይህ በምድራዊነት የሚገኝ ሥጋዊ ክብር ላንተ ባዶ (ዜሮ) የሆነበት ወቅት ላይ ስለተደረሰ፥ ከእንግዲህ እንቅስቃሴህ ሁሉ ለሰማያዊ ሕይወት ዝግጅት ነውና፤ ለእውነት ስትል ተናገር።”

<u>ቶማስ</u>

“ወደ ዘለአለማዊነት ከመሸጋገሬ በፊት በአካላዊነቴ ጥቅም ሳልሰጥ እንዳልቀር መከርከኝ። አዲስ ሕይወት የማገኝ እንዲመስለኝ ልዩ ሃሳብ በጭንቅላቴ ሰረጽክብኝ (መሰለኝ)። አንድ ሰማያዊ ተስፋ የሚሰጠኝ መንፈሳዊ ንግግር አሰማኸኝ። በደንብ ነገርከኝ፤ ሰምቻለሁ፤ ሰማሁህ፤ እንዳልከውም አደርጋለሁ።

የቆሸሸው ቤቴ ይህ ነው፡- በተፈጠሮአችን (እርፎ የማይተኛ መንፈስ) ብዙ ጉዳት ይደርስብን ዘንድ፥ ከመሆኑ አስቀድሞ ብናውቅም (በግልጽ እየታየን)፥ ጉዳቱ ሲደርስብን “ለምን - ለምን ሆነ!…” እያልን፥ በሥጋችን ብንጎዳ፥ ያም እድል ፈንታችን ነውና፤…ነገር ግን ይህ አይነቱ ሁኔታ ሲፈጠር፥ ወደ መንፈሳዊ ጉዞ ውስጥ እየከተተን፤ ከጊዜ ወደ ጊዜ መንፈሳዊ ብርታት እየሰጠን ሲሄድ፥ የሥጋ ጭንቀት ወደ መንፈስ ብርታት ይለወጣል ብለን ስናስብም፥ ከምድር ጭንቀት ሲሆን፥ ተስፋ ከሰማይ እንዲሆንልን እየተመኘን፤ በዘወትር ኑሮ (በምድራዊነት) መጠመድ ግዴታ ቢሆንና ቢያስቸግረን፥ *“ሥጋንም የሚገድሉትን፥ ነፍስን ግን መግደል የማይቻላቸውን አትፍሩ፤ ይልቅስ ነፍስንም ሥጋንም በገኃነም ሊያጠፋ የሚችለውን ፍሩ”* የሚለውን የጌታ ቃል እየሰማንና እየተጽናናን…፤ ሰውም ከባዶነት የመንፈስ ስሜት ለመላቀቅ ሲታገል፥ ወደ ምኞታዊ ያልታወቀ ስሜትም ሲሸጋገር፤…. የመንፈሶች ትርምስ እንደ ቅዠት ሲሆንበት፥ በሥጋው ቢጎዳ፥ ነፍሱ እንድትተርፍለት ሲል፥ ወደ እግዚአብሔር ለመጠጋት ሲታገል፥ መንፈሳዊነቱ ከምድራዊ እልህ ጋር ሲቀላቀልበት፥ እርር ድብን ብሎ ሲያለቅስ፤ ለመኖርም እንዳይችል የሚያደርግ የውጪ ኃይል ሲመጣበትና መቋቋም ሲያቅተው፤……. እንዲህና ይህንን የመሳሰሉ “የተፈጻሚ ድርጊቶች ጥላዎች” የሰውን አስተሳሰብ በልዩ ኃይል ሲነበኙት፥ ጭንቅላት የራሱን ስዕሎች በነጻነት ይስላል። ይቅርታ፤ ሕልም አየሁ ለማለት ስል ብዙ ለፈለፍኩ መሰለኝ።

የሚከተለውን ሕልም አየሁ፡- እኔ ቶማስ መኪና እየነዳሁ ስሄድ፥ ከበስተኋላዬ የትራፊክ ፖሊሶች ይከታተሉኛል። ቁም የሚለውን ምልክት አላከበርክም በማለት መኪናዬን ካስቆሙ በኋላ፥ ሁለት የትራፊክ ፖሊሶች ሁለት ሽጉጦች በሁለት ጆሮዬዎቼ ላይ ደገኑብኝ። የሚገድሉኝ መሰለኝና ደነገጥሁ። “የኃጢአቴ ብዛትና ቅጣቴ አልተመጣጠነም...” ብዬ አሰብኩና በድንጋጤ ፈዘዝኩ።

“በእርግጥ አጥፍቻለሁ፤ ግን ከፍርድ መድረክ ቀርቤ ቅጣቴን ብቀበል አይቆጨኝም፤ ይህ በሽጉጥ ማስፈራራት ግን ሊገባኝ አይችልም...” እያልኩ ከራሴ ጋር ስነጋገር፥ አንደኛው ፖሊስ ከአንድ ለየት ያለች ሳጥን (የመጀመሪያ እርዳታ መስጫ ሳጥን

የመሰለች) ውስጥ መቀስ የመሳሰሉ መሳሪያዎች አወጣና “እጅህን ዘርጋ!” አለኝ በቁጣ። ወዲያውም ከግራ እጄ ላይ ቆዳዬን ቆረጠና (በላቦራቷር ለመመርመር) ወደ ሳጥኑ ካስገባ በኋላ፥ “በል ሂድ!” ብሎ ለቀቀኝ።

ጥፋቴ - ኃጢአቴ ከላይ በተነገረው ሕልም ውስጥ ጥቅልል ብሎ ተቀምጧል። ሕልም አላሚ የራሱን ሕልም በራሱ መፍታት ይገባዋል። ምክንያቱም ያንን ያለመውን ሕልም በእውን ከሠራው ሥራ ጋር ሊያመሳክር የሚችል እርሱ (ባለቤቱ) ብቻ ነውና።

እንዲህ ነው የሕልሜ ፍቺ፡- በአንድ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ውስጥ ገደቤን ሳልጠብቅ (የቁም ምልክት ሳላከብር) መለፋለፌ ትዝ ይለኛል። በንግግራችሁ “ቁም” የሚል ምልክት መኖር አለበት፤ እውነት አለን ብላችሁ ካለ ገደብ አታውሩ፤ ንግግራችሁን ቆረጥ ቆረጥ በማድረግ እያሰባችሁ ተናገሩ።

አዎ! ቁም የሚለውን ምልክት አለማክበር በሥጋ አለም ከባድ ጥፋት አይደለም፤ በትራፊክ ሕግ መሠረት መቀጫውም ቀላል ነው እንጂ፥ ሽጉጥ የሚያስመዝዝ አይደለም። ነገር ግን፥ እኛ በሥጋዊ አለም ለስላሳው ሥጋችን እንዳይጎዳብን ስንል ነገሮችን እናቃልላለን። ካለ ሥጋ ጉዳት በመንፈስ ያየናቸው እንደሆነ ግን፥ ነገሮች ምንኛ የከረሩ ሊሆኑ በቻሉ።

መቼም እንደኔ ያለውን ግትር ሰው በቀላሉ ማስረዳት ያስቸግራል። በመንፈሳዊ አለም ነገሮች የከረሩና የተጠናከሩ መሆናቸውን፤ ሌላም ሌላም ነገር እንዲገባኝ የሚያደርጉ ህልሞች እኔን እየለወጡኝ ተምታቱብኛል። እኔስ እንዳልቀጣ ምን ማድረግ እንዳለብኝ አላወቅሁትም። ከሕጻንነቴ ጀምሮ ያልገባኝ ነገር ያለ ይመስለኛል። አይቼና አውቄ ወድፊት መራመድ ነው ያቃተኝ። እንዲሁም በሌላ ቀን.....”

<u>ዮሐንስ</u>

“ቢቃ፤ ያሰብከውን እና የተናገርከውን ግለጽ፤ ድፍንፍን አታድርገው፤ እንዲህ አይደለም፥ ኑዛዜ ማለት።”

<u>ቶማስ</u>

“በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አብረን ብንጸልይ፥ አብረን ብንቀድስ፥ ብንሰግድም፥ የሁላችንም መንፈሳዊነት በአንድ አይምሮ እየተመራ የሚጓዝበት አለም ውስጥ አይደለም ያለነው። ሰው ሁሉ በአንድ አይነት መንገድ ሊገባው አይችልምና፤ ሃይማኖታችን አንድ፤ መንፈሳዊ አለማችንና ግባችን ግን አንድ እንዳይሆን የገንዘብና የመሳሰሉ ምድራዊ አስተሳሰቦች ያውኩናል።

ከበድ ከበድ ያለ ፈተና ውስጥ ስንገባ በአይምሮአችን እንጠቀም ወይንስ የመንፈስን ሥራ እንጠብቅ? ለዚህ መልስ ሳላገኝ ያሰብከውን እና የተናገርከውን ግለጽ መባሌ ከብዶኛል። በአለም ውስጥ የምናየውን አለማዊነት እና መንፈሳዊነት ሁሉ በእጃችን ይዘን በምርጫችን ወደአይምሮአችን የምንሰደው ሁሉ በሙሉ ፈቃዳዊ ነጻነት - ሚዛናዊ አስተሳሰብ - ሳይንሳዊ - ስነአመክኖአዊ - እየሆነ እንዳይመጣ የሚያደርግ፥ ከቁጥጥራችን እየሆነ ነገር አለ።

አንጎላችን በብዙ ምድራዊ ነገሮች ስለተጣበበ፥ ሲሰበክ የምንሰማውን የምንቀበለውንም ልክ ለመንፈሳዊነታችን የተዘጋጀ ባዶ (ትርፍ) ሥፍራ ሲገኝ ብቻ ይመስላል። ሁላችንም በተፈጠሮና በአኗኗር የተለያየን እንደመሆናችን መጠን፥ ኑሮአችንና ሚዛናዊ አስተሳሰባችን በመንፈሳዊነታችን ላይ ተጽንኦ ሊኖረው ይችላል። የአንድ ሰው መንፈሳዊነት የሚወሰነው በግለሰቡ እና በእግዚአብሔር (በሁለቱም) እንደመሆኑ መጠን፥ እያንዳንዳችንን የእግዚአብሔር መንፈስ በተለያየ መንገድ ነው የሚቀርበን።

የእውነት እውነትነት ለብዙ ሰዎች (ለሕብረተሰብ) የሚስማማ ሆኖ መቅረብ አለበት? እኔስ፥ የሚጸለይበት የእግዚአብሔር ቤት ከአለማዊው አላማ ተለይቶ፥ ከመንፈሳዊ አላማ ጋር አብሮ መራመድ አለበት፤ ሰማያዊ መልኩን ጠብቆ መገኘት አለበት ከሚል ሃሳብ ተነሳሁ።

መንፈሳዊ እንቅስቃሴ የተመላበት ጉዟችን ሰማያዊ መስሎ የሚታይበት እንዲሆን ለማድረግ ስንደክም፥ አንዳንድ ጥቃቅን - ስንኩል ምድራዊ አስተሳሰቦች በመካከል መከሰታቸው አይቀርም በማለት በኃላፊነት ያልተሰጠኝ ሥራ ውስጥ ገብቼ፥ የሚከተለውን እና የመሳሰሉትን እያሰብኩ ቆይቻለሁ።

እኚህ ታላቅ ምሁር (መነኩሴ) እንደ ማግኔት የሚስብ ትምህርታቸው እንዳይቀንስ ብዬ መናገሬንም አስታውሳለሁ። “ቤተ ክርስቲያን ሥሩ፤ ተሰባስባችሁ ጸልዩ፤ እኔም በመላከላችሁ እገኛለሁ...፤” ይላል እግዚአብሔር። ይህን መስማት

ለሚችል ጆሮ፥ የበለጠ እንዲሰማ የሚያደርገው፥ የሰማውን የሚያረጋግጥለት መንፈሳዊ ትምህርት በየሳምንቱ ሲመገብ ነው እንጂ በየሳምንቱ ገንዘብ አዋጡ ተብሎ ሲነገረው ስላልሆነ፥ እሳቸው በትምህርቱ ላይ እንዲያተኩሩ፥ የተቀረው ሁሉ ጊዜውን ጠብቆ እንደሚመጣ ተናገርኩ። ሌላም ብዙ የተናገርኩት ቢኖርም ከዚሁ ከመደበኛ አስተሳሰቤ አይወጣም። አለሳልሶ መናገር አለመቻሌ እኔን ጎዳኝ።"

<u>ዮሐንስ</u>

"ሁሉ ነገር ጊዜውን ጠብቆ እንደሚመጣ ግልጽ ነው፤ ግን ሰዎች፥ በተለይም መንፈሳዊ አባቶች ጥሩውን ጊዜ ቶሎ እንዲመጣ የማፋጠን ኃላፊነት አለባቸው፤ ጥበብና ብለሃትን ከምዕመናን መንፈሳዊ ቅንአት ጋር በማጣመር።

ከራስ አስተሳሰብ ወጣ ብሎ፥ የሌላውን አስተሳሰብ ተረድቶ፥ በጥሞና አገናዝቦ፥ ለሰው የሚጠቅመውን መፈለግ ብልህነት ነው።

ልክ እንደአካላውያን በምድራችን ላይ የሚመላለሱ እርኩሳን መናፍስት (ሰይጣናት - አጋንት) መኖራቸውን ባለመገንዘብህ፥ ለክፉ ነገር ተጋለጥህ። ነገር እየጠለፈ ልዩ ትርጉም የሚያሰጥ እርኩስ መንፈስ ባይኖር ኖሮ፥ ጸብና ጭቅጭቅ ይጠፋ ነበር። መንፈሳዊነት በሥጋዊ አንጎል ከማሰብ ዘልቆ ይሄዳልና፤ "ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ሥር ነውና...አንተ ግን የእግዚአብሔር ሰው ሆይ ከዚህ ሽሽ...። " ፩ኛ ጢሞ. 6፥10 የሚለውን ጥቅስ ባግባቡ ካለመጠቀም የተነሳ፥ ከስህተት ላይ እንወድቃለን። ሰው አስቦ፥ ከጊዜው ሁኔታ ጋር አብሮ ተራምዶ፥ ትክክለኛውን መንፈሳዊ አቋም መውሰድ ቀላል አለመሆኑን ከተገነዘብን ይበቃናል።

በእውነት ከኔ ባልመጣ ነገር፥ አንድ የእግዚአብሔር ሰው (መነኩሴ) ተቀይመውብኛል ብለህ አዝነሃል። የመጥፎ መንፈስን መኖር ያልተገነዘቡ ሰዎች እራሳቸውን ከፉኛ ይጎዳሉ። አንተም ቶሎ ገብቶህ እንደ ብልጦች መንገድህን ለመቀየስ ባለመቻልህ ነው የተጎዳኸው። ካንተ ውስጣዊ ስሜት ያልፈለቀውን ካፍህ ነጥቆ፥ ካንተ ያልመጣውን ሁሉ በማጋነን ነገር ያቀባበለብህ መጥፎ መንፈስ እንደሆነ በደንብ እንዲገባህ ሆኗል።

የመንፈስ አካሄዱ አይታወቅምና፥ ሰውን አታስቀይሙ። በተለይም በመንፈሳቸው የሚኖሩ አባቶችን ማስቀየም ጉዳት ላይ ይጥላል። ምክንያቱም እነርሱ በአለማዊ መንገድ ቁጭት አይወጡም፤ አይማቱም፤ አይሳደቡም። ልባቸው ቅይም ሲል

ግን፥ እነርሱ ሳያውቁትና ሳያስቡት መንፈሳቸው ያስቀየማቸውን ሰው ሊቀጣው ይችላል።

ምንጊዜም በሰው ላይ መጠነኛ ጉዳት ቢፈጸም፥ የግለሰቡ ተፈጥሮአዊ - ስነአይምሮአዊ ሁኔታ (ወይም እንደ ሰዉ ጠባይ) ጉዳቱን ያቀለዋል ወይንም ያገነዋል። አንድ ሰው ካቅሙ በላይ የሆነ እጅግ ከባድ ችግር አንድ ጊዜ ቢደርስበት፥ በሌላ ጊዜ ጥቃቅን ችግሮች ባጋጠሙት ቁጥር፥ ያ የበፊቱ ከባድ ችግር ተመልሶ የሚመጣበት ይመስለውና የሚያጋጥመው ችግር ሁሉ ከመጠን በላይ ይጋነንበታል። ሆኖም፥ ምን ጊዜም የነበረ፥ ዛሬና ለወደፊት፥ ለዘለአለምም የሚኖር እግዚአብሔርን - “አባቴ ሆይ እባክህ አትለየኝ፤ ከመከራ ሥጋ - ከመከራ ነፍስ ሰውረኝ...” ብሎ ዘወትር በመጸለይ ችግሮች ሁሉ ይቃለላሉ። አለበለዛ በሕልምም ሆነ በእውን ምድራዊ ክፋቶች እየተጋነኑ ሰውን ያስጨንቃሉ።

የሰዎች ችግርና መከራን የመቀበል ችሎታ እጅግ ከፍተኛ እንደሆነ ከሐዋርያት ተምረናል። መጪው ዘመን ለሕዝቦች ሁሉ የከፋ መሆኑ አይቀርም። ሰው የራሱን ማንነት ከአካባቢው ጋር ለማገናዘብ ባለመቻሉ ብቻ ከፉኛ እንደሚጎዳ ይህን የጠቀስከውን ኢምንት የሆነ ጉዳይ እንደ ምሳሌ መውሰድ ይቻላል።

ገደቤን ሳልጠብቅ (የቁም ምልክት ሳላከብር) ከሰዎች ጋር መለፋለፌ (ነገር ማብዛቴ ማለትህ ነው) ትዝ ይለኛል አልክ። በንግግርህ ምንም ኃጢአት አልሠራህም። አንተ የሥርራኸው ሥራ ጥፋት ማጥፋት ይባላል እንጂ ኃጢአት አይባልም። ነገር ግን ትልቁ ስህተት፥ ይህ ጥፋትህ ኃጢአትን ቀስቃሽ መሆኑን አለመገንዘብህ ነው።

ኃጢአተኛ በመሆንህና ከኃጢአት የማትላቀቅ ስለሆንክ አጠፋህ፤ ይህም ጥፋትህ ኃጢአቶችህን ሁሉ ቀሰቀሰብህ። በእርጋታ ወደ ራስህ ተመልሰህ እራስህን ስትመረምርና ሲገባህ፥ እልኸኛነትህ አፍኖ ያዘህ። በንዴትና በቁጣ፥ ትንሿ ጥፋትህ ወደ ትልቅ ኃጢአት ተለወጠችብህና ከድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ገባህ። ኃጢአት ካለ ሥራ ዝም ብሎ ቁጭ አይልም። “ተሳስቻለሁ - አጥፍቻለሁ” በማለት፥ ገና ኃጢአት ያልሆነውን ጥፋት በጊዜው ካልደመሰሱት፥ ያድጋል፤ አድጎም ሌላ ኃጢአትን ይወልዳል፤ ኃጢአትም ዝም ካሉት ይገድላል።

ሰው ተወልዶ፥ አድጎ፥ ጎልምሶና አርጅቶ እስኪሞት ድረስ መንፈሳዊ እራሱን ሲያሻሽል፥ በየቀኑ ምድራዊነቱን እየገደለ፥ በሰማይ በየቀኑ ይፈጠራል።”

<u>ቶማስ</u>

"አልገባኝም። ስላቋረጥኩህ ይቅርታ አድርግልኝና፥ እኔ እንደማስበው - ማንኛውም ፍጡር በምድር ላይ ሲፈጠር ባንዴ ነው፤ ወይንም ህልውናው በአካላዊ ሕያውነት እስኪከሰት ድረስ አካላዊ ክስተቶችን ሁሉ እናያቸዋለን (ለምሳሌ ሕጻን እስኪወለድ ድረስ ያለው አካላዊ ክስተት)። ታዲያ፥ ሰው ምድራዊ ማንነቱን በየቀኑ ካልገደለ፥ በሰማይ አይፈጠርም ስትል ምን ማለትህ ነው?"

<u>ዮሐንስ</u>

"ያልኩትን አካብደህ ካልተመለከትከው፥ የምድራዊ ክንውኖች ውጤት በአይን ካልታየ፥ ውጤቱ የሚታይበት ሌላ ሥፍራ ይኖራል ማለቴ ነው። ቀድሞም ፍጥረታችን ከሰማይ ነበር፤ ያንኑ ሰማያዊ ፍጥረታችንን ይዘን ነው በምድር የምንኖረው። ግን ኃጢአተኛው ሰማያዊ ፍጥረቱን በየቀኑ እያኮሰሰ (እየገደለ) ምድራዊ ማንነቱን ያጎለምሳል። ጻድቁ ግን በተቃራኒው፥ ምድራዊ ፍጥረቱን በየቀኑ እያኮሰሰ (እየገደለ) ሰማያዊ ማንነቱን ያጎለምሳል። አንድ ቀን ያ ኃጥእ ይሞታል፤ ጻድቁም ይሞታል። ሁለቱም ያጎለመሱትን አዲስ ሰው ያገኙታል ማለቴ ነው።

አንድ ሰው በምድር ላይ ጻድቅ የሚያሰኘውን ቅዱስ ሥራ ሁሉ በሚሠራበት ወቅት ምድራዊ ሽልማቶችን ላያገኝ ይችላል። ነገር ግን የቅዱስ ሥራው ውጤት ሲሞት ከሰማይ ይጠብቀዋል እንጂ፥ በየቀኑ በምድር ላይ የሚፈጽማቸው መልካም ተግባሮች ሁሉ ውጤት አልባ አይሆኑም። ለምሳሌ፥ ሐዋርያት እራሳቸውን (ምድራዊ ማንነታቸውን) በየቀኑ ሲገደሉ፥ ያ በምድር ያደረጉት ተጋድሎ፥ ምንም እንኳን ትርፉ በኛ በክርስቲያኖች ላይ ቢገለጽም፥ እነርሱም በሰማያዊ ክብር በሰማይ ተፈጥረውበታል። "እኔ በሕይወት ብኖርም ክርስቶስን ለማገልገል ነው፤ ብሞትም ዋጋ አለኝ፡" ፊሊ. 1፡ 21

አዎ! መንገድህን አቅንተህ ጥሩ ሰው ለመሆን ካልቻልክ፥ ከእግዚአብሔር ትለያለህ፤ ለማለት ነው የፈለግሁት። ሰው ከእግዚአብሔር ተለይቶ የሚሄድበትን ሥፍራ እዛው ሲደርስ ነው ሊያውቅ የሚችለው፣ ግን ያንን ሥፍራ ሰዎች ገኃነም ይሉታል። የእግዚአብሔር መንፈስ በብዛት እንደሚያስፈልግህ ከተገነዘብክ፥ በአሳዛኝ ሁኔታ ውስጥ የወደቅኸው ለምን እንደሆነ አስበው - እራስን በመንፈሳዊ መንገድ ማሻሻል ለሰዎች ሁሉ የተሰጠ በረከት ስለሆነ፥ እስከ ዛሬ፥ ከልጅነትህ ጀምሮ የሠራሃቸውን ኃጢአቶች ተመልከታቸው።

መጠነኛ ጥፋት ብታጠፋ አካባቢህ (ሰው፥ እንስሳ፥ ሳር፥ ቅጠል፥ የተደበቀ መንፈስ፥ የተገለጸ መንፈስ..ወዘተ. እንዴት ብዬ ልግለጽልህ!) ሁሉም በቀላሉ ይረሳዋል። ነገር ግን በእብሪተኛነት፥ በትምክህተኛነት፥ በንዴትና በእልህ ምክንያት እርቅን የማትሻ ብትሆን፥ ይህን ደካማ ጎንህን ይዞ ሰይጣን ይጠቀምብሃል፤ ይህቺን ትንሿን ጥፋት ወደ ትልቅ ኃጢአት ለመለወጥ ሲል ያንተን ንዴት የሚቆሰቁሱ ሃሳቦችን በጭንቅላትህ ይቀርጽብሃል።

የሠራሃቸው ኃጢአቶች ሁሉ እንዲደመሰሱልህ፥ ተጸጸት፥ ተናዘዝ (ንስሐ ግባ)፥ ቀጥሎም ይቅርታ አድርግና እርሳ። ደካማ ጎንህን እወቅ - የሠራሃቸውን ጥፋቶችም ሆኑ ኃጢአቶች ታረምባቸው እንጂ ችላ ብለህ አትለፋቸው። በጧት ተነስተህ ፊትህን ከምትታጠብበት ጊዜ ጀምሮ ላንተ አስተሳሰብ የማይስማሙ ብዙ ሃሳቦች ያጋጥሙሃል። በዚህች ምድር ውስጥ ብዙ አለሞች አሉ፤ ሰውም ሕይወቱን እየደረበ ይኖራል። ከእንግዲህ ተስፋዬ ምንድነው ብለህ ጠይቅ እንጂ፥ በተለመደው የእልኸኝነት ጠባይህ ለምን - ለምን እያልክ ስትነድና ስትቃጠል አትኑር።

አንተኑ ሁኜ ስናገር፥ ኃጢአተኛ ባስመስልህ፥  ከዛው ፍቀህ ልታጠፋው ከማትችለው ጠባይህ አንጻር ጉልህ የሆነውን ለይቶ ለማውጣት ነው እንጂ፥ የኃጢአት ሚዛኑን አውቃለሁ በማለት አይደለም፤ ፈራጅ እግዚአብሔር ነውና።

አንድ ምዕመን በጠባዩ ይታረም ዘንድ የሚሰነዘርበትን ትችት ሁሉ በደስታ መቀበል ይኖርበታል። ይህን ካላደረገ፥ አፈንጋጭ፥ ትእቢተኛ፥ እልኸኛ፥ አመጸኛ ይባላል። እስቲ እራስህን ተመልከተው፤ አንተ በመንፈስ ለመታረም ድፍረት ያጣህ፥ ለሥጋህ በመሳሳት፥ በፍርኃት የምትደናበር ደካማ ሆንክና እራስክን ከቤተ ክርስቲያን አገለልክ። በዚህም ምክንያት፥ ከምድርም ከሰማይም ሳትሆን መቅረትህ ጥፋት ሆነብህ። ከጥፋትህ ሳትታረም ብዙ ጊዜ በመቆየትህ፥ ይኸው ጥፋትህ ኃጢአት ሆነብህ።

ካሁን ቀደም የደረሰብህ ችግር አንተን ልዩ ደካማ ፍጡር አድርጎሃል። ይህ ለምን ተፈጸመ ስንል፥ ለምድራውያን በቀላሉ የሚገባውን እንናገራለን። ሰው በአይምሮው የሚያስጨንቁ ጉዳዮችን ይዞ ለብዙ ጊዜ ከቆየ ይታመማል፤ ይህም ህመም ሰውነትን እና አይምሮን የሚወር መጥፎ ህመም ነው። የሚጨነቅ ሰው በራሱ የተስፋ ጭላንጭል ለማግኘትም ካልጣረ - ካላወራና ሃሳቡን ካላካፈለ በስተቀር፥ በራሱ የታመቀ ሃሳብ ምክንያት የአይምሮ ህመምተኛም ሊሆን ይችላል። በአንድ አቅጣጫ ብቻ እየተመለከትን ከሰማይ የሚመጣውን ውሳኔ - ለምን እና እንዴት እንደሆን ስለማይገባን - በቀላሉ መቀበል ያስቸግረናል።

እኛ ምድራዊ ሰማያዊ ሆነን ስንኖር፥ የመኖራችን ፍልስፍና በምድራዊነት ብቻ አይካተትም። ከሚጠፋውና ከሚያልፈው ሕይወት መጪው የበላይነት ያለው ስለሆነ፥ ከላይ የሚመጣውን ፍርድ መቀበል ግዴታ ይሆናል። ድሃ ሰው የድህነቱን ያህል ሲከፋው፥ ሃብታምም የሃብቱን ያህል ደስ ሲለው አልተመለከትንም። የሰው ልጅ በጠቅላላ፥ እዛው ሰማይ (ገነት) ተመልሶ እስኪኖር ድረስ የምድር ነገር እየጣፈጠው፥ እየጎመዘዘውና እየመረረው መሆን አለበት።

አንተ እራስክን ስታሳንስ፥ እኔም ስላንተ ክፋት በመናገር ከሰው ሁሉ በታች ሳደርግህ፥ ከመጥፋት እንድትተርፍ ያህል ሆነህ በመቅረትህ ብቻ ፍዝዝ ያለ ደስታ ይሰማሃል። እኔ ግን ባለማወቅ ላይ የተመሠረተ ትግል እንዳይሆን እጥራለሁና፤ አሁንም አድምጠኝ። እስከ ዛሬ በሕይወትህ ውስጥ ለምድራዊ ኑሮና ለገንዘብ የተስገበገብክበት ወቅት ነበር። ይህ ትክክል አለመሆኑ የገባህ አሁን ነው። ገና ብዙ ማወቅ የሚገባህ ጉዳይ ስላለ ታገስ። ከመሬት ለመራቅና ለሰማይ ለመቅረብ የምታደርገውን ጥረት አታቋርጥ። እውነተኛ ሰው ነህ፤ ግን ያንተ እውነተኛነት በእግዚአብሔር ፊት እንደጨለማ የሚቆጠር መሆኑ በደንብ እንዲገባህ ተቀጣህ። እግዚአብሔር ሰውን አቅሙ ከሚፈቅድለት በላይ አይፈትነውም።

"…..ትታገሱም ዘንድ እንድትችሉ ከፈተናው ጋር መውጫውን ደግሞ ያደርግላችኋል። " 1ኛ ቆሮ. 10፡13

እግዚአብሔር በሰዎችና በርሱ መካከል መላእክትን ፈጥሯቸዋልና፤ ከሰዎች ጋር መግባቢያ የሚሆኑ ቃላት አጥተህ ዝም ብለህ አትቀመጥ። መላእክትም ከጎንህ ናቸው። "……መላእክቱን መንፈስ የሚያደርግ፤ አገልጋዩቹንም የእሳት ነበልባል። " መዝ.4፡4

የእግዚአብሔርን ቸርነት እየለመንክ ኑር፤ ሁሉም (በዚህም በዛም፥ በማንኛውም አለም ቢሆን) የእግዚአብሔር ቸርነት ነውና ያለው። ኃጢአተኛ ለጻድቅ ሰው ብሎ እራሱን አይጎዳም፤ ጻድቅ ሰው ግን ለኃጢአተኛ ብሎ ራሱን ይጎዳል። ኃያል አምላክ ካለ እግዚአብሔር ማንም የለምና፤ እጅህን ይዞ ወደ ገደል የሚከትህ የውጪ ኃይል ቢኖር፥ ከገደል የሚያወጣህ እርሱ እግዚአብሔር ነው። ጨለማን ወደ ብርሃን የሚለውጥ አምላክ፥ ምን ይሳነዋል?

ጸልይ፤ ስትጸልይም የጸሎትህን መነሻና መድረሻ እወቀው (በተመስጦ - በጥልቀቱ እያሰብክ)፥ እንጂ፥ እንዲሁ አታነብንብ። ስትጸልይም እግዚአብሔር

ጸሎትህን ሰምቶ እንደሚያደርግልህ እያመንክ ይሁን። ጸሎትህን ሳትጨርስ እንቅልፍ አይውሰድህ። ጸሎትን ጀምሮ ካለመጨረስ ጭራሹን አለመጀመር ይሻላል።

በምድር ስለሚሠራው ክፋት ሁሉ ብታስብ ጭንቀትህ ይጋነናል። ቅር የሚልህን ሁሉ ለፈጣሪ አምላክህ ስትነግረው በፍጹም ቅንነት ከሆነ ይሰማሃል፤ ሰምቶህም ያናግርሃል። ሰው ወሬ ሲያወራልህ ማቋረጥ ነውር እንደሆነ ሁሉ፥ አንተ ስትጸልህ እግዚአብሔርም ሲሰማህና ሲያናግርህ  የምታውቀው ጸሎትህን በሚገባ ስትጨርስ ነው። አንተ የሰማዩን ማወቅ አይቻልህምና፤ ዑራኤል ለዕዝራ እንዳስረዳው ለአንተም የሚያስረዳህን መልአክ ይልክልሃል። የሰው ልጅ በእግዚአብሔር ፍቅር ተጠምዶ፥ ለመንፈስ ቅዱስ የቀረበ በመሆን፥ ከራሱም መንፈስ ጋር በመዋሐድ ደግ ሥራ ብቻ እየሠራ እንዲኖር የሚያደርገውን ሰማያዊ ተስፋ ከዕዝራ ሱቱኤል እንማር።

እስራኤሎችን የከበቧቸው ሕዝቦች ሁሉ መከራና ጭንቅ ሲያመጡባቸው እንደነበር ሁሉ፥ በናቡከደናጾር ዘመን ብዙ እስራኤላውያን አለቁ፤ የተረፉትም ተሰደዱ። በስደት ላይ ሆኖ የባቢሎን ሰዎች ሲደሰቱ ያስተዋለ፤ የኢየሩሳሌምንም መጥፋት የተመለከተ፥ ዕዝራ ሱቱኤል የተባለ ነቢይ እጅግ ተጨነቀ፤ “ለምን እንዴትስ ይህ ይሆናል? የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን፥ ኢየሩሳሌምን ገንብተን፥ እዚህ ከደረስን በኋላ፥ ይኼ ሁሉ መከራ የሚደራረብብን ምንድነው ምክንያቱ?” በማለት እጅግ አዘነ።

በኢየሩሳሌም አይሁዶች በቅኝ አገዛዝ ሲሰቃዩ፥ በአንጻሩ ደግሞ በባቢሎን ኃጢአት ሲሠራ፥ ኃጢአተኞችም እየተደሰቱ ሲኖሩ ዕዝራ ተመለከተ። የእብራይስጦች ሃዘንተኛ ሆኖ መቅረት ሊገባው አልቻለምና አእምሮው ታወከ።

“ጽዮን የምትባል አገርን እጅ ያደርጓት (ይወርሱ) ዘንድ፥ በባቢሎን የሚኖሩ ሰዎች፥ እውነት ሥራን በመሥራት በእውኑ ይበልጡናልን? ” ዕዝራ ሱቱኤል 1፡27 በማለት ዕዝራ ሲጨነቅ ሳለ፥ ዑራኤል የተባለ መልአክ ቀርቦ አነጋገረው።

“እሳትን መመዘን፥ ነፋስን መስፈር ይቻልሃል? ትላንት ያለፈችውን ቀን እንደዛሬ አድርገህ ልታሳየኝ ትችላለህ? በጥልቅ ባህር ውስጥ ስላለው፥ በሰማይና በሲዖልም ስላለው ጎዳና ምን የምታውቀው አለ?”  ብሎ ዑራኤል ዕዝራን ጠየቀው።

ዕዝራም ለተጠየቀው ጥያቄ መልስ የማያገኝለት መሆኑን ነገረው። መልአኩም አለው፡- “የልዑል የእግዚአብሔር ፍርዱ ባለመመርመር ተወስኗልና፤ የእግዚአብሔር የፍርዱን ምሥጢር ማወቅ አይቻልህም።....” ዕዝራ ሱቱኤል 2፡11

ዕዝራ ግን፥ በቀድሞ ሃሳቡ በመጽናት፡- እኔኮ የአምላክን ፍርድ ልመርምር አካልኩም፤ ግን ሁል ጊዜ በኛ በእስራኤላውያን ላይ ስለሚመጣው መከራ ምክንያት

ግራ ተጋብቼ ተጨነቅሁ እንጂ አለው። መልአኩም፡- “የማትሞት ብትሆን ኖሮ ሁሉንም ታየው ነበር። ከሞትክ በኋላ ስለሚከተለው እንዴት ታውቃለህ?” በማለት፤ የሰዎች ጭንቀት ጊዜያዊ መሆኑን አስረዳው።

ዕዝራ አሁንም ጥያቄው አልተመለሰለትም። ስለዚህም እንደገና ሱባኤ (የሰባት ቀን ጾምና ጸሎት) ቀጠለ። አሁንም ጸለየ፡- “ከአህዛብም ሁሉ ህግን ያስተማርከው አንድ እስራኤልን መረጥክ፤ ለአህዛብም አሳልፈህ ሰጠኸው። ወገኖችህንስ ከጠላሃቸው አንተው ብትጨርሳቸው ይሻል ነበር” እያለ፥ ፈጣሪውን አማረረ።

ሱባኤውንም እንደጨረሰ፥ ዑራኤል ተመልሶ መጣና፥ ስለ አለም መጨረሻና ስለ አዲስ አለም (መንግሥተ ሰማያት) ከበፊቱ የበለጠ በማብራራት ለዕዝራ ነገረው። በተጨማሪ ለማወቅ ከፈለገ ለሦስተኛ ጊዜ ሱባኤ እንዲገባ መከረው። ዕዝራም የበለጠ የማወቅ ጉጉት ገፋፍቶት፥ ሦተስተኛ ሱባኤን አገባደደ። ከዚህም በኋላ፥ ዑራኤል ተመልሶ መጣና፤ “መንግሥተ ሰማያት ተዘጋጅቶላችኋል፤ ለምን ስለዚህ አለም መከራ ብቻ ታስባለህ” አለው።

“አሁንስ ፈራሽ በስባሽ የምትሆን፥ አንተ ለምን ትታወካለህ፥ ሟች የምትሆን አንተ፥ ለምን እንደ ተልባ ትፈናጠራለህ። በዚህ አለም ያለውን ነው እንጂ፥ የሚመጣውን አለም በልቦናህ ለምን አታስብም።” ዕዝራ ሱቱኤል 5፡ 15-16 በማለት የመጨረሻውን ምክር መከረው።

ይህን የዕዝራ ንግግር መልሰህና መላልሰህ አስበው። የኛ ሕይወት ከምድራዊነታችን ባሻገር ዘልቆ ይሄዳልና፤ ምድራዊ ተንኮሎችንና መጥፎ ሥራዎችን ሁሉ እንደሌሉ ቆጥረን በሰማያዊ ተስፋ እንዳንደሰት የሚያደርገንን “ምድራዊ ሚዛናዊ” አስተሳሰባችን አልፈን - ከራሳችን ወጣ እያልን እንሂድ። በምድራዊነታችንም ውስጥ ሆነን፥ የረቀቀውን መንፈሳዊ ሕይወታችንንም ልንኖርበት እንችላለን ማለቴ ነው።

ከዕዝራ የምናገኘው ትምህርት - ከዚህ “ምድራዊ ሚዛናዊ” አስተሳሰባችን ወጣ ብለን፥ ምንም ሆነ ምንም (ምድራዊ ሃብት ቢጠፋ፥ ሰው ቢታመም ወይንም ቢሞት፥ ማንኛውም አይነት ጥቃት ቢደርስ)፥ ከዚህ ሁሉ በስተጀርባ ሰማያዊውን ሕይወት በተስፋ ብንጠባበቅ የሚሻል መሆኑን ነው። በዚህ አለም ያለውን ወደ ኋላ እየተውን፥ የሚመጣውን አለም “በልቦናችን” ብናሳድር ምድራዊ ችግሮቻችን ይቃለላሉ። አንድ ሰው ባልታወቀ መንገድ ሕይወቱ ቢበላሽ፥ ጉስቁል ቢል፥ እጅግ ቢደኸይ፥ ልብሱም ራካ (ጨርቃም) ቢመስል፥ ይህን ሰው በሰማያዊ ሚዛን

ስንመለከተው ከማንም የማያንስ ነው፤ በምድራዊ ሚዛናዊ አስተሳሰብ ግን እንደ ዝቅተኛ ስለሚቆጠር፥ ከሃብታሞቹ መንደር የሚያስጠጋው የለም።

ድሃን ሰው በድህነቱ የሚጠላ፥ የሚጸየፍ፥ የሚንቅና የሚያንቋሽሽ - እርሱ ሰማያዊ ሚዛን በውስጡ የሌለው ነው። በሰዎች መካከል፥ በሃብት፥ በእውቀት…ወዘተ. ምንም አይነት መበላለጥ የማያደርግ - እርሱ ሰማያዊ ሚዛን በውስጡ ያለው ጻድቅ ነው። በድሆች መካከል ገብቶ የተቸገሩትን ከልብ ለመርዳት ሰዎችን በጉስቁልናቸው ሳይሆን በሰውእነታቸው (ሰብእነታቸው) መውደድ ያስፈልጋል። አንዲት ጎስቋላ ድሃ ሴት ከበር ቆማ የሚበላ ብትለምንህ፥ በድሃይቱ ሴት ውስጥ በአይነ ሕሊናህ እመቤታችንን ማርያምን ተርባ ለማየት ብትችልና ለዛች ሴት ብትመጸውት፤ አንተ ከምድራዊ ሕይወት በስተጀርባ በእውነት አዲስና ዘለአለማዊ ሕይወት የሚታይህ ሰው ነህ።

እንግዲህ የኔን ምክር ስማ፤ የሰማይን የበላይነት አትጠራጠር፤ ምድራዊ አስተሳሰቦችህን በሰማያዊነት ለውጣቸው። ከላይ የሚመጣውን ፍርድ ሁሉ አሜን ብለህ ተቀበል። ሰው ሆነህ ስትፈጠር ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ለመኖር መሆኑን አስብ። በምድር ከሰዎች ጋር መኖር ቢያቅትህ በሰማይም እንደዛው ሊሆንብህ ይችላልና፤ ከዚሁ ሳለህ የሚጠብቅህን ግዴታ ተወጣ።

ከመሞቴ በፊት ለሰው ልጅ ምን ላቆይለት ብለህ አስብ። በምትሠራው ጥሩ ሥራ መጠን ሽልማትን የምትጠብቅ ከሆንክ፥ ያን የጠበቅኸውን ሽልማት በምታጣበት ወቅት ቅር ትሰኛለህ። ነገር ግን ጥሩ መሥራትህን ዋጋ የማትጠብቅበት ብትሆን፥ በሥራህ ትደሰታለህ (ትረካለህ)።

አንተ ምግብ እየበላህና ኃጢአት እየሠራህ በምድር ላይ ስትኖር፥ ላንተ ወደ ሰማያዊ ሕይወት የሚያመራ ጎዳና በሃይማኖትህ ውስጥ ተሰጥቶሃል፤ ክርስቶስ አስተምሮሃል (አሳውቆሃል)፤ መንፈስ ቅዱስ ያጽናናሃል፤ ማርያም ታማልድሃለች፤ እንዲሁም መላእክት፥ ጻድቃን እና በምድር የሞቱ ደጋግ ወዳጆችህ ሁሉ በመንፈስ ዙሪያህን ከበው ይጠብቁሃል። እምነትህን የራስህ ታደርግ ዘንድ ከነኚህ ከተጠቀሱት ውስጥ ለኔ ይበዛል እንጂ ያንሰኛል የምትለው ምን ሊኖር ይችላል?

ፍቅር ሰማያዊ ነው፤ ከሁሉ በላይ የእግዚአብሔርን ፍቅር ካስበለጥህ ምድራዊ ምሬቶች ሁሉ ካንተ ይጠፋሉ። በመሬት የምትኖረውን እንደ ወጥ ቅምሻ ቁጠረው፤ ከሰማይ ቤት ገና ብዙ ደስ የሚል ሕይወት ይጠብቅሃል። በሁለት የተለያዩ ሃሳቦች ስትጠመድ፥ የትኛው ነው ለክርስቶሳዊነት የሚቀርብ ብለህ አቋምህን ካለማወላወል

አስተካክል፤ አለበለዚያ ከክርስቶሳዊነት ርቀህ ከሄድክ ወደ ጥፋት ትገባለህ። ግን ርቀህ መሄድህ ካልታወቀህ፥ ርቀህ እንድትሄድበትም ክርስቶስ ካልፈለገ፥ ከስህተትህ እንድትማር የሚያበቃ ቅጣት ይሰጥሃልና፤ ሁሉንም በትእግስት ተቀበል።

እግዚአብሔር ይሰማል፤ አንተ የማትገነዘበው አይነት መስማት ነው። እግዚአብሔር ለሰዎች ብዙ ደግ ነገር ይሠራል። ሰዎች ግን በምድር የተፈጸመውን ደስ የማይል ነገር ሁሉ ብቻ እያሰቡ ያማርሩታል፤ ሕይወታቸውንም በገዛ ራሳቸው በሃዘን የተሞላ ያደርጉታል። የሰው ተስፋው ከዚህ ከሚታየው አለም አልፎ ወደማይታየው የሚሸጋገር ባለ ብዙ ዘርፍ ነው። ይህ ዘርፍ እጅግ ያምራል። ስለዚህ በፍጹም ተስፋ አትቁረጥ፤ ይልቅስ ቶሎ ቶሎ እየተማርክ ከፈተናና ከሃዘን ለመራቅ ሞክር፤ ከተማርክ ቅጣትና ሃዘን አይጸናብህም።

“ልጄ ሆይ የጌታን ቅጣት አታቃል፥ በሚገስጽህም ጊዜ አትድከም፤ ጌታ የሚወደውን ይቀጣዋልና፥ የሚቀበለውንም ልጅ ያደርገዋል።” ወደ ዕብ. 12፡6

ስለ ሰማያዊ ተስፋ እያሰብክ እንድትኖር፥ በምድር የመከፋት ምክንያታዊነቱን መርምር እንጂ፥ ለመከፋት እጅህን አትስጥ። እውነትን አቆያት፥ ታቀፋት፥ አትልቀቃት፥ የራስህ አድርጋት። ከዚህ ሁሉ የምድር ውካታ ባሻገር፥ አንተ በመንፈሳዊነትህ ትጸና ዘንድ በምድር ስትኖር፥ ማድረግ የሚያስፈልግህን ሁሉ አትዘንጋ። ትጥቁን እንደሚያሳምር ወታደር ሁን፤ ማረሻውን ዘንግቶ ወደ እርሻ እንደሚሄድ ገበሬ አትሁን። “እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ! ብትቀጣኝም ያንተው አድረገኝ እንጂ ችላ አትበለኝ..” ብለህ ጸልይ።

ሰውን በእምነቱም ሆነ በሥራው አትራቀው፤ አትጸየፈው፤ አትጥላው። አንተ የምትጸድቅ ሌላው የሚኮነን መስሎ አይታይህ፤ ይህን አንተ ልታውቅ አትችልምና፤ ያንተን አመለካከት እና ያንተን እምነት ከሌሎች በላይ አድርገህ አትገምት። አንተ ጽድቅ ሥራ የምትለው፥ የምትጾመውና የምትጸልየው ሁሉ ተደምሮ ከጎንህ ላለው ሰው ከምታደርገው በጎ ሥራ ላይበልጥ ይችላል። በምድራዊም ሆነ በመንፈሳዊ ሕይወትህ ውስጥ፥ ምንጊዜም ሌላውን በሥጋም ሆነ በመንፈስ የሚጎዳ ሥራ አትሥራ።

የሌላውን መጎዳት እንደራስህ መጎዳት ቁጠረው፤ ከራስህ ርቀህ መሄድ እንደማትችል ሁሉ ከተጎዳው ወገንህም ርቀህ አትሂድ። እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘዋል ብለህ የምትጀምረው ሥራ ሁሉ ሌላውን ሰው የሚጎዳ መስሎ ሲታይህ፥ በቅድሚያ ለዚያ ሰው አስብለት፥ ቀጥሎ ለእግዚአብሔር አስብ። ምንጊዜም ከጎንህ ካለው ሰው ርቀህ ለክርስቶስ ልትቀርብ እንደማትችል እወቅ። ሰዎችን በመንፈስ የሚያቀራርብ

ተግባር ውስጥ ተሳታፊ በምትሆንበት ወቅት፥ አላማህ ከሰው ሁሉ ጋር በክርስቶስ አንድነትን ለመመሥረት ይሁን። ደግ ሃብታም ሰው ሲቸር ጥሩ ሰው ይባላል፤ የድሃን ሰው ደግነት ግን የሚያውቅለት የለም። ሲለምኑት የማይሰጥ ሰው ለማኝ ይሆናል፤ ሳይለምኑት የሚሰጥ ደግ ሃብታም ነው። ሰጪም ነሺም እግዚአብሔር ነውና፥ እኛ ምንጊዜም ደግ እንሁን። ማንም ሰው ስላንተ ችሮታ፥ ማንኛውንም ነገር ሲጠይቅ፥ የምትችለውን ሁሉ አድርግለት እንጂ ችላ አትበለው። አንተ በእግዚአብሔር ችሮታ የምትኖር ሰው ሆነህ ሳለ፥ በሰው ላይ ንፉግ በምትሆንበት ጊዜ እግዚአብሔር ከመቅጽበት ሊያጠፋህና በምድር ላይ የሰበሰብከውን ሁሉ ሊያጠፋብህ እንደሚችል ተገንዘብ።

*“ነገር ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ፤ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል።” ማቴ. 6፡33*

የሰውን ልባዊነቱን ለማጥፋት የሚታገል ምድራዊ ኃይል (ክፉ መንፈስ) የሚፈራው ባንተው መንፈሳዊ ብርታትና የእምነትህ ጽናት መሆኑን አትርሳ። የሰው እንባው ወደ ሰማይ የሚወጣው በማልቀሱ ብዛት አይደለም - በጸጸት እራስህን ለማሻሻል (ለመታረም) እና ወደ ተሻለ ሕይወት ለመሸጋገር ያልሆነ ልቅሶ ከንቱ ነው - እራስን መጉዳት ብቻ ነው የሚሆነው።

“እስቲ በዚህ አለም ላይ ጤነኛ የሆኑ ሰዎች እነማን ናቸው?” ብለህ ጠይቅ። አብዛኛዎቹ በሽተኞች ናቸው ብለህ ብታስብ፥ አንተም እራስክን የምታዛምድበት ሰው አታጣም። ግን እንዳትሳሳት፤ በጤነኛውና በበሽተኛው መካከል ወሰን የሚያበጅ ማነውና። ሁሉን ነገር እኛ እንደስሜታችን እየተረጎምን ነገር ከማክረርና በከንቱ ከማማረር እንቆጠብ።

አንተ እና እኔ በመንፈስና በሥጋ መካከል የምንገኝ የሰው ቀውስ - ምድራዊ ሰማያዊ ዲቃላ ሆነን ስንኖር፥ አንተ እኔን ብትመስል፥ እኔም አንተን ብመስል፥ በበኩሌ የሚሰማኝ እኔንም እንደሚያመለክት ሆኖ እኔም እንዳንተ እናዘዛለሁ።

እኔ ከኔ የተገነጠልህ - ለብቻህ ምድራዊ ሰው መስለህ፥

በስሜቶችህ ተጨናንቀህ፥ ሥጋዊነትክን አጉልተህ በመኖርህ፥

ከውድቀት በስተቀር ምንም ባይበጅህ፥

እኔም ካንተ ተገንጥዬ - ለብቻዬ ሰማያዊ ሰው ብመስልም፥

ሞት እስኪመጣ ድረስ - ያንተ የኔ ነፍስ ማለት አንችልም።

ከእንግዲህስ በቃ የኔ ዳኝነት፥
ሁለታችንም በአንድ ነፍስ ስለምንካተት፥
አብረን እንጓዝ በአንድነት፥ በጸጾትና በጸሎት።”

# ምዕራፍ ስድስት

## አንድነት - የሥጋና የመንፈስ ውህደት

እኔ ቶማስ ልዩ በሆነው ሃሳቤ ዮሐንስ ብባል፥ ወይንም እኔ ዮሐንስ ልዩ በሆነው ሃሳቤ ቶማስ ብባል፥ በዚያም በዚህም ብገላበጥ ምንጊዜም እኔው መሆኔ ገብቶኛልና፤ በሁለት ተከፍሎ መለፍለፍ አክትሟል። ብቻዬን ስሆን ጥላ ቢስ (ቀልበ ቢስ) ሆኘ ወዳላሰብኩት ሥፍራ እንዳልሄድ ልጠንቀቅ። የማንነቴ ግንዛቤ - ምድራዊ ሰማያዊ ፍጥረቴ። ይልቅስ ብቻዬን ላለመሆን የራሴን መንፈስ አልራቅ፤ ወይንም ከደጋግ ሰዎች (ከዘመዶቼም) ልጠጋ፤ የዛን ጊዜ የነርሱ መልካም መንፈስ ይከብበኛል። ለማህበራዊ ግንኙነቶች፥ ለወሬ፥ ለሳቅና ጨዋታ ጊዜ ላብጅለት። ሃሳቤ ምን ጊዜም ከሌላው ጋር እንዳይጋጭ መንገድ ልፈልግለት። ምንጊዜም እራሴን ልጠብቅ፤ ካለ ሥራም አልቀመጥ።

ሃዘን በማብዛትና ተስፋ በመቁረጥ ፋንታ፥ በመንፈሳዊ እድገት ወደፊት ብቻ ልገስግስ፤ በኑሮዬ ውስጥ ንጽህና ከፍተኛ ሥፍራ ይኑረው - ከቤቴ ውስጥ ብዙ ቁሻሻ ተጠርጎ እንዳይወጣ - ከሰውነቴና ከልብሴም ለስሜት ተስማሚ ያልሆነ ሽታ እንዳይወጣ ልጠንቀቅ።

የአንድ ሰው ሕይወቱ ሃዘን የተሞላበት ቢሆንም፥ ምድሪቱን ለሁሉም ሰው እኩል እንድትሆን የሚያደርጋት ከግለሰብ አንጻር ሳይሆን፥ ከሰብአዊነት (ከአዳም ጀምሮ የሰው ልጅ በምድር እስከሚኖርበት ድረስ) አንጻር በመሆኑ - የሰው ልጅ (ሰብአዊነት) እዚህ የደረሰው እንደ ማዕበል አንዴ ከፍ አንዴ ዝቅ ሲል (አንዴ በልቶ ሲጠግብ፥ በሌላም ጊዜ የሚበላ አጥቶ ሲራብ) መሆኑን በመረዳት፥ ምንጊዜም የእግዚአብሔር ጸጋ እንዳይለየን መጸለይ ይገባል። "...የተራቡትን ከበረከቱ አጠገባቸው፤ ባለጠጎችንም ባዶአቸውን ሰዷቸዋል።...."ሉቃ. ፩፥53

በምድሪቱ ላይ ምሬት ማብዛት ተፈጥሮአዊ ክስተቶችን እንደመካድ፥ እንደመጥላትም ሊሆን ስለሚችል፥ ጠንቀቅ - ቆጠብ ማለትና፤ የሚከተሉትን ነጥቦች ማገናዘብ ይገባል።

፩ኛ) ምንጊዜም ሰውን ወደ ከፋት የሚገፋፋ - የውጭ ጠላት - ክፉ መንፈስ በዙሪያችን መኖሩን፥

2ኛ) ይህ ክፉ ጠላት በተለይ የግለሰብን ደካማ ጎኖች እንደሚጠቀምባቸው፥

3ኛ) የዚህ ክፉ ጠላት አቸናፊ የእግዚአብሔር መንፈስ ብቻ መሆኑን።

ሰብአዊነት (ሰው ሁሉ በአንድላይ) ወደ "እሩቅ አገር" የሚጓዝ ቢሆን እኛ አናውቅም። ሁለት አለም እንዴት ሊገናኝ እንደሚችል አይገባንም፤ ከሰማያዊ ምሥጢሮች የራቅን ነን። ስለዚህ፥ በራሱ ላይ ታቦት እንደተሸከመ ቄስ፥ ምን ጊዜም የበላይ መኖሩን ማወቅ ይገባል።

ተመስገን ! ሊገባኝ የሚችለው እስኪገባኝ ድረስ፥ የመኖር እድል ለኔ ተሰጠ። ከእንግዲህስ፥ ከፋም ለማም እኔ (ቶማስ - ዮሐንስ) እኔው ነኝ።

እኔስ ስጽፍ ደስታን እየሸመትኩ ከዚህ ደርሻለሁ፤

በምርጫዬ ምድርን ትቻታለሁ፤

በምድር የሚሠራውን ክፋት ሁሉ ጠልቻለሁ፥

አለምን ላለመምሰል ቆርጫለሁ፤

በሰማያዊ ተስፋና በእምነት እኖራለሁ።

ይህ የማይረሳ ውለታ፥ ይህ ስጦታ - ይህ የመኖር እድል፥

ለክብር ለምስጋና እንዲውል፥

እንዳይረሳም በልቤ እንድዘምር፥

ይህ ነው የኔ የመቆያ ምሥጢር።

ፀሐይም ፀሐይ ናት ኮከብም ኮከብ ናት፥

ፈጥረህ አልተውከውም ሰውን እንደ እንስሳት፤

ከጥንት ጀምሮ አስበህለታል፤

መድህን እንዲሆነን ልጅህን ልከሃል።

ሌሊቱም አያምጽ፥ አይልም አልነጋም፥

ቀኑ አይሸፍትም፥ አይልም አልመሽም፥

ትእዛዝ ጠባቂ ነው፥ አንድ ሳይቀር ሁሉም።

ታዲያ- ምን ጭንቀት አለበት የሰው ልጅ በእውነት፥

የረገጠው መሬት፥ ከበላዩም ከዋክብት፥

ዙሪያው ተስተካክሎ ለዚህ ትንሽ ፍጥረት።

እስቲ ተነስቼ ብቻዬን ልሁን፥

በጸሎት ልበርታ፥ ልለምን አምላኬን፤
ወደ ማታ ሲሆን ሰው ይበራከታል፥
በጧቱ ልነሳ፥ ጊዜው ከፉ ብሏል።
ትላንት ተጀምሮ በአንድ እናት አባት፥
ሲወለድ፥ ሲሞት፥ ቅጥልጥል ሰብአዊነት፥
መጨረሻው ቀርቧል፥ የሰው ዘር ፍጥረት፥
ቢዘጋጅ ይሻላል ላዲስ ሰውነት።
ትዝታ ምንድነው፥ ደስታን የሚሰጠው፥
ከሃሳብ የማይጠፋው፥ ጊዜ የማይሽረው፤
ሰው ፍቅር - ፍቅር ሲሆን ሰው፥
ተከታትሎ 'ሚሄድ፥ ሞት የማይመክተው፥
አብሮ የመኖር ምሥጢር፥ ስሜቱ የማይጠፋው፥
የሰው ሕያውነት አፈር የማይቀብረው።
ምድራዊነት በቃኝ፥ በጣም ሰለቸኝ፥
ሥጋን መሸከሙ ድካም ሆነብኝ፤
የተዥጎረጎረ በእውነትና በውሸት፥
አስቆ 'ሚያስለቅስ የዚህ አለም ሕይወት፤
ችላ ብሎ ማለፍ፥ ቢበዛም እንቅፋት፥
ረጋ ብሎ መኖር፥ በጾም በጸሎት።
ልክ እንደ አንድ ዛፍ፥ ግንድና ቅርንጫፎች፥ ቅጠሎች የበዙበት፤
ዛፉ ሲገረሰስ ሲወድቅ፥ ቅጠሎቹም ሲረግፉ፥ ሌላ ግንድ ከሥሩ ሲተካለት፤
ባንድ በኩል ግለሰብነት፥
ለጊዜው ብቻ በርቶ ጥፍት የሚልበት፤
በሌላም በኩል ቁርጥርጥ ሥጋዊነት፥
ውል የጠፋው፥ ግን የማያቋርጥ - ቅጥልጥል ሰብአዊነት።
ሕይወት ምን ያደርጋል፥ ይቅርብኝ እንዳልል፥
የፍቅር ገመዱ ተብትቦ ይዞኛል፤
ሕሊናዬ በሃሳብ ይራቀቃል፤

ራቅ ራቅ እያለ በናፍቆት ይጓዛል፤
መንፈሴ ኪርያተ ሰማይን ይመለከታል።
እጅግ ቆንጆ ቤት ኃያል አምላክ ሲሰጠኝ ይታየኛል፤
"ስለዚህ አለሁ! ስለዚህ አለሁ!..." ያሰኘኛል፤
መንፈሳዊነት ምርጫዬ፥ ይህን እንዳልረሳ አድርጎኛል።

ሥጋ ሲቸገር፥ በችግር ላይ ችግር ሲታከልበት፥
መንፈስ ብቻውን ሲገሰግስ፥ ሲነጉድ፥ ሲሄድ ጥሎት፥
ጊዜው ሲረዝም - መንገዱም ሲርቅ ያባት ቤት፥
ሲያፈዝ፥ ሲያደነግዝ አለማዊነት፥
ፍጹም ፍቅርን በምድር ላይ መግለጽ ሲያቅት፥
ሰላም ማጣት፥ ምንጊዜም መጠማት - አለመርካት...፤
መቼ ነው ሰማያዊ አባታችን "ተሰብሰቡ ልጆቼ.." ብሎ የሚጠራን?
መቼ ነው ፈጣሪያችን ፊቱን የሚያበራልን።

አለማዊ የሆነ ሁሉ ስላስጠላኝ ጎመዘዘኝ፥
ምድራዊ ሕይወት ልክ እንደ እሾኽ እየወጋጋ አሳመመኝ፥
ወደ ማረፊያዬ - ወደ እግዚአብሔር ልሩጥ፥
ሌላም ምርጫ የለኝ።

ካሁን በፊት፥ በምድራዊነቴ ምክንያት ውስጣዊ አይኔ ተከድኖ፥ በአለማዊ አስተሳሰቤም ተጽንኦ መንፈሳዊ ክስተቶችን ማገናዘብ አቅቶኝ ነበር። አሁን ግን፥ በምድራዊነታችን የምንመጻደቅባቸው - ሃብት እና ሥልጣን ሁሉ ለሰማያዊነት ውርደት መሆኑን ተገነዘብኩ። "በሰው ዘንድ የከበረ፥ በእግዚአብሔር ፊት ርኩሰት ነውና።" ሉቃስ ፲፮፡፲፬

ከእምነት ጋር ሁሉ ነገር የተሟላ ስለሚሆን፥ ሰው ደስተኛ ኑሮ እንዳያገኝ የሚከላከል ድህነት ድርሽ አይልም። "ጻድቅ ያለው ጥቂት፥ ከብዙ ከኃጢአተኞች ሃብት ይበልጣል።" መዝ. 37፡16

ሲያገኝ ደስ የሚለው፥ ሲያጣም የማይከፋ በመንፈሱ የጠነከረ ሰው ነው። በሰማያዊ ተስፋ መኖር የሚችል መንፈሳዊ ሰው ለምድር የውሸት ኑሮ ስለማይጨነቅ፥ በደስታ ይዘምራል። "በመጠን ኑሩ፥ ንቁም፥ ባላጋራችሁ ዲያቢሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሳ አንበሳ ይዞራልና፤... " ፩ኛ ጴጥ. 5፡8

በእርግጥ ምድራዊ ችግሮች ሰውን ከሁለት ይከፍሉታልና፤ ለሁለት ከመከፈል ሊያድነው የሚችል መድኃኒት ቀርቦለታል። ሰው ከመንፈሱ ጋር በደንብ (በጥሩ መንገድ) ለመዋሐድ በሃይማኖት ትምህርት የሚሰበከውን ሁሉ ይከታተላል፤ ትምህርቱንም በሥራ ለመተርጎም ይጥራል። ግን በጥሩነት ብቻ መኖር ያቅተዋል። ለምንድነው ሰው ለራሱ ነፍስ ኃላፊ መሆን የሚያቅተው?

ይህ በፍጥረቱ "ብቁ" ያልሆነ ሰው ፍጹም ከሆነው ከክርስቶስ ጋር ለመቅረብ ይረዳው ዘንድ፥ አንድ የተለየ መንፈሳዊ - ሰማያዊ ስጦታ አዘወትሮ ከሚሄድበት ቤተ ክርስቲያን ይሰጣል፤ ይኸውም ቅዱስ ቁርባን ነው። በመንፈሳዊነት ወደፊት እንዳልጓዝ የሚያግደኝ ነገር ሁሉ ይህን የመንፈስ ምግብ እንዳልመገብ - ለብዙ ዓመታት ሳወጣ ሳወርድ እንድቆይ አደረገኝ። አሁን ግን፥ ቅዱስ ቁርባን ብቀበል ከክርስቶስ ጋር ለመቅረብ ይረዳኛል ብዬ አመንኩ።

ቅዱስ ቁርባን " ከሰማይ የወረደ የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ፤ ከዚህ እንጀራ የበላ ለዘለዓለም ይኖረል፤ ስለ ዓለም ሕይወት የምሰጠው ይህ እንጀራ ሥጋዬ ነው። "ዮሐ. 6፡51 የሚለውን የጌታ ቃል በተግባር ለመተርጎም የሚወሰድ፤ ክፉውን ለመርሳትና የወደፊቱን ጥሩውን እየተመለከቱ ለመኖር የሚረዳ አንድ እርምጃ ነው።

ቆራቢ ሰው በማወቅ ወይም ባለማወቅ ከስህተት ቢወድቅ፥ አቁራቢው ቄስ በቆራቢው ሰው ሕይወት ላይ ኃላፊነት እንደሌለበት ከመገንዘብ አልፎ፥ ጠቃሚውን ቅዱስ ቁርባን ለመቀበል የሚያበቃ በጎ መንፈስ ለሚገፋፋው ሰው ምንም አይነት አቀበት አይኖርም። የቄሱ እጅ መታጠብ እንደ ጲላጦስ እጅ መታጠብ ቢመስልም፥ ወደ እግዚአብሔር ሲቀርቡ እንደ አሮንና ልጆቹ መታጠብ ቢመስልም (ኦሪት ዘጸ. 30፡ 17 – 21) ጠቃሚውን ቅዱስ ቁርባን የሚያስብ አይምሮ ከምድራዊነት ባሻገር አልፎ ይሄዳል። ቆራቢ በእምነቱ በእውነት ሥጋ ወደሙን ይቀበላል - ወደ መንፈሳዊ እውነታም ይጠጋል።

እውነት በሰው አይመዘንም። እውነት ያለው ከእግዚአብሔር ዘንድ ነውና፤ ወደ እግዚአብሔር ለመጠጋት ስንል፥ እኛ የምናደርገው ጥረት ከልባችን ከሆነ፥ ከመንገዳችን ላይ እንቅፋቶችን እርሱ ያነሳልናል፤ መንገዱንም አቀበትና ቁልቁለት የሌለው ሜዳ ያደርገዋል፤ አሁንም የምንሮጠው በእውነት ከልባችን ከሆነ እርሱ መንገዱን ያሳጥረዋል።

ሁሉን ነገር በአካላዊነት ብቻ እንድናይ የሚያደርገን ምድራዊነታችን፥ "ይህ ቅዱስ የተባለ ቁርባን ሥጋዊ ወይንም ስነ አይምሮአዊ ምክንያት ነው ሊገኝለት የሚችል እንጂ፥ ቀጥተኛ መንፈሳዊ ለውጥ አያመጣም" እያልን እንድናስብ ይገፋፋናል። ግን፥ "እኔ ደካማ ስለሆንኩ፥ በተዳጋጋሚ ከስህተት እወድቃለሁ፤ ስለዚህ ቅዱስ ቁርባን

ለእንደኔ አይነት ኃጢአተኛ አይገባም" በማለት ፋንታ፥ "እኔ ደካማ ስለሆንኩ በተዳጋጋሚ ከስህተት እንዳልወድቅ፥ ሥጋ ወደሙን መቀበል ለኔ ያስፈልገኛል" ማለት ወደ መንፈሳዊ እውነታ መጠጋት እንደሆነ ስለ ምሥጢረ ቁርባን በመመራመር ሊደረስበት ይችላል[68]።

በእለተ ሐሙስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ ባርኮ ያቀበላቸውን፥ ካህናትና ምዕመናንም በመደጋገም ሲፈጽሙ፥ ክርስቲያኖች ሁሉ መንፈሳዊ ማንነታቸውን በየጊዜው የሚያስታውሱበት ከመሆኑም በላይ፥ ይህ እንደ አንድ የተቀደሰ እርምጃ ይቆጠራል። ስለዚህ፥ የሚጠቅመውን በመገንዘብ ደፍሮ የቀረበ ሰው፥ ከምድር ወደሰማይ በሚወስድ፥ ባለ አንድ አቅጣጫ መንገድ ውስጥ በመግባት ወደፊት ይጓዛል (ከመጣበት ቤት ይመለሳል - ከምድራዊነታችን ባሻገር - መንገዱ አንድ - አቅጣጫው አንድ)።

እግዚአብሔር ለሰማይ መንግሥቱ ሰውን ስለሚፈልግ፥ እያንዳንዳችንን በተለያየ መንገድ ያስጠጋናል፤ ወደ መንግሥቱም እርሱ በሚፈልገው መንገድ ያስገባናል። "ወደ ግብዣው ሥፍራ እንሂድ ! " ብሎ የሚመክር አንድ በጎ መንፈስ በሁላችንም ውስጠ ልቡና ውስጥ ይኖራል። ይህም በጎ መንፈስ የግለሰቡም ፈቃድ ክቡር መሆኑን እና፥ ያ ግለሰብ ባይቀርብም፥ እግዚአብሔር እንደሚወደው፥ ወደ መንግሥቱም እርሱ በሚፈልገው መንገድ እንደሚያስገባው ያውቃል። ሆኖም፥ ዘለአለማዊ የሆነው የእግዚአብሔር ፍቅር የሚገኘው ከእርሱ ጋር ሥጋዊነት የሌለበት መንፈሳዊ አንድነትን ስንመሠርት እንደሆነም መመልከታችን ከስህተት ላይ እንደማይጥለን እናምናለን። ምክንያቱም - በክርስቶስ፥ በእግዚአብሔር እና በደቀ መዛሙርቱም መካከል መንፈሳዊ አንድነት እንዲመሠረት ሲል፥ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ ሲል ጸልዮአልና።

"ከዚህም በኋላ በአለም አይደለሁም፤ እነርሱም በአለም ናቸው፤ እኔም ወዳንተ እመጣለሁ። ቅዱስ አባት ሆይ፥ እነዚህን የሰጠኸኝን <u>እንደኛ አንድ እንዲሆኑ</u> በስምህ ጠብቃቸው።" ዮሐ. 17፥11

ከዚህ ጸሎት በኋላ መጨረሻው ተጀመረ። የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው፥ መንፈሳዊ ሕብረተሰባዊ አንድነትን ለመመሥረት ታጥቀው ተነሱ፤ መንፈሳዊ ሕብረተሰባዊ አንድነት ማለት በሥጋ (በአካል) ለየብቻ ከመገኘት ባሻገር በመንፈስ አንድ መሆን ማለት ነውና።

[68] (ማቴ. 26፥26-30፤ ማር. 14፥ 22 – 26፤ ሉቃ. 22፥7-23)

እኔም እራሴን በመመርመር ላይ ሆኜ፥ የልቤን ክፋት አስተውያለሁ፤ በኃጢአቴ አዝኜ ተከዣለሁ። እኔ ምንም ምንም ሥራ የሌለኝ እንደ ዘኬዎስ ኃጢአተኛ ነኝ፤ አምላኬ አንተ ዘንድ ለመድረስና ባንተ የመንፈስ ክልል ውስጥ ለመዋል ስል፥ ሮጬ ሮጬ ደክሜአለሁ።

ዘኬዎስ አንተን ለማየት ከበለስ ዛፍ ላይ ተንጠልጥሎ ሳለ፥ "ዛሬ ከቤትህ እውል ዘንድ ይገባኛል" ሉቃ.19፡1-10 እንዳልከው፥ ከእኔም ቤት ተገኝልኝ፤ ጎብኘኝ - ተመልከተኝ። ከእንግዲህስ የቆሸሸውን ቤቴን አጸዳለሁ፤ አንተ ምራኝ፤ እኔም የሚቻለኝን ሁሉ አደርጋለሁ። እኔነቴ ግራ ቢያጋባኝም፥ በእግዚአብሔር እያመንኩ፥ ከእርሱ ፈቃድ ሳልወጣ ለመኖር፥ ዛሬ ለራሴ ቃል ኪዳን እገባለሁ። እምነቴን ከምን ጊዜውም የተጠናከረ ላደርገው ቆርጬ ተነስቻለሁ።

መቼም የሥጋ ነገር ሰውን አይለቀውም፤ ሆኖም ቅዱስ ቁርባን ፍጹም ሰማያዊ ስለሆነ ወደ ሰማያዊ አንድነት ይመራዋል። ከፈጣሪያችን ጋር አንድነትን ለመመሥረት የሚደረግ ትግል የተቀደሰ ነውና፤ ንስሐ ገብቼ ቅዱስ ቁርባን መቀበል እንደሚገባኝ በጣም እርግጠኛ የሆንኩበት ቀን ደረሰ።

ከልቤ ቂምና በቀልን አጥፍቻለሁ፤

ትግሉ ከራሴ እንደሆን አውቄአለሁ፤

ከእንግዲህ በእግዚአብሔር ፍቅርና ቸርነት እኖራለሁ፤

እርሱ ሲጠራኝ እሄዳለሁ፤

እስከዛው ፈቃዱን ለመፈጸም እታገላለሁ።

ቄሶች አቁርቡኝ እባካችሁ፤

እኔን እንደ ሞተለሚ ቆጥራችሁ።

ኃጢአቴ ተነገሮ አያልቅም፤ ጸልዩልኝ አሁን፤

እንደ ቸርነቱ አንጂ እንደ በደሌ እንዳይሆን።

የመራኝ - ፈቃዱ ሁሉ የእርሱ የሆነ አምላክ- ሁሉን ነገር በአዎንታዊነት እየተመለከቱ፥ ዶሮ ጫጩቶቿን እንደምታቅፍ፥ ምዕመንን በፍቅር የሚያቅፉ፥ አንድ ደግ አባት (ካህን) ፊት ለፊት አስቀመጠኝ። እርሳቸው በአንድ በክፉ ቀን ከጎኔ ቁጭ ብለው ያናገሩኝና የተጨነቀውን አንጎሌን ያፍታተልኝ ናቸው (የደግ ሰው ውለታ አይረሳም)።

እኔም- "እነኚህ የእርስዎ ልጆች የሆኑ፥ ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚያዘወትሩ ወጣቶች ሁሉም በጣም ጥሩዎች ሆነው ይታዩኛል፤ እኔ ግን ለብዙ ዓመታት

የወጣትነቴን ጊዜ ሁሉ ከቤተ ክርስቲያን ቀርቼ፥ ብልሹ (ከዳተኛ) ሆኜ ያሳለፍኩትን ጊዜ፥ ኮሙኒስት ሆኜም - በእግዚአብሔር ያላመንኩበትን ዘመን ሳስበው ይቆጨኛል፤ ያንገበግበኛል” አልኳቸውና ከፊታቸው ምርር ብዬ አለቀስኩ።

እርሳቸውም እንደ ህጻን አባበሉኝና፥ “ከእንግዲህ የወደፊቱን እንጂ ያለፈውን አትመልከት።” በማለት፥ ለወደፊት የሚጠቅመኝን መከሩኝ። ቅዱስ ቁርባን እያዘወተሩ በመቀበል ከቤተ ክርስቲያን አለመለየት ምን ያህል እንደሚጠቅምም አስረዱኝ። ከእንግዲህ፥ እኔ አንድ ኃጢአተኛ ጭንጋፍ ከበቃሁ ለቅዱስ ቁርባን፥ ሌላ ማን ይኖራል የማይበቃ።

ሥጋውና ደሙን ያቀበሉኝ፥
ለኔ ለኃጢአተኛው መድኃኒት ሆነልኝ፤
በእውነት እንዳሰብኩት አዲስ ሰው አደረገኝ፤
ለውጡን ተመልክተው ሌሎችም ነገሩኝ።

አልፎ አልፎም ቢሆን ለቁርባን ሳደርግ ዝግጅት፥
አጉልቼም ሳየው የእኔነቴን ክፋት፥
ትግሉንም ሳስበው ቂምና በቀልን ከልብ ስለማጥፋት፥
መቆየቴን ወደድኩት፤
እውን የሚሆንልኝን ሕይወቴን ቃኘሁት፤
የመኖር ትርጉሙን በጥልቀት አየሁት፤
በውስጣዊ ደስታም ኑሮዬን አደስኩት።

ከፍጹማዊ እውነት ጋር በምድር የተመላለሰ ክርስቶስ ጋር አንድነትን ስለመሠረትን፥ በእውነት ውስጥ የመቆየት እድል አገኘን። ከእንግዲህ ምንም ቢደርስብን አንፈራም። “ ልባቸውን የቆሰሉትን ይፈውሳል፤ ህመማቸውንም ይጠግናል”መዝ. 147፥3

ሁለት ሺህ ዓመታት ቆይቶ አሁንም እንደ አዲስ፥
ከቶ ‘ማይቀየር  የእግዚአብሔር ፍቅር፥
ምሥጢሩ የመስቀሉ ምልክት፥
በመስዋእትነት ራስን አሳልፎ እስከ መስጠት፥

ተሰቃይቶ፤ ሞቶ በመነሳት[69]

እግዚአብሔር ፍቅሩን ለሰው ልጆች የገለጸበት።

“ይህ ሥጋዬ ነው ብሉት፥ ይህ ደሜ ነው ጠጡት...........፤”

ሰማያዊ ምሥጢር የቁርባን ምልክት፥

ላመነበት ይሆናል መድኃኒት።

የሰውን መንፈሳዊ ፍላጎት - አያሟላም ምድራዊነት፤

የሰው ደካማነት - የኃጢአቱም ብዛት፥

ኑሮን ያበላሻል፥ ይመራል ወደ ሞት።

ሰዎች ሲጨነቁ፥ ፈጣሪያቸውንም ሲፈልጉት፥

በናፍቆት - ለአንድ ወጥ አለም - ለሰላም በጉጉት፥

የእግዚአብሔር ልጆች ለመባል፥ ከብቸኝነት ለመውጣት፤

ምንም ቢጎድል እውቀት፥ ከሁሉም ይበልጣልና እምነት፤

ከአስርቱ ትእዛዛት ሲፈልቅ ሃይማኖቱ፤

በወጣ ገብ ምድር፥ ለዚህ ሕዝብ ፍጥረቱ፤

ለጠባይ ማረሚያ  ምን አለ የሚሰጥ፤

ምን አለ! ምን አለ!  ከሥጋ ወደሙ ‘ሚበልጥ።

ከእንግዲህስ እግዚአብሔር በሚፈቅድልኝ መንገድ እኖር ዘንድ፥ የራሴን ፈቃድ ለርሱ ሰጥቼዋለሁ። “አቤቱ የቤትህን ስፍራ፥ የክብርህንም ማደሪያ ቦታ ወደድሁ።” መዝ. 25፡8

አንባብያን ሆይ! የእኔ ዛሬ ባለ ታሪክ ሆኖ መገኘት፥ በዚህም ሆነ በዚያ ለመጪው ትውልድ ምክር ይሆን ዘንድ፤ በአንድ በኩል እራሴን ስመክር፤ በሌላም በኩል እኔን መሳይ ተመካሪ ስለማይታጣ ጠቃሚውን ለማስተላለፍ ፈልጌ ነው።

ከግለሰብ ባለ ታሪክነት የሚበልጠው ሁላችንንም የሚመለከተው ነውና፤ የሰው ኃጢአተኛነት ተገልጾ መድኃኒቱ ከተነገረ ይበቃል።

---

[69] “ነፍሴን በሲኦል አትተዋትምና፥ ጻድቅንም መበስበስን ያይ ዘንድ አትተወውም።” መዝ. 15፡10

ጠብቆ እዚህ ላደረሰን፥ የርሱን ፈቃድ ለመፈጸም ላበቃን አምላካችን ይክበር ይመስገን። ሰው ሁሉ ከሥጋዊ ተጽንኦ በላይ በመሆን፥ መጪውን የመከራ ጊዜ ለመቋቋም የሚያስችል ብርታት እንዲያገኝ የእግዚአብሔር ፈቃድ ይሁንልን። አሜን።

በእውነት ፈጣሪ አምላካችን እግዚአብሔር ፍጹምና ኃያል፥

ስሙ ክቡር፥ ለዘለአለምም የተመሰገነ ነው።

አስጀምሮ ላስጨረሰን ለፈጣሪ አምካችን ታላቅ ምስጋና ይድረሰው። አሜን።

**ተፈጸመ**

# አባሪዎች

## ደብዳቤ፥
## እንጉርጉሮ
## ጸሎታት
## መዝሙሮች (መንፈሳዊ)

## ካልአይ ደብዳቤ

"ይድረስ ለተከበርሽውና በጣም ለማፈቅርሽ ለውድ ባለቤቴ ኮከቤ።[70]

ሁለታችንም ባለንበት የሚጠብቅ አምላክ ስለ ደህንነትሽ አሳውቆኛልና፤ ደስ ብሎኛል። ለአለማዊ - ምድራዊ ሕይወቴ የሚጠቅመኝን እያሰብኩ ኑሮዬን ልቀጥል እያልኩ እንዳላስብ ይህ አንድ ጥቅስ ብቻውን መለሰኝ፡-

"ነገር ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ፤ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል" ማቴ. 6፡ 33

"ይህም ሁሉ" ለኔ የወደፊት ሕይወቴ - ገንዘብ ብቻ እልነበረም፤ ሌላም - ሌላም - ብዙ - ብዙ ተጨምሮልኛል። የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም መፈለግን እቀጥላለሁ።

የልጆቻችንን ነገር አደራ ያልሺውን፥ እኔም ላንቺ ቃል ኪዳን የገባሁትን በአንድ በኩል ፈጽሜአለሁ እንድል ያደረገኝ- ሁለቱም ልጆቻችን በከፍተኛ ትምህርት ተመርቀዋል (ሁለቱም ዶክተሮች ሆነውልናል)።

ኮከብዬ፥ ምንም እንኳን በአካል ብትለይኝ፥ ያንቺ ፍቅር ከውስጤ አልጠፋም። ባንቺ፥ በእኔና በልጆቻችን መካከል ያለው ፍቅር ዘለአለማዊ ነው፤ ለዚህም ይመስለኛል፥ አንዱ ምክንያት፥ ሁላችንም ብርቱ የሆነው።

---

70 ቀዳማይ ደብዳቤ - "ከምድራዊነታችን ባሻገር" በአንደኛው መጽሐፍ ላይ አባሪ ሆኗል።

ልጆቻችን አድገው ከቤት ሲወጡ፥ እኔም ብቻዬን እንዳልሆን ያሰብሽልኝን መልካም ሴት አግብቻለሁ። ሰው ሁለተኛ ሚስት፥ በምክንያቱ ቢያገባ፥ ሰማያዊ የፍቅር ሰንሰለቱን የሚበጥስበት ምድራዊ ክስተት አይኖርም። እኔም ለሁለተኛ ሚስቴ ያለኝ ፍቅር ለመጀመሪያ ሚስቴ ያለኝን ፍቅር አባባሰው እንጂ አልቀነሰውም። ይህም ሊሆን የቻለው፥ ሁለተኛ ሚስቴን የቀረብኳት (እርሷም የቀረበችኝ) ከሥጋዊ ይልቅ በመንፈሳዊ ፍቅር - በቅዱስ ቁርባን አንድነት ስለሆነ ይመስለኛል። እርሷም እንዳንቺው አስተዋይ ስለሆነች፥ እኔን ስትወደኝ፥ እኔ ከምወዳቸው ጋር ሁሉ ነው። ስለዚህም፥ ባንቺ እናትና አባት ዘንድ፥ ልክ እንደ ልጃቸው ተቆጥራለች። ከምድራዊነታችን ባሻገር ሰማያዊያን መሆናችንንም ስናገናዝብ በመንፈሳዊነት የጸናው ህልውናችን ሁላችንንም በአንድ ፍቅር አቆራኝቶናል።

ምድራዊ ሆነን ብንፈጠርም፥ ሰማያውያኖችም ስለሆንን፥ የምናፈቅራቸው በሥጋ ቢለዩንም፥ አይጠፉም ከጎናችን። እያፈቀርኩሽ እኖራለሁ፤ ሳስታውስሽ፥ በሁለንተናዊ ፍቅር እጠናከራለሁ። ስለዚህ በምድር ስኖር የምሠራው ሁሉ ፍቅር የተሞላበት ይሆናል።

በአካላዊ ሕይወትሽ ከኔ ጋር ከነበርሽበት ባላነሰ መንገድ፥ ያንቺ ፍቅር ለኔ መንፈሳዊ መቀስቀስ በመሆኑ ነው፥ አራት መጻሕፍት ተጽፈው ለሕዝቦች እንዲዳረሱ የሆነው። ይህንን በቀላሉ አልመለከተውም።

ስላንቺ መለየት ከፍተኛ ሃዘን ውስጥ በገባሁበት ወቅት፥ እኔን ለማጽናናት የሚከተለውን አጽናኝ ምክርሽን በደንብ እንዲገባኝ ብለሽ፥ በግርግዳ ላይ ጽፈሽ አሳየሽኝ።

"እኛ እግዚአብሔርን በምንፈልግበት ጊዜ ብቻ ወደ እርሱ እየተጠጋን፤ ሲያሻንም ከእርሱ እየራቅን ለመኖር የማንችል መሆናችንን፤ እግዚአብሔር ምን ጊዜም - እኛ ከርሱ እንድንርቅበት የማይፈልግ መሆኑን አሳወቀን።"

ይህ ለኔ መንፈሳዊ መቀስቀስ እንደሆነ ሁሉ፥ መጻሕፍቱን ለሚያነቡትም ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርብ እንዲሆንልን እመኛለሁ።

በይ እንግዲህ ኮከብዬ! ወዳንቺ እስከመጣ ድረስ፥ ስለ "ሁሉም ነገር" የእግዚአብሔርን ፈቃድ እየለመንሽ ጠብቂኝ። እስከዛው ደህና ሁኚልኝ፤ በሰላም ለመገናኘት ያብቃን።"

በቶማስና በዮሐንስ የተከፈልኩ እኔው ነኝ ባለቤትሽ።

<u>ትዝታ ከዛን ጊዜ</u>

ደጋግ ሰዎች በደግነታቸው ጸንተው እንዳይቆዩ ምድራዊነት ሲያስጨንቃቸው፥ በተረፈ እድሜአቸው እንዳይሳሳቱና ኃጢአትም ሥርተው ከእርሱ እንዳይርቁ ሲል፥ ሁሉን የሚያይ እግዚአብሔር በተለያየ ጊዜ ይወስዳቸዋል። እርሱን ለማመን ብዙ እውቀት ያስፈልገናል ከሚሉ ተጠራጣሪዎች ይለያቸዋል። እነኚህን ተጠራጣሪዎች ግን፥ እስኪገባቸው ድረስ ያቆያቸዋል።

እግዚአብሔር ሲለመን ለጤንነት፥ በንባብ፥ በጾም፥ በጸሎት፥
የአዲስ አለም በር ሲከፈት፥ ባለቤቴን ሲወስዳት፤
ወይ ጉድ! ወ ጉድ! ብሎ ቅርት! ወይ ጉድ ብሎ ቅርት!
የአለም በር ሲዘጋ፥ ሰው ለሰማይ በር ሲጠጋ፥
የት ይገኛል በፍለጋ፥ የት ይገኛል በፍለጋ።

መጥፎነቴን የምትደብቅልኝ፥ ጥሩነቴን የምታንጸባርቅልኝ፥
ለኔ አንድ ብሩህ ተስፋ ኮከቤ ነበረችኝ።
አሁን ይህ የሞት አደጋ ሲደርስብኝ፥
እኔ ካለ ኮከቤ እንዴት እኖራለሁኝ?

ኮከቤ፡- የሰዎችን ሻካራነት አለሳልሰሽ፥
እሬት ወስደሽ፥ ማር መልሰሽ፥
ሁሉን እንደ ጠባዩ ይዘሽ፥ ለባልሽ ለልጆችሽ ብለሽ፥
ደክመሽ፥ ደክመሽ፥ አረፍሽ።
አንቺ መልካም ሴት፥ የሰውን ጥሩነት ያየሁብሽ፥
ኮከቤ፥ ማንም ያላወቀልሽ እንቁ ነሽ፤
አንቺ ወዳጄ፥ የማርያም ፈቃዷ ነሽ።

ሥጋ ከጂ ነው፤ መንፈስ ግን አይከዳም፤
የእውነት ፍቅር ልጆች ፍቅር ናቸው ምንጊዜም፤
አውቃለሁ፥ እኔ ከአንቺ አልለይም፤
አውቃለሁ፥ አንቺ ከኔ አትለዪም።
እግዚአብሔር እባክህ፥ የኮከብዬን ነፍሷን ማርላት፤
እንግዲህ ይኸው ነው የኔ የማያቋርጥ ጸሎት።

የሚንቀሳቀስ ቀጥ ይላል፥ የሚጮህም ዝም ይላል፤ የሚበራ ይጠፋል፥ የተገኘም ጥፍት ይላል፤ ግን ፍጹም ፍቅር በመሬት ቋንቋ አይገለጽም፤ ፍቅር በምድራዊ ኑሮ አይተረጎምም።

ኮከብዬ ፍቅርይዬ፥ የኔ ሺጋ፥ ቆንጅይዬ፥
ስላንቺ ሳለቅስ አልቆም አለ እንባዬ።
የማይለይ መንፈስሽ፥ የማይነካ ሰውነትሽ፥
እስቲ ደግመሽ አናግሪኝ ፍቅርዬ ቀረብ ብለሽ፤
በለዛ አንደበትሽ፥ በሰማያዊ ድምጽሽ፥
ጊዜው ደርሷልና አብረን ልንሆን ነው ብለሽ።
ከልጆቼ ተርፈሽ ለኔም እናት ነበርሽ፤
ሙሉ ሰውነቴን ጠግነሽ ያቆየሽ፤
በዓይነ ሕሊና እየተመለከትኩሽ፥
ከግራም ከቀኜ,ም ምን ጊዜም አንቺ አለሽ።
ኮከብዬ ፍቅርይዬ፥ የኔ ሺጋ፥ ቆንጅይዬ፥
ስላንቺ ሳለቅስ አልቆም አለ እንባዬ።
ጥንትም የምድር ነገር አልገባህ የሚለኝ፥
ኑሮዬ ካለ አንቺ ቀፎ ሆነብኝ፤
እንጀራ እንዳልበላ እንባ ተናነቀኝ፤
ተጫውቼ እንዳልስቅ ማስመሰል አቃተኝ።
የሥጋን ከንቱነት ተረድቼዋለሁ፤
በልቤ አንቺን ይዤ በምድር እኖራለሁ፤
ጥርት ያለ እውነት ሲከበኝ አያለሁ፤
ኑሮ ከሰማይ ቤት መሆኑን አውቃለሁ።
ኮከብዬ ፍቅርይዬ፥ የኔ ሺጋ፥ ቆንጅይዬ፥
ስላንቺ ሳለቅስ አልቆም አለ እንባዬ።
ምድር ላንቺ ባትሆን ከሰማይ ቤት ገባሽ፤
ይኸው እስከ ዛሬ ከኔ ምንም አልራቅሽ፤
የእውነት ፍቅር ልጆች ከሩቅ ይመጣሉ፤

ሥጋን እየከዱ ለመንፈስ ያድራሉ።

የማይሞት ፍቅር፤ የሚመነጭ ከሁለታችን፤

አንድ አድርጎናልና በመንፈስ - በነፍሳችን፤

በሁለት አለም በሚገኝ በአምላካችን፥

አይዞሽ ምን ጊዜም አብረን ነን።

ኮከብዬ ፍቅርይዬ፥ የኔ ሺጋ፥ ቆንጅይዬ፥

ስላንቺ ሳለቅስ አልቆም አለ እንባዬ።

እንዲህ ሃዘንተኛ በነበርኩበት ወቅት እነኚህ ነፍስ ያላወቁ ትናንሽ ልጆቼ እየመከሩ አቆዩኝ። ይኸውላችሁ!! የማይረሳ የልጅ ውለታ። የልጆቼ ጨዋታ ስነአይምሮዬን መለስ ያደርገዋል። መልካቸውን በየቀኑ ማየቴ በሥጋ ለመቆየቴ ምክንያት ሆኑልኝ።

የኮከቤ ቢፈርስ ሰውነቷ፥ መንፈሷ ሕያው ሆኖ ከባለቤቷና ከልጆቿ፥ ከልጅ ልጆቿ፥ ከትውልድ ትውልድ ይተላለፋል፤ ሰብአዊነት ይቀጥላል። እያንዳንዱ ሰው ሲሞት ልጆቼ! ልጆቼ! እያለ እግዚአብሔር የሚጠራቸው መንፈሶች ከሥጋ ተለይተው ሰላምና ጸጥታ፥ ደስታና ፍቅር ወዳለበት - የእግዚአብሔር መንፈሱ በሰፈነበት ሥፍራ ይሄዳሉ። ይህ ነው ሞት ማለት።

ኮከቤ ከዛው ካለችበት ሁና፥ ለልጆቻችን ማሳደጊያ፥ ለምድራዊ ኑሮዬም የሚጠቅሙ፥ መንፈሳዊነቴንም የሚያጎለምሱ ብዙ ምክሮች አስተላልፋልናለች። ለኑሯችን በማደርገው ውሳኔ ውስጥ የተለያዩ ስሜቶችን በውስጤ እያስተጋባች፥ አንዳንድ ጉዳዮች እንዲስተካከሉ የረዳችኝ ይመስለኛል። እኔም ከርሷ ላለመለየት ስል በብዙ ነገር እርሷ እንደምትፈልገው ሆኜ ኖርኩ።

እግዚአብሔር ልጆቻችን በጤንነት ጠብቆልን፥ ከክፉ ነገር ጠብቆልን እዚህ ስላደረሰን፥ በየቀኑ መንፈሳዊ ደስታ ይሰማኛል። "እነሆ፥ ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታ ናቸው።" መዝ. 126፡3

እነኚህን የልጅ አዋቂዎች የአባታቸው እና የእናታቸው መንፈስ የሚመራቸው ስለሆኑ፥ ከአበቦች መካከል ጣፋጩን ጮርቃ እንደሚቀምሱ ወፎች ሆነው የሚያድጉ፥ በብርሃን ውስጥ የሚመላለሱ ይሆናሉ።

ልጆቻችን ይህን መጽሐፍ በሚያነቡበት ወቅት፥ በቃል ከነገርኳቸው ጋር ሁሉ ሲያዛምዱት፥ ብዙ እውነቶች ይረጋገጡላቸዋል። በሥጋ በምለይበት ወቅት፥ ከምንጊዜውም በበለጠ በመንፈስ እንደምቀርባቸውና በምድር ያደረኩላቸውን

እንክብካቤም እንደምቀጥልና ምንጊዜም በመንፈስ አብረን እንደምንሆን በደንብ ይገባቸዋል።

__እንጉርጉሮ__

እንደዛሬው ሞት ባልረከሰበት በጥንት ዘመን፥ ዘመድ ወዳጅ የሞተባቸው ሰዎች ሲያዝኑ እየተጣሩም ነበር። ተገንጥሎ የሄደው የራሳቸው መንፈስ ይመስል - ናልኝ (ነይልኝ) ምነው ሄድክብኝ (ሄድሽብኝ) እያሉ ሲማጸኑ፥ የሞተውን መመለስ እንደሚቻል ያስመስሉት ነበር። በሚያሳዝን ግጥም ካለማቋረጥ ያዜማሉ፤ ከእነኚህም ዜማዎች እና ግጥሞች መካከል አንዳንዶቹ እስከዚህ ትውልድ ድረስ ዘልቀዋል።

__አንቺ ወዳጄ (ባል) - አንተ ወዳጄ (ሚስት)__

አንቺ ወዳጄ፥ ካጠገቤ ያለሽ፥
ምን - ምን ወሬ ታሰሚኛለሽ፤
ምንም - ምንም አላሰማህም፥
ባናግርህ፥ አትሰማኝም፤
እሰማሻለሁ፥ በውስጠ መንፈሴ፥
እባክሽ አናግሪኝ፥ አካሌ ነፍሴ፤
አንተ ባታየኝ፥ እኔ አይሃለሁ - እኔ አይሃለሁ፤
በኑሮህም ውስጥ እሳተፋለሁ - እሳተፋለሁ፤
እውነትሽን ነው፥ ይህን አውቃለሁ፥
ከሁለት አለም ተከፍያለሁ፤
አይዞህ ታገስ፥ ትደርስበታለህ፥
እዚህ ስትመጣ ሁሉን ታያለህ።
በመንፈስ ሳይሽ፥ አንቺም ስትቀርቢኝ፥
ሆዴ እየባባ አስቸገረኝ - አስቸገረኝ፤
ሕያው መሆከን ካወቅህ ይበቃል፤
ፍጹም ፍቅር አለ፥ ይጠብቅሃል - ይ...ጠ..ብ.ቅሃል ።

*(ባንድነት)*

ጊዜው ነጎደ፥ ገሰገሰ - ገሰገሰ፥
ቁስ አካል ሁሉ ፈራረሰ - ፈራረሰ፤
ምድራዊ ኑሮ ተባባሰ - ተባባሰ፥
ተስፋ እየሰጠ፥ አስለቀሰ - አስለቀሰ፤
መቼ ነው ጊዜው የጉዟችን - የጉዟችን፥
የሰማይ ባቡር ማግኘታችን - ማግኘታችን፤
መቼ ነው ቀኑ መነሻችን - መድረሻችን፥
ኪርያተ ሰማይ መግባታችን - መግባታችን፤
መቼ ነው ወቅቱ የደስታችን - የደስታችን፥
ከዘመድ ወዳጅ መታያችን - መታያችን።
ናፈቀኝ በጣም ክብራችን - ክብራችን፥
የአዲስ አለም ሰው መሆናችን - መሆናችን።
ቀርቧል ተዳርሷል በዓላችን - በዓላችን፥
የእግዚአብሔር መንግሥት መውረሳችን - መውረሳችን።

*************************************************

<u>መንፈሳዊ መዝሙር - ጥሩነቴን ላጉላ</u>

<u>አዝማች</u>

መጥፎነቴን ልተው፥ ክፉነቴን ልጥላ፤
ጠባዬን ላሻሽል፥ ጥሩነቴን ላጉላ።

ከገነት ተባሮ በገዛ ኃጢአቱ፥
ሥጋዊ - ደማዊ፥ የሆነ ፍጥረቱ፥
መስዋዕት ለመሆን ይድከም ሰውነቱ፤
የመኖር ትርጉሙ እንዳይሆን በከንቱ።
ሲያስጎመጀው ገንዘብ፥ ውል - ውል ሲለው፥
የምድር ሃብት ይቅርበት፥ ሥጋዬም አይድላው፥
ለዚች አለም ደስታ ምንም ቅር አይበለው፥
ከራስ ወጥቶ ማሰብ ነው የሚበልጠው።

<u>አዝማች</u>

መጥፎነቴን ልተው፥ ክፉነቴን ልጥላ፤
ጠባዬን ላሻሽል፥ ጥሩነቴን ላጉላ።

    መድከሙ ለምን ነው? ቅጣይ ሕይወት ባይኖር፥
    ይህን ጠባይ ይዤስ ከዛ እንዳልሻገር፥
    ካሁኑ ልዘጋጅ፥ እራሴን ልቀይር፥
    እንደዚህ ሲሆን ነው፥ መንፈስ የሚዳብር።
    ለአላፊ - ጠፊ አለም፥ ላስወግድ ጭንቀትን፥
    ወደፊት ልገስግስ፥ ልርሳ ያለፈውን፥
    በሰላም ለመኖር አላብዛ ቅሬታን፥
    መስቀሉን ልመልከት፥ ተስፋ 'ሚሰጠኝን።

<u>አዝማች</u>

መጥፎነቴን ልተው፥ ክፉነቴን ልጥላ፤
ጠባዬን ላሻሽል፥ ጥሩነቴን ላጉላ።

    የሰው ልጅ ጠባዩ ከሆነ ሁለት፥
    ደጉ ለኔ ይቅር፥ ክፉው ይግባ መሬት፤
    ይሁን የኔ ጠባይ ፍቅር የሞላበት፤
    ይዤ የምሄደው አገረ ሕይወት።
    የአዲስ አለም ተስፋ፥ ደስታ የሞላበት፤
    አለ የሚጠብቀኝ ከላይ ከሰማይ ቤት፤
    እውነትን ያዘለ የኔ እምነት ሃይማኖት፥
    ያስመለከተኛል የዘለአለም ሕይወት።

<u>አዝማች</u>

መጥፎነቴን ልተው፥ ክፉነቴን ልጥላ፤
ጠባዬን ላሻሽል፥ ጥሩነቴን ላጉላ።

<u>መንፈሳዊ መዝሙር - አምላኬ - አምላኬ</u>

<u>አዝማች</u>

ያንተው ነኝ አምላኬ - ያላንተ ማን አለኝ፤
በምድራዊነቱ ሕይወት ጨለመብኝ፥
የመንፈስከን ብርሃን እባክህ አብራልኝ፤
ፈጣሪዬ አትራቀኝ፤ በምህረትህ ጎብኘኝ።

    አምላኬ - አምላኬ እላለሁ ሁል ጊዜ፥
    በምድራዊነቴ ሲሰማኝ ትካዜ።
    አንተ ነህ አምላኬ - ጋሻ መከታዬ፥
    የፍቅር ባለቤት - አምባ መጠጊያዬ፥
    መዳኛዬ አንተ ነህ፥ ምንጊዜም 'ማልተውህ፥
    እምነቴም ባንተው ነው፥ ተስፋ 'ማልቆርጥብህ።

<u>አዝማች</u>

ያንተው ነኝ አምላኬ - ያላንተ ማን አለኝ፤
በምድራዊነቴ ሕይወት ጨለመብኝ፥
የመንፈስከን ብርሃን እባክህ አብራልኝ፤
ፈጣሪዬ አትራቀኝ፤ በምህረትህ ጎብኘኝ።

    ሰላም፥ ፍቅር፥ ደስታ፥ አንተ ካለህበት፥
    ወዳንተ ለመቅረብ የማደርገው ጥረት፥
    ተስፋ ይሰጠኛል መንፈሳዊነት፥
    ደስታም ይሰማኛል፥ አገኛለሁ እረፍት፤
    ስለዚህ ኑሮዬ ከምድር ርቆ ሄዷል፥
    በሥጋ ብደክምም መንፈሴ ጠንክሯል።

<u>አዝማች</u>

ያንተው ነኝ አምላኬ - ያላንተ ማን አለኝ፤
በምድራዊነቴ ሕይወት ጨለመብኝ፥
የመንፈስከን ብርሃን እባክህ አብራልኝ፤
ፈጣሪዬ አትራቀኝ፤ በምህረትህ ጎብኘኝ።

ሥጋ ለባሽ ብንሆን - ከውስጥ መንፈስ አለን፥
ከወላዲተ አምላክ የሚያስተሳስረን፤
ለጸሎታችን - ለልመናችን አጋዥ እናት አለች፥
ክብርት፥ ቅድስት ማርያም ታማልደናለች፤
ጌታችን ክርስቶስ እናቱን ይሰማል፥
የኛም ጸሎት በርሷ - ወደ ላይ ያርጋል።

<u>አዝማች</u>

ያንተው ነኝ አምላኬ - ያላንተ ማን አለኝ፤
በምድራዊነቴ ሕይወት ጨለመብኝ፥
የመንፈስከን ብርሃን እባክህ አብራልኝ፤
ፈጣሪዬ አትራቀኝ፤ በምህረትህ ጎብኘኝ።

<u>*መንፈሳዊ መዝሙር - ጽናት በእመቤታችን*</u>

<u>አዝማች</u>

በሰማይ ላይ ሆነሽ፥ ጸዳልሽ ያበራል፤
በየአህጉራቱ ብዙ ሰው አይቶሻል፤
እኔም አንቺን ሳስብ እጅግ ደስ ይለኛል፤
መጠጊያ ረዳቴ አጽናኝ ሆነሽኛል።

ማርያም፥ ማርያም፥ ማርያም፥ እላለሁ ከልቤ፥
አንቺው ነሽና ያለሺኝ፥ የመንፈስ እናቴ።
ማርያም እመቤቴ የክርስቶስ እናት፥
ልበ ርህሩህ ማርያም - ንጽህት ቅድስት።
ጌታዬን ልፈልግ፥ አንቺንም ልቅረብሽ፥
ሰዎችን ለማዳን  አልቅሰሽ፥ ጸልየሽ፥
መጽናናት ሆነልኝ፥ እኔ አንችን ሳስብሽ፥
እመቤቴ ማርያም ፍጹም ደግ እናት ነሽ።

<u>አዝማች</u>

በሰማይ ላይ ሆነሽ፥ ጸዳልሽ ያበራል፤

በየአህጉራቱ ብዙ ሰው አይቶሻል፤
እኔም አንቺን ሳስብ እጅግ ደስ ይለኛል፤
መጠጊያ ረዳቴ አጽናኝ ሆነሽኛል።

ኑሮዬ ሲያስከፉኝ፥ ኃጢአቴም፥ ሲከብደኝ፥
ለመንፈሴ ብርታት ተስፋ እንድትሰጪኝ፥
እለምንሻለሁ ቀርበሽ እንድታይኝ፤
ይቅርታን ከልጅሽ እንድትለምኚልኝ።
በእናታዊ ፍቅር ሁሉንም ያቀፍሽ፥
አንቺ የጠፈር ንግሥት ጽናት ትሰጪያለሽ፤
ውዳቂ የሚየነሳ ልጅሽ ክርስቶስን፥
እመቤቴ 'ባክሽ አማልጂኝ እኔን።

<u>አዝማች</u>

በሰማይ ላይ ሆነሽ፥ ጸዳልሽ ያበራል፤
በየአህጉራቱ ብዙ ሰው አይቶሻል፤
እኔም አንቺን ሳስብ እጅግ ደስ ይለኛል፤
መጠጊያ ረዳቴ አጽናኝ ሆነሽኛል።

<u>መንፈሳዊ መዝሙር - እንግዳ ሰው ነኝ</u>

<u>አዝማች</u>

በአፈጣጠሬ ለዚች አለም የሚሆነኝ፥
እውቀት ተመጥኖ የተሰጠኝ፥
በምድር ጊዜያዊነቴ በጣም የታወቀኝ፤
እኔ በዚች አለም እንግዳ ሰው ነኝ።

ፍጹም ደስታ ሕይወት ከሰማይ ካለልኝ፥
በምድር የውሸት ኑሮ ምን አስጨነቀኝ፤
ወደ አምላኬ ልቅረብ፥ ይህ መሬት ይብቃኝ፤
በሁለትነት ስኖር ሥጋዬ እኔን ጎዳኝ፥
የመጣሁበትን ሰማይን አስረሳኝ፤

እኔ በዚች አለም እንግዳ ሰው ነኝ።

<u>አዝማች</u>

በአፈጣጠሬ ለዚች አለም የሚሆነኝ፥
እውቀት ተመጥኖ የተሰጠኝ፥
በምድር ጊዜያዊነቴ በጣም የታወቀኝ፤
እኔ በዚች አለም እንግዳ ሰው ነኝ።

ከሰማይ በር ከፍተው መላእክት ሲጠሩኝ፥
አውቃለሁ ትልቅ ቤት እንደሚያስረክቡኝ፥
እስከዛም ይህ ምድር ምንም የማይጥመኝ፥
እኔ በዚች አለም እንግዳ ሰው ነኝ።
በሥጋ ደክሜ ባዶዬን ቀረሁኝ፤
በመንፈስ ስተጋ የሰማይ ቤት ታየኝ።

<u>አዝማች</u>

በአፈጣጠሬ ለዚች አለም የሚሆነኝ፥
እውቀት ተመጥኖ የተሰጠኝ፥
በምድር ጊዜያዊነቴ በጣም የታወቀኝ፤
እኔ በዚች አለም እንግዳ ሰው ነኝ።

*************************************************

## ጸሎት - ስለ ድክመቶቻችን

አቤቱ የፈጠርከን ቸሩ አምላካችን ሆይ! ኃጢአታችንን ብቻ ሳይሆን ተፈጥሮአዊ ድክመታችንንም ተመልከትልን።

በልባቸው ጥሩዎች ሆነው፥ ጥሩ ሥራ ለመሥራት እየፈለጉ፥ ነገር ግን ምድር መጥፎ ስለሆነችባቸው ብቻ ጥሩ ለመሥራት ላልቻሉ ሰዎች እንጸልያለን።

የሰማዩን አለም ለማየት ባለመቻላቸው ትኩረታቸው በምድራዊ ሕይወታቸው ላይ እየሆነ በመንፈሳቸው ለሚጎዱ እንጸልያለን።

ጥሩ ሥራ ለመሥራት በትግል ላይ እንዳሉ፥ በግዴታ መጥፎ ሥራዎችን እንዲሠሩ ለሚገደዱ እንጸልያለን።

በልባቸው ጥሩነታቸው እና መጥፎነታቸው በመታገል ላይ ሳሉ፥ ከቁጥጥራቸው ውጪ በሆነ ምክንያት ለመጥፎ ሥራ እየተሸነፉ ከስህተት ውስጥ ለሚገቡ እንጸልያለን።

በተለያየ ምክንያት ኃጢአት ከመሥራት ያልተቆጠቡ ሰዎችን ሁሉ፥ ኃጢአታቸውንና በደላቸውን ብቻ ሳይሆን፥ ምድር ያተረፈችላቸውንም የፈተና ክብደትም አምላክ ሆይ እባክህ ተመልከትላቸው።

አምላክ ሆይ! አንተ ለሁሉም እንደየሥራቸው ፍርድ እንደመስጠትህ፤ በአንተ ሚዛናዊ ፍርድ ጣልቃ ለመግባት ሳይሆን፤ እባክህ በምድራዊ ኑሮ ውስጥም የሰዎችን ችግር ተመልከት።

አቤቱ! ሁሉን የምታውቅ፤ ከሁሉ በላይ ያለኸውም አንተ ነህና፡- በጸሎታችን የምንለምንህን ሁሉ አንተ አስተካክለህ፥ መልካሙን ሁሉ ታደርግ ዘንድ፤ አሁንም ለወደፊትም ያንተው ፈቃድ ይፈጸምልን እያልን እንለምንሃለን። አሜን።

## ጸሎት - ስለ ሰላማችን

አምላክ ሆይ፥ ሕዝቦች ሁሉ ለፍቅር፥ ለሰላምና ለአንድነት የሚቻኮሉ፥ በጽድቅ ጎዳና በአንተ ፈቃድ የሚመላለሱ የእውነት ሰዎች ለመሆን በሚያደርጉት ጥረት ቅዱስ መንፈስህ እንዳይለያቸው እንለምንሃለን።

አቤቱ እግዚአብሔር አምላካችን ፈጣሪያችን ሆይ! እኛ ሰዎች አብረን ስንኖር በፖለቲካ፥ በሃይማኖት እየተለያየን እርስ በርሳችን ከመጣላት የሚያድነን ሰላማችንን

እና አንድነታችንን የምናገኝበትን መንገድ አንተ ታሳውቀን ዘንድ፤ በምድራዊነታችንም ከእለት ህኪት የራቅን፥ ጤነኞችና፥ ደስተኞችም ታደርገን ዘንድ እንለምንሃለን።

አቤቱ እግዚአብሔር አምላካችን ፈጣሪያችን ሆይ! ቅዱስ መንፈስህን ከአለም ሕዝቦች አታርቅ፤ የምንኖርበትን አገራችን ባርክልን፤ ለምድራችን ሰላምን ስጠን፤ ኢትዮጵያን ጠብቃት።

## <u>ጸሎት - ስለ ንጹህ ልብ</u>

አቤቱ ፈጣሪ አምላኬ ቸሩ እግዚአብሔር ሆይ! ሁሉን የምታውቅ አንተ ነህና፤ ህይወቴም ያንተ ነው። ከእንግዲህ መላ ሰውነቴን ላንተ ሰጥቻለሁ። ከምንጊዜውም የበለጠ ባንተ መንፈስ እመራ ዘንድ ፈቃድህ ይሁን።

ጌታዬና መድኃኒቴ ኢየሱስ ክርስቶስ ካጠገቤ አትለይ። ከፊትለፊቴ - ከኋላዬም፥ ከቀኜ - ከግራዬም፥ ከበላዬ - ከበታቼም፤ በዙሪያዩ ሁሉ አንተ ኑርልኝ፤ ክበበኝ፤ በውስጤ ኑር፤ እኔም በአንተ ብርታትና ኃይል ምንም ሳልፈራ እኖር ዘንድ እርዳኝ።

አቤቱ አምላኬ፥ ሆይ! በአይምሮዬ፥ በልቤም ያለውን ሁሉ አንተ ታውቃለህና፤ ከእንግዲህ፥ ሁሉንም አንተ ታስተካክለው ዘንድ ትቼአለሁ።

“አቤቱ ንጹህ ልብን ፍጠርልኝ፤ ቀናውንም መንፈስ በውስጤ አድስ። ከፊትህ አትጣለኝ፤ ቅዱስ መንፈስህንም ከእኔ ላይ አትውሰድብኝ።” መዝ. 50፡10-11 አሜን።

## <u>ጸሎት - ቀናውንም መንገድ አሳየን</u>

ቸሩ እግዚአብሔር አምላካችን፥
በመንፈስ - በሥጋ ፈጣሪያችን፤
ስንጨነቅ አንተው ነህ መጽናኛአችን፤
ስንፈራ አንተ ነህ ብርታታችን፤
ስንጠቃ አንተ ነህ መከታችን፤
አለማወቅ ሲያሳውረን፥ አንተ ነህ ብርሃናችን፤
እምነት ከእውነት አልሰምር ቢለን፥ ባንተ ነው ትኩረታችን።
ከጨለማ/ከጉርጓድ አውጣን፥ ቀናውንም መንገድ አሳየን፤
ድርጊታችን ሁሉ ወዳንተ የሚመራ ይሁንልን። አሜን።

<u>ጸሎት - ሚካኤል እርዳኝ</u>

ስምክን ስጠራው -- ሚካኤል ስልህ፥
የጌታ መልአክ - ናልኝ ‘ባክህ።
ከአዳም ጀምሮ - ለዘመናት፥
ችግር ሲጠና - ሁነሃል ረዳት።
ዘበኛውን ጥሰህ፥ እስረኛ ፈተሃል፤
ዲያቆን ሆነህም ቀድሰሃል፤
ከክርስቲያኖችን ጎን ሆነህ ታግለሃል፤
እርዳኝ ላለህም ቶሎ ደርሰሃል።
ታግለህ ጥለሃል - ጠላታችንን፤
ገና ከጥንትቱ - ተንኮል ጠንሳሹን።
ከእንግዲህ እኛንም አለሁ በለን፥
በተቻለህ እርዳን - ችላ አትበለን።

<u>ጸሎት - አምላኬ አንተ ምራኝ</u>

እስቲ ልቀስቀስ ከእንቅልፌ፥ ላመስግን ስምህን፤
እግዚአብሔር አምላኬ፥ እያልኩ አንተን፤
ከኃጢአቴ ርቄ፥ እንዳገኝ ጽድቅን፤
ፈቃድህን ልፈጸም፥ ልጅህ እንድሆን።
ተፈጥሮዬን ሳርቅ እንደ ባላጋራ፥
ሳላስበው ኃጢአት እንዳልሠራ፥
ጠንቀቅ ብዬ ልኑር ሰይጣን ሳልፈራ፤
ጥሩ ሰው ለመሆን አለብኝ አደራ።
እኔም አንድ ኢምንት፥ ያንተ ፍጡር፥
ካለ አንተ ፈቃድ ስፍጨረጨር፥
የምድር ብቻ ሆኜ እንዳልቀር፤
እባክህ ኃጢአት - በደሌን ማር።
ሕይወቴም ለምክንያት፥ እዚህ ደርሷልና፤

እባክህ ጠብቀኝ፥ እንዳልወጣ ካንተ ጎዳና፤
እባክህ አበርታኝ፥ ባንተ መንፈስ እንድጽናና፤
ካለ አንተ ልቤ ጨለማ ነውና።

<u>ጸሎት - ስለ በጎ ነገር</u>

ይህ መጽሐፍ በእጁ የገባ፥ ለማንበብም የጀመረ፥ በከፊል ወይም በምልአት አንብቦ የጨረሰ፥ ወይንም ሲነበብለት የሰማ፥ በመጽሐፉ ውስጥ ስለተጠቀሱት አንዳንድ ጠቃሚ ህብረተብአዊ - መንፈሳዊ ጉዳዮች ያሰበ፥ እንደገና አብራርቶ በመጻፍም ሆነ ከጎኑ ላለው ሰው ጋር በማውራት ለበጎ መንፈስ ጥርጊያ መንገድ የከፈተ ሁሉ፥ አምላክ ሆይ ከአንተ መንፈስ ርቆ እንዳይሄድ፤ ወደጥሩው የሚመራ እንጂ የሚሰናከል እንዳይሆን አንተ ጠባቂ አድርግለት። በዚህ መጽሐፍ የተጠቀሱ ሃሳቦች ልዩነቶችን የሚደመስሱ፥ መግባቢያና የሚያቀራርቡ ታደርጋቸው ዘንድ እንለምናለን። አሜን።

****************************************************

# ዋቢ መጻሕፍት

(ለአራቱም መጻሕፍት)


Abdullah Yusuf Ali (Translation by), 2002: **The Qur'an**, Published by Asir Media.

Bartusiac Marcia (edited and with Introduction), 2006: **Archives of the Universe**, Vintage Books, A Division of Random House, INC. New York.

Bhaktivedanta Swami Prabhupada A.C (His Devine Grace), 1972, 1983: **Bhagavad Gita As it is,** The Bhaktivedanta Book Trust

Charles Darwin, 1958: **The Origin of Species**, Signet Classics.

Close Frank, 2009: **Anti Matter,** Oxford University Press.

Coogan Michael D., 2003: **World Religions,** Duncan Baird Publications, London.

Davidson Basil, 2005: **Africa in History**; Touchstone, Rockfeller Center, New York, N.Y.

Drage Hale Rosemary, 2004: **Understanding Christianity**, Duncan Baird Publishers, London.

Ehrlich Carl S., 2003: **Understanding Judaism**, Duncan Baird Publishers, London.

Elain Murray Stone, 2004: **A Saint and His Lion, the Story of Tekla of Ethiopia,** Paulist Press.

Hammond, 2002: **Concise Atlas of World History**, $6^{th}$ Edition, Map Makers for the $21^{st}$ Century; HarperCollins Publishers.

Hausman Gerald, 1997: **The Kebra Nagast**: St. Martin's Press, New York

Hawking W. Stephen And Leonard Mlodinow 2010: **The Grand Design**; Bantam Books, New York.

Hawking W. Stephen, 1988: **A Brief History of Time**, From The Big Bang to Black Holes; Bantam Books, New York.

Hawking W. Stephen, 2005: **The Theory of Everything**, Fate of The Universe; Phonix Books.

Houston Drusilla Dunjee, 2007: **Wonderful Ethiopians of The Ancient Empire**; Nuvision Publications, LLC, Sioux Falls, SD, USA.

Jackson G. John, 1939 And 1985: **Ethiopia and the Origin of Civilization**; Nuvision Black Classic Press, Baltimore, MD. USA.

John Brockman (Editor), 2010: **This Will Change Everything**, Ideas That Will Shape The Future; Harper Collins Publishers, New York, NY. 10022.

Laszio Ervin, 2006: **Science and The Enchantment of The Cosmos**; The Rise Of The Integral Vision Of Reality, Inner Traditions, Rochester Vermont.

Leslau Wolf, 1976: **Concise Amharic Dictionary**, Amharic - English, English - Amharic, Otto Harrassowitz – Wiesbaden, Commercial Printing Press, Adds Ababa, Ethiopia

Mary And John Gribbin, 2003: **From Atoms to Infinity**; Icon Books.

Muhaiyaddeen Bawa M.R., 1987, revised 2004: **Islam and World Peace, Explanations of a SUFI,** The fellowship Press, Philadelphia, PA.

Oldstone Moore Jennifer, 2003: **Understanding Confusianism**, Duncan Baird Publishers, London.

Rana Fazal & Ross Hugh 2004: **Origin of Life**; Navpress, Colorado Springs, CO80920.

Ross Hugh 2010: **Beyond the Cosmos**, **What Recent Discoveries in Astrophysics Reveal About the Glory and Love of God,** 2010:Signalman Publishing, Orlando, Florida.

Southwood, Richard 2002: **The Story of Life**, Oxford University Press.

Steinberg Milton, 1975: **Basic Judaism**, Harcourt Brace Jovanovich, Publishers. San Diego, New York, London.

Vorilhon Claude, 1983፡ **Le Livre Qui Dit La Verite**

Wallis Budge (1932): **The Kebra Negast,** Oxford University Press, London, Humphrey Milford.

ልዑለ ቃል አካሉ (መምህር)፥ 1994፤ **ሥርአተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ**፥ አትላንታ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን፥ ዩ ኤስ ኤ፥ አታሚ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ።

ተስፋ ገብረ ሥላሰሴ (አዘጋጅ)፥ 1978፤ **ገድለ አቡነ አረጋዊ**፥ ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፥ አዲስ አበባ።

ተስፋ ገብረ ሥላሴ (አዘጋጅ)፥ 1992፤ **መልክአ ሚካኤል በአማርኛ**፥ ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፥ አዲስ አበባ።

ተስፋ ገብረ ሥላሴ (አዘጋጅ)፥ 1964፤ **መዝሙረ ዳዊት ወጸሎታት ዘነቢያት ወመዐልየ ዘሰለሞን**፥ ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፥ አዲስ አበባ።

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ (1951)፤ **የኢትዮጵያ ታሪክ** 2ኛ መጽሐፍ።

ትንሳኤ የመጻሕፍት ማሳተሚያ ድርጅት (አሳታሚ)፥ 1990፤ **ፍትሐ ነገሥት ንባቡና ትርጓሜው**፥ ትንሳኤ የመጻሕፍት ማሳተሚያ ድርጅት፥ አዲስ አበባ።

አቡነ ሽኑዳ 3ኛ የግብፅ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ (ውርስ ትርጉም በዲያቆን ታደሰ ወንድም አገኘሁ)፥ 1993፤ **የንስሐ ሕይወት**፥ ኢትዮጵያ መጻሕፍት ድርጅት፤ አዲስ አበባ።

አባ ኤልያስ ሊቀ ጳጳስ፥ 2009፤ **በአዲስ መሠረት ላይ የነበረው ጥሪት**፥ Washington D.C. 20018 USA.

አባ ጎርጎርዮስ፥ 1978፤ **የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ**፥ ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፥ አዲስ አበባ።

አንዱ ዓለም ዳግማዊ (መምህር)፥ 1998፤ **ወላዲተ አምላክ በነገረ ድኅነት**፥ ኅትመተ ብራና ማተሚያ ድርጅት፥ አዲስ አበባ።

አንዱ ዓለም አባተ (የአጸደ ልጅ)፥ 2010፤ **ንጉሥ ዘርዓ ያዕቆብ**፥ እና ሌሎች ግለ-ወንች።

ብሩህ ዓለምነህ፥ 2010፤ **የኢትዮጵያ ፍልስፍና የዘርርዓ ያዕቆብና የወልደ ሕይወት ሐተታዎች ትንታኔ** (ከነሐተታቸው)

ኢንተርናሺናል መጽሐፍ ቅዱስ ማሕበር፥ 2001፤ **መጽሐፍ ቅዱስ**፥ አዲሱ መደበኛ ትርጉም፥ International Bible Society.

ዓሥራት ገብረ ማርያም፤ 1991፤ **ትምህርተ መለኮት**፥ ሁለተኛ እትም፥ ንግድ ማተሚያ ቤት ድርጅት፥ አዲስ አበባ።

ዓባይነህ ካሴ፥ 1992፤ **የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት**፥ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አንደኛ መጽሐፍ፥ አሳታሚ ማሕበረ ቅዱሳን፥ አዲስ አበባ።

ኤፍሬም አሰፋ ወረደወርቅ፥ 1992፤ **አዲሱ የአማርኛ መዝገበ ቃላት**፥ ሁለተኛ እትም።

ኤፍሬም አሰፋ ወረደወርቅ፥ 1995፤ **ሚሊንየም እንግሊዝኛ-አማርኛ መዝገበ ቃላት**፥ Revised Edition.

እሸቱ ታደሠ ወንድም አገኘሁ (ዲያቆን) እና ደጀኔ ሽፈራው በላቸው (ዲያቆን)፥ 1991፤ **ወላዲተ አምላክ በመጽሐፍ ቅዱስ**፥ ኢትዮጵያ መጻሕፍት ድርጅት፤ አዲስ አበባ።

ወሰኔ ይፍሩ፤ አዘጋጅ፤ 1990፤ **ሄኖክ**፤ በየዓመቱ የሚታተም የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር መጽሔት፥ 1101 S.W. Washington St. Suite 129 Portland, OR 97205

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማሕበር (አሳታሚ)፥ 1980፤ **መጽሐፍ ቅዱስ፥** የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት፥ መጀመሪያ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ታተመ፥ United Bible Societies Africa Regional Centre, Nirobi, Kenya

የጥንት ሊቃውንት እንደ ጻፉትና እንደተረጎሙት፥ 1983፤ **ተአምረ ማርያም፥** አንደኛ መጽሐፍ፥ አዘጋጅና አከፋፋይ ተሰፋ ገብረ ሥላሰሴ፥ አዲስ አበባ።

የጥንት ሊቃውንት እንደጻፉትና እንደተረጎሙት፥ 1946፤ **ገድለ ተክለ ሃይማኖት፥** ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት።

ዲበኩሉ ዘውዴ፥ 1986፤ **ፍትሐ ነገሥት ብሔረ ሕግ ወቀኖና፥** ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፥ አዲስ አበባ።

ጥዑመ ልሳን ካሳ (ሊቀ ካህናት - ርዕሰ ደብር)፥ 1981፤ **ያሬድና ዜማው፥** ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፥ አዲስ አበባ።